# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ዕቅድ (2018 – 2022)

የትውልድ ቁጭትን ለትውልድ ልዕልና የማነጽ ትልም

**Amhara National Regional State**

**Plan for Transformative Growth and Sustainable Development (2026 - 2030)**

ሚያዚያ 2017

ባሕር ዳር

# ይዘት


መቅድም ........................................................................ 6

ክፍል አንድ ........................................................................ 9

**መግቢያ** ........................................................................ 9

ምዕራፍ አንድ ........................................................................ 9

ምዕራፍ ሁለት ........................................................................ 11

ክፍል ሁለት ........................................................................ 14

ምዕራፍ ሦስት ........................................................................ 15

3.1. ክልላዊ እና አገራዊ ሁኔታዎች ........................................................................ 15

3.2. ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ........................................................................ 21

ምዕራፍ አራት ........................................................................ 23

4.1. የኢኮኖሚ ልማት አፈጻጸም ........................................................................ 23

4.2. ትምሕርት ........................................................................ 32

4.3. ጤና ........................................................................ 33

4.4. ፈርጀ - ብዙ ማሕበራዊ ጉዳዮች ........................................................................ 34

4.5. መሠረተልማት ........................................................................ 35

4.6. የመንግሥት ገቢ እና ወጪ አፈጻጸም ........................................................................ 37

ምዕራፍ አምሥት ........................................................................ 38

5.1. መነሻ ........................................................................ 38

5.2. ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች እና የረጅም ጊዜ የትኩረት አቅጣጫዎች ........................................................................ 39

5.3. የመዋቅራዊ ለውጥ ግብ ........................................................................ 44

ምዕራፍ ስድስት ........................................................................ 47

ክፍል ሦስት ........................................................................ 48

ምዕራፍ ሰባት ........................................................................ 49

7.1. የዕቅዱ ዓላማዎች ........................................................................ 49

7.2. የዕቅዱ ግቦች ........................................................................ 49

7.3. የትኩረት አቅጣጫዎች ........................................................................ 49

7.4. የትኩረት መስኮች ........................................................................ 50

ምዕራፍ ስምንት ........................................................................ 51

8.1. የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ ........................................................................ 51

8.2. የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ ........................................................................ 52

8.3. መዋዕለ ንዋይ እና ቁጠባ ........................................................................ 52

8.4. የሰው ኃይል ፍላጎት ........................................................................ 54

ክፍል አራት ........................................................................ 55

ምዕራፍ ዘጠኝ ........................................................................ 55

9.1. መነሻዎች ........................................................................ 55

9.2. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 64
9.3. የትኩረት መስኮች ........ 65
9.4. ዓላማ ........ 65
9.5. ዋና ዋና ግቦች ........ 65
9.6. የማስፈጸሚያ ሥልቶች ........ 65
ምዕራፍ አሥር ........ 66
10. 1. የዘርፉ ሚና ........ 66
ምዕራፍ አሥራ አንድ ........ 70
11.1. መነሻዎች ........ 70
11.2. የአመሥት ዓመት አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች እና ዋና ዋና ግቦች ........ 83
11.3. የማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 84
ምዕራፍ አሥራ ሁለት ........ 85
12.1. የትኩረት መነሻ ........ 85
ምዕራፍ አሥራ ሦስት ........ 101
13.1. መነሻዎች ........ 101
ምዕራፍ አሥራ አራት ........ 109
14.1. የትኩረት መነሻ ........ 109
ምዕራፍ አሥራ አምሥት ........ 120
15.1. ሚና ........ 120
15.2. ክልል አቀፍ እና አገር አቀፍ የንግድ ሥርዓት ሁኔታ ........ 120
15.3. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 121
15.4. የትኩረት መስኮች ........ 121
15.5. ዓላማ እና ግቦች ........ 122
15.6. የማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 122
ምዕራፍ አሥራ ስድስት ........ 123
16.1. መነሻ ........ 123
16. 2. የትኩረት አቅጣጫ ........ 123
ምዕራፍ አሥራ ሰባት ........ 125
17.1. የትኩረት መነሻዎች ........ 125
ምዕራፍ አሥራ ስምንት ........ 140
18.1. መግቢያ ........ 140
18.2. የጤናው ዘርፍ ሁኔታ ትንተና ........ 140
18.3. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 150
18.4. ዋና ዋና ግቦች ........ 150
ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ........ 151
19.1. የዘርፉ ሚና ........ 151

19.2. የሁኔታ ትንተና ..... 152
19.3. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ..... 164
19.4. የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 164
19.5. ዓላማ ..... 164
19.6. ዋና ዋና ግቦች ..... 164
19.7. የማስፈጸሚያ ስልቶች ..... 165
ምዕራፍ ሃያ ..... 167
20.1. መነሻ ..... 167
20.2. የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 168
20.3. ዓላማዎች ..... 168
20.4. የትኩረት መስኮች ..... 168
20.5. ሥልቶች ..... 168
ምዕራፍ ሃያ አንድ ..... 170
21.1. መነሻዎች ..... 170
21.2. አፈጻጸም ..... 170
21.2. ስትራቴጅክ ጉዳዮች ..... 171
21.3. የትኩረት መስኮች ..... 172
21.4. የከተማ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 172
ክፍል አምሥት ..... 174
መግቢያ ..... 175
ምዕራፍ ሃያ ሁለት ..... 177
ምዕራፍ ሃያ ሦስት ..... 181
23.1. መነሻ ..... 181
23.2. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ..... 182
23.3. የትኩረት መስኮች ..... 182
23.4. የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 182
23.5. ዓላማ እና ግቦች ..... 182
23.6. የማስፈፀሚያ ሥልቶች ..... 184
ምዕራፍ ሃያ አራት ..... 185
**ቴክኖሎጂ** ..... 185
24.1. መነሻ ..... 185
24.2. የረጅም ዘመን የቴክኖሎጂ ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 198
24.3. የቴክኖሎጂ ዝግጁነት (Technological Readiness) ..... 201
24.4. የማስፈጸሚያ ሥልቶች ..... 202
ምዕራፍ ሃያ አምሥት ..... 203
25.1. መነሻ ..... 203

ክፍል ስድስት ........ 213
ምዕራፍ ሃያ ስድስት........ 214
26. 1. መነሻዎች ........ 214
26. 2. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 218
26.3. የመዋዕለ ንዋይ ግቦች........ 219
26.4. የማስፈጸሚያ ሥልቶች........ 219
ምዕራፍ ሃያ ሰባት ........ 220
27.1. መግቢያ ........ 220
27.2. የመንግሥት ፋይናንስ ወጪ እና ገቢ አፈጻጸም ትንተና........ 221
ክፍል ሰባት........ 230
ምዕራፍ ሃያ ስምንት ........ 231
28.1. የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ........ 231
28.2. ሥርዓታት፤ የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረታዊያን........ 232
28.3. የፖለቲካ ሥርዓት እንደ ገዢ ሥርዓት........ 234
28.4. ሥርዓታት እና ልማት በኢትዮጵያ ........ 235
28.5. የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ታሳቢ የሚያደርገው የሥርዓታት ሚና ........ 237
ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ........ 239
29.1. የዘርፉ ሚና ........ 239
29.2. የዘርፉ ዓለማቀፋዊ እና አህጉራዊ ሁኔታ ........ 240
29.3. የዘርፉ ሀገራዊ ሁኔታ ........ 242
29.4. የዘርፉ ክልላዊ ሁኔታ........ 245
29.5. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች........ 252
29.6. የስትራቴጅክ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ግቦችና ተግባራት ........ 254
29.6.1. የስትራቴጅያዊ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች........ 254
29.6.2. ስትራቴጅክ ግቦች እና ተግባራት፣........ 255
29.7. የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ የክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ስርዓት፣ ........ 260
ምዕራፍ ሠላሳ ........ 262
ምዕራፍ ሠላሳ አንድ ........ 271
ክፍል ስምንት ........ 275
ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት........ 276
ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት........ 286
ምዕራፍ ሠላሳ አራት........ 296
ምዕራፍ ሠላሳ አምሥት ........ 297
35 1. መነሻ........ 297
35.2. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 298
35.3. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የትኩረት መስኮች ........ 298

36.4. የመረጃ ሥርዓት....................................................................................................................300
37.4. ተቋማዊ አደረጃጀት ..........................................................................................................300
ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት.............................................................................................................................301

# መቅድም

የአገር እና ማሕበረሰብ ዕድገት፣ ልማት፣ እና ብልጽግና መጨረሻ የሌላቸው የትውልዶች የቅብብሎሽ ጥረት ውጤቶች ናቸው። በአንጻራዊነት በብልጽግና ጫፍ ላይ የሚገኙ ማሕበረሰቦች ዛሬ ዓለም የደረሰበትን የሥልጣኔ አድማስ ከፍ ለማድረግ ይታትራሉ። የሩቅ እና የቅርብ ዘመን ታሪክ እንደሚያወሳን ማሕበረሰቦች ለማሳያነትት ከሚጠቀስ የከፋ ድህነት ተዓምር በተባለለት እና ለአብነት በሚጠቀስ የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት ከዓለም የብልጽግና ጫፍ በመድረስ ተረኛ ትውልዳቸው የተሻለ ማሕበራዊ ደህንነት ፈጥሮ ለማለፍ ከማያልቅባት ተፈጥሮ ጓዳ የተሻሉ የቴክኖሎጂ አቅሞችን ለማዋለድ በሣይንሳዊ ጥበብ ይተጋል። ይህ የታሪክ እና ሕያው ዕውነታ በአገራችን እና በክልላችን ከተነሱት መለስተኛ የግጭት አዟራዎች አሻግሮ ማየት የሚችል ትውልድ ከተፈጠረ ከዓለም የስልጣኔ ማማ ጋር ለመስተካከል የአንድ ትውልድ ዕድሜ ብቻ ሊወስድብን እንደሚችል ያመላክተናል።

በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ እንደ ሌላው ዓለም ሁሉ ትውልዶቿ በአጋጣሚም፣ በጥረትም፣ በብልሃትም፣ በስህተትም የአገራችንን የማሕበረሰብ የኑሮ እና የሥልጣኔ ደረጃ በከፍታ እና ዝቅታ መሃል አስኪደውታል። የሰው ዘር አብዛኛውን ዘመኑን ያሳለፈበት የድንጋይ ዘመን ስልጣኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሩ ወይም ከተጀመረባቸው የዓለም አካባቢዎች አንዱ ለመሆኑ የዚያ ዘመን ሰው ድንቅነሽ ወይም ሉሲ ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቷ ምስክር ነው። የሰው ልጅ የስልጣኔ ማሳያ አንዱ ፈርጅ የሆነው የራስን ፊደል ቀርጾ የመጠቀም ችሎታ በዓለም ላይ ለጥቂት ሕዝቦች ብቻ የተሳካ ሲሆን በሦስት ሺህ ዓመታት የዘመን ልኬት ከተሳካላቸው ጥቂት አገራት  አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ከአንደኛው ክፍለ ዘመን መባቻ እስከ 9ኛው ክፍለ ዘመን በቆየው የአክሱም ሥርዎ መንግሥት በተለይ እስከ 7ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ሥልጣኔ ከምሥራቃዊ ሮማ የዘመኑ ገናና ሥልጣኔ ጋር ይስተካከል እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። ድህረ ሮማ አውሮፓ በግጭት እና ድህነት አዙሪቶች በተሰፋ እና ስጋት ከፍታ እና ዝቅታዎች ሲተራመስ ከቆየ በኋላ በ17ኛው ክፍለ ዘመን በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት ለዛሬው የስልጣኔ ደረጃ መነሻ የሆነውን የከፍታ መስመር በጥረቱ ሲይዝ፣ ድህረ አክሱም ኢትዮጵያ በሚያጥመለምሉ የድህነት እና የግጭት አዙሪቶች በመለስተኛ ስልጣኔዎች እና በከፉ ውድቀቶች መሃል እየተላጋች ዛሬ ላይ የቆምንበት የታሪክ መታጠፊያ ላይ ደርሰናል።

ለዚህ ትውልድ ቅርብ ከሆኑት የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ኩነቶች ለመነሳት በአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ያራመዱን፣ በአንጻሩም ያደናቀፉን እና ሊደፍቁን የሚገዳደሩን ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ርምጃዎች ተወስደው ለተስፋም ለስጋትም የሚጋብዙ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በኢኮኖሚ ልማት ረገድ በአፍሪካ ፈጣን በሚባል የዕድገት ምጣኔ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ከገባንበት የከፋ ድህነት ቅርቃር ከማገገም ባለፈ ለመካከለኛ ገቢ ደረጃ የሚያቃርብ ተግባር ተከናውኗል። በማሕበራዊ ልማት ረገድ በትምህርት፣ እና በጤና እንዲሁም በማሕበራዊ ደህንነት ዘርፎች አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። ከተሞቻችን በተገነቡ አቅሞች ከትናንት የተሻሉ የመኖሪያ እና የሥራ ስፍራዎች ሆነዋል። በእነዚህ ድምር ውጤት ክልላችንን ጨምሮ የአገራችን ሕዝብ በሕይወት የመቆያ አማካይ ዕድሜ በ1983 ከነበረበት 47.5 ዓመት በ2014 ወደ 65.6 ዓመት ከፍ ብሏል። ነገር ግን፣ ከመነሻችን ዝቅተኛነት እና ዓለም አቀፍ ተስተካካይነትን በማሰብ ልንደርስበት ከሚገባን የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ደረጃ አንጻር በኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት በተለይም በመዋቅራዊ ለውጥ አዝጋሚነት የሚገለጹ ውስንነቶች ተስተውለዋል፤ በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ወደ የማይቀለበስ የልማት ደረጃ ለመመንጠቅ የሚደረገውን ተስፋም የሚገዳደሩ ሆነዋል። ከሁሉም በላይ በፖለቲካው መስክ በተተገበሩት ከፋፋይ ትርክቶች ምክንያት በማንቆጣጠረው ትናንት ላይ ሙሉ አቅማችንን አባክነን የፈጠርነው የግጭት አዙሪት ከድህነት አዙሪት ወጥተን እኩል የተሳካላቸው የዓለም ዜጋ ለመሆን የምናደርገውን ጥረት ጠልፎ ሊጥል በመፈታተን ላይ ይገኛሉ።

የግጭቶቹ ባሕርያት ከትልቅ እና ታላቅነት ግብ ይልቅ ከኪራይ ያላለፉ ትንንሽ ሸንጋይ ግቦች፣ ሲከፋም ለአጥፊ መዳረሻዎች ሲባል ትልቁን ርዕይ የሚደፈጥጡ፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዓለም በተቀራረበበት እና በተሳሰረበት፣ ግን ደግሞ የዓለም ሥልጣኔ ጫፍ ስለት ለልማትም ሆነ ለጥፋት ቅርብ በሆነበት ዘመን ከትርምሱ ባሻገር ማስተዋል የጎደላቸው ክስተቶች ናቸው። የዚህ ዓይነት የዘመን እንቆቅልሽ የሚፈታው በማይቆጣጠሩት ትናንት እሰጥ አገባ የሚፈጠር እሳት እየሞቁ አገር እና ትውልድን በመለብለብ ሳይሆን፣ ከትናንት የመቻል ታሪክ ላይ ቆሞ እና ከስህተቶች ትምህርት ወስዶ በትርምሱ መሃል አሻግሮ መዳረሻን አርቆ በማየት መነሻን በማነጣጠር ነው። የዚህ የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖት - ካርታ አካል የሆነው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ መነሻም ይህ የሩቅ ግብን አይቶ ዛሬን የማስተካከል እና የማደላደል መርህ ነው።

ይህ ከ2018 እስከ 2022 ድረስ የሚተገበር የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በ2042 የአማራ ብሔራዊ ክልልን በቴክኖሎጂ እና በኢኮኖሚ ተስተካካይነት የበለጸገ ክልል የማድረግ ርዕይ ያለው ሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖት - ካርታ የመጀመሪያ ርከን ማስፈጸሚያ ዕቅድ ነው። ይህ ዕቅድ በአሁኑ ወቅት እንደ ክልል እና እንደ አገር የገጠሙንን የጥቅል ኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ችግሮች እንዲሁም ቅርብ እና መሠረታዊ መንስኤዎቻቸውን

በጥልቅ ትንተና በመለየት ይጀምራል። በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በርካታ ዜጎች ከድህነት የተላቀቁ እና ወደ መካከለኛ ገቢ ደረጃ የመሸጋገራቸውን ያህል ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የክልሉ ዜጎች አሁንም ከድህነት ወለል በታች ይኖራሉ። ወጣቱን ትውልድ በትምህርት በተለይም በሣይንስ እና ቴክኖሎጂ ዕውቀት በማነጽ ለዕውቀት መር ኢኮኖሚ አቅም እንዲሆን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በማስፋፋት ጭምር ጥረት ቢደረግም ከፍተኛ የወጣቶች የሥራ አጥ ቁጥር መፈጠሩ ከማሕበራዊ ልማት ግብ አኳያ ትልቅ ችግር፣ ከኢኮኖሚ ልማት አንጻርም ከፍተኛ ብክነት ሆኗል። ለወትሮው በክልላችን የሚታገሱት ዓይነት ምጣኔ የነበረው የዋጋ ንረት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኑሮ ውድነት ምንጭ ሆኗል። በትምህርት ዘርፍ በተደረገ ርብርብ አብዛኛውን የክልሉ ህጻን እና ወጣት ተደራሽ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም የትምህርት ማቋረጥ፣ የጥራት እና በትምህርት የችግር መፍቻ መሣሪያነት የነበረ እምነት መሸርሸር ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት መሆን ጀምሯል።

የእነዚህ ችግሮች ቅርብ ምክንያት ከኢኮኖሚ አንጻር አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ፣ የምክንያቶቹ ምክንያት እና መገለጫም ዝቅተኛ ምርታማነት እና ዝቅተኛ ቅልጥፍና እንደሆኑ የዕቅዱ የትንተና ክፍል ያሳያል። እነዚህ ጉዳዮች በአለፉት አሥራ አምሥት የልማት ዓመታት ተለይተው ያደሩ እና በተከታታይ ዕቅዶች መፍትሄ ሊሰጣቸው ግብ የተጣለላቸው ቢሆንም የተጠበቀውን ያህል አመርቂ ለውጥ አልተገኘም። የዚህ የሃያ አምሥት ዓመት የልማት ፍኖተ ካርታ አንዱ መለያ ባሕርይም በረጅም ዘመን ወደኋላ በመጓዝ በሥርዓታት የሚጠቃለሉ መሠረታዊ ምክንያቶችን መለየቱ ነው። መሠረታዊ ምክንያቶቹ በታሪክ አጋጣሚዎች የተቀሰቀሱ ግጭቶች፣ በጂኦግራፊ እና በባሕል ሊሳበቡ ቢችሉም፣ ከፖሊሲ ጋር የሚያያዙ የኢኮኖሚ ሥርዓታት፣ ከሁሉም በላይ ግን አስቻይ የኢኮኖሚ ሥርዓታትን ማስፈን እና ማስፈጸም የሚጠበቅባቸው የፖለቲካ ሥርዓታት (political institutions) ዋናዎቹ ናቸው።

ከዚህ በመነሳት የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ - ካርታ ከአንድ ትውልድ በኋላ ክልላችን ሊደርስበት የሚገባውን እና የሚችለውን ግብ አመላክቷል። ይህን ግብ ለማሳካት በየደረጃው መሟላት የሚገባቸውን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የመዋቅራዊ ለውጥ፣ የማሕበራዊ ልማት ግቦች እና የሚያስፈልጓቸው ግብዓቶች፣ ስትራቴጂ እና የፖሊሲ ማዕቀፍ በአምሥት ዓመታት ርከኖች ተከፋፍለው በቴክኒክ ደረጃም ተተግባሪነታቸው ተመሳክሮ በፍኖተ ካርታው ተመላክተዋል። ከአለፉት ዕቅዶች በተለየ ሁኔታም የዘርፍ ዕቅዶችን በመተንተን እና ከዚያም ባለፈ ለዕቅዱ መተግበር መሠረታዊ የሥርዓታት ጉዳዮች በሰላም እና በፍትህ፣ በማሕበረሰብ እሴቶች፣ እንዲሁም በመንግሥት ተቋማት እና የፖለቲካ አመራር ሚና ላይ የሚያተኩሩ ትንታኔዎች እና የተግባር ግቦች በተለይም የፍኖተ ካርታው የመጀመሪያ ክፍል የሆነው የዚህ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ አካል ሆነው እንዲቀርቡ ተደርጓል። እነዚህ የሥርዓታት አካላት የዕቅዱ አምዶች የሆኑትን የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት የማረጋገጥ፣ ክልላዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ የማፍራት፣ ሣይንሳዊ ዕውቀትን የርትዕ ማሕበረሰብ እሴት እና የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት የማድረግ፣ እንዲሁም ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በማሳደግ ጥራት ያለው ኢኮኖሚ የመገንባት ዓላማዎችን ለማሳካት የተነደፉ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በአለፉት የልማት ዕቅዶች ያልታዩ ምናልባትም ችላ የተባሉ የቀጠና ልማት ዕቅድ (ስፓሻል ፕላን)፣ የልዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ዝርዝር ዕቅድ፣ የስትራቴጂ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ እንዲሁም ከርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት እስከ ቀበሌ በሚደርስ መዋቅር የሚተገበር ችግርን በወቅቱ የመፍታት ዓላማ ያለው ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የረጅም ጊዜ የሥርዓት አካል እንዲሆኑ በፍኖተ ካርታው አቅጣጫ የተቀመጠ ሲሆን የአምሥት ዓመት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ሥልቶች ሆነው ተዘጋጅተዋል።

ይህ ዕቅድ የሕዝብ ዕቅድ ነው። የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ርዕይ (ርዕይ 2042) "ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ አቅም፣ ሁለንተናዊ ብልጽግና" ሲሆን ሦስት ርከን ርዕዮች አሉት። የመጀመሪያው ርከን በተለይም የመጀመሪያው የአምሥት ዓመት ዕቅድ ርዕይ በ2022 የአማራ ብሔራዊ ክልል ሰላም እና ደህንነቱ የተረጋገጠ ማሕበረሰብ፣ በወሳኝ ዘርፎች ንቅናቄ የኢኮኖሚ ልማት መመንጠቅን ያረጋገጠ ክልል፣ እና የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ የገነባ ክልል ሆኖ ማየት ነው፤ የሁለተኛው ርከን ርዕይ በ2027 የአማራ ብሔራዊ ክልል በመሠረታዊ ኢንዱስትሪ ምርቶች የራሱን ፍላጎት የሸፈነ እና የተሳካ የመዋቅራዊ ሽግግር በማድረግ በትክክለኛ የብልጽግና ፍኖት ላይ ሆኖ ማየት ሲሆን፤የ ሦስተኛው ርከን ርዕይ ደግሞ በ2042 የአማራ ብሔራዊ ክልል በዓለም በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ የሆነ የዘመናዊ ኢኮኖሚ አቅም ባለቤት ሆኖ ማየት ነው። ዕቅዱ የሕዝብ ዕቅድ ነው ሲባል የሚተገበረው በሕዝብ፣ የውጤቱ ተጠቃሚም ሕዝብ ነው ማለት ነው። ለዚህም የምልዓተ ሕዝቡ ተሳትፎ ለዕቅዱ ተግባራዊነት ምትክ የለውም። ነገር ግን ይህ ታላቅ ግብ ያለው ግዙፍ ዕቅድ አፈጻጸም በአዘቦት ቀን የማሕበረሰብ ተሳትፎ የሚበገር አይሆንም፤ ይልቁንም ቁጭትን፣ በተለይም በቁጭት መቆዘም ሳይሆን ሠርቶ የመለወጥ ቁጭትን የሚጠይቅ ዕቅድ ነው። ሰው እንደ አንድ የኢኮኖሚ ግብዓት ከማሽን የሚለየው ማሽኑን በመፍጠር አቅሙ ብቻ ሳይሆን ሲቆጭ አንዱ እንደ ሺህ መሥራት የሚችል መሆኑ ነው። በቁጭት መንፈስ ለመሥራት የሚያበቁ እና የሚገፋፉ የረጅም እና የቅርብ ዘመን በቂ ምክንያቶችም አሉን። ይህ የልማት ዕቅድ የቁጭት ዕቅድ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው።

ዕቅድ ተስፋ የሚደረግበት፤ ድርጊት እና ተግባር ደግሞ ለውጤታማነት ቁርጠኝነት የሚገለጽበት ነው። ሕዝብን ወደ የማይቀለበስ የብልጽግና ፍኖት አሻግሮ በሚያልፍ ሕይወት የማይሞት ታሪክ መሥራትን የመሰለ ታላቅ የትውልድ ስኬት በዘመናት አንዴ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህ በየመስኩ በሚከፈል መስዋዕትነት የሚረጋገጥ ግብ ዕድለኛነትንም ይጠይቃል። የትውልዱ ሚና ሁሉንም ነገር ለአርባ ቀን ዕድል ሰጥቶ ከመቆዘም ለእድለኛ ትውልድነት የሚያቃርቡ መልካም አጋጣሚዎችን በመልካም እሴቶች እና ማሕበራዊ ካፒታል እየተንከባከቡ በማረቅ ለለውጥ በሥራ መትጋት ነው። ይህን ክልል እና ይቺን አገር በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በርትዕ አመራር ለማስቀጠል የሃያ ዓመት ዕድሜ ከዚህ ዘመን መሪ ትውልድ ይልቅ ለወጣቱ እና ለተተኪው ትውልድ ይቀርባል። ይህ ዕቅድ የወጣቱ እና የልጆቻችን ዕቅድ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው።

የዚህ ትውልድ የፖለቲካ አመራር ሚና ሕዝብን ለማገልገል ማሕበራዊ ኮንትራት እንደወሰደ አካል ብሩህ ነገን አሳይቶ ማሕበረሰብን በተለይም ወጣቱን ለልማት ማነሳሳት እና ማስተባበር ነው። የዚህ ነገን የማሳየት ትልም እና ተግባር ኢኮኖሚን እና አገርን በዕውቀት ከመምራት ይጀምራል። የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ፣ እንዲሁም ከዚህ የሚቀዳ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ሲወስን እና ይህም ክልሉ እና አገሪቷ ባፈራቻቸው ሣይንቲስቶች እና ባለሙያዎች እንዲተገበር ሙሉ ነጻነቱን እና ድጋፉን ሲሰጥ በዕውቀት የሚመራ ክልል፣ በዕውቀት የምትመራ አገር፣ ከሁሉም በላይ የአዋቂዎች መፍለቂያ የሆነ ለርትዕ ዕውቀት ቀናኢ የሆነ ማሕበረሰብ እንዲፈጠር ያለውን ፍላጎት ማሳያ ነው። ይህ ዕቅድ መሬት ወርዶ ተፈጻሚነቱ እስከሚረጋገጥ ድረሰም የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ታሪካዊ ግዴታውን እና ሕዝብ ለማገልግል የተሰጠውን መልካም ዕድል ፍሪያማ ለማድረግ በትጋት ይሠራል።

በዚህ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት ስለሕዝባችሁ በቁጭት ተነሳስታችሁ የተሳተፋችሁ የቅን እጆች፣ አዕምሮዎች፣ እና ቅን ልቦች ባለቤት የሆናችሁ የክልሉ እና የአገራችን ኢትዮጵያ ልጆች፤ ምሁራን፣ የየዘርፉ ባለሙያዎች እና አስተባባሪ አመራሮች እስከ አሁን ላበረከታችሁት አስተዋጽዖ እና መልካም ሥራ በክልሉ ሕዝብ እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስም እያመሰገንኩ ዋናው ምንዳችሁ የዚህ ዕቅድ ርዕይ እና ግብ ተፈጽሞ ዳር መድረስ እንደሆነ አምናለሁ። ይህን ዕቅድ በመወጠን እና በዝግጅት ደረጃ በቁጭት እንደጀመርነው ሁሉ መፈጸም እንችል ዘንድ ፈጣሪ ዕውቀት እና ማስተዋልን እንዲነሻ ይታደገን።

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

ባሕር ዳር

መስከረም 2018

# ክፍል አንድ

# መግቢያ

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | **መንደርደሪያ** |
| ምዕራፍ ሁለት | **የዕቅዱ አስፈላጊነት እና ልዩ ባሕርያት** |

## ምዕራፍ አንድ
### መንደርደሪያ

1. ኢትዮጵያን በ2022 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የማድረግ ርዕይ ያለው አገራዊ የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ (2013 – 2022) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ተነድፎ በትግበራ ላይ ይገኛል። የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትም ክልሉን በፍትሃዊ የልማት ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት የበለጸገች ኢትዮጵያ አካል በሚያደርግ ርዕይ ክልላዊ የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ (2013 - 2022) አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ አሸጋግሯል። የክልሉ የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ መተገበር ከተጀመረ አራት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ያለፉትን ዓመታት አፈጻጸም መገምገም እና የቀጣዩን የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ (2018 – 2022) ማዘጋጀት ወቅታዊ ጉዳይ ነው።

2. ክልላዊ የአምስት ዓመቱ ዕቅድ ሰነድ መነሻ ከአስር ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸምን መሠረት በማድረግና ክልሉ አሁን ያለበትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ነው። የአሥር ዓመታት መሪ የልማት ዕቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ በነበሩት ዓመታት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ ድርቅና የአንበጣ መንጋ መከሰት፣ የሰሜኑ ጦርነት እና በአሁኑ ወቅት በክልሉ ያለው ግጭት ያስከተሉት ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ስነልቦናዊ ቀውሶች ኢኮኖሚው ከዕቅድ በታች የሆነ አፈጻጸም እንዲኖረው አስተዋጽዖ አድርገዋል። በአለፉት አራት ዓመታት ክልሉ ካጋጠመው ውስጣዊ እና ውጫዊ ተግዳሮቶች አኳያ አጠቃላይ የኢኮኖሚ አፈጻጸሙ ተግዳሮትን በመቋቋም ረገድ ያሳየው ጥንካሬ አበረታች ቢሆንም በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ከተቀመጡት ግቦች አንፃር ጉልህ ጉድለቶች በመታየታቸው የቀጣዩን አምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በልዩ ትኩረት ፈጥኖ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

3. ከዝቅኛ መሠረት በመነሳት በፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያልም አገር ከመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ባለፈ መዳረሻውን ማመላከት የልማት አቅጣጫዎችን ትክክለኛነት ለመወሰን ይጠቅማል። ከዚህ አንጻር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሥራ ላይ ካለው የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ጋር የሚጣጣም የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ (2018 – 2042) (Roadmap for Transformative Growth and Sustainable Development: 2026 -2050) አዘጋጅቷል። ከዚህ አንጻር ቀጣዩን የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በረጅም ዘመን ዕቅድ ማዕቀፍ መቃኘቱ አስፈላጊ ነው።

4. በዚህም መሠረት የቀጣዮቹ አምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዓላማ የአሥር ዓመቱን የልማት ዕቅድ ግቦች ለማሳካት ያለፉትን አምሥት ዓመታት አፈጻጸም ማካካሻ የሚሆኑ ልዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን ማመላከት፣ እና ለረጅም ዘመን የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ ማስፈንጠሪያ የሚሆኑ ግቦችን፣ እና ስትራቴጂዎችን መንደፍ ነው።

5. በመሆኑም የአማራ ብሔራዊ ክልል ይህን የአምሥት ዓመታት (2018-2022) የልማት ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡ ይህ ዕቅድ በዋናነት ለዘመናዊ ግብርና ልማት፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለማዕድን ልማት፣ ለቱሪዝም ልማት እና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። በተለይም  በዚህ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን በሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የከፍተኛ ኢንዱስትሪ፣ የኃይል፣ የግብዓት ማዕድናት፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን፣ እና ትምሕርት ልዩ ትኩረት በመስጠት ለረጅም ዘመን አቅሞች መሠረት ይጣላል። በእነዚህ ዘርፎች ላይ በሚደረግ ርብርብም ክልሉ ያለውን ዕምቅ የተፈጥሮ እና ሰብዓዊ አቅም በማነጽ የክልሉን አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች አማካይ ገቢ ጋር ከማስተካከል ባለፈ በአንድ ትውልድ የኢኮኖሚ ተስተካካይነት ግብን ለማሳካት መሠረት የሚጥል የቁሳዊ፣ ሰብዓዊ እና የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ገዢ ግብ ነው።

6. በአጠቃላይ ይህ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ መነሻዎችን፣ የጥቅል ኢኮኖሚ ግቦችን፣ የዘርፎች ዕቅድን፣ የልማት አቅሞችን፣ የልማት ፋይናንስን፣ ሥርዓታት፣ እና የማስፈጸሚያ ሥልቶችን በአካተቱ ክፍሎች የተዋቀረ ነው። የዕቅዱ መነሻዎች የክልሉን ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ፣  የጥቅል ኢኮኖሚና የዘርፎች አፈጻጸም፣ የክልሉ የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ፣ እና የክልሉ ርዕይ እንዲሁም ስትራቴጂካዊ አምዶች   ላይ የተመሠረተ ነው። የጥቅል ኢኮኖሚ ግቦች በፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ሊቀረፍ የሚችለውን እና የሚገባውን የድህነት መጠን፣ የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫዎች፣ የሥራ ተሳትፎ ምጣኔዎች እና የማሕበራዊ ግቦችን ያጠቃልላል።

7. የዘርፎች ዕቅድ ክፍል በሚጠበቅ ሚና እና አስተዋጽዖ፣ ከአፈጻጸም ትንተና በሚመነጩ ጠንካራ ጎኖች እና ለስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫ መነሻ በሚሆኑ ክፍተቶች፣ እንዲሁም ሊደረስባቸው በሚገቡ እና በሚቻሉ ግቦች የተዋቀሩ ምዕራፎችን የያዘ ነው። የዘርፎች ዕቅድ ይዘቶችም
    1. የግብርና ልማት፣
    2. የአካባቢ ጥበቃ እና ልማት፣
    3. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት፣
    4. የማዕድን ሀብት ልማት፣
    5. የግንባታ ዘርፍ ልማት፣
    6. የቱሪዝም ልማት፣
    7. የንግድ እና ገበያ ልማት፣
    8. የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ልማት፣
    9. ትምህርት፣
    10. ጤና፣
    11. የማሕበራዊ እና ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች ልማት፣
    12. የገጠር ልማት፣ እና
    13. የከተማ ልማት ናቸው።

8. ለዘርፎቸ ልማት መነሻ የሚሆኑ አቅሞችን በሚዳስሰው ክፍል ቁሳዊ እና የማይዳሰሱ አቅሞች፣ መሠረተ ልማት፣ የሰብዓዊ ሀብት ልማት፣ እና ቴክኖሎጂ ተካትተዋል። በተለይም ቴክኖሎጂ የኢኮኖሚ ተስተካካይነት ግብ ማረጋገጫ እና የመወዳደሪያ ዋና መሣሪያ በመሆኑ ከአገራት ልምድ እና ከዘርፉ ንድፈ ሃሳብ፣ እንዲሁም ከአማራ ብሔራዊ ክልል እና የኢትዮጵያ የዘርፉ አቅሞች በመነሳት ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶታል።

9. ከልማት አቅሞች በተለየ ሁኔታ የልማት ፋይናንስ የተዳሰሰ ሲሆን ይህ ክፍል የመዋዕለ ንዋይ፣ ቁጠባ እና የፋይናንስ ተቋማት፣ እንዲሁም የመንግሥት ፋይናንስ ተካትተውበታል። የመዋዕለ ንዋይ መረጣ እና ስምሪት የዕቅዱ ዋና ግቦች ማስፈጸሚያ እና ማሳኪያ ዋና መሣሪያ ነው። የመንግሥት ፋይናንስ ከዕቅዱ ግቦች አንጻር የመንግሥት ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች የሚፈጸሙበት እና የመንግሥት ትኩረት የሚለካበት የፊስካል መሣሪያ ነው።

10. ሥርዓታት የዕድገት መሠረታዊያን በመሆናቸው በዚህ ክፍል የሥርዓታት እና ልማት መስተጋብር፣ ሰላም፣ ፍትህ እና የሕግ የበላይነት፣ ማሕበራዊ እሴቶች፣ የመንግሥት ተቋማት እና አመራር ሚና በምዕራፎች

ተለይተው ተካትተዋል። የእነዚህ ጉዳዮች የልማት ዕቅዱ አካል ሆነው መቅረባቸው የአለፉ ጉድለቶችን ለማረም ዕድል እንደሚሰጥ ተስፋ ተጥሏል።

11. በመጨረሻም የማስፈጸሚያ ሥልቶች በአምሥት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም

    1. የቀጠና ልማት፣
    2. ልዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች፣
    3. የዘርፍ ስትራቴጂዎች እና ፖሊሲዎች፣
    4. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት፣ እንዲሁም
    5. የተቋማት አደረጃጀት እና ሚና የያዙ ምዕራፎች ናቸው።

12. ልዩ ፕሮግራሞች በአለፉት ጥቂት ዓመታት በተከሰቱ ግጭቶች የወደሙ አቅሞችን እና የኑሮ መሠረቶችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን የሚያካትት ሲሆን የተቋማት አደረጃጀት እና ሚና ይህን ዕቅድ ማስፈጸም የሚችል የክልል የዘርፍ ተቋም አደረጃጀት ምን መምሰል እንዳለበት በሳይንሳዊ መንገድ ተንትኖ የሚለይ ምዕራፍ ነው።

## ምዕራፍ ሁለት
## የዕቅዱ አስፈላጊነት እና ልዩ ባሕርያት

1. አገራዊ ልማትን በሣይንሳዊ አግባብ በዕቅድ መምራት ያለው ፋይዳ የመካከለኛ እና የረጅም ልማት ዕቅድ አቅደው ከድህነት ወደ ብልጽግና በተሸጋገሩ የደቡብ ምሥራቅ እና ደቡብ ኤሲያ አገራት ተሞክሮ የተመሰከረለት ነው። በተለይም ደቡብ ኮሪያ የአንድ ትውልድ የኢንዱስትሪያላዊነት ዕቅድ ነድፋ ከዚህ የረጅም ዘመን ዕቅድ የሚቀዱ ተከታታይ የአምሥት ዓመታት የልማት ዕቅዶች መተግበሯ የሩቅ ግብን አይቶ የአጭር ጊዜ መርሃ ግብሮችን ለማነጣጠር በማስቻሉ ከቁርጠኛ አፈጻጸም ጋር ተዳምሮ ለኢኮኖሚ መመንጠቅ አብቅቷታል። በዘመኑ ልማትን በዕቅድ መምራት የሶሻሊዝም አስተሳሰብ ቢመስልም የደቡብ ኮሪያ የልማት ዕቅድ እና ትግበራ አማካሪዎች ምዕራባዊያን ሲሆኑ ደቡብ ኮሪያም በዕቅድ የገነባችው የልማት አቅም የግሉን ዘርፍ በግንባር ቀደምትነት የሚያሳትፍ ካፒታሊሥት ሥርዓት አቅም ነው።

2. ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ የሚጀምር ልማትን በዕቅድ የመምራት የረጅም ዘመን ልምድ አላት። በተለይም ከ1949 የሚጀምሩት የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሦስት ተከታታይ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች የልማት ተሞክሮን በአገር ደረጃ ከማለማመድ ባለፈ የየራሳቸው ጠንካራ ጎኖች ነበሯቸው። የመጀመሪያው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በመሠረተ ልማት፣ በግብዓት ማዕድን ልማት እና በልማት ፋይናንስ ላይ፤ የሁለተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ፤ በመጨረሻም የሦስተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በግብርና በተለይም በዘመናዊ ግብርና ላይ ማተኮራቸው በታሰቡት ዘርፎች መልካም ጅምሮች አሳይተዋል። በተለይም በሁለተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ የትግበራ ወቅት ከፍተኛ የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገት የተመዘገበ ሲሆን ይህ ዕድገት የፈጠረውን የግብዓት እና የምግብ ፍላጎት ለማሟላት በሦስተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ወቅት በግብርናው ዘርፍ የተደረገው ርብርብ ለዛሬው የአርሲ አካባቢ ከፍተኛ የአዝዕርት ምርታማነት፣ ለታችኛው አዋሽ የፍራፍሬ እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ልማት፣ እንዲሁም የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የቡና ልማት መሠረት ጥሎ አልፏል። የሦስተኛው ዓመት የልማት ዕቅድ ተገምግሞ ወደ አራተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በሚሸጋገርበት የ1960ዎቹ አጋማሽ ከምርት ዕድገት በላይ ለሀብት ክፍፍል እና የፖለቲካ ሥርዓት የበለጠ ትኩረት የሰጠው የሶሻሊዝም ንቅናቄ አብዮታዊ የሥርዓት ለውጥ አስከትሎ የልማት ቅኝቱም በዚያው ልክ ተቀይሯል።

3. በጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳር ደርግ ዘመን በኋላም በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) መንግሥት የተተገበረው ዕቅድ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለምን መሠረት ያደረገ ሲሆን የሶሻሊዝም ሥርዓቱ በዓለም ላይም ሆነ በኢትዮጵያ እስከሚወድቅ ድረስ በተለይ በኢንዱስትሪ ልማት የተገኙት መለስተኛ አቅሞች በዕቅድ የተመሩ ነበሩ። በደርግ ዘመን በግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የታዩት የአፈጻጸም ችግሮች የተከሰቱት እና አጠቃላይ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማሽቆልቆል የተፈጠረው ከዕቅድ ጉድለት ይልቅ ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን በማያበረታታው የሶሻሊዝም የወል ተሳቶፎ ሥልተ ምርት ምክንያት ነበር።

4. የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) መንግሥት ወደ ሥልጣን ከወጣበት ከ1983 መጨረሻ ጀምሮ እስከ 1995 ድረስ የሚጠቀስ የልማት ዕቅድ ያልነበረ ሲሆን ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትርጉም ባለው ደረጃ ማገገም እንኳ ያልቻለበት ጊዜ ነበር። ከ1998 በፊት በነበሩት ሦስት ዓመታት ከተተገበረው የዘላቂ ልማት እና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ (Sustainable Development and Poverty Reduction Program - SDPRP) ቀጥሎ ከ1998 እስከ 2002 ድረስ በዕቅድ ደረጃ በጉልህ የተተገበረው "ፈጣን እና ዘላቂ ልማት ድህነትን ለማትፋት (Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty- PASDEP)" የተሰኘው ሲሆን ይህ ዕቅድ በተለይም በመሠረተ ልማት እና በከተሞች የግንባታ ዘርፍ ማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ንቅናቄ ፈጥሯል። ይህ የመሠረተ ልማት እና የሕንጻዎች ግንባታ የፈጠረው አዲስ ፍላጎት የግብርናው ዘርፍ እንዲነቃቃ በማስቻሉ በግንባታ ዘርፍ፣ በግብርና ዘርፍ እና በአገልግሎት ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ፈጣን ዕድገት በመመዝገቡ አጠቃላይ አገራዊ ምርት በሁለት አኀዝ ምጣኔ ማደግ ችሏል።

5. የፈጣን እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ ትግበራ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ቢያሳይም የአምራች ኢንዱስትሪው ያልተነቃቃ እና የግብርናው ዘርፍም የከተማው የግንባታ ልማት የፈጠረለትን ፍላጎት በመጠቀም ጊዜያዊ አቅሙን ከማሳደግ ባለፈ ቀጣይነት ያለው ፈጣን የምርታማነት እድገት ባለማረጋገጡ ኢኮኖሚው በዋጋ ንረት መፈተን ጀምሯል። ይህ ክስተት በኢሕአዴግ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ለአምራች ኢንዱስትሪው ትኩረት የሚሰጥ የአምሥት ዓመት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (Growth and Transformation Plan - GTP) ተዘጋጅቶ በ2003 ወደ ትግበራ እንዲገባ ምልክት ሰጥቷል። የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተለይም በመንግሥት የሚሠሩ ግዙፍ የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የዘመናዊ ግብርና መሠረተ ልማቶች፣ የኃይል አቅም ግንባታ፣ እና የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ትኩረት ሰጥቶ ወደ ሥራ የተገባ ቢሆንም አፈጻጸሙ በአብዛኛው ስኬታማ አልነበረም። ዕቅዱን በሁለተኛ ምዕራፍ ለማስቀጠል የተደረጉ ጥረቶችም ለውጤት ሳይበቁ የ2010 ለውጥ ቀድሟቸዋል።

6. ከዕቅድ ትግበራ አንጻር ለዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያልተሳካ አፈጻጸም ሦስት ተያያዥ ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው። የመጀመሪያው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት በአመክንዮ ረገድ በዋናነት በግሉ ዘርፍ መመራት የነበረበት ሲሆን በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረው ይህ ዘርፍ በደርግ ዘመን ፋብሪካዎቹ በመወረሳቸው እና ከ500 ሺህ ብር በላይ ካፒታል በሚጠይቁ ማንኛውም ኢንዱስትሪ እና ቢዝነስ እንዳይገባ ተከልክሎ በመኖሩ በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ልክ ማሳተፍ የሚችል አቅም አልነበረውም። ሁለተኛው ምክንያት የመጀመሪያውን ክፍተት ለመሙላት መንግሥት ራሱ በስኳር ኢንዱስትሪ፣ በማዳበሪያ ፋብሪካ፣ በከፍተኛ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ፣ እና በኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንዱስትሪዎች በፍጥነት መግባቱ ቀድሞውኑ የሚታወቀው የመንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ዝቅተኛ ምርታማነት እና ቅልጥፍና መነጸባረቁ ነው። ሦስተኛው ምክንያት መንግሥት የልማት ዕቅድ ሣይንስ አስፈላጊ በነበረበት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በሰለጠነ የሰው ኃይል እና በመዋቅር የሚገለጽ የልማት ዕቅድ አቅም አልነበረውም። በንጉሡ ዘመን የተፈጠሩ፣ በኋላም በደርግ ዘመን በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ እስከ ሁለተኛ ድግሪ የልማት ዕቅድን በማስተማር የተፈጠሩ ሰብአዊ አቅሞች እና መዋቅሮች ከ1983 ጀምሮ በመቋረጣቸው እና በመፍረሳቸው ምክንያት ዕቅድን በአሳታፊነት አቅዶ ከላይ እስከ ታች በሚደርስ መዋቅር በተገቢው የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ለመተግበር አልተቻለም፤ የዕቅድ ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታም ለክትትል እና ግምገማ ፖለቲካዊ ድጋፍ አልተደረገም። በውጤቱም በቅንጅት ጉድለት፣ በኮንትራት አስተዳደር ድክመት፣ በአቅም ማነስ እና በሙስና በሚገለጹ የሥርዓታት ጉድለቶች በቅርብ ዘመን የተሻለ የተባለለት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል።

7. የለውጡ መንግሥት ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሣሌት የማድረግ ርዕይ ያለው የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ (2013 - 2022) ነድፎ ወደ ተግባር ተሸጋግሯል። የአማራ ብሔራዊ ክልልም በተዋረድ የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ከተሸጋገረ አራት ዓመታት ተቆጥረዋል። ክልሉ የቀጣዮቹን የአምሥት ዓመታት ዕቅድ በማዘጋጀት ሂደት ያለፉትን አራት ዓመታት የአፈጻጸም ጉድለቶች ለማካካስ እና ከዚያም በላይ ለመመንጠቅ የሚያግዝ መደላድል ለመፍጠር በአለፉት ዕቅዶች ግምት ውስጥ ያልገቡ እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ነቅሶ የተሻለ ተተግባሪነት ያለው ዕቅድ ለማዘጋጀት ዕድል አለው።

8. የዚህ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ እስከ አሁን ከተተገበሩት የልማት ዕቅዶች የሚለዩት የሚከተሉት ልዩ ባሕርያት አሉት፤

- የረጅም ጊዜ ችግሮችን ከጥቅል ኢኮኖሚ፣ ከዘርፎች፣ ከአቅሞች፣ እና ከልማት ፋይናንስ አንጻር በመተንተን ከክፍተቶች እና ክፍተቶችን ለመሻገር በልማት ከተሳካላቸው አገራት ልምድ በመውሰድ ተቀምሯል፣
- የክልሉ ችግሮች ፈርጀ-ብዙ እንደመሆናቸው መጠን እቅዱ ከማሕበራዊ እና ኢኮኖሚ ልማት በተጨማሪ የሥርዓታት ሚናን እንዲያካትት ተደርጓል፣ እንዲሁም
- ዕቅዱ እንዴት እንደሚፈጸም የሚያመላክቱ የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተነድፈዋል።

9. የጥቅል ኢኮኖሚ፣ የዘርፎች፣ የአቅሞች፣ እና የልማት ፋይናንስ ዕቅዶች የእስከ አሁን አፈጻጸማቸው የዓለም አገራት ከደረሱበት አድማስ አንጻር ተገምግሞ የተገኙ ክፍተቶችን በመለየት መፍትሄ የሚሆኑ ጥቅል ስትራቴጂዎች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች እና ጥቅል ግቦችን በሚያመላክት ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው። በዚህ ረገድ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ግብ ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ በሚያስችለው አቅም፣ ከመዋዕለ ንዋይ እና የቴክኖሎጂ ደረጃ አንጻር በቴክኒክ ደረጃ ባለው የተተግባሪነት መስፈርት፣ እንዲሁም በቅርብ ዘመናት በፈጣን ዕድገት ላይ የነበሩ እና ያሉ አገራት ካሳኩት የዕድገት መጠን አንጻር ተገናዝቦ የተቀመረ ነው። የሰው ኃይል፣ የመዋዕለ ንዋይ፣ እና የምርታማነት ግቦች የታቀዱትም ከዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በሚጣጣም መልኩ ነው።

10. በአቅሞች ደረጃ የክልሉ የሚታነጹ የተፈጥሮ ሀብቶች እና የማይዳሰሱ አስቻይ አቅሞች፣ የመሠረተ ልማት አውታር እና ፍላጎት፣ የቴክኖሎጂ ፍላጎት፣ እና የሰው ኃይል አቅም እና ፍላጎት በምዕራፎች ተለይተው ተተንትነው ቀርበዋል። በተለይም የአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ በቴክኖሎጂ ተስተካካይነት የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን በአንድ ትውልድ ማሳካትን ግባ ላደረገው የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ መሠረት መጣል በመሆኑ ለቴክኖሎጂ ዘርፍ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶ ዘርዝር ዕቅድ ተዘጋጅቷል። በዚህ ረገድ የዓለም የረጅም ዘመን የቴክኖሎጂ ጉዞ እና ወሳኝ ልምዶች የተተነተኑ ሲሆን ከክልሉ እና ከአገሪቷ አንጻራዊ የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ በመመሥረት ለቴክኖሎጂ ተስተካካይነት የሚያግዙ ስትራቴጂዎች፣ ዝግጁነቶች፣ ግቦች እና የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተመላክተዋል።

11. የልማት ፋይናንስ አንዱ የዕቅዱ ወሳኝ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በመዋዕለ - ንዋይ፣ ቁጠባ እና የፋይናንስ ተቋማት ልማትን፣ እንዲሁም የመንግሥት ፋይናንስን በያዙ ሁለት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው። መዋዕለ ንዋይ ዋና የዕቅዱ ማስፈጸሚያ መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን የዘርፉ የአለፉ ዘመናት አፈጻጸም በበርካታ መስፈርቶች ተመላክቶ ከመቅረቡም በላይ ከጉድለቶች በመነሳት የወደፊት ስትራቴጂዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች ተመላክተዋል። ዕቅዱን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የመንግሥት ወጪዎች እና የፋይናንስ ምንጮችም ከባለፈ አፈጻዓጸም ትንተና በመነሳት ተለይተው ታቅደዋል።

12. ሥርዓታትን በማካተት ረገድ የዕድገት መሠረታዊያን የሆኑትን የሕግ፣ የባሕል፣ እና የተቋማት እና አመራር ሚና ጉዳዮች በእቅዱ በአስቻይነት እንዲካተቱ ተደርጓል። የሥርዓታት ክፍል የመጀመሪያ ምዕራፍ የሥርዓታት እና ልማት መስተጋብርን የሚዳስስ ሲሆን፣ ፍትህ እና የሕግ የበላይነት፣ ባሕል፣ እንዲሁም የተቋማት እና የአመራር ሚና በምዕራፎች ተከፋፍለው ቀርበዋል።

13. የዕቅዱ ማስፈጸሚያ ሥልት የያዘው የዕቅዱ ስምንተኛው እና የመጨረሻው ክፍል የልማት ቀጠናዎች (ስፔሺያል ፕላን)፣ የልዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች፣ የዘርፎች ስትራቴጂ እና ፖሊሲ፣ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት፣ እንዲሁም የተቋማት መዋቅር እና ሚና በያዙ አምሥት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው። በተለይም የቀጠና ልማት እንዲሁም የልዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ዕቅድ በቅርብ ዘመን ዕቅዶች ያልተስተዋሉ ሲሆኑ፣ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓትም ትኩረት ያልተሰጠው መስክ ነው። የዚህ አምሥት ዓመት የልማት ዕቀወድ አንድ ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫ ከርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት እስከ ቀበሌ ድረስ በሚዘረጋ መዋቅር የልማት ችግርን በወቅቱ መፍታትን ግብ ያደረገ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ማስፈን ሲሆን ይህ በተቀናጀ የዘመናዊ መረጃ፣ በዘርፎች ቅንጅት፣ እና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን ተቋማዊ አደረጃጀት የሚተገበር የማስፈጸሚያ ሥልት የዕቅዱ አንዱ መለያ ባሕርይ ነው።

# ክፍል ሁለት

# የዕቅዱ መነሻዎች

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሦስት | **ዓለም አቀፋዊ ፣ ቀጣናዊ፣ አገራዊ፣ እና ክልላዊ ሁኔታዎች** |
| ምዕራፍ አራት | **ክልላዊ የልማት አፈጻጸም** |
| ምዕራፍ አምሥት | **የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ** |
| ምዕራፍ ስድስት | **የአማራ ብሔራዊ ክልል ርዕይ እና ስትራቴጂክ ምሰሶዎች** |

# ምዕራፍ ሦስት
# ክልላዊ፣ አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

## 3.1. ክልላዊ እና አገራዊ ሁኔታዎች

### በግጭት መሃል የተገኘ ልማት

14. ከ2010 ለውጥ በኋላ መንግሥት ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሣሌት የማድረግ ርዕይ ያለው የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ (2013 - 2022) ነድፎ ወደ ተግባር ተሸጋግሯል። የአማራ ብሔራዊ ክልልም ከአገራዊ ግቦች ጋር የተጣጣመ የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ከተሸጋገረ አራት ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ከልማት አፈጻጸም አኳያ ሁለት መንታ ዕውነታዎች ተስተውለዋል። የመጀመሪያው ዕውነታ ክልሉ እንደ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ የአንበጣ መንጋ፣ ድርቅ፣ እንዲሁም የጸጥታ መታወክ በመሳሰሉ ደፋቂ ኩነቶች (adverse shocks) በተከታታይ ከመጠቃቱ አንጻር ቀላል የማይባል የኢኮኖሚ ዕድገት እና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ መመዝገቡ ነው። ሁለተኛው ዕውነታ ደግሞ የክልሉ ኢኮኖሚ ተግዳሮትን መቋቋም መቻሉ የሚያበረታታ ቢሆንም በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ከተቀመጡት ግቦች እና በፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት መፈታት ከነበረባቸው ሥር የሰደዱ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ችግሮች አኳያ የልማት አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የመሆኑ ጉዳይ ነው።

15. ከ2013 እስከ 2016 በነበሩት አራት የትግበራ ዓመታት ክልላዊ ጥቅል ምርት በ5.1 በመቶ ያደገ ሲሆን ይህ በአሥር ዓመቱ ዕቅድ በግብ ከተመላከተው የ9.4 በመቶ አማካይ ዕድገት ያነሰ ነው። በዘርፍ አፈጻጸም ደረጃ ከአምራች ኢንዱስትሪ በስተቀር የዋና ዋና ዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት ምጣኔዎች ከዕቅዱ ግቦች የራቁ ናቸው። የአምራች ኢንዱስትሪ ተጨማሪ ዕሴት በአራት ዓመቱ የትግበራ ወቅት በ16.1 በመቶ ያደገ ሲሆን ይህ ምጣኔ ከሌሎች ዘርፎች አፈጻጸም አንጻር በዕቅድ ከተቀመጠው የ19.8 በመቶ የዕድገት ምጣኔ ግብ ጋር የሚቀራረብ ነው። ነገር ግን፣ በአጠቃላይ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ እና የአገልግሎት ዘርፎች እንደ ቅደም ተከተላቸው በ3.4 በመቶ፣ በ6.9 በመቶ፣ እና በ7.5 በመቶ ብቻ በማደግ ከግብ በታች የሆነ አፈጻጸም አሳይተዋል። በከፋ ደረጃም የኮንስትራክሽን እና የትምሕርት ንዑስ ዘርፎች የአራት ዓመታት አማካይ የተጨማሪ ዕሴት ዕድገት ከዜሮ በታች ነበር።

16. ይህ አዝጋሚ የኢኮኖሚ ዕድገት ማሕበረሰቡ በኑሮው ለሚለካቸው የኑሮ ውድነት፣ ከፍተኛ ሥራ አጥነት እና ዳተኛ ድህነት መባባስ ምክንያት ሆኗል። የክልሉ የሸማቾች ጥቅል ዋጋ (consumers price index) በአራት ዓመቱ ወቅት ከ15.4 በመቶ እስከ 33.2 በመቶ በሚደረስ ምጣኔ የጨመረ ሲሆን ለወትሮው ከአገር አቀፍ አማካይ በታች የነበረው የክልሉ የዋጋ ንረት ምጣኔ በአለፉት ሁለት ዓመታት ከአገር አቀፍ ምጣኔ በላይ ሆኗል። በ2013 መረጃ መሠረት የክልሉ ሥራ አጥነት ምጣኔ በ2003 ከነበረበት 3.4 በመቶ በ2013 ወደ 7.5 በመቶ ከፍ ብሏል። በብዛት ደረጃም ከአገሪቷ ሥራ አጥ ውስጥ 24.7 በመቶ ወይም ከአራት ሥራ አጥ መካከል አንዱ በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚገኝ ነው። ከ2013 በኋላ ባሉት ዓመታት ክልሉ ካለበት የጸጥታ ችግር በመነሳት ይህ ምጣኔ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር ይጠበቃል። በ2008 የዳሰሳ ጥናት መሠረት 26.1 በመቶ የነበረው ከብሔራዊ ድህነት ወለል በታች የሚገኝ የክልሉ ሕዝብ ምጣኔ ባለው አዝጋሚ የኢኮኖሚ ዕድገት እና የጸጥታ ችግር ምክንያት እንደሚሻሻል አይጠበቅም። የትምህርት ጥራት መጓደል እንዳለ ሆኖ ቢያንስ ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ እና ሽፋንን በማሳደግ ረገድ በክልሉ በሁሉም ደረጃ ታይቶ የነበረው አበረታች ውጤት እስከ 2016 ባሉት ጥቂት ዓመታት በአሳሳቢ ሁኔታ ቀንሷል።

17. ከግብ በታች ለተመዘገበ የኢኮኖሚ ዕድገት እና አበረታች ያልሆኑ ተያያዥ የጥቅል ኢኮኖሚ ምልክቶች የአለፉትን አራት ዓመታት ደፋቂ ኩነቶች በተለይም ግጭት የወለደው የጸጥታ ችግርን በምክንያትነት ማቅረብ ይቻል ይሆናል። ከዚህ በመነሳት ሁለት መንታ ጥያቄዎችን ማንሳት ይገባል፤ አንደኛ፣ በአለፉት አራት ዓመታት የተከሰተው የሰላም መደፍረስ ቢስተካከል የኢኮኖሚ ዕድገት እና በአጠቃላይም ዘላቂ ልማት በቀላሉ ይረጋገጣልን? ሁለተኛ፣ በድህረ ግጭት ወቅት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግሮች ተፈትተው ልማት በትክክለኛ አሻጋሪ ፍኖት ላይ መትመም ቢጀምር ግጭት እንደ ክልል እና እንደ አገር ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ይቆም ዘንድ የኢኮኖሚ ዕድገት ዋስትና ይሆናልን?

## ተስፋ ያጫረ ዕድገት እና የአንድ ትውልድ የአዝጋሚ መዋቅራዊ ሽግግር ዳፋ

18. ከኢኮኖሚ ዕድገት እና ልማት አፈጻጸም ትንተና አንጻር ከአጭር ጊዜ የጥቅል ኢኮኖሚ ክስተቶች ደራሽ ምክንያቶች ባለፈ የክልሉን እና የአገሪቷን የረጅም ጊዜ (long run) እና የሩቅ ዘመን (very long run) ጉዞ መቃኘት ተገቢ ይሆናል። የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ያሉት ሦስት አሥርት ዓመታት የማይቀለበስ የኢኮኖሚ ዕድገት በማረጋገጥ ለመመንጠቅ በቂ ነበሩ። በዚህ ወቅት ከ1980ዎቹ ጀምሮ እስከ 1997 የነበሩት አሥራ አራት ዓመታት ከኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም አኳያ በከፊል ከሶሻሊዝም አጥመልማይ ተጽዕኖ እና ከረጅም ዓመታት ጦርነት አመድ ለማገገም፣ በከፊል ደግሞ በፖሊሲ ስሕተቶች ምክንያት የባከኑ ዓመታት ነበሩ። ከ1998 ጀምሮ ለአምሥት ዓመታት በተተገበረው የተፋጠነ እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ (Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty - PASDEP) እና ከ2003 እስከ 2007 በተተገበረው የመጀመሪያው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (Growth and Transformation Plan – GTP) ወቅት በአገር አቀፍም ሆነ በአማራ ብሔራዊ ክልል የተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በኢኮኖሚ የመመንጠቅ እና የመልማት ተስፋን ፈንጥቆ ነበር። ከ1998 ጀምሮ በነበሩት ቀጣይ አሥር ዓመታት የክልላዊ ጥቅል ምርት በአማካይ በዓመት በ9 በመቶ አድጓል። ይህ ዕድገት የክልሉን የድህነት ምጣኔ በ1992 ከነበረበት 41.6 በመቶ በ2008 ወደ 26.1 በመቶ እንዲቀንስ አስችሏል። በጤናው ዘርፍ እና በሌሎች ዘርፎች በተደረገ ጥረትም የክልሉን ጨምሮ አገር አቀፍ አማካይ በሕይወት የመቆያ ዕድሜ (longevity) በ1983 ከነበረበት 47.5 ዓመት በ2014 ወደ 65.6 ዓመት ከፍ እንዲል አስችሏል።

19. የዚህ ዕድገት ሌላው ገጽታ ሲታይ የሁለቱ ዕቅድ ዘመናት አፈጻጸም አበረታች የመሆኑን ያህል በአንድ አሥርት ዓመታት የተመዘገበው ፈጣን ዕድገት በቀጣዮቹ የዕቅድ ዓመታት ወደ የማይቀለበስ ዕድገት መመንጠቅ እና መዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጥ አልቻለም። የአለፉትን ሁለት አሥርት ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም በጥቅል ሲታይ ከ1998 እስከ 2016 ባሉት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት የክልሉ ኢኮኖሚ በክልላዊ ጥቅል ምርት ሲለካ በ6.9 በመቶ አድጓል። ይህ የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ከዓለም 7ኛ ከአፍሪካ ደግሞ ኢትዮጵያን ሳይጨምር 1ኛው ፈጣን ምጣኔ ነው። ይህ ዕድገት በተለይ ከሌላው ዓለም አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የመቻል ስነ ልቦናን በመፍጠር ረገድ አበረታች እና ለወደፊት ጥረቶች መነሻ አቅም ይሆናል።

20. ነገር ግን፣ ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ በክልሉ ያለውን የገነነ ድህነት በአንድ ትውልድ ለመናድ የሚያስችል ፍጥነት አልነበረውም። ከዚህ ጋር በተያያዘ እና በበለጠም የኢኮኖሚ ዕድገቱ በጥቅል ምርትም ሆነ በዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት ከ1998 እስከ 2002 በነበረበት ከፍተኛ ምጣኔ ከመዝለቅ ይልቅ ከግጭት በፊት በነበሩት ዓመታት ቀድሞውኑም እየቀነሰ ነበር። የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት በመጀመሪያው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወቅት ከነበረበት የ9 በመቶ ምጣኔ በሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ወቅት ወደ 5.9 በመቶ፣ በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመጀመሪያዎቹ አራት ዓመታት ደግሞ ወደ 5.1 በመቶ ቀንሷል። ከዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት መቀዛቀዝ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት፣ ሥራ አጥነት፣ እና አዝጋሚ የድህነት ቅነሳ ምጣኔ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የተጀመሩ የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መጓተት እና ከፕሮጀክቶቹ አለመሳካት ጀርባ ያሉ ሙስናን ጨምሮ ያልተገቡ ምክንያቶች ከሌሎች ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ጋር ተዳምረው ሕዝብን ለተቃውሞ አነሳስተው ለ2010 የፖለቲካ ሪፎርም እና ለውጥ ምክንያት ሆነዋል።

21. ሥዕል 1 -1፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል ክልላዊ ጥቅል ምርት ዕድገት በዕቅድ ዘመናት




| | ክልላዊ ጥ. ምርት | ግብርና | ኢንዱስትሪ | አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| የተፋጠነ እና ዘላቂ ል. ዕ.፤ 1998 - 2002 | 8.8 | 10.0 | 5.6 | 8.3 |
| ዕ.ት.ዕ. - 1፤ 2003 - 2007 | 9.0 | 7.2 | 14.1 | 11.2 |
| ዕ.ት.ዕ - 2፤ 2008 - 2012 | 5.9 | 4.1 | 8.1 | 8.3 |
| የአሥር ዓመት ዕቅድ*፤ 2013 - 2016 | 5.1 | 3.4 | 6.9 | 7.5 |

ምንጭ፤ የአብክመ ፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃን መሠረት በማድረግ የተቀናበረ
*የአራት ዓመት አፈጻጸም

22. በዚህ ሁኔታ በአንድ በኩል ለተቀዛቀዘው የኢኮኖሚ አፈጻጸም ከግጭት የሚያልፉ መሠረታዊ እና መዋቅራዊ ችግሮች መኖራቸውን፣ በሌላ በኩል በእነዚህ መሠረታዊ ምክንያቶች የአኮኖሚ አፈጻጸም እንደ አገር መዳከም የተቀሰቀሰን የሕዝብ የማደግ ተስፋ ማርካት ባለመቻሉ የኢኮኖሚ መንገራገጭ ወደ ግጭት ማምራቱን ማስተዋል ይቻላል። የረጅም ዘመን የክልሉ እና የአገሪቷ አዝጋሚ የኢኮኖሚ እድገት ምንጭ አሻጋሪ ያልሆነ እና አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ ሲሆን ከዚህ ጋር የሚያያዙ ቁልፍ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ዝቅተኛ ምርታማነት (low productivity) እና ከአቅም በታች በማምረት፣ አዋጭ ባልሆነ የሀብት ስምሪት፣ በብክነት፣ በመጓተት፣ እና በተጋነነ የወጪ ክለሳ የሚገለጹ ዝቅተኛ ቅልጥፍና (inefficiency) ናቸው። አሻጋሪ መዋቅራዊ ለውጥ የምርት ሥርዓትን ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው ዘርፎች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ዘርፎች ያሸጋግራል፤ በዘርፎቹም ቅልጥፍና ይሰፍናል። እነዚህ ከአሻጋሪ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተያያዙ የምርታማነት እና የቅልጥፍና ጉዳዮች በተለይ በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ሳለ ዕቅዱ ግቡን ሳያሳካ ኢኮኖሚው የዕድገት ፍጥነቱን መቀነስ የጀመረው ባልዳበረ የአገር በቀል ኢንዱስትሪያላዊ የግል ዘርፍ፣ በአፈጻጸም ወቅት በታዩ የፕሮጀክት አስተዳደር ድክመት፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ በሣይንሳዊ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት መጓደል፣ ሙስናን ጨምሮ ያልተገቡ አፈጻጸሞችን የሚያርም ተጠያቂነት በሚያሰፍን የፖለቲካ አመራር ክፍተት በሚገለጽ የሥርዓታት ድክመት ነው

## የሰባት አሥርት ዓመታት የኢትዮጵያ የልማት ውጥኖች እና ያልተሻገረቻቸው መታጠፊያዎች

23. የኢትዮጵያን የልማት ጉዞ በመበየን ረገድ የሥርዓታት ሚና መሠረታዊነት ከአለፉት የሁለት አሥርት ዓመታት ክስተቶች ይልቃል፤ መፍትሄውም የቅርብ ዓመታት መስተጋብሮችን በመተንተን ብቻ የሚገለጽ አይደለም። የተሟላ የኢኮኖሚ መረጃ መያዝ ከተጀመረበት ከ1950ዎቹ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በተስፋ እና በስጋቶች አልፏል። በዚህ ወቅት የነበረው የአገሪቷ ኢኮኖሚ በአብዛኛው በዕቅድ የተመራ ነበር። በመሠረቱ ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ የሚጀምር ልማትን በዕቅድ የመምራት የረጅም ዘመን ልምድ አላት። በተለይም ከ1949 የሚጀምሩት የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሦስት ተከታታይ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች የልማት ተሞክሮን በአገር ደረጃ ከማለማመድ ባለፈ የየራሳቸው ጠንካራ ጎኖች ነበሯቸው። በጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዘመን በኋላም በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) መንግሥት የተተገበረው ዕቅድ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለምን መሠረት ያደረገ ሲሆን የሶሻሊዝም ሥርዓቱ በዓለም ላይም ሆነ በኢትዮጵያ እስከሚወድቅ ድረስ በተለይ በኢንዱስትሪ ልማት የተገኙት መለስተኛ አቅሞች በዕቅድ የተመሩ ነበሩ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) መንግሥት በተለይ ከ1998 እስከ 2002 ድረስ በዕቅድ ደረጃ በጉልህ የተተገበረው "ፈጣን እና ዘላቂ ልማት ድህነትን ለማጥፋት (Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty- PASDEP)" የተሰኘው፣ ከ2003 እስከ 2007 የተተገበረው

የመጀመሪያው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ እንዲሁም ከ2008 እስከ 2010 ለውጥ እና ከዚያም እስከ 2012 የቀጠለው ሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዕድገት ተስፋ እና ስጋት በማመላከት ረገድ ተጠቃሽ ናቸው።

24. ኢትዮጵያ የሰባት አሥርት ዓመታት የልማት ዕቅድ ልምድ ያላት አገር ሆና ሳለ ስለምን ዕቅዶቹ እስከ አሁን ሳያሻግሩ ቀሩ ለሚለው ጥያቄ እንደየዘመኑ የራሱ ምክንያት አለው። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተተገበሩት ሦስት ተከታታይ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች የራሳቸው ጥሩ አፈጻጸም ቢኖራቸውም የመሬት ሥሪትን ለመቀየር ዳተኛ የሆነው ሥርዓት ከሶሻሊዝም አክራሪ ርዕዮት ዓለም መከሰት ጋር ተዳምሮ ቢያንስ በኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ፈር ይዞ የነበረው ጅምር በ1966 አብዮት እንዲኮላሽ አስተዋጽዖ አድርጓል። በደርግ ዘመን በግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የታዩት የአፈጻጸም ችግሮች የተከሰቱት እና አጠቃላይ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማሽቆልቆል የተፈጠረው ከዕቅድ ጉድለት ይልቅ ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን በማያበረታታው የሶሻሊዝም የወል ተሳትፎ ሥልተ ምርት ምክንያት ነበር።

25. ከዕቅድ ትግበራ አንጻር ለዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያልተሳካ አፈጻጸም ሦስት ተያያዥ ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው። የመጀመሪያው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት በአመክንዮ ረገድ በዋናነት በግሉ ዘርፍ መመራት የነበረበት ሲሆን በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረው ይህ ዘርፍ በደርግ ዘመን ፋብሪካዎቹ በመወረሳቸው እና ከ500 ሺህ ብር በላይ ካፒታል በሚጠይቁ ማንኛውም ኢንዱስትሪ እና ቢዝነስ እንዳይገባ ተከልክሎ በመኖሩ በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ልክ ማሳተፍ የሚያስችል አቅም አልነበረውም። ሁለተኛው ምክንያት የመጀመሪያውን ክፍተት ለመሙላት መንግሥት ራሱ በስኳር ኢንዱስትሪ፣ በማዳበሪያ ፋብሪካ፣ በከፍተኛ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ፣ እና በኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንዱስትሪዎች በፍጥነት ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ቀድሞውኑ የሚታወቀው የመንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ዝቅተኛ ምርታማነት እና ቅልጥፍና መንጸባረቁ ነው። ሦስተኛው ምክንያት፣ የልማት ዕቅድ ሣይንስ አስፈላጊ በነበረበት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መንግሥት በሰለጠነ የሰው ኃይል እና በመዋቅር የሚገለጽ የልማት ዕቅድ አቅም አልነበረውም። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተፈጠሩ፣ በኋላም በደርግ ዘመን በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ እስከ ሁለተኛ ድግሪ የልማት ዕቅድን በማስተማር የተገነቡ ሰብአዊ አቅሞች እና መዋቅሮች ከ1983 ጀምሮ በመቋረጣቸው እና በመፍረሳቸው ምክንያት ዕቅድን በአሳታፊነት አቅዶ ከላይ እስከ ታች በሚደርስ መዋቅር በተገቢው የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ለመተግበር አልተቻለም፤ የዕቅድ ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታም ለክትትል እና ግምገማ ፖለቲካዊ ድጋፍ አልተደረገም። በውጤቱም በቅንጅት ጉድለት፣ በኮንትራት አስተዳደር ድክመት፣ በአቅም ማነስ እና በሙስና በሚገለጹ የሥርዓታት ጉድለቶች ምክንያት በቅርብ ዘመን ታሪክ የተሻለ የተባለለት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተጠበቀው ልክ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል።

26. በሁሉም መንግሥታት ዘመን የተተገበሩ የልማት ዕቅዶች ለአሻጋሪ ልማት ውጤት አለመብቃት ገዢ ምክንያት የሥርዓታት ጉዳዮች ትኩረት ማጣት ነው። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የልማት ዕቅዶች ወቅት ማሕበረሰብ ለዘመናዊ ልማት የነበረው ኋላቀር አመለካከት እና የመሬት ሥሪት ለዕቅዶቹ ተተግባሪነት እንደ ትልቅ ተግዳሮት ተጠቅሰው ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው በዕቅድ ሰነዶቹ ተመላክቶ ነበር። ሥርዓታት በባሕርያቸው በጣም የረጅም ጊዜ ጉዳዮች ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የአለፉ ዘመናት ዕቅዶች ከአምሥት ዓመት ያልዘለሉ የመካከለኛ ዘመን ዕቅዶች ናቸው። ከሥርዓታት ለውጥ አንጻር በትምህርት እና በባሕል አብዮት ለውጥ ለማምጣት በዘመቻ መልክ ሙከራ ያደረገው የደርግ መንግሥት ሲሆን አጠቃላይ የልማት ውጥኖቹ የቆሙበት የሥልተ ምርት ባሕርይ እና ፋታ ያልሰጠው ጦርነት የባሕል ዘመቻው ከንቃት ባለፈ ለዕድገት መደላድልነት እንዳይበቃ ምክንያት ሆነዋል።

## የኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የድህነት እና የግጭት አዙሪቶች፤ የሥርዓታት ሚና

27. ግጭት የክልሉ እና የአገሪቷ የወቅቱ ትልቅ ፈተና ነው። ግጭት ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ አለው። በማሕበራዊ ትንታኔ ረገድ ግጭት ያለ ምክንያት በሰዎች ጠብ አጫሪ ባሕርያት ምክንያት ሊነሳ ይችላል። የዚህ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ማሕበረሰብን ማስተባበር የሚያስችል የኃላፊነት ሚና ሲኖራቸው ግጭት የሥርዓት መልክ ይይዛል።

28. ነገር ግን፣ ከለየለት ወረራ ውጪ ያለ የውስጥ ግጭት በሰበብ በተለይም በፍትህ እና መልካም አስተዳደር መጓደል፣ በጭቆና፣ በፖለቲካ ውክልና እና በመሳሰሉት ሊፈጠር ይችላል። ተራማጅ ባልሆነ ማሕበረሰብ የግጭት ሰበቦች ብዙ ናቸው፤ ወደ ቤት መግባት ያለባቸው የግለሰብ ጉዳዮች ሁሉ አደባባይ ወጥተው መንግሥት እንዲፈታቸው ስለሚቀርቡ በማሕበረሰብ መካከል፣ እንዲሁም በማሕበረሰብ እና ሕግ ማስከበር በሚጠበቅበት መንግሥት ማካከል ግጭት ሊነሳ ይችላል።

29. ከኢኮኖሚ ትንታኔ አንጻር፣ ለታዳጊ አገራት ግጭት የብሔርም ሆነ የመደብ ጭቆና በአብዛኛው ሰበቦች ናቸው:: እውነተኛው የግጭት ምክንያት የልሂቃን ግላዊ ጥቅም (ኪራይ) ነው:: የድህነት እና የግጭት ዘለበቶች በአንዴ መስበር የሚያቅተውም ከግጭት የሚያተርፉ ሰላም ሲሰፍን ወጪአቸው የሚበዛ ተዋንያን ስለሚኖሩ ነው።

30. ዋናው ጉዳይ ግጭትን እና የድህነት አዙሪቶችን በአንዴ ለመስበር ግጭተን በልማት፣ ድህነትን ግጭትን በማስቆም ብቻ የሚቋጭ ሳይሆን ሁለቱን አዙሪቶች በመሠረታዊነት የሚበይኑ ጉዳዮች ወይም መሣሪያዎችን መለየት ያስፈልጋል። ጉልህ የሥርዓታት ፈርጀችም የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባሕል በተለይም የዕምነት፣ ልማድ እና ወጎች፣ የትምሕርት፣ እና የቤተሰብ ሥርዓታት ናቸው። ከሥርዓታት መካከልም በተለይ የኢኮኖሚ ሥርዓታት እና የፖለቲካ ሥርዓት የጠንካራ ቁርኝት ባሕርይ ለዘላቂ መፍትሄ ፍንጭ ይሰጣል።

31. በመሠረታዊነት በሥርዓታት ምክንያት፣ በኢኮኖሚ አውድ ደረጃ ደግሞ በዝቅተኛ ምርታማነት እና ቅልጥፍና የሚድህ አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የኑሮ ውድነት፣ ሥራ አጥነት፣ እና ድህነት የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ችግር ከመሆን አልፈው ለግጭት ምክንያት ሆነዋል። የዚህ ሌላው ገጽታ ደግሞ ታሪክን፣ እምነትን፣ ማንነትን፣ እና ፖለቲካን በመሳሰሉ መሠረታዊ ጉዳዮች የሚከሰት ግጭት ኢኮኖሚን ይጎዳል፤ የግጭት አቧራ ሲሰክንም ድህነት በተራው ይነግሳል። ይህ ማለት ግጭት እና ድህነት በሌሎች መሠረታዊ ምክንያቶች አንዴ ከተጫሩ እርስ በእርሳቸው ለማሕበራዊ ጥፋት ይመጋገባሉ።

32. በዚህ ዘመን የምንኖረው ይህ የአንድ ትውልድ ክስተት በአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በታዩ የምክንያት እና ውጤት መስተጋብር ብቻ የሚገለጽ አይደለም። በአንድ ትውልድ ቁሳዊ ካፒታል፣ ሰብዓዊ ካፒታል፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂን የመሳሰሉ የማምረቻ አቅሞች፣ እና የዕድገት መደላድል እና የርትዕ ማሕበረሰብ መገለጫም የሆኑ ማሕበራዊ ካፒታል ይገነባሉ። በአጭር ጊዜ ደፋቂ ኩነቶች የሚከሰት የጥቅል ኢኮኖሚ ስብራት በኢኮኖሚ ፖሊሲ ይቀለበሳል፤ በመካከለኛ እና በአንድ ትውልድ ዘመን የሚከሰት ግጭት መለስተኛ አቅሞችን ያሳጣል፤ ግጭት በተፈታ ማግስት የአጥፊ ኃይሎች ፀፀት ቁጭትን ወልዶ አቅምን መልሶ እና አስበልጦ ይገነባል። በዘመን በሚለካ አገራዊ ታሪክ የሚደረግ የግጭት አዙሪት ግን ሁሉንም አቅሞች ጨርሶ የመጨረሻው ትውልድ ቅድመ አያቶቹ የሥልጣኔ ባለቤት ስለመሆናቸው እንኳ አሳማኝ ምልክት እና እንጥፍጣፊ የውስጥ የመቻል ስሜት በማይተውበት ደረጃ ሥልጣኔን ያጠፉል።

33. ኢትዮጵያ ከ7ኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም የሥልጣኔ መታጠፊያ በኋላ የመጣችበት የግጭት አዙሪት፣ ከከፍታዋ ጀምሮ በመለስተኛ ስልጣኔዎች እና ድህነት በሚፈራረቅ አዙሪት በቁልቁለት አቅጣጫ ስልጣኔን ንዶ የዛሬው ትውልድ ስለ ዕድገቱ ለዘመናት በተገነባ መደላድል ሳይሆን በጥፍሩ ቆሞ መሥራት ግድ እንዲሆንበት መጥፎ የታሪክ ብያኔ ሰጥቶ አልፏል። ለአክሱም ስልጣኔ መውደቅ የባሕር ማዶ ግዛቶቹን በአመጽ ማጣቱ እና ዓለም አቀፍ የንግድ እና የፖለቲካ ግንኙነቶቹ የቀይ ባሕር በባዕዳን ቁጥጥር ሥር መውደቅን ተከትለው በመዳከማቸው፣ በዚህም ሰበብ በዋናነት ከንግድ ውጭ ለዘመናዊ ኢኮኖሚ ዝግጁነት አለመኖር የወለደው የኢኮኖሚ መታገት (economic stagnation) በቀዳሚ ምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ነገር ግን፣ የስልጣኔው መሠረት የሆነውን የቀይ ባሕር መስመር ያጣው እና ከዚያም በመለስ ከባሕር ወዲህ በነበረ ግዛቱ ላይ ሥልጣኔን ማስጠበቅ ያቃተው በውስጥ የእርስ በእርስ ሽኩቻ እና ጦርነት አቅሙ በመዳከሙ ነው። የዚህ በጦርነት የሚደመደም የጋራ ውድቀት መሠረታዊ ምክንያት ደግሞ ከፖለቲካ እስከ እምነት ያሉ ሥርዓታት ለለውጥ ዝግጁ አለመሆን ነው።

34. ከአክሱም በኋላ የነበሩ የዛግዌ፣ የሐረር፣ እና የጎንደር መለስተኛ ስልጣኔዎችም የተዳከሙት እንዲሁ በጦርነት ምክንያት ነው። ነገር ግን፣ እንደ አክሱም ዘመን ሁሉ በጦርነት ተገፍተው እስኪወድቁ ድረስ እነዚህ ስልጣኔዎች እንደ አውሮፓ ማሕበረሰብ በዘመናዊነት ሳይሻገሩ የቀሩት ዘመኑ ከሚጠይቀው የሣይንስ እና የቴክኖሎጂ ዓለም አቀፋዊ አውድ በተለይም ለዚህ ምቹ መደላድል የሚፈጥር ሥርዓታ ስላልገነቡ ነው። በ12ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ጀምሮ አውሮፓ በተሃድሶ (renaissance) ሲተጋ ኢትዮጵያ ከ11ኛው እስከ

13ኛው ክፍለ ዘመን የዕምነት እና የፖለቲካ መሪነትን ጠቅለለው የያዙ መሪዎቿ በአብዛኛው በእምነት ተቋማት ባተኮሩ ኪነ ሕንጻዎች ግንባታ ላይ ተጠምደው ነበር። አውሮፓ ከሮማ ስልጣኔ መዳከም እና ውድቀት ማግስት በ17ኛው ክፍለ ዘመን የትራንስ - አትላንቲክ አዲስ የስልጣኔ ቀጠና ሲመሠርቱ፣ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ለ80 ዓመት የተካሄደን እምነትን ማዕከል ያደረገ ጦርነት መቋጫ ሰጥተው፣ ዕምነት እና መንግሥትን ለይተው፣ የፊውዳሊዝም ሥርዓት አስጠባቂ ሥርዓታትን ከሕዝብ ድጋፍ አላቅቀው፣ እና ሕዝብን ከዐርባ ቀን እድል አምላኪነት አውጥተው የኢንዱስትሪ አብዮት ሲያሰፍኑ፣ ኢትዮጵያ በተራራዎቿ ተከብባ ይህን ዓለም አቀፍ ንቅናቄ አልሰማችም ነበር። በእንግሊዝ የተቀጣጠለው የኢንዱስትሪ አብዮት በመላው አውሮፓ ናኝቶ ወደ ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት በተሸጋገረበት የ19ኛው ክፍለ ዘመን ወቅት ኢትዮጵያ ስልጣንን በዘር ሃረግ፣ ስልጣንን በእምነት፣ ስልጣንን በጉልበት ለመነጣጠቅ በሚፋለሙ የሰፈር የጦር አለቆች የምትመራ ጦርነት ሰርክ የማይለያት አገር ነበረች። የአውሮፓ በቴክኖሎጂ የመገስገስ ዜና በኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት የተሰማው የኢትዮጵያን አንድነት ለማጽናት ይዋትቱ በነበሩት አጼ ቴዎድሮስ ዘመን ሲሆን የአውሮፓ ኢንዱስትሪ አብዮት ማዕበል እምብርት ከሆነችው እንግሊዝ የመከላከያ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር የተደረገው ጥረት በድፕሎማሲ ጥበብ ጉድለት ሲከሽፍ አጠቃላይ የርዕዩ መኮላሸት ምክንያት ግን በዋናነት በፖለቲካ ተቀናቃኝ ልሂቃን እና ሌሎች የሥርዓታት አካላት አስተባባሪነት የተነፈገ የአገር ውስጥ ድጋፍ ነው።

35. ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ ሥርዓተ መንግሥት አጽንተው እና የኢትዮጵያን አንድነት አስጠብቀው ከግጭት ፋታ ካገኙ በኋላ በአውሮፓ የተስፋፉት የቴክኖሎጂ ውጤቶች በፍጥነት ወደ አገር እንዲገቡ አድርገዋል። ነገር ግን፣ ከቴክኖሎጂ ውጤቶች ባሻገር ራሱ ቴክኖሎጂ ወደ አገር ተሸጋግሮ እና ሰርፆ ሽግግር ከመደረጉ በፊት የአገሪቷ ከባሕር በር መራቅ እና የንጉሱ ሕልፈት ምናልባት ሁለት መጥፎ የታሪክ መታጠፊያዎች ናቸው።

36. ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሕልፈት እስከ ሁለተኛው የጣሊያን ጦርነት ወቅት የነበረው ጊዜ በፖለቲካ ሽኩቻ የባከነ እና ኢትዮጵያንም በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ዋጋ ያስከፈለ ጊዜ ነው። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከጦርነቱ በኋላ በነበረ ቁጭት የተጀመረው የሰብዓዊ አቅም ግንባታ እና በእቅድ የተደገፈ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአሥራ አምሥት ዓመታት ጉዞ ሲለካ አጠቃላይ አቅጣጫው ተስፋ ሰጪ ነበር። የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ከመሬት ይልቅ የኢንዱስትሪ ቁሳዊ ካፒታል፣ ከፍ ሲልም ሰብዓዊ ካፒታል፣ እውቀት እና ቴክኖሎጂ ሆኖ ሳለ በአንድ በኩል ከምስለኔ እስከ እምነት ተቋም ያለ የሥርዓቱ አካል መሬትን እንደ ዋና የሥርዓት አቅም በመቁጠር ለለውጥ ዳተኛ ሆነ። በሌላ በኩል ኮምዩኒዝም በቁሳዊ ካፒታል ላይ በተመሠረተ የዳበረ ካፒታሊዝም እንደሚሰፍን የሚያትት የሶሻሊዝም አስተምህሮት የሚያነበንብ ወጣት ልሂቅ ሶሻሊዝምን በአነስተኛ ግብርና ላይ ሊመሠርት መሬት ወይም ሞት አለ። በዚህ መደማመጥ በጠፋበት ሥርዓት አልበኝነት ውስጥ ለዓመታት የተገነቡ ጥቂት የኢኮኖሚ አቅሞች ተወርሰው ለብዙሃን በመከፋፈላቸው ማሕበረሰብ አቅምን እና ሀብትን ሳይሆን ድህነትን እኩል ተከፋፈለ።

37. በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በብዙ ውጣ ውረድ ለመጀመሪያ ጊዜ ለከፍተኛ ትምህርት የበቃ ትውልድ በሰብዓዊ ካፒታል አቅም የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን የማረጋገጥ ተስፋ ተጥሎበት ነበር። ያ ትውልድ በሳይንሳዊ ዕውቀት ራሱን የማነጽ ግብን ትኩረት ነፍጎ በንቃተ ሕሊና ሰበብ ራሱ እንኳ በማይስማማበት እና በማይግባባበት ርዕየተ ዓለም አብዛኛውን ጊዜውን ማዋሉ በመጨረሻ አገር ከሚመሩ የተማሩ ልሂቃን ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚዘልቅ ሰብዓዊ ካፒታል ከፍ ሲልም ሰብዓዊነት እንደ ዋዛ ረገፈ። ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የተማሩ ወጣቶችም ጫካ ገብተው በ17 ዓመታት የርስ በርስ ጦርነት ራሳቸውን ከግጭት አዙሪት ተዋንያን የታሪክ ማሕደር ውስጥ አስመዘገቡ። የዚያ ዘመን አስከፊ የግጭት ማቀጣጠያ የኢኮኖሚ ጉዳይ ከነበረው እድሜ ጠገብ የመሬት ጥያቄ ይልቅ ከሶሻሊዝም ጋር ድንገት የገባው እና እስከ ዛሬም ማጥፋት ላቃተው የግጭት ሰደድ ምክንያት የሆነው የብሔር ጥያቄ ነው። ከዚህ ሁሉ ግጭት ወለድ መተላለቅ በኋላ ዛሬ ላይ መሬቱም፣ የሕዝቦች ቋንቋም በአለበት አለ። የሌለው አገር ተስፋ ያደረገችበት ርትዕ ሰብዓዊ ካፒታል እና ማሕበራዊ ካፒታል ሲሆን፣ የጠፋውም ከውጭ በጥሬው በተወሰደ ርዕዮት የታጀለ ሥርዓት ምክንያት ነው።

38. የዚያ ትውልድ ጦስ ባልኖረበት ዘመን ትርክት እየተነዳ በዚህ የ21ኛው ክፍለ ዘመን በዘር ተከፋፍሎ ለግጭት ውረድ እንውረድ የሚባባል ወጣት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። በሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በተጀመረ ጥረት በአንድ ክፍለ ዘመን ቅብብሎሽ ዛሬ ላይ የደረሰ የተማረ ወጣት ትውልድ ከአያቶቹ ያገኘውን ማሕበራዊ ካፒታል እንኳ ከበጣጠሰ እና የግጭት አዙሪትን ችግርን ሊከላበት በሚገባ ቴክኖሎጂ እያከረረ መበልጸግን የማይፈታ ሕልም ካደረገ የትኛው አቅም የኢትዮጵያን ብሎም የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብን ያሻግር? መማርስ ለምቼ?

39. ኢትዮጵያ የመጣችበት ረጅም መንገድ ሲጠቃለል የኢትዮጵያ የትናንት እና የዛሬ መጥፎ ኩነቶች የግጭት እና የድህነት አዙሪት ናቸው። በረጅም ዘመን ሂደት ይህ ትውልድ በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በሚረጋገጥ ልማት በራሱ ዘመን ከበለጸጉ አገራት እኩል የዓለም ዜጋ መሆን የሚችለው ሁለቱን አዙሪቶች በአንዴ የመስበርን እንቆቅልሽ ከፈታ ብቻ ነው። የመፍትሄው አንዱ አካል ከቴክኒካዊ የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ በላይ የሩቅ መዳረሻን የሚያሳይ የትውልድ ዕቅድ፣ ከዚህም በላይ የሥርዓታት ጉዳዮችን በታሳቢነት ከማለፍ ይልቅ ዕውቅና እና መፍትሄ ሰጥቶ አስቻይ መደላድል መፍጠር ነው። "ታላቅ ነበርን፤ ታላቅ እንሆናለን" ሲባል ይህ ገቢራዊ ይሆን ዘንድ ትውልዶችን ያንሸራተቱ ረጅም የኋላ የታሪክ እጥፋቶችን እና ረጅም የወደፊት መወጣጫ መሰላልን ማጤን ይጠይቃል።

40. ከሥርዓታት ፈርጆች መካከል የሁሉም የጋራ መገለጫ የሆነ የማሕበረሰብ ወግ፣ ልማድ፣ እና እሴትን የሚያጠቃልል የባሕል ጉዳይ አለ። በረጅም ሂደት የተሳካለት አገር በየደረጃው የተፈጥሮ ሀብትን መሠረት ካደረገ ካፒታል (natural capital) የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ወደሚሆን ቁሳዊ ካፒታል (physical capital)፣ ወደ ሰብዓዊ ካፒታል (social capital)፣ እና ማሕበራዊ ካፒታል (social capital) ይሸጋገራል። በኢትዮጵያ እነዚህ አቅሞች በግጭት አዙሪት ምክንያት ለአሻጋሪ ዕድገት መነሻነት በማይበቁበት ደረጃ ተመናምነዋል። እነዚህን አቅሞች በአቋራጭ ለመገንባት ተሞክሮው ያለ ቢሆንም በረጅም ዘመን በኢትዮጵያ ተንሰራፍተው ዛሬ ላይ የሚገኙት መሠረታዊ የሥርዓታት መገለጫዎች አንድም የተዛባ ትርክት ሁለትም ቴክኖሎጂን እና የሣይንሳዊ ዕውቀትን እንደ ችግር መፍቻ በቅጡ ያልተቀበለ ማሕበረሰብ በመሆናቸው ቀጥተኛ የሆኑትን የልማት አቅሞች ከመገንባት ያለፈ ማሕበረሰብን የማነጽ እና ሥርዓታትን ለለውጥ የማትጋት ጥረት ይጠይቃል። የማሕበራዊ ሣይንስ እንደሚያስተምረው በትናንት፣ በዛሬ፣ በቅርብ ነገ፣ እና ከሞት በኋላ ባለ ነገ በሚገለጽ የጊዜ ምድብ ውስጥ የመበልጸግ ተስፋ ያለው ተራማጅ ማሕበረሰብ ጊዜውን የሚያውለው በማይቆጣጠረው ትናንት እና ከሞት በኋላ ባለው ነገ ሳይሆን፣ ዛሬ ላይ ስለ ልጆቹ መልካም ነገ ሲል በሚቆጣጠረው የቅርቡ ነገ በትጋት በመሥራት ነው። ይህ ተራማጅ ማሕበረሰብ ችግር ሲገጥመው በሌላ በውጫዊ ኃይል ከማሳበብ ይልቅ የችግሩ መፍትሄ በራሱ እጅ እንደሆነ ያምናል፤ ይህን እምነት በተግባር ለመተርጎምም ሣይንሳዊ ዕውቀትን ከምር ይሻል። የዚህ ዓይነት ማሕበረሰብ ለመፍጠር ዕድለኛ መሪ ትውልድ ይጠይቃል።

41. ኢትዮጵያ ስልጣኔን በመምራት እና በመከተል መሃል ያለፈች አገር ስትሆን የዚህ መገለጫ ከሌሎች አገራት የተለየ አይደለም። የአክሱም እና የምሥራቅ ሮማ ሥርዎ መንግሥታት በስልጣኔ አቻ ነበሩ። የእነዚህ ሕዝቦች የዛሬ ልዩነት የአንድ ወቅት የመሪዎች እና የሕዝብ መናበብ ልዩነት የፈጠረው ጉዳይ ነው። የአውሮፓ ለውጥ መነሻ የእንግሊዝ መንግሥት እና የእንግሊዝ ሕዝብ መደማመጥ ነው። ከእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ የመጡ ግን የፈጠኑ ለውጦች ደግሞ በመማር እና በመለወጥ አቻ የመሆን ፍላጎት እና ቁጭት የወለዳቸው ለውጦች ናቸው። በቅርብ ዘመን የሚታወቁት በአንድ ትውልድ የአገራት በኢኮኖሚ የመስተካከል ሕልም መሳካት ምስጢር የድህነት ቁጭት የፈጠረው የመሪዎች እና የሕዝብ ስለ መለወጥ በምልዓት መግባባት መቻል ነው። ለዚህ አብነት የሚሆኑ የቅርብ እና የሩቅ ዘመን ተሞክሮዎች አሉ።

## 3.2. ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

### የአገራት የልማት ተሞክሮ

42. ከኋላ ገስግሰው በቴክኖሎጂ ከገፉ አገራት ጋር መወዳደር የቻሉ የቅርብ ዘመን አገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የካፒታል ጥራት፣ እና በምርት፣ በንግድ፣ እና በቴክኖሎጂ የሚገለጽ አሻጋሪ መዋቅራዊ ለውጥ የመመንጠቂያ መሠረቶች ናቸው። የቅርብ ዘመን የቻይና ኢኮኖሚ ከሦስት ዓሥርት ዓመታት በላይ ከ10 በመቶ በላይ በሆነ ምጣኔ ከኋላ ገስግሶ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነትን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል። ደቡብ ኮሪያ ከፍጹም ድህነት ለአብነት ወደሚጠቀስ ብልጽግና የተሸጋገረችው ለሦስት አሥርት ዓመት ባልቀዘቀዘ የ9 በመቶ እና በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ነው።

43. የደቡብ ኮሪያ እና የሌሎች ቀዳሚ አገራት የኢኮኖሚ ዕድገት በሰላም ጊዜ ብቻ የተገኘ አልነበረም። ታሪክ እንደሚባጀው የዘመናችን ስልጣኔዎች የጦርነት አዙሪት ቁጭት የወለዳቸው ናቸው። አሜሪካ ከእርስ በእርስ ጦርነት በኋላ በተፈጠረ ቁጭት የማይቀለበስ የዕድገት ግስጋሴን ለመቀናጠጥ የፈጀባት 20 ዓመታት ብቻ ነው።

የራሺያ ስልጣኔ የ1850ዎቹ የክሬሚያ ጦርነት ሽንፈት የፈጠረው ቁጭት ውጤት ነው። የአሁኗ ጀርመን የአውሮፓ የኢኮኖሚ ኃይል የመሆን ምንጭ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ሽንፈት የፈጠረው ቁጭት ነው። የደቡብ ኮሪያ አስደማሚ የኢኮኖሚ ዕድገት ግስጋሴ በቻይናዎች እና በጃፓኖች ቅኝ ግዛት ሥር የመማቀቅ፣ ኋላም በአሜሪካ እና ሶቭዬት ሕብረት ፉክክር በጦርነት የመላሸቅ ቁጭት ውጤት ነው። ጀርመኖች በሰላም ጊዜ በበርካታ አሥርት ዓመታት የገነቧቸውን ከተሞች በጦርነት ከወደሙ በኋላ መልሶ ብቻ ሳይሆን አሻሽሎ ለመገንባት የፈጀባቸው የመንፈቅ ዕድሜ ነው፡፡ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1948 እስከ 1951 በቆየው የአውሮፓ የመልሶ ግንባታ ፕሮግራም ወይም ማርሻል ፕላን ወቅት የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርታቸው በእቅድ ከተቀመጠው በላይ የ11 በመቶ እና 40 በመቶ ምጣኔ ያደገው በጦርነት መሃልና ማግስት ባሉ አራት ዓመታት ነው፡፡ በምዕራብ ጀርመን በጦርነት ማግስት የተከሰተ ከማገገም ያለፈ የ32 በመቶ የአጠቃላይ ዓመታዊ ኢኮኖሚ ዕድገት በቁጭት እንጂ በአዘቦት ጊዜ የትጋት መንፈስ ሊገኝ የሚችል አልነበረም፡፡ በሃያ አምሥት ዓመት በምግብ ራሷን ከቻለች ተዓምር ነው የተባለላት ደቡብ ኮሪያ በተመሳሳይ ጊዜ ድህነትን አሽቀንጥራ ጥላ ከናቋት ተርታ ያሰለፋት የዕድገት ፍኖት የተወጠነው በጦርነት መሃል እና ማግሥት ነው፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልል እንዲሁም የኢትዮጵያ ከግጭት እና የድህነት አዙሪቶች መውጫ አንዱ እና ዋናው መንገድ በየትኛውም ሁኔታ ማምረት መሆኑ ግልጽ ነው። መሣሪያውም በሳይንሳዊ መንገድ አቅዶ ምልዓተ-ሕዝቡን አነቃንቆ ወደ ሥራ መግባት ሲሆን ከዓለም አገራት ስኬት የሚወሰደው ትልቁ ትምህርት በራስ አውድ የሚፈጠር ለልማት የተሳለ ቁጭት ነው።

## የወቅቱ ዓለም አቀፋዊ ተስፋ እና ስጋቶች

44. በኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ፖሊሲ ማዕቀፍ ሥር የአማራ ክልል ሕዝብ በተለይ ተጠቃሚ ሊሆንባቸው ከሚያስችሉ ምክንያቶች መካከል

- በዕድገት ግስጋሴ ላይ ያሉ አገራት የመኖር መልካም አጋጣሚን የመጠቀም ፍላጎት
- የኢኮኖሚ ትብብር በተለይም የልማት ፋይናንስ፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ-ንዋይ፣ ንግድ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ እና የቱሪዝም ልማት ፍላጎቶች፣
- የአየር ንብረት ለውጥ
- የክልሉን ዲያስፖራ ለክልሉ መረጋጋት እና ልማት የመግራት እና የማነጽ ፍላጎት፣
- ጂኦፖለቲካ፤ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የውሃ ሀብት እና ስትራቴጂካዊ የጋራ ድንበሮች፣ ዓለም አቀፍ ግጭቶችን በጋራ የመመከት ፍላጎት መኖር ተጠቃሽ ናቸው።

45. ፈጣን ዓለም አቀፋዊ የቴክኖሎጂ ለውጥ፣ ለትብብር መሠረት የሚሆን ልዩ ግንኙነት (የኢትዮጵያ የአይበገሬነት እና የፓን አፍሪካ ፋናወጊነት የፈጠረው የፖለቲካ ካፒታል)፣ አብሮ ለማደግ ተመሳሳይ ፍላጎት እና ቁጭት ለመፍጠር ያለ አቅም፣ እና ሰፊ ገበያ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። በሌላ በኩል ያልተገቡ ፉክክሮች እና የሩቅ ጂኦፖለቲካ ፍላጎቶች መረማመጃ የሆነ ቀጠና፣ ለትልቅ ሕዝብ የሚገባን የባሕር በር የተጽዕኖ ማራመጃ የማድረግ ፍላጎት እና ትብብርን መግፋት፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ጎጂ ጽንፍ በሥጋትነት የሚወሰዱ ናቸው።

# ምዕራፍ አራት
# ክልል አቀፍ የልማት አፈጻጸም

## 4.1. የኢኮኖሚ ልማት አፈጻጸም

### የኢኮኖሚ ዕድገት

1. የክልሉ የረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም ከአገር አቀፍ፣ ከቀጠናው እና ከዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ እና አበረታች ነው። ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት የክልሉ ጥቅል ምርት (Gross Regional Product) በ6.9 በመቶ፣ ክልላዊ የነፍስ ወከፍ ምርት ደግሞ በ5 በመቶ አድጓል። በተመሳሳይ ወቅት የኢትዮጵያ አገራዊ የነፍስ ወከፍ ምርት (per capita GDP) በ6.3 በመቶ አድጓል። ዓለም አቀፍ መረጃ በተገኘበት ከ1998 እስከ 2015 ድረስ የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያደገበት የ6.4 በመቶ ምጣኔ በጊዜው ከዓለም 4ኛው፣ ከአፍሪካ ደግሞ 1ኛው ፈጣን የዕድገት ምጣኔ ነው። በተመሳሳይ ወቅት የአማራ ብሔራዊ ክልል የነፍስ ወከፍ ገቢ 5.1 በመቶ ያደገ ሲሆን በዚህ መሠረት የክልሉ የሁለት አሥርት ዓመታት የኢኮኖሚ አፈጻጸም በነፍስ ወከፍ ምርት ዕድገት ሲለካ ከኢትዮጵያ ውጭ ከዓለም 7ኛው ከአፍሪካ ደግሞ 1ኛው ፈጣን ዕድገት ነው።

2. በሁለት አሥርት ዓመታት የተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ኢትዮጵያ ከሃያ ዓመታት በፊት በአገራዊ ምርት መጠን ይበልጧት የነበሩ አሥራ ሁለት አገራትን በመቅደም ከግብጽ፣ ከናይጄሪያ፣ ከደቡብ አፍሪካ እና ከአልጄሪያ ቀጥላ ከአፍሪካ የአምሥተኛዋ ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት መሆን ችላለች።

3. ስዕል 4-1፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መጠን ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ያለው ንጽጽር




ምንጭ፤ የዓለም ባንክ መረጃን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ

4. በስዕል 4.2 ማስተዋል እንደሚቻለው፣ በሁለት አሥርት ዓመታት በተተገበሩት ሦስት የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች[1] ወቅት በዕቅዶቹ የመጀመሪያ ሁለት እና ሦስት ዓመታት ፈጣን ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም በየዕቅዶቹ የመጨረሻ አንድ እና ሁለት ዓመታት የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ይታያል። ለዚህም አንዱ ምክንያት የልማት ዕቅዶቹ ዑዴት ከምርጫ ወቅቶች (election cycle) ጋር የተቆራኘ በመሆኑ የመንግሥት ትኩረት ከኢኮኖሚ ይልቅ ወደ ፖለቲካ ጉዳዮች ስለሚያዘነብል እንደሚሆን ይገመታል።

5. ስዕል 4.2፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የነፍስ ወከፍ ምርት፤ 1998 - 2015

---

[1] ከ1998 እስከ 2002 የተተገበረው የልማት ዕቅድ የተፋጠነ እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ ድህነትን ለማጥፋት (Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty – PASDEP) ሲሆን፣ ከ2003 እስከ 2012 የተተገበሩት የመጀመሪያው እና ሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች (Growth and Transformation Plan - GTP I and GTP II) ናቸው።

**ሀ.** ክልላዊ የነፍስ ወከፍ ምርት (per capita gross regional product)




**ለ.** የአጭር ጊዜ የኢኮኖሚ ዑዴት (cycle)




**ሐ.** የረጅም ጊዜ ፍኖት (trend)




*ምንጭ፤ የአብክመ ፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃን መሠረት በማድረቅ የተቀመረ*

6. ይህ በንጽጽር ከፍተኛ ሊባል የሚችል የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ለዕድገት መነሳሳት ተስፋ ሰጪ የመሆኑን ያህል በአንድ ትውልድ ሊደረስበት ከሚገባው ትልቅ ግብ አንጻር ጥራት እና አሻጋሪነቱ ምርመራ እና ትንተና የሚያስፈልገው ነው። የ5 በመቶ የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ከድህነት ወለል በታች ያለን ሕዝብ ምጣኔ በ1 መቶኛ ነጥብ ለመቀነስ ያስፈልጋል ተብሎ ከሚገመተው የ7 በመቶ የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ምጣኔ ያነሰ ሲሆን በተለይም በአማራ ብሔራዊ ክልል በ2008 የተመዘገበውን የ26.1 በመቶ የድህነት ምጣኔ ትርጉም ባለው ደረጃ ለመናድ ከሚያስፈልገው ምጣኔ አንጻር ዝቅተኛ ነው። በኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ተስተካካይነትን ለሚያልም አገር እና ክልል ዘላቂ የኢኮኖሚ ሽግግር ማሳካት በቻሉ እንደ ደቡብ ኮሪያ እና በፈጣን መዋቅራዊ ሽግግር ላይ በሚገኙ እንደ ቻይና ካሉ አገራት የሦስት አሥርት ዓመታት ፈጣን የዕድገት ምጣኔ አንጻር የክልሉ የዕድገት ምጣኔ አዝጋሚ ሊባል የሚችል ነው፤ በደቡብ ኮሪያ እና በቻይና ለሦስት አሥርት ዓመታት የተመዘገበው የነፍስ ወከፍ ምርት ዕድገት እንደ ቅድም- ተከተላቸው 7.7 በመቶ እና 9.0 በመቶ ነበር።

7. ከድህነት ምጣኔው ከፍተኛ መሆን ባሻገር በክልሉ ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት ከፍተኛ ነው። በ2008 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት (ኢፌዲሪ) የፕላን እና ልማት ኮሚሽን መረጃ መሠረት ከክልሉ ሕዝብ 26.1 በመቶ ወይም 5.4 ሚሊዮን ሕዝብ ከብሔራዊ የድህነት ወለል በታች ይኖር የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላ በነበሩ የትግበራ ዓመታት የተከሰቱት ተግዳሮቶች ይህ ምጣኔ ትርጉም ባለው ደረጃ ሊሻሻል እንደሚችል መጠበቅ አያስችሉም።

8. ሠንጠረዥ 4-1፤ ከብሔራዊ ድህነት ወለል በታች የሚገኝ ሕዝብ ምጣኔ በመቶኛ (Poverty head-count indices)

| | | ኢትዮጵያ | አማራ ክልል |
|---|---|---|---|
| 1992 | **አጠቃላይ** | **44.2** | **41.8** |
| | ከተማ | 36.9 | 31.1 |
| | ገጠር | 45.4 | 42.9 |
| 1997 | **አጠቃላይ** | **38.7** | **40.1** |
| | ከተማ | 35.1 | 37.8 |
| | ገጠር | 39.3 | 40.4 |
| 2003 | **አጠቃላይ** | **29.6** | **30.5** |
| | ከተማ | 25.7 | 29.2 |
| | ገጠር | 30.4 | 30.7 |
| 2008 | **አጠቃላይ** | **23.5** | **26.1** |
| | ከተማ | 14.8 | 11.6 |
| | ገጠር | 25.6 | 28.8 |

ምንጭ፤ ብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን፣ መስከርም 2009

9. የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት እንደ ግቡ ሁኔታ አንጻራዊ ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልል የነፍስ ወከፍ ምርት በ5 በመቶ ባደገበት የአሥራ ዘጠኝ ዓመታት ጊዜ የቀሪው ኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ አገራዊ ምርት በ6.7 በመቶ አድጓል። ይህ የ1.6 መቶኛ ነጥብ የዕድገት ምጣኔ ልዩነት በአብዛኛው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፈጣን እድገት የፈጠረው ልዩነት እንደሆነ ሲገመት፣ በረጅም ዘመን አፈጻጸም የነፍስ ወከፍ ምርት ላይ ልዩነት ፈጥሯል። በዚህም መሠረት በ1998 የአማራ ብሔራዊ ክልል የነፍስ ወከፍ ምርት ከቀሪው ኢትዮጵያ አማካይ የነፍስ ወከፍ ምርት በ27 በመቶ ብቻ ያንስ የነበረ ሲሆን፣ በ2016 ይህ ልዩነት ወደ 65 በመቶ ሰፍቷል። የዚህ ዓይነት እየሰፋ የሚሄድ የገቢ ልዩነት የክልሎች ተመጣጠነ ልማት ግብን የሚቃረን ቢሆንም መፍትሄው የክልሉን ልማት በጥረት ማፋጠን ነው።

10. ስዕል 4.3፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የነፍስ ወከፍ ምርት እና የቀሪው ኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ምርት ንጽፅር




ምንጭ፤ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር እና አማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃዎችን በመጠቀም የተቀናበረ

11. ከዕድገት ምጣኔው ፍጥነት ባሻገር ቀጣይነቱን በተመለከተ በአጠቃላይ በረጅም ዘመን የኢኮኖሚ አፈጻጸም ረገድ ከ1998 በኋላ በነበሩት አምሥት ዓመታት እና በ2003 ወደ ትግበራ በተሸጋገረው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት አበረታች እና የመቻል ተስፋን ያጎናጸፈ የኢኮኖሚ አፈጻጸም በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የተመዘገበ ሲሆን፣ በመጨረሻዎቹ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዓመታት የልማት ግስጋሴው በተለያዩ ምክንያቶች ተቀዛቅዟል። የዚህ እና የሌሎች መልካም ያለሆኑ አፈጻጸም ምልክቶች የፈጠሩት ጫና ለ2010 ለውጥ እና ኢኮኖሚያዊ ሪፎርም ምክንያት ሆነዋል። በተለይም የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በ2013 ወደ ትግበራ የገባ ሲሆን፣ ለዚህ ዕቅድ መሳካት ፈር-ቀዳጅ የሆነው አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተነድፎ ወደ ተግባር ተሸጋግሯል። የኢኮኖሚ ማሻሻያው እና የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ የአጭር ጊዜ የጥቅል ኢኮኖሚ መዛባቶችን ከማስተካከል ባሻገር መዋቅራዊ ችግሮችን

በመፍታት ምርታማነት እና ቅልጥፍናን በማሳደግ ጥራት ያለው እና አሻጋሪ እውቀት- መር ኢኮኖሚ መገንባት ነው፡፡

## የአጭር ጊዜ የጥቅል ኢኮኖሚ፤ ክልላዊ ምርት፣ የዋጋ ንረት እና ሥራ አጥነት

12. ከድህረ-ሪፎርም ወቅታዊ ወይም የአጭር ዘመን የጥቅል ኢኮኖሚ አፈጻጸም አኳያ የክልሉ የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ትግበራ በተጀመረበት ወቅት እና ማግስት በክልሉ የተከሰቱ የጸጥታ ችግሮችን በመቋቋም ከተግዳሮቶቹ ክብደት አንጻር ቀላል የማይባሉ የልማት እንቅስቃሴዎች ተከናውነው ውጤት ተመዝግቦባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የክልሉ ኢኮኖሚ ከ2013 እስከ 2016 በነበሩት አራት ዓመታት በአማካይ የ5.1 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው ንዑስ ክፍለ-ኢኮኖሚ ተጨማሪ ዕሴት በተመሳሳይ ወቅት የ16.1 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህ የዕድገት ምጣኔም በመጀመሪያዎቹ አምሥት የልማት አቅድ ዓመታት በዕቅድ ከተያዘው የ19.8 በመቶ የንዑስ ዘርፉ ተጫማሪ ዕሴት የዕድገት ምጣኔ ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአገልግሎት ዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በተመሳሳይ የትግበራ ወቅት በዓመት በአማካይ በ7.5 በመቶ አድጓል፡፡ በ2016 ከክልሉ ኢኮኖሚ 51.9 በመቶ ድርሻ ያለው የግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ ተጨማሪ ዕሴት አፈጻጸሙ ከዕቅድ በታች ቢሆንም ከ2013-2016 በነበሩት ዓመታት የተመዘገበው የ3.4 በመቶ ዕድገት የክልሉ ሕዝብ ቁጥር ያድግበታል ተብሎ ከሚገመተው የ1.5 በመቶ ምጣኔ በላይ መሆኑ የምግብ እጥረት፣ የኑሮ ውድነት እና የከፋ ድህነት እንዳይባባስ የማድረግ አቅም እንደነበረው ማስተዋል ይቻላል፡፡

13. የክልሉ የጥቅል ኢኮኖሚ አፈጻጸም ክልሉ በበርካታ ተግዳሮቶች ከመፈተኑ አንጻር አዎንታዊ ግምገማ ሊሰጠው ቢችልም ሥር የሰደዱ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል ደረጃ ኢኮኖሚው እንዲያድግ ከተቀመጠለት ግብ አንጻር የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔው ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህም በላይ፣ ይህ ያለፉት አራት ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ከቀዳሚዎቹ ዓመታት አፈጻጸም ያነሰ ነው፡፡ በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግሮች እና በቅርቡም በተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት በድህረ ሪፎርም ወቅት መፈታት የነበረባቸው እና ያለባቸው ዋና ዋና የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ ችግሮች ገና አልተቀረፉም፡፡ ከነዚህም መካከል የክልሉ የረጅም ጊዜ ችግር ከሆነው መዋቅራዊ ድህነት እና ይህን ድህነት ለመናድ ተስፋ ከተጣለበት የክልሉ ኢኮኖሚ አዝጋሚነት ባሻገር ከፍተኛ የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት፣ እንዲሁም ከፍተኛ የሥራ አጥነት ምጣኔ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ የአጭር እና መካከለኛ ጊዜ ችግሮች ሆነዋል፡፡

14. በአገር አቀፍ ደረጃ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ምጣኔ በአማራ ክልልም ከፍተኛ ጫና አሳድሯል፡፡ በ2013 የበጀት ዓመት የክልሉ አጠቃላይ የዋጋ ንረት 15.4 የነበረ ሲሆን ከ2014 ጀምሮ እስከ 32.8 በመቶ ድረስ አሻቅቧል፡፡ በቀዳሚዎቹ ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልል የዋጋ ንረት ምጣኔ ከአገር አቀፍ ምጣኔ አይበልጥም ነበር፡፡ ነገር ግን በ2015 የክልሉ የዋጋ ንረት ምጣኔ ከአገር አቀፉ ምጣኔ በትንሹም ቢሆን በልጦ ታይቷል፡፡ በ2016 የበጀት ዓመት የዋጋ ንረት በአገር አቀፍም ሆነ በክልሉ የቀነሰ ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልል የተመዘገበው ምጣኔ ከአገር አቀፉ ምጣኔ በሰፋ ልዩነት ይበልጣል፡፡

15. ሠንጠረዥ 4.2 ፤ ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ንረት ምጣኔ፤ የአማራ ክልል እና የብሔራዊ አኀዞች ንጽጽር

| | አማራ ብሔራዊ ክልል | | | ኢትዮጵያ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **አጠቃላይ** | ምግብ ነክ | ምግብ ነክ ያልሆኑ | **አጠቃላይ** | ምግብ ነክ | ምግብ ነክ ያልሆኑ |
| 2012 | **19.9** | 23.7 | 15.7 | **19.9** | 23.3 | 15.8 |
| 2013 | **15.4** | 18.9 | 11.3 | **20.2** | 23.1 | 16.4 |
| 2014 | **32.8** | 35.8 | 29.0 | **33.7** | 40.2 | 25.1 |
| 2015 | **33.2** | 32.3 | 34.4 | **32.6** | 31.8 | 33.8 |
| 2016 | **23.9** | 28.6 | 18.0 | **19.9** | 22.7 | 15.9 |
| | **Headline inflation** | Food inflation | Non-food inflation | **Headline inflation** | Food inflation | Non-food inflation |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃን በመጠቀም የተቀናበረ
*እስከ ሚያዝያ ወር ድረስ ባሉት አሥር ወራት የተመዘገበ

16. **በክልሉ የሚገኘው ሥራ ፈላጊ ዜጋ በ2005 እና በ2013 በነበሩት ስምንት ዓመታት ከእጥፍ በላይ ጨምሯል።** በ2013 የዳሰሳ ጥናት መሠረት 891,911 በክልሉ የሚኖሩ ለሥራ የደረሱ ዜጎች ሥራ ፈላጊ ነበሩ። ይህ የሥራ አጥ ቁጥር ከአገሪቱ አጠቃላይ ሥራ አጥ ቁጥር 24.7 በመቶ ይሆናል። በክልሉ ከሚኖረው ሥራ አጥ ውስጥ 58.6 በመቶ የሚሆነው ኃይል ዕድሚያቸው ከ15 እስከ 29 የሆኑ ወጣቶችን የያዘ ነው። ዕድሚያቸው ከ15 እስከ 29 ዓመት የሆኑ ወጣቶች የሥራ አጥነት ምጣኔ በ2013 በክልሉ 23.6 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህ አኀዝ ከአገር አቀፉ 17.9 በመቶ የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ በላይ ነው። የዚህ ዓይነት ልዩነት በማሕበረሰቡ በተለይም በወጣቱ ላይ የመገለል ስሜት ከፈጠረ ሌላ ዙር ማሕበራዊ ቀውስ ሊጭር ይችላል።

17. **በአገር አቀፍ ደረጃ እንደሚስተዋለው ሁሉ የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ በክልሉ ከፍተኛ ሲሆን በቅርብ ዓመታት የክልሉ የወጣት ሥራ አጥ ምጣኔ ከአገር አቀፍ የሥራ አጥ ምጣኔ በልጧል። የክልሉ አጠቃላይ የሥራ አጥ ምጣኔ** በ2013 የጥናት ዓመት 7.5 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህ አኃዝ ከአገር አቀፉ የ8.0 በመቶ ምጣኔ በመጠኑ ያነሰ ነበር። የክልሉ የከተማ ሥራ አጥነት ምጣኔ 2005 ከነበረበት 13.9 በመቶ በ2013 ከአገር አቀፉ የሥራ አጥነት ምጣኔ እኩል ወደ 17.9 በመቶ አሻቅቧል። በተለይም ዕድሚያቸው ከ15 እስከ 29 ዓመት የሆኑ ወጣቶች የሥራ አጥነት ምጣኔ በ2013 በክልሉ 23.6 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህ አኀዝ ከአገር አቀፉ 17.9 በመቶ የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ በላይ ነው።

18. ሠንጠረዥ 4-3 ፤ የሥራ አጥነት ምጣኔ፤ የክልሉ እና አገር አቀፍ አኀዞች ንጽጽር
    ሀ. ከአሥር ዓመት ዕድሜ በላይ

| | | | **አማራ ክልል** | **ኢትዮጵያ** |
|---|---|---|---|---|
| 2005 | **አጠቃላይ** | **ድምር** | **3.4** | **4.5** |
| | | ወንድ | 2.0 | 2.7 |
| | | ሴት | 4.9 | 6.5 |
| | ከተማ | **ድምር** | **13.9** | **16.5** |
| | | ወንድ | 9.4 | 10.5 |
| | | ሴት | 18.2 | 23.0 |
| | ገጠር | **ድምር** | **1.6** | **2.0** |
| | | ወንድ | 0.9 | 1.1 |
| | | ሴት | 2.5 | 2.9 |
| 2013 | **አጠቃላይ** | **ድምር** | **7.5** | **8.0** |
| | | ወንድ | **4.7** | **5.0** |
| | | ሴት | **11.0** | **11.7** |
| | ከተማ | **ድምር** | 17.9 | 17.9 |
| | | ወንድ | 11.3 | 11.2 |
| | | ሴት | 24.9 | 25.4 |
| | ገጠር | **ድምር** | 4.9 | 5.2 |
| | | ወንድ | 3.3 | 3.4 |
| | | ሴት | 7.0 | 7.6 |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 የሠራተኛ እና የፍልሰት ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት (Statistical report on the 2021 labour force and migration survey)፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የ2005 የሠራተኛ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት (Statistical report on the 2013 national labour force survey)

ለ. ከ15-29 ዕድሜ ክልል

| | | | አማራ ክልል | ኢትዮጵያ |
|---|---|---|---|---|
| 2005 | **አጠቃላይ** | **ድምር** | **5.5** | **6.8** |
| | | ወንድ | 3.7 | 4.6 |
| | | ሴት | 7.4 | 9.1 |
| | ከተማ | **ድምር** | **19.5** | **21.6** |
| | | ወንድ | 14.6 | 16.1 |
| | | ሴት | 23.4 | 26.4 |
| | ገጠር | **ድምር** | **2.6** | **3.1** |
| | | ወንድ | 1.7 | 1.9 |
| | | ሴት | 3.6 | 4.3 |
| 2013 | **አጠቃላይ** | **ድምር** | **11.7** | **8.0** |
| | | ወንድ | **7.9** | **5.0** |
| | | ሴት | **16.0** | **11.7** |
| | ከተማ | **ድምር** | **23.6** | **17.9** |
| | | ወንድ | 16.3 | 11.2 |
| | | ሴት | 29.0 | 25.4 |
| | ገጠር | **ድምር** | **8.0** | **5.2** |
| | | ወንድ | 5.9 | 3.4 |
| | | ሴት | 10.6 | 7.6 |

ምንጭ፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 የሠራተኛ እና የፍልሰት ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት (Statistical report on the 2021 labour force and migration survey)፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የ2005 የሠራተኛ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት (Statistical report on the 2013 national labour force survey)

19. **በ2013 በክልሉ ከሚገኙት ሥራ ፈላጊዎች መካከል የትምህርት ዝግጁነት የሌላቸው፣ ኢ-መደበኛ ትምህርት የተከታተሉ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ የነበራቸው ዜጎች ከአጠቃላይ ሥራ ፈላጊ የክልሉ ዜጎች 71.5 በመቶ ነበሩ።** በጥናት ዘመኑ 297,694 ያህሉ ምንም ዓይነት የትምህርት ዝግጅት ያልነበራቸው፣318,432 ያህሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ የነበራቸው፣ 136,620 የሚሆኑት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳተፎ የነበራቸው ሲሆን 117,597 የሚሆኑት ደግሞ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በላይ ተሳተፎ የነበራቸው ናቸው።

## የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫዎች

20. በኢኮኖሚው ውስጥ የግብርና ዘርፍ በተጨማሪ ዕሴት፣ በሠራተኛ ኃይል ስምሪት፣ እና በወጪ ንግድ ባለው አስተዋጽዖ የኢኮኖሚ ዋልታ ተደርጎ መወሰዱ ትክክል ቢሆንም ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አንጻር የድሃ አገር ኢኮኖከሚ መገለጫ ነው። የአገራት የነፍስ ወከፍ ገቢ እና በኢኮኖሚያቸው ውስጥ የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ቁርኝት እንደሚያሳየው ከፍተኛ የግብርና ድርሻ ያላቸው አገራት በነፍስ ወከፍ ገቢ ዝቅተኛ የሆኑ አገራት ናቸው። በዚህ ረገድ ከኢትዮጵያ የበለጠ የግብርና እሴት ድርሻ ያላቸው አገራት ሲራሊዮን እና ኒዠር ሲሆኑ እነዚህ አገራት በነፍስ ወከፍ ገቢም ከዓለም ዝቅተኛ ከሚባሉት አገራት መካከል ናቸው።

21. ስዕል 4.4፤ ነፍስ ወከፍ ገቢ እና የግብርና ተጨማሪ እሴት ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ ቁርኝት




ምንጭ፤ የዓለም ባንክ መረጃን በመጠቀም የተዘጋጀ

22. **በክልሉ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተስተዋለው የተጨማሪ ዕሴት ዕድገት ተስፋ ሰጪ ቢሆንም በአለፉት የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች የትግበራ ዓመታት አጠቃላይ የመዋቅራዊ ሽግግር አዝጋሚነት ተስተውሏል።** በ2016 የግብርና ዘርፍ ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ 51.9 በመቶ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ የዚህ ዓይነት የኢኮኖሚ መዋቅር የተስተዋለው ከ20 ዓመታት በፊት በ1990ዎቹ አጋማሽ ነው። በመዋቅራዊ ጉዳዮች አፈጻጸም ረገድ ከክልሉ ኢኮኖሚ የግብርና ድርሻ እየቀነሰ ቢመጣም የመዋቅራዊ ሽግግር የሚያመላክት የመዋቅር ለውጥ ጎልቶ አልታየም። የግብርናው ዘርፍ የክልሉን የእድገት ፍጥነት ሲመራ የነበረ ሲሆን የዘርፉ ተጨማሪ እሴት ዕድገት መቀዛቀዝ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ዕድገት ምጣኔ መቀነስ አስተዋጽዖ አድርጓል። በአለፉት ጥቂት ዓመታት በአምራች ኢንዱስትሪው የታየው ፈጣን ዕድገት የቅርብ ጊዜ ክስተት በመሆኑ ለመዋቅራዊ ሽግግር የሚኖረው ፋይዳ ወደፊት በሚኖረው አቅጣጫ ይወሰናል።

23. ስዕል 4.5፤ የዘርፎች ተጨማሪ እሴት ምዝን ዕድገት በመቶኛ ነጥብ (የአምሥት ዓመታት ተንከባላይ አማካይ ውጤት)




ምንጭ፤ የአብክመ የፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃን መሠረት በማድረግ የተቀናበረ

24. **ለበርካታ ዓመታት የኢኮኖሚውን የዕድገት ፍጥነት ሲመራ የነበረው የአዘርዕት ንዑስ ዘርፍ ለክልላዊ ጥቅል ምርት ዕድገት የነበረው አስተዋጽዖ በፍጥነት የመቀነሱን ያህል የኢኮኖሚውን ዕድገት የመምራት ብቃት ያለው ሌላ ንዑስ ዘርፍ ባለመፈጠሩ ኢኮኖሚው የአዝዕርት ምርት ዕድገት በተቀዛቀዘበት ልክ ዕድገቱ በዝቅተኛ ምጣኔ ተገድቧል።** ይህ ዋና የመዋቅራዊ ሽግግር ስኬት ጥያቄ ነው፤ በግብርና ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ በግብርና የዕድገት ፍጥነት ልክ ከተወሰነ ዓመታት በላይ  መዝለቅ ስለማይችል የዕድገት ምንጫቸው እና ግለታቸው የማይቀዘቅዝ እንደ አምራች ኢንዱስትሪ ዓይነት ዘርፎች የኢኮኖሚውን ዕድገት ሊረከቡ ግድ ይሆናል። በዚህ ረገድ ከ2010 የበጀት ዓመት ጀምሮ በአማራች ኢንዱስትሪው የታየው መነቃቃት በአዝዕት ምርት ዕድገት መቀዛቀዝ የተፈጠረውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት መቀዛቀዝ ባያካክስም የዕድገት አቅጣጫው ከተጠናከረ በአጭር ጊዜ ኢኮኖሚውን በተሻለ ፍጥነት ለመምራት ያለው አቅም ተስፋ ሰጪ ነው። የዚህ ዘርፍ መጠናከርም በዓለም የአዝዕርት ምርታማነት አንጻር ዝቅተኛ እና የማደግ አቅም ያለው የግብርና ዘርፍ ሌላ ዙር የዕድገት ምንጭ እንዲሆን ምክንያት ይፈጥራል።

25. ስዕል 4.6፤ የንዑስ ዘርፎች ተጨማሪ እሴት ምዝን ዕድገት በመቶኛ ነጥብ (የአምሥት ዓመታት ተንከባላይ አማካይ ውጤት)




ምንጭ፤ የአብክመ የፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃን መሠረት በማድረግ የተቀናበረ

26. **ከሠራተኛ ኃይል ስምሪት ጋር በተያያዘ በዋናነት ከግብርናው ዘርፍ የሚወጣው ኃይል እና ተጨማሪ የሰው ኃይል ከአምራች ኢንዱስትሪ እና ዘመናዊ አገልግሎት ዘርፎች ይልቅ ዘላቂ ወዳልሆኑ ዘርፎች መግባቱ ሌላው የመዋቅራዊ ሽግግር አቅጣጫ እንደገና መቃኘት እንዳለበት ምልክት የሚሰጥ ክስተት ነው።** በ1997 እና በ2013 መካከል ባሉት አሥራ ስድስት ዓመታት በግብርና ዘርፍ የተሰማራው የሰው ኃይል ከአጠቃላይ የሰው ኃይል ያለው ድርሻ ከ86 በመቶ ወደ 66.4 በመቶ ወይም በ20 የመቶኛ ነጥብ የቀነሰ ቢሆንም በተመሳሳይ ጊዜ የአምራች ዘርፍ የሰው ኃይል ድርሻ ከ4.9 ወደ 3.3 በመቶ ቀንሷል። ከአምራች ዘርፎች በተለይም ከግብርና ዘርፍ ከወጣው ሠራተኛ ኃይል አብዛኛው ከዘመናዊ አገልግሎት ዘርፍ ይልቅ ለራስ ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ በሚውሉ ምናልባትም ይፋዊ ባልሆኑ የቅጥር ሥራ አገልግሎቶች ነው።

27. ሠንጠረዥ 4-6፤ የሠራተኛ ኃይል ስምሪት አቅጣጫ

| | የዘርፎች ድርሻ | | ዕድገት በ2005 እና 2013 (%) | የዘርፎች ድርሻ ለውጥ (በ2005 እና በ2013 መካከል) |
|---|---|---|---|---|
| | 2005 | 2013 | | |
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 77.9 | 66.4 | -15.6 | -11.5 |
| ማዕድን እና ኳሪንግ | 0.1 | 0.3 | 135.9 | 0.2 |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 4.8 | 3.3 | -32.8 | -1.6 |
| ኤሌክትሪክሲቲ፣ ጋዝ እና ውሃ | 0.6 | 1.0 | 61.8 | 0.4 |
| ኮንስትራክሽን | 1.8 | 1.9 | 4.3 | 0.1 |
| ጅምላ፣ ችርቻሮ እና ተዛማጅ ሥራዎች | 3.3 | 5.4 | 63.5 | 2.1 |
| ትራንስፖርት እና የክዘና ሥራዎች | 0.4 | 1.1 | 202.9 | 0.8 |
| የመስተንግዶ እና የምግብ አገልግሎቶች | 0.8 | 1.6 | 100.9 | 0.8 |
| ኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን | 0.1 | 0.2 | 200.1 | 0.2 |
| የፋይናንስ ማሳለጥ አገልግሎት | 0.2 | 0.5 | 153.7 | 0.3 |
| ሪል እስቴት | 0.0 | 0.0 | 856.0 | 0.0 |
| የሳይንሳዊ እና ቴክኒካዊ የሙያ አገልግሎቶች | 0.2 | 0.3 | 29.4 | 0.1 |
| የሕዝብ አስተዳደር እና ፀጥታ አገልግሎት | 0.7 | 1.3 | 75.8 | 0.6 |
| ትምህርት | 1.4 | 2.6 | 88.2 | 1.2 |
| የጤና እና የማሕበራዊ አገልግሎት | 0.3 | 0.7 | 170.8 | 0.5 |
| የቤተሰብ ቅጥር እና የራስ ፍጆታ አገልግሎቶች | 6.6 | 9.9 | 48.1 | 3.3 |
| የጥበብ ሥራዎች እና ሌሎች አገልግሎቶች | 0.9 | 3.5 | 307.4 | 2.7 |
| **ጠቅላላ ሠራተኛ** | **11,174,123** | **11,076,384** | **-0.9** | |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል ዳሰሳ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

28. **የክልሉ የከትመት ምጣኔ ግስጋሴ የዘላቂ ከተማ ልማት ፍጥነትን እንደገና ለመቃኘት የሚያስገድድ ነው።** በተለያዩ ሳቢ እና ገፊ ምክንያቶች ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት እና የገጠር ቀበሌዎች ወደ ከተማነት ደረጃ ማደግ ምክንያት የክልሉ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ምጣኔ በ1991 ከነበረበት በ2013 19.6 በመቶ ደርሷል። የከትመት ምጣኔ ዕድገቱ ፍጥነት መጨመር ከከትመት መስፋፋት አይቀሬነት ጋር ተዳምሮ እንደ መሬት ያለ ሀብት እና ግብርናን የመሰለ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ መሠረቱን ጥሎ ከተማ ለሚገባ ሕዝብ የተለየ ዝግጁነት ይጠይቃል። ከ1991 ጀምሮ በነበሩት ያለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት የከትመት ምጣኔ እና የከተማ ሕዝብ የመጨመሩን ያህል ሰፊ እና ዘላቂ የሥራ ዕድል በመፍጠር የተሳካ መዋቅራዊ ሽግግር ሊያረጋግጥ ወደሚችለው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አልተሰማራም።

29. ሠንጠረዥ 4 -7፤ የከትመት ምጣኔ

| | በከተማ የሚኖረው ሕዝብ ምጣኔ በመቶኛ | የምጣኔ ለውጥ በመቶኛ ነጥብ (percentage points) | የዘርፎች የሠራተኛ ኃይል ድርሻ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ግብርና | አምራች ኢንዱስትሪ | ለራስ ፍጆታ የቤተሰብ ቅጥር ሥራ አገልግሎት |
| 1991 | 8.3 | | 85 | 4.7 | 0.5 |
| 1997 | 9.9 | 1.6 | 86 | 4.9 | 0.6 |
| 2005 | 14.4 | 4.5 | 77.9 | 4.8 | 6.6 |
| 2013 | 19.6 | 5.2 | 66.4 | 3.3 | 9.9 |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃን በመጠቀም የተሰላ

## 4.2. ትምሕርት

30. ከትምሕርት ሽፋን አኳያ ከ1988 ጀምሮ በነበሩት ከሁለት አሥርት በላይ ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልል አፈጻጸም ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል። በትምህርት ሚኒስቴር መረጃ መሠረት የክልሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ጥቅል ተሳትፎ በ2004 ከነበረበት 15.5 በ2015 ወደ 55 በመቶ አድጓል። ይህ ምጣኔ ከ50 በመቶ የአገር አቀፍ ምጣኔ የሚልቅ ሲሆን የክልሉ የአፈጻጸም ብልጫ በአብዛኛው ከአፀደ ሕጻናት ፕሮግራም ይልቅ በየአቻ ለአቻ እና ማሕበረሰብ አቀፍ ትምህርት ፕሮግራሞች የተገኘ ነው። በአንጻሩ የክልሉ መዋዕለ ሕጻናት የትምሕርት ሽፋን በ2015 የትምሕርት ዘመን 7.5 በመቶ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ምጣኔ ከአገር አቀፉ የ21.5 በመቶ ምጣኔ በጣም ያነሰ ነው። ይህ አፈጻጸም በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ፕሮግራም አማካይነት የሚደረጉ የሕጻናት ዕድገት ቀረጻዎች ላይ የበለጠ ትኩረት መደረግ እንዳለበት የሚያመላክት ነው።

31. ሠንጠረዥ 4-8፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት እና አጸደ ሕጻናት ጥቅል ተሳትፎ

| | ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት | | አፀደ ሕጻናት | |
|---|---|---|---|---|
| የትምሕርት ዓመት | አማራ ብ. ክልል | አገር አቀፍ | አማራ ብ. ክልል | አገር አቀፍ |
| 2004 | 15.5 (11.8) | 21.6 | 2.4 (2.2) | 5.3 |
| 2009 | 45.1 (37.0) | 45.9 | 2.9 (2.8) | 7.7 |
| 2010 | 46.6 (40.8) | 44.2 | 3.2 (3.1) | 8.6 |
| 2011 | 43.4 (38.4) | 40.7 | 3.7 (3.4) | 11.7 |
| 2012 | 41.9 (33.3) | 45.4 | 4.3 (3.8) | 10.4 |
| 2013 | 42.1 (32.5) | 36.7 | 4.2 (3.7) | 7.8 |
| 2014 | 45.8 (32.8) | 44 | 5.7 (4.8) | 11.1 |
| 2015 | 55 (38.3) | 50 | 7.5 (6.1) | 21.4 |
| 2016 | 55.5 | 57.8 | | |

ምንጭ፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምሕርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የትምሕርት ስታትስቲክስ መጽሔት እና የአብክመ ትምሕርት ቢሮ
**ማስታዎሻ፤** በቅንፍ ውስጥ ያለው መረጃ ከአብክመ ትምሕርት ቢሮ የተገኘ ነው። የሁለቱ መረጃዎች ልዩነት የትምሕርት ሚኒስቴር እና የክልሉ ቢሮ የተጠቀሙበት የክልሉ የሥነ ሕዝብ መረጃ ምንጮች ልዩነት የፈጠረው ነው።

32. የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ጥቅል ተሳትፎ በ2015 69.3 በመቶ ላይ ይገኛል። የደረጃው ተሳትፎ በቀዳሚዎቹ ዓመታት የተሻለ አፈጻጸም ነበረው። በተለይም ከ1988 እስከ በ2010 በነበሩት 22 ዓመታት ከ22.3 በመቶ ወደ 90.3 በመቶ ማደጉ አበረታች ውጤት የነበረ መሆኑን ያሳያል። ከ2010 ጀምሮ ምጣኔው እየቀነሰ የመጣ ሲሆን በአለፉት አምሥት ዓመታት የክልሉ የአንደኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎ በ21.3 የመቶኛ ነጥብ ቀንሷል።

33. ስዕል 4-7፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎ (1988 – 2015)



ምንጭ፤ የአብክመ ትምህርት ቢሮ

34. በተመሳሳይ የክልሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ጥቅል ተሳትፎ በ1998 ከነበረበት 5.9 በመቶ ምጣኔ በ2002 ወደ 50 በመቶ በማደግ አበረታች ውጤት ታይቶበት ነበር። ከ2002 የትምሕርት ዘመን በኋላ በነበሩት ዓመታት የታየው አፈጻጸም ወጣ ገባ እና ከ50 በመቶ ምጣኔ ያልበለጠ ነው። በ2015 የትምሕርት ዘመን የክልሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ጥቅል ተሳትፎ ወደ 38 በመቶ አሽቆልቁሏል።

35. በአጠቃላይ በዘርፉ በተሰጠው ትኩረት የመጀመሪያዎቹ ሁለት አሥርት ዓመታት አፈጻጸም አበረታች የነበረ ሲሆን የቅርብ ዘመናት አፈጻጸም ወጣ ገባ ነው። የአጸደ ሕጻናት ትምሕርት እና የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት አፈጻጸሞች ዝቅተኛ መሆን ሕጻናትን ከታች ከመቅረጽ እና ከአንደኛ ደረጃ በኋላ ቀጣይነትን ከማረጋገጥ ግቦች አኳያ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበት አመላካች ነው።

36. ከትምሕርት ሽፋን ባሻገር ሌላው ቁልፍ የትምሕርት አምድ የጥራት ጉዳይ ነው። የስርዓተ ትምህርቱን ተገቢነትና ጥራት ከማሻሻል አኳያ የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ መካከለኛ ደረጃ መጽሐፍ-ተማሪ ጥምርታ 1፡1 ማድረስ አልተቻለም፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ - ክፍል ጥምርታን 1፡35፣ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ - ክፍል ጥምርታን 1፡31 እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ - ክፍል ጥምርታን 1፡48 ደርሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የ1ኛ ክፍል የመድገም ምጣኔ 4.38 በመቶ ሲሆን የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች 47.84 በመቶ፣ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎችም 4.01 በመቶ ነበር፡፡

37. የትምህርት ፍትሐዊነት እና አካታችነት ከማሻሻል አንፃር የሥርዓተ ፆታ ምጥጥን በተመለከተ የቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል እና ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትምህርት 1.0፣ 0.99፣ 1.19 እና 1.28 ምጥጥን እንደ ቅደምተከተላቸው ደርሰዋል፡፡ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በተመለከተም የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል፣ ከ7ኛ-8ኛ እና ከ9ኛ-12ኛ ክፍል 0.63 በመቶ፣ 7.49 በመቶ፣ 4.39 በመቶ፣ 2.68 በመቶ ደርሷል፡፡

38. የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የመደበኛ የሰልጣኝ ቅበላ በ2016 በ4፡15፡4 ጥምርታ 65,079፣ ከዚህም ጋር ጠቅላላ ቅበላውን 1,190,820 ማድረስ ተችሏል። በተመሳሳጥ ዓመት የማሰልጠኛ ኮሌጆች ብዛት 126 እና የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ብዛት ደግሞ 42 ደርሷል፡፡

39. በአጠቃላይ በትምህርት እና ስልጠና ረገድ በ1980ዎቹ አጋማሽ ከነበረበት የሽፋን ደረጃ አንጻር በአሁኑ ወቅት የተሻለ አፈጻጸም ተመዝግቧል። ይሁን እንጂ መደረስ ከነበረበት የሽፋን ግብ አኳያ በተለይ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት እና በሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት አፈጻጸሞቹ አጥጋቢ አይደሉም። የአለፉት አራት ዓመታት ዝቅተኛ የትምሕርት ዘርፍ አፈጻጸም እንደ ሌሎች ዘርፎች አፈጻጸም ሁሉ በወቅቱ ከደረሱ ተደጋጋሚ ደፋቂ ኩነቶች በተለይም ከኮቪድ -19 ወረርሽኝ እና ከጦርነት ክስተቶች ጋር የተያያዙ ናቸው። ነገር ግን ቀድሞውንም ዝቅተኛ ለነበረው የአፀደ ሕጻናት ትምሕርት ተሳትፎ ዋና ምክንያት የትኩረት መጓደል ነው። ከግጭት ክስተት በፊትም ለሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ተሳትፎ በተጠበቀው ልክ አለማደግ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት እንደ ምክንያትነት ቢጠቀስም ከመጀመሪያ ደረጃ ትምሕርት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ያለው የተማሪዎች ሽግግር የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች በሚገኙበት ሁኔታ ጭምር ዝቅተኛ መሆኑ፣ ወይም የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔ ከፍተኛ መሆኑ፣ እና የመድገም ምጣኔ እየጨመረ መምጣቱ ለትምሕርት ሽፋን ግብ አለመሳካት ከአቅርቦት በላይ ሌሎች መሠረታዊ ምክንያቶች እንዳሉ አመላካች ነው።

40. ከትምሕርት ሽፋን የሚልቀው አሳሳቢ ጉዳይ የትምሕርት ጥራት መጓደል ነው። የትምሕርት ጥራት በግብዓት አቅርቦት ብቃት እና ጥራት፣ በሥርዓት ትምሕርት አግባብነት፣ እና በትምሕርት አስተዳደር ርትዕነት ይወሰናል። በእነዚህ እና ተያያዥ ምክንያቶች የትምሕርት ጥራት መጓደል በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ተስተውሏል። እነዚህ ቅርብ እና የተለመዱ ምክንያቶች ሲሆኑ በመሠረታዊነት ጥራት ያለው ትምሕርት ማዳረስ ያልተቻለው እና በኢትዮጵያ በረጅም ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚስተካከል ሽፋን ማረጋገጥ ያልተቻለው በውስን መነሻ ሀብት የሚጣረሱ የሽፋን እና የጥራት ግቦች የሚያዙ በመሆኑ፣ የትምሕርት ሥርዓት ከሣይንሳዊ ዕውቀት ግብነት ባለፈ የርዕዮት ዓለም መሣሪያ በመሆናቸው፣ እና ዕውቀትን የሚሻ እና የሚሸልም የኢኮኖሚ መዋቅር በየደረጃው ባለመፈጠሩ ምክንያት ነው።

## 4.3. ጤና

41. ከጤና አኳያ በኢትዮጵያ በሕይወት የመኖር ምጣኔ በ1992 ከነበረበት 50.6 ዓመት በ2014 ወደ 68.7 ዓመት አድጓል፡፡ በወሊድ ምክንያት የሚከሰት የእናቶች ሞት ምጣኔ በሕይወት ከሚወለዱ 100,000 ህጻናት መካከል በ2007 ከነበረበት 401 በ2012 ወደ 267 ወርዷል፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የጨቅላ ህፃናት እና ከ5

ዓመት በታች የሚገኙ ህፃናት ሞት ምጣኔ በህይወት ከሚወለዱ 1000 ህፃናት መካከል ወደ 46 እና 69 በቅደም ተከተል መውረድ ችሏል፤ ሁሉንም ዓይነት ክትባት ያገኙ ህፃናት ሽፋን 96 በመቶ የደረሰ ሲሆን ዕድሜያቸው ከአምሥት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት የመቀንጨር መጠንን 40 በመቶ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከአምሥት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት የመቀጨጭ ምጣኔ 15 በመቶ ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከአምሥት ዓመት በታች የሚሆኑት ህጻናት 53 በመቶ የሚሆኑት የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ያለባቸው ናቸው፡፡ በአለፉት ዓመታት እንደ ኤች አይ ቪ፣ ቲቢ እና ወባ ባሉ ዋና ተላላፊ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰት ህመምና ሞት በከፍተኛ መጠን መቀነስ ተችሏል፡፡ ሆኖም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና አደጋዎች ስርጭት መጨመር ላይ ይገኛል። 75 በመቶ የሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶች ቢያንስ ለ4 ጊዜ የቅድመ-ወሊድ ክትትል ያደረጉ ሲሆን 64 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች በጤና ተቋም ውስጥ የወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

42. መንግሥት የጤና የሰው ኃይል ልማትን ለማሻሻል በቁጥርና በሙያ ስብጥር ላይ ያተኮረ ኢንቨስትመንት አድርጓል። ሆኖም ግን የጤና የሰው ኃይል ጥምርታ 0.98 ለ1000 ሰው ሲሆን ይህም ከስታንዲርዱ አንፃር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው፡፡ መንግሥት ለጤና የሚውል ሀብት ለማሰባሰብ እና ህብረተሰቡ በገንዘብ እጦት ከጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት እንዳይስተጓጎል ለማድረግ እንደ ጤና መድህን ያሉ የተለያዩ የጤና መዋዕለ ንዋይ ማሰባሰብያ ስልቶች በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ የሚሰበሰበው ሀብትም የመክፈል አቅም ለሌላቸው ዜጎች እና ከክፍያ ነፃ ለሆኑ አገልግሎቶች እንዲሁም ከፍተኛ ተጸዕኖ ለሚፈጥሩ ስትራቴጂክ እርምጃዎች የሚውሉ ናቸው።

46. የጤና ዘርፍ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ የአገልግሎት ተደራሽነት እና የመቆራረጥ ፈተና ገጥሞታል፡፡ በተለያዩ የክልሉ ቦታዎች የተካሄዱ ግጭቶች ለበርካታ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውድመት እና የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን እንዲታወክ አድርጎታል፡፡ የተለያዩ ወረርሽኝ፣ ድርቅ፣ ጎርፍ እና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች በጤና ሥርዓቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ነበራቸው፡፡

## 4.4. ፈርጀ - ብዙ ማሕበራዊ ጉዳዮች

47. የሴቶች፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዊያንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነትንና ተሳታፊነት ከማሳደግ አንጻር በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ይሁን እንጅ በህብረተሰቡ ዘንድ የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት፤ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ለአረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች በቂና ዘላቂ አለመሆናቸው፣ የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን፤ የሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ድርሻ በአስፈፃሚው፣ በህግ አውጭው እና በህግ ተርጓሚው የውሳኔ ሰጪነት አናሳ መሆን፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ የኃይል ጥቃቶች እና መጤ ልማዶች መበራከት፤ ነፃና ጠንካራ አደረጃጀቶች አለመፈጠራቸው፤ የህግ አፈጻጸም ክፍተት፤ የመንግስት ተቋማት የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ የዋና ስራቸው አካል አድርገው አለመመልከት፣ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ያልተቀናጀ እና ያላደገ መሆኑ፣ አካል ጉዳተኞች የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የባህል መብቶቻቸው በሚፈለገው ደረጃ እየተከበሩ አለመሆኑ የአካል ጉዳተኞች ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለመረጃና የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና ለሌሎች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ያላቸው ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ዝቅተኛ መሆን፣ የማህበራዊ እሴቶች /Social Values/ እየቀነሰ ማህበራዊ ችግሮች እየተባባሱ የጎዳና ተዳዳሪነት እና ሱሰኝነት እየከፋ መምጣት፣ የስራ ባህል በሚፈለገው ደረጃ ያልዳበረ መሆን የሚሉት ዋና ዋናዎች ናቸው። በመሆኑም በቀጣይ የሚመለከተው አካል ሁሉ በሚታቀደው የ5 ዓመት ዕቅድ ወስጥ አካቶ በማቀድ ከላይ የቀርቡትን ተግዳሮቶችን መፍታት ያስፈልጋል።

48. የወጣቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥን በተመለከተ በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ የሆኑ የወጣት አደረጃጀቶችን 176,499 ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የስፖርት ሃብትን ከማሳደግ አንጻር 33,0316,921 ብር የተገኘ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ የስፖርታዊ ዉድድር መድረኮችን በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን በተመለከተ ክልል አቀፍ የውድድር መድረኮችን በማዘጋጀት ስፖርታዊ ውድድሮችን ማካሄድ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በታዳጊ ስልጠና ፕሮግራም 67 የኤሊት ስፖርተኞችን ማፍራት ተችሏል።

49. ይሁን እንጅ አሁንም በርካታ ወጣቶችን በሚፈለገው ደረጃ አለማደራጀት፤ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ አለመስጠት፣ ለችግሮቻቸው ራሳቸውን የመፍትሄ አካል አድርገው አለመውሰድ፣ በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች

ያለድምጽ በቋሚነትና በሚፈለገው መጠን አለማሳተፍ፣ በመንግስት አመራሮችና በአስፈፃሚ አካላት ለወጣቱ የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆን፣ ወጣት ተኮር የዉይይትና የተሳትፎ መድረኮች ማነስ ማነቆ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ስለሆነም በቀጣይ 5 አመታት በልዩ ትኩረት ወጣቶችን በተደራጀ አግባብ ንቅናቄ በማድረግ የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስራ መስራት ያስፈልጋል።

50. በስፖርቱም ባለፉት ዓመታት የስፖርት ማህበራትን በማደራጀትና በማጠናከር፣ የስፖርት ምክርቤት ጉባኤዎችን ለማካሄድ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በየደረጃው የስፖርት ማህበራት ራሳቸውን ችለው ስፖርቱን አለመምራት፣ የፋይናስ ድጋፍ በማድረግ በኩል ውስንነቶች መኖሩ እና የስፖርት ምክርቤቶች ጉባኤ አለመካሄድ የሚስተዋሉ ችግሮች ስለሆኑ በቀጣይ 5 አመታት የስፖርት ማህበራት ራሳቸውን ችለው ስፖርቱን እንዲመሩ የማድረግ ስራ መከናዎን ይኖርበታል።

51. የክልሉን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች የሚወድ፣ የሚጠብቅ፣ የሚያበለፅግና ወደ ልማት ኃይልነት የሚቀይር ትውልድ በመፍጠር፣ ባህልና ኪነ-ጥበብን ዋነኛ የልማት ኃይል በማድረግ እና የቱሪስት መስህቦችን በማስተዋወቅ የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መስራት ያስፈልጋል። ቅርሶችን በመጠበቅ፣ በማጥናትና በመመዝገብ ለቅርሶች ክትትል፣ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ፣ ሙዚየሞችን ማደራጀት መምራትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የክልሉን ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራቱን በጠበቀና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ገበያ መፍጠር፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቱሪስት መረጃ ማዕከል እንዲኖር ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ሊሆን ይገባል፡፡

## 4.5. መሠረተልማት

52. የተገነቡ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ለከተሞች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር እንደ መፍቻ የሚወሰዱ የልማት ማዕከል ናቸው፡፡ በመሆኑም ባለፉት 4 ዓመታት /2013-2016/ የUIIDP ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ እና ከፕሮግራሙ ውጭ ያሉ ከተሞች የገነቧቸው መሰረተ-ልማቶች በሰንጠረዡ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

53. ከከተማ መሰረተ ልማት አኳያ የኮብል ስቶን መንገድ 1,229.85 ኪ.ሜ፣ የጠጠር መንገድ 7,142.21 ኪ.ሜ፣ የጥርጊያ መንገድ 9,995.409 ኪ.ሜ እንዲሁም የአስፓልት መንገድ 167.344 ኪ.ሜ በድምሩ 18,535 ኪ.ሜ ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የጎርፍ መከላከያ ግንባታ 1,990.84 ኪ.ሜ ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል በከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሰረተ ልማት ዝርጋታ 6,731.57 ኪ.ሜ የማድረስ ስራ የተሰራ ሲሆን የመንገድ መብራት አቅርቦት መሰረተ ልማት 4,577.1 ኪ.ሜ እንዲሁም በሁሉም ከተማ አስተዳደሮች የእሳትና ድንገተኛ አደጋ አገልግሎት እና ዘመናዊ የቄራ አገልግሎት ሽፋንን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡ የገበያ ማዕከላት ግንባታ በቁጥር 132 እንዲሁም የመስሪያና መሸጫ ሸድ ግንባታ በቁጥር 20,324 የማድረስ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተለያዩ ከተሞች ከከተሞች አረንጓዴ ልማት አኳያም የተለያዩ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

54. ከትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አኳያ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን እስከ 2015 በጀት ዓመት 252 መናኸሪያዎች የተሰሩ ሲሆን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የተግባር ፈተና መስጫ የትራፊክ ኮምፕሌክሶችን 5 እንዲሁም የደረቅ ጭነት ወደቦችን 3 የማድረስ ስራ እንዲሁም የአትክትና ፍራፍሬ እና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል 2 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ተገንብተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የመንገድ ትራፊክ አደጋን በ10 ሽህ ተሽከርካሪ በ2015 በጀት ዓመት 32 በመቶ ላይ የሚገኝ ሲሆን በትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰው የሰው ሞት በአማካኝ በየዓመቱ 772 እንደሆነና ከፍተኛ የሆነ የአካል መጉደልና የንብረት መውደም እንደሚደርስ መረጃው ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የብዙሃን ትራንስፖርተ አገልግሎት ህዝብ የማጓጓዣ ድርሻ 1.3%፣ የገቢ እቃዎች ከደረቅ ወደብ ላይ ቆይታን 30 ቀን እንዲሁም ወጪ እቃዎች ከተመረቱበት አካባቢ መጋዘን ተጭነው ወደ ወደብ የሚደርሱበት ጊዜ 30 ቀን እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

55. በአጠቃላይ ገበያ ተኮር የግብርና ምርት በስፋት እንዲያመርት የሚታሰበው የገጠሩ ህብረተሰብ ተገቢውን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ እየተሠራ ያለው ተግባር ውስንነት ያለበት በመሆኑ እና ክልላችንን በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሊያደርግ የሚያስችል ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ ደህንነቱና ምቾቱም የተጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ በቀጣይ የዕቅድ ዓመታት ከዘርፉ የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል።

56. የክልሉ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በገጠር 78.22 በመቶ በከተማ 78.84 በመቶ በአጠቃላይ 78.84 በመቶ ሲሆን የብልሽት ምጣኔ 22.4 በመቶ እንዲሁም የሚባክን ውሃ መጠን 22.05 በመቶ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ስርጭት ሽፋን 73.02%፣ የቤተሰብና የተቋማት የባዮ ጋዝ ዳይጀስተር ፕላንቶችን በመገንባት የተጠቃሚነትን ቁጥር 19,000፣ የተቋም ባዮ ጋዝ ዳይጀስተር ፕላንት ግንባታ 5፣ በገጠር መንደሮችና በአነስተኛ ከተሞች የተለያዩ አማራጭ የኢነርጂ ኃይል ሽፋን 10.5 ሜጋ ዋት እንዲሁም የሶላር ስርጭት 532,318 ደርሷል፡፡

57. በመሆኑም ከውሃ ልማቱ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅም አሁን ከተደረሰበት በበለጠ ተደራሽነቱን ለማረጋገጥና የተጀመረውን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ ያጋጠሙ ቁልፍ ችግሮች የውስጥ የመፈጸም አቅም ችግር፣ የአማካሪዎች የተቋራጮች እና የቁፋሮ ድርጅቶች አቅም ውስንነት፣ በገጠር የውሀ ተቋማት ግንባታ የህብረተሰቡ ተሳትፎዉ ውስንነት እንዲሁም የትርንስፎርመርና የሀይል አቅርቦት ችግር ደረጃ በደረጃ በመፍታትና መልካም ልምዶችን በማዳበር የቀጣዩን አምስት ዓመት የእቅድ ዘመን እንዲሳካ ለማድረግ የበለጠ ጥረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ከኢነርጅ አኳያ የተለያዩ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በክልሉ ካለው የኢነርጂ ፍላጎት አኳያ በአማራጭ ኢነርጅዎችም ሆነ በአጠቃላይ ኢነርጅ ካለው ከፍተኛ ችግር አንጻር ችግሩን ለመቅረፍ በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

58. የክልሉን አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን በ2015 በጀት ዓመት 31,392.89 ኪ.ሜ ማድረስ የተቻለ ሲሆን የመንገድ ጥግግትን በ1000 ካሬ ኪ/ሜትር 171.89 ኪ/ሜትር እንዲሁም በ1000 ህዝብ 1.35 ኪ/ሜትር ነው፡፡ በቅርብ ከሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ ያለው አማካይ ርቀትም 2.95 ኪ/ሜትር እንዲሁም በቅርብ ከሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ የሚወስደው አማካይ የእግር ጉዞ በሰዓት 35.43 ደቂቃ ማድረስ ተችሏል። የመደበኛ መንገድ ግንባታን እስከ 2015 በጀት ዓመት 4,921.2 ኪ.ሜ የማድረስ ስራ የተሰራ ሲሆን የነባር መንገዶችን ደረጃ ማሻሻልና መልሶ ግንባታ 143.64 ኪ.ሜ፣ የወረዳ ገጠር መንገድ ግንባታን 13,057 ኪ.ሜ፣ በመንገድ ተደራሽነት ቀበሌን ከቀበሌ፣ ወረዳን ከዋና መንገድ ማገናኘት 2,621 ቀበሌዎች እንዲሁም የመደበኛ እና የወቅታዊ ጥገና 4305.47 ኪ.ሜ የማሳደግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የወረዳ ገጠር መንገድ ጥገናን እስከ 2015 በጀት ዓመት 21,902.05 ኪ/ሜ መጠገን የተቻለ ሲሆን የመንገድ ተደራሽ ባልሆኑ አካባቢዎች በመቀናጀ በጀት የእግረኛ ተንጠልጣይ ድልድዮችን ግንባታ 21 መገንባት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ለመንገድ ግንባታና ጥገና ከወረዳ ም/ቤትና ከህብረተሰቡ ተሳትፎ ከ2.2 ቢሊዮን ብር በላይ በማሰባሰብ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

59. ለመንገድ ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን የሚጠቀሱ ዋና ዋና ምክንያቶች በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የግንባታ ፕሮጀክቶች መቆም፣ የገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ የግንባታ ማሽነሪዎች መዘረፍ፤ የኮንስትራክሽን ግንባታ ግብዓት እጥረትና የዋጋ ንረት እንዲሁም የገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ የበጀት እጥረት ናቸው፡፡ስለሆነም በመደበኛ መንገድ የታዩ ጉድለቶችን ለመፍታት የመንገድ እና የድልድይ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው ጊዜ፣ በጀት እና ጥራት እንዲሰሩ ከፍተኛ የሆነ የድጋፍና ክትትል ስራ የሚጠይቅ በመሆኑ በውስን በጀት በርካታ ቁጥር ያለው ፕሮጀክት በረዥም ዓመታት ከመጨረስ ይልቅ ትንሽ ቁጥር ያለው ፕሮጀክት በአጭር ዓመታት እያጠናቀቁ በመሄድ የመንገድ ተደራሽነትን ማረጋገጥ በቀጣይ ዓመታት በትኩረት ሊሰሩ ይገባል።

60. ከመስኖ አኳያ የተገነቡ ፕሮጀክቶች ቁጥር 6,148 እንደሆነና የሚለማው መሬት 260,269 ሄ/ር እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግንባታቸው በፌደራል የተጀመሩና 22,310 ሄ/ር የሚያለሙ 7 ሜጋ ፕሮጀክቶችን በግንባታ ላይ ያሉ ሲሆን የተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበር ቁጥርም 1,600 እንደደረሰ መረጃው ያመላክታል፡፡ በመሆኑም በመስኖ እየለማ ያለውን መሬት በመንግስት፣ በግለሰብ እና በልማት ድርጅቶች መረጃ ለይቶ በመያዝ፣ የተጠናቀቁና የተቋረጡ ከፍተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ልማት እንዲገቡ በማድረግ፣ ለተለያዩ ብልሽቶች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣ አስፈላጊ ቴክኖሎጅዎችን በሚፈለገው መጠን ለህብረተሰቡ በማቅረብ፣ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማጠናከር እንዲሁም የህብረተሰቡን የመስኖ ተጠቃሚነት በማሻሻልና ህብረተሰቡን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

61. ከኢኖቬሽንና ቴክኖለጂ ልማት አኳያ ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ በኢንተርፕራይዞች/ካፓኒዎች 23 ቴክኖሎጅዎች የለሙ ሲሆን ለተለያዩ ተቋማት በተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች ላይ ለ87 ኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በምርምር የተለዩ 9 ቴክኖሎጅዎችን ማሸጋገር የተቻለ ሲሆን በተሸጋገሩ

ቴክኖሎጅዎችም 359 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጅ የመንግስትም ሆነ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ባለማደጉ ለዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጅ እንዲሁም ለፈጠራ ሥራዎች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው። የተለዩ ቴክኖሎጅዎችን ለይቶ እንዲሸጋገር በማድረግ በኩልም ያለው አፈጻጸም እንደ ክልል ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም በክልሉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ኢኮኖሚ ለመገንባት ለእውቀት፣ ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ትኩረት በመስጠት፣ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጋር በመተባበር የሚሰራበት ሁኔታን ማመቻቸት፣ የምርምር ተቋማት በቴክኖሎጂ ማላመድና ፈጠራ ላይ አተኩሮ መስራት እንዲሁም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት በተመረጡ የምርምር ሥራዎች፣ የቴክኖሎጂ መረጣ መቅዳት፣ ማላመድና ስርፀት ላይ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተገቢ ይሆናል።

## 4.6. የመንግሥት ገቢ እና ወጪ አፈጻጸም

### የክልሉ የገቢ አሰባሰብ ሁኔታ

62. የክልሉን የልማት ፍላጎት ለመመለስ ቀደም ባሉት ዓመታት የነበረውን ዝቅተኛ የገቢ አሰባሰብ ለመቀየር እና የተሻለ የገቢ አሰባሰብ እንዲኖር ለማድረግ በገቢ አሰባሰብና አስተዳደር ዙሪያ ሰፊ የማሻሻያ እርምጃዎች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ናቸው። በመሆኑም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ መጀመሪያ ላይ በክልል ደረጃ ይሰበሰብ ከነበረው ብር 7.744 ቢሊየን በ2014 በጀት ዓመት ወደ ብር 29.04 ቢሊየን ከፍ ማድረግ ተችሏል።

63. ሠንጠረዥ 4-9፤- በክልሉ የተሰበሰበ ገቢ እና የፌደራል ጥቅል ድጎማ መጠን (በሚሊየን ብር)

| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የክልሉ ውስጥ ገቢ | 7,744 | 8,947 | 10,551 | 12,169 | 13,877 | 21,939 | 29,044 |
| የፌደራል ድጎማ | 19,720 | 24,894 | 26,056 | 29,576 | 32,728 | 38,383 | 45,696 |
| **ድምር** | **27,464** | **33,841** | **36,607** | **41,745** | **46,605** | **60,322** | **74,740** |
| በክልል ውስጥ ገቢ የመሸፈን አቅም በ% | 28.2 | 26.4 | 28.8 | 29.2 | 29.8 | 36.4 | 38.9 |

ምንጭ፡ የአብክመ ገንዘብ ቢሮ

64. ከጠቅላላ የክልል መንግስት ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው የፌደራል ድጐማ ሲሆን ይህም በ2008 ከነበረበት 71.8 በመቶ ድርሻ በ2014 በጀት ዓመት ወደ 61.1 በመቶ ዝቅ ብሏል።

### የመደበኛና የካፒታል በጀት ወጪ

65. የክልሉ ጠቅላላ ወጪ በ2008 በጀት ዓመት ብር 25.96 የነበረ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት አጠቃላይ በክልሉ ለልማት ጥቅም ላይ የዋለው የወጪ መጠን ወደ ብር 86.057 ቢሊየን አድጓል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ከጠቅላላ ወጪው 68.22 በመቶ የሚሆነው ለመደበኛ ወጪ የዋለ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ወጪው በመጨመር 80.13 በመቶ የደረሰ እንደሆነና የካፒታል በጀት ወጪ ደግሞ ከዓመት ዓመት ድርሻው በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ በመምጣት በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት 31.75 በመቶ ድርሻ በ2015 በጀት ዓመት ወደ 19.87 በመቶ ቀንሷል፡፡

66. ሠንጠረዥ 4-10፤ በክልሉ ለመደበኛና ካፒታል የወጣ ወጪ (በሚሊየን ብር)

| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመደበኛ ወጪ | 17,710 | 24,171 | 27,516 | 31,073 | 36,730 | 49,658 | 61,800 | 68,958 |
| የካፒታል ወጪ | 8,242 | 8,784 | 8,614 | 10,068 | 9,847 | 11,498 | 12,293 | 17,099 |
| **ጠቅላላ ወጪ** | **25,962** | **32,955** | **36,130** | **41,141** | **46,578** | **61,157** | **74,093** | **86,057** |
| የካፒታል ወጪ ድርሻ በ% | 31.75 | 26.65 | 23.84 | 24.47 | 21.14 | 18.80 | 16.59 | 19.87 |

**ምንጭ፡ የአማራ ብሔራዊ ክልል ገንዘብ ቢሮ**

67. ከመንግስት ገቢ አንጻር የፊሲካል ፖሊሲው ዋና ግብ የሆነውን የታክስ ገቢ ማሻሻል ቢሆንም ካለው የልማት ፍላጎት አንፃር እየተሰበሰበ ያለው የገቢ መጠን ሲታይ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ከመንግስት ገቢ አንጻር የታክስ GDP ጥምርታው/ድርሻው/ ሌሎች አገሮችና ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮችም እጅግ በጣም ያነሰ ነው። ዘላቂና አስተማማኝ የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር ካስፈለገ የክልሉን ገቢ የማደግ ጉዳይ ቁልፍ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በብድርና በእርዳታ የሚሠሩ ሥራዎች ቀጣይነታቸውና ዘላቂነታቸው አስተማማኝ ስለማይሆን በቀጣይ የክልሉ ኢኮኖሚ ሊያመነጨ የሚችለውን የታክስ ገቢ በብቃትና በቁርጠኝነት መሰብሰብ ተገቢ ነው።

# ምዕራፍ አምሥት
# የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ - ካርታ

## 5.1. መነሻ

### ፋይዳ

1. የመካከለኛ እና የአጭር ዘመን የጥቅል ኢኮኖሚ አፈጻጸም እንደሚያመላክቱት በክልሉ ለሚስተዋሉት የገነገነ ድህነት፣ ሥራ አጥነት እና የኑሮ ውድነት ችግሮች የተሰባበረ ሲከፋም አዝጋሚ የኢኮኖሚ ዕድገት እና አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ በቅርብ ምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ከአዝጋሚ የኢኮኖሚ ዕድገት እና አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጀርባ በዓለም አቀፍ መስፈርቶች ዝቅተኛ ምርታማነት እና የቅልጥፍና ዳተኝነት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የዕድገት ማረጋገጫ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በየዘመኑ ታቅደው ወደ ተግባረ በተሸጋገሩ የልማት ዕቅዶች የተወሰሁ ቢሆንም በአፈጻጸም ደረጃ አሻጋሪ ዕድገት በዘላቂነት ማስመዝገብ አልተቻለም። የክልሉ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መዋቅራዊ ናቸው ሲባልም ከኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ባለፈ በአፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ የሥርዓታት ችግሮች እንደሆኑ ይታመናል። መፍትሄው እነዚህን ከማሕበረሰብ አመለካከት እስከ ፖለቲካዊ አመራር የሚዘልቁ የዕድገት መሠረታዊያንን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የአንድ ትውልድ (የረጅም ዘመን) መዳረሻን በርዕይ አመላክቶ በአዲስ እይታ በሳይንሳዊ መንገድ ሁሉን አቀፍ የልማት ዕቅድ በመንደፍ አሻጋሪ ዓላማዎችን፣ ግቦችን፣ ስትራቴጂዎችን እና፣ የአፈጻጸም ስልቶችን መንደፍ ነው።

2. በዕቅዱ ላይ የተለየ ባሕርይ ከመለየት አንጻር ያለፉት የልማት ዕቅዶች ሲቃኙ በተለይ በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሁም በአሥር ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን መዋቅራዊ ሽግግር፣ እና ጥራት ያለው አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያረጋግጡ የሚችሉ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ ዓላማዎች፣ ግቦች እና ከሞላ ጎደል የማስፈጸሚያ ስልቶች ተመላክተዋል። በዚህ ዕቅድ ከቀዳሚዎቹ ዕቅዶች የሚወሰዱ ጠንካራ ልምዶች ያሉ ሲሆን ለተሻለ አፈጻጸም ከቀዳሚዎቹ ዕቅዶች የተለዩ ባሕርያት ተካትተዋል። አንዱ የዕቅዱ ልዩ ባሕርይም የክልሉን የልማት መዳረሻ በአንድ ትውልድ ዘመን (25 ዓመት) በማመላከት የቀጣዩን የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ መነሻ መዳረሻውን ኢላማ ያደረገ ምክንያታዊ እና ሳይንሳዊ ዕቅድ ማድረግ ነው። የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ-ካርታ

   1. በቴክኒካዊ ደረጃ በየትኛውም መንገድ ከተገኘ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ዕድገት መሰል ክስተት ባለፈ የቴክኖሎጂ - መር የኢኮኖሚ ዕድገት እና የመዋቅራዊ ሽግግር መዳረሻዎችን ያሳያል፤
   2. በረጅም ዘመን ክልል እና አገር የሚገነባው ከገቢ በላይ አቅም በመሆኑ የሚታነጹ የቁሳዊ ካፒታል፣ የሰብዓዊ ካፒታል፣ የቴክኖሎጂ፣ እና የማሕበራዊ ካፒታል አቅሞች ዓይነት፣ መጠን እና ጥራት በዕቅድ ለማመላከት ዕድል ይሰጣል፤
   3. ከፍ ባለ ደረጃም ማሕበረሰብ ወይም አገር ሲሰለጥን እና ሲበለጽግ ምን እንደሚመስል ለማየት እና ለማጤን ያስችላል፤ በተለይም ማሕበረሰብ ሲሰለጥን የልማት ግብዓትና ግብ ሰው እንደሚሆን፣ ከመሬት እና ቁስ በላይ እውቀትና ሰው እንደሚከበር፣ መንግሥት እንዲፈታቸው አደባባይ የሚወጡ ብዙ ግን የሚጣረሱ ፍላጎቶች ወደ ቤት እንደሚሰተሩ፣ የጉልበትና የመሣሪያ የበላይነት በሃሳብ የበላይነት እንዲሁም፣ ግጭት በውይይት፤ ሥርዓት አልበኝነት በሥርዓት እንደሚተካ፣ መንግሥት እና ሕዝብ ዴሞክራሲ መብትን መስጠት ብቻ ሳይሆን ግዴታንም ማስከበር መሆኑን እንደሚገነዘብ፣ እና ጠንካራ ተቋማት ኃያል መሪዎችን እንደሚተኩ ለማስተዋል ያስችላል፤
   4. ልምድ ከመቀመር አኳያም ከከፋ ድህነት ወደ ብልጽግና የተመነጠቁ የቅርብ ዘመን አገራት የረገጧቸውን እና የጨበጧቸውን መወጣጫዎች፣ የከፈሏቸውን መስዋዕትነቶች፣ እና የወሰደባቸውን ጊዜ ለማየት ያስችላል፤
   5. በዚህም መዳረሻን በቅጡ ማወቅ የመልማት ተስፋን ጨምሮ መነሻን በአግባቡ ለመቀመር እና ለማነጣጠር፣ በጊዜያዊ ተግዳሮቶች መለቀቅ የሌለባቸውን ፍኖቶች ለመለየት ያስችላል፤ መነሻዎች እና መንገዶች ሁሉ ወደታለመ ግብ ያለማድረሳቸው ዕውነታ መዳረሻን አውቆ ማቀድ የስኬት ማረጋገጫ አንዱ እና ዋና ጉዳይ ስለሚያደርገው መነሻን በአግባቡ ለማቀድ ዕድል ይሰጣል።

### የአንድ ትውልድ ርዕይ

2. የአጭር እና መካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶችን በረጅም ዘመን ዕይታ በማስመርኮዝ ምክንያታዊ እና ስኬታማ ለማድረግ የአማራ ብሔራዊ ክልል የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ነድፏል። የአማራ ብሔራዊ ክልል የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ መዳረሻ ርዕይ **ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ አቅም እና ሁለንተናዊ ብልጽግና** ነው። በሃያ አምሥት ዓመት የልማት ዘመን ውስጥ በየደረጃው የሚደረስባቸው ሦስት ንዑስ ርዕዮች
    1. በ2022 የአማራ ብሔራዊ ክልል በወሳኝ ዘርፎች ንቅናቄ የኢኮኖሚ ልማት መመንጠቅ አስተማማኝ መሠረት የጣለ እና የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆኖ ማየት፤
    2. በ2027 የአማራ ብሔራዊ ክልል በመሠረታዊ ኢንዱስትሪ ምርቶች የራሱን ፍላጎት የሸፈነ እና የተሳካ የመዋቅራዊ ሽግግር በማድረግ በትክክለኛ የብልጽግና ፍኖት ላይ ሆኖ ማየት፤ እና
    3. በ2042 የአማራ ብሔራዊ ክልል በዓለም በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ የሆነ የዘመናዊ ኢኮኖሚ አቅም ባለቤት ሆኖ ማየት ነው።
3. የሃያ አምሥት ዓመት አመላካች የዕድገት ፍኖተ-ካርታ በአምሥት የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች የሚተገበር ሆኖ ሦስት የወሳኝ ርምጃ ርከኖች ይኖሩታል። እነዚህም
    1. የኢኮኖሚ መረጋጋትና ማገገም ፕሮግራም (Economic Stabilization and Recovery Program)፣
    2. የመመንጠቅ ደረጃ (Stage of Economic Rebound)፣ እና
    3. የመበልጸግ ደረጃ (Stage of Economic Prosperity) ርከኖች ናቸው።

4. የ2017 የዝግጅት ዓመትን ጨምሮ እስከ 2019 ባሉት ሦስት ዓመታት ኢኮኖሚውን የማረጋጋት እና የማገገም ርብርብ የሚደረግ ሲሆን ከአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን በመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ለዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪ መሠረት መጣል እና መደላድል መፍጠር ይጀመራል። ከ2023 ጀምሮ በሚኖሩት አምሥት የዕቅድ ዓመታት በመሠረታዊ የኢንዱስትሪ ምርቶች ራስን የመቻልን ርዕይ ለማሳካት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል፤ የግብርና ዘርፍ በምግብ ራስን ከማስቻል አልፎ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት መፋጠን ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከ2033 ጀምሮ ቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት ጊዜ የተሳካ የኢኮኖሚ መመንጠቅ (economic take-off) የሚረጋገጥበት እና በአንድ ትውልድ በዓለም ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ የመገንባት እና የሁለንተናዊ ብልጽግና ርዕይን የማሳካት ጥረት ዳር የሚደርስበት ጊዜ ይሆናል።

## 5.2. ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች እና የረጅም ጊዜ የትኩረት አቅጣጫዎች

3. የቀጣዮቹን አምሥት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ጨምሮ በአንድ ትውልድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራባቸው አራት ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።
    1. **የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ማረጋገጥ፤** የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ችግርን በውይይት የመፍታት ልምምድን ማሳደግ፣ የክልሉን የመደራረደር አቅም ማጎልበት፣ የሽግግር ፍትህን መተግበርና ክልሉ ሚናውን በሚጠበቅበት ደረጃ እንዲወጣ ማድረግ፣ አገራዊ ምክክርን ማጠናከር፣ የፍትህና የፀጥታ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚገባ እንዲወጡ ማስቻል፣ የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ መንግሥት ላይ ያለቸው አመኔታ እንዲጨምር ማድረግ እንዲሁም ምክር ቤቶች የህዝብ ውክልናቸውን በተገቢው መንገድ እንዲወጡ ማድረግ በዕቅድ ዘመኑ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

    2. **ክልላዊ ወጎችን፣ ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፤** ክልላዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት ከሥርዓታት አንፃር የመንግሥት፣ የማሕበረሰብ፣ የትምህርት ተቋማት፣ የዕምነት ተቋማት፣ የልሂቃን (የፖለቲካና የኢኮኖሚ) እና የሚዲያ ተቋማት ሥርዓታትን በማጠናከር፤ በተጨማሪም በታሪክ፣ በባህል፣ በፖለቲካል ኢኮኖሚ የክልሉን እሴቶች ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን አድርጎ በስፋት ይሠራል።

    3. **ሣይንሳዊ ዕውቀትን የርትዕ ማሕበረሰብ እሴት እና የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ማድረግ፤** የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት እና ለዘመኑ የሚመጥን ዲጂታል ዝግጁነትን በማሳደግ ሀብት ፈጠራን መሠረት ያደረገ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ ለመገንባት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

    4. **ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በማሳደግ ጥራት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት፤** ከድህነት መውጫው መንገድ ማምረት ነው። ቁጥሩ በሚጨምር ሕዝብ፣ በሚያድግ፣ በሚሰፋ እና በሚራቀቅ ፍላጎት ፊት

ከድህነት ለመውጣት እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመገንባት መሠረታዊ ጉዳይ ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን ማሳደግ ነው። በዋናነት በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በዘመናዊ ግብርና እና በሁለገብ ቴክኖሎጂ ላይ በሚደረጉ ጥረቶች የሚረጋገጥ የምርታማነት ዕድገት እና ቅልጥፍና ለዕውቀት መር ኢኮኖሚ መሠረት ይሆናል።

4. ከኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ችግሮቹ፣ እንዲሁም ከመሠረታዊ ምክንያቶቹ በመነሳት የክልሉ የቀጣዮቹ ሃያ አምሥት ዓመታት የትኩረት አቅጣጫዎች
    1. በሜካናይዜሽን (ማሽን)፣ በኃይል፣ በግብዓት፣ እና አቶሜሽን (ዲጂታላይዜሽን) ትስስር የቴክኖሎጂ ተስተካካይነትን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ ኢኮኖሚ መገንባት፣
    2. ዘላቂ እና ዘመናዊ ከትመት ማረጋገጥ፣
    3. የገጠር ማሕበራዊ ሽግግር ማረጋገጥ፣
    4. ሰላም፣ ፍትህ፣ እና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት ማረጋገጥ፣ እና
    5. ሣይንሳዊ ዕውቀትን ከመልካም አገራዊ እሴቶች ጋር አጣጥሞ የሚዘልቅ ርትዕ ማሕበረሰብ መገንባት ናቸው።

5. **የክልሉ የግብርና ዘርፍ ገዢ ስትራቴጂ በዘመናዊ ግብርናን (የግብርና ትራንስፎርሜሽን) እና የገጠር ትራንስፎርሜሽን በመተግበር ድህነትን በሁለት አቅጣጫ መቅደም፣** እና የአምራች ኢንዱስትሪው በመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚውን ፍጥነት እንዲመራ በሚያስችል ሁኔታ የረጅም ጊዜ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት እና ተወዳዳሪነትን መሠረት ላደረገ የመዋቅራዊ ለውጥ መሠረት መጣል ነው።

6. የግብርና ትራንስፎርሜሽን የረጅም ጊዜ ዋና ዓላማ ለዘመናዊ ግብርና ኢንዱስትሪ በግብዓት፣ በምርት፣ እና በስርጭት የሚገለጽ ዘላቂ ቴክኖሎጂ ማሸጋገር ነው። ዋና ስትራቴጂው ቴክኖሎጂ መር፣ ኢኖቬሽን ተኮር፣ እና ዓለም አቀፍ ገበያ ሰበር ይሆናል። በውጤቱም ምርታማነት፣ ቅልጥፍና፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት፣ እና አትኩሮተ - ሙያ (specialization) ይረጋገጣሉ።

7. **የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የኢኮኖሚ ተስተካካይነት** (economic catch up) **በቴክኖሎጂ ተስተካካይነት (technological catch up) እና ተወዳዳሪነት የሚረጋገጥበት መሪ ዘርፍ ነው።** በሚቀጥሉት ሃያ አምሥት ዓመታት በመሠረታዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ራስን በመቻል ግብ ተጀምሮ በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በዓለም ተወዳዳሪ አቅም የመገነባት ትልም ይሳካ ዘንድ ርብርብ ይደረጋል። በተለይም በረጅም ዘመን የክልሉ አምራች ኢንዱሰትሪ በሜካናይዜሽን (ማሽን ቴክኖሎጂ)፣ በኃይል ቴክኖሎጂ፣ በግብዓት ቴክኖሎጂ፣ እና በኦቶሜሽን (ዲጂታል) ቴክኖሎጂ ትስስር እመርታ መፍጠር ይጠበቅበታል። በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የቴክኖሎጂ ሽግግር ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ ልማት መሠረት ይጣላል።

8. **ከትመት የዛሬ እና የወደፊት አይቀሬ ክስተት ነው።** የከተማ ልማት ዋና ዓላማ ከተሞች የወደፊት የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ አውዶች እንደመሆናቸው መጠን ለኑሮ እና ለሥራ ምቹ የሆኑ ከተሞችን ቀድሞ በተመላከተ መሪ ፕላን በመግራት መፍጠር ነው። የተሳካ ዘመናዊ ከትመት የመዋቅራዊ ሽግግር ማሳረጊያ እና የስልጣኔ መገለጫ ስለሆነ ትጉሃን የሚሹት እንጂ የሚሸሹት አይደለም። ለለውጥ ለቆረጠ ማሕበረሰብ የዓለም ቴክኖሎጂ ከሚፈቀወደው በታች ዝቅተኛ የግብርና ምርታማነት ለዕድገት ዕድል እነደሆነ ሁሉ፣ በኃይል እጥረት በግማሽ አቅም የሚሠራ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የኃይል እጥረት ችግር ሲፈታ የአዲስ ምርታማነት ዕድገት ምንጭ እንደሚሆን ሁሉ፣ በችግርነት የምንፈርጀው ሥራ አጥነት ወደ የተሟሟቀ የልማት ሥራ ሲገባ የልማት አቅም እንደሚሆን ሁሉ፣ ዝቅተኛ የከትመት ምጣኔም ለዘመኑ የሚመጥን ስልጡን ከተማ ለመገንባት በመቶ ዓመት የተከማቸ የከተማ አውታረ-አቅምን ማፍረስ ሳይስፈልግ ዘላቂ ከትመትን የማረጋገጥ አንጻራዊ ዕድልን ይሰጣል። በውስን የአመለካከት አድማስ የገዘፈ ችግር የሚመስለን የከትመት ግስጋሴ በሌላው ዓለም ከአማራ ሕዝብ ቁጥር ጋር የሚስተካከል ሕዝብ በአንድ ፍጹም ስልጡን ከተማ የሚኖር መሆኑን ለሚያስተውል ትልቁ ችግር የከትመት ግስጋሴው ሳይሆን አቅዶ እና ጠንክሮ አለመሥራት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

9. ስዕል 5 -1፡ የከትመት ምጣኔ ትንበያ




10. **አብዛኛው ማሕበረሰብ በሚኖርበት አውድ የገጠር ልማት የማይታለፍ ርከን ነው።** በአንድ ትውልድ በሚለካ የመዋቅራዊ ሽግግር ሂደት ውስጥ አብዛኛው የገጠር ማሕበረሰብ ከተሜ የሚሆንበት እና ጥቂት መክሊቱ ያላቸው ዘመናዊ የግብርና ዘርፍ ተዋንያን አገራዊ የግብርና ምርት ፍላጎትን አትረፍርፈው የሚያሟሉበት አውድ እንደሚፈጠር ግብ የተጣለ ሲሆን፣ በዚህ የረጅም ጊዜ ሽግግር ወቅት በገጠር የሚኖረው ማሕበረሰብ ልዩ ትኩረትን እንደሚሻ ግንዛቤ ተወስዷል። በዚህም መሠረት፣ የገጠር የኑሮ መሠረትን እና ዘይቤን ከግብርና እና ከግብርና የሀብት መሠረት ጋር ብቻ ከሚያቆራኘው አስተሳሰብ በመላቀቅ በብዝሃ ዘርፍ ተሳትፎ በተቀናጀ የገጠር ልማት የገጠር ማሕበረሰባዊ ሽግግር (rural transformation) ተግባራዊ ይደረጋል። የዚህ የገጠር ማሕበረሰባዊ ሽግግር ዋና ዓላማ የተሻሻለ እና ጥራት ያለው ኑሮ በገጠር ማረጋገጥ፣ ዘመናዊ መሠረተ ልማትን በተማከለ ሁኔታ እና በጥራት ማዳረስ፣ የቤተሰብ ገቢ ምንጭን ማስፋት እና ማሳደግ፣ የገጠር አካባቢን መልሶ ማልማት፣ እና ለገጠር - ከተማ ሽግግር ምቹ መሠረት መጣል ነው። በውጤቱም በስልጡን መንደር በራሱ የሚተማመን እና የሚደጋገፍ ስልጡን ሰው፣ ስልጡን ኢኮኖሚ፣ ስልጡን አኗኗር፣ ስልጡን እንቅስቃሴ፣ ስልጡን አካባቢ፣ እና ስልጡን አመራር የመፍጠር ግብ ይረጋገጣል።

11. **የረጅም ዘመን ዕቅድ ዋና ግብ ከገቢ በላይ የገቢ ማስገኛ አቅሞች ናቸው።** በዚህ ረገድ በማምረቻ መሣሪያዎች እና መሠረተ ልማት የሚገለጹ የቁሳዊ ካፒታል መጠን እና ጥራት፤ በትምሕርት፣ በጤና እና በርትዕነት የሚገለጹ የሰብዓዊ ካፒታል አቅሞች፤ የግለሰቦች ግንኙነት፣ ማሕበራዊ መደጋገፍ፣ ሲቪክ ተሳትፎ፣ መተማመን እና መተባበር የሚገለጹ የማሕበራዊ ካፒታል፤ እና ቴክኖሎጂ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራባቸው አቅሞች ናቸው። በተለይም ኢኮኖሚ ተስተካካይነት ዋና ማረጋገጫ የሆነው ቴክኖሎጂ በሜካናይዜሽን፣ በኃይል፣ በግብዓት፣ እና በኦቶሜሽን ላይ አበክሮ የሚሠራ ሲሆን መሪ ዘርፎች እና መሪ አቅሞች፣ የተቀናጁ እና የተሳሰሩ አቅሞች፣ በአቋራጭ ከዓለም ቴክኖሎጂ ጫፍ የመድረስ ስልት፣ እና ሕዝባዊ መሠረት ያለው ቴክኖሎጂ ማስፈን የሃያ አምሥት ዓመት የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

12. **ጤና እንደ መጨረሻ የልማት ግብ እና በሰብዓዊ ካፒታል አምድነት እንደ ልማት አቅም ትኩረት ይሰጠዋል።** ከዚህ አንጻር መከላከል፣ መጠበቅ፣ እና ማሻሻልን እንደ ዋና የጤና አምዶች በመውሰድ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የሚሠራ ይሆናል። በተለይም የማሕበረሰብ የጤና ግንዛቤ ዝቅተኛ በሆነበት በክልሉ ነባራዊ ሁኔታ የትምሕርት እና ሥልጠና እንዲሁም በጤና አጠባበቅ ልዩ የትምሕርት ፕሮግራሞች ጭምር የታገዘ የመከላከል ፖሊሲ ዛሬም ፋይዳው የላቀ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እየጨመሩ በመጡበት ሁኔታ የጤና አጠባበቅ እና የማዘመን ወይም ማሻሻል ሥርዓቶች ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል። በዚህ ረገድ መረጃ፣ ቅኝት እና ምርምር፤ የጤና አገልግሎት አስተዳደር፤ የሰው ኃይል፤ እንዲሁም የጤና ፋይናንስ ትኩረት የሚሰጣቸው የጤና ሥርዓቶች ናቸው።

13. **በምርታማነት እና ቅልጥፍና የሚረጋገጥ የኢኮኖሚ ልማት ግብ ማሕበራዊ ፍትህን ማረጋገጥ ነው።** በማሕበራዊ ልማት ረገድ የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ በዋናነት ማሕበራዊ ፍላጎቶችን በራስ ኢኮኖሚያዊ አቅም የማሟላት ዓለማን ማሳካት ነው። የተለያዩ በጾታ፣ እና በዕድሜ በመሳሰሉ ምድቦች የሚገለጹ የማሕበረሰብ ክፍሎች ከተሳትፎ የላቀ በኑሯቸው የመወሰን አቅም (empowerment) እንዲኖራቸው ይደረጋል። በተደራሽነት፣ በፍትሃዊነት፣ በብዝሃነት፣ በአሳታፊነት፣ እና በሰብዓዊ መብት የሚገለጹ የማሕበራዊ ፍትህ ግቦች ትኩረት ይሰጣቸዋል። ከዚህም በላይ በገበያ ጉድለቶች፣ በደራሽ ደፋቂ ኩነቶች፣ እንዲሁም በዕድሜ፣ በጾታ፣ እና በመሳሰሉት ማሕበራዊ መገለጫዎች የሚንጸባረቁ ክፍተቶችን በማሕበራዊ ጥበቃ ወይም ከለላ (social protection) ማዕቀፍ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል። የማሕበራዊ ጥበቃ ማሕበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ፣ ማሕበራዊ ድጋፍን ለሚገባቸው በማቅረብ፣ ማሕበራዊ ዋስትናን ለተጋላጭ ዜጎች በማስፈን፣ እንዲሁም ሰብዓዊ መብት እና አካታችነትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ተደራሽ ለማድረግ ማበሕበራዊ ማበረታቻን ዕውን በማድረግ ማዕቀፎች ተተግባሪ ይሆናል።

14. **ትምሕርት የማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግቦች ማረጋገጫ ዋና መሣሪያ ነው።** የኢኮኖሚ ልማት፣ ማሕበራዊ ልማት፣ እንዲሁም አጠቃላይ ማሕበረሰባዊ ንቃት በሣይንሳዊ ዕውቀት ላይ ይመሠረታል። ከዚህ አንጻር ሣይንሳዊ ዕውቀትን ለችግሮቹ መፍቻ መሣሪያ ማድረግ የሚችል ማሕበረሰብ በመፍጠር ረገድ ትምሕርት የማይተካ ሚና አለው። ለዚህም ተደራሽነትን ከጥራት ጋር ያገናዘብ እና ግብ ተኮር የሆነ ቀልጣፋ የትምሕርት ሥርዓት በማስፈን ትርጉም ያለው እና አሻጋሪ ዕውቀት ለመገንባት ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል።

15. **ዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓት በምርታማነት እና ቅልጥፍና ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ልማት ማሳለጫ፣ የማሕበራዊ ፍትሕ ማረጋገጫ እና የመልካም እሴቶች ባለቤት የሆነ ርትዕ ማሕበረሰብ ለመገንባት የመግሪያ ሥርዓት ነው።** ቅልጥፍና እና ምርታማነት የሚረጋገጠው ያለ ውድድር ኪራይ ከሚሰበስቡ እና ሲከፋም ባልተገባ መንገድ በአቋራጭ ከሚበለጽጉ ተዋንያን ሳይሆን በላባቸው እና ዕውቀታቸው ከሚታትሩ ዜጎች ነው። ያልተገባ አቋራጭ ብልጽግና ገዢ ስትራቴጂ ከሆነ አገራዊ ልማት ከመሳካቱ በፊት የጋራ ውድቀት ይከተላል። የተሳካ የፍትሕ ሥርዓት አንዱ ሚናም በውድድር እና በራስ ጥረት ለልማት የሚተጉ ዜጎችን ከኪራይ ሰብሳቢ ስጋቶች መታደግ ነው። ሰላም እና ጸጥታ፣ በሰፊው አውድም ማሕበራዊ ፍትህ የላቀ ፍትህን ተደራሽነትን፣ የሕግ የበላይነትን እና የዳኝነት ነጻነትን ከተጠያቂነት ጋር በማስፈን በሚገነባ ዘመናዊ የሕግ ሥርዓት ይረጋገጣሉ።

## የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ

16. የክልሉን የመልማት አቅም፣ በየደረጃው ሊቀነስ የታሰበውን የድህነት መጠን፣ የአገራትን ተሞክሮ፣ እና ቴክኒካዊ አግባብነት ግምት ውስጥ በማስገባት የአማራ ብሔራዊ ክልል ኢኮኖሚ በክልል አቀፍ ምርት ሲለካ ከ2018 እስከ 2042 ባሉት ሃያ አምሥት ዓመታት በአማካይ በ10.2 በመቶ እንዲያድግ ግብ ተጥሏል። የፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት (የ10.2 በመቶ አማካይ ክልላዊ ምርት ዕድገት ወይም የ8.8 በመቶ የነፍስ ወከፍ ክልላዊ ምርት ዕድገት) ድህነትን በአንድ ትውልድ ትርጉም የለሽ ለማድረግ ያስችላል። በመጀመሪያዎቹ አምሥት ዓመታት ለዘመናዊ ግብርና በሚሰጠው ትኩረት እና በገጠር ልማት ንቅናቄ የገጠር ድህነት ትርጉም ባለው ደረጃ እንዲቀንስ ታቅዷል። እነዚህ ጥረቶች ከከተማ ልማት ንቅናቄዎች ጋር ተዳምረው በ10.6 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ከድህነት ወለል በታች የሚኖርን ሕዝብ ምጣኔ ወደ 15 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ተከታታይ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ የተሰሉትም የድህነት ምጣኔን በመጀመሪያው የአምሥት ዓመት የዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 15 በመቶ፣ በሁለተኛው የዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 10 በመቶ፣ በሦስተኛው የዕቅድ ዘመን መጨረሻ ደግሞ ወደ 5 በመቶ ለማውረድ በሚያስችል መልኩ ነው።

17. ሠንጠረዥ 3-1፤ የሃያ አምሥት ዓመት የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦች

| | አፈጻጸም | አማካይ የዕድገት ምጣኔ ዕቅድ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013-16 | 2018-22 | 2023-27 | 2028-32 | 2033-37 | 2038-42 | 2018- 42 |
| **ክልላዊ ጥቅል ምርት** | **5.1** | **10.6** | **10.4** | **10.9** | **10.4** | **8.5** | **10.2** |
| ግብርና | 3.4 | 8.8 | 6.4 | 5.6 | 3.6 | 2.6 | 5.4 |
| ኢንዱስትሪ | 6.9 | 16.2 | 14.7 | 13.4 | 12.3 | 9.5 | 13.2 |
| *አምራች ኢንዱስትሪ* | *16.1* | *17.5* | *15.7* | *14.0* | *13.6* | *11.0* | *14.4* |
| አገልግሎት | 7.5 | 10.1 | 12.7 | 14.1 | 13.2 | 10.3 | 12.1 |
| | | ተያያዥ ግቦች | | | | | |
| የነፍስ ወከፍ ምርት ዕድገት ምጣኔ (%) | 3.6 | 9.1 | 9.0 | 9.5 | 9.1 | 7.4 | 8.8 |
| የክልሉ የድህነት ምጣኔ (%)* | | 15.0 | 10.0 | 5.0 | 1.0 | 1.0 | |
| የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ (%) | 1.5 | 1.5 | 1.4 | 1.4 | 1.3 | 1.1 | 1.4 |

*የድህነት ምጣኔ ግቦች የየአምሥት ዓመታት ዕዶች መጨረሻ ዓመት ላይ የሚደረስባቸው ናቸው።

18. ይህ ፈጣን ዕድገት በአንድ ትውልድ ጊዜ ማለትም በ25 ዓመታት ክልላዊ ምርትን በ14 እጥፍ፣ የነፍስ ወከፍ ገቢን ደግሞ በአሥር እጥፍ የማሳደግ አቅም ያለው ሲሆን፣ በዚህ መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2013 ቋሚ የመግዛት አቅም ሲሰላ በ2042 ወደ 20,270 ዓለም አቀፍ ዶላር ይደርሰላ። በዚህ ወቅት የአማራ ብሔራዊ ክልል እንዲሁም ኢትዮጵያ እንደ አገር ለከፍተኛ መካከለኛ ገቢ አገራት አማካይ ገቢ የቀረበ የነፍስ ወከፍ ገቢ ይኖራቸዋል። የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት በታቀደለት ፍጥነት ማደግ ከቻለ በ2040 የክልሉ ገቢ ዝቅተኛ ከመካከለኛ ገቢ አገራት አማካይ ገቢ በላይ ይሆናል።

19. ስዕል 5-2፤ የነፍስ ወከፍ ክልላዊ ምርት መዳረሻ በ2013 የዓለም አቀፍ ዶላር የመግዛት አቅም




ምንጭ፥ የዓለም ባንክ እና የአብክመ ፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃዎችን በመጠቀም የተሰላ

20. የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔዎቹ ፍጥነት ድህነትን ለመቀነስ ከሚኖር ግብ ባለፈ በቴክኒክ ደረጃ የሚቻሉ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት። አንዱ የማረጋገጫ ዘዴ የቋሚ ግብዓቶች በተለይም የሠራተኛ፣ የካፒታል እና የነገራተ-ምርቶች ምርታማነት (total factor productivity) እድገት ምጣኔ ተዓማኒነት ነው። በዚህም መሠረት የነገራተ - ምርት ምርታማነት ዕድገት ከ4 በመቶ በማይበልጥበት፣ የካፒታል - ምርት ጥምርታ (incremental capital – output ratio - ICOR) አማካይ 2.5 በሚሆንበት አግባብ ታቅዷል። የክልል አቀፍ መዋዕለ - ንዋይ ወይም የካፒታል ክምችት ምጣኔ ከክልል አቀፍ ምርት ያለው ድርሻ በመጀመሪያው አምሥት ዓመት 36.3 በመቶ፣ በዕቅድ ዘመኑ ማገባደጃ ደግሞ 40.5 እንዲሆን ታቅዷል። በዚህም መሠረት የየአምሥት ዓመታቱ የመዋዕለ - ንዋይ ምጣኔ ከክልል ምርት አንጻር ታቅዷል (ሠንጠረዥ 6 -3)።

21. ሠንጠረዥ 3-2፤ የመዋዕለ - ንዋይ ምጣኔ ግምት

| | 2018-22 | 2023-27 | 2028-32 | 2033-37 | 2038-42 | 2018-42 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ክልላዊ ምርት ዕድገት (%) | 10.6 | 10.4 | 10.9 | 10.4 | 8.5 | 10.2 |
| ዕልቀት (%) | 5.0 | 5.0 | 5.0 | 5.0 | 5.0 | 5.0 |
| የካፒታል - ምርት ጥምርታ | 2.2 | 2.4 | 2.4 | 2.5 | 3.0 | 2.5 |
| **(የመዋዕለ-ንዋይ ምጣኔ (% ከምርት)** | **36.0** | **37.0** | **38.2** | **38.5** | **40.5** | **37.6** |

## 5.3. የመዋቅራዊ ለውጥ ግብ

22. የማይቀለበስ ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ዋስትና የሚሆነው የተሳካ መዋቅራዊ ለውጥ ሲረጋገጥ ነው። የተሳካ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረግ የቻሉ በርካታ አገራት ልምድን በመቀመር እንደ ክልሉ የዕድገት ደረጃ መፈጠር ያለበትን የመዋቅራዊ ለውጥ ስብጥር የዘርፎችን ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ምርት የሚኖረውን ድርሻ (static contributions)፣ ለክልላዊ ምርት ዕድገት ዘርፎች የሚኖራቸውን አስተዋጽዖ (dynamic contributions)፣ እና የሠራተኛ ኃይል የዘርፍ ስምሪት ስብጥር በመጠቀም ተመላክቷል።

23. በዚህም መሠረት የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2016 ከተመዘገበው 51.9 በመቶ በ2042 ወደ 17 በመቶ እንዲቀንስ የታቀደ ሲሆን፣ የኢኮኖሚውን ፍጥነት እንዲመራ የሚፈለገው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት በተመሳሳይ ወቅት ከ9.4 በመቶ ወደ 25 በመቶ እንዲደርስ ታቅዷል። በተመሳሳይ ወቅት የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የማዕድን እና ኳሪንግ፣ የውሃ እና ኤሌክትሪክሲቲ፣ እና የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፎች የተካተቱበት አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ምርት የሚኖረው ድርሻ ከ16.2 በመቶ ወደ 33 በመቶ እንዲያድግ ግብ ተጥሏል።

24. ሠንጠረዥ 3-3፤ የዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ጥቅል ምርት የሚኖረው ድርሻ

| | **መነሻ** | **የዘርፎች ድርሻ ከአጠቃላይ ክልላዊ ምርት (%)** | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2022 | 2027 | 2032 | 2037 | 2042 |
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 51.9 | 47.4 | 39.4 | 30.9 | 22.5 | 17.0 |
| *ሰብል* | *35.0* | *31.9* | *27.0* | *18.5* | *13.0* | *8.2* |
| *የእንስሳት ሀብት* | *12.3* | *10.5* | *11.2* | *10.5* | *7.9* | *8.0* |
| ኢንዱስትሪ | 16.2 | 21.4 | 25.9 | 28.9 | 31.5 | 33.0 |
| *አምራች ኢንዱስትሪ* | *9.4* | *13.3* | *16.8* | *19.3* | *22.3* | *25.0* |
| *ኮንስትራክሽን* | *6.0* | *7.5* | *8.4* | *8.9* | *8.4* | *7.2* |
| አገልግሎት | 33.4 | 32.6 | 36.2 | 41.6 | 47.1 | 51.0 |
| **ክልላዊ ምርት*** | **101.5** | **101.4** | **101.0** | **101.0** | **101.0** | **101.0** |

*የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች፣ የኢንዱስትሪ፣ እና አገልግሎት ተጨማሪ ዕሴት ድርሻዎች ድምር 100 በመቶ አይሰጥም። ለዚህ ምክንያቱ በክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ (Regional Accounts) ስሌት ስነ ዘዴ፣ ክልላዊ ምርት ከዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት ድምር በተዘዋዋሪ በሚሰላ የፋይናንስ ተቋማት የማሳለጫ አገልግሎት ክፍያ (Financial Intermediation Services Indirectly Measured – FISM) መጠን ልክ ስለሚያንስ ነው።

25. ስዕል 5-3፡ የመዋቅራዊ ለውጥ ግቦች፤ የዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት ከክልል ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ




26. የአምራች ኢንዱስትሪ ከክልላዊ ምርት የሚኖረው ድርሻ በሂደት እየጨመረ ከግብርናው ዘርፍ ድርሻ መብለጥ ካለበት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት መፍጠን እና ከአጠቃላይ የክልል አቀፍ ምርት ዕድገት ውስጥ የሚኖረው ድርሻ በዚያው ልክ ከፍ ማለት ይኖርበታል። ነገር ግን የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት ዋና ግብ በምግብ ራስን ከመቻል ባለፈ ለኢንዱስትሪ ግብዓት እና ለወጪ ንግድ ትርፍ ምርት ማምረት ስለሆነ፣ ይህንንም ዕውን ለማድረግ የዘርፉ ዝቅተኛ ምርታማነት ደረጃ ዕድል ስለሚሰጥ በቀጣዮቹ አሥር ዓመታት የግብርና ዘርፍ ለአጠቃላይ ዕድገቱ የሚኖረው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ይሆናል። ከግብርናው ዘርፍ ፈጣን እድገት ትይዩ የአምራች ዘርፉ በፍጥነት በማደግ ከ10 ዓመታት በኋላ የዕድገት መሪነቱን ከግብርና ይረከባል። በዚህም መሠረት ከ2018 – 2022 ባሉት አምሥት ዓመታት ከ10.6 በመቶ የክልሉ ምርት ዕድገት ውስጥ 4.5 የመቶኛ ነጥብ ወይም የዕድገቱ 42.5 በመቶ የግብርና ድርሻ ሲሆን፣ በተመሳሳይ የዕቅድ ዘመን የአምራች ኢንዱስትሪ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ 1.6 የመቶኛ ነጥብ ወይም የክልላዊ ምርት ዕድገቱን 15 በመቶ ይይዛል። በአንጻሩ በሦስተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ (2028 – 32)፣ ከ10.9 ክልላዊ ምርት ዕድገት ውስጥ ግብርና 2 የመቶኛ ነጥብ፣ አምራች ኢንዱስትሪ ደግሞ 2.8 የመቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ በማድረግ የኢኮኖሚውን ዕድገት ይመራል። በዚህ ዕቅድ ውስጥ ከእነዚህ አኀዞች በተሰሉት ልክ የመሳካት ደረጃ (precision) ይልቅ የዘርፎችን የሚና ለውጥ የሚያመላክቱ መሆናቸውን ማጤን ይገባል።

27. ሠንጠረዥ 3-4፤ የዘርፎች የዕድገት አስተዋጽዖ

| | ምዝን የዕድገት ምጣኔ (weighted growth rates) በመቶኛ ነጥብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **አፈጻጸም** | **ዕቅድ** | | | | |
| | 2012-16 | 2018-22 | 2023-27 | 2028-32 | 2033-37 | 2038-42 |
| ግብርና | 1.8 | 4.5 | 2.8 | 2.0 | 1.0 | 0.7 |
| ኢንዱስትሪ | 1.1 | 3.0 | 3.4 | 3.6 | 3.7 | 3.1 |
| *አምራች ኢንዱስትሪ* | *1.2* | *1.9* | *2.3* | *2.5* | *2.8* | *2.6* |
| አገልግሎት | 2.4 | 3.3 | 4.3 | 5.4 | 5.8 | 4.8 |
| **ክልላዊ ጥቅል ምርት** | **5.1** | **10.6** | **10.4** | **10.9** | **10.4** | **8.5** |

28. የመዋቅራዊ ለውጥ ሦስተኛው ማሳያ የዘርፎች የሠራተኛ ስምሪት ሲሆን በግብርናው ዘርፍ የተሰማራው የሠራተኛ ኃይል በ2013 ከነበረበት 66.4 በመቶ በ2042 ወደ 30 በመቶ እንዲቀንስ ታቅዷል። በአንጻሩ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ድርሻ በ2013 ከተመዘገበው 3.3 በመቶ በ2042 ወደ 21 በመቶ እንዲጨምር በእቅድ ተይዟል። የአገልግሎት ዘርፍ የሰው ኃይል ስምሪት ድርሻ በ2013 የዳሰሳ ጥናት ወቅት 27.5 ሲሆን በእቅዱ ዘመን መጨረሻ 43.9 እንደሚሆን በዕቅድ ተመላክቷል።

29. ሠንጠረዥ 3- 5፤ የዘርፎች የሰው ኃይል ስምሪት እቅድ

| | | መነሻ | ዕቅድ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | 2022 | 2027 | 2032 | 2037 | 2042 |
| **የሠራተኛ ኃይል ድርሻ** | ግብርና | 66.4 | 57.1 | 52.5 | 46.3 | 38.2 | 30.0 |
| | አምራች ኢንዱስትሪ | 3.3 | 6.9 | 10.3 | 14.9 | 17.5 | 21.0 |
| | ሌሎች ኢንዱስትሪዎች | 2.8 | 3.4 | 3.8 | 4.2 | 4.6 | 5.1 |
| | አገልግሎት | 27.5 | 29.8 | 31.1 | 33.6 | 38.0 | 43.9 |
| | | | | | ትንበያ | | |
| **የከትመት ምጣኔ** (%) | | 19.6 | 27.8 | 33.9 | 41.2 | 50.1 | 61.0 |

30. ግራፍ 5- 4፡ የመዋቅራዊ ለወጥ ግቦች፡ የሰው ኃይል ስምሪት



# ምዕራፍ ስድስት

# ርዕይ እና ስትራቴጂክ ምሰሶዎች

## ርዕይ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምሥት ዓመት ልማት መነሻ የሆነው ርዕይ የክልሉ የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ርዕይ ነው። የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ መዳረሻ ርዕይ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ አቅም እና ሁለንተናዊ ብልጽግና ነው። ይህ የአንድ ትውልድ ርዕይ በ2042 የአማራ ብሔራዊ ክልል በዓለም በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ የሆነ የዘመናዊ ኢኮኖሚ አቅም ባለቤት ሆኖ ማየት ነው። የዚህ ርዕይ ማስፈጸሚያ የመጀመሪያ ርከን የሆነው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ መዳረሻ በ2022 የአማራ ብሔራዊ ክልል በወሳኝ ዘርፎች ንቅናቄ ለኢኮኖሚ ልማት መመንጠቅ አስተማማኝ መሠረት የጣለ እና የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆኖ ማየትን ያለመ ነው።

## ተልዕኮ

2. የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ የአፈጻጸም ዘመን ተልዕኮ ሁሉንም የክልሉ የልማት ኃይሎች፣ በአገሪቱ ክልሎች እና በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎችን በተቀናጀ መንገድ በማሳተፍ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ እና በእውቀት መር የኢኮኖሚ ልማት በመታገዝና ያለውን ፀጋ በላቀ ደረጃ በመጠቀም፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን በዘላቂነት በማረጋገጥ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትና ለአገሪቱ ልማት ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ የሚያበረክት ዕድገት በክልሉ ማምጣት ነው።

## ስትራቴጅካዊ ምሰሶዎች

3. **የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ማረጋገጥ፤** የክልሉን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ችግርን በውይይት የመፍታት ልምምድን ማሳደግ፣ የክልሉን የመደራረደር አቅም ማጎልበት፣ የሽግግር ፍትህን መተግበርና ክልሉ ሚናውን በሚጠበቅበት ደረጃ እንዲወጣ ማድረግ፣ ሀገራዊ ምክክርን ማጠናከር፣ የፍትህና የፀጥታ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚገባ እንዲወጡ ማስቻል፣ የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ መንግስት ላይ ያለቸው አመኔታ እንዲጨምር ማድረግ እንዲሁም ምክር ቤቶች የህዝብ ውክልናቸውን በተገቢው መንገድ እንዲወጡ ማድረግ በዕቅድ ዘመኑ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

4. **ክልላዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፤** ክልላዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት ከሥርዓታት አንፃር የመንግሥት፣ የማሕበረሰብ፣ የትምህርት ተቋማት፣ የዕምነት ተቋማት፣ የልሂቃን (የፖለቲካና የኢኮኖሚ) እና የሚድያ ተቋማት ስርዓታትን በማጠናከር በተጨማሪም በታሪክ ፣በባህል፣ በፖለቲካል ኢኮኖሚ እሴቶቻችንን ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን አድርጎ በስፋት መስራት ያስፈልጋል።

5. **ሣይንሳዊ ዕውቀትን የርትዕ ማሕበረሰብ እሴት እና የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ማድረግ፣** የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት እና ለዘመኑ የሚመጥን ዲጂታል ዝግጁነትን በማሳደግ ሀብት ፈጠራን መሰረት ያደረገ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት ያስፈልጋል።

6. **ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በማሳደግ ጥራት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት፤** ምርታማነትንና ቅልጥፍናን ማሳደግ ላይ መሰረት ያደረገ ዘመናዊ ግብርና አምራች ኢንዱስትሪ ትኩረት በማድረግ ጥራትና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት ያስፈልጋል።

ክፍል ሦስት

# የጥቅል ኢኮኖሚ ማዕቀፍ

## (2018 – 2022)

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሰባት | **ዓላማ፣ ግቦች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የትኩረት መስኮች** |
| ምዕራፍ ስምንት | **ዋና ዋና የጥቅል ኢኮኖሚ ግቦች** |

# ምዕራፍ ሰባት

# ዓላማ፣ ግቦች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የትኩረት መስኮች

## 7.1. የዕቅዱ ዓላማዎች

1. የአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ በፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ ፍትሃዊ እና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ ነው። የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች
    1. ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን መሠረት ያደረገ ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ፣
    2. ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ ከአንድ ትውልድ በኋላ ድህነትን ትርጉም የለሽ ለማድረግ መሠረት መጣል፣
    3. ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነትን በየደረጃው ማረጋገጥ፣
    4. የተረጋጋ የጥቅል ኢኮኖሚ አውድ መፍጠር፣
    5. በመልሶ ግንባታ ለረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ አቅም እና የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት መሠረት መጣል፣
    6. ጤናማ፣ በሣይንሳዊ ዕውቀት እና መልካም እሴቶች የተገነባ ርትዕ ማሕበረሰብ መፍጠር፣
    7. ማሕበራዊ ፍትህ ማስፈን፣
    8. ምቹ እና ዘላቂ የመኖሪያ እና የሥራ ቦታ በገጠር እና በከተማ መፍጠር፣
    9. በማልማት፣ በመንከባከብ እና በመጠበቅ ሚዛን ዘላቂ አካባቢን ማረጋገጥ ናቸው።

## 7.2. የዕቅዱ ግቦች

2. የዕቅዱ ጥቅል ግቦች የሚከተሉት ናቸው፤
    1. ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት (ከ10.6 በመቶ) በማስመዝገብ የመካከለኛ ገቢ አገራት አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማረጋገጥ፣
    2. በ2022 ከድህነት ወለል በታች የሚኖርን ሕዝብ ምጣኔ ወደ 15 በመቶ መቀነስ፣ የፈርጀ-ብዙ ድህነት ምጣኔን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣
    3. ሥራ አጥነትን በ2016 ከሚገመተው 9.1 በመቶ በ2022 ወደ 4.0 በመቶ መቀነስ፣
    4. የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ተሳትፎን ከጥራት ጋር በማመጣጠን ማሳደግ፣
    5. በተቀናጀ የጤና ልማት አማካይ በሕይወት የመቆያ ዕድሜን ትርጉም ባለው ደረጃ ከፍ በማድረግ 70 ዓመት ማድረስ ናቸው።

## 7.3. የትኩረት አቅጣጫዎች

3. ከችግሮቹ እና መሠረታዊ ምክንያቶቹ በመነሳት የክልሉ የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፤
    1. ቅልጥፍና እና ምርታማነትን መሠረት በማድረግ በዘመናዊ ግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች እመርታ መፍጠር፣ በውጤቱም ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ጨምሮ የመዋቅራዊ ሽግግር ዓላማዎችን ማሳካት፣
    2. በጥብቅ ክትትል በሚፈጸም ፕላን በሚመራ የከተማ ልማት ለማይቀረው ከፍተኛ የገጠር - ከተማ ሽግግር ለዘላቂ ክትመት ቀድሞ መዘጋጀት፣
    3. በዘርፎች የበጀት አመዳደብ፣ በዘርፎች አቅም እና ቅንጅታዊ አሠራር፣ በየደረጃው ባሉ የአመራር ቁርጠኝነት እና አቅም፣ በማሕበረሰብ ግንዛቤ፣ በተቋማት ሚና፣ እንዲሁም በስትራቴጂ፣ በፖሊሲ እና በሕግ ግልጸኝነት በሚገለጹ የሥርዓታት ርትዕነት ላይ አትኩሮ መሥራት፣
    4. ሰላም፣ ፍትህ እና የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ፣
    5. ከክልል ርዕሰ-መስተዳድር ጽሕፈት ቤት እስከ ቀበሌ ማሕበረሰብ በሚዘልቅ አስተዳደራዊ እና ሕዝባዊ አደረጃጀት መዋቅር ችግርን በወቅቱ መፍታትን ዓላማ ያደረገ ጥብቅ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ማስፈን።

## 7.4. የትኩረት መስኮች

4. በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ (2013 – 2022) የብዝሃ-ዘርፍ ልማት ስትራቴጂ የዘርፎች ትስስር ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና መዋቅራዊ ለውጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በዚህም መሠረት በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት (2018 – 2022)፣

    1. ዘመናዊ ግብርና እና ለጠንካራ የኢንዱስትሪ ልማት፣ ለከተማ የምግብ ፍላጎት መሟላት፣ እና ለገጠር ሽግግር ከፍተኛ ሚና እንዲጫዎት፣
    2. አምራች ኢንዱስትሪ በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት መርህ ወሳኝ የመዋቅራዊ ሽግግር እና የረጅም ጊዜ የአዕድገት ምንጭ እንዲሆን፣
    3. የማዕድን ልማት ዘርፍ በዋናነት የዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ስትራቴጂክ ግብዓቶችን በማበልጸግ እንዲደግፍ፣ እንዲሁም የዘመናዊ ማዕድን ልማት መሠረት እንዲጥል፣
    4. ዘመናዊ ቱሪዝም የክልሉን በዘርፉ የመልማት አቅም ታሳቢ ባደረገ መልኩ በትንሽ ጥረት የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ እንዲሆን፣ እና የአገር ገጽታ ግንባታ ሚና እንዲጫወት፣
    5. የገጠር ልማት በገጠር ሽግግር (rural transformation) መርህ በሰፊ የኢኮኖሚ መሠረት ላይ የቆመ ከከተማ ኑሮ ጋር የሚመጣጠን ምቹ የሥራ እና የመኖሪያ አጋባቢ ማድረግ፣
    6. ከትመት የወደፊቱ የአገራችን እና የክልላችን የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ አውድ እና ማዕከል በመሆኑ ለ21ኛው ክፍለ-ዘመን ስልጣኔ በሚመጥን ደረጃ የከተማ ልማት ዝግጁነት እንዲደረግ፣
    7. መንገድ፣ ኤነርጂ፣ ዘመናዊ ሎጂስቲክስ፣ እና አይሲቲ በመሠረተ-ልማትነት ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ማሕበራዊ ልማት ተደራሽነት ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ፣
    8. ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን በአጠቃላይ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ግብን እንዲያሳካ፣ በተለይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመሠረተ-ልማትነት፣ በቢዝነስ መስከነት እና በቴክኖሎጂ ለውጥ መሣሪያነት ለእውቀት - መር እና ዲጂታል ኢኮኖሚ፣ ለማሕበራዊ ለውጥ፣ ለመንግሥታዊ አገልግሎቶች እና ማሕበራዊ ፍትህ መሳለጥ ዋና መሣሪያ መሆኑን እንዲያረጋግጥ፣
    9. ከኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ግቦች አንጻር በተገቢ የትምህርት እና የሥልጠና ፖሊሲ የታረቀ ሰብዓዊ ልማት እንዲታነጽ፣
    10. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ራስን በመቻል መርህ የዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ልማት መሠረት እንዲሆን፣ እንዲሁም
    11. የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የፍትህ ሥርዓት እና መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ፤ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዘርፎች የትኩረት መስክ እንዲሆኑ ታቅዷል።

5. ለእነዚህ መስኮች የሚሰጠው ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ ለሁሉም ዘርፍ አንቀሳቃሽ ለሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የዘመናዊ ግብርና፣ የግብዓት ማዕድን፣ ቴክኖሎጂ እና የትምህርት እና ሥልጠና ዘርፎች የተለየ ትኩረት ይደረጋል።

# ምዕራፍ ስምንት

# ዋና ዋና የጥቅል ኢኮኖሚ ግቦች

## 8.1. የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ

1. ከ2018 እስከ 2022 ባሉት አምሥት ዓመታት የክልሉ ኢኮኖሚ በአማካይ በ10..6 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል። ይህ የዕድገት ምጣኔ የክልሉ ኢኮኖሚ በአለፉት ሦስት ዓመታት በ4.9 በመቶ ብቻ በማደግ ካሳየው መቀዛቀዝ የሚኖረውን የማገገሚያ አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። የ10.6 በመቶ ዕድገት ምጣኔም በክልሉ በአሁኑ ወቅት ይኖራል ተብሎ የሚገመተውን የ21 በመቶ የድህነት ምጣኔ (ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ሕዝብ መጠን በመቶኛ) በ2022 ወደ 15 በመቶ ለመቀነስ የሚያስችል ነው።

2. ስዕል 8-1፡ የ10.6 በመቶ የክልላዊ ምርት ዕድገት ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ ያስችላል።




የ1.5 በመቶ የሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔን ታሳቢ በማድረግ የ10.6 በመቶ የክልላዊ ምርት ዕድገት የ9.1 በመቶ የነፍስ ወከፍ ክልላዊ ምርት ዕድገት ያስገኛል። ይህም ማለት የአንድ አማካይ የክልሉ ነዋሪ ገቢ በአማካይ በዓመት በ9.1 በመቶ ይጨምራል። የ7 በመቶ የነፍስ ወከፍ ገቢ የድህነት ምጣኔን በ1 መቶኛ ነጥብ እንደሚቀንስ ታሳቢ በማድረግም ይህ የ9.1 በመቶ የነፍስ ወከፍ ክልላዊ ምርት ዕድገት በአምሥት ዓመት ውስጥ ድህነትን ከ21 በመቶ ወደ 15 በመቶ ለመቀነስ ያስችላል።

3. የክልላዊ ዕድገት ምንጮች በጥቅል ኢኮኖሚ ደረጃ የሰው ኃይል፣ የካፒታል፣ እና ነገራት - ምርት ዕድገት (total factor productivity – TFP) ነው። ከ10.6 በመቶ ዕድገት ውስጥ 1.8 በመቶ ከሠራተኛ ኃይል ዕድገት፣ 4.8 በመቶ ከካፒታል እድገት፣ እና ቀሪው 4.0 በመቶ ደግሞ ከምርታማነት ዕድገት እንደሚገኝ ታሳቢ ተደርጓል። እነዚህ አኀዞች አመላካች እና በአብዛኛው የ10.6 በመቶ ዕድገት ቢያንስ በምጣኔ ሀብት ሳይንስ ቴክኒካዊ እሳቤ ረገድ ተደራሽ መሆኑን መረጋገጫ ናቸው።

4. የክልሉ የሰው ኃይል ከ2005 ጀምሮ ለአለፉት ዘጠኝ ዓመታት በአማካይ በዓመት ከ1 በመቶ በታች ሲያድግ የነበረ ሲሆን የአገር አቀፉ የሰው ኃይል ዕድገት ምጣኔ ደግሞ በ1 በመቶ አካባቢ ሲያድግ ነበር። ነገር ግን በክልሉ በሥራ ላይ የሚገኝ ኃይል ጭማሪ ከማሳየት ይልቅ የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል። ከሥራ የሚወጣውም ሆነ አዲስ ወደ ኢኮኖሚው የሚገባ እድሜው ለሥራ የደረሰ ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆነ ኃይል በአብዛኛው በፍልሰት፣ በኃብቻ፣ እና በሃዋላ አማራጭ የገቢ ምንጭ ከሠራተኛ ኃይል ውጪ ሆኗል። የ2 በመቶ የሰው ኃይል ዕድገትም በእነዚህ በተጠቀሱ ምክንያቶች ከሰው ኃይል ማዕቀፍ ውጪ የሆነውን ኃይል ወደ ሥራ እንደሚሰማራ ታሳቢ አድርጓል። ልዩ የስልጠና ፍላጎቶችም ከሌላ አካባቢ የሰው ኃይል ቅጥር እንደሚኖር ይጠበቃል።

5. የክልሉ ኢኮኖሚ በአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የካፒታል ተጠቃሚነት ደረጃው በጣም ዝቅተኛ ነው። በዘመናዊ ግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪው የሚደረጉ የመዋዕለ -ንዋይ ስምሪቶች የካፒታል ክምችትን በፍጥነት ያሳድጋሉ፤ በትንሽ የካፒታል ዕድገትም ከፍ ያለ ምርት ማስገኘት እንደሚቻል ታሳቢ ተደርጓል። ካፒታልን በሠራተኛ ኃይል እድገት ምጣኔ ልክ ብቻ ማሳደግ እስከሚቻልበት አነስተኛው

ምጣኔ ድረስ መዋዕለ - ንዋይ ወይም ተጨማሪ ካፒታል ተጨማሪ እድገትን እየፈጠረ እንደሚሄድ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

6. የ4.0 በመቶ የነገራተ - ምርት (TFP) ዕድገት ከአገራት ተሞክሮ አንጻር ከፍ ያለ ቢመስልም በአምሥት ዓመታት የመካከለኛ ጊዜ ከቴክኖሎጂ ለውጥ በላይ ከአቅም በታች የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በኃይል አቅርቦት መሟላት ምክንያት እንደሚጨምሩ፣ በመስኖ መሠረተ-ልማት ምክንያት በበርካታ የሰብል ልማት አካባቢዎች በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ ማምረትን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርት በሄክታር ቴክኖሎጂው ከሚፈቅደው በታች እርቆ መገኘቱ በትንሽ ትረት ምርታማነት ስለሚጨምር የነገራተ-ምርት በዚህ ደረጃ መታሰቡ ተገቢ ነው፡፡

7. የክልሉን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የሚመራው የግብርናው ዘርፍ ነው፡፡ የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች ተጨማሪ እሴት በአማካይ በዓመት በ8.8 እንዲያድግ የታቀደ ሲሆን፣ ይህም ማለት ከ10.6 በመቶ የክልል አቀፍ ምርት ዕድገት ውስጥ 4.6 መቶኛ ነጥብ ወይም የክልል አቀፍ ጥቅል ምርት ዕድገቱ 43.4 በመቶ የግብርና ዘርፍ አስተዋጽዖ ይሆናል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከፍተኛው የዕድገት አስተዋጽዖ የሚጠበቀው ከሰብል ንዑስ ዘርፍ ነው፡፡

8. ሠንጠረዥ 8- 1፤ የክልላዊ ምርት እና የዘርፎች ዕድገት ምጣኔ ዕቅድ (2018 – 2022)

| | የ2013–2016 የዕድገት ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ | የ2018-2022 የዕድገት ዕቅድ በመቶኛ | ምዝን ዕድገት በመቶኛ ነጥብ (ዕቅድ) |
|---|---|---|---|
| **ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች** | **3.4** | **8.8** | **4.5** |
| የሰብል ምርት | 3.5 | 8.7 | 3.0 |
| የእንስሳት ሀብት ምርት | 1.7 | 7.7 | 0.9 |
| **ኢንዱስትሪ** | **6.9** | **16.2** | **3.0** |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 16.1 | 17.5 | 1.9 |
| ኮንስትራክሽን | -2.2 | 14.7 | 1.0 |
| **አገልግሎት** | **7.5** | **10.1** | **3.3** |
| **ጥቅል ክልላዊ ምርት** | **5.1** | **10.6** | **10.6** |
| **ክልላዊ የነፍስ ወከፍ ምርት** | **3.6** | **9.1** | |

9. የኢንዱስትሪው ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በ16.2 በመቶ እንዲያድግ የታቀደ ሲሆን ይህም ለ10.6 በመቶ የክልል አቀፍ ምርት ዕድገት የ3.0 መቶኛ ነጥብ (የዕድገቱን 28.3 በመቶ) አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው ተጨማሪ እሴት ዕድገት ምጣኔ 17.5 በመቶ እንዲሆን የታቀደ ሲሆን ይህ ፍጥነት በሁለተኛው የአመሥት ዓመት ዕቅድ አጋማሽ የአምራቸ ኢንዱስትሪው የኢኮኖሚውን ዕድገት መሪነት ከግበርና ለመረከብ ያስችለዋል፡፡ የአገልግሎት ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በጥቅሉ በ10.1 በመቶ እንዲያድግ ግብ ተጥሏል፡፡

## 8.2. የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ

10. የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጨው በሂደት የግብርና ዘርፍ ከጥቅል ምርት ያለው ድርሻን መቀነስ፣ በምትኩ የአምራች ኢንዱስትሪውን ድርሻ መጨመር ነው፡፡ በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት ግን ክልሉን በምግብ ራሱን የማስቻል ግብ እንዲሳካ በሚኖረው ሚና ግብርና የኢኮኖሚውን ዕድገት ፍጥነት ይመራል፡፡ ነገር ግን፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚኖረው የ17.5 ፈጣን ዕድገት ምክንያት የንዑስ ዘርፉ ተጨማሪ እሴት ለክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2016 ከነበረበት 9.4 በመቶ በ2022 ወደ 13.3 በመቶ ሲጨምር፣ በአንጻሩ የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ድርሻ በ2016 ከነበረበት 51.9 በመቶ በ2022 ወደ 47.4 በመቶ እንደሚወርድ ይጠበቃል፡፡ በተለይም የሰብል ንዑስ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከጥቅል ክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2016 ከነበረበት 35 በመቶ በ2022 ወደ 31.9፣ የእንስሳት ሀብት ንዑስ ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ድርሻ ደግሞ በ2016 ከነበረበት 12 በመቶ በ2022 ወደ 10.5 በመቶ ዝቅ እንደሚል ግብ ተጥሏል፡፡

## 8.3. መዋዕለ ንዋይ እና ቁጠባ

11. መዋዕለ-ንዋይ የዕቅዱ ማስፈጸሚያ እና ማረጋገጫ ዋና መሣሪያ ነው፡፡ በአምስት ዓመቱ የዕቅድ ዘመን የመዋዕለ -ንዋይ ምጣኔ ከክልላዊ ጥቅል ምርት በአማካይ 36 በመቶ ይሆናል፡፡ በዚህ ምጣኔ መሠረት የኢኮኖሚ ዕድገት

ግቡን ለማሳካት በአጠቃላይ በአምሥት ዓመቱ ውስጥ በጊዜው ዋጋ 5.774 ትሪሊየን ብር መዋዕለ-ንዋይ ያስፈልጋል። ይህ መጠን በግብርናው ዘርፍ የአርሶ አደሩን የግብርና እንቅስቃሴ፣ አዳዲስ የኮሜርሻል ግብርና መዋዕለ ንዋይን፣ በሌሎች ዘርፎች የሚደረጉ የአነስተኛ፣ ማካከለኛ እና ከፍተኛ የቢዝነስ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። ከዚህ መጠን ውስጥ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ 1.005 ትሪሊዮን ብር መዋዕለ ንዋይ ይጠበቃል። ክልላዊ የቁጠባ ምጣኔ መነሻ የሚሆን መረጃ ባይኖርም በታቀደው የመዋዕለ - ንዋይ ምጣኔ (36 በመቶ) ልክ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። ነገር ግን ጉድለቱ በአገር አቀፍ ደረጃ እና ከውጭ በሚገኝ ቀጥተኛ መዋዕለ ንዋይ እንደሚሸፈን ታሰቢ ተደርጓል።

12. የመዋዕለ-ንዋይ መፍላነት ሲሰላ በካፒታል መጠን፣ በዘርፍ ስምሪት፣ በምንጭ ለመወሰን መነሻዎቹ
    1. የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ
    2. የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ ፍላጎት
    3. የቴክኖሎጂ ግብ
    4. የስትራቴጂካዊ አቅም ግቦች
    5. የተመጣጠነ ቀጠናዊ ልማት ግብ፣
    6. የሀብት መሠረት፣ እንዲሁም
    7. የሥራ ዕድል ፈጠራ ግቦች ናቸው።

13. የፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት እና የመዋቅራዊ ሽግግር ግቦች በተለይ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ በዘመናዊ ግብርና፣ በስትራቴጂካዊ ማዕድናት፣ በአማራጭ ኃይል እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ላይ በግንባር ቀደምትነት ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰሰት እንደሚኖር ያመለክታል። የቱሪዝም፣ የሰብዓዊ ሀብት፣ እንዲሁም የመሠረተ-ልማት ዘርፎች ሌሎቹ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰሰት የትኩረት መስኮች ናቸው። በአምራች ኢንዱስትሪ ረገድ የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የመዋዕለ-ንዋይ የትኩረት ምርቶች በሁለት ደረጃ የሚከፈሉ ሲሆን ገቢ ንግድን መተካት የሚያስችሉ የምግብ ማቀነባበሪያ፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የመዲሃኒት እና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች የአገር ውስጥ ገበያን እንዲሁም የመካከለኛ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ታሳቢ በማድረግ እንዲስፋፉ ይደረጋል። ከዚህም ጎን ለጎን ለከፍተኛ የማሽን እና የፋብሪኬሽን ኢንጂኔሪንግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሶፍት ዌር እና ሀርድ ዌር ምርቶች መሠረት ለመጣል ዝግጅት የሚደረግ ይሆናል። በዘመናዊ ግብርና በምግብ ራስን መቻል ግብ የሚሳካው በኮመርሻል ግብርና በሚደረግ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰሰት ነው።

14. የመዋዕለ-ንዋይ ዋና ስትራቴጂ የአገር ውስጥ ኢንዳስትሪያሊስቶችን መፍጠር፣ በስትራቴጂካዊ መስኮች የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ነው። የአገር ውስጥ አልሚ፣ የልማት ድርጅቶች፣ የውጭ አገር አልሚዎች እንደ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ይሳተፋሉ።

15. መዋዕለ-ንዋይ (investment) በክልሉ አነስተኛ መሆኑ ይታወቃል፤ ከመጠኑ ማነስ ባሻገር የመዋዕለ-ንዋይ መጠን፣ መረጣ፣ የዘርፍ ስምሪት፣ እንዲሁም በወቅቱ የመጠናቀቅ ሁኔታ የፐራት እና የመዋቅራዊ ለውጥ ግቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሚተገበር አይደለም። ሌሎች የዘርፉ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆኖ በተበታተነ ተቋማት መመራቱ ለዘርፎች የሚሰጠውን ተነጻጻሪ ትኩረት ማዛባቱ አልቀረም።

16. በአማራ ብሔራዊ ክልል የቁጠባ ባሕል ያልዳበረ በመሆኑ ፐረት ይጠይቃል። ዋና መሣሪያው ግን የቁጠባን ጥቅም ከማስረዳት ባለፈ ለቁጠባ ገገር ምክንያት የሚሆን ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ግቦች ለማሕበረሰቡ መፍጠር ነው። በተለይ በገጠሩ አካባቢ መኖር ሕይወትን ለማትረፍ አንድ እንጀራ በልቶ ከማደር በላይ መሆኑን ከተሻሻለ የቤት አሠራር እና አያያዝ ጀምሮ ማመላከት ያሻል። ከክልሉ ጋር ቅርብ ትስስር ያላቸው ባንኮች መኖር ለፋይናንሻል ቁጠባ ግቦች መሳካት ትልቅ አበርክቶ ይኖራቸዋል።

17. መዋዕለ-ንዋይን ለመሳብ የቢዝነስ ተወዳዳሪነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ በገበያ አቅም ስፋት፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም በማክሮ ኢኮኖሚ ረገድ ከአበዛኛው ከሰሃራ በታች ያሉ አገራት የተሻለ ተወዳዳሪነት የነበራት ቢሆንም እንደ ከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት ያለው የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጂ ዝግጁነት፣ በመሳሰሉ ወሳኝ መስፈርቶች በአህጉር ደረጃ ሳይቀር አነስተኛ አፈጻጸም አላት። በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመወዳደር በሁሉም መሥፈርቶች መሻሻል ይጠይቃል።
18. ስዕል 8-2፤ የኢትዮጵያ ቢዝነስ ተወዳዳሪነት ደረጃ




ምንጭ፤ ዎርልድ ኢኮኖሚክ ፎረም፣ 2018 (እኤአ)

## 8.4. የሰው ኃይል ፍላጎት

19. በ2013 ብሔራዊ የሠረተኛ ኃይል እና ፍልሰት ዳሰሳ ጥናት መሠረት ዕድሜው ከ10 ዓመት እና በላይ የሆነ ለሥራ ዝግጁ የሆነ ኃይል ብዛት 11,968,296፣ በሥራ ላይ የነበረ ኃይል ደግሞ 11,076,385 ነበር። ይህ ማለት 891,911 የመሆነው ለሥራ ዝግጁ የሆነ ኃይል ሥራ ፈላጊ የነበረ ሲሆን፣ የሥራ አጥነት ምጣነውም 7.5 በመቶ ነበር።  ከዓለም አቀፍ የሠራተኛ ምርታማነት ምጣኔ አኳያ አሁን ያለው የአማራ ብሔራዊ ክልል በሥራ ላይ ያለ ኃይል ብቻ የቻይናን ሠራተኛ 7 እጥፍ፣ የአሜሪካን ሠራተኛ 26 እጥፍ አገራዊ ምርት ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይችል ነበር። ነገር ግን፣ የነፍስ ወከፍ ካፒታል አነስተኛነት፣ የካፒታል የዘርፍ ስምሪት፣ የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ እና የሠራተኛ የስልጠና እና ክህሎት ዝግጁነትን ግምት ውስጥ በማስገባት ኢኮኖሚው አሁን ካለው ሠራተኛ ኃይል በተጨማሪ መቅጠር ይጠበቅበታል። በአሁኑ ወቅት ከክለሉ ውጪ የሚፈልሰው ከፍተኛ የሰው ኃይል እንደሚገታ፣ በክልሉ በተለያዩ ምክንያቶች ከሠራተኛ ኃይል ውጪ የሆኑ በሠራተኛ ዕድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች ወደ ሥራ እንደሚገቡ፣ የተሟሟቀ ልማትን ተስፋ በማድረግ ከሌላ አካባቢ የሚደረግ ገቢ ፍልሰትን፣ እንዲሁም ልዩ የስልጠና ሙያ ያላቸው ዜጎች ከሌላ አካባቢ በውድድር ወደ ሥራ እንደሚገቡ ታሳቢ በማድረግ አጠቃላይ የሠራተኛ ኃይል አቅርቦት በ2018 የምርት ዘመን 12.6 ሚሊዮን፣ በ2022 ደግሞ 13.6 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። ከዚህ ውስጥ በ2018 የምርት ዘመን 11.3 ሚሊዮን፣ በ2022 ደግሞ 12.6 ሚሊዮን ሠራተኛ ኃይል ኢኮኖሚው እንደሚቀጥር ይጠበቃል።

20. በዚህ ስሌት መሠረት በአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን በመነሻ ዓመት ጀምሮ እስከ 2022 ድረስ እስከ 1.57 ሚሊዮን የሚደርስ ተጨማሪ የሰው ኃይል ወደ ሥራ ይሰማራል። ይህም ማለት ኢኮኖሚው በየዓመቱ በአማካይ 314 ሺህ ተጨማሪ የሰው ኃይል ይፈልጋል፣ ወይም ለ314 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ይጠበቅበታል። በአምሥት ዓመት ውስጥ አንድ ዜጋ ቢያንስ ለሦስት ያህል ጊዜ የሥራ ዕድል የሚፈጠርለት ቢሆን፣ በአምሥት ዓመቱ ውስጥ በትንሹ  4.7 ሚሊየን የሥራ ዕድሎች መፈጠር ይኖርባቸዋል። በተመሳሳይ ጊዜም የሥራ አጥነት ምጣኔ  በ2005 እና 2013 መካከል የነበረው ፍኖት ቢቀጥል በ2017 ከሚገመተው 10.9 በመቶ  የበጀት ዓመት በ2022 ወደ 7.3 በመቶ እንዲቀንስ ግብ ተጥሏል። በዚህ ምጣኔ መሠረት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 992 ሺህ ያህል ዜጎች ሥራ ፈላጊ ይሆናሉ። ነገር ግን፣ በተለይ ከ10 እስከ 18 ዓመት ያሉ ወጣቶች የትምሕርት ተሳትፎን ከፍ በማድረግ የሥራ ፈላጊ ቁጥሩን እና የሥራ አጥነት ምጣኔውን ከዚህ በታች ማድረግ እንደሚቻል ይጠበቃል።

21. የዘርፎች የሰው ኃይል ስምሪት በመዋቅራዊ ለውጥ ግብ ላይ የሚመሠረት ሲሆን የግብርና የሰው ኃይል ድርሻ ሲቀንስ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች የሰው ኃይል ድርሻ ይጨምራል።

# ክፍል አራት
# የዘርፎች የልማት ዕቅድ
# (2018 – 2022)

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ግብርና

### 9.1. መነሻዎች

### የዘርፉ ሚና

1. **የአማራ ብሔራዊ ክልል የግብርና ዘርፍ ለበርካታ ዜጎች የኑሮ መሠረት ከመሆኑ  ዕውነታ በላይ በክልሉ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት፣ እና ዋጋ ለማረጋጋት ባለው ድርሻ የሚገለጹ ጉልህ አስተዋጽዖች አሉት።** በ2014 የምርት ዘመን ከአገሪቱ የአዝዕርት ምርት 33.8 በመቶ የአገዳ እና የብርዕ እህሎች፣ 33.1 በመቶ የጥራጥሬ እህሎች፣ 41.1 በመቶ የቅባት እህሎች፣ 18.6 በመቶ የአትክልት ምርት፣ እና 13.2 በመቶ የሥራ ሥር ምርት ሸፍኗል። በተመሳሳይ ዓመት ክልሉ ከኢትዮጵያ የእንስሳት ሀብት የ22.9 በመቶ የቀንድ ከብት፣ የ36.9 በመቶ የጋማ ከብት፣ የ39.5 ዶሮ፣ እና የ22.2 በመቶ የለማ የንብ ሀብት አስተዋጽዖ ነበረው። ከ1998 ጀምሮ በአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ከአጠቃላይ ክልላዊ ምርት ከፍተኛውን ድርሻ በመያዝ ከክልሉ የ7.2 በመቶ ዕድገት ምጣኔ 3.7 የመቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ በማድረግ የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት መርቷል። የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት  ከክልል አቀፍ ምርት በ1998 የምርት ዘመን 62 በመቶ ድርሻ፣ በ2016 ደግሞ 51.9 በመቶ ድርሻ ነበረው። በ2013 የብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል እና ፍልሰት ዳሰሳ ጥናት መሠረት በክልሉ በሥራ ላይ ከሚገኘው ሠራተኛ ኃይል 66.4 በመቶ የሚሆነው በግብርና ዘርፍ የተሰማራ ዜጋ ነው።

2. ከዚህ የመልማት አቅሙ በመነሳት የክልሉ የግብርና ዘርፍ በገጠር የሚኖረውን ከፍተኛ ሕዝብ የመመገብ፣ በክልል እና በአገር አቀፍ ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪውን የጥሬ ዕቃ ፍላጎት፣ እና እያደገ የሚመጣውን የከተማ ሕዝብ የምግብ ፍላጎት የማሟላት፣ በዓለም ላይ እጨመረ የሚመጣውን የምግብ ፍላጎት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የክልሉን እና የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት የመደገፍ፣ በአጠቃላይ ክልል አቀፍ እና አገር አቀፍ ኢኮኖሚውን ወደ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት የማሸጋገር ሚና ይጠበቅበታል።

### የሀብት መሠረት

3. የአማራ ብሔራዊ ክልል ካለው የቆዳ ስፋቱ 180,631.7 ካሬ ኪ.ሜ ወይም 1,806,317 ሄክታር ከሆነ የመሬት ሀብቱ ውስጥ 52.09 በመቶ ያህሉ ለእንስሳት ግጦሽ የሚዉል ሲሆን 33.87 በመቶ ደግሞ ለሰብል ምርት ልማት ሊውል የሚችል ነው፡፡ የአገዳ እና ብርዕ እህሎች፣ የጥራጥሬ እህሎች፣ የቅባት እህሎች፣ አትክልት እና ፍራፍሬን ጨምሮ ለሁሉም ዓይነት ሰብሎች የሚስማማ ከቆላ እስከ ደጋ የሚደርስ የአየር ጠባይ እና ሰፊ መሬት አለው። ክልሉ እስከ አስከአሁን በቅጡ ላልለሙ የትሮፒካል እና ደጋ የፍራፍሬ ምርቶች ልማት የሚሆን አመቺ መሬት እና የአየር ንብረት አለው። በ2014 የምርት ዘመን በክልሉ 4,757,465 ሄክታር መሬት በአዝዕርት ተሸፍኖ ነበር። ከዚህ የለማ መሬት ውስጥ 90.76 በመቶ የሚሆነው በእህል ሰብል ተሸፍኖ የነበረ ሲሆን በድምሩ 110,301,005 ኩዩንታል እህል ተመርቷል። የዚህን መሬት ምርታማነት ዓለም ከደረሰበት 90 ኩዩንታል በሄክታር ማድረስ ቢቻል የእህል ሰብልን ምርት በ3.5 እጥፍ በማሳደግ በተመሳሳይ ዓመት በመላው ኢትዮጵያ ከተመረተው መጠን 20 በመቶ የበለጠ ምናልባትም ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ምርት ማምረት ይቻላል።

4. ክልሉ የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር ውኃ በመጠቀም በመስኖ ሊለማ የሚችል 2.2 ሚሊየን ሄክታር መሬት እንዳለው ይገመታል፡፡ ይህ አቅም የምርት ዑደትን በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ ከፍ በማድረግ እና የግብርና ዘርፉን

ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የግብርና ምርትን ለማሳደግ ተጨማሪ እና ወሳኝ አቅም ነው። በ2014/15 የምርት ዘመን አጠቃላይ በመስኖ የለማው መሬት መጠን 278,134 ሄክታር ብቻ ነው።

5. በእንስሳት ሀብት ብዛት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አንደኛ የመሆኗን ያህል የአማራ ብሔራዊ ክልል ለዚህ ከፍተኛ ቁጥር ከፍተኛ ድርሻ መኖሩ የክልሉን ለእንስሳት ሀብት ልማት ያለውን አመችነት እና አቅም ያሳያል። ይህ አመችነት በክልሉ ከብዛት ይልቅ ወደ እንስሳት ተዋጽዖ ምርታማነት ላይ በማተኮር ለመሥራት ለተወጠነው የዕንስሳት ልማት ስትራቴጂ ትልቅ አቅም ይፈጥራል። የሰብል ንዑስ ዘርፍ ልማት ማሽን ወደሚጠቀም ዘመናዊ አስተራረስ ሲሻገርም በዓመት ከሁለት እስከ አራት ሳምንት እርሻ ለማረስ ብቻ ለዓመታት የሚባክኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በሬዎች በማድለብ ሥልት ወደተሻለ የእንስሳት ለማስገባት አቅም ናቸው።

## የአፈጻጸም ትንተና

6. **ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በ6.1 በመቶ አድጓል።** ይህ ምጣኔ ትልቅ የሚባል ሲሆን ከ7.2 በመቶ የክልሉ ጥቅል ምርት ዕድገት ውስጥ የ3.7 መቶኛ ነጥብ ወይም የዕድገቱን 51.4 በመቶ በመሸፈን ኢኮኖሚውን መርቷል። በተመሳሳይ ወቅት የአዝርዕት እና የእንስሳት ሀብት ልማት ተጨማሪ እሴት፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው በ6.7 በመቶ እና 4.4 በመቶ አድጓል። በተለይ የአዝዕርት ምርት ከ7.2 በመቶ ክልላዊ ምርት ውስጥ 2.6 የመቶኛ ነጥብ ወይም የዕድገት ምጣኔውን 36.1 በመቶ፣ ከግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት ውስጥ ደግሞ 70.3 በመቶ በመሸፈን የኢኮኖሚ ዕድገቱን መርቷል። በአንጻሩ በ2016 ከክልላዊ ምርት 12.3 በመቶ ድርሻ የነበረው የእንስሳት ሀብት በአሥራ ስምንት ዓመት ውስጥ በ4.4፣ ባለፉት አራት ዓመታት ደግሞ በ1.7 በመቶ ብቻ አዝግሟል። ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት ዓመታት ንዑስ ዘርፉ ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት የነበረው አስተዋጽዖ 0.7 የመቶኛ ነጥብ ወይም የክልላዊ ምርት ዕድገቱን 9.6 በመቶ ብቻ ነበር።

7. **የግብርና ዘርፍ አጠቃላይ ተጨማሪ እሴት የዕድገት ምጣኔ የረጅም ጊዜ አፈጻጸም አበረታች ቢሆንም ከ2011 ጀምሮ ባሉት የአለፉት ስድስት ዓመታት ወደ 3.1 በመቶ ቀንሷል።** የ3.1 በመቶ ምጣኔ መዋቅራዊ ሽግግር በማሳካት ላይ ላለ አገር ትልቅ የዕድገት ምጣኔ ነው። ነገር ግን በአማራ ክልል እና በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ደረጃ የዘርፉ ምርታማነት በሄክታር ከዓለም አማካይ ምርት በእጅጉ ባነሰበት ሁኔታ ይህ ምጣኔ ዝቅተኛ ነው።

8. ሠንጠረዥ 9-1፤ የክልሉ የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት አፈጻጸም

| | 1998 - 2016 | | 2011 - 16 | | ከክልላዊ ምርት ድርሻ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕድገት | ምዝን ዕድገት | ዕድገት | ምዝን ዕድገት | 1998 | 2016 |
| **ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች** | **6.1** | **3.7** | **3.1** | **1.7** | **62.0** | **51.9** |
| *አዝዕርት* | 6.7 | 2.6 | 3.0 | 1.1 | 38.0 | 35.0 |
| *የእንስሳት ሀብት* | 4.4 | 0.7 | 2.3 | 0.3 | 20.4 | 12.3 |
| *ዓሣ* | 20.0 | 0.0 | 15.9 | 0.0 | 0.0 | 0.1 |
| *ደን* | 6.6 | 0.3 | 6.5 | 0.3 | 5.1 | 4.5 |
| **ክልላዊ ምርት** | **7.2** | **7.2** | **4.9** | **4.9** | | |

ምንጭ፤ የአብክመ የፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

9. **ከዘርፉ ያልተነካ የመልማት አቅም ባሻገር የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ምልክት በወሳኝነት ባልታየበት ሁኔታ የገብርና ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት መቀነስ ጊዜውን የጠበቀ አይደለም።** የግብርናው ዘርፍ ከአጠቃላይ የክልል አቀፍ ምርት ከፍተኛ ድርሻ ያለው የመሆኑን ያህል፣ ከፍተኛ ቁጥር ላለው የሰው ኃይል የሥራ ዕድል የመፍጠሩን ያህል ኢኮኖሚው መዋቅራዊ ለውጥ ባላረጋገጠበት ሁኔታ የዘርፉ ተጨማሪ እሴት ዕድገቱ ተቀዛቅዟል። የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ መቀነስ እና የዘርፉ ተጨማሪ እሴት የዕድገት ምጣኔ መቀነስ በራሱ ችግር ባይሆንም ይህ ክስተት የተፈጠረው አሻጋሪ ዘርፍ በተለይ አምራች ኢንዱስትሪው የዕድገት መሪነቱን በቅጡ ባልተረከበበት ሁኔታ መሆኑ የዘርፉ ዕድገት መዳከም ለክልል አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መዳከም ቀጥተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

10. ስዕል 9-1-፤ የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ለክልላዊ ምርት ዕድገት የነበረው አስተዋጽዖ እና የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ




ሀ. ዘርፎች ለክልላዊ ምርት ዕድገት የነበራቸው አስተዋጽዖ (መቶኛ ነጥብ)




ለ. ንዑስ ዘርፎች ለክልላዊ ምርት ዕድገት የነበራቸው አስተዋጽዖ (መቶኛ ነጥብ)

ምንጭ፤ የፕላን እና ልማት ቢሮ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

11. **የክልሉ የሰብል ምርት አፈጻጸም በአፍሪካ ደረጃ ከፍተኛ እና አበረታች ሲሆን፣ ነገር ግን አብዛኛው ዓለም ከደረሰበት፣ ቴክኖሎጂ ከሚፈቅደው እና ከክልሉ ብሎም ከኢትዮጵያ ፍላጎት አኳያ ብዙ ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል።** ለጊዜው እንደ ተግዳሮት፣ ከተሠራበት እንደ አቅም ሊቆጠር በሚችል ሁኔታ የሰብል እና የእንስሳት ሀብት ምርታማነት ዝቅተኛ ነው። በ2014 የምርት ዘመን ከአጠቃላይ ከታረሰ መሬት 76.7 በመቶ፣ ከጠቅላላ ሰብል (crop) ምርት ደግሞ 81.3 ድርሻ የነበረው የአገዳ እና የብርዕ እህሎች (cereals) ምርት በአንድ ሄክታር (yield) 26.9 ኩዩንታል ነበር። በተመሳሳይ 2015 የክልሉ የአገዳ እና የብርዕ እህሎች ምርት ወደ 27.3 ኩዩንታል በሄክታር የጨመረ ሲሆን የአገር አቀፉ አኀዝ ደግሞ 29.0 ኩዩንታል በሄክታር ነበር።

12. ስዕል 9-2፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአገዳ እና የብርዕ እህሎች ምርታማነት ከዓለም አቀፍ አፈጻጸም ንጽጽር




የኢትዮጵያ የአገዳ እና ብርዕ እህሎች ምርት በሄክታር መረጃ ከተገኘለት የ2014 የአገራት አፈጻጸም ጋር ሲወዳደር ከግብፅ እና ከደቡብ አፍሪካ ቀጥሎ ከአፍሪካ ሦስተኛው ከፍተኛ አኀዝ ነው። በ2014 የአገዳ እና ብርዕ እህሎች ምርታማነት የግብፅ 74.2 ኩዑንታል በሄክታር፣ የደቡብ አፍሪካ 49.6 ኩዑንታል በሄክታር፣ እና የኢትዮጵያ 28.1 በሄክታር ነበር። የአማራ ብሔራዊ ክልል የአገዳ እና ብርዕ እህሎች ምርታማነት በተመሳሳይ ወቅት 26.9 ኩዑንታል በሄክታር የነበረ ሲሆን ይህ አኀዝ ከግብፅ፣ ከደቡብ አፍሪካ እና 27.9 ኩዑንታል በሄክታር ካስመዘገበችው ማዳጋስካር ቀጥሎ በአፍሪካ 4ኛው ከፍተኛ 'የመሬት ምርታማነት' ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራት አማካይ የአገዳ እና የብርዕ እህሎች ምርት በሄክታር 16.1 ኩዑንታል ነበር።

ይህ ውጤት የሚያበረታታ ነው። ነገር ግን አብዛኛው ዓለም ከደረሰበት፣ ቴክኖሎጂ ከሚፈቅደው እና ከክልላችን ብሎም የአገራችን ፍላጎት አኳያ ገና ብዙ መሥራትን ይጠይቃል። በ2014 የዓለም አማካይ የአገዳ እና ብርዕ እህሎች ምርት በሄክታር 41.8 ኩዑንታል የነበረ ሲሆን የአነስተኛ ምርት አምራች የሆኑትን ጥቂት የአረብ አገራት ሳይጨምር የእነዚህ ሰብሎች ምርታማነት ከ89 ኩዑንታል በሄክታር ተመዝግቧል።

13. **ከ1998 እስከ 2015 በነበሩት አሥራ ስምንት ዓመታት የታየው ከፍተኛ ሊባል የሚችል የብርዕ እና አገዳ እህሎች ምርት ዕድገት በምርታማነት ዕድገት እና በመሬት ማስፋፋት ዕድገት የተገኘ ሲሆን በአለፉት አምሥት ዓመታት በሁለቱም የዕድገት ምንጮች መቀነስ ምክንያት የእነዚህ ሰብሎች ምርት ዕድገቱ ተቀዛቅዟል።** በአሥራ ስምንት ዓመቱ ውስጥ የብርዕ እና የአገዳ እህሎች ምርት በ7.2 በመቶ ያደገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 4.7 መቶኛ ነጥብ በምርታማነት ዕድገት፣2.4 መቶኛ ነጥብ በመሬት ማስፋፋት ዕድገት የመጣ ነው። ነገር ግን እስከ 35 በመቶ እድገት የታየበትን የ1999 እና የ11 በመቶ የምርት መቀነስ የታየበትን 2000 በማስቀረት ከ2001 ጀምሮ ያለፉትን አሥራ አምሥት ዓመታት አፈጻጸም ሲታይ የብርዕ እና አገዳ እህሎች ምርት በ5.6 በመቶ ያደገ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 4.2 መቶኛ ነጥብ በምርታማነት ዕድገት፣ 1.4 መቶኛ ነጥብ በመሬት ማስፋት የተገኘ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል። ከ2011 ጀምሮ የአምሥት ዓመታት አፈጻጸም ሲታይ የብርዕ እና አገዳ እህሎች ምርት በ2.3 በመቶ ብቻ ያደገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2.1 መቶኛ ነጥብ በምርታማነት ዕድገት 0.2 መቶኛ ነጥብ በመሬት ማስፋፋት ዕድገት የመጣ ነው።

14. **በሄክታር ከሚገኘው የሰብል ምርት በተጨማሪ በባለይዞታ የሚገኘው የሰብል ምርት ለዓመታት እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ዕድገቱ የአርሶ አደሩን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ከሚጠበቀው ምጣኔ አንጻር ዝቅተኛ ነበር።** በሄክታር የሚገኝ ምርት በአፈር ምርታማነት እና በአምራች ኃይል ምርታማነት ሊመጣ ይችላል። ከሁለቱ ምንጮች የሚገኘውን ምርታማነት መለካት የራሱ መንገድ ቢኖረውም መረጃ በተገኘለት በባለይዞታ ሲለካ በ2015 የምርት ዘመን የክልሉ የአገዳ እና የብርዕ እህሎች አማካይ ምርት በባለይዞታ 21.2 ኩዑንታል የነበረ ሲሆን በአለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት በየዓመቱ የጨመረበት መጠን 0.61 ኩዑንታል ነው። ይህም ማለት ምርት በሄክታር በየዓመቱ በ0.83 ኩዑንታል ቢጨምርም የእያንዳንዱ ባለይዞታ ምርት የሚጨምረው በ0.22 ኩዑንታል ባነሰ ወይም በ0.61 ኩዑንታል ነው። በተለይ በአንድ ባለይዞታ ሥር የሚተዳደር ሠራተኛ ኃይል እየጨመረ የሚሄድ ከሆነ የሠራተኛ ምርታማነት ይቀንሳል፤ በዚያው ልክ የቤተሰብ አባላት ብዛት የሚጨምር ከሆነ የነፍስ ወከፍ ምርት እና በአጠቃላይ የኑሮ ደረጃ ትርጉም ባለው መጠን ላይሻሻል ይችላል። በዚህ ረገድ የክልሉ የሰብል ምርታማነት ከሰው ኃይል ምርታማነት ይልቅ ወደ መሬት ምርታማነት ያደላ ነው።

15. ስዕል 9-3፡ የመሬት እና የባለይዞታ የአገዳ እና የብርዕ እህሎች ምርታማነት




ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2015 መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

16. ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ብዛት ከአፍሪካ 1ኛ፣ ከዓለም ከ10 በታች ደረጃ ያላት ቢሆንም በክልልም ሆነ በአገር ደረጃ ትርፍ ከብት ውስን ነው። የእንስሳት ሀብት ተጨማሪ እሴት ላለፉት 19 ዓመታት በ4.4፣ ባለፉት 6 ዓመታት ደግሞ በ2.3 በመቶ ብቻ አዝግሟል። በክልሉ ከአንድ ላም በአማካይ በቀን የሚገኘው ወተት 1.21 ሊትር ሲሆን (የኢትዮጵያ 1.45 ሊትር ነው) ዓለም አቀፍ አማካዩ 35 ሊትር በቀን፣ ከፍተኛው 60 ሊትር በቀን ነው። የዶሮ ጫጩት ከሚያድገው የሚሞተው ይበልጣል፤ በ2014 ከነበሩት 26,631,000 ዶሮዎች (በነፍስ ወከፍ አንድ ዶሮ- ከ4 እስከ 5 ዶሮዎች በቤተሰብ በዓመት) 65.3 በመቶዎቹ ሞተዋል።

17. የእንስሳት ሀብት የማምረቻ 'ካፒታል' እና ጥሪት መያዥያ ነው። በ2014 የምርት ዘመን ከ6.1 ሚሊየን በሬ እና ወይፈን መካከል 94.4 በመቶ ለእርሻ የሚውል ሲሆን ከ5.3 ሚሊዮን ላሞች እና ጊደሮች መካከል 82.7 በመቶ ለእርባታ፣ 11.1 በመቶ ብቻ ለወተት የሚውሉ ናቸው።

18. **በአጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚ ላይ እንደተስተዋለው ሁሉ በግብርናው ዘርፍም አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም ዕድሜውን፣ ሚናውን እና የሀብት መሠረቱን አመችነት የሚመጥን የግብርና ሽግግር (ትራንስፎርሜሽን) በወሳኝነት አልተስተዋለም። የቀጣይ ዓመታት የግብርና ልማት ዕቅድ ዝግጅትም እነዚህን መዋቅራዊ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ሆኗል።** የግብርና ኢኮኖሚ በመዋቅራዊ ለውጥ ሂደት በጥሩ የዕድገት አቅጣጫ ላይ መሆኑን ሊያመላክቱ የሚችሉ ጉዳዮች በተወሰኑ አዋጭ የሰብል ዓይነቶች የምርት - መሬት መጠን ጥምርታ፣ የምርት - ሠራተኛ ኃይል ጥምርታ፣ የመሬት - ሠራተኛ ኃይል ጥምርታ መጨመር፤ የሀብት መሠረቱ እስካለ ድረስ ከአዝርዕት ማምረት ወደ እንስሳት ውጤት ልማት መሸጋገር፣ የዘመናዊ ግብዓቶች እና ሜካናይዜሽን የመጠቀም ደረጃ መጨመር፣ እነዚህን ዕውን ለማድረግ ጥራት ያለው የግብርና መዋዕለ-ንዋይ፣ እና የዘርፍ ክህሎት መዳበር ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህ መለኪያዎች የክልሉ ግብርና ብዙ መሥራት ይቀረዋል።

1. **ዝቅተኛ የሰብል ምርታማነት፤** በአፈር ለምነት መቀነስ፣ በሰው ኃይል ምርታማነት አዝጋሚነት፣ እና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝግመት የሚገለጽ ዝቅተኛ ምርታማነት ይስተዋላል። በተለመደው አሠራር እና ፍጥነት ከቀጠለ ከ25 ዓመት በኋላ የሚደረስበት የሰብል ምርት መጠን ከ45 – 49 ኩዪንታል በሄክታር ብቻ ይሆናል። በአሁኑ ዘመን ዓለም የደረሰበት ምጣኔ 90 ኩዪንታል በሄክታር ነው።
2. **አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ፤** መሬት፣ የሰው ኃይል እና ምርታማነት ወደተወሰኑ አዋጭ ምርቶች የመከማቸት አዝማሚያ የለም በሚያስብል ደረጃ ውስን ነው።
3. **ዝቅተኛ የግብርና አቅሞች፤** የግብርና መሠረተ-ልማት በተለይም የመስኖ እና ተያያዥ አቅሞች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፣ የሜካናይዜሽን አቅሞች፣ የቴክኖሎጂ ስርፀት ውስን ነው። ክልሉ ለሜካናይዜሽን እርሻ ምቹ የሆነ ከ2.2 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ቢኖረውም እስከ 2015/16 ምርት ዘመን በትራክተር የታረሰው 14.78 በመቶ፣ እንዲሁም በኮምባይነር እና በአነስተኛ መውቂያ መሳሪያዎች የተሰበሰበው ከ379,548 ሄክታር አቅም ውስጥ 7.37 በመቶ ብቻ ነው፡፡

4. **ከጥራት ይልቅ ብዛት ላይ ያተኮረ የእንስሳት ሀብት አያያዝ፤** በእንስሳት መኖ፣ በእንስሳት ዝርያ ማዳቀል፣ እና በእንስሳት ጤና ዝቅተኝነት የሚገለጹ ችግሮች መኖር ለዝቅተኛ የእንስሳት ተዋጽዖ ምርታማነት መከሰት ምክንያት ሆኗል።
5. **ዝቅተኛ መዋዕለ-ንዋይ፤** ግብርና እንደ አዋጭ ኢንዱስትሪ ባለመቆጠሩ የአልሚዎች የዘርፍ መዋዕለ-ንዋይ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው፣
6. **የክህሎት እና የአመለካከት ችግር፤** ዘርፉን በዕውቀት ለመምራት የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት አለ።

## የሃያ አምሥት ዓመት የግብርና ፍኖተ - ካርታ

### *መሠረታዊ ስትራቴጅ*

19. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት በ2016 ከክልላዊ ጥቅል ምርት 51.9 በመቶ ድርሻ ባለው እና በዝቅተኛ ምርታማነት በሚታወቀው የግብርና ዘርፍ በመንጠልጠሉ፣ አንደኛ ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ፣ ሁለተኛ ለዘመናዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ከዘርፉ የሚጠበቀውን ሚና በበቂ መጠን ለማግኘት፣ ሦስተኛ በገጠር በዘርፉ የተሰማራውን ከክልሉ ሕዝብ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን ዜጋ የኑሮ ደረጃ ትርጉም ባለው ደረጃ ለማሻሻል በአሁኑ ወቅት የሚታየው የኢኮኖሚ መዋቅር እና በግብርናው ዘርፍ የሰፈነው የረጅም ዘመን ሥልተ-ምርት በቂ እና ዘላቂ አይደለም። በመሆኑም
    1. በግብርናው ዘርፍ ዘመናዊ ግብርናን (የግብርና ትራንስፎርሜሽን) እና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ዓላማ ያደረገ ባለ ሁለት ፍኖት የግብርና ዘርፍ ልማት ስትራቴጂ በመከተል ድህነትን በሁለት አቅጣጫ መቅደም፣
    2. የአምራች ኢንዱስትሪው በመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚውን ፍጥነት እንዲመራ በሚያስችል ሁኔታ የረጅም ጊዜ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት እና ተወዳዳሪነትን መሠረት ላደረገ የመዋቅራዊ ለውጥ መሠረት መጣል ያስፈልጋል።
20. የግብርና ትራንስፎርሜሽን የረጅም ጊዜ ዋና ዓላማ ለዘመናዊ ግብርና ኢንዱስትሪ በግብዓት፣ በምርት፣ እና በስርጭት የሚገለጽ ዘላቂ ቴክኖሎጂ ማሸጋገር ነው። ዋና ስትራቴጂው ቴክኖሎጂ መር፣ ኢኖቬሽን ተኮር፣ እና ዓለም አቀፍ ገበያ ሰበር ይሆናል። በውጤቱም ምርታማነት፣ ቅልጥፍና፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት፣ እና አትኩሮተ - ግብር(specialization) ይረጋገጣሉ። እነዚህን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ዓላማዎች ለማሳካት የተዋናያን ቅንጅት ወሳኝ ሚና የሚጫዎት ሲሆን የግሉ ዘርፍ፣ መንግሥት፣ የምርምር ተቋማት፣ የውጭ አልሚዎች፣ እና የውጭ አጋር ድርጅቶች የዚህ ቅንጅት አካል ይሆናሉ።

21. በዚህ ስትራቴጂ ብቁ የግሉ ዘርፍ አልሚዎች፣ የመንግሥት የልማት ተቋማት፣ የግብርና ኮሌጅ እና የግብርና ቴክኒክ ተመራቂዎች፣ እና አቅም ያላቸው የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮች በተናጠልም ሆነ በማሕበር በቴክኖሎጂ-መር ኮሜርሻል ግብርና ይሳተፋሉ።

22. ስዕል 9-4፡ የባለሁለት ፍኖት የግብርና ልማት ስትራቴጂ ማዕቀፍ



23. የገጠሩ ሥልተ - ምርት በዋናነት በግብርና ዘርፍ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም የማሕበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ሁሉን አቀፍ የአኗኗር ዘይቤ (livelihood) ለውጥ ማካሄድ ያስፈልጋል። የገጠር ትራንስፎርሜሽን በማካሄድ ከተሳካላቸው አገራት በመማር ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ በመቀመር ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለው ስትራቴጂ ማሕበረሰብ አቀፍ አሳታፊ የተቀናጀ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ንቅናቄ መፍጠር ነው። የዚህ ንቅናቄ ጥቅል ዓላማ በሁሉን አቀፍ የገጠር ልማት አውድ በአነስተኛ ግብርና የተሰማሩ ዜጎች በራስ ጥረት እና በትብብር የተሻለ ገቢ ከማግኘት ባለፈ ለተሻለ ሕይወት እንዲተጉ ማስቻል ነው። በገጠር የገቢ እጥረት ከፈጠረው ድህነት በላይ ገቢ ከሚያስገኘው የኑሮ ደረጃ በታች የመኖር ኩርኩድ ባሕል የፈጠረው ፈርጀ - ብዙ ድህነት ይሰፋል። በዚህ ስትራቴጂ የተሻለ ገቢ መፍጠር፣ ጥራት ያለው አኗኗር እና የሕይወት ዘይቤ ማስፈን፣ ዘመናዊ የገጠር የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ መሠረተ - ልማት ማስፋፋት፣ ጠንካራ የገጠር ተቋማት መገንባት፣ የነቃ ማሕበረሰብ መፍጠር፣ ጽዱ እና ዘላቂ የመኖሪያ አካባቢ ማረጋገጥ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው። የማሕበረሰብ አቀፍ አሳታፊ የተቀናጀ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ንቅናቄ የብዙ ዘርፎችን ቅንጅታዊ አሠራር የሚጠይቅ ሲሆን የንቅናቄው አንዱ ንዑስ ዘርፍ የገጠር ግብርና ልማት ይሆናል።

24. ባለሁለት ፍኖት የግብርና ልማት ስትራቴጂ
    1. እንደ ሀብት መሠረታቸው እና ማሕበረሰባዊ ልዩ ፍላጎት በተመረጡ የልማት ቀጠናዎች ይተገበራል፤
    2. ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው የአዝርዕት እና የእንስሳት ዓይነቶች እና ዝርያዎች ተመርጠዋል፤ ይመረጣሉ፣
    3. ለዘማናዊ ግብርና ልማት የሚመጥን ልዩ ችሎታን በክሕሎት የሚለይ የስልጠና ሥርዓት ይነደፋል፣
    4. ግብርና መሬት ላለው አርሶ አደር ብቻ የተተወ አድርጎ ከሚያየው አስተሳሰብ በመላቀቅ በዘርፉ መክሊት እና የትምህርት ዝግጅት ላላቸው ትኩረት በመስጠት በፈቃድ አሰጣጥ፣ በመሬት ድልድል፣ በፋይናንስ አቅርቦት እና በቴክኖሎጂ መረጣ ረገድ በመንግሥት ልዩ ድጋፍ ይደረጋል።

## ዋና ዋና የረጅም ጊዜ አመላካች ግቦች

25. ከ2018 እስከ 2042 ባሉት ሃያ አምሥት ዓመታት የግብርና እና ተያያዥ ዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት በአማካይ በዓመት በ5.4 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል። የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በተለይ በመጀመሪያው የአምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ልማት ዕቅድ ወቅት (2018 – 2022) በ8.8 በመቶ ምጣኔ በማደግ በአጭር ጊዜ በምግብ ራስን የመቻል፣ እና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የማረጋገጥ ግቦችን የማሳካት ሚና እንዲወጣ ታቅዷል። የመዋቅራዊ ለውጥ ሕግ እንደሚጠይቀው በሂደት የግብርና ምርትን በማትረፍረፍ በተጨማሪ ዕሴት ደረጃ የዕድገት መሪነቱን ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ማመቻቸት ይኖርበታል። በዚህም መሠረት የግብርና ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ በ2016 ከነበረበት 51.9 በመቶ በ2042 ወደ 17 በመቶ እንዲቀንስ ግብ ተጥሏል። በንዑስ ዘርፍ ደረጃም የሰብል ምርት ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2016 እና 2042 መካከል ከ35 በመቶ ወደ 9.5 በመቶ፣ የእንስሳት ሀብት ተጨማሪ ዕሴት ድርሻም ከ12.3 በመቶ ወደ 5.8 በመቶ እንዲቀንሱ ታቅዷል።

26. ሠንጠረዥ 9 -2፤ የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች የዕድገት ምጣኔ ዕቅድ

| | 2013-16 (መነሻ) | 2018-22 | 2023-27 | 2028-32 | 2033-37 |
|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 3.4 | 8.8 | 6.4 | 5.6 | 3.6 |
| አዝዕርት | 3.5 | 8.7 | 6.4 | 3.8 | 2.6 |
| የዕንስሳት ሀብት | 1.7 | 7.7 | 7.0 | 9.6 | 6.2 |
| ደን | 11.5 | 8.9 | 8.9 | 13.9 | 4.2 |
| ዓሳ | 7.9 | 12.5 | 5.0 | 7.8 | 2.0 |

27. ሠንጠረዥ 9 -3 ፤ የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች ከክልል ጥቅል ምርት እና የሠራተኛ ኃይል የሚኖራቸው ድርሻ

| | | 2016 (መነሻ) | 2022 | 2027 | 2032 | 2037 | 2042 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከክልላዊ ጥቅል | ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 51.9 | 47.4 | 39.4 | 30.9 | 22.5 | 17.0 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምርት ድርሻ (%) | አዝዕርት | 35.0 | 31.9 | 26.5 | 19.0 | 13.2 | 9.5 |
| | የዕንስሳት ሀብት | 12.3 | 10.5 | 9.0 | 8.5 | 7.0 | 5.8 |
| | ደን | 0.1 | 0.1 | 0.1 | 0.1 | 0.1 | 0.1 |
| | ዓሳ | 4.5 | 4.9 | 3.8 | 3.3 | 2.2 | 1.7 |
| ከሠራተኛ ኃይል ድርሻ (%) | ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች (መነሻ 2013) | 66.4 | 57.1 | 52.5 | 46.0 | 37.4 | 30.0 |

28. **ትምህርት በገጠር በመስፋፋቱ፣ በከተሞች የልማት እንቅስቃሴዎች በመስፋፋታቸው፣ እና በሌሎች ገፊም ሆኑ ሳቢ ምክንያቶች ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት በገጠር በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል በፍጥነት እየቀነሰ መሆኑ ይስተዋላል።** ከ2005 እስከ 2013 በነበሩት ዘጠኝ ዓመታት በግብርና የተሠማራ የሰው ኃይል በ15.6 በመቶ (በ.7 በመቶ በዓመት) ከዘርፉ ወጥቷል። በ2013 የአገር አቀፍ የሰው ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ጥናት መሠረት በቀዳሚዎቹ አምሥት ዓመታት በክልሉ እና ከክልሉ ከፈለሰው 2.1 ሚሊዮን ዜጋ ውስጥ 644,679 ወይም የጠቅላላ ፍልሰቱን 30.7 በመቶ የሚሆነው ከገጠር ወደ ከተማ የፈለሰ ነው። በክልሉ የሃያ አምሥት ዓመት የልማት ፍኖተ-ካርታ በተመላከተው መሠረት በክልሉ በግብርና ዘርፍ የሚሰማራ የሰው ኃይል በ2013 ከነበረበት 66.4 በመቶ በ2042 ወደ 30 በመቶ ይቀንሳል።

29. **ይህ ከግብርና ዘርፍ የሰው ኃይል በፍጥነት የሚወጣበት ክስተት ዕድልም ሥጋትም ይዞ ይመጣል።** በሥጋት ረገድ በጉልበትም ሆነ በክህሎት አቅም ሊሆን የሚችለው ወጣት ከግብርናው ዘርፍ እግር ነቅሎ በመውጣቱ ምክንያት ጥቂት ጎልማሶች ብቻ በዘርፉ ተሰማርተው የክልሉንም ሆነ የአገሪቷን የግበርና ምርት ፍላጎት ማሟላት ሊያዳግት የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር የሚችል መሆኑ ነው። ክስተቱ የሚፈጥረው ዕድል የጥቂት ግን ለዘርፉ ሙያ ፍላጎቱ፣ መክሊቱ፣ ክህሎቱ እና አቅሙ የሚኖራቸው ገበሬዎች ወይም አልሚዎች የመሬት ይዞታ ስለሚጨምር ምርታማነት እንዲተባ፣ በገጠር የአርሶ አደር የገቢ እና የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል፣ ዘመናዊ ግብርና እንዲስፋፋ፣ በአጠቃላይ የግብርና ሽግግር እንዲሳካ ስለሚያደርግ ነው። ቁልፉ ጉዳይ ይህ ዕድል በራሱ የሚከሰት ወይም የሚረጋገጥ ሳይሆን በፖሊሲ እና በስትራቴጂ፣ እንዲሁም በአፈጻጸም ሥልት ተገርቶ የሚሳካ የጥረቶች ውጤት የመሆኑ ዕውነታ ነው።

30. በዚህም መሠረት በቀጣዮቹ ሃያ አምሥት ዓመታት በመሬት እና በሠራተኛ ምርታማነት ላይ በሚተገበሩ ሥራዎች የሚከተሉት ግቦች ተመላክተዋል።
    1. የመሬት ምርታማነትን በአለፉት ዓመታት ከሚያድግበት 0.83 ኩዊንታል በሄክታር በዓመት ወደ 1.5 ኩዊንታል በሄክታር በዓመት በማሳደግ የአገዳ እና የብርዕ እህሎችን ምርታማነት የአሁኑ ሂደት ቢቀጥል በ2042 ሊገኝ ከሚችለው 49.7 ኩዊንታል በሄክታር ወደ 67.8 ኩዊንታል በሄክታር ለማድረስ ተመላክቷል። የዚህ የመሬት ምርታማነት ለውጥ ብቻ በዘርፉ የተሰማሩ ዜጎች አሁን ያለው አሠራር ቢቀጥል በየዓመቱ በባለይዞታ ሊያገኙት የሚችሉት ተጨማሪ ምርት ከ0.6 ወደ 1.2 ኩዊንታል ያድጋል፤ በ2042 የአንድ ባለይዞታ አማካይ ምርት በተለመደው አሠራር ቢቀጥል ሊደረስበት ከሚችለው 37.7 ኩዊንታል ወደ 52.6 ኩዊንታል ከፍ ይላል። [በ2015 የክልሉ አማካይ የአገዳ እና የብርዕ እህሎች ምርት በሄክታር 27.3 ኩዊንታል፣ በባለይዞታ ደግሞ 21.2 ኩዊንታል ነበር።]

31. ስዕል 9-5፡ የመሬት ምርታማነት ለውጥ የሚያስገኘው ተጨማሪ ምርት በባለይዞታ




ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2015 መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

32. **የመሬት መጠን በባለይዞታ መጨመር ምርታማነትን ከማበረታታት ባሻገር የአርሶ አደሮችን የኑሮ ደረጃ ያሻሽላል።** ከግብርናው ዘርፍ እየወጣ ያለውን የሰው ኃይል ምጣኔ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት፣ በግብርና መዋዕለ - ንዋይ በሰፊ እርሻ ወደ ዘርፉ የሚገቡ አልሚዎችን፣ እና መንግሥት በመሬት ሥሪት ላይ ሊወስዳቸው የሚችላቸውን የፖሊሲ ርምጃዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በአሁኑ ጊዜ የመቀነስ አዝማሚያ የሚታይበት በአንድ ባለይዞታ የሚታረስ መሬት መጠን በ0.05 ሄክታር ወይም በ500 ካሬ ሜትር በዓመት እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል። በዚህም መሠረት የይዞታ መጠን በ2042 አሁን ያለው አዝማሚያ ቢቀጥል ሊሆን ከሚችለው 0.77 ሄክታር ወደ 2.1 ሄክታር ያድጋል።

33. ስዕል 9-6፤ የመሬት - ባለይዞታ ምጣኔ ለውጥ አስፈላጊነት




ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2015 መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

34. **የአምራች አርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ መጠን በአማካይ በ0.05 ሄክታር በዓመት መጨመር የባለይዞታ ምርትን በዓመት በአማካይ በ4.6 ኩዩንታል እንዲጨምር አስተዋጽዖ ያደርጋል።** ይህም የመሬት ምርታማነትን

በመጨመር ብቻ በ2042 አንድ ባለይዞታ ሊያገኘው ከሚችለው 67.8 ኩዪንታል ወደ 143 ኩዪንታል ያሳድገዋል።

35. ስዕል 9 -7፡ የባለይዞታ መሬት መጠን መጨመር በአርሶ አደር ምርት ላይ የሚያስገኘው ለውጥ




ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2015 መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ፤ 2016

36. **በግብርና ዘርፍ ውስጥ ከሚደረጉ የመዋቅራዊ ለውጥ ግቦች አንዱ የእስሳት ሀብት ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽዖ ከፍ ማድረግ ነው።** ኢኮኖሚ ከዝቅተኛ ወደ መካከለኛ ገቢ ደረጃ ሲሸጋገር የሥርዓተ - ምግብ አቅጣጫ ከእህል እና ጥራጥሬ ወደ እንስሳት ውጤቶች እንደሚያዘነብል ልምዶች እና ጥናቶች ያሳያሉ። በዚህም መሠረት በቀጣዮቹ ሃያ አምሥት ዓመታት የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከአጠቃላይ ክልላዊ ኢኮኖሚ የሚኖረው ድርሻ የሚቀንስ ቢሆንም የእንስሳት ሀብት ንዑስ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ለክልላዊ ጥቅል ምርት ያለው አስተዋጽዖ ከሰብል ንዑስ ዘርፍ አስተዋጽዖ ጋር የተስተካከለ ይሆናል። በ2015 የምርት ዘመን የሰብል እና የእንስሳት ሀብት ተጨማሪ እሴት ለጥቅል ክልላዊ ምርት የነበራቸው አስተዋጽዖ፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው፣ 35.5 በመቶ እና 12.5 በመቶ ነበር።

37. ለእንስሳት ሀብት ልማት ከብዛት ይልቅ ጥራትን ባስቀደመ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት የእንስሳት ተዋጽዖን ከዓለም አቀፍ አማካይ ማቀራረብ በዘርፉ የተሰማራውን ማሕበረሰብ የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋል፤ የእንስሳት ግብርናን ወደተሻለ ደረጃ በማሸጋገር አዋጭ ኢንዱስትሪ ያደርጋል። በተለይም፣
   1. በበሬ ማረስን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ የቁም ከብት ሽያጭ ገቢን ትርጉም ባለው ደረጃ ይጨምራል፣ ከተዋጽዖ የሚገኝ ቋሚ ገቢን ያሳድጋል፣
   2. ከአንድ ላም በቀን የሚገኘን ወተት 10 እጥፍ ማሳደግ እና የወተት ላም ቁጥርን በግማሽ መቀነስ የወተት አቅርቦትን በ5 እጥፍ ያሳድጋል፣
   3. የዶሮ ሞትን በመቀነስ እና አመጋገብን በማሻሻል ተቀዳሚ የፕሮቲን ምንጭ ማድረግ በምግብ ራስን የመቻል ግቦችን ፈጥኖ ለማረጋገጥ ያስችላል፣
   4. የፍየል እና የበግ ልማት ቀጠናዎች በማቋቋም ከጥሪትነት ወደ ተከታታይ ገቢ መቀየር በዘርፉ ለተሰማራው ማሕበረሰብ የቋሚ ገቢ ምንጭ ይፈጥራል።

## 9.2. የትኩረት አቅጣጫዎች

38. ከዚህ በላይ የተገለጹትን የክልሉን የግብርና ዘርፍ አቅሞች፣ የአፈጻጸም ትንተና ውጤቶች፣ በተለይም ዘርፉን ለማዘመን እና የዘመናዊ ኢኮኖሚ አቅም፣ አካል እና ውጤት ለማድረግ የሚያግዙ የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል። እነዚህም
   1. ጥምር የግብርና አቅሞችን ማጎልበት፤ መስኖ፣ ሜካናይዜሽን፣ ቴክኖሎጂን ለዘርፉ የሰብል ልማት በጥምር (package) መጠቀም፣

2. የተሻሻለ መኖ፣ የተሻሻለ ዝርያ፣ እና የእንስሳት ሕክምና (feed-breed- vet) በመጠቀም የእንስሳት ሀብት ልማትን ማሳደግ፣
3. ምርታማነት እና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የግብርና ምርቶች ላይ አተኩሮ መሥራት፣
4. የግብርና መዋዐለ-ንዋይን በምርት ግብ፣ በቦታ፣ በጊዜ፣ እና በአልሚ አቅዶ ዘመናዊ ግብርናን በፍጥነት ማስፋን፣
5. የዘርፎችን ትስስር እና የተቋማትን ቅንጂታዊ አሠራር በማዳበር የግብርና ግብይትን ማዘመን፣ የእሴት ሰንሰለት ማሻሻል፣
6. ከኢኮኖሚ ግቦች ጋር የተቀናጀ የአካባቢ ጥበቃ ልማት ማረጋገጥ፣
7. በስፓሻል ፕላን የተለየ የግብርና ልማት ኮሪደር ማስፋፋት፤ የልማት ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን መቅረጽ፣ እና
8. ለዘመናዊ ግብርና የሚመጥን የሰለጠነ የሰው ኃይል መፍጠር ናቸው።

## 9.3. የትኩረት መስኮች

39. የሚከተሉት የግብርና ዘርፎች የትኩረት መስክ ይሆናሉ፤
    1. የግብርና ኢንቨስትመንት፤ ቴክኖሎጂ - መር የሰብል ንዑስ ዘርፍ የኮሜርሻል ግብርና ልማት፣
    2. የግብርና ኢንቨስትመንት፤ ዘመናዊ የእንስሳት ሀብት ልማት፣ እና
    3. የአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ትራንስፎርሜሽን፣ እና

## 9.4. ዓላማ

40. ከ2018 ጀምሮ ለቀጣዮቹ አሥር ዓመታት የግብርና ዘርፍ በምግብ ራስን የመቻል፣ የፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እና የመዋቅራዊ ለውጥ ግቦችን ያሳካል።

## 9.5. ዋና ዋና ግቦች

41. ዝርዝር ግቦች በግብርና ዘርፍ ዝርዝር ዕቅድ ውስጥ የሚለዩ ሆኖ ከ2018 ጀምሮ በቀጣዮቹ አሥር ዓመታት የግብርና ዘርፍ በምግብ ራስን የመቻል እና የፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦችን ለማሳካት የተያዘለትን ዓላማ ዳር ለማድረስ የሚከተሉት ጥቅል ግቦች ይኖሩታል፤

    1. የዘርፉ ተጨማሪ እሴት በመጀመሪያው የአምሥት ዓመት ዕቅድ በ8.8 በመቶ፣ (በሁለተኛው አምሥት ዓመት ዕቅድ በ6.9 በመቶ) እንዲያድግ ታቅዷል፤
    2. በሂደት የእንስሳት ሀብት ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ ከአዝዕርት ተጨማሪ እሴት ድርሻ ጋር ይመጣጠናል፣
    3. በ2042 የእህል ሰብል ምርታማነትን 65 ኩዩንታል በሄክታር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን፣
        - በቀጣዮቹ 5 ዓመታት ተጨማሪ መሬት በማልማት እና ምርታማነት በማሳደግ
        - ከ5 ዓመት በኋላ ምርታማነትን በማሳደግ ብቻ ግቡን ለማሳካት ታቅዷል።
    4. የቀንድ ከብት እንስሳት ሀብትን ከጥሪት መያዣነት እና ከእርሻ ሥራ ተከታታይ እና ዘላቂ ገቢ ወደሚያስገኝ ኮመርሽያል ሥርዓት ማሸጋገር መጀመር፣
    5. የዶሮ ሀብትን በማዘመን የተደራሽ ፕሮቲን ምንጭ ማድረግ።

## 9.6. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

42. ምርታማነትን ለማሳደግ የሚወሰዱ ሥልቶች፤
    1. በዘርፎች ትስስር መርህ የማዕድን፣ የማኑፋክቸሪንግ እና የግብርና ዘርፎችን በማስተባበር በኖራ ድንጋይ አሲዳማ አፈርን ማከም
    2. በመስኖ ልማት የምርት ዑደትን መጨመር
    3. ቴክኖሎጂን ጨምሮ ዘመናዊ አቅሞችን መጠቀም
    4. የከፍተኛ ምርታማነት አቅም ለአላቸው ዝርያዎች ትኩረት መስጠት
    5. የተፈተኑ የግብርና ሥርዓቶችን መተግበር፤
        - የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት
        - የግበርና ንግድ ሥርዓት
        - የግብርና ማሕበራት ሥርዓት
        - የግበርና ፋይናንስ ሥርዓት
        - የግበርና ትምህርት፣ ስልጠና፣ ጥናት እና ምርምር ሥርዓት

- የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሥርዓት
- የግብርና ዘርፍ አደረጃጀት ሥርዓት፣ እንዲሁም
- የመንግሥት የግበርና ፖሊሲ ሥርዓት።

# ምዕራፍ አሥር

# የአካባቢ ልማት እና ጥበቃ

## 10. 1. የዘርፉ ሚና

1. ከምድር እስከ ሕዋ ባለው የዓለም አውድ አካባቢ ሕይወት እና የሕይወት መሠረት ነው። በነጻ ከተሰጠ ንጹህ አየር እስከ የምድር ውሃ እና አፈር፣ በዓይን ከማይታዩት ደቂቅ ነፍሶች እስከ ትላልቅ ተክሎች እና እንስሳት የሚዘልቁ ብዝሃ ሕይወት እና መስተጋብራቸው የዚህ ዓለም የሕይወት መሠረት ናቸው።

2. ሰው ኑሮውን ለማሻሻል እና ለመዘመን በሚያድርገው ጥረት የተፈጥሮ ሀብቶችን ይጠቀማል፣ ምርት ያመርታል፣ የፍጆታ ሥርዓቶችን ይፈጽማል። እነዚህ መስተጋብሮች መጠን ሲያልፉ ከአካባቢ እስከ ዓለም የሚደርሱ ዳፋዎች ያስከትላሉ። በዚህ ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ አየር መዛባት እና ብክለት፣ በአገር ደረጃ ደግሞ የደን መመናመን፣ የአፈር መከላት፣ የአካባቢ መበከልን የመሳሰሉ ፈታኝ ኩነቶች ተከስተዋል። የአማራ ብሔራዊ ክልል መጠኑ ቢለያይም በሁሉም ደረጃ ተጠቂ ነው።

## 10.2. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

1. **የአየር ንብረት ለውጥ መጨመር አሳሳቢነት፡-** የሙቀት አማቂ ጋዞች መጨመር፣ የሙቀት መጠን መቀያር፣ የዝናብ ስርጭት መለዋወጥ፣ የጎርፍ አደጋ፣ የድርቅ መከሰት፣ የመሬት መንሳቀል እንዲሁም የጤና ችግር ለአየር ንብረት ለውጥ መጨመር ዋና ዋናዎቹ ምልክቶች ናቸው፡፡

2. **የአካባቢ ብክለትና ብክነት መጨመር፡-** ጥቅም ላይ የሚውል ጸረ-አረምና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው መሆኑ፣ አካባቢን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ከመያዝና ከመጠበቅ አኳያ ያለው አዝማሚያ ውስንነት ያለበት መሆኑ፣ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ዝቅተኛ መሆን፣ የአካባቢ ደረጃ/ስታንዳርድ በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ የስርዓተ-ምህዳር የአገልግሎቶች የገበያ ዋጋ በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ በዘርፉ የሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶች ተገቢውን የተጽዕኖ ማቃለያ ዘዴዎችን ማካተትና መተግበር ላይ ውስንነት መኖሩ፣ ወራሪና መጤ አረሞች እየተስፋፉ መምጣት፣ ለውሃና ውሃ አዘል መሬቶች የሚደረገው ተገቢ እንክብካቤና አያያዝ ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም በከተሞች የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት አለመዘመን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

3. **የተፈጥሮ ስርዓተ-ምህዳር ሀበት መራቆትና መመናመን፡-** የቆላ ደኖችን በዘላቂነት ለመጠቀም በሚያስችል ደረጃ የሚደረገው እንክብካቤና ልማት ዝቅተኛ መሆን፣ የእምነት ቦታዎች የብዝሃ ህይዎት መገኛ ቢሆኑም የሚደረግላቸው ድጋፍና እገዛ ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም በደን መመንጠር ምክንያት የመሬት መራቆት ለአፈር ለምነት ችግር መዳረጉ፣ ያሉትን ፓርኮችና ጥብቅ ስፍራዎች በሚጠበቀው ደረጃ ማልማት አለመቻሉ፣ በክልሉ በርካታ ጥብቅ ስፍራ የመሆን እምቅ አቅም ያላቸው አካባቢዎች ቢኖሩም በሚጠበቀው ልክ ተገቢ የሆነ ጥናትና ልየታ አለመከናወኑ፣ በጥብቅ ስፍራዎችና ከጥብቅ ስፍራዎች ውጭ በርካታ የዱር እንስሳትና ሌሎች ብርቅየ የብዝሃ-ህይዎት ሀብቶች ስብጥር ቢኖርም የሚደረገው ልማትና ጥበቃ በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ እንዲሁም የጥብቅ ስፍራዎችን ሽፋን ማሳደግና የብዝሃ ህይወት ሀብቱን በሚፈለገው ልክ መጠበቅ አለመቻሉ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 10.3. የትኩረት መስኮች

4. የሚከተሉት የአካባቢ ጥበቃ እና ልማት የትኩረት መስኮች ናቸው፤
   1. የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን መቀነስ

2. ዘላቂነት ያለው የአካባቢ አያያዝና አጠቃቀም
3. የብዝሃ-ህይዎት ሀብት ጥበቃና ልማት
4. የአካባቢ ህግ ተከባሪነትና ተፈጻሚነት

## 10.4. የትኩረት አቅጣጫዎች

5. የአካባቢ ጥበቃ ግቦችን ከረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ ልማት ግቦች ጋር ማቀናጀት ዋና የአካባቢ ልማት የትኩረት አቅጣጫ ነው። የረጅም ዘመን የአካባቢ መራቆት ከድህነት ጋር የተቆራኘ ነው። በዚህም መሠረት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎቹ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ።

1. በአካባቢ መራቆት ላይ ጫና የሚፈጥሩ የባዮ ማስ፣ የገጠር የቤት ግንባታ፣ የባሕላዊ ግብርና መሣሪያዎች፣ የእንስሳት መኖ፣ እና የከተማ ግንባታ የመሳሰሉት ፍላጎቶች በገጠር - ከተማ ሽግግር፣ በኃይል አማራጭ፣ በዘመናዊ ግብርና ሥልተ - ምርት የሚፈቱ በመሆናቸው የረጅም ጊዜ የአካባቢ ጥበቃ ዓላማ እና ግቦችን ከአጠቃላይ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ሽግግር ዓላማ እና ግቦች ጋር እንዲጣጣም ይደረጋል።
2. የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ የአካባቢ ጥበቃ እርምጃዎች በአንድ በኩል በሕዝብ ተሳትፎ እና በዘመቻ የሚሠሩ፣ በሌላ በኩል ዘላቂነታቸው ከትግበራ እና ሥልቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በዕቅድ እና ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የሚከናወኑ ተግባራትን በሚለይ ሁኔታ ይተገበራሉ።
3. የአፈር መከላትን ለመከላከል ከሚደረጉ ርምጃዎች መካከል አንዱ ለሆነው የእርከን እና የክትር ሥራ በሕዝብ ተሳትፎ በዘመቻ ሊከናወን የሚችል ተግባር እንደሆነ ሁሉ፣ የአካባቢ ደን ልማት ሥራዎች ከማሕበረሰብ ዘላቂ ጥቅም፣ የድን ሀብት ፍላጎቶችን ከሚተኩ አማራጭ አቅሞች የመፍጠር ዕቅድ፣ ለዘመናት የታረሰ መሬትን የሚተካ የኢኮኖሚ መሠረት ከመፍጠር፣ እንዲሁም ካላሰለሰ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ጋር የመያያዛቸው እውነታ ግምት ውስጥ ይገባል።

## 10.5. ዓላማ እና ግቦች

### ዓላማ

6. በክልሉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ዕውን ለማድረግ የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሀ ሕይወት ሀብቶችን በማልማት፣ በመጠበቅ እና የአጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት ጤናማ የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብር በማሳደግ ዘላቂ ልማት እና ዕድገት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

### ዋና ዋና ግቦች

7. የዘርፉን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ማለትም በክልሉ ውስጥ በ2016 በጀት ዓመት የሚገኘውን 3.99 ሚሊዮን ሄ/ር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደን ሀብት በ2022 በጀት ዓመት 0.8 ሚሊዮን ሄ/ር የሚሆነውን መለካት፣ መከለል፣ የይዞታ ካርታ ማረጋገጫ (Certification) ማሰጠት፣ በዘላቂነት ማልማት፣ መጠበቅና መጠቀም፣ በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ታቅፎ እየተዳደረ ያለውን 128,945 ሄ/ር የደን ሃብት በየዓመቱ 5% በመጨመር በ2022 ወደ 164,570 ሄ/ር ማሳደግ፣ በ2016 በጀት ዓመት የደን አያያዝ እና አጠቃቀም የተዘጋጀላቸው የመንግስት፣ የማህበረሰብ፣ እና የማህበራት 118 ደኖች በየዓመቱ 10% በመጨመር በ2022 ወደ 209 ደኖች የአያያዝና የአጠቃቀም ዕቅድ እንዲኖራቸው ማድረግ እንዲሁም በ2016 በጀት ዓመት የነበረውን 27,000 ሄ/ር ዓመታዊ የደን ጭፍጨፋ በ2022 በጀት ዓመት ከ50% በላይ በመቀነስ 24,000 ሄ/ር ማድረስ የሚሉት ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

8. በዘርፉ በ2022 ለዘላቂ የደን ሀብት ልማት ምቹ የሆነ 0.7 ሚሊየን ሄ/ር መሬት በአዲስ ለመለየት፣ ለመከለል እና የይዞታ ካርታ ማረጋገጫ ለመስጠት፣ የተቀናጀ ዘላቂ የደን ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን በመተግበር የክልሉ የደን ሽፋን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 3.99 ሚሊዮን ሄ/ር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 4.59 ሚሊዮን ሄ/ር ከፍ በማድረግ፣ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው 83,262 ሄክታር የተራቆተና ያገገመ መሬት በተጨማሪ መታረስ የሌለባቸውን ተራራማ እና በሰፋፊ ውሃ አካላት ዙሪያ ያሉ ቦታዎችን በ2022 በጀት ዓመት 173,348 ሄ/ር መሬት እንዲያገግም ለማድረግ፤ እንዲሁም የተቀናጀ የደን ልማት ሥራዎችን በማከናወን የደን ውጤቶች አቅርቦትና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 2.7 ሚሊዮን ኩንታል ከሰል፣ 417,128 ሜ/ኩ ሌሎች የእንጨት ነክ ምርቶች እና 3,250 ኩ/ል እጣንና ሙጫ በ2022 በጀት ዓመት በየዓመቱ 10%፣ 12% እና

10% በቅደም ተከተል በማሳደግ የከሰል ምርት 4.78 ሚሊዮን ኩ/ል፣ ሌሎች የእንጨት ነክ ምርቶችን 738,968 ሜ/ኩብ እና የዕጣንና ሙጫ ምርት ወደ 6,415 ኩንታል ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡

9. በሌላ በኩል የተቀናጀ የደን ልማት ሥራዎችን በማከናወንና እሴት በመጨመር (ለጣውላ፣ አጣና፣ ዕጣንና ሙጫ፣ ቀርቀሃ፣ የጫካ ማር፣ ከሰል፣ ፍራፍሬ፣ ካርቦን ትሬዲንግና ሌሎች ምርቶች...) ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ0.2354 ቢሊየን ብር በየዓመቱ 10% በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 0.38 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን የደን ዘርፍ ኢንዱስትሪውን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 7 ኢንዱስትሪ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 9 ከፍ እንዲል በማድረግ የደን ውጤቶች ኤክስፖርት ከነበረበት 2.2 ሚሊዮን ዶላር ወደ 4.34 ሚሊዮን ዶላር ማሳደግ እና ወደ ክልሉ የሚገባውን የደን ውጤት ከነበረበት 50 ሚሊዮን ዶላር ወደ 44 ሚሊዮን ዶላር ለመቀነስ ግብ ተይዟል፡፡ እንዲሁም በደን ዘርፍ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 150,000 ተጠቃሚዎች ቁጥር በየዓመቱ 10% በመጨመር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 265,734 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች የማሳደግ እና በ2016 በጀት ዓመት ከደን ዘርፍ ተጠቃሚ የሆኑ 170,150 የህብረተሰብ ክፍሎች ከዓመታዊ የገቢ ድርሻቸው ከ5-10% የሆኑ ቤተሰቦችን በየዓመቱ በ10% በማሳደግ ተጠቃሚ የህ/ሰብ ክፍሎችን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 301,431 ሚሊዮን የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

10. ከዚህ በተጨማሪም የክልሉን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬታ መጠን በ2012 ከነበረበት 79.8 ሚሊየን ሜትሪክ ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይ ኢኩይቫለንት እስከ 2022 ይህንኑ የማስጠበቅ ስራ የሚሰራ ሲሆን የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ የወሰዱ አዳዲስ የማምረቻ፣ የአገልግሎት መስጫና የልማት ፕሮጀክቶችን ቁጥር በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 3,043 በየዓመቱ በ13% በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6,335 የማሳደግ ስራም በትኩረት የስራል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት በማምረቻ፣ የአገልግሎት መስጫና የልማት ፕሮጀክቶች በከተሞች፣ በተቋማትና ላይ የተደረገውን 1,911 ክዋኔ ኦዲት በየዓመቱ በ14% በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 4,195 በማድረስ የህግ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ፣ በልማት ፕሮጀክቶች፣ በከተሞችና በተቋማት ላይ የተደረገውን 1,185 የአካባቢ ጥናት፣ ክትትልና ቁጥጥር /ኢንስፔክሽን/ በ2022 በጀት ዓመት በየዓመቱ በ13% በማሳደግ ወደ 2,467 በማደረስ የህግ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም በከተሞች፣ በተቋማትና በፕሮጀክቶች አካባቢ የነበረውን 40 የአካባቢ ብክለት (የአየር፣ የውሃ፣ የአፈርና የድምጽ) ፍተሻ የተሟላ ላቦራቶሪ በማደራጀትና ዕውቅና በማሰጠት በየዓመቱ 20% በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 119 ለማሳደግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

11. በክልሉ የሚገኙ የዱር እንስሳት መኖሪያ ጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር እስከ 2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 14 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 15 ከፍ በማድረግ የክልሉን የጥብቅ ስፈራዎች ሽፋን አሁን ካለበት ከ3.5% ወደ 3.8% የማሳደግ ግብ የተቀመጠ ሲሆን በክልሉ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠበትን 306 የዋልያ ቁጥር እና 102 የቀይ ቀበሮ ቁጥር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 545 እና 212 በቅደም ተከተል የማሳደግ፣ በ2015 በጀት ዓመት የነበረውን 826,432 ሰው/ሰዓት አሰሳና ቅኝት በ2022 በጀት ዓመት ወደ 897,269 ሰው/ሰዓት የማድረስ እንዲሁም የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎችን በማልማት፣ ህገ ወጥ ዝውውርን በመቆጣጠር፣ በማስተዋወቅና የቁጥጥር አደን ቀበሌ በማቋቋም እንዲሁም ሌሎች የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመተግበር በ2015 በጀት ዓመት ከነበረው 21,558 ቀጥተኛ ተጠቃሚ የማህበረሰብ ቁጥር በየዓመቱ በ5% በመጨመር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 28,890 የማሳደግ ግቦች ተይዘዋል፡፡

12. በክልሉ እስከ 2016 በጀት ዓመት ያለውን 238,000 ሄ/ር የውሃ አዘል መሬቶች መጠን የአያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት በ2022 በጀት ዓመት 65% ያህሉን መጠበቅና የሚሰጡትን አገልግሎት የማሳደግ፣ የእምቦጭና ሌሎች የመጤ፣ አደገኛና ወራሪ አረም ዝርያዎችን ቁጥጥር (አወጋገድ) በ2016 በጀት ዓመት ከነበረት 40% በ2022 በጀት ዓመት ቁጥጥሩን ወደ 90% የማድረስ ግብ የተቀመጠ ሲሆን በሌላ በኩል የዘርፉን ተቋማት የመፈጸምና ማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራዎች (ግንዛቤ ፈጠራና ማስተዋወቅ፣ ስልጠና፣ ወዘተ...) በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው 65% በ2022 በጀት ዓመት ወደ 70% ለማሳደግ ይሰራል፡፡

13. ከዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አኳያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር በአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ላይ ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፣ በአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ከበባት፣ ግሪን ኢንተርፕራይዞችና የአካባቢ ተቆርቋሪ ማኅበራት ውስጥ ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን በንቃት እንዲሳተፉ የማድረግ፣ በከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥርአት እንዲሁም ቆሻሻን መልሶ መጠቀም የሚችሉ አረንጓዴ ቴክኖሎጅዎችን በማቅረብ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፣ በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ለመቋቋም በሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ልዩ

ትኩረት እንዲያገኙ የማድረግ፣ በደን ዘርፍ በሚፈጠሩ ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎች ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ እንዲሁም በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን በኢኮ-ቱሪዝም ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ግቦች ተየዘዋል፡፡

14. ከወጣቶች አኳያም ወጣቶች በተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና ጥበቃ ሥራ ላይ ልዩ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከውጤቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን ወጣቶች በደን ጥበቃና ልማት ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ የማድረግ ግብም ተይዟል፡፡ በተጨማሪም ወጣቶች የተጎዱና የተራቆቱ የደን መሬቶችን እንዲያገግሙ በማድረግ የአካባቢያዊ የኢኮኖሚያዊ ልማትን በማሻሻል ወጣቶቹን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰራ ሲሆን በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በቦይ ጠረጋ፣ በጽዳት ዘመቻ በመጤ አረም ቁጥጥር በችግኝ ማፍላት፣ በደን ተከላና እንክብካቤ ስራዎች ላይ በስፋት እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ማስተባበርና መደገፍ፣ በጥብቅ ስፍራዎች አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች በልዩ ልዩ የኢኮቱሪዝም ስራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ መለየትና ለተጨማሪ ጥቅም ማዋል ላይ የወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠሪያና ገቢ እንዲያገኙ ለማድረግም የሚሰራ ይሆናል፡፡

15. በሌላ በኩል የህዝብ ቁጥር እድገት መጨመር ከተፈጥሮ ሀብቶች እና ከአካባቢ ጋር ያለውን ትስስር ለህብረተሰቡ የማስተማር እንዲሁም የህዝብ ቁጥር እድገት መጨመር ለአየር ንብረት ለዉጥ ያለዉን ጫና ለሰራተኞች የግንዛቤ ፈጠራ ትምህርት የመስጠት ግቦች ተካተዋል፡፡

## 10.7. የማስፈጸሚያ ስልቶች

16. በፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በማከናወን በየደረጃው የሚገኙ አካላትን የመፈጸምና የማስፈፀም አቅም መገንባት፣ የዘርፉን ተቋማት የስራ አፈፃፀም በሚድያና ኮሚዩኒኬሽን ስራዎች በማስደገፍ ለህብረተሰቡ ማቅረብና በዚህም ሠፊ የህብረተሰብ ንቅናቄ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲፈጠር ማድረግ፣ የዘርፉን ስራ ለማሳለጥ ከሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ሃብት በማፈላለግ ለስራ የሚያስፈልጉ ግባዓቶችን ማሟላት፣ በዘርፉ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት እና በመቀመር ማስፋት፣ የመረጃና የቴክኖሎጅ አቅርቦትና ሽግግርን ማሳደግ፣ ክልላዊ የስርዓተ ምህዳር እና የሙቀት አማቂ ጋዝ መረጃ መሰብሰቢያ የመረጃ ቋት በማሻሻል ወደ ስራ መግባት፣ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ ሴክተር ዘለል ተግባራትን አካቶ በመተግበር (የወጣቶችና ሴቶችን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ኤች አይቪ/ኤድስ፣ ስነ-ህዝብ ወዘተ) በልዩ ትኩረት መፈፀም፣ የተቀናጀና የተናበበ አሳታፊ የዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ አሰራር ስርዓት ማዕቀፍ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ለስራ ማስፈፀሚያ የሚያግዙ ስትራቴጂዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማሻሻል፣ ማውጣትና መተግበር የሚሉት የዘርፉ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

# የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት

## 11.1. መነሻዎች

### የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ልዩ ትኩረት አስፈላጊነት

1. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት እና የመዋቅራዊ ሽግግር ግብ የተቆራኙ ናቸው። በተሞክሮ ደረጃ ቢያንስ መሠረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችል የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ሳይገነባ ያደገ ተጠቃሽ አገር የለም። የተሳካ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረግ የቻሉ አገራት የኢኮኖሚ መሠረታቸውን በአምራች ኢንዱስትሪ ላይ ያነጹ አገራት ናቸው። የአገልግሎት ዘርፍ በባሕርይው የዘመናዊነት ደረጃው እንደተመሠረተበት የምርት ዓይነት እና ምንጭ ስለሚወሰን ያለ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት በአቋራጭ ወደ አገልግሎት ዘርፍ በመሸጋገር ዘላቂ ልማት ማሳካት አዳጋች ነው። ይህ ዕውነታ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ስትራቴጂካዊነት ያጠናክራል።

2. የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች በሁሉም ዘርፍ ከመፈለጋቸው እና ረጅም የእሴት ሰንሰለትን መፍጠር የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ በውስን ሀብት ፊት የሚሰፋውን፣ የሚያድገውን እና የሚራቀቀውን እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ጤና (መዲሃኒት)፣ መጓጓዣ፣ መገናኛ፣ ቴክኖሎጂ፣ ደህንነት እና ከፍ ሲልም ሉአላዊነት በመሳሰሉት የሚገለጹ ፍላጎቶችን ማሟላት የሚቻለው በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ነው። በቴክኒካዊ ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪ የዚህ መሠረታዊ ሀብትን የማብዛት፣ የማሳደግ፣ እና የማራቀቅ አቅም የዘርፉ የቋሚ ግብአቶች ምርታማነት ከፍተኛ መሆን ነው። የአገራት የኢንዳስትሪያላይዜሽን ልምድ እንደሚያሳየው እንደ ግብርና ባሉ ዘርፎች አንድ ብር ዋጋ ያለው ተጨማሪ ምርት ለማምረት ቢያንስ 5 ብር ዋጋ ያለው ተጨማሪ ካፒታል ማሰማራት የሚያስፈልግ ሲሆን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አንድ ብር ዋጋ ያለው ተጨማሪ ምርት ለማምረት ከአንድ ብር ያልበለጠ ዋጋ ያለው ተጨማሪ ካፒታል ብቻ ማሰማራት ይበቃል። በሌላ መልኩ ከሌሎች ዘርፎች በተለየ ሁኔታ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምርትን ግብዓቶችን ቆጣቢ በሆነ መልኩ ከግብዓቶች ዕድገት ምጣኔ በላይ ማሳደግ ይቻላል (advantages of economies of scale and increasing returns to scale)። ለእንደዚህ ዓይነት ጠቃሚ የዘርፉ ባሕርይ መሠረታዊ ምክንያት የአምራች ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ - ገብ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት የተሳካ የአምራች ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት ስትራቴጂ የተሳካ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ስትራቴጂ ነው።

3. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን በክልሉ የማፋጠን ስትራቴጂን ምክንያታዊ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ነው። በ2014 የበጀት ዓመት ኢትዮጵያ ከውጭ ካስገባቻቸው 882 ቢሊዮን ብር ወይም 16 ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ውስጥ ከ68 በመቶ በላይ የሚሆነው ወጪ የወጣው ለአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ነው። ከዚህ 16 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የገቢ ንግድ ወጪ ከእቃዎች ወጪ ንግድ በተገኘ የውጭ ምንዛሪ የተሸፈነው 23 በመቶ ወይም 3.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነው። ከዚህ የወጪ ንግድ ግኝት ውስጥ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆነው ከግብርና ምርቶች ወጪ ንግድ ነው። እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመሳሰሉ ድንበር - ዘለል የአገልግሎት ዘርፎች የተገኘ የተጣራ የውጭ ምንዛሪ የገቢ ንግድ ወጪችንን የመሸፈን አቅም ወደ 26 በመቶ ብቻ ከፍ አድርጎታል። በአንጻሩ ከውጭ በግል ኃዋላ የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ የአገሪቷን የገቢ ንግድ ወጪ የመሸፈን አቅም በ39 በመቶ ጨምሮ 65 በመቶ አድርሶታል። ቀሪው የ35 በመቶ ጉድለት በውጭ ብድር፣ እርዳታ፣ እና ቀጥተኛ መዋዕለ - ንዋይ የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ መዋዕለ - ንዋይ የሸፈነው መጠን 1.4 በመቶ ብቻ ነው።

4. ስዕል ፲፩ - ፲፤ የአገር አቀፍ የገቢ ንግድ አሸፋፈን በምንጭ




5. ይህ ክፍተት እንደ ችግር ስንመለከተው በበሬ ጫንቃ ላይ በቆመ የኢኮኖሚ አቅም በሮቦት ኃይል የረቀቀ ፍላጎትን የማሟላት ዘይቤ የፈጠረው አገራዊ የዕዳ ጫና፣ ጥገኝነት፣ እና በተለያዩ ምክንያቶች የውጭ ድጋፍ ሲጓደል የሚፈጠረው የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት እና የኢኮኖሚ መንገራገጭ ሊያሳስብ ይገባል። ወደ ራስ አቅም መመለስም ማሕበረሰቡ ከለመደው ፍላጎት መውረድን እና የልማት ጥረቶች መስተጓጎልን ስለሚያስከትል ልናመልጠው ወደምንሸሸው የድህነት አረንቋ መውረድ ይሆናል። መፍትሄው ይህን ክፍተት እንደ ትልቅ አገራዊ የፍላጎት አቅም ቆጥሮ ይህን በመተካት ጀምሮ መዳረሻውን በዘርፉ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ባደረገ ስትራቴጂ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ማስፋፋት ሲሆን በውጤቱም ሰፊ የሥራ ዕድል፣ ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮነሚ ዕድገት ማስመዝገብ ይቻላል።

## የኢንዱስትሪ ልማት የሀብት መሠረት እና ዕድሎች

6. **ሰፊ የግብርና መሠረት ለኢንዳስትሪያለዊነት መነሻ አቅም ነው።** እንደ ምግብ፣ ጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ የቆዳ ውጤቶች የመሳሰሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች የግብርና ውጤቶችን በግብዓትነት ይጠቀማሉ። በዚህ ረገድ ክልሉ ሁሉንም ዓይነት የግብርና ምርቶች በስፋት ለማምረት ትልቅ አቅም አለው።

7. **ማዕድናት ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ልማት የማይተካ ሚና አላቸው።** እስከ አሁን በጥናት በተረጋገጠው መሠረት በክልሉ የሚገኙ ማዕድናት በዋናነት የኮንስትራክሽን፣ የኢንዱስትሪ እና የግብርና ማዕድናት በክልሉ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ሥነ - ምድር አወቃቀር ለሁሉም ዓይነት ማዕድናት መገኘነት አመቺ በመሆኑ እና ይህም ከሞላ ጎደል በጥናት በመረጋገጡ በርካታ የኮንስትራክሽን እና የኢንዱስትሪ ማዕድናት በአጎራባች ክልሎች መገኘታቸው ለጋራ ልማት የሀብት መሠረት ናቸው።

8. **ሰፊ የሰው ሀብት ትልቅ የቴክኖሎጂ አቅም ነው።** የኢትዮጵያ ከ፲፳ ሚሊዮን የሚልቅ ሕዝብ በገቢ አቅም ሲደገፍ ለኢንዱስትሪ ልማት ትልቅ ገበያ ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልል በአገሪቷ 2ኛው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለው ሲሆን ይህም በራሱ የገበያ ዕድል ይፈጥራል። ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ለኢንዱስትሪ ልማት የሚውል የሠራተኛ ኃይል በስፋት በማስገኘት ረገድ ተጨማሪ ዕድል ይፈጥራል። ነገር ግን ከኢንዱስትሪያላዊነት አኳያ የከፍተኛ ሕዝብ ቁጥር ከሁሉም የላቀው እምቅ አቅም የቴክኖሎጂ አቅም ነው። የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በባሕርይው ከመሠረታዊ የምግብ ማቀነባበሪያ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የብረታ ብረት፣ የማሽን እና የኬሚካል ምርቶች ይዘልቃል። ዘርፉ በየደረጃው የሚጠቀማቸው ግብዓቶችም ውስብስብ እና እንደየዘርፉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ናቸው። ሁሉም ሰው በአንድ ዘርፍ እኩል ተሰጥዖ ስለማይኖረው የበዛ ምርት እና የተራቀቀ ቴክኖሎጂ ትርጉም ያለው ቁጥር፣ ዕውቀት፣ እና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ይጠይቃል። የዚህ ዓይነቱን ጥቂቶች ብቻ የሚሳካላቸው የቴክኖሎጂ ዕውቀት ለበርካታ ንዑስ ዘርፎች በሚበቃ ደረጃ ማግኘት የሚቻለው ከብዙ ሕዝብ መካከል ነው። በዚህ ረገድ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ቁጥር በተነጻጻሪነት ከፍተኛ ቢሆንም እንደ ትልቅ አቅም ሊወሰድ የሚችለው በትምህርት በተለይም በሣይንስ እና ቴክኖሎጂ ሲታነጽ ነው።

9. **ሰፊ አገር፣ ሰፊ አህጉር፣ ሰፊ ቀጠና ለኢንዱስትሪያላዊነት ማደግ ከፍተኛ የጥሬ እቃ እና የገበያ አቅም ነው።** ኢንዱስትሪያላዊነት ሲታሰብ የጥሬ ዕቃ በቅርብ ርቀት ከመገኘት አስፈላጊነት በላይ ሰፊ ገበያ ይጠይቃል። እንደ ኬሚካል፣ ብረታ ብረት፣ የአረብ ብረት እና የመሳሰሉት የኢንዱስትሪ ምርቶች አዋጭነታቸው የሚመሠረተው በስፋት በማምረት (economies of scale) ነው። ለዚህም ከገበያ አንጻር ለሰፊ ክልል ከሚመጥኑት እስከ ሰፊ አገር፣ ሰፊ ቀጠና እና ሰፊ አህጉር የሚመጥኑ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ለማምረት ከክልል እስከ አህጉር ያለው የሕዝብ ብዛት ሀብት ነው። ይህን መሰል የገበያ አቅም ለመጠቀም መሠረተ ልማት እና የጋራ ልማት የፖሊሲ ማዕቀፎች መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው።

10. **ለቴክኖሎጂ ሽግግር አመቺ የሆነ የተሳሰረ ዓለም (ሉላዊነት) ለፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት አቅም ነው።** የኢንዱስትሪ ልማት ከየትኛውም ዘርፍ በበለጠ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ነው፤ የዘርፉ የማይነጥፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭነትም የሚመሠረተው ከዚሁ ባሕርይ ነው። የዓለም የቴክኖሎጂ ዓይነት እና ብዛት ሰፊ በሆነበት እንዲሁም አድማሱ ከፍ ባለበት ሁኔታ ቴክኖሎጂን ከመፍጠር ይልቅ ማሸጋገር የበለጠ አዋጭ ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ራሱ ቴክኖሎጂው በፈጠረው መደላድል አገራት ከመቼውም በበለጠ የተሳሰሩ በመሆናቸው ለቴክኖሎጂ ሽግግር አመቺ ነው።

11. **በቅርብ በኢንዱስትሪ እያደጉ ያሉ አገራት መኖር በዘርፉ ፈጣን ዕድገት በማምጣት ኢንዱስትሪያላዊነትን ለማረጋገጥ መልካም አጋጣሚ ነው።** የአገራት በኢኮኖሚ መበልጸግ በተለይም በኢንዱስትሪ መግፋት ከአገር አገር ተላላፊ እና የሚስተጋባ እንደሆነ ይታመናል። ኢንዱስትሪያላዊነት ከእንግሊዝ ወደ ጀርመን፣ ከዚያም ወደ ጃፓን፣ ቀጥሎም ወደ ደቡብ ኮሪያ፣ በኋላም ወደ ሌሎች የደቡብ ምሥራቅ ኤሲያ አገራት፣ በቅርቡም ወደ ቻይና ተስተጋብቷል። በኢንዱስትሪ ልማት የተሳካላቸው አገራት የረገጡትን ረግጦ፣ የጨበጡትን ጨብጦ በእነዚህ አገራት መንገድ ለማደግ ከአቅም እና ከነባራዊ ሁኔታዎች አንጻር ከቅርብ ርቀት መሆንን ይጠይቃል። ለዚህ አንዱ መሥፈርት ተደርጎ የሚወሰደው ልምድ ለመውሰድ እና ለማደግ የሚታትር አገር የነፍስ ወከፍ ገቢ ልምድ የሚወሰድበትን አገር የነፍስ ወከፍ ገቢ ቢያንስ 20 በመቶ ያህል መሆን ይኖርበታል። ከዚህ አንጻር እንደ ቻይና ያሉ በነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ብዙ ያልራቁ፣ ነገር ግን የዕድገት ግለታቸው ገና ያልበረደ አገራት መኖራቸው ከተሞክሯቸው ለመማር ትልቅ ዕድል ነው።

## የክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አፈጻጸም ትንተና

12. **ከ1998 ጀምሮ በነበሩት ሁለት አሥርት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አፈጻጸም ከአገር አቀፍ የዘርፉ የዕድገት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ውጤት የታየበት ነበር።** ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት የክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በዓመት በአማካይ በ19.9 በመቶ በማደግ ከክልል አቀፍ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ በ1998 ከነበረበት 1.5 በመቶ በ2016 የበጀት ዓመት 9.4 በመቶ ደርሷል። ይህ አፈጻጸም መነሻው አነስተኛ ከመሆኑ አንጻር መካከለኛ ቢሆንም፣ በተለይ ከአገር አቀፍ አማካይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ እመርታ የታየበት ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ የዘርፉ ተጨማሪ እሴት በተመሳሳይ ወቅት በ11.4 በመቶ በማደግ ከአገራዊ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻም በ2016 የበጀት ዓመት 6.7 በመቶ ላይ ተገድቧል። ከ2011 እስከ 2016 በነበሩት ስድስት ዓመታት የክልሉ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በአማካይ በ16.2 በመቶ በዓመት አድጓል። ይህ ምጣኔ ከቀዳሚዎቹ ዓመታት የዕድገት ምጣኔ በ4 የመቶኛ ነጥብ የቀነሰ ቢሆንም ከአገር አቀፍ አፈጻጸም ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ ነው። በተመሳሳይ ያለፉት ስድስት ዓመታት የዘርፉ አገር አቀፍ ተጨማሪ እሴት በ6.7 በመቶ ብቻ አድጓል።

13. **የክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት ፈጣን ቢሆንም ከመሠረቱ ከጥቅል ክልል አቀፍ ምርት ያለው ድርሻ ዝቅተኛ የነበረ በመሆኑ የግብርና ዘርፍ አፈጻጸም በተቀዛቀዘበት ወቅት እንኳ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነቱን ገና ከግብርና ዘርፍ አልተረከበም።** ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት ከተመዘገበው የ7.2 በመቶ የክልላዊ ጥቅል ምርት ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስተዋጽዖ ያደረገው 0.7 የመቶኛ ነጥብ ወይም የኢኮኖሚ ዕድገቱን 9.7 በመቶ ብቻ ነበር። በተመሳሳይ ወቅት የግብርና እና ተያያዥ ዘርፎች ከ7.2 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ 3.7 የመቶኛ ነጥብ ወይም የኢኮኖሚ ዕድገቱን 51.4 በመቶ አስተዋጽዖ ነበረው። ከ2011 እስከ 2016 በነበሩት ስድስት የበጀት ዓመታት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት ከክልሉ 4.9 በመቶ የጥቅል ምርት ዕድገት 1.1 የመቶኛ ነጥብ ወይም የኢከኖሚ ዕድገቱን 22.4 በመቶ አስተዋጽዖ አድርጓል። በተመሳሳይ ወቅት ግብርና ከ4.9 በመቶ የክልል አቀፍ ጥቅል ምርት ዕድገት ውስጥ 1.7 የመቶኛ ነጥብ ወይም የኢኮኖሚ ዕድገቱን 35 በመቶ አስተዋጽዖ አድርጓል።

14. ሠንጠረዥ 11-1፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት የዕድገት አፈጻጸም

| | 1998 - 2016 | | 2011 - 16 | | ከክልላዊ ምርት ድርሻ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕድገት | ምዝን ዕድገት | ዕድገት | ምዝን ዕድገት | 1998 | 2016 |
| **ኢንዱስትሪ** | **9.0** | **1.2** | **6.4** | **1.0** | **13.1** | **16.2** |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 19.9 | 0.7 | 16.2 | 1.1 | 1.5 | 9.4 |
| መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ | 36.2 | 0.3 | 19.3 | 0.5 | 0.2 | 4.5 |
| አነስተኛ ኢንዱስትሪ | 25.6 | 0.3 | 16.4 | 0.6 | 0.5 | 4.2 |
| የጎጆ ኢንዱስትሪ/ዕደ ጥበባት | 4.4 | 0.0 | 3.8 | 0.0 | 1.1 | 0.7 |
| ማዕድን እና ኳሪንግ | 10.3 | 0.0 | 8.3 | 0.0 | 0.1 | 0.1 |
| ኤሌክትሪክሲቲ እና ውሃ | 10.2 | 0.0 | 10.7 | 0.1 | 0.4 | 0.6 |
| ኮንስትራክሽን | 3.6 | 0.4 | -2.2 | -0.2 | 11.5 | 6.0 |
| **የክልላዊ ምርት ዕድገት** | **7.2** | **7.2** | **4.9** | **4.9** | **100.0** | **100.0** |

ምንጭ፤ የአብክመ የፕላንና ልማት ቢሮ ክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ መረጃ መሠረት በማድረግ የተሰላ

15. **ንዑስ ዘርፎቹ ከአቅም በታች የሚያመርቱ ሲሆን ይህ ክፍተት ለጊዜው ተግዳሮት፣ ችግሮቻቸው ተፈትተው በሙሉ አቅም ማምረት ሲቻል ደግሞ የዕድገት አቅም ይሆናል።** በ2015 የበጀት ዓመት የዋና ዋና አምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች አማካይ የማምረት አቅም 54.4 በመቶ ነው። ለዚህም ዝቅተኛ የማምረት አቅም የግብዓቶች እጥረት፣ የኃይል እጥረት፣ የመሠረተ-ልማት አለመሟለት እና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው። የግብዓት እጥረት በዘርፎች የእሴት ሰንሰለት ትስስር፣ የኃይል እጥረት ተጨማሪ የኃይል አቅም በማሻሻል፣ እንዲሁም የመሠረተ-ልማት እና የሰው ኃይል የክህሎት ችግሮች ሲፈቱ የንዑስ ዘርፎቹ ወደ ሙሉ አቅም መቃረብ ማስፋፊያ እና ተጨማሪ መዋዕለ-ንዋይን ሳይጨምር በዘርፉ ፈጣን እድገት ማስመዝገብ ይቻላል። የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የማምረት አቅም ከ2017 ጀምሮ እስከ 2022 ድረስ 85 በመቶ ማድረስ ከተቻለ፣ ምርት እና የወቅታዊ ግብዓቶች ወጪ (intermediate consumption) በተመሳሳይ ምጣኔ እንደሚያድጉ ታሳቢ በማድረግ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በዓመት በአማካይ በ8.2 በመቶ ማደግ ይችላል። ማስፋፊያዎች፣ የዘርፉ መዋዕለ-ንዋይ፣ እና የነገራት-ምርት ምርታማነት መጨመር የማምረት አቅምን በማሻሻል ከሚገኘው ዕድገት ጋር ተዳምረው የዘርፉ ተጨማሪ እሴት በአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ከተቀመጠው የ15.4 በመቶ በላይ ምጣኔ ማስመዝገብ ይቻላል።

16. ሠንጠረዥ 11-2፤ የ2015 የበጀት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች የማምረት አቅም (ከሙሉ አቅም በመቶኛ)

| ንዑስ ዘርፍ | ዕቅድ (በመቶኛ) | ክንውን (በመቶኛ) |
|---|---|---|
| ምግብ እና መጠጥ (አግሮ - ፕሮሰሲንግ) | 62 | 49.9 |
| ጨርቃጨርቅ እና አልባሳት | 65 | 51.2 |
| ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች | 57 | 55.3 |
| ኬሚካል እና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች | 65 | 57.5 |
| እንጨት እና ብረታ ብረት | 58.3 | 58.3 |
| **አማካይ** | **61.5** | **54.4** |

ምንጭ፤ የአብክመ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ

17. **የክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋቅር በሰው ኃይል ስምሪት፣ በካፒታል መጠን፣ እና በተጨማሪ እሴት ወደ መሠረታዊ የፍጆታ ሸቀጦች ያመዘነ ነው። ይህ ሁኔታ በመካከለኛ ጊዜ ከግብርና ዘርፍ ጋር ለሚኖር ትስስር እንደ መነሻ ጠቃሚ ቢሆንም ፈጣን እና የማይቀለበስ ቴክኖሎጂ-መር የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ወደሚያስችሉ የብረታ ብረት እና ማሽነሪ ንዑስ ዘርፎች ለመሸጋገር መሠረት መጣል እንዳለበት አመላካች ነው።** ብረታ ብረት ያልሆኑ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች፣ የምግብ ምርቶች፣ ጨርቃጨርቅ እና አልባሳት፣ መጠጥ፣ እንዲሁም ኬሚካል እና ተያያዥ ምርቶች በሰው ኃይል ስምሪት ከ12.9 በመቶ እስከ 23.6 በመቶ የሚደርስ ድርሻ ያላቸው ሲሆን እሴት በመጨመር ረገድ 82.4 በመቶ የሚሆነው የመጠጥ ንዑስ ዘርፍ ድርሻ ነው። በአንጻሩ የብረታ ብረት፣ ማሽን እና የብረታ ብረት ዕቃዎች፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮኒክስ ንዑስ ዘርፎች ከሰው ኃይል ቅጥር እና ከተጨማሪ ዕሴት ያላቸው ድርሻ፣ እንደ ቅደም ተከተሉ፣ 5 በመቶ እና 0.7 በመቶ ነው።

18. ሠንጠረዥ 11-3፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች መዋቅር በሰው ኃይል ስምሪት እና ተጨማሪ እሴት ድርሻ

| | ድርሻ በመቶኛ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ከሰው ኃይል | ከድርጅቶች ብዛት | ከምርት | ከተጨማሪ እሴት |
| ምግብ | 17.4 | 28.6 | 12.7 | 0.6 |
| መጠጥ | 12.9 | 5.5 | 61.8 | 82.4 |
| ጨርቃጨርቅ እና አልባሳት | 17.4 | 8.1 | 4.0 | 0.5 |
| የቆዳ ውጤቶች | 0.1 | 0.2 | 0.0 | 0.0 |
| የእንጨት እና ተያያዥ ምርቶች | 10.1 | 18.6 | 4.5 | 2.1 |
| ሌሎች ብረታ ብረት ያልሆኑ ዕቃዎች | 23.6 | 25.5 | 1.7 | -0.7 |
| ኬሚካል እና ኬሚካል ነክ ምርቶች | 12.9 | 6.5 | 12.0 | 14.3 |
| ብረታ ብረት እና የአረብ ብረት | 4.2 | 4.6 | 2.6 | 0.5 |
| ማሽን እና የብረታ ብረት እቃዎች | 0.3 | 0.7 | 0.3 | 0.1 |
| ኤሌክትሪክ እቃዎች እና ኤሌክትሮኒክስ | 0.5 | 0.7 | 0.3 | 0.1 |
| ማጓጓዣ | - | - | - | - |
| ሌሎች | 0.6 | 0.9 | 0.2 | 0.2 |
| **ድምር** | **100.0** | **100.0** | **100.0** | **100.0** |

ምንጭ፤ የአብክመ የፕላንና ልማት ቢሮ ክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ መረጃ መሠረት በማድረግ የተሰላ

19. የመጠጥ ንዑስ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአማካይ የሰው ኃይል ቅጥር፣ በምርት፣ እና በእሴት ከፍተኛ ድርሻ አለው። የጨርቃጨርቅ ንዑስ ዘርፍ በሰው ኃይል ቅጥር ከመጠጥ ንዑስ ዘርፍ ቀጥሎ የተሻለ የድርጅት መጠን ቢኖረውም እሴት በመጨመር ረገድ ዝቅተኛ ነው።

20. ሠንጠረዥ 11-4፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች የድርጅቶች መጠን (firm size) በሰው ኃይል ቅጥር እና ምርት መጠን

| | የሰው ኃይል በድርጅት | ምርት | | እሴት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በድርጅት (ሺህ ብር) | በሰው ኃይል (በሺህ ብር) | በድርጅት (በሺህ ብር) | በሰው ኃይል (በሺህ ብር) |
| ምግብ | 38.5 | 32,472 | 844 | 693 | 18 |
| መጠጥ | 146.7 | 818,718 | 5,582 | 524,340 | 3,575 |
| ጨርቃጨርቅ እና አልባሳት | 135.3 | 36,111 | 267 | 2,075 | 15 |
| የቆዳ ውጤቶች | 27.0 | 9,571 | 354 | 8,902 | 330 |
| የእንጨት እና ተያያዥ ምርቶች | 34.4 | 17,848 | 519 | 3,954 | 115 |
| ሌሎች ብረታ ብረት ያልሆኑ ዕቃዎች | 58.5 | 4,900 | 84 | (974) | (17) |
| ኬሚካል እና ኬሚካል ነክ ምርቶች | 126.3 | 136,080 | 1,077 | 77,973 | 617 |
| ብረት እና የአረብ ብረት | 58.2 | 41,143 | 707 | 4,066 | 70 |
| ማሽን እና የብረታ ብረት እቃዎች | 23.8 | 27,020 | 1,138 | 2,562 | 108 |
| ኤሌክትሪክ እቃዎች እና ኤሌክትሮኒክስ | 39.8 | 27,810 | 700 | 3,062 | 77 |
| መጓጓዥያ | - | - | - | - | - |
| ሌሎች | 41.8 | 12,994 | 311 | 7,093 | 170 |
| **አማካይ** | **63.2** | **73,335** | **1,161** | **35,224** | **558** |

ምንጭ፤ የአብክመ የፕላንና ልማት ቢሮ ክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ መረጃ መሠረት በማድረግ የተሰላ

21. የኬሚካል ንዑስ ዘርፍ ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሰው ኃይል ስምሪት ከመጠጥ እና ጨርቃጨርቅ ቀጥሎ፣ በምርት እና በተጨማሪ እሴት ከመጠጥ ቀጥሎ ከፍተኛ መጠን ያለው ሲሆን የምርት ዓይነቶቹ ለሰፊ ኢንዱስትሪ ልማት መሠረት የሚጥሉ እና ለዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ እንደ ኮስቲክ ሶዳ፣ ስታርች እና የመሳሰሉት ሳይሆኑ በአብዛኛው ለመጨረሻ ፍጆታ የሚውሉ የጽዳት አላቂ ምርቶች፣ እንዲሁም ቀለም ናቸው።

22. **የአማራ ብሔራዊ ክልል የመካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በድርጅቶች ብዛት በ2009 በነበረው ድርሻ ከፈርኒቸር በስተቀር በሁሉም ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች እና በአጠቃላይ የአዲስ አበባ የከተማ መስተዳድርን እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልልን በርቀት ይከተላል።** የበክልሉ በ2009 የዳሰሳ ጥናት ወቅት የነበሩ የመካከለኛ እና ከፍተኛ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ብዛት 489 የነበሩ ሲሆን ይህ አኀዝ ከአጠቃላይ አገራዊ የዘርፉ ድርጅቶች ብዛት 13.5 በመቶ ነበር። በ2011 በተደረገ ተመሳሳይ ጥናትም የክልሉ የዘርፉ የድርጅቶች ብዛት 14 በመቶ ነበር። በተመሳሳይ ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የዘርፉ

የድርጅቶች ብዛት አገር አቀፍ ድርሻ፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው፣ 39 በመቶ እና 35 በመቶ ነበር። ክልሉ በአንጻራዊነት የተሻለ ድርሻ የወሰደባቸው ንዑስ ዘርፎች የቤት ቁሳቁስ (27.6 በመቶ)፣ ብረታ ብረት ያልሆኑ ማለትም የተጠረበ ዲንጋይ፣ ጂሶ፣ ሴራሚክ፣ የመሳሰሉ የግንባታ እቃዎች (18.3 በመቶ)፣ ምግብ እና መጠጥ (15.9 በመቶ)፣ እንዲሁም የተፈበረኩ የብረታ ብረት ውጤቶች (13.5 በመቶ) ነበሩ። በአንጻሩ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ ልማት መሠረት በሆኑ እንደ ብረት እና የአረብ ብረት፣ ማሽን እና መሣሪያዎች፣ እንዲሁም ኬሚካሎች ከ3 በመቶ በታች ድርሻ ነበረው።

23. ሠንጠረዥ 11-5፡ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአገራዊ የተቋማት ብዛት ያለው ድርሻ

| | አማራ | አዲስ አበባ | ኦሮሚያ | ደ. ሕዝቦች | ትግራይ | ሌሎች | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምግብ እና መጠጥ | 15.9 | 27.3 | 31.9 | 10.2 | 6.6 | 8.1 | 100.0 |
| ጨርቃ ጨርቅ | 4.8 | 86.6 | 5.5 | 0.3 | 1.4 | 1.4 | 100.0 |
| አልባሳት | 5.9 | 62.7 | 25.5 | 2.0 | 0.0 | 3.9 | 100.0 |
| የቆዳ ውጤቶች | 4.4 | 76.7 | 13.8 | 0.0 | 4.4 | 0.6 | 100.0 |
| የእንጨት ሥራ | 6.6 | 47.4 | 25.0 | 17.1 | 0.0 | 3.9 | 100.0 |
| ወረቀት | 2.2 | 59.1 | 20.4 | 3.6 | 2.9 | 11.7 | 100.0 |
| ኬሚካል | 2.7 | 47.3 | 42.6 | 0.7 | 5.4 | 1.4 | 100.0 |
| ጎማ እና ፕላስቲክ | 3.8 | 48.7 | 39.8 | 1.1 | 0.8 | 5.7 | 100.0 |
| ለሎች ብረታ ብረት ያልሆኑ | 18.3 | 20.3 | 27.6 | 11.7 | 15.3 | 6.8 | 100.0 |
| ብረት እና የአረብ ብረት | 1.2 | 58.0 | 14.8 | 0.0 | 22.2 | 3.7 | 100.0 |
| የተፈበረኩ ብረታ ብረት | 13.5 | 43.9 | 18.8 | 5.8 | 10.8 | 7.2 | 100.0 |
| ማሽን እና መሣሪያዎች | 2.7 | 56.8 | 29.7 | 5.4 | 5.4 | 0.0 | 100.0 |
| ማጓጓዥያ ዕቃዎች | 0.0 | 42.9 | 35.7 | 0.0 | 21.4 | 0.0 | 100.0 |
| የቤት ቁሳቁስ (ፈርኒቸር) | 27.6 | 23.2 | 22.4 | 16.8 | 4.2 | 5.8 | 100.0 |
| ድምር | **13.5** | **39.4** | **26.0** | **8.2** | **7.0** | **5.9** | 100.0 |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ (የአሁኑ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት) የከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ዳሰሳ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ

24. **በክልሉ የተሰማሩ የአምራች ኢንዱስትሪ ተቋማት በሰው ኃይል ቅጥር እና በካፒታል አቅም በንጽጽር ከአገራዊ አማካይ ያነሱ ናቸው።** የክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የድርጅቶች የሰው ኃይል ስምሪት እና የካፒታል መጠን አገራዊ ድርሻ ከድርጅቶች ብዛት አገራዊ ድርሻ ያነሰ ነው። በክልሉ የሚገኙ የአምራች ኢንዱስትሪ ተቋማት ብዛት ከአገር አቀፍ ብዛት ያለው ድርሻ 13.5 በመቶ ሲሆን፣ የሰው ኃይል እና የካፒታል መጠን ከአገር አቀፍ ያለው ድርሻ፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው፣ 7.8 በመቶ፣ እና 5.3 በመቶ ነው። በክልሉ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች በአማካይ 47 ሰው ሲቀጥሩ፣ በአንጻሩ የትግራይ ብሔራዊ ክልል፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል እንደ ቅድም ተከተላቸው 133 ሰዎች፣ 86 ሰዎች እና 85 ሰዎችን ይቀጥራሉ። የአገር አቀፍ የዘርፉ የሰው ኃይል ስምሪት በድርጅት በአማካይ 82 ሰው ነው። በካፒታል ደረጃም በአማራ ብሔራዊ ክልል አማካይ የድርጅት ካፒታል መጠን 19.97 ሚሊዮን ሲሆን፣ አገራዊ አማካይ የካፒታል መጠን በድርጅት 47 ሚሊዮን ነው። በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በ117.6 ሚሊዮን ብር በድርጅት ይመራል። ይህ ሁኔታ በድርጅቶች ምርት እና ተጨማሪ እሴት ላይ ተመሳሳይ ሥሪት አለው።

25. ሠንጠረዥ 11-6፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ከአገራዊ አቅም ንጽጽር

| | አማራ | አዲስ አበባ | ኦሮሚያ | ደ. ሕዝቦች | ትግራይ | ሌሎች | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከድርጅቶች ብዛት | 13.5 | 39.5 | 26.0 | 8.2 | 7.0 | 5.7 | 100.0 |
| ከሰው ኃይል ብዛት | 7.8 | 41.2 | 26.8 | 7.6 | 11.4 | 5.3 | 100.0 |
| ከቋሚ ካፒታል | 5.3 | 19.0 | 68.1 | 2.4 | 3.1 | 2.1 | 100.0 |
| ከኢንቨስትመንት | 7.9 | 35.0 | 48.5 | 3.4 | 4.4 | 0.8 | 100.0 |
| ከምርት መጠን | 7.0 | 32.2 | 43.2 | 4.8 | 6.4 | 6.5 | 100.0 |
| ከተጨማሪ እሴት | 5.2 | 32.8 | 47.4 | 3.2 | 5.2 | 6.3 | 100.0 |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ (የአሁኑ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት) የከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ዳሰሳ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ

26. በካፒታል ስርጸት (ካፒታል በነፍስ ወከፍ የሰው ኃይል) የአማራ ብሔራዊ ክልል ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ቀጥሎ ከፍተኛ ነው። የክልሉ ካፒታል በነፍስ ወከፍ የሰው ኃይል 334 ሺህ ብር ሲሆን፣ የኦሮሚያ ብሔራዊ

ክልል 1.2 ሚሊዮን ብር፣ እና አገራዊ አማካይ ደግሞ 484 ሺህ ብር ነው። የክልሉ የ1.8 ካፒታል - እሴት ጥምርታ ወይም የካፒታል ቅልጥፍና መለኪያ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮ ጋር የሚቀራረብ ነው።

27. ሠንጠረዥ 11-7፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ ምርታማነት ከአገራዊ አቅም ንጽጽር

| | አማራ | አዲስ አበባ | ኦሮሚያ | ደ. ሕዝቦች | ትግራይ | ሌሎች | አገራዊ አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምርት በድርጅት (ሺህ ብር) | 23,659 | 37,386 | 76,054 | 26,638 | 41,945 | 51,593 | 45,848 |
| እሴት በድርጅት | 8,541 | 18,235 | 40,008 | 8,595 | 16,150 | 23,922 | 21,981 |
| የሰው ኃይል በድርጅት | 47 | 86 | 85 | 76 | 133 | 76 | 82 |
| ካፒታል በድርጅት(ሺህ ብር) | 19,972 | 25,510 | 117,615 | 14,554 | 22,244 | 15,453 | 47,024 |
| ካፒታል በሰው ኃይል (ሺህ ብር) | 334 | 223 | 1,232 | 152 | 133 | 190 | 484 |
| ምርት በሰው ኃይል (ሺህ ብር) | 500 | 436 | 899 | 351 | 315 | 678 | 557 |
| እሴት በሰው ኃይል (ሺህ ብር) | 181 | 213 | 473 | 113 | 121 | 315 | 267 |
| ምርት በካፒታል | 1.5 | 2.0 | 0.7 | 2.3 | 2.4 | 3.6 | 1.2 |
| እሴት በካፒታል | 0.5 | 1.0 | 0.4 | 0.7 | 0.9 | 1.7 | 0.6 |
| ካፒታል-እሴት ጥምርታ | 1.8 | 1.1 | 2.6 | 1.3 | 1.1 | 0.6 | 1.8 |
| ምንዳዕ በሰው ኃይል (ሺህ ብር) | 36.6 | 41.5 | 57.2 | 17.4 | 30.2 | 29.1 | 41.6 |
| እሴት -ምንዳዕ | 4.9 | 5.1 | 8.3 | 6.5 | 4.0 | 10.8 | 6.4 |

*ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ (የአሁኑ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት) የከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ዳሰሳ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ*

28. **የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አፈጻጸም በአገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ ቢያንስ ከክልሉ የሕዝብ ብዛት፣ እና ከሀብት መሠረቱ አንጻር በአሉታዊነት የሚገለጽ ሰፊ ልዩነት የተስተዋለ ቢሆንም እንደ አገር ኢትዮጵያ በዘርፉ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የዓለም አገራት አንዷ ናት።** በኢንዱስትሪ ልማት አሸጋጋሪነት የዓለም የብልጽግና አድማስ ላይ ከሚገኙ አገራት መካከል የአሥሩ አገራት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርታቸው በአማካይ 24 በመቶ አካባቢ ሲሆን ኢትዮጵያ ከኤርትራ መገንጠል በኋላ ያስመዘገበችው ከፍተኛው የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ 7.1 በመቶ ብቻ ነው።

29. ከዚህም በላይ የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ አነስተኛ መሆን የዘርፉ መዋቅር በትክክለኛ አቅጣጫ ላይ ስለመሆኑ ለመበየን ባያስችልም፣ ከአገር አቀፍ መዋቅሩ ጋር ሲነጻጸር የአማራ ብሔራዊ ክልል የዘርፉ መዋቅር ከወዲሁ መቃኘት እንዳለበት የዓለም አገራት ተሞክሮ ያመላክታል። በሠንጠረዥ 10 -8 ማስተዋል እንደሚቻለው በዓለም ላይ ኢንዱስትሪያላዊነት ወደ የማይቀለበስ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ብልጽግና ያሻገራቸው፣ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአገራዊ ምርታቸው ነበረው ድርሻ ከፍተኛ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ያተኮሩባቸው ንዑስ ዘርፎች ዓይነት እና ስብጥር ነው። በአጠቃላይ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከአገራዊ ምርታቸው በአማካይ ከ24 እስከ 26 በመቶ ከደረሰባቸው አገራት መካከል ከምግብ እና መጠጦች፣ እንዲሁም ከጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ይልቅ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የተራቀቁ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ በተለይም ማሽነሪ እና ብረታ ብረት እንዲሁም ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ላይ ያተኮሩት ናቸው።

30. ሠንጠረዥ 11-8፤ የኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋቅር ከዋና ዋና የዓለም አገራት መዋቅር ጋር ያለው ንጽጽር

| | የአምራች ኢንዱስትሪ ድርሻ ከአገራዊ ምርት | | የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ድርሻ ከአምራች ኢንዱስትሪ በመቶኛ (2013)* | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መረጃ ከተያዘበት ከፍተኛው | 2013 | መካከለኛ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ | ማሽነሪ እና ትራንስፖርት | ኬሚካል | ጨርቃጨርቅ | ምግብ እና መጠጥ | ሌሎች | የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2013 የዶላር የመግዛት አቅም |
| **ኢትዮጵያ** | **7.1** | **4.6** | **16.1** | **5.5** | **10.6** | **10** | **36.6** | **37.3** | **2,628** |
| ሲንጋፖር | 27.1 | 20.3 | 81.8 | 61.5 | 20.0 | 0.1 | 3.6 | 14.8 | 131,864 |
| አየርላንድ | 38.0 | 35.0 | 54.4 | 0.2 | 42.7 | 0.2 | 5.3 | 51.7 | 114,121 |
| ስዊዘርላንድ | 19.8 | 19.1 | 68.0 | 28.8 | 36.7 | 0.6 | 7.3 | 26.6 | 81,603 |
| ደንማርክ | 18.1 | 12.5 | 56.7 | 26.2 | 26.0 | 1.1 | 12.3 | 34.4 | 69,879 |
| ኔዘርላንድስ | 23 | 11.1 | 52.5 | 34.8 | 15.7 | 1.6 | 16.3 | 31.7 | 67,693 |
| ቤልጂየም | 18.4 | 12 | 53.1 | 15.1 | 34.1 | 2.1 | 16.9 | 31.8 | 62,123 |
| ጀርመን | 24.8 | 18.9 | 60.6 | 40.3 | 10.9 | 1.1 | 8.2 | 39.5 | 61,940 |
| ፈረንሳይ | 22.7 | 9 | 51.7 | 30.8 | 15.6 | 2.6 | 18.8 | 32.7 | 53,835 |
| ደ. ኮሪያ | 28.2 | 25.5 | 63.6 | 48.2 | 11.8 | 2.9 | 6.7 | 30.5 | 48,571 |
| ጃፓን | 23.5 | 20.9 | 56.1 | 42.7 | 11.9 | 1.5 | 13.5 | 30.4 | 44,549 |
| **አማካይ** | **24.4** | **18.4** | **59.9** | **32.9** | **23.0** | **1.4** | **10.9** | **36.7** | **73,618** |
| ቻይና | 32.5 | 27.5 | 41.5 | 24.5 | 10.8 | 10 | 11.8 | 42.8 | 20,407 |
| ቦትስዋና | 11.6 | 5.2 | 28.0 | 17.6 | 11.1 | 5.5 | 28.1 | 37.7 | 16,664 |
| ደ. አፍሪካ | 24.8 | 12.9 | 24.0 | 14.6 | 7.0 | 1.8 | 22.3 | 54.4 | 14,173 |
| ኢንዶኔዥያ | 32.0 | 19.2 | 30.1 | 13.2 | 12.2 | 12.9 | 28.9 | 35.6 | 12,897 |
| **አማካይ** | **25.2** | **16.2** | **30.9** | **17.5** | **10.0** | **7.6** | **22.8** | **42.6** | **16,035** |
| ባንግላዴሽ | 22.3 | 21.2 | 7.8 | 3.6 | 3.0 | 56.8 | 15.4 | 21.1 | 7,366 |
| ናይጀሪያ | 21.1 | 14.6 | 33.4 | 7.0 | 25.5 | 11 | 30.0 | 25.8 | 5,624 |
| ዛምቢያ | 33.3 | 8.3 | 9.7 | 5.0 | 8.7 | 1.1 | 30.9 | 58.3 | 3,527 |
| ዚምባብዌ | 26.9 | 12.4 | 9.6 | 1.3 | 6.5 | 2.8 | 65.4 | 24.0 | 3,276 |
| **አማካይ** | **25.9** | **14.1** | **15.1** | **4.2** | **11.0** | **17.9** | **35.4** | **32.3** | **4,948** |

ምንጭ፤ የዓለም ባንክ ድረ-ገጽ የአገራት መረጃዎች፣ 2023

## የክልሉ የሃያ አምሥት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት አቅጣጫ እንደ መነሻ

## ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ

31. የአማራ ብሔራዊ ክልል የሃያ አምሥት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ዋና ዓላማ በዘርፉ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት እና ተወዳዳሪነት ሲሆን በዚህም በተሳካ የኢንዱስትሪ ልማት የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን ማረጋገጥ ነው። በስትራቴጂ ደረጃ በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት ግብዓታቸው በአገር ውስጥ በተለይም ከግብርናው እና ከማዕድን ዘርፎች ሊገኙ የሚችሉ መሠረታዊ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በመተካት፣ በቀጣዮቹ ተከታታይ አራት የአምሥት ዓመት ዕቅድ ዘመናት የከፍተኛ ኢንዱስትሪ እና ኬሚካል ልማት ማረጋገጥ ነው። የምግብ፣ የመጠጥ፣ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት፣ የቆዳ እና የጫማ፣ የእንጨት፣ እንዲሁም የግንባታ እና ተያያዥ ብረታ-ብረት ያልሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ልማት በአብዛኛው የአገር ውስጥ የአላቂ እና ቋሚ የፍጆታ ዕቃዎች ፍላጎትን በአገር ውስጥ ምርት ለማሟላት፣ እንዲሁም ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታስበው የሚተገበሩ ይሆናል። ብረታ ብረት፣ እና የኬሚካል ኢንዱስትሪዎችን መሠረት የሚያድርጉ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማቶች ለአጠቃላይ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ እድገት ለመፋጠን እና መዋቅራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ የሚተገበሩ ናቸው።

32. ለዘመናት የቆየ የኢንዳስትሪያላይዜሽን ስትራቴጂ ክርክር የባለ ብዙ ዘርፍ የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ (balanced growth) እና ጥቂት የተመረጡ ኢንዱስትሪ ዘርፎች (unbalanced growth) ስትራቴጂ የመተግበር ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው ስትራቴጂ ጽንሰ-ሃሳብ የተመሠረተው የኢንዱስትሪ ዘርፎች በባሕርያቸው አንዱ በግብዓት ሌላው በፍላጎት የተሳሰሩ ስለሆነ የተውሰኑ ዘርፎች ላይ ብቻ ማተኮር በግብዓት ወይም በፍላጎት ወይም በሁለቱም እጥረት ምክንያት ይቆማሉ የሚል ነው። የወጭ ንግድ የፍላጎት እጥረትን ሊተካ፣ የገቢ ንግድ ደግሞ

የግብዓት እጥረትን ሊሸፍን እንደሚችል እንደመከራከሪያ ሊቀርብ ቢችልም የተመጣጠነ እድገት ደጋፊዎች የታዳጊ አገራት ምርት በአብዛኛው ከግብርና የሚገኝ ስለሆነ በተፈለገው መጠን ወጪ ንግድን መሸፈን እንደማይቻል እና የገቢ ንግድም ቀድሞውንም የችግር አካል የሆነውን ንግድ ሚዛን የባሰ በማዛባት በቂ ግብዓት ማስገባት እንዳይቻል ሊያደርግ ይችላል በሚል ያጣጥሉታል።

33. የሁለተኛው ስትራቴጂ ጽንሰ - ሃሳብ ደግሞ ከአገራት ተሞክሮ፣ እንዲሁም ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ከፋይናንስ፣ እና ከሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረቶች በመነሳት በተመጣጠነ ልማት እሳቤ በሁሉም የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ልማት መጀመር እንደሚያስቸግር ያወሳል። በታሪክ ረገድ የኢኮኖሚ ልማት እድገት የተሳካላቸው አገራት የኢንዱስትሪ እድገታቸውን የመሩት ከሌላው ፈጥነው የሚያድጉ ጥቂት ዘርፎች ብቻ እንደነበሩ፣ በተለይም በእንግሊዝ፣ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ፤ በአሜሪካ የባቡር መንገድ፣ በጃፓን፣ ግብርና፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ እና ብረታ ብረት፤ በስዊድን፣ የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስተሪ ፈጥኖ ማደግን ለአብነት ያህል ማንሳት ይቻላል። ከሀብት እጥረት አኳያ አንድ አገር በሁሉም ዓይነት የኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋዕለ-ንዋይ ለማፍሰስ በቂ የፋይናንስ እና የሰለጠነ የማናጀሪያል እንዲሁም የዳበረ ተሰጥዖ እጥረት ስለሚገድብ ከቋሚ ግብዓቶች ማደግ ጋር ምርትን የማሳደግ እና ለበርካታ ዘርፎች ተደራሽ የመሆን አቅም (increasing returns to scale and economices of scale) ያላቸውን እንደ ባቡር መንገድ፣ መንገድ፣ እና የተፋሰስ መስኖ ልማቶችን የመሳሰሉት ላይ ማተኮር የእነዚህን ዘርፎች መልማት ተከትለው ወደ ልማት ለሚገቡ ዘርፎች በር ከፋች እንደሚሆን ንድፈ-ሃሳቡ ይተነትናል። በተለይም በመንግሥትም ሆነ በግሉ ዘርፍ ውስን የአንተርፕሪነራል እና ውሳኔ የመስጠት ማናጀሪያል አቅም ውስንነት ስለሚያጋጥም በሁሉም ዘርፎች ላይ በአንዴ መሠማራት ይህን ውስን አቅም በስፋት ከመበታተን ይልቅ ለተሻለ ውጤታማነት በጥቂት ዘርፎች ላይ በማሰማራት በሂደት እነዚህን አቅሞች መገንባት የበለጠ አዋጭ እንስለሚሆን ያትታል።

34. ከኢትዮጵያ ልምድ አንጻር የግብዓቶች እጥረት በተለይ በንጉሱ ዘመን በመጀመሪያው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ (1942 - 1946) ወቅት ለኢንዱስትሪ ልማት ግቦች ከግብ በታች ለተስተዋለ አፈጻጸም አንዱ ዋና ምክንያት ነበር። በእቅዱ የመጨረሻ ዓመት ማለትም በ1946 የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የእንጨት፣ እንዲሁም የግንባታ እና ብረታ ብረት ያልሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ያልተጣራ ተጨማሪ እሴት ከ72 በመቶ እስከ 225 በመቶ አፈጻጸም የነበራቸው ሲሆን የብረታ ብረት፣ የኬሚካል፣ እና የቆዳ ውጤቶች ምርት ከምንም እስከ 33 በመቶ አፈጻጸም ብቻ ነበራቸው። የተሻለ አፈጻጸም የነበራቸው ንዑስ ዘርፎች እያደገ የመጣውን የፍጆታ ፍላጎት፣ ይህን ፍላጎት ለማሟላት የተሰጠው ትኩረት፣ እና ለእነዚህ ምርቶች ግብዓት የሚሆን ጥሬ እቃ ከግብርናው እና ከደን ዘርፎች በቀላሉ ማግኘት ስለተቻለ ነው። በሌላ በኩል ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር መሳካት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው የተጠበቁት የብረታ ብረት እና የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ዝቅተኛ አፈጻጸም እና ሙሉ በሙሉ አለመጀመር ምክንያት በጥሬ ዕቃ፣ በኃይል፣ በፋይናንስ፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ እና በዘርፉ የአንተርፐረነርሺፕ እጥረቶች ነው።

35. ከዚህ ጋር ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ሁሉንም ዓይነት ኢንዱስትሪዎች በአንዴ ጀምሮ ለማሳካት ከሀብት እስከ አቅም የሚደርስ ውስንነት ስለሚኖር፣ በአንድ የመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ ወቅት የተወሰኑ ዘርፎች ላይ በማተኮር አድምቶ መሥራት፣ እና በተመሳሳይ ጊዜ ከፍተኛ የካፒታል፣ የቴክኖሎጂ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለሚጠይቁ ስትራቴጂካዊ ዘርፎች ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በሌላ በኩል በአገራችን የረጅም የልማት ዕቅድ ታሪክ ለወሳኝ እና ስትራቴጂካዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት መሠረተ-ልማቶች ተገንብተው እያለ የግሉ ዘርፍ ውስን ሀብትን ወደ እነዚህ ዘርፎች ልማት ከማዋል ይልቅ የአጭር ጊዜ አዋጭነታቸው ወደ የተረጋገጠው የሕንጻ ግንባታ እና ሆቴሎች ሲያውለው ተስተውሏል። ሁለቱንም ጉዳዮች ለማስታረቅ ፈጥነው በሚደርሱ የዘርፍ ትስስሮች በመጀመር እና ለዘርፎች ትስስር ወሳኝ ሆነው ሳለ ግብዓታቸው በቴክኖሎጂ በፋይናንስ አቅም ውስንነት ምክንያት በአገር ውስጥ ሊመረቱ የማይችሉትን ግብዓታቸውን ከውጭ በማስገባት የዘርፎቹን ልማት መጀመር፣ በሂደትም በተጠና የጊዜ ሰሌዳ በዘርፎች ትስስር ውስጥ የጎደሉትን እየሞሉ እና ትስስሩን እያጠናከሩ መሄድ የተሻለ አማራጭ ነው።

36. የአምራች ኢንዱስትሪ እንደ መነሻ የግበርና ዘርፍ ውጤቶችን በግብዓትነት በሚጠቀምባቸው ዘርፎች የሚያተኩረው በሦስት ዋና ምክንያቶች ነው፤ አንደኛው የአገር ውስጥ ግብዓትን በመጠቀም ረገድ ቀዳሚው የግብርና ምርት ነው፤ ሁለተኛው ምክንያት የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ ያስችላል፤ ሦስተኛ፣ በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎች (አርሶ አደሮች) ገቢያቸው ሲጨምር ለኢንዱስትሪ ምርቶች ያላቸው ፍላጎት አብሮ ስለሚጨምር ተጨማሪ የፍላጎት ምንጭ ይሆናሉ።

37. በምግብ ነክ የኢንዱስትሪ ምርቶች ረገድ እንደ ምግብ ዘይት፣ ፓስታ እና ማካሮኒ፣ አልሚ ምግቦች፣ ስኳር፣ የተሰናዱ ቅመማ ቅመሞች፣ የታሸጉ ፍራፍሬ እና የፍራፍሬ ጭማቂዎች፣ የታሸጉ የአትክልት ዓይነቶች፣ እና ለመሳሰሉት ምርቶች ከቅባት ዕህሎች እስከ ሸንኮራ አገዳ ያሉ በቂ ግብዓቶች የሚጠበቁት ከግብርናው ዘርፍ ነው። የበቆሎ እና የሸንኮራ አገዳ ምርቶች የግብርና ምርቶች ከምግብነት በላይ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ሞላሰስ፣ ስታርች፣ እና ኢታኖል ለመሳሰሉ ምርቶች ግብዓት ናቸው።

38. የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት የገቢ ንግድ በመተካት እና ከፍተኛ የሥራ እድል በመፍጠር አቅሙ አንዱ የትኩረት መስክ ነው። የግብርና ዘርፍ ለአዳዲስ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች በቂ የጥጥ፣ የተልባ፣ እና የሱፍ ምርት ማስገኘት ይጠበቅበታል። ምርት ሳይበላሽ ለማሸግ እና ተቀባይነቱንም ከፍ ለማድረግ የሚያገለግሉ የቃጫ፣ እና የገመድ ምርቶች ግብዓት የሚጠበቀው ከግብርና እና ተያያዥ ዘርፎች ነው።

39. የአገር ውስጥ እና የወጪ ገበያን ታሳቢ ያደረገ የእንስሳት እርድ ቄራዎች በማስፋፋት የከብት፣ እንደ የአካባቢው ሥነ ምህዳር አመችነትም የፍየል እና የበግ ርባታን በተጠና መልክ በስፋት በማስጀመር፣ በውጤቱም ቆዳ ሳይበላሽ ጥቅም ላይ እንዲውል የጫማ፣ እና ተያያዥ የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎችን በመክፈት የዘርፍ ትስስር እንዲጠናከር ማድረግ ይቻላል። የግብርና ዘርፍ ከአምራች ኢንዱስትሪው እያደገ የሚመጣውን ፍላጎት ለማሟላት ሜካናይዜሽን ያስፈልገዋል። ይህ በግብርናው ዘርፍ ዕቅድ ላይ የተንጸባረቀ ጉዳይ ነው። ነገር ግን የኢንዱስትሪው ዘርፍ በበኩሉ ከቀላል የተሻሻሉ የግብርና መሣሪያዎች እስከ ከባድ የግብርና ማሽነሪዎች (ትራክተር፣ ኮምባይነር)፣ እና ማዳበሪያ፣ የእንስሳት መዲሃኒት፣ የመሳሰሉት ምርቶችን ማምረት ይጠበቅበታል። ከፍተኛ ማሽነሪዎችን የማምረት ሂደት በቀጣይ የዕቅዱ ዘመን ውስጥ የሚታሰብ ሆኖ ቀላል የግብርና መሣሪያዎችን ማምረት ለግብርናው ምርታማነት መጨመር አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

40. የኮንስትራክሽን እና ግንባታ ዘርፍ በክልሉ የኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫዎታል። ለዚህም የኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት በክልሉ ይገኛሉ። የአምራች ኢንዱስትሪው ሲሚንቶ፣ መስታዎት፣ ሴራሚክስ፣ የወለል ንጣፍ፣ ለተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ የሚውሉ ቀድመው የተሳነዱ ምርቶች፣ ሸክላ፣ እና ብሎኬት ያመርታል። ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚውሉ የተለያዩ የግንባታ ብረቶች፣ የጣሪያ ቆርቆሮ፣ ምስማር፣ ቡለን፣ ማምረት ይጠበቅበታል። የፍሳሽ እና የባኞ ቤት እቃዎች የኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚፈልጋቸው ሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶች ናቸው። በተመሳሳይ የእንጨት ውጤቶች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ሰፊ የግንባታ ዘርፍ ግብዓቶች ናቸው።

41. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከግብርና ዘርፍ እና ከራሳቸውም ጋር ከፍተኛ ትስስር በመፍጠር መሠረታዊ ፍላጎቶችን የማሟላት ግብን ከማሳካት ባለፈ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ለቀጣይ የኢንዱስትሪ ልማት መነሻ አቅም በመገንባት እና ለኢኮኖሚውም የመጀመሪያ ዙር የዕድገት ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ። ነገር ግን ከዘርፎች ግብርና እና አገልግሎት፣ እንዲሁም ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ጨርቃ ጨርቅ፣ እንጨት፣ የቆዳ ውጤቶች የመሳሰሉት  በአብዛኛው ውስብስብ ቴክኖሎጂ የማይጠይቁ ለሌላው ዘርፍ ከመጨረሻ ፍጆታ በላይ ግብዓት የማይሰጡ በመሆናቸው በተከታታይ ማሳደግ የሚቻለው የካፒታል አቅምን በማስፋፋት ብቻ ነው። ካፒታልን ማስፋፋት ደግሞ ገደብ ያለው ሲሆን የረጅም ጊዜ አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ የሚቻለው በቴክኖሎጂ እድገት ነው።

42. በተከታታይ የቴክኖሎጂ ለውጥ ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚኖራቸው የብረታ ብረት እና የአረብ ብረት (steel)፣ የኤልክትሪክ፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የሚታወቁባቸው ሦስት ለዕድገት ወሳኝ የሆኑ ባህርያት የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በግብዓትነት በስፋት መጠቀማቸው፣ የሚጠቀሟቸው መካከለኛ ግብዓቶች ውስብስብ እና በየጊዜው የሚሻሻሉ ቴክኖሎጂ - ገብ መሆናቸው፣ እና በሁሉም ዘርፎች ተፈላጊ መሆናቸው ነው። ከዚህ አንጻር ከመሠረታዊ የኢንዱስትሪ ምርቶች ውስብስብ ቴክኖሎጂ ወደ የሚጠቀሙ እና ለሌሎች ዘርፎች ምርታማነት መጨመር አስተዋጽዖ ወዳላቸው ዘርፎች ለመሸጋገር ወሳኙ ጉዳይ የዕድገት ምንጭ ገደብ ካለበት ካፒታል ገደብ የለሽ የዕድገት ምንጭ ወደሆነው ቴክኖሎጂ ለመሸጋገር ነው። በዚህ ሁኔታ ከፍተኛ እና ውስብስብ ቴክኖሎጂ ግብዓት የሚጠቀሙ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ ድርሻ ሲጨምር ተወዳዳሪነት በዚያው ልክ ይጨምራል። የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን ያረጋግጣል።

43. የብረታ ብረት እና ስቲል ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማ የማሽን ማምረት እና አጠቃላይ የኢንዳስትሪያላይዜሽን ግብን ማሳካት ነው። ይህ ከ5 እስከ 10 ዓመት ባለው ጊዜ የሚገፋበት እና የቴክኖሎጂ መረጣን የሚያካትት

ነው፡፡ ይህ ደረጃ የብረት ማዕድን፣ ከፍተኛ ኃይል፣ እና የቴክኖሎጂ ዕውቀት አቅም የሚጠይቅ ሲሆን የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት እና ተወዳዳሪነት የሚረጋገጥበት ደረጃ ነው፡፡ ለማሳያ ያህል በዚህ ደረጃ የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች የመኪና ሞተሮችን እና ተያያዥ ክፍሎችን ወደ ማምረት፣ በሂደትም የመኪና አካላትን የሚያመርቱ ማሽኖችን ወደ ማምረት፣ በመጨረሻም በዘርፉ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነትን ወደመፍጠር የሚሸጋገሩበት ነው፡፡

44. ሠንጠረዥ II-9፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች የቴክኖሎጂ አቅም ደረጃ

| **የተራቀቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ** | **በመካከለኛ ደረጃ የተራቀቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ** |
|---|---|
| አውሮፕላን፣ መንኮራኩር<br>የፋርማሲ መዲሃኒቶች<br>ኮምፒውተር፣ የሂሳብ ማሽኖች<br>ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ የመገናኛ መሣሪያዎች<br>የህክምና መሣሪአዎች | የኤሌክትሪክ ማሽኖች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች<br>የሞተር ተሽከርካሪዎች<br>ከፋርማሲ መዲሃኒቶች ውጪ ያሉ ኬሚካሎች<br>የባቡር እና የመጓጓዥያ መሣሪያዎች እና ዕቃዎች<br>ማሽኖች እና የብረታ ብረት ዕቃዎች |
| **መለስተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ** | **ቀላል ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ** |
| የመርከብ እና የጀልባ ሥራ<br>የጎማ እና ፕላስቲክ ውጤቶች<br>ፔትሮሊየም እና ሌሎች የኃይል ምንጮች<br>ብረታ ብረት ያልሆኑ ሌሎች ቁሳቁሶች<br>መሠረታዊ ብረት እና የብረት ውጤቶች | የእንጨት ሥራ<br>ወረቀት፣ የህትመት ሥራዎች<br>ምግብ፣ መጠጥ፣ ትምባሆ<br>ጨርቃጨርቅ፣ አልባሳት<br>የቆዳ ውጥቶች፣ መጫሚያዎች |

45. የኬሚካል ኢንዱስትሪ ሌላው የኢንዳስትሪያላይዜሽን መሠረት ሲሆን በአብዛኛው የአገር ውስጥ ግብዓቶችን የሚጠቀም እንደ ፐልፐ እና ወረቀት፣ ካውስቲክ ሶዳ፣ ሶዳ አሽ፣ ሰልፈሪክ አሲድ፣ ካርበን ባይሰልፌት፣ የፋርማሲ ምርቶች፣ ጠርሙስ፣ ብርጭቆ፣ ሳሙና፣ ክብሪት፣ የቆዳ ፋብሪካ ግብዓቶች፣ ጎማ እና የመሳሰሉትን በበርካታ ዘርፎች ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ማምረት ይጠበቅበታል፡፡

46. የከፍተኛ ቴክኖሎጂ መር የብረታ ብረት እና ኬሚካል ኢንዱስትሪ ልማት ሲታሰብ የአንድ አገር ገበያ ብቻ አዋጭ አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያ ካላት ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የጎረቤት አገር፣ የቀጠናው አገራት፣ እንዲሁም አፍሪካ መነሻ የመወዳደሪያ የገበያ አቅሞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ሲረጋገጥ ዓለም የእነዚህ ምርቶች ገበያ ናት፡፡

47. ከዚህ በመነሳት የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ የረጅም ዓመት ዕቅድ ዋና ዓላማ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ሲሆን በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የመግብ ሸቀጦች፣ ጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ መዲሃኒት፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ እና መሠረታዊ የኤልክትሮኒክስ ዕቃዎችን የመሳሰሉ የመሠረታዊ ኢንዱስትሪ ምርቶችን በአገር ውስጥ ማምረት እና በሂደትም ገቢ ንግድን መተካት ይሆናል፡፡

48. ሠንጠረዥ 11-10፤ የአምራች ኢንዱስትሪ የረጅም ዘመን ግቦች

| | **እስከ 5 ዓመታት** | **ከ5 – 10 ዓመታት** | **ከ10 – 20 ዓመታት** |
|---|---|---|---|
| ዓላማ | የአገራዊ መሠረታዊ የፍጆታ እና የግብዓት ፍላጎት ማሟላት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የዘመናዊ ግብርና ዓላማዎችን መደገፍ | የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ ተወዳዳሪነትን ማጎልበት፣ ለከፍተኛ እና ኬሚካል ኢንዱስትሪ መሠረት መጣል | የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት |
| ስትራቴጂክ ምርቶች | ምግብ፣ ጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ ውጤቶች፣ መዲሃኒት፣ መሠረታዊ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ ቀላል የግብርና መሣሪያዎች<br><br>የብረታ ብረት፣ ማሽኖችን እና ልዕለ ማሽኖች፣ የግብዓት እና ኬሚካል ቴክኖሎጂ መጀመር | አይሲቲ፣ ጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ ውጤቶች፣ መዲሃኒት፣ መሠረታዊ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የግብርና መሣሪያዎች፣ የግብርና ግብዓቶች (ማዳበሪያ)<br><br>የብረታ ብረት፣ ማሽኖች እና ልዕለ ማሽኖች፣ እንዲሁም የኬሚካል ኢንዱስትሪ ማጠናከር | መሠረታዊ የብረታ ብረት ፋብሪካዎች፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች፣ ቴክኖሎጂ |
| ቴክኖሎጂ | በማሽን፣ በአማራጭ ኃይል አቅርቦት፣ በግብዓት እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ወጥ ትስስር ላይ ቴክኖሎጂዎችን ማስገባት/መገልበጥ (copy)፣ በአይቲ ዘርፍ ማሻሻል እና መፍጠር | መማር (learn)፣ ማሻሻል (innovate) | ማሻሻል (innovate)፣ መወዳደር (compete) |
| ገዢ ስትራቴጂ | • ፈጠራን የሚያበረታታ አሳታፊ የፋብሪኬሽን ኢንጂነሪንግ<br>• የከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ሽግግር<br>• ለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ የአይቲ ዝግጁነት | | |
| ሥልቶች | የስትራቴጂክ አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ልየታ፤ ጥብቅ የመዋዕለ ንዋይ ስምሪት፤ የልማት ቀጠና፣ የኢኮኖሚ ዞን፣ የወጪ ንግድ ማሳለጫ ቀጠና የሚለይ ስፓሻል ፕላን፤ የመሠረተ-ልማት እና ሎጂስቲክስ ዝርጋታ፤ የመዋዕለ-ንዋይ ማበረታቻ ሥርዓት፤ ዘርፍ ተኮር የሰው ኃይል ስልጠና | | |

## የረጅም ዘመን የአምራች ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

49. ከ2018 እስከ 2042 ባሉት ሃያ አምሥት ዓመታት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በአማካይ በዓመት በ14.3 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል። የዘርፉ ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻም በ2016 ከነበረበት 9.4 በመቶ በ2042 የምርት ዘመን 25 በመቶ ይደርሳል። ከአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች መካከል በተለይ የከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት በሃያ አምሥት ዓመቱ የዕቅድ ዘመን በዓመት በአማካይ በ16.2 በመቶ ያድጋል። የንዑስ ዘርፉ ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ በ2016 ከነበረበት 4.5 በመቶ በ2042 ወደ 18.2 በመቶ ያድጋል።

50. ሠንጠረዥ 4-11፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች የዕድገት እና መዋቅር ግብ

| | የዕድገት ምጣኔ (በመቶኛ) | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013-16 | 2018-22 | 2023-27 | 2028-32 | 2033-37 | 2038-42 | 2018-42 |
| **ኢንዱስትሪ** | **6.9** | **16.2** | **14.6** | **13.4** | **12.3** | **9.6** | **13.2** |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 16.1 | 17.5 | 15.6 | 14.0 | 13.7 | 11.0 | 14.3 |
| ከፍተኛ እና መ. ኢንዱስትሪ | 18.4 | 21.2 | 17.5 | 15.4 | 14.6 | 12.4 | 16.2 |
| አነስተኛ ኢንዱስትሪ | 16.5 | 14.0 | 13.3 | 12.0 | 12.1 | 7.8 | 11.8 |
| የጎጆ ኢንዱስትሪ | 3.7 | 7.9 | 7.2 | 7.2 | 6.9 | 4.8 | 6.8 |
| | ከክልላዊ ምርት ድርሻ (በመቶኛ) | | | | | | |
| | 2016 | 2022 | 2027 | 2032 | 2037 | 2042 | |
| **ኢንዱስትሪ** | **16.2** | **21.4** | **25.8** | **28.8** | **31.4** | **33.0** | |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 9.4 | 13.3 | 16.7 | 19.2 | 22.2 | 25.0 | |
| ከፍተኛ እና መ. ኢንዱስትሪ | 4.5 | 7.6 | 10.4 | 12.7 | 15.2 | 18.2 | |
| አነስተኛ ኢንዱስትሪ | 4.2 | 5.1 | 5.8 | 6.1 | 6.6 | 6.4 | |
| የጎጆ ኢንዱስትሪ | 0.7 | 0.5 | 0.5 | 0.4 | 0.3 | 0.4 | |

## የረጅም ዘመን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የመዋዕለ ንዋይ አቅጣጫ

51. በተሳካ ኢንዳስትሪያላይዜሽን ሂደት የዜጎች ገቢ ሲጨምር የፍጆታ ወጪ (consumption expenditure) ከገቢ ያለው ድርሻ ይቀንሳል፣ የመዋዕለ ንዋይ ምጣኔ ይረጋጋል፤ የውጭ ንግድ ምጣኔ ይጨምራል፤ በውጭ ንግድ ውስጥ የብረታ ብረት፣ የማሽን እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ድርሻ የተለመዱትን እና እንደ ጨርቃ ጨርቅ እና የቆዳ ውጤቶችን ይተካል። የመዋዕለ-ንዋይ ምጣኔ ከተረጋጋ በኋላ ከመጨመር ይልቅ ስብጥሩ ወደ ስትራቴጂካዊ ዘርፎች ማለትም ብረታ ብረት እና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ይለወጣል።

52. የአምራች ኢንዱስትሪ የመዋዕለ-ንዋይ ፖሊሲ ቁልፍ ጉዳዮች (1) የመዋዕለ -ንዋይ መምረጫ መስፈርት (2) ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎች መረጣ እና ስምሪት (3) ለተመረጡ ፕሮጀክቶች ተጨባጭ የፋይናንስ ምንጭ ማረጋገጥ ናቸው።

53. በተለይም በቀጣዮቹ ሦስት የዕቅዱ የትግበራ ዓመታት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዋና የመዋዕለ-ንዋይ ግብ አሁን ያሉትን ድርጅቶች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ የኃይል ተደራሽነት፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት በማሻሻል ወደ ሙሉ የማምረት አቅም እንዲመጡ በማገዝ ትርፋማ ማድረግ፣ የመሠረታዊ ፍጆታ ሸቀጥ እና እቃዎች ለማምረት የሚያስችሉ ድርጅቶች ማቋቋም ሲሆን በአምሥት ዓመቱ መጨረሻ ጥናታቸው ተጠናቅቆ በሁለተኛው አምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በስፋት ለሚጀመሩት የብረታ ብረት እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ላይ መሥራት ነው። ከዚህም ጎን ለጎን ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማቶች ላይ ርብርብ ማድረግ ነው። የመጀመሪያው እና ሁለተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች ከፍተኛ የካፒታል ግብዓት እና ቴክኖሎጂ የሚጠይቁ በመሆኑ ይህን የገቢ ዕቃዎች የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ከማሟላት ጎን ለጎን ከዘመናዊ ግብርናው እና ከአንዳንድ መሠረታዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች፣ እንዲሁም ማዕድናት ወጪ ንግድን በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ፍላጎትን ለማሟላት ጥረት ይደረጋል። ከዚህም ጎን ለጎን የውጭ ድጋፍን በቁጠባ እና ምርታማነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መጠቀም ተገቢ ይሆናል።

54. በቁልፍ የመዋዕለ-ንዋይ ዘርፎች የሚደረጉ ልማቶችን የፋይናንስ ፍላጎት ለማሟላት የመዋዕለ-ንዋይ ፈንድ ይቋቋማል። ያልተገባ እና የተጋነነ የፍጆታ እና የመንግሥት ወጪን በመቀነስ ቁጠባ ይበረታታል፣ በሂደትም የውጭ ድጋፍን ይተካል። በሁለተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ የኢንዱስትሪዎች ትስስርን ግምት ውስጥ ያስገባ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ይተገበራል፤ በዚህም የኬሚካል እና የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች

የሌሎች ዘርፎችን ፍላጎት በሚያሟሉበት እና ከሌሎች ዘርፎችም የሚፈልጉት ግብዓት በአብዛኛው ከአገር ውስጥ ምንጭ በሚሆንበት አግባብ መተሳሰር ይጀምራሉ።

55. የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ ንዋይ ከውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ጋር እንዲያያዝ፣ ስትራቴጂካዊ በሆኑ ዘርፎች ላይ ከአገር ውስጥ አለሚ እና ከመንግሥት የልማት ተቋማት ጋር ማቀናጀት ያስፈልግል። የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በልዩ ተልዕኮ እና ድጋፍ በቂ የግል ዘርፍ ስምሪት በሌለባቸው ግን ስትራቴጂክ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል።

## 11.2. የአመሥት ዓመት አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች እና ዋና ዋና ግቦች

56. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች
    1. የአገር ውስጥ ግብዓቶችን በተለይም የግብርና ምርቶችን እና በክልሉ የሚገኙ የማዕድን ሀብቶችን የሚጠቀሙ የመካከለኛ እና ከፍተኛ የምግብ ነክ፣ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ እና መዲሃኒት ንዑስ ዘርፎችን በማስፋፋት የገቢ ንግድን የመተካት ግብ ማሳካት፣
    2. ለረጅም ጊዜ የኬሚካል እና ከፍተኛ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት መሠረት ለመጣል በፋብሪኬሽን ኢንጂነሪነግ የሽግግር ዝግጅት ማድረግ፣
    3. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የንዑስ ዘርፎችን ስብጥር ለመዋቅራዊ ሽግግር በተተለመለት ዕቅድ መሠረት እንዲከናወን በጥብቅ የመዋዕለ - ንዋይ ስምሪት መምራት ናቸው።

57. የዘርፉ የአምሥት ዓመት ልማት ዋና ዋና ግቦች
    1. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት በዓመት በአማካይ በ16.1 በመቶ ማሳደግ፣ በተለይም የመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ተጨማሪ እሴትን በ21.2 በመቶ በማሳደግ፣
    2. የአምራች ኢንዱስትሪ መዋዕለ - ንዋይ መጠንን በዕቅድ ዘመኑ 1 ትሪሊየን ብር ማድረስ ነው።

58. በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የታቀደው ፈጣን ዕድገት በሥራ ላይ ያሉ በተለይም የመካካለኛ እና ከፍተኛ የአምራች ዘርፍ ኢንዱስትሪዎችን አቅም አሁን ከአለበት 54.4 በመቶ በ2022 ወደ 85 በመቶ በማሳደግ፣ የቋሚ ግብዓቶችን ምርታማነት በመጨመር እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በማስጀመር ነው። የመካካለኛ እና የከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ ድርጅቶችን የማምረት አቅም በመሻሻል እና ምርታማነትን በማሳደግ የዘርፉን ተጨማሪ እሴት ከ3.5 እስከ 5 በመቶ ዕድገት ምጣኔ ማሳደግ እንደሚቻል ተገምቷል። ነገር ግን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚጠበቀውን የ16.1 በመቶ ዕድገት እና በተለይም የመካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ዘርፎች ተጨማሪ እሴት እንዲያድግበት የታቀደውን የ21.2 በመቶ ምጣኔ ግብ ለማሳካት ጥራቱን የጠበቀ መዋዕለ-ንዋይ በቁልፍ ንዑስ ዘርፎች ማሰማራትን ይጠይቃል።

59. **በአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የ205.3 ቢሊዮን ብር መዋዕለ- ንዋይ እንደሚያስፈልግ ተገምቷል።** ይህ የመዋዕለ-ንዋይ መጠን በአምሥት ዓመቱ የዘርፉ ተጨማሪ እሴት እንዲያድግ የታቀደበትን ዓመታዊ የ16.1 በመቶ ምጣኔ፣ የካፒታል - ምርት ጥምርታ ስሌት እና የሚጠበቀውን የዋጋ ንረት ምጣኔ ታሳቢ በማድረግ የተሰላ ነው።

60. **ከዚህ የ1 ትሪሊየን ብር የዘርፉ መዋዕለ-ንዋይ መጠን ውስጥ 618.6 ቢሊየን ወይም የዘርፉን አጠቃላይ መዋዕለ-ንዋይ 61.8 በመቶ እንደሚሸፍን ታቅዷል።** የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የአምሥት ዓመት ጥቅል የኢንቨስትመንት መጠን ግምት 286 ቢሊየን ብር ወይም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አጠቃላይ መዋዕለ-ንዋይ 28.6 በመቶ ነው። ቀሪው 96 ቢሊየን (ከአምራች ኢንዱስትሪ መዋዕለ-ንዋይ 9.6 በመቶ የሚሆነው) ከጎጀ ኢንዱስትሪዎች እና እደ-ጥበባት የሚጠበቅ ነው። የየዓመቱን የዘርፉን እና የንዑስ ዘርፎችን ተጨማሪ እሴት ግምት ውስጥ በማስገባትም በየዓመቱ ሊኖር የሚገባው የመዋዕለ-ንዋይ መጠን ግምትም ተመላክቷል።

61. የመዋዕለ - ንዋይ ስምሪቱ የሚያተኩርባቸው ዘርፎች በዋናነት የክልሉን የሰብል እና የእንስሳት ሀብት የሚጠቀሙ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች፣ በክልሉ በተመረጡ ቀጠናዎች የሚተገበሩ ሰፋፊ የጨርቃጭርቅ እና አልባሳት ፋብሪካዎች፣ የቆዳ እና መጫሚያ ፋብሪካዎች፣ ብረት ነክ ያልሆኑ

የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የመዲሃኒት ፋብሪካዎች፣ ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ግብዓትነት የሚውሉ የኬሚካል ፋብሪካዎች፣ እና የብረታ ብረት ውጤቶች ይሆናሉ። ከዚህም ጎን ለጎን ለመሠረታዊ ብረታ ብረት እና ማሽነሪ ኢንዱስትሪ መሠረት የሚጥል ሰፊ ጥናት እና ዝግጅት ይደረጋል።

## 11.3. የማስፈጸሚያ ስልቶች

62. የማስፈጸሚያ ስልቶቹ

1. የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎችን፣ ዞኖችን፣ ፓርኮችን መለየት እና ማስፋፋት፣
2. በአልሚ መረጣ፣ በዘርፍ ስብጥር፣ በካፒታል መጠን፣ የሥራ እድል በመፍጠር አቅም፣ እና በኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገለጽ ጥብቅ የመዋዕለ-ንዋይ ስምሪት ማከናወን፣
3. የተቀላጠፈ የአንድ መስኮት የመዋዕለ-ንዋይ አገልግሎት መተግበር፣
4. ከዘርፎች ጋር በግብዓት፣ በመሠረተ-ልማት፣ እና በፍላጎት ትስስር ቅንጂታዊ አሠራር መከተል፣
5. ቀድሞ ችግርን መፍታት ዓላማ ያደረገ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚመራ፣ አኀዛዊ መረጃን ከፊዚካል መረጃ ጋር ያጣጣመ፣ የጊዜ እና የፋይናንስ ብክነትን የማይታገስ ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ማስፈን፣ እና
6. የተቀናጀ እና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት ናቸው።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

# የማዕድን እና ተያያዥ የከርሰ ምድር ሀብቶች ልማት

## 12.1. የትኩረት መነሻ

### የማዕድናት ሚና

1. **የሰው ልጅ የረጅም ዘመን የስልጣኔ ለውጥ እና የቴክኖሎጂ መራቀቅ በማዕድናት እና ተያያዥ የከርሰ ምድር ሀብቶች ልማት (mining) ላይ የተመሠረተ ነው፤ የማሕበረሰብ የዕድገት ልዩነቶችም የማዕድን ሀብቶችን የማነጽ አቅም ልዩነት ነጸብራቆች ናቸው።** ከ3.4 ሚሊዮን ዓመታት በፊት ጀምሮ ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ 550 ድረስ የነበሩ የሰው ልጅ የዕድገት ደረጃዎች የድንጋይ ዘመን (stone age)፣ የመዳብ ወይም የነሃስ ዘመን (copper or bronze age)፣ እንዲሁም የብረት ዘመን (iron age) በሚሉ በማዕድናት ስሞች የተሰየሙ ነበሩ። በድንጋይ ዘመን ሰው የሠራው የመጀመሪያው ማሽን የተጠረበ፣ የሾለ፣ እና የተወቀረ ድንጋይ ሲሆን የተሠራው በቀላሉ ከሚገኝ የባልጩት (obsidian)፣ የጥቁር ድንጋይ (basalt, sandstone)፣ እምቡልጭት (flintz) ከተባሉ ዓለቶች እና ማዕድናት ነው። የመዳብ ወይም የነሃስ ዘመን ሰው ቆርቆሮን (tin) ከቆርቆሮ አዋላጅ ዓለት (cassiterite- $SnO_2$) አጣርቶ ከመዳብ ጋር በመቀላቀል ጎራዴ፣ ጦር፣ ጋሻ፣ መጥረቢያ፣ ቢላ፣ የቤት ቁሳቁስ፣ እና ቅርጻቅርጾች ለመሥራት ማዕድናትን ተጠቅሟል። በብረት ዘመን የሰው ልጅ ከእሳት የሚገኝ የኃይል አጠቃቀም ሲዳብር በተፈጥሮ ከሚገኝ ሜትዮሪክ ብረት (የብረት እና ኒኬል ድብልቅ) ባለፈ ጥሬ ብረትን ከብረት አዋላጅ ማዕድናት (iron ores) ከከሰል የሚገኝን የሙቀት ኃይል (heat energy) ተጠቅሞ በመለየት እና ከካርበን ጋር በመቀላቀል የዐረብ ብረት (steel) ሠርቷል። በዚህም መሣሪያዎችን ለመሥራት ክብደቱ አስቸጋሪ የነበረውን ነሃስ በዐረብ ብረት ተክቷል። እነዚህ የብረታ ብረት መሠረታዊ ዕውቀቶች በአማራ ብሔራዊ ክልል እና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ዛሬም ይገኛሉ።

2. **በዘመናዊ ታሪክ የማዕድን ሀብት ትልቁ ፋይዳ አቶሜሽንን መሠረት ላደረገ ኢንዱስትሪያላዊነት በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በግብዓትነት ማገልገሉ ነው።** የኢንዱስትሪ አብዮት በማሽን እና አቶሜሽን እመርታ በመፍጠር የኢኮኖሚ መመንጠቅ ሲያረጋግጥ በግብዓቶች ላይም በተደረጉ ለውጦች እና መሻሻሎች ላይ ተመሥርቶ ነው። ይህ ለውጥ በዋናነት ከእንስሳት ውጤቶች እና ከአዝርዕት የሚገኙ ግብዓቶችን በማዕድናት እና ሃይድሮ ካርበንን መሠረት ያደረጉ ሰው ሠራሽ ቁሶች ተክቷል። የብረታ ብረት፣ የዐረብ ብረት እና የማሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ የሚጠቀሙት የብረት ማዕድንን ሲሆን በብረት ማጣራት ሂደት በግብዓትነት የሚያገለግሉት የድንጋይ ከሰል (ካርበን ለማግኘት ከሰልን የተካው) እና የኖራ ድንጋይ ራሳቸው ማዕድናት ናቸው። ጥሬ ብረት (pig iron) ወደ መሠረታዊ ብረት (cast iron) ወይም ንጹህ ብረት (wrought iron)፣ ከዚያም ወደ አረብ ብረት (steel) እና የማይዝግ ዐረብ ብረት (stainless steel) ሲቀየር በሂደቶቹ ሌሎች ማዕድናት ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተለይም የዐረብ ብረትን ለማጠንከር፣ ዝገት መቋቋም እንዲችል ለማድረግ፣ እና አንጸባራቂነትን ለመጨመር ከካርበን በተጨማሪ ጥቅም ላይ የሚውሉት ክሮምየም፣ ኒኬል፣ ሞሊብድነም፣ እና ማንጋኒዝ ስማቸው የተለመደ ማዕድናት ናቸው። ቀላል ብረት የሚጠይቁ የበረራ ቴክኖሎጂዎች እና የቤት ማጠናቀቂያ ሥራዎች ሲፈጠሩ የአሉሚኒየም ማዕድን (bauxite ore) ከመሬት ወጥቶ ጥቅም ላይ ውሏል። እንግሊዝ ውስጥ ከፔትሮሊየም ዝቃጭ የተገኘ ሰማያዊ ሰው ሠራሽ ቀለም ወደ ትልቅ የኬሚካል ኢንዱስትሪ አድጎ የተለያዩ ቀለማት፣ የፎቶ ግርፍ ሥራዎች፣ የሰው ሠራሽ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች (ፕላስቲክ)፣ ማዳበሪያ እና የመሳሰሉት አድጓል። ለበርካታ የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓት የሚሆነው ሶዳ አሽ (sodium carbonate – $Na_2CO_3$) በራሱ ማዕድን ሲሆን በሌሎች ማዕድናት ውህደት የሚገኝ ነው፤ ኮስቲክ ሶዳ (sodium hydroxide - NaOH) የሚፈበረኩት ከጨው ማዕድናት ነው። ለግብርና ልማት አብዮት ምንጭ የሆነው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በዋናነት የናይትሮጅን፣ ፎስፈረስ እና ፖታሲየም ንጥረ ነገሮች መገኛ የሆኑ ማዕድናት ውጤት ነው።

3. **የማዕድናት ጥቅም እና ተፈላጊነት የቴክኖሎጂ ለውጥን ይከተላል፤ ቴክኖሎጂ በበለጸጉ ማዕድናት የሚሰርግ ሀሳብ (embodied) ስለሆነ ማዕድናትም በልዩ ባሕርያቶቻቸው የቴክኖሎጂ ዕድገትን ያፋጥናሉ።** የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ አብዮት 'የሲሊከን ዘመን' ተብሎም ይጠራል። ሣይንስ ከሜካኒካል ፊዚክስ ወደ ኤሌክትሮማግኔቲዝም እና ከዚያም ወደ ኳንተም ሜካኒክስ ሲዘልቅ፣ በዚህም ተመሥርቶ ቴክኖሎጂ ወደ ኤሌክትሮኒክስ፣ የዲጂታል አብዮት ዘመን፣ እና ወደ አረንጓዴ የኃይል አማራጭ ሲሸጋገር እንደ ዋዛ ረግጠን ከምናልፈው አሸዋ የሚገኝ ሲሊከንን ጨምሮ እንደ ጀርማኒዬም፣ ጋሊዬም እና አርሴኒክ የመሳሰሉ ከፊል አስተላላፊዎች (semi-conductors) ተፈላጊነታቸው በዚያው መጠን ጨምሯል። የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች፣ የዘመኑ ቴሌቪዥን መቀበያዎች፣ ብልጥ ስልኮች (smart phones)፣ የጭን - ላይ መቀመሪያዎች (laptop computers)፣ እና የፀኃይ ኃይል መቀበያ ቁሶች

(panel cells) እና የሚጠቀሟቸው ባትሪዎች ከጋሊዬም እና ጀርመንዬም በተጨማሪ እንደ ኢንድዬም፣ ሰለኒዬም፣ እና ሊቲዬም የመሳሰሉ ማዕድናትን ፍላጎት ጨምሮታል።

4. **የሕንጻ ግንባታ፣ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ እና የኢንዱስትሪ ግንባታ የሚያከናውነው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ከአሸዋ እና ጠጠር እስከ ሲሚንቶ፣ ከኮረት እስከ ድንጋይ፣ ከማዕዘን ድንጋዮች እስከ እምነ በረድ እና ግራናይት የሚደርሱ ዓለቶችን ይጠቀማል።** የየከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናት ለዘመናት ተፈላጊ በመሆናቸው ለአምራች አገራት የውጭ ምንዛሪ ምንጭ፣ ለአልሚ አገራት ደግሞ ከፍተኛ የማዕድን ኢንዱስትሪ ምንጭ ሆነዋል። አገራት እንደ እድል የሚቆጥሩት የነዳጅ ማዕድን ለበርካታ አገራት የገቢ ምንጭ፣ በዓለም ደረጃ ላሉ ሁሉም አገራት፣ የኃይል ምንጭ፣ አላቂ መሆኑን ለተገነዘቡ ጥቂት የነዳጅ ሀብታም አገራት ደግሞ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት አስችሏል። ከሁሉም በላይ የፔትሪሊዬም እና ጋዝ መገኘት ለፔትሮኬሚካል ኢንዱስትሪ ግንባታ ትልቅ መሠረት ጥሏል።

5. **ማዕድናት ተሸጠው የማሕበረሰብ እና የአገራት የገቢ፣ ከፍ ሲልም የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ምንጭ ይሆናሉ፤ ነገር ግን ማዕድናትን ሸጠው ኪራይ ከሚሰበስቡ አገራት ይልቅ እነዚህን ሀብቶች አንጸው ዘመናዊ ኢንዱስትሪ የገነቡ አገራት የተሻለ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ አቅም ፈጥረዋል።** ማዕድናትን ለኢንዱስትሪያላዊነት የተጠቀሙበት ያሉ አገራት የመኖራቸውን ያህል ማዕድናትን እና ነዳጅ ሸጠው በሚያገኙት ገቢ የሚተዳደሩ እና የመንግሥት ወጪን የሚሸፍኑ አገራት በርካታ ናቸው። በዓለም ባንክ የ2013 መረጃ መሠረት ከአገራዊ ምርታቸው ከ20 በመቶ በላይ ከተፈጥሮ ሀብት የኪራይ ገቢ ከሚያገኙ 23 አገራት አሥሩ፣ ከ10 በመቶ በላይ ከሚሰበስቡ 43 አገራት ሃያዎቹ የአፍሪካ አገራት ሲሆኑ ሊቢያ በ61 በመቶ ከዓለም አንደኛ፣ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ በ39 በመቶ፣ ኮንጎ ሪፐብሊክ በ38 በመቶ፣ እና ዛምቢያ በ35 በመቶ ከዓለም ከ3ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ ያለውን የከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ምጣኔ ተጠቃሚ አገራት ናቸው። የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ ምጣኔ የዐረቡ ዓለም አማካይ 20 በመቶ፣ የዝቅተኛ ገቢ አገራት አማካይ 13 በመቶ፣ ከሰሃራ በታች ያሉ አገራት አማካይ 10 በመቶ፣ ሲሆን የዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ አገራት አማካይ 4 በመቶ፣ የከፍተኛ መካከለኛ ገቢ አማካይ 3.9 በመቶ፣ የከፍተኛ ገቢ አገራት አማካይ 2.5 በመቶ፣ የአውሮፓ ሕብረት አገራት 0.2 በመቶ ነው። በአገራት ደረጃ የቻይና፣የዩናይትድ ስቴትስ፣ የደቡብ ኮሪያ፣ የጃፓን የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ እንደቅድም ተከተላቸው 1.7 በመቶ፣ 1.3 በመቶ፣ 0.05 በመቶ እና 0.04 በመቶ ነው። በአንጻሩ እነዚህ አገራት ከፍተኛ የማዕድን ግብዓት ተጠቃሚ አገራት ናቸው። በተመሳሳይ ወቅት የኢትዮጵያ የማዕድና ኪራይ ገቢ ከአገር ውስጥ ምርት 5.9 በመቶ ነበር።

6. **ሠንጠረዥ 12-1፤** የአገራት የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ ምጣኔ እና የነፍስ ወከፍ ገቢ ንጽጽር፤ 2013 (2021)

| | የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ ከአገራዊ ምርት በመቶኛ | የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2009 የዶላር መግዛት አቅም (በዩ.ኤስ. ዶላር) |
|---|---|---|
| የአረብ አገራት | 20.2 | 13,470 |
| ዝቅተኛ ገቢ አገራት | 13.2 | 1,964 |
| ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራት | 10.0 | 3,717 |
| የታችኛው መካከለኛ ገቢ አገራት | 4.1 | 7,242 |
| የላይኛው መካከለኛ ገቢ አገራት | 3.9 | 18,193 |
| ዓለም | 3.0 | 16,997 |
| ከፍተኛ ገቢ አገራት | 2.5 | 50,122 |
| የአውሮፓ ሕብረት | 0.2 | 44,138 |
| ሊቢያ | 61.0 | 21,965 |
| ኢራቅ | 43.4 | 8,962 |
| ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ | 38.8 | 1,074 |
| ኮንጎ ሪፐብሊክ | 37.7 | 3,234 |
| ዛምቢያ | 35.3 | 3,237 |
| ኖርዌ | 10.1 | 65,662 |
| ኢትዮጵያ | 5.9 | 2,319 |
| ካናዳ | 4.9 | 47,893 |
| ቻይና | 1.7 | 17,603 |
| አሜሪካ | 1.3 | 63,670 |
| ደቡብ ኮሪያ | 0.05 | 44,232 |
| ጃፓን | 0.04 | 40,784 |
| ሲንጋፖር | 0.00 | 106,032 |

ምንጭ፤ World Mining Data 2024: Iron and Ferro-Alloy Metals, Non-Ferrous Metals, Precious Metals, Industrial Minerals, Mineral Fuels; International Organizing Committee for the World Mining Congresses.

7. **ከተፈጥሮ ሀብት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ከአገራት የነፍስ ወከፍ ገቢ ጋር ያለው ግንኙነት በአማካይ አሉታዊ ሲሆን፣ በዝርዝር ሲታይ በሁሉም አገራት ወጥ እና ተመሳሳይ አይደለም፤**

(1) እንደ ላክሰምበርግ፣ ሲንጋፖር፣ አየርላንድ፣ ጃፓን እና ደቡብ ኮሪያን የመሳሰሉ አገራት ብዙም የተፈጥሮ ሀብት ሳይኖራቸው እና ከዚህም የተነሳ የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ ሳይሰበስቡ ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማረጋገጥ የቻሉ አገራት ናቸው።

(2) እንደ ኖርዌ፣ ካናዳ፣ አሜሪካ ያሉ አገራት ሀብታቸውን በመጠቀም ወይም ከሀብታቸው የሚገኘውን ኪራይ በመጠቀም ከኪራዩ የሚልቅ ኢኮኖሚ የሚያመነጭ የኢንዱስትሪ አቅም ገንብተዋል።

(3) አውስትራሊያ፣ የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች (ዩኤኢ)፣ እና ኳታር የመሳሰሉ አገራት የተፈጥሮ ሀብትን በተለይም የነዳጅ ማዕድናትን ለዘመናዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ተጠቅመው ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማረጋገጥ ችለዋል።

(4) እንደ ብሩነይ እና ሳኡዲ አረቢያ ያሉ አገራት ከከፍተኛ ማዕድን በተለይም የነዳጅ ማዕድን ኪራይ ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያገኛሉ። [የኢኮኖሚ መዋቅራቸውን ማየት]

(5) ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራት የማዕድን ሀብት ልማታቸው አሻጋሪ ባለመሆኑ የከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ጥገኝነት ከድህነት እና/ወይም ከግጭት አዙሪት ሊያወጣቸው አልቻለም።

(6) በመጨረሻ አብዛኛዎቹ ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገራት የተፈጥሮ ሀብታቸውን በዋናነትም ማዕድናትን በቅጡ አልምተው ለአሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ባለማዋላቸው ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ላይ ይገኛሉ።

8. ስዕል 12-1፤ የዓለም አገራት የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ እና የነፍስ ወከፍ ገቢ ንጽጽር




*ምንጭ፤ የዓለም ባንክ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰናዳ።*

9. የተፈጥሮ ሀብት በተለይም የማዕድናት ኪራይ ገቢን እና የነፍስ ወከፍ ገቢ ንጽጽር በአፍሪካ ደረጃ ሲታይ

(1) ሲሺዬልስ እና ሞሪሸየስ ያለ ማዕድን ሀብት ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማረጋገጥ የቻሉ ደሴቶች ናቸው።

(2) ቦትስዋና፣ ናሚቢያ እና ደቡብ አፍሪካ በአንጻራዊነት ማዕድንን ለልማት ማነጽ የቻሉ የአፍሪካ አገራት ናቸው።

(3) ጋቦን እና ኢኳቶሪያል ጊኒ በማዕድን ሀብት ኪራይ ላይ የተመሠረቱ ነገር ግን የተሻለ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማረጋገጥ የቻሉ አገራት ናቸው።

(4) ዛምቢያ፣ ኮንጎ ደሞክራቲክ ሪፐብሊክ (ኪኒሻሳ) እና ኮንጎ ሪፐብሊክ (ብራዛቪል) ኢኮኖሚያቸው በከፍተኛ የማዕድን ሀበት ኪራይ ገቢ ላይ የተመሠረተ ነገር ግን በዝቅተኛ ገቢ ደረጃ የሚገኙ አገራት ናቸው።

(5) ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋ በማዕድን ሀብት ኪራይ ላይ ያልተመሠረተ ነገር ግን በአሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት የኢኮኖሚ ተስተካካይነት ለማረጋገጥ የማዕድን ሀብቷን በቅጡ አጥንታ ማነጽ የሚጠበቅባት አገር ናት።

10. ስዕል 12-2፤ ከሳሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራት የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ ገቢ እና የነፍስ ወከፍ ገቢ ንጽጽር




ምንጭ፤ የዓለም ባንክ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰናዳ።

11. ኢኮኖሚያቸው በማዕድን እና ነዳጅ ኪራይ ገቢ ላይ የተመሠረተ አገራት ትልቁ ስጋት እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች አላቂ እና የማይተኩ መሆናቸው ነው። አብዛኛው ማሕበረሰብ በባህላዊ መንገድ ማዕድናትን በማውጣት የዕለት ገቢውን በሚያገኝባቸው አገራት ግጭቶች ይስተዋላሉ። የግጭት አዙሪት የገቡ አገራትም ለልማት ፋታ አግኝተው ከድህነት መላቀቅ ያቅታቸዋል። በዚህም ምክንያት እንደ አፍሪካ ባሉ አገራት ማዕድን እና ነዳጅን የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሀብቶች እንደ ርግማን (resource curse) እስከመቆጠር ደርሰዋል። ዋናው ማጠንጠኛ የማዕድን ሀብት አላቂ በመሆኑ ልማትን ሳያረጋግጡ ለኢንዱስትሪያላዊነት የሚያገለግሉ ማዕድናትን እና ተዛማጅ ሀበቶችን ለውጭ ገበያ መሸጥ የኢኮኖሚ ዕድገት እና የልማት ዕድልን እንደመሸጥ ሊቆጠር ይችላል።

12. የማዕድን ኢንዱስትሪ አቅም የግድ የማዕድን ሀብት በአገር ውስጥ መገኘትን አይጠይቅም። ጠቃሚ ማዕድናት በሁሉም አገራት ተሟልተው አይገኙም። ነገር ግን አገራት ማዕድናትን በማውጣት የተሻለ የቴክኖሎጂ አቅም በመገንባት በሌሎች አገሮች በማዕድን ማውጣት ሥራ ይሠማራሉ፤ በዚህም ተወዳዳሪ የማዕድን ኢንዱስትሪ ይገነባሉ።

13. የማዕድን እና ተያያዥ የከርሰ ምድር ሀብቶች ልማት (mining) በዘርፉ ሣይንስ ማዕድን (minerals) ብለው ከተለዩት የብረት እና ፌሮ ብረታ ብረቶች (iron and ferro – alloy matals)፣ ፌሮ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች (nonferrous metals)፣ የከበሩ ብረታ ብረት (precious metals)፣ እና የኢንዱስትሪ ማዕድናት (industrial minerals) በተጨማሪ የነዳጅ ማዕድናትን (mineral fuels)፣ የተፈጥሮ ወይም የማስጌጫ ድንጋይን (natural or ornamental or dimension stones)፣ እና የጌጣጌጥ ማዕድናትን (gemstones) ያጠቃልላል። በዚህ የዕቅድ ሰነድ ውስጥ ማዕድናት የሚለው ቃልም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እና በሥራቸው ከአሸዋ እና ጠጠር እስከ የብረት ማዕድን የሚካተቱባቸውን ሰባት ክፍሎች ያጠቃልላል።

14. ኢትዮጵያ ካላት የሥነ ምድር አወቃቀር (geological formation) ለሁሉም ዋና ዋና ማዕድናት መገኛ ልትሆን እንደምትችል ጥናቶች ቢያመላክቱም እስከ አሁን የተለየው የማዕድን ሀብት አቅምም ሆነ ከዘርፉ የሚገኘው ውጤት ከዓለም አቀፍ ተሞክሮ አንጻር ውስን ነው። በ2014 ወይም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2022 በዓለም ላይ የከበሩ ድንጋዮችን (gemstones) እና የማጋጌጫ ወይም የተፈጥሮ ድንጋዮችን (natural or dimension stones) ሳይጨምር የ62 ማዕድናት የምርት መጠን ሪፖርት ተደርጓል። የማዕድን ምርት ሪፖርት ካጠቃለላቸው 194 አገራት መካከል አንዷ የሆነቸው ኢትዮጵያ በ10 የማዕድን ዓይነቶች ተጠቃሽ ናት። በዓመቱ የእነዚህ ማዕድናት ጠቅላላ ምርት በዋጋ ሲተመን 7.5 ትሪሊየን ዶላር የነበረ ሲሆን የኢትዮጵያ ማዕድናት ጠቅላላ ዋጋ 384 ሚሊዮን ዶላር ወይም ከዓለም 0.005 በመቶ ያህል ብቻ ነበር። ከዚህ ገቢ ውስጥ ቻይና 19.1 በመቶ፣ ዩናይትድ ስቴትስ 13.5 በመቶ፣ እና ሩሲያ 9.6 በመቶ በመሸፈን ከፍተኛውን ድርሻ ወስደዋል። ደቡብ አፍሪካ 2.6 በመቶ፣ አልጄሪያ 0.9 በመቶ፣ እና ናይጄሪያ 0.8 በመቶ የዓለም የማዕድን ገቢን በመሸፈን ከአፍሪካ ከፍተኛ ደረጃን ይዘዋል።

15. የኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍ ገቢ ከማስገኘትም ሆነ በግብዓትነት ለአምራች ዘርፎች የሚያደርገው ውስን የመሆኑን ያህል የአማራ ብሔራዊ ክልል የዘርፉ አቅም ከአገር አቀፉ አቅም በጣም ያነሰ እና በአብዛኛው የግንባታ ማዕድናት እና ኦፓልን የመሳሰሉ ውስን የጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ የተመሠረተ ነው። ለማሳያም ከ2013 እስከ 2016 በነበሩት ዓመታት ከክልሉ የማዕድን ዘርፍ የወጪ ንግድ የተገኘ የውጭ ምንዛሪ በአማካይ በዓመት 5.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የነበረ ሲሆን ይህም የአገር አቀፉን የዘርፉን የውጭ ምንዛሪ ግኝት 1.9 በመቶ ያህል ነው።

16. **ሠንጠረዥ 12-2፤** በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ ከማዕድን ወጪ ንግድ የተገኘ የውጭ ምንዛሬ መጠን በአሜሪካ ዶላር

| | ኢትዮጵያ | የአማራ ብሔራዊ ክልል | የክልሉ ድርሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2013 | 682,712,000 | 3,608,600 | 0.53 |
| 2014 | 543,113,000 | 5,603,700 | 1.03 |
| 2015 | 226,850,000 | 10,721,931 | 4.73 |
| 2016 | 221,973,000 | 3,242,778 | 1.46 |
| **አማካይ** | **418,662,000** | **5,794,252** | **1.94** |

ምንጭ፤ የአብክመ የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ

17. ስብጥርን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከነዳጅ፣ የግንባታ፣ እና የጌጣጌጥ ማዕድናት ውጪ ያሉ ማዕድናት አጠቃላይ ምርት በዋጋ ሲተመን የ2014 ምርት ዓመት 1.5 ትሪሊየን ዶላር ነበር። ከዚህ ውስጥ የብረት እና ተያያዥ ብረቶች ድርሻ 37 በመቶ የነበረ ሲሆን ደቡብ አፍሪካ በ21.3 በመቶ፣ አውስትራሊያ በ15.8 በመቶ፣ እና ቻይና በ7.9 በመቶ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል። በዚህ ምድብ ኢትዮጵያ ከክሮምዬም፣ ከኑብዩም፣ እና ታንታለም 23 ሚሊዮን ዶላር ወይም የምድቡን 0.004 በመቶ ዋጋ ያለው ማዕድን አምርታለች። ኢትዮጵያ በምርት መጠን ደረጃ በተለይም በታምታለም ማዕድን 90 ሜትሪክ ቶን ወይም የዓለምን 5.2 በመቶ ማምረት ችላለች። በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚታወቅ የብረት እና ፌሮ ብረታ ብረቶች ምርት አልተመዘገበም።

### ሀ. ብረት እና ፌሮ ብረታ ብረቶች (Iron and ferro-alloy metals)

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብረት (Fe) | **ክሮሚየም (Cr)** 400 ሜ. ቶን (0.000%) | ኮባልት (Co) | ማንጋኒዝ (Mn) |
| ሞሊብደነም (Mo) | ኒኬል (Ni) | **ኒዮቢዩም (Nb)** 17 ሜ.ቶን (0.2%) | **ታንታለም (Ta)** 90 ሜ.ቶን (5.21%) |
| ቲታኒዬም (Ti) | ተንግስተን (W) | ቫናዲየም (V) | |

18. ፌሮ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ከ1.5 ትሪሊዮን ዋጋ ያላቸው ማዕድናት ምርት ውስጥ 33 በመቶ ይሸፍናሉ። እነዚህ ማዕድናት የዲጂታል ቴክኖሎጂ እና የአረንጓዴ ኃይል አማራጭ በመስፋፋቱ ምክንያት ፍላጎታቸው እየጨመረ የመጣ ሲሆን ቻይና በ32.2 በመቶ፣ ቺሌ በ11.4 በመቶ፣ እንዲሁም ፔሩ በ5.9 በመቶ የከፍተኛ አምራችነት ደረጃን ይዘዋል። ቻይና የእነዚህ ማዕድናት ከፍተኛ አምራች ብቻ ሳትሆን ከፍተኛ ተጠቃሚም ናት። ከእነዚህ ማዕድናት መደብ አማራ ብሔራዊ ክልልም ሆነ ኢትዮጵያ በአጠቃላይ ትርጉም ያለው ምርት አያመርቱም።

### ለ. ፌሮዎስ ያልሆኑ ብራታ ብሮቶች (Nonferrous metals)

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አሉምንዩም (Al) | ጀርመኒዩም (Ge) | አርሴኒክ (As) | ዚንክ (Zn) | ሰለንዬም ((Se) |
| ጋሊዩም (Ga) | ቆርቆሮ (ቲን) (Sn) | አንቲሞኒ (Sb) | ካድሚዩም (Cd) | ቴሉሪዬም (Te) |
| ኢንዲዩም (In) | እርሳስ (ሊድ) (Pb) | ቢስሙዝ (Bi) | ሜርኩሪ (Hg) | ብርቅዬ ማዕድናት |
| ሊትዩም (Li) | በሪሊዩም (Be) | ርሄንዩም (Re) | መዳብ (Cu) | |

19. የከበሩ የብረት ማዕድናት ወርቅ፣ ፓላዲዩም፣ ፕላቲኒዩም፣ ሮዲዩም፣ እና ብርን የሚጠቃልል ሲሆን በ2014 የምርት ዘመን ከአጠቃላይ የብረት ነክ እና የኢንዱስትሪ ማዕድናት ውስጥ የ17 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ኢትዮጵያ በዚህ ምድብ 5900 ኪሎ ግራም ወርቅ ወይም የዓለም አቅርቦትን 0.18 በመቶ እና 800 ኪሎ ግራም የብር ማዕድን አምርታለች። በአማራ ብሔራዊ ክልል በባሕላዊ መንገድ ወርቅ ከሚያወጡ አነስተኛ ግለሰቦች ውጪ በዘመናዊ መንገድ ወርቅም ሆነ የብር ማዕድን የሚያወጣ ኩባንያ የለም።

### ሐ. የከበሩ ብረት ነክ ማዕድናት (Precious metals)

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ወርቅ (Au)** 5900 ኪ.ግ. (0.18%) | ፓላዲዩም (Pd) | ፕላቲንዬም (Pt) | ርሆዲዩም (Rh) | ብር (Ag) 800 ኪ.ግ. (0.000 %) |

20. በአብዛኛው በግብዓትነት የሚያገለግሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ከ2014 ዓለም አቀፍ የብረታ ብረት እና ኢንዱስትሪ ማዕድናት የምርት ዋጋ ውስጥ 13 በመቶ ይሸፍናሉ። እንደ ግራፋይት፣ ፐራይት፣ ፍሎሮስፓር፣ እና ቦሮን የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ተፈላጊነታቸው እየጨመረ ያሉ ማዕድናት ናቸው። ከእነዚህ ሃያ የሚደርሱ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ውስጥ ኢትዮጵያ ዲያቶማይት፣ ጂፕሰም፣ ካኦሊን እና ጨው በዋናነት አምርታለች። በ2016 የምርት ዘመን በአማራ ብሔራዊ ክልል 251,583 ጂፕሰም፣ 3,110 ቶን ቤንቶናይት፣ 2,750 ቶን ፌልድስፓር፣ እና 2,420 ቶን ካኦሊን ተመርቷል።

### መ. የኢንዱስትሪ ማዕድናት (Industrial minerals)

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አስቤስቶስ | ባራይት | ቤንቶናይት | ቦሮን | አልማዝ |
| ዲያቶማይት 5000 ቶን (0.2%) | ፌልድስፓር | ፍሉርስፓር | ግራፋይት | ጂፕሰም 110000 ቶን (0.06%) |
| ካኦሊን 1000 ቶን (0.000%) | ማግኔዛይት | ፐርላይት | ፎስፌት | ፖታሽ |
| ጨው 100000 ቶን (0.04%) | ዲኝ | ታልክ | ቨርሚኩላይት | ዚርኮን |

21. የዓለም አቀፍ የኃይል አማራጭ ከሃይድሮ ካርበን ውጤቶች ወይም የሕያው ቅሪት (ፎሲል) ማዕድናት ወደ አረንጓዴ የኃይል አማራጭ እየተሸጋገረ ቢሆንም የነዳጅ ማዕድናት በዓለም የማዕድናት ገበያ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በ2014 ከተመረተው 7.5 ትሪሊየን ዶላር ዋጋ ያለው የማዕድን ምርት ውስጥ 6 ትሪሊየን ዶላር ወይም የብረታ ብረት፣ የኢንዱስትሪ፣ እና የነዳጅ ማዕድናት ዋጋን 81 በመቶ የሚሆነው የነዳጅ ማዕድናት

ድርሻ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ የሚጠቀስ የምርት ተሳትፎ የሌላት ሲሆን በተመሳሳይ ዓመት 2700 ሜትሪክ ቶን የድንጋይ ከሰል አምርታለች። አገሪቷ ቀላል የማይባል የድንጋይ ከሰል ክምችት እንዳላት የሚታወቅ ቢሆንም እየተመረተ ያለው መጠን ከዓለም አቀፍ የማዕድኑ ምርት አንጻር ትርጉም ያለው አይደለም።

### ሠ. የነዳጅ ማዕድናት (Mineral fuels)

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የድንጋይ ከሰል 2700 ቶን (0.000%) | የተፈጥሮ ጋዝ | ፔትሮሊዬም | አይል ሳንድስ | አይል ሼልስ |
| ዩራኒዬም | | | | |

22. በአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በአገር አቀፍ ደረጃ ለተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገ ሲሆን ጥቅል የግንባታ ግብአቶች (አሸዋ፣ ጠጠር፣ እና የተፈጨ ድንጋይ)፣ የሲሚንቶ ማምረቻ ግብዓቶች፣ እና የጌጥ ድንጋዮች ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ነገር ግን የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከውጭ በሚገቡ የማጠናቀቂያ ዕቃዎች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ ነበር። በተመሳሳይ ወቅት በአማራ ብሔራዊ ክልል የኖራ ድንጋይ፣ እምነ በረድ፣ እና ግራናይትን የመሳሰሉ የማጋጌጫ ድንጋዮች ተመርተዋል። አሸዋ፣ ጠጠር፣ እና የተፈጨ ድንጋይ በክልሉ በስፋት የሚገኙ እና ትርጉም ባለው መጠን ጥቅም ላይ የሚውሉ ቢሆንም እነዚህን ግብዓቶች የሚጠቀመው የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዝቅተኛ አፈጻጸም የግንባታ ማዕድናት በተገቢው መጠን ጥቅም ላይ አለማዋለቸውን ማሳያ ነው።

### ረ. የኮንስትራክሽን ማዕድናት (Construction Minerals)

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ጥቅል የኮንስትራክሽን ግብዓቶች (Aggregates)** | | | |
| አሸዋ | ጠጠር | የተፈጨ ድንጋይ | |
| **ሸክላ (Clay)** | | | |
| የግንባታ ሸክላ (Bricks clay) | | | |
| **የተፈጥሮ ወይም የጌጥ ወይም የማዕዘን ድንጋይ (Natural or ornamental or dimension stones)** | | | |
| ግራናይት | እምነበረድ | ስሌት | ኦኒክስ |
| ሰርፐንታይን | ኳርትዛይት | ሶፕስቶን | ትራቨርታይን |
| የኖራ ድንጋይ | ዶሎማይት የኖራ ድንጋይ | | |

23. በዓለም ላይ አልማዝን ጨምሮ ከ350 በላይ የሚደርሱ የጌጣጌጥ ማዕድናት (gemstones) የሚመረቱ ሲሆን የ2015 የኢንዱስትሪው ገበያ 58.3 ቢሊዮን ዶላር ነበር። ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የቅንጦት የጌጣጌጥ ማዕድናት አልማዝ (diamond)፣ ሳፋይር (sapphire)፣ ሩቢ (ruby)፣ ኤመራልድ (emerald)፣ ኦፓል (opal)፣ ፐርል (pearl)፣ አምበር (amber)፣ አኳማሪን (aquamarine)፣ ቶፓዝ (topaz)፣ ጋርኔት (garnet)፣ ታንዛናይት (tanzanite)፣ ቱርማላይን (tourmaline)፣ ፓይናይት (painite)፣ ጃዳይት (Jadeite)፣ ግራንዲደራይት (grandidierite)፣ ታአፋይት (taaffeite)፣ አሌክሳንደራይት (alexandrite)፣ ሙስግራቫይት (musgravite) እና ቤኒቶይት (benitoite) በከፍተኛ ዋጋ ከሚሸጡ የቅንጦት ማዕድናት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከእነዚህ ማዕድናት መካካል በአማራ ብሔራዊ ክልል እስከ 2016 ድረስ 90.1 ሺህ ኪሎ ግራም ጥሬ ኦፓል ተመርቷል። በተመሳሳይ ዓመት እሴት የተጨመረበት በክልሉ የተመረተ ኦፓል 2 ሺህ ኪሎ ግራም ነው። በአጠቃላይ በ2016 የምርት ዘመን 3.2 ሚሊዮን ዶላር ከንዑስ ዘርፉ የተገኘ ሲሆን ይህ መጠን የክልሉን የጌጣጌጥ ማዕድናት አቅም በተገቢው መጠን እና በቅጡ ማልማት እንዳልተቻለ አመላካች ነው።

### ሰ. የጌጣጌጥ ማዕድናት (Gemstone)


ሰማያዊ አልማዝ
(Blue diamond)


ሐምራዊ አልማዝ
(Pink diamond)


ቀይ አልማዝ
(Red diamond)


ፓይናይት
(Painite)


ጃዴይት
(Jadeite)


ግራንድደራይት
(Grandidierite)


ኤመራልድ
(Emerald)


ግልጽ አልማዝ
(Clear diamond)


ታአፋይት
(Taaffeite)


አሌክሳንደራይት
(Alexandrite)


ሙስግራቫይት
(musgravite)


ሩቢ
(Ruby)


ቤኒቶይት
(Benitoite)


ጥቁር ኦፓል
(Balack opal)


ደማንቶይድ ጋርኔት
(Demantoid Garnet)

## 12.2. ዓለም አቀፍ የማዕድናት ፍላጎት አቅጣጫ እና የአማራ ብሔራዊ ክልል የማዕድን አለኝታ

24. በሲሊከን ዘመን በዓለም ላይ ሁለት ክስተቶች የማዕድናትን የፍላጎት አቅጣጫ እየቀየሩት ይገኛሉ፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂ እና አረንጓዴ የኃይል አማራጭ ቴክኖሎጂዎች። በዚህም መሠረት ከፌሮ ብረታ ብረቶች ማዕድናት፣ ፌሮ ካልሆኑ ብረታ ብረቶች ማዕድናት፣ እና ከኢንዱስትሪ ማዕድናት መካከል በአብዛኛው ለዝርግ የቴሌቪዥን መቀበያ መስኮቶች (flat screen TV)፣ ለብርሃን ፈንጣቂ ቁሶች (Light Emiting Diode - LED)፣ በጣት የሚዳሰሱ መስኮቶች ያሏቸው የጭን ላይ መቀመሪያዎች (touch screen laptop) እና የተንቀሳቃሽ ስልኮች (smart phones)፣ የኤልክትሪክ ተሽከርካሪዎች፣ የፀኃይ ኃይል መቀበያ ሕዋሶች (solar cells) ወይም ፓኔሎች (solar panels)፣ እንዲሁም ለእነዚህ ሁሉ የኃይል ምንጭ የሆኑ ባትሪዎች መፈብረኪያ የሚውሉ ማዕድናት ፍላጎት ጨምሯል። ሲሊከን በዘመነ ዲጂታላይዜሽን ተፈላጊ የመሆኑን ያክል በአቅርቦት ደረጃ የትኩረት ማዕድን (critical mineral) አይደለም። ለዚህ ምክንያቱ ሲሊከንን ለማምረት ሲሊከን አዘል ቁሶች ማለትም ኳርትዝ እና አሸዋ (SiO2) በስፋት የሚገኙ በመሆናቸው ነው፤ ሲሊከን ከኦክስጅን ቀጥሎ በመሬት ላይ በከፍተኛ መጠን የሚገኝ ንጥረ ነገር ነው።

25. ከ2010 እስከ 2014 በነበሩት አምሥት ዓመታት ከፌሮ ብረታ ብረት ማዕድናት መካከል የኒኬል፣ ቫናዲዩም፣ ቲታኒዩም፣ እና ኒዮብዩም ምርት እንደ ቅድም ተከተላቸው በ36.6 በመቶ፣ በ35.7 በመቶ፣ በ19.9 በመቶ፣ እና በ8.4 በመቶ ጨምሯል። ኒኬል ለመኪና ባትሪ፣ ቋሚ ማግኔጢስ መሥሪያ እና ለኤሌክትሮኒክስ ሥራ አገልግሎት ላይ ይውላል። ቫናዲዩም ለባትሪ መስሪያ፣ ለብረታ ብረት ማጠንከሪያ እና ለሕክምና አገልግሎት ተግባራት አገልግሎት ይሰጣል። ቲታንዩም ለኤሮስፔስ (አውሮፕላን እና መንኮራኩር) ሥራዎች፣ ለወታደራዊ መርከቦች፣ በከላዲንግ ለሚሠሩ የሕንጻ ግንባታዎች፣ እና ለሕክምና አገልግሎት ይውላል። ኒዮቢዩም ልዕለ - ኤሌክትሪክ አስተላላፊ (super conductor) በመሆኑ ለማግኔጢሳዊ ምስለ አካል መሣሪያ (Magnetic Resonance Imaging - MRI)፣ ለዲጂታል ትዕይንት ምስል (Liquid Crystal Display - LED)፣ ኳንተም መቀመሪያዎች (quantum computers)፣ ለኒኩሊየር ጥናት፣ እና ሕክምና ጥቅም ላይ ይውላል። ከእነዚህ ማዕድናት ውስጥ ኒዮቢዩም በኢትዮጵያ የሚመረት ሲሆን በ2010 እና 2014 መካከል ምርቱ በ10.7 በመቶ

ቀንሷል። በተመሳሳይ ከዚህ የማዕድናት ምድብ ውስጥ ኢትዮጵያ የምታመርታቸው ክሮምየም እና ታንታለም ምርቶች በ95 በመቶ እና በ13.5 በመቶ፣ እንደ ቅድም ተከተላቸው ቀንሷል።

26. ስዕል 12 - 3፤ የብረት እና ፌሮ ብረታ ብረቶች ዓለም አቀፍ የምርት ለውጥ (በ2010 እና 2014 መካከል)




ምንጭ፤ World Mining Data 2024: Iron and Ferro-Alloy Metals, Non-Ferrous Metals, Precious Metals, Industrial Minerals, Mineral Fuels; International Organizing Committee for the World Mining Congresses.

27. **የአማራ ብሔራዊ ክልል የማዕድን አለኝታ** የእስካሁን ጥናት እንደሚያሳየው በእነዚህ ማዕድናት ምድብ የብረት አዘል ማዕድን (hematite – $Fe_2O_3$) በአራት ዞኖች በተገኙ ምልክቶች የአሰሳ ጥናት እየተካሄደ ነው። በተጨማሪ መጠኑ ያልተረጋገጠ የማንጋኒዝ፣ እና የኒኬል ክምችት እዳለ ጥናቶች አመላክተዋል።

28. በተመሳሳይ ወቅት በዓለም ላይ ፌሮ ካልሆኑ ብረታ ብረት ማዕድናት መካከል የጋሊዬም ምርት በ90.7 በመቶ፣ የሊቲዬም ምርት በ73.8 በመቶ፣ የብርቅዬ ማዕድናት (rare earth elements -REE) ምርት በ62.9 በመቶ፣ የጀርመኒየም ምርት በ31.1 በመቶ፣ እና የኢንዲዬም ምርት 21.3 በመቶ ጨምሯል። የእነዚህ ማዕድናት ዋና አገልግሎትም ከፈርጀ ብዙ የዲጂታል ቴክኖሎጂ እና ከአረንጓዴ የኃይል አማራጮች ጋር የተያያዘ ነው። እስከ አሁን እነዚህን ከዘመኑ የቴክኖሎጂ ለውጥ አቅጣጫ ጋር ተፈላጊነታቸው እየጨመረ ያሉ ማዕድናትን ኢትዮጵያ አታመርትም።

29. ስዕል 12 - 4፤ ፌሮ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ዓለም አቀፍ የምርት ለውጥ (በ2010 እና 2014 መካከል)



ምንጭ፤ World Mining Data 2024: Iron and Ferro-Alloy Metals, Non-Ferrous Metals, Precious Metals, Industrial Minerals, Mineral Fuels; International Organizing Committee for the World Mining Congresses.

30. **የዚህ ምድብ ማዕድናት የአማራ ብሔራዊ ክልል ክምችትን** በተመለከተ በዋናነት የሲሊከን ተሸካሚ ማዕድናት በስፋት ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሃያ ከሚደርሱት ፌሮ ያልሆኑ ማዕድናት መካከል ሊትዬም፣ መዳብ፣ እና እርሳስ እስካሁን መጠኑ ያልተረጋገጠ ክምችት በአራት የክልሉ ዞኖች እንደሚገኝ ጥናቶች ያሳያሉ።

31. በአለፉት አምሥት ዓመታት የሁሉም ዋና ዋና የከበሩ ብረት ማዕድናት ምርት በዓለም ላይ ቀንሷል። ከ2010 እስከ 2014 በነበሩት ዓመታት በተለይም ፓላዲዬም፣ የብር ማዕድን፣ እና ፕላቲንዬም ምርቶች እንደቅደም ተከተላቸው በ9.6 በመቶ፣ በ4 በመቶ፣ እና በ3.3 በመቶ ቀንሰዋል። የወርቅ የዓለም ጠቅላላ ምርትም በ1.3 በመቶ የቀነሰ ሲሆን የኢትዮጵያ የወርቅ ምርት በተመሳሳይ ወቅት ከዓለም የወርቅ ገበያ አቅጣጫ በተለየ በ68.8 በመቶ ጨምሯል። ነገር ግን የኢትዮጵያ የብር ማዕድን ምርት በተመሳሳይ ጊዜ በ20 በመቶ ቀንሷል።

32.

33. ስዕል 12 – 5፤ የከበሩ ብረት ማዕድናት ዓለም አቀፍ የምርት ለውጥ (ከ2010 እስከ 2014)




ምንጭ፤ World Mining Data 2024: Iron and Ferro-Alloy Metals, Non-Ferrous Metals, Precious Metals, Industrial Minerals, Mineral Fuels; International Organizing Committee for the World Mining Congresses.

34. በአማራ ብሔራዊ ክልል ከከበሩ ብረት ማዕድናት መካከል መጠኑ ያልተረጋገጠ የወርቅ ክምችት በአራት ዞኖች መኖሩ ይታወቃል። በክልሉ እስከ 2016 ድረስ 136.5 ኪሎ ግራም ወርቅ በባህላዊ መንገድ ለምቷል።

35. ከበርካታ የኢንዱስትሪ ማዕድናት መካከል የፍሎሮስፓር፣ ቦሮን፣ ፐሪላይት፣ ቨርሚኩይላይት፣ ፌልድስፓር፣ እና ግራፋይት ምርቶች እንደቅደም ተከተላቸው በ33 በመቶ፣ በ19 በመቶ፣ በ16 በመቶ፣ በ14.5 በመቶ፣ በ13 በመቶ፣ እና በ10.6 በመቶ ጨምሯል። ፍሎሮስፓር፣ ፐርላይት እና ፌልድስፓር ለበርካታ የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረቻ ግብዓትነት የሚውሉ ሲሆን ቨርሜኩላይት ለዘመናዊ ግብርና አገልግሎት ላይ ይውላል። ግራፋይት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች፣ ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ስልኮች እና የጭን ላይ መቀመሪያዎች ለሚጠቀሙባቸው ባትሪዎች መሥሪያ በግብዓትነት ከማገልገሉም በላይ ከመጻሚያ እርሳስ እስከ አረብ ብረት መሥሪያ፣ የሰበቃ መቀነሻ፣ ለጨረር ፈንጣቂ ቁሶች እና የኒኩሊየር ማብለያ ሥራዎች ጥቅም ላይ ይውላል። በተመሳሳይ ቦሮን ለበርካታ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ግብዓትነት የሚያገለግል ሲሆን በተለይም ለመስታዎት፣ ፋይበር ግላስ፣ ብረታ ብረት፣ ኮምፒውተሮች፣ ኒኩሊየር ማብላያዎች፣ ዘመናዊ ግብርና እና ሕክምና ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ይውላል።

36. ምርታቸው በከፍተኛ ደረጃ ከቀነሱ የኢንዱስትሪ ማዕድናት መካከል አልማዝ ቀዳሚው ሲሆን ለኢንዱስትሪ የሚውል የአልማዝ ምርት በ32 በመቶ ቀንሷል። እንደ ባራይት፣ ቤንቶናይት፣ እና ዚርኮን የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርትም ቀንሶ ታይቷል። ኢትዮጵያ ከምታመርታቸው የኢንዱስትሪ ማዕድናት መካከል የጂፕሰም ምርት በ56.6 በመቶ የቀነሰ ሲሆን የካኦሊን እና የዳያቶማይት ምርቶች ለውጥ አላሳዩም።

37. ስዕል 12 – 6፤ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ዓለም አቀፍ የምርት ለውጥ (ከ2010 እስከ 2014)




ምንጭ፤ World Mining Data 2024: Iron and Ferro-Alloy Metals, Non-Ferrous Metals, Precious Metals, Industrial Minerals, Mineral Fuels; International Organizing Committee for the World Mining Congresses.

38. የአማራ ብሔራዊ ክልል የኢንዱስትሪ ማዕድናት ክምችትን በተመለከተ ጂፕሰም በስፋት ይገኛል። እንደ ካኦሊን፣ ፌልድስፓር፣ ቤንቶናይት፣ እና ናትሮላይት - ዚዮላይት ማዕድናት መጠኑ ያልተረጋገጠ ክምችት በተለያዩ ዞኖች እንደሚገኝ ጥናቶች ያመለክታሉ። ነገር ግን ቴክኖሎጂ ገብ ለሆኑ እና ሰፊ የኢንዱስትሪ ሥራዎች ግብዓትነት የሚያገለግሉት እንደ ፍሎሮስፓር፣ ቦሮን፣ ፐርላይት፣ እና ግራፋይት የመሳሰሉ ማዕድናት ክምችት መኖሩ አይታወቅም።

39. በዓለም ላይ ምርታቸው ቀንሶ ከታዩት ስትራቴጂካዊ የነበሩ ማዕድናት ውስጥ ፔትሮሊዬም እና ዩራንዬም ይገኙበታል። በአለፉት አምሥት ዓመታት የፔትሮሊዬም ምርት በ1.45 በመቶ ቀንሷል። የበሰለ የድንጋይ ከሰል ምርት በ9 በመቶ የጨመራ ሲሆን ያልበሰለ የድንጋይ ከሰል (ሊግናይት) ምርት ደግሞ በ10.5 በመቶ ቀንሷል። ከነዳጅ ማዕድናት መካከል ዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ጋዝ ምርት በ5 በመቶ ጨምሯል። እነዚህ በነዳጅ ማዕድናት ላይ የተስተዋሉ ለውጦች በዓለም ላይ የኃይል አማራጭ ሽግግር ወቅትን አመላካች ናቸው።

## 12.3. የአማራ ክልል የማዕድን ልማት ዋና ዋና መገለጫዎች እና ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች

### የክልሉ የማዕድን ሀብት ልማት መገለጫዎች

40. የአማራ ክልል የማዕድን ሀብት ልማት ባሕርያትን ከንድፈ ሃሳባዊ ማዕድን አለኝታ (prospect of mineral deposit)፣ ከተቋማዊ አቅም፣ ከተረጋገጡ የማዕድን አለኝታዎች መጠን፣ እና ከዘርፉ ልማት አንጻር መቃኘት ይቻላል። የአማራ ብሔራዊ ክልል በተለይ በማዕድን ክምችት፣ በተቀቋማዊ አቅም፣ እና ዘርፉ ልማት ረገድ ከአጠቃላይ ኢትዮጵያ ጋር የሚጋራቸው ባሕርያት ስላሉ በአገር ደረጃ የሚገለጹ ዘርፉን የሚመለከቱ ጉዳዮች የአማራ ብሔራዊ ክልልንም የሚመለከቱ ናቸው።

41. **የአማራ ብሔራዊ ክልልን ጨምሮ የኢትዮጵያ የሥነ ምድር አወቃቀር ለአብዛኛዎቹ የማዕድን ዓይነቶች መገኛ ነው።** በኢትዮጵያ እስካሁን በተገኙ መረጃዎች መሠረት አገሪቷ ካላት 1.1 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ውስጥ 25 በመቶ የሚሆነው የቅድመ-ካምብሪያን (Precambrian) ቅርጸ ልውጥ እና እሳተ-ገሞራ ወለድ ዓለት፣ ተጨማሪ 25 በመቶ የሚሆነው የመካከለኛው ዘመን (Mesozoic) ንብብር ዓለት፣ እና 50 በመቶ የሚሆነው የቅርብ ዘመን (Cenozoic) የእሳተ ገሞራና ንብብር ዓለት የጂኦሎጂ ቅንብር ያለው ነው፡፡ የቅድመ-ካምብሪያን የጂኦሎጂ ቅንብር በተለይም ለብረት እና እንደ ኒኬል የመሳሰሉ የፌሮ ብረታ ብረት ማዕድናት፣ መዳብን ለመሳሰሉ ፌሮ ያልሆኑ ብረታ ብረት ማዕድናት፣ እንዲሁም እንደ ወርቅ ላሉ የከበሩ ብረት ማዕድናት አለኝታ መሠረት ነው። የመካከለኛው ዘመን የጂኦሎጂ ቅንብር ብረታ ብረት ነክ ለሆኑ እና ለነዳጅ ማዕድናት መገኛ ነው፡፡ በአብዛኛው የአገሪቷን አካባቢ የሚሸፍነው የቅርብ ዘመን የጂኦሎጂ ቅንብር ለነዳጅ ማዕድናት (የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ)፣ ፖታሽ፣ ጨው፣ የኖራ ድንጋይ፣ ጀሶ፣ የብርጭቆ አሸዋ፣ ዶሎማይት፣ ቤንቶናይት፣ ዳያቶማይት፣ ሶዳ አሽ፣ ፑሚስ፣ ኦፓል እና ዲኝ ለመሳሰሉት የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ እንዲሁም ኦፓልን ለመሳሰሉ የጌጣጌጥ ማዕድናት መገኛ መሠረት ነው፡፡

42. **ኢትዮጵያ የሁለት ምዕተ ዓመት የማዕድን ሀብት ልማት ውጥን እና በዘርፉ የሰባት አስርት ዓመታት የተቋም ግንባታ ታሪክ አላት።** በኢትዮጵያ የሥነ ምድር ጥናት፣ እንዲሁም የማዕድን ፍለጋና ምርመራ የተጀመረው በ1831 ሲሆን፣ የማዕድን ልማት ከሌሎች ዘርፎች ጋር በተቀናጀ መልኩ የታቀደው በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በመጀመሪያው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ (1949 – 1953) ነበር፡፡ የዕቅዱ መነሻም አብዛኛው የአፍሪካ የውጭ አገር ኢንቨስትመንት በማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ያተከረ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ከዚህ ትምህርት በመውሰድ ኢትዮጵያ የነበራትን ነጻነትና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ተጠቅማ በከፊል ከውጭ የሚገቡ፣ በከፊል ደግሞ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎችን ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በማዋል ለኢንዱስትሪያላዊነት ፈር መቀደድ ነበር። ከዚህ በመነሳት የማዕድን ሀብት ልማት የትኩረት አቅጣጫም የአገር ውስጥ የጥሬ ዕቃ ፍላጎትን ማሟላት እና የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ነበር፡፡ በተቋማ ደረጃ ደረጃ በ1958 የማዕድን ሚኒስቴር፣ በ1959 ደግሞ የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት ማቋቋም ተችሏል።

43. **በማዕድን ሀብት ልማት ዙሪያ የክልላዊ እና የአገራዊ ጥቅል ጭብት በአገር አቀፍ ደረጃ ለዋና ዋና ማዕድናት መፈጠር መሠረት የሚሆን የሥነ ምድር አወቃቀር እና በማዕድን ሀብት ልማት የረጅም ዘመን ተቋማዊ ተሞክሮ እንደመኖሩ መጠን የማዕድን ሀብት በቅጡ ለምቶ ለአጠቃላይ አገራዊ የኢኮኖሚ ልማት ደጋፊ ሚናውን ያለመወጣቱ ዕውነታ ነው።** በአሁኑ ጊዜ ያለው የክልሉ የማዕድን ልማት፣ የማዕድን አለኝታን በቅጡ ከመለየት፣ ማዕድናት ለምተው ለማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠን አቅም እንዲሆኑ ከማድረግ፣ እንዲሁም የማዕድን ዘርፍን እንደ አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ ከማዘመን አኳያ በአገር አቀፍ ደረጃ በየዘመኑ በተለያዩ የልማት ዕቅዶች የመወጠኑንና የመመላከቱን ያህል በሚጠበቀው ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ የዚህ ጭብጥ ዋና ዋና መገለጫዎች፤

    (1) በአገር አቀፍ ደረጃ እስከ 2007 የኢትዮጵያ የሥነ ምድር መረጃ ካርታ ሽፋን በ1፡250,000 መስፈርት 63 በመቶ መድረሱን፣ ከዚህም ውስጥም የአገሪቱ የጂኦሎጂ ካርታ ሽፋን በተመሳሳይ ወቅት 82 በመቶ መድረሱን፣ በተለይም የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምትን በተመለከተ በ1፡50,000 እና በላይ መስፈርት 74 የአለኝታ ቦታዎች መለየታቸውን፤ በክልል ደረጃ ደግሞ የክልሉን መሠረታዊ የጂኦሳይንስ ካርታ ሽፋን በ1፡50,000 መስፈርት 31,868 ካሬ ኪሎ ሜትር የደረሰ መሆኑንና በዚህም 17 በመቶ የሚሆነውን የክልሉን የቆዳ ስፋት መሸፈኑን፣ ከዚህም ባለፈ በማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት 4998.365 ካሬ ኪሎ ሜትር ወይም የክልሉን

የቆዳ ስፋት 2.8 በመቶ መሸፈን መቻሉን መረጃዎች ቢያመላክቱም እስከ አሁን በክልሉ በስትራቴጂካዊ ቁልፍ ማዕድናት ዙሪያ የተረጋገጠ መጠን በበቂ እና አስተማማኝ ሁኔታ አለመለየቱ፣

(2) በአገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በክልሉ የአገር ውስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ማዕድናት ላይ እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ውስን መሆናቸው፣

(3) በማዕድን ሀብት ልማት በተለይም ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የማዕድን ዓይነቶች ደፍረው የገቡ አልሚዎች ውስን መሆናቸው እና በአጠቃላይ የዘርፉ መዋዕለ ንዋይ ዝቅተኛ መሆኑ፣

(4) በዘርፉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ማዕድናትን በዓይነት፣ በብዛት፣ በጥራት፣ በቦታ፣ በአመላካች አዋጭነት እና በጊዜ ለይቶ ማቅረብ የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣ እና

(5) የማዕድን ሀብትን የኢንዱስትሪ ልማት መሠረትነት በአግባቡ ለይቶ በዘርፎች የፍላጎት እና አቅርቦት መስተጋብራዊ ቅንጅት የማዕድን ሀብትን ለተመረጡ አሻጋሪ ግቦች ማልማት የሚያስችል ትኩረት የሚሰጥ ሥርዓት አለመዘርጋት ናቸው።

44. **ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መገለጫዎች አንዱ ለሌላው በምክንያትነት ይመጋገባሉ።** ለማዕድን ዘርፉ አለመልማት፣ እና በተለይም በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢ ሚና መጫወት ላለመቻሉ ቀጥተኛ ምክንያት በዘርፉ የሚፈስሰው መዋዕለ ንዋይ በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት ዝቅተኛ የመሆን ችግር ነው። በዘርፉ ለሚታየው የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ዝቅተኛነት በአገሪቱ ዝቅተኛ የሆነ የማዕድን አለኝታ ሽፋን መረጃ በዝርዝርና በጥራት አለመኖር፣ መረጃው በሚገኝበትም ጊዜ መረጃ ከማቅረብ፣ የተቀላጠፈና ፈጣን የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ከማስፈን፣ ከማስተዋወቅና አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች ከመመለመል ጀምሮ ዘርፉን የማስተዳደር አቅም ውስንነት በቅርብ ምክንያትነት ተጠቃሽ ናቸው። የዝቅተኛ መረጃ ሽፋን እና የተቀላጠፈ የመዋዕለ ንዋይ አገልግሎት አሰጣጥ ምክንያቶች ደግሞ አጠቃላይ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና የቴክኖሎጂ አቅሞች ደካማነት ተጠቃሽ ነው።

45. **በጥቅል ደረጃ በአማራ ብሔራዊ ክልልም ሆነ በኢትዮጵያ ማዕድናትን ጨምሮ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት መኖሩ እየታወቀ፣ የተፈጥሮ ሀብቶች በተለይም ማዕድናት በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ መገኘታቸው የክልሉ እና የአገሪቷ ከሌሎች የበለጸጉ አገሮች አንጻር በልማት ወደኋላ የመቅረታቸው ምክንያትም፣ መገለጫም ነው።** ኢንዱስትሪያላዊነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአገር ውስጥ ያሉ ማዕድናትን አንጾ ዘመናዊ የማዕድን ኢንዱስትሪ መገንባት አለመቻል የመዋቅራዊ ሽግግር ስብራት አንድ መገለጫ ነው። ለአገር ውስጥ ግብዓት የሚሆን የለማ ማዕድን በክልሉ ወይም በአገር ውስጥ ባለመኖሩ ምክንያት የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ ከውጭ በማስገባት ሂደት ይቸገራሉ፤ በዚህም የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ተገቢ እሴት እንዳይጨምሩ፣ አትራፊ እንዳይሆኑ፣ በውጤቱም ኢንዱስትሪዎች እንዳይስፋፉ የጥሬ ዕቃ እጥረት ምክንያት ይሆናል። የዚህ ግልባጭ ዕውነታ ደግሞ በአገር ውስጥ የሚለሙ ማዕድናትን በበቂ እና አትራፊነትን በሚያረጋግጥ መጠን መጠቀም የሚችሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ተቋማት አለመኖራቸው የማዕድን ሀብት ልማትን የዘመናዊ ኢኮኖሚ አካል የሆነ ዘመናዊ የማዕድን ኢንዱስትሪ መፍጠር አዳጋች ሆኗል። ሁለቱ ዘርፎች በመልማትም ሆነ ወደ ኋላ በመቅረት የሚመጋገቡትን ያህል በጋራ የሚጎድሏቸው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና ይህን ቴክኖሎጂ መፍጠር፣ መተርጎም፣ እና መተግበር የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት አለባቸው።

46. **በክልል እና በአገር አቀፍ ለተስተዋለው የረጅም ዘመን የማዕድን ልማት ወደኋላ መቅረት መሠረታዊ ምክንያት በአጠቃላይ በኢኮኖሚ አፈጻጸሞች ላይ የሚስተዋለው የሥርዓታት ክፍተት ነው።** በማዕድን ዘርፍ ውስጥ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመዳበር፣ እና ለዚህ የሚሆን ሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር ለዘርፉ ልማትም ሆነ በአጠቃላይ ለመዋቅራዊ ሽግግር ትግበራ ተግዳሮት የመሆናቸውን ያህል የቴክኖሎጂ መረጣ እና የተመጠነ ውጤት ተኮር የሰው ኃይል ሥልጠና በዘርፎች ትስስር እና አጠቃላይ የመዋቅራዊ ሽግግር ማዕቀፍ ውስጥ የማዕድን ልማትን ሚና ለይቶ የሚረዳ እና ትኩረት የሚሰጥ በስትራቴጂ፣ በተቀናጀ ዕቅድ፣ እና በፖሊሲ የሚገለጽ ሥርዓት (system) ያስፈልጋል። በሁሉም የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች በአንድ ጊዜ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ እና ሙሉ ድጋፍ በማድረግ ልማት እንደማይረጋገጥ ሁሉ በሁሉም የማዕድን ዓይነቶች ከፍለጋ እስከ ማልማት በሚደርስ ሂደት መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ አዋጭ አይሆንም። የክልሉ እና የአገሪቷ አንዱ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተግዳሮትም ስትራቴጂካዊ በሆኑ በተመረጡ የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ከማተኮር ይልቅ በግብዓት፣ በኃይል ምንጭ፣ በማሽን እና በኦቶሜሽን ትስስር አግባብ የእሴት ሰንሰለትን ባልጠበቁ በርካታ ንዑስ ዘርፎች መበታተኑ ነው። የዚህ ነጸብራቅም ውስን ሀብትን ለውስን ግን ስትራቴጂካዊ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ግብዓት በሚሆኑ ውስን ግን ስትራቴጂካዊ ማዕድናት ላይ ለማዋል መቸገር ነው። በዚህ የዘርፎች እና የተቋማት ቅንጅት በጎደለበት አውድ በአጠቃላይ የዘርፉን ልማት ከሌሎች ዘርፎች ልማት ነጥሎ የማየት ችግር ወይም የመዋቅራዊ ሽግግር መሠረቱ የማዕድን ሀብትን በቅጡ ማነጽ መሆኑን በተገቢው

ደረጃ ግምት ውስጥ ያለማስገባት እሳቤ ይፈጠራል። ይህ እሳቤ የማዕድን ዘርፍ የተናጠል ዕቅድ እንዲወስድ እና ማዕድናትን ለኢንዱስትሪ ልማት እና ኢንዱስትሪያላዊነት ግብ ከፍ አድርጎ ከማቀድ ይልቅ የውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ የወጣቶች ሥራ ፈጠራ የመሳሰሉ የአጭር ጊዜ ግቦችን ታሳቢ ባደረጉ እና በአብዛኛው በከበሩ እና በጌጣጌጥ ማዕድናት ልማት ላይ እንዲያተኩር ያደርገዋል።

## የማዕድን ሀብት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች

47. የማዕድን ዘርፍ ልማት ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫ ማዕድናትን እና ተያያዥ የከርሰ ምድር ሀብቶችን ለኢንዱስትሪያላዊነት ማነጽ ነው። በዚህም መሠረት የማዕድን ዘርፍ ልማት ከኢንዱስትሪያላዊነት ግቦች ጋር የሚጣጣሙ ስድሥት ዋና ዋና ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ይኖሩታል፤

(1) **ማሽንን፣ ግብዓትን፣ የኃይል ምንጭን፣ እና የአቶሜሽን ሥርዓትን ከጫፍ እስከ ጫፍ የማስተሳሰር የኢንዱስትሪ እና ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ በማዕድን ሀብት ልማት መደገፍ፤**

- የብረታ ብረት እና የማሽን ቴክኖሎጂ የብረት (iron) እና የተያያዥ ብረታ ብረት (ferro – alloy metals) ማዕድናት ልማትን መፈለግ፣ ማጥናት እና ማብልጸግን ታሳቢ ያድርጋል።
- የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምግብ እና መጠጥ፣ ጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ እንዲሁም የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን የመሳሰሉ መሠረታዊ ምርቶችን ለማምረት የግብርና ዘርፍ ውጤቶችን በግብዓትነት የሚጠቀም ቢሆንም ከፍተኛ እና ዘመናዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስብስብ መካከለኛ ግብዓቶችን የሚያገኘው ከማዕድናት ነው። ለዚህም የሚያገለግል ጠንካራ የኬሚካል ኢንዱስትሪ መሠረት ለመጣል እና የኮንስትራክሽን ማጠናቀቂያ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት የአገር ውስጥ ማዕድናት ልማት ከፍተኛ ሚና ይጠበቅበታል።
- አረንጓዴ የኃይል አቅርቦት የማረጋገጥ የረጅም ጊዜ ግብ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመጭር እና መካከለኛ ጊዜ የማዕድን የኃይል ምንጮችን መጠቀም የሽግግር ጊዜ የኃይል እጥረትን ለመፍታት ያስችላል።
- በዘመነ ዲጂታል ቴክኖሎጂ እና የአረንጓዴ የኃይል ምንጭ ሽግግር ወቅት የኮምፒውተር ቺፐስ፣ የኮምፒውተር እና የተንቀሳቃሽ ስልክ ባትሪዎች፣ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ የመኪና ባትሪዎች፣ የፀሐይ ኃይል ማጠራቀሚያ ቁሶች የመሳሰሉት መተግበሪያዎች የሚጠቀሙት በብዛት ከሚገኘው ሲሊከን እስከ ሊትዬም፣ ኮባለት፣ መዳብ፣ ኒኬል፣ ማንጋኒዝ፣ ግራፋይት፣ እና ሌሎች እናሳ የመሬት ንጥረ ነገሮችን (rare earth elements) የሚያካትቱ ማዕድናትን በመሆኑ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት እነዚህን ማዕድናት እንደመገኘታቸው መጠን በአገር ውስጥ ማልማትን ይጠይቃል።

(2) **የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማትን የግብዓት እና የማጠናቀቂያ ቁሶች ፍላጎትን በአገር ውስጥ የማዕድን ሀብት ማሟላት፤** በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለሚረጋገጥ ኢንዱስትሪያላዊነት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚና ከፍተኛ ነው። አብዛኛው የመዋዕለ ንዋይ ስምሪት ይብዛም ይነስም የኮንስትራክሽን ደረጃ አለው። ተደራሽ እና ዘላቂ ኢኮኖሚን ለማረጋገጥ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማትን በአገር ውስጥ ግብዓቶች ላይ እንዲመሠረት ይደረጋል።

(3) **የክልሉን እና የአገር ውስጥ ማዕድናትን ለዘመናዊ ግብርና ልማት ማነጽ፤** ዘመናዊ ግብርና ከሚፈልጋቸው አቅሞች ውስጥ በአምራች ኢንዱስትሪ የሚፈበረኩ ማሽኖች እና ሰው ሠራሽ ማዳበሪያዎች ዋናዎቹ ሲሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለእነዚህ አቅሞች ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን የክልሉን እና የአገር ውስጥ ማዕድናትን ለእነዚህ አቅሞች ግንባታ ያውላል። ከዚህም በተጨማሪ በክልሉ ከፍተኛ ተግዳሮት የሆነውን የአፈር አሲዳማነት ለመከላከል እንደ የኖራ ድንጋይ የመሳሰሉ የከርሰ ምድር ሀብቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

(4) **በማዕድን ሀብት ልማት ዘላቂ ማሕበረሰባዊ፣ ክልላዊ እና አገራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤** የማዕድን ሀብት አላቂ ነው። በዚህም ምክንያት የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀሙ በዝባዥ ሳይሆን አሻጋሪ (transformative) መሆን ይገባዋል። በዚህም መሠረት፣

- በማዕድን ዘርፍ የሚደረጉ የከበሩ ማዕድናትን እና ሌሎች ትርፍ ማዕድናትን ያማከሉ የወጪ ንግድን ግብ ያደረጉ የመዋዕለ ንዋይ ስምሪቶች ተገቢ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ፣ የተገኘው

የውጭ ምንዛሪ ለተሻሉ የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የዘመናዊ ግብርና እና ዘማናዊ አገልግሎት ዘርፍ መዋሉ፣ ከዚህ ልማትም የክልሉ እና የአካባቢው ማሕበረሰብ ተጠቃሚ መሆኑ ይረጋገጣል።

- ለሥራ ፈጠራ እና አነስተኛ የገቢ ማግኛ ግቦች የሚደረጉ የዘርፉ እንቅስቃሴዎች የማዕድን ሀብቱ በሽሚያ እና በፍጥነት ሲያልቅ የማሕበረሰብ ተጠቃሚነት ቀጣይነት እንዳይስተጓጎል እና የግጭት ምንጭ እንዳይሆን በተመጠነ እና ጥሬ ማዕድን ሽጦ ከሚገኝ ገቢ በላይ ለተሻለ የኢኮኖሚ መሠረት በግብዓትነት እንዲውል በሚያስችል የዕሴት ፈጠራ አግባብ ይቃኛሉ።
- በማዕድን ልማት ወቅት አካባቢ እንዳይበከል እና እንዳይራቆት የማዕድን ልማቶች ተገቢ የአካባቢ ጥበቃ መስፈርቶችን መከተላቸው ይረጋገጣል፤ በልማቱ ምክንያት የተራቆቱ አካባቢዎች በአረንጓዴ መልሶ ልማት እንዲሸፈኑ ይደረጋል።

(5) **የማዕድን ዓይነት፣ ጥራት፣ ክምችት፣ ስርጭትን ለስትራቴጂካዊ ማዕድናት ቅድሚያ ሰጥቶ በጥናት ማረጋገጥ፤** የማዕድናት አለኝታ ጥናት ክልሉ ያሉትን ስትራቴጂካዊ ማዕድናት ከኢንዱስትሪያላዊነት ግቦች አንጻር የዘርፎችን የግብዓት ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በዘመኑ ቴክኖሎጂ እና በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ ተጨባጭ ጥናት በማካሄድ መልማት የሚችሉትን ለማልማት፣ በክልሉ የማይገኙ ወሳኝ ማዕድናትን ከክልሉ ውጪ ካሉ ምንጮች ለማፈላለግ ዕድል በሚሰጥ አግባብ በትኩረት ይካሄዳል።

(6) **በሰው ኃይል እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረት ተወዳዳሪ የማዕድን ኢንዱስትሪ መፍጠር፤**

- በመካከለኛ ጊዜ በአገር ውስጥ አቅም ፈጥሮ በረጅም ጊዜ በቀጠናው እና ዓለም አቀፍ ደረጃ በማዕድን ፍለጋ እና ማልማት ላይ አቅም መገንባት የሚችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ እና ብቁ የሰው ኃይል አቅም ያለው የማዕድን ኢንዱስትሪ የመፍጠር ግብ የኢንዱስትሪያላዊነት አንዱ አካል ነው። ዘርፉን ለማዘመን ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ መማርና ከራስ ሁኔታዎች ጋር በማዋሃድ በማዕድን ምርት ብቻ ሳይሆን በዘርፉ የቴክኖሎጂ መስክ ጭምር መወዳደር ግድ የማለቱን ያህል፣ ይህን እውን ለማድረግ የሰው ኃይልን ማብቃት ምትክ የሌለው ጉዳይ ነው። ለዚህም የመስኩ ሠራተኞችና የማዕድን መሃንዲሶች በውጭ አገር ጭምር የተግባር ሥልጠና እንዲወስዱ በማድረግ የዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ይፋጠናል።
- የማዕድን ዘርፍ በተለይም በከበሩ ማዕድናት ንዑስ ዘርፍ ዓለም አቀፍ ንግድ የሚካሄድበት በመሆኑ የአገር ውስጥ የማዕድን ሀብት አቅም ላይ በመጀመር የዘርፉ ተወዳዳሪ ለመሆን መሠረት ይጣላል።
- የክልላዊ እና አገራዊ የተወዳዳሪ ማዕድን ኢንዱስትሪ መሠረት በዘርፉ የሚደረግ ጥናት እና ምርምር በመሆኑ የዘመኑን ሣይንስ እና ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ እና ብቁ ተመራማሪዎች ያሉት የጥናት እና ምርምር ተቋማዊ አቅም ይገነባል።

## 12.4. ዓላማ እና ግቦች

48. የማዕድን ዘርፍ ልማት ዋና ዓላማ ለክልሉ ማሕበረ-ኢኮኖሚያዊ እድገት መነሻ የሚሆን መሠረታዊ የስ-ምድር ካርታ በማዘጋጀት ማዕድናትን በአይነት፣ በጥራት፣ በስርጭት፣ ክምችት መጠን በማጥናት የዘርፉን መዋዕለ ንዋይ አስፋፍቶ የክልሉን የፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ ማሳካት፣ እና የዘመናዊ ኢኮኖሚ አካል የሆነ የማዕድን ኢንዱስትሪ መገንባት ነው። የማዕድን ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ዝርዝር ዓላማዎች፤
    1. ለብረታ ብረት እና ለማሽን ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ የብረት እና ተያያዥ የብረታ ብረት ማዕድናት (iron and ferro alloys)፣ ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ልማት፣ ለኬሚካል ኢንዱስትሪ፣ ለዘመናዊ ግብርና፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ፣ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ማዕድናትን መፈለግ፣ ማጥናት እና ማበልጸግ፤
    2. የከበሩ ማዕድናትን ልማት በማፋጠን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት እና ለአገራዊ ቱሪዝም ልማት አስተዋጽዖ ማድረግ፣
    3. በማዕድን ልማት ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትን፣ ማሕበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ በማዕድን ልማት ሂደት ከብክለት የጸዳ አካባቢን ማረጋገጥ፣
    4. የማዕድን ልማት መዋዕለ- ንዋይን ማበረታታት እና ማስፋፋት፣ እና
    5. በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በጥናት እና ምርምር፣ እንዲሁም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተጠናከረ አገር በቀል የማዕድን ኢንዱስትሪ አቅም መገንባት ናቸው።

49. የማዕድን ሀብት ልማት ዕቅድ ዝርዝር ግቦች በዝርዝር የዘርፍ የዕቅድ ሰነድ የሚለዩ ሲሆን፣ ዋና ዋና የዘርፉ ልማት ግቦች የሚከተሉት ናቸው፤

1. በ1፡50,000 መስፈርት የስነ ምድር ጥናትና ካርታ ዝግጅት ሽፋንን ከ31,868 ካሬ ኪሎ ሜትር ወደ 61,732.4 ካ.ኪ.ሜትር ማሳደግ፣
2. የክልሉን የማዕድን ሀብት አይነት፣ ክምችት፣ጥራት እና ስርጭት ሽፋንን በ1፡50,000 በላቀ መስፈረት ከ5,298.04 ካሬ ኪሎ ሜትር ወደ 6,357.66 ካሬ ኪሎ ሜትር ማሳደግ፣
3. የብረት (iron)፣ የተያያዥ ብረታ ብረት (ferro – alloy metals)፣ ከዘመኑ ቴክኖሎጂ እና የኢንዱስትሪ አቅጣጫ ጋር የሚሄዱ የወሳኝ ማዕድናት (critical minerals) እና የከፊል አስተላላፊ (semi conductors) ማዕድናትን በክልሉ በአስተማማኝ መጠን መኖሩን ማረጋገጥ፣
4. በክልሉ የሚገኙ የተፈጥሮ ድንጋይ (natural or dimension stone) ዓይነት፣ ጥራት፣ እና መጠን ሙሉ በሙሉ ማረጋገጥ እና ለልማት ዝግጁ ማድረግ፣
5. ለክልሉ አሲዳማ አፈር ማከሚያ የሚሆን የኖራ ድንጋይ ምርት ችግሩ ባለባቸው አካባቢዎች ተደራጅተው ለሚያለሙ እና ለሚያቀርቡ አልሚዎች ፈቃድ መስጠት፣ ችግሩንም ሙሉ በሙሉ መቅረፍ በሚያስችል ሁኔታ የተፈላጊ ማዕድናትን አቅርቦት ማረጋገጥ፣
6. ከውጭ የሚገቡ ለግብዓትነት እና ለመጨረሻ ፍጆታ (final consumption) የሚውሉ የኢንዱስትሪ ማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ በሚመረቱ የማዕድን ውጤቶች የመተካት አቅምን ማዕድናቱ እንደመገኘታቸው መጠን ማሳደግ፣
7. የአምራች ኢንዱስትሪን ጨምሮ የሌሎች ዘርፎችን የግብዓት ፍላጎት እና የዘማናዊ ማዕድን ኢንዱስትሪ ግብን ታሳቢ ያደረጉ በወሳኝ እና ስትራቴጂካዊ ማዕድናት ልማት ላይ የሚያተኩሩ አምሥት ፕሮጀክቶች መለየት፣ ማጥናት እና ለልማት ዝግጁ ማድረግ።

## 12.5. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

50. የማዕድን ዘርፍ ልማትን ግቦች ለማሳካት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች

- የክልሉን የቆዳ ስፋት የሚሸፍን ሁሉን አቀፍ የማዕድን አለኝታ ጥናት የማድረግ የረጅም ጊዜ ግብ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመዋቅራዊ ለውጥ ግቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሌሎች ዘርፎችን በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግብዓት ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ለቁልፍ ማዕድናት ትኩረት ሰጥቶ ጥራት ያለው የማዕድን አለኝታ መረጃ መሰብሰብ፣
- በዘርፉ ልማት ፈጥኖ ተስተካካይነትን ለማረጋገጥ የክልሉን የመልከዓ - ምድር ሁኔታ፣ የትራንስፖርትና የማዕድናት ዓይነትን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ የፍለጋ ቴክኖሎጂ መጠቀም፣
- የዘርፉን የሥራ ድርሻ የሚወስኑና ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት ግልጽ የሚያደርጉ ሕግጋት በዝርዝር ማውጣት፣ ከተቋማት ጋር በጋራ የማቀድ እና የማዕድን ሥራዎችን በጋራ ለማልማት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣
- አግባብነት ያለው፣ በተግባር የተደገፈ የሰው ኃይል ሥልጠና ማቀድ እና ማጠናከር፣
- በማዕድን ልማት ላይ የዘርፎች፣ የግሉ ዘርፍ፣ የመንግሥት እና የምርምር ተቋማት ጥምረት መፍጠር እና ማጠናከር፣ በጋራ ማልማት፣
- የማዕድን ልማት መዋዕለ ንዋይ እስኪመጣ ከመጠበቅ እና የመጣውን ሁሉ ከመቀበል ቀድሞ በጥናት በተረጋገጡ የመዋዕለ ንዋይ ፕሮጀክቶች፣ በተለይም የብረት እና ፌሮ ብረታ ብረት ማዕድናት ፕሮጀክት፣ የቴክኖሎጂ ነክ ቁልፍ ማዕድናት ልማት ፕሮጀክት፥ የፖታሽ ማዕድን ልማት ፕሮጀክት፣ የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፕሮጀክት፣ የከበሩ ማዕድናት ፕሮጀክት በመሳሰሉ ተጨባጭ ፕሮጀክቶች መመራት፤
- ለዘመናዊ የማዕድን ሀብት መዋዕለ - ንዋይ፣ ልማት፣ እና ግብይት የሚመጥን የሕግ ሥርዓት መዘርጋት፣ እንዲሁም
- በዘርፉ ተፈጻሚ እና ችግርን በወቅቱ መፍታት የሚያስችል የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ማስፈን ናቸው።

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

# የግንባታ ዘርፍ ልማት

## 13.1. መነሻዎች

### የትኩረት መሠረት

1. **በመካከለኛውም ሆነ በረጅም ጊዜ ዕቅዱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በተለየ ሁኔታ ትኩረት እንዲሰጠው የሚያደርጉ ሁለት ዐበይት ምክንያቶች፣ በሁሉም አምራች ዘርፎች እና ሌሎች የትኩረት መስክ ዘርፎች መዋዕለ - ንዋይ ወስጥ የኮንስትራክሽን ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ፣ እና በመዋቅራዊ ሽግግር ሂደት በሚያልፍ ኢኮኖሚ እንደ አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ በመዘመን ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ ስለሚኖረው ነው።** በዚህ የልማት ዕቅድ ትኩረት በተሰጣቸው እንደ ግብርና አምራች ኢንዱስትሪ፣ ማዕድን፣ ቱሪዝም፣ መሠረተ-ልማት እና በርካታ የአግልግሎት ዘርፎች ከሚደረግ መዋዕለ - ንዋይ ውስጥ ከ30 እስከ 40 በመቶ የሚሆነው የኮንስትራክሽን ድርሻ እንደሚሆን ይጠበቃል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ብቃት በእነዚህ ዘርፎች ላይ የሚገነቡ የማምረቻ አቅሞችን ጥራት እና ቅልጥፍና ይወስናል። በኮንስትራክሽን ዘርፍ አጥብቆ የሚሠራ ሥራ በሌሎች ዘርፎች የሚታዩ የቅልጥፍና ጉድለቶች (ኢ-ቅልጥፍናዎች) ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቅረፍ ያስችላል። በሌላ በኩል የዘርፎች የኮንስትራክሽን ፍላጎት በጨመረ መጠን አናጺዎች፣ የቤት ሀብት አልሚዎች፣ አጠቃላይ ተቋራጮች፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ ማሕበራት፣ የአርክቴክቸር እና የምህንድስና ባለሚያዎች ከዲዛይን እስከ አርክቴክቸር፣ እቅድ፣ ቅየሳ፣ ግንባታ፣ እና የፕሮጅክት አስተዳደር ባሉ እርከኖች ሁሉ በመሳተፍ ዘረፉን አንድ ትልቅ ኢንዱስትሪ ማድረግ ይቻላል፤ ትልቅ ኢንዱስትሪ በትልቅ ዕቅድ በላቀ ትኩረት መመራት ይኖርበታል።

2. **የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን ሚና ተገንዝቦ ዘርፉን ለማዘመን እና የሚጠበቅበትን አበርክቶ ከፍ ባለ ደረጃ ለማረጋገጥ ንዑስ ዘርፎቹን በቅጡ መረዳት ይጠይቃል።** የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሕንጻ ግንባታ (building construction)፣ መሠረተ - ልማት (heavy civil or heavy engineering)፣ እና የኢንዱስትሪ ኮንስትራክሽን (industrial construction) ናቸው። የሕንጻ ግንባታ የመኖሪያ፣ የኮሜርሻል፣ የተቋማት፣ እና የቅይጥ ተብሎ በአራት ንዑስ - ንዑስ ዘርፎች ሊከፈል ይችላል። የመሠረተ - ልማት ግንባታ ግድቦችን፣ ድልዲዮችን፣ መንገድ እና አውራ ጎዳናዎችን፣ የባቡር ሃዲዶችን፣ የአየር ማረፊያዎችን፣ ወደቦችን፣ የውሃ ሥራዎችን፣ እና የማሕበረሰብ መሠረታዊ አገልግሎቶች ማሰራጫዎችን ያካትታል። የኢንዱስትሪ ኮንስትራክሽን የነዳጅ ማውጫ ግንባታን፣ የማዕድን እና ኳሪንግ ሥራዎች ግንባታን፣ የኬሚካል እና ሌሎች የማኑፋክቸሪንግ ማምረቻ ፋብሪካዎች ግንባታን፣ የብረት እና ዐረብ ብረት ማቅለጫ እና ማትቢያ ምንቸቶችን ያጠቃልላል።

3. **የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በሁሉም ወሳኝ ዘርፎች በሚደረጉ መዋዕለ - ንዋይ ሂደቶች ውስጥ መኖር፣ የሚያድግ እና እንደ ኢኮኖሚው መዋቅር ደረጃ የሚቀየር እንጂ የሚያከትም ወይም የሚደክም የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚና እንደሌለ፣ ለዚህም የረጅም ጊዜ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ - ካርታ እንደሚያስፈልገው ያሳያል።** ከአጭር ጊዜ አኳያ በአማራ ብሔራዊ ክልል በከተማ ሙት ካፒታል (dead capital) ሆነው ከቆሙ ዕድሜ ያስቆጠሩ ባለ ብዙ ወለል ጅምር ፎቆች በላይ በርካታ የቤተሰብ አባላትን የኑሮ መሠረታቸው ከሆኑት እንስሳት እና እህል ጭምር ሰትረው የሚይዙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የገጠር ደሳሳ ጎጆዎች የበለጠ ፋይዳ እንዳላቸው ለመገንዘብ ይቻላል። የኮንስትራክሽን ዘርፍ አንድ ግንባር ቀደም ተግባር የገጠር ጎጆዎችን ማሻሻል እና የአርሶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ ለመቀየር ለሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና መጫዎት ነው።

4. **የተዘረዘሩት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ንዑስ - ንዑሳን ዘርፎች መብዛት እና በሁሉም የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ዘርፎች ውስጥ የራሱ ወሳኝ ድርሻ መኖር** ዘርፉን አማክሎ ለመምራት አስቸጋሪ ስለሚያደርጉት፣ ይህ ዕውነታ የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊነት የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው ያመላክታል። በአለፉት የልማት ዕቅድ ትግበራዎች ወቅት በሁሉም መስክ ሊባል በሚችል ደረጃ ጎልቶ የወጣ ተግዳሮት የቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆን እና የአንድ ዘርፍ በሌላ ዘርፍ አፈጻጸም እስረኛ የመሆን ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር በተለይ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለሁሉም ዘርፎች መሠረታዊ የትግበራ አካል መሆን የኢንዱስትሪው አንዱ ቁልፍ ስትራቴጂ ዘርፉን ከማዘመን በተጨማሪ ውጤታማ የዘርፎች ቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት ማስፈን ነው።

## አፈጻጸም

5. **በአለፉት ተከታታይ የልማት ዕቅዶች የትግበራ ወቅት የአማራ ብሔራዊ ክልል የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናማ በማድረግ ለኢኮኖሚው ማበርከት የሚጠበቅበትን ሚና መጫዎት እንዲችል የሬጉላቶሪ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወንን፣ በክልሉ የሚገነቡ ግንባታዎች የአገሪቱን ህንፃ ኮድና የጥራት ደረጃዎች ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥን እና ጥራታቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ማድረግን፣ እንዲሁም የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ኮንትራት አስተዳደር ስራዎች ውጤታማነትን በማጠናከር በዘርፉ የሚታየውን ምዝበራ ለመታገል የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርን ዓላማ ያደረጉ ግቦችን ለማሳካት እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡** በተለይም የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ወቅትን ጨምሮ በአለፉት አሥራ አራት ዓመታት በክልሉ (1) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉሌሽን አቅም ግንባታ ስራዎች፣ (2) የሥራ ተቋራጮች፥ አማካሪዎችና ባለሙያዎች አቅም ግንባታ፥ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ ስራዎች፣ እንዲሁም (3) የኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጅ ጥናትና ምርምር ስራዎች ታቅደው ወደ ተግባር ተሸጋግረዋል። በእነዚህ ዋና የዘርፉ የትኩረት መስኮችም የተቆጠሩ አፈጻጸሞች ተመዝግበዋል።

6. **ዘርፉ የሚጠበቅበትን ጉልህ ሚና ይጫዎት ዘንድ የተወሰዱት ርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የዘርፉ የአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት አፈጻጸም በተጨማሪ ዕሴት ሲለካ ከአገራዊ አፈጻጸምም ሆነ በክልሉ ሊጫዎት ከሚገባው ሚና አንጻር አበረታች አልነበረም።** ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት የክልሉ የዘረፉ ተጨማሪ እሴት  በዓመትበአማካይ በ3.6 በመቶ ብቻ ያደገ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ የአገር አቀፍ የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በ16.5 በመቶ ተመንጥቋል። በተለይም ከ2011 እስከ 2016 በነበሩት ስድስት ዓመታት የክልሉ የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በየዓመቱ በአማካይ በ2.2 በመቶ ቀንሷል። በአንጻሩ የአገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተጨማሪ ዕሴት በአለፉት ተመሳሳይ አምሥት ዓመታት በ8.7 በመቶ በዓመት አድጓል።

7. ሠንጠረዥ 13-1፤ የክልል እና የአገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት ዕድገት አፈጻጸም

**አማራ ብሔራዊ ክልል**

| | የዕድገት ምጣኔ | | ከክልላዊ ምርት ድርሻ | | ከክልላዊ ምርት ዕድገት ድርሻ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1998 - 2016 | 2011 - 16 | 1998 | 2016 | 1998 - 2016 | 2011 - 16 |
| ኮንስትራክሽን | 3.6 | -2.2 | 11.5 | 6.0 | 0.4 | -0.2 |
| ክልላዊ ምርት | 7.2 | 4.9 | 100 | 100 | 7.2 | 4.9 |

**ኢትዮጵያ**

| | የዕድገት ምጣኔ | | ከአገራዊ ምርት ድርሻ | | ከአገራዊ ምርት ዕድገት ድርሻ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1998 - 2016 | 2011 - 16 | 1998 | 2016 | 1998 - 2016 | 2011 - 16 |
| ኮንስትራክሽን | 16.5 | 8.7 | 6.7 | 21.0 | 2.0 | 1.8 |
| አገራዊ ምርት | 9.0 | 7.2 | 100 | 100 | 9.0 | 7.2 |

*ምንጭ፤ ምንጭ፣ የኢፌዴሪ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር አገራዊ የሀብት ማጠቃለያ እና የአብክመ የፕላን እና ልማት ቢሮ ክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ መረጃዎችን በመጠቀም የተሰላ*

8. **ከ1998 እስከ 2016 በነበሩት ዓመታት በክልሉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዝቅተኛው አፈጻጸም የተስተዋለው የአገር አቀፍ የዘርፉ አፈጻጸም ከፍተኛ በነበረበት ወቅት ጭምር ነው።** በዚህ ወቅት ዝቅተኛው የዘርፉ የዕድገት ምጣኔ የተመዘገበው በ2002 የበጀት ዓመት ሲሆን የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በ5.1 በመቶ ቀንሶ ነበር። በተመሳሳይ ዓመት የአገር አቀፍ የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት የዕድገት ምጣኔ ከ1998 እስከ 2011 በነበሩት ዓመታት ከተመዘገቡት ምጣኔዎች ዝቅተኛው ቢሆንም በ10.9 በመቶ አድጓል። ከ2002 በኋላ በነበሩት ሁለት ዓመታት የአገር አቀፉን ፍኖተ - ኩነት (trend) ተከትሎ በ2003 በ11.7 በመቶ አገግሞ፣ በቀጣዩ ዓመት በ14.2 በመቶ ማደግ ችሎ ነበር። ከ2005 እስከ 2010 በነበሩት ስድስት ዓመታት የክልሉ ተጨማሪ እሴት በ4.9 በመቶ ያዘገመ ሲሆን፣ ይህ ክስተት

የአገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በአማካይ ፈጣን በሚባል የ25.9 በመቶ ምጣኔ በአደገበት ወቅት የታየ ነው።

9. ግራፍ 13-1፤ የክልል አቀፍ እና አገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት (በመቶኛ)




ምንጭ፤ የኢፌዴሪ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር አገራዊ የሀብት ማጠቃለያ እና የአብክመ የፕላን እና ልማት ቢሮ ክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ መረጃዎችን በመጠቀም የተሰላ

10. **ለአለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት የክልሉ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ለክልላዊ ምርት እና የምርት ዕድገት የነበረው አስተዋጽዖ ከአገር አቀፉ ሁኔታ በተለየ በግማሽ ያህል ቀንሷል።** የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ በ1998 ከነበረበት 11.5 በመቶ በ2016 ወደ 6 በመቶ አሽቆልቁሏል። በዚያው መጠን የዘርፉ የዕድገት አስተዋጽዖ ከአነስተኛ ደረጃ ወደ ኅታች (ኔጋቲቭ) ወርዷል። በአንጻሩ በአገርአቀፍ ደረጃ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በ1998 ከነበረበት 6.7 በመቶ በ2016 ወደ 21 በመቶ ያሻቀበ ሲሆን፣ በውጤቱም የዘርፉ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት የነበረው አስተዋጽዖ በአማካይ 22.2 በመቶ ወይም ከ9.0 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ 2 የመቶኛ ነጥብ ነበር።

11. ግራፍ 13-2፡ የክልል አቀፍ እና አገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት (በመቶኛ)




ምንጭ፤ የኢፌዴሪ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር አገራዊ የሀብት ማጠቃለያ እና የአብክመ የፕላን እና ልማት ቢሮ ክልላዊ የሀብት ማጠቃለያ መረጃዎችን በመጠቀም የተሰላ

12. **የክልሉ የአምራች ዘርፍ ዝቅተኛ አፈጻጸም ከጊዜያዊ ደፋቂ ኩነቶች** (temporary negative shocks) **ያለፈ ነው።** ለክልሉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት በዚህ ደረጃ መቀነስ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የዕድገት ምጣኔው በአንጻራዊነት መቀዝቀዝ አንዱ ምክንያት ምናልባት በዚያው ዓመት የተካሄደው አገራዊ ምርጫ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከዚያ በኋላ በነበሩ ዓመታት የአገር አቀፍ አፈጻጸም ከፍተኛ በነበረባቸው ዓመታት ሳይቀር የተስተዋለው ዝቅተኛ አፈጻጸም የችግሩ ምንጭ ከአጭር ጊዜ ደፋቂ ኩነቶች የዘለለ ያደርገዋል። እንደ መነሻ፣ ተጨማሪ እሴት (gross value added) የሚሰላው በመነሻ ወይም በወቅቱ ዋጋ ከተሰላው ምርት ወይም አገልግሎት (gross value of output) ላይ የአጭር ጊዜ (ከአንድ ዓመት በላይ የማይዘልቁ) ግብዓቶችን ወጪ (intermediate consumption) በመቀነስ በመሆኑ የተጋነኑ የግብዓቶች የዋጋ ክለሳዎች ዝቅተኛ ተጨማሪ ዕሴት እንዲፈጠር ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዚህም በላይ በክልሉ በአንጻራዊነት የዘርፉ እንቅስቃሴ አነስተኛ መሆን እና አቅም ያላቸው ተቋራጮች መሠረታቸውን ከክልሉ በማዛወራቸው ምክንያት በእንቅስቃሴው መቀነስ ልክ የዘረፉ ተጨማሪ እሴት ቀንሶ ሊሆን ይችላል። ከእነዚህ መላ ምቶች ባለፈ ግምገማ ወስዶ የቀጣዮቹን ዓመታት የመካከለኛ እና የረጅም ዘመን ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ በማያሻማ ሁኔታ ለማመላከት በተጨባጭ መረጃ ላይ የተደገፈ ጥናት ይጠይቃል። ነገር ግን፣ በአሉት መረጃዎች መሠረት ቢያንስ በተወሰኑ የግንባታ ንዑስ ዘርፎች የሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች እንደሚከተለው ተለይተዋል፤

1. በየደረጃው ያለው አመራር የዘርፉን ልዩ ፋይዳ ተገንዝቦ ድጋፍና ክትትል በማድረግ እና በተለይም የህንጻ አዋጁን በማስፈፀምና በመፈፀም ረገድ አሁንም ከፍተኛ የእውቀትና የክህሎት ክፍተት የሚታይበት ሲሆን፣ ይህም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በጠንካራና አስተማማኝ በሆኑ የሬጉላቶሪ ሥርዓት እንዳይመራ አድርጎታል፤ በውጤቱም በግንባታ ጥራትና አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፤
    i. አብዛኛው የመንግስት ተቋማት ግንባታ በሚያከናውኑበት አካባቢ ዲዛይኑ ሳይጣጣምና በአዋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል (ህንፃ ሹም) ሳያፀድቁ ያለግንባታ ፈቃድ ግንባታ ማከናወን የተለመደ ነው፤
    ii. የህንጻ አዋጁን ከመተግበር አንጻር ዋናው ትኩረት የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሚገነቡ ግንባታዎች ደህንነታቸው የተረጋገጠ፣ አደጋ የማይፈጥሩ፣ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽነታቸው የተረጋገጠ፣ በአሰሪና በተቀጣሪ መካከል የግንባታ መድህን የተረጋጋጠ መሆኑን የመከታተልና የመቆጣጠር እንዲሁም ሌሎች የግንባታ ስታንዳርዶች ተከብረው ስለመፈፀማቸው የመቆጣጠር ጉዳይ በሚፈለገው ልክ እየተከናወነ አይደለም፤
2. አገር በቀል የሥራ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች የካፒታልና መሣሪያዎች፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት (የማቀድ፣ የመተግበር፣ የመከታተል እና ኮንትራት የማስተዳደር)፣ የቴክኖሎጂ እና የፋይናንስ አቅም ውስንነት ስላለባቸው ለፕሮጀክቶች ጥራት መጓደል፣ መጓተት እና ከነአካቴውም ከስሮ ከዘርፉ የመውጣት ምክንያት ሆነዋል፤
3. ከዘርፉ የግብዓትና ቴክኖሎጅ ጥናትና ምርምር አኳያ በክልሉ በሁለት ከተሞች (ባሕር ዳር እና ኮምቦልቻ) የኮንስትራክሽን ግባዓቶች ጥራት ምርምር እና መፈተሻ ቢኖሩም ተቀዋማቱ ዘመኑ ባፈራው ቴክኖሎጅ እና ብቃት ባለው የሰው ሃይል እንዲጠናከሩ በማድረግ እና በሌሎች ከተሞችም ተጨማሪ ላብራቶሪዎችን የምርምር ማዕከላትን በማቋቋም በኩል ውስንነቶች በመኖራቸው በዘርፉ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፤
4. የአገር ውስጥ የፋብሪካ ምርቶች ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እድገት ጋር በተጣጣመ ደረጃ ባለማደጋቸው የተነሳ የግብዓት አቅርቦቱ በአብዛኛው ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ጥገኛ በመሆኑ ከውጭ ምንዛሪ እጥረቱ ጋር ተዳምሮ የኒፈጠር የግብዓቶች እጥረት እና መዘግየት ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም መጓተት አንዱ ምክንያት ሆኗል።

13. ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ተግዳሮቶች በአገር አቀፍ ደረጃም ሊገጥሙ የሚችሉ በመሆናቸው የክልሉ የዘርፍ አፈጻጸም ከአገር አቀፍ አፈጻጸም በተለየ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆን ከዚህ የዘለሉ መሠረታዊ ምክንያቶች ያሉት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚነሱ እና በክልልም ሆነ በአገር ደረጃ ዘርፉ ሚጋራቸው ተግዳሮቶች የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የግብዓቶች ዋጋ መናር፣ የግንባታ ሥራ ላይ ደህንነት እና የሬጉላቶሪ ደንቦችን አለመከተል፣ በርካታ ትንንሽ እና መካከለኛ የዘርፉ ተዋንያን መኖር ለማስተባበር እና ለማቀናጀት አስቸጋሪ መሆን፣ ዘርፉ ቴክኖሎጂ - ገብ አለመሆን፣ እና በታዳጊ አገራት ደረጃ ይፋዊ ያልሆነ (ኢንፎርማል) ተዋናይ መብዛት ተጠቃሽ ናቸው።
14. በኢንዱስትሪው ውስጥ መረጃ ተወስዶ ችግሮቹ የተነቀሱባቸው ንዑስ ዘርፎች ውስን መሆን በራሱ ከበርካታ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ንዑስ እና ንዑሰ - ንዑሳን ዘርፎች መካከል ለጥቂቶች በተለይም በአንጻራዊነት

ለሕንጻ ግንባታ ያጋደለ ትኩረት እንደተሰጠ እና በዚህም ምክንያት ከዘርፉ የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ፋይዳ ማስገኘት አዳጋች እንደነበረ ያመላክታል። ይህም ኢንዱስሰትሪውን በአካታችነት እና በወጥነት ባለቤት ሰጥቶ በትኩረት መምራት አስፈላጊ እንደሆነ ያመለክታል።

## 13.2. የትኩረት አቅጣጫዎች

### ኢኮኖሚ አቀፍ ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን የሚያረጋግጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

15. **የልማት ዕቅዱ ገዢ የትኩረት አቅጣጫ በሁሉም ዘርፍ በተለይም በአምራች ዘርፎች ምርታማነት እና ቅልጥፍናን ማሳደግ በመሆኑ ይህን የማረጋገጥ አንዱ እና ዋናው መንገድ በግንባታ ወቅት የወጪ እና የጊዜ ብክነትን መቀነስ እና የግንባታ ጥራትን ማረጋገጥ ነው።** የአብዛኛዎቹ የአምራች ዘርፎች መዋዕለ - ንዋይ ከ30 እስከ 40 በመቶ የሚደርስ ወጪ የኮንስትራክሽን ድርሻ የመሆኑ ዕውነታ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ የሚደረግ ቅልጥፍና የኢኮኖሚ አቀፍ ቅልጥፍናን ያሳልጣል። በተለይም በመሠረተ- ልማት ግንባታ በክልሉ ከፍተኛ መጓተት እና የዋጋ ክለሳ መኖሩ በአጠቃላይ ክልል አቀፍ የኢኮኖሚ ቅልጥፍና ማረጋገጥ የሚቻለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አቅም በማጎልነት ነው። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ምርታማነት እና ቅልጥፍና በመጨመር አስተዋጽዖ ማድረግ እንዲችል ዘርፉ
    i. ለዘማናዊ ግብርና
    ii. ለገጠር ትራንስፎርሜሽን
    iii. ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት
    iv. ለማዕድን ልማት
    v. ለቱሪዝም ልማት
    vi. ለመሠረተ-ልማት እና
    vii. ለዘላቂ ከተመት ከፍተኛ ሚና ሊጫዎት በሚችልበት አግባብ መቃኘት እና አቅምም በዚህ ልክ መገንባት ይኖርበታል።

16. በዘርፉ ቅልጥፍና መረጋገጥ ያለበት በሁሉም የኮንስትራክሽን ደረጃዎች ማለትም በዲዛይን እና በግንባታ ሂደቶች ሲሆን ሥልቶቹም ተገቢ እና ተስማሚ ግብአቶችን በመጠቀም፣ ጥራት ያለው የፋይናንስ ፐላን በማዘጋጀት፣ ምክንያታዊ የግዥ ሂደት በመተግበር፣ እንዲሁም ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት በማስፈን ነው። ለዚህም በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እና የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት ከዘልማዳዊ አሠራር የላቀ አግባብነት ያለው የኮንስትራክሽን ዘርፍ መዋቅር (organization) ያስፈልጋቸዋል።

### ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መፍጠር

17. ለፈጣን ልማት በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለሚገነባ አገር እና ክልል የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚና የላቀ ነው። ለተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ግንባታ ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ያስፈልጋል። የዚህ ግብ ሌላው ጠቃሚ ውጤት ከሚያድግ እና ለመወዳደር ከሚታትር ኢኮኖሚ ተጠቃሚ በመሆን እንደ አንድ አዋጭ የኢኮኖሚ ኢንዱስትሪ ሊያድግ የሚችል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መፈጠሩ ነው። የኮንስትራክሽን ዘርፍ ኢንዱስትሪ ዘርፉን ለኑሮ መሠረትነት የሚገለገሉ አነስተኛ ተዋንያን የተሞላ በመሆኑ እነዚህን ወደ ሥርዓት ማስገባት እንደተጠበቀ ሆኖ ዘርፉን ተወዳዳሪ ለማድረግ በየንዑስ ዘርፉ ተጠቃሽ አቅም ያላቸው አልሚዎችን መፍጠር፣ የግል እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ለእዚህ ዓላማ ማትጋት አስፈላጊ ነው።

18. የመጀመሪያው የአቅም ግንባታ ደረጃ የውጭ አገር ተቋራጮችን በመተካት የሕንጻዎቻችን እና ሌሎች አቅሞቻችንን በራስ አቫራ በመተካት ሀብትን መቆጠብ በዚህ ሂደትም የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ እንዲሆን ማድረግ ትልቅ ርምጃ ነው። ተወዳዳሪነት ዓለም አቀፋዊ በመሆኑ ሁለተኛው የተወዳዳሪ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ርምጃ  የጎረቤት አገራት፣ የቀጠናው እና ዓለም አቀፍ ገበያን በማሰብ ለዚህ የሚመጥን አደረጃጀት እና ቴክኒካል ብቃት ማረጋገጥ ነው። በዚህ ረገድ የአማራ ብሔራዊ ክልል  ለአገር በቀል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሠረት ለመጣል አንድ ወቅት ላይ የቆመ ግን ሕያው የረጅም ዘመን ተሞክሮ አለው።

### ተደራሽ እና ማሕበረሰብ - ተኮር የኮንስትራክሽን አቅም መፍጠር

19. የኮንስትራክሽን ዘርፍ መሠረታዊ ፍላጎት ከሚባሉት ለአብዛኛው የክልሉ ማሕበረሰብ በዘርፈ-ብዙ ልማት መስፈርት ወደ ኋላ መቅረት የገቢ አቅም ከፍተኛ ሆኖም ከቤት አሠራር እና አያያዝ የሚጀምር ያልዘመነ

የአኗኗር ዘይቤ ነው። ይህን ለማሻሻል የቤት ጥራትን በጣሪያ ቁርቁሮ ከሚለካው አስተሳሰብ በማላቀቅ ከእንስሳት መኖሪያ በራቁ፣ የማብሰያ እና የንጽህና መጠበቂያ ያካተቱ፣ ለሕጻናት እና ለልጆች የማጥኛ፣ የመዝናኛ እና የመጫዎቻ ጥጎችን ግምት ውስጥ ያስገቡ፣ የኃይል፣ የውሃ፣ የመንገድ፣ መሠረተ - ልማት የተዘረጋላቸው አካባቢውን ግብዓት በብዛት የሚጠቀሙ ቤቶች ያሏቸው አካባቢዎች ይፈጠራሉ። ከቤት ማሻሻል እስከ መሠረተ ልማት ግንባታ ባለው ሂደት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ይጫዎታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት በገጠር ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ሥር ከሚከናወኑ ንዑስ ፕሮግራሞች መካከል አንዱ **“ቤት ለልጅ፤ ጉረኖ ለእምቦሳ”** በሚል መርህ በገጠር እና ታዳጊ ከተሞች ያሉ የአርሶ አደር ቤቶች በተሻሻለ ዲዛይን፣ በአካባቢው በሚገኙ ግብዓቶች ደረጃቸውን ጠብቀው እና ለኑሮ አመች ሆነው እንዲገነቡ ማድረግ ነው። በዚህም አንድ ሚሊዮን ቤቶችን በማሻሻል እና በመገንባት በአሁኑ ወቅት ይኖራል ተብሎ ከሚታሰበው የአርሶ አደር ቤት አንድ አራተኛውን ለኑሮ ምቹ የማድረግ ግብ ተጥሏል። ለዚህ የሚመጥኑ የሰለጠኑ ወጣቶች የሚሳተፉባቸው ኢንተርፕራይዞች ወደ ኮንስትራክሽን ዘርፍ ይገባሉ፤ ለአገር በቀል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሠረት ይሆናሉ።

## መሠረታዊ እና ዲጂታል ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

20. ቴክኖሎጂ፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በተለይም የሕንጻ ግንባታ ንዑስ ዘርፍ ቴክኖሎጂ ብዙም ያልዘለቀው እና እስከ አሁንም የሰው ጉልበት በሰፊው የሚጠቀም ዘርፍ ነው። አንዱ ለቴክኖሎጂ-ገብነት አስቸጋሪ የሚያደርገው ጉዳይ የዘርፉ ባሕርይ በቁፋሮ፣ በሜካኒካል፣ ኤሌክትሪካል፣ በውሃ እና ፍሳሽ፣ በማጠናቀቂያ ሥራዎች የተከፋፈለ መሆኑ፣ እና የቴክኖሎጂ መሻሻሎች ከጥቅል ይልቅ በተናጠል መምጣት ስለሚኖርባቸው እንደሆነ ይታመናል። ነገር ግን ዓለም አቀፍ የጥናት ውጤቶች እንደሚያመለክቱት በቅርብ እየተፈጠሩ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የዘርፉን ምርታማነት ከ50 እስከ 60 በመቶ የማሳደግ ዕድል አለ። እነዚህም ቴክኖሎጂዎች፤
    2. 3ዲ/4ዲ ህትመት፣ ኦቶሜትድ አርክቴክቸር (Automated Architecture- AUAR)፣ ድሮን፣ ሰው ሠራሽ አትኩሮት መጠቀምን፣
    3. የተሻሻሉ የሕንጻ ኮንስትራክሽን ግብዓቶች (በራሳቸው የሚጠነክሩ- self-healing - ኮንክሪቶች፣ ልዕለ - ጠንካራ (ultra strong) ኮምፖሳይትስ፣ ሆሎው ብሎክስ፣ ጂፕሰም ቦርድ፣ ሬዲ-ሚክስ ኮንክሪት፣ ሞጁላር እና ቀድመው የተዘጋጁ መገጣጠሚያዎች መጠቀምን፣
    4. ዘላቂነት - ኃይል ቆጣቢ አረንጓዴ ግንባታ ማስፋፋትን ይጨምራል።

21. ከቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ የዲጂታል ቴክኖሎጂ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በሚከተሉት ንዑስ ዘርፎች ያግዛል፤
    5. ቢአይኤም (Building Information Modelling – BIM)
    6. ዲጂታል ሰነዳ (digital documentation)
    7. የሞባይል የሚጠቀም የመረጃ ልውውጥ (Mobile – first tool)
    8. የሂደት መከታተያ ኦቶሜሽን (process automation)
    9. የመረጃ ሶፍትዌር (data software)

## ጠንካራ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሥርዓት መገንባት

22. **ከዘርፉ ባሕርይ በመነጨ የክልሉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች በአብዛኛዎቹ የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ ዘርፎች የተበታተኑ በመሆኑ ለዘርፉ ልማት የመጀመሪያው ርመጃ አማክሎ የሚመራ ባለቤት ተቋም ማጠናከር ነው።** ተቋሙ የሚያተኩርባቸው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሥርዓት አካላት ዘረፉ የሚመራበት የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፍ፣ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት፣ የተቋማት ግንባታ እና መዋቅር (የፕላን፣ የምርምር፣ የሥልጠና ተቋማት)፣ ከአነስተኛ የኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዞች እስከ ትልልቅ ተጠቃሽ ተቋራጮች፣ በኮርፖሬሽን ደረጃ የሚጠራ የባለ - ብዙ ንዑስ ዘርፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ የምርምር፣ እና የስልጠና ተቋማት ናቸው።

23. **ክልል አቀፍ ዝርዝር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መረጃ ለዘርፉ ልማት ወሳኝ ነው።** ዘርፍ የዘርፉን መዋቅር፣ ተግዳሮት እና አቅም መርምሮ ተገቢ የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀመጥ የዘርፉ መረጃ በመሠረታዊነት አስፈላጊ ነው። ከመረጃ ጋር በተያያዘ ከአስተዳደራዊ መረጃዎች በተጨማሪ እና በላቀ፣ የክልሉ የፕላን እና ልማት ቢሮ

የስታትስቲክስ ክፍል የዳሰሳ መረጃዎችን በየዓመቱ እንዲይዝ ከዘርፉ በሚቀርብ ጥያቄ የተሻለ የመረጃ ሥርዓት እንዲሰፍን ይደረጋል።

24. **በኮንስትራክሽን ኢንዱስሪ ሥርዓት ዋና ተዋንያን በዘርፉ የሚሠማሩ ኢንተርፐራይዞች እና ድርጅቶች ናቸው።** ትልልቅ እና ተጠቃሽ የግል ድርጅቶች የኢንዱስትሪው መሪ ተዋናይ ናቸው። አነስተኛ የኮንስትራክሽን ኢንተርፐራይዞች በአጭር እና በመካከለኛ ጊዜ የሥራ ዕድለ መፍጠሪያ እና የተደራሽ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅሞች፣ በረጅም ጊዜ ደግሞ የአገር በቀል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሠረቶች ናቸው። በሽግግር ጊዜ የረጅም ዘመን የዘመናዊ ኢንዱስትሪ መሠረት መጣል ዓላማ ያለው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በአትኩሮተ- ዘርፍ (specialization) የሚሰማሩባቸው ንዑስ የኮንስትራክሽን ዘርፎችን ያቀፈ **የአማራ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን** መቋቋም ገንቢ ሚና ይኖረዋል።

25. **የሕንጻ ግንባታ እና ኮንስትራክሽን ምርምር ተቋም** ሳይንሳዊ ምርምርን በማስፋፋት ረገድ በሥሩ በአሁኑ ጊዜ የግብዓት ጥራት ምርመራ የሚያደርጉትን ሁለት ተቋማት ቁጥር እና ተግባር በማስፋት የአፈር ምርመራን፣ የጥራት ማረጋገጫን፣ አማራጭ የግንባታ ቴክኖሎጂን፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች አቅርቦትን፣ የተሻሉ የግንባታ ቴክኒኮችን፣ የግንባታ እና ሲቪል ኢንጂነሪንግ የሚገዙ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ ምክረ ሃሳቦች ማፍለቅን፣ ቴክኒካዊ ዕውቀቶችን ማሰራጨት፣ የዘረፉን ምርምር በቪዲዮ፣ በተጻፉ ሚዲያዎች፣ በአጫጭር እና ድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ማሰራጨትን የሚያጠቃልሉ ሚናዎችን እንዲወጣ ማድረግ ይጠበቃል።

26. **የጥናት ጣቢያዎች (research stations)** ዓላማው በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ጀማሪዎች እና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች በቅርብ ቴክኒካል ድጋፍ የመስጠት፣ የአነስተኛ ዋጋ ግብዓት ዲዛይን የመሥራት እና አጠቃቀምን የማስረጽ፣ ደረጃዎች/መስፈርቶች የማውጣት፣ ለአካባቢው የሚመጥን የፕላን እና ቅየሳ ሥራ ከሚመለከተው ሕጋዊ ተቋም ጋር በመተባበር የመተግበር፣ የማሕበራዊ እና ኢኮኖሚክ መሠረተ ልማት ዝርጋታን የማቀድ ሚና ይኖራቸዋል።

27. **የስልጠና ተቋማት እና የሥልጠና ማዕከላት** ከኮሌጅ፣ ከቴክኒክ ትምሕርት ቤቶች፣ እና ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ እና ዝንባሌው ያላቸውን ወጣቶች በመምረጥ የማሰልጠን፣ ለልምምድ በየዘርፉ የመመደብ፣ ከውጭ ከሚመጡ ባለሙያዎች የቴክኒክ ዕውቀት እና ክህሎት የማሸጋገር ሚና ይኖራቸዋል።

## 13.3. የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማት ዓላማ እና ግቦች

28. **የኮንስትራክሽን ዘርፍ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ ለጠንካራ ኢኮኖሚ ግንባታ የሚመጥን ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሠረት መጣል ነው።** ይህም የዘርፉን ሚና እና እምቅ አቅም በቅጡ በመለየት፣ ይህንንም አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ አደረጃጀት በመፍጠር፣ የአገር በቀል የዘርፉ ኢንዳስትሪያሊስቶችን በመደገፍ እና በማፍራት፣ ቴክኖሎጂን የዘርፉ መወዳደሪያ ፈርጅ በማድረግ የሚገለጽ ይሆናል።

29. **በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የሚተገበሩ ዋና ዋና ግቦች የሚኖሩ ሲሆን በጥቅል የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በዓመት በአማካይ በ20.4 በመቶ እንዲያድግ ግብ ተጥሏል።** ከዚህ ውስጥ የ4 የመቶኛ ነጥብ (percentage point) ዕድገት ምጣኔ በአለፉት አራት ዓመታት የክልሉ የዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት የቀነሰበትን የ3.9 በመቶ ዕድገት ማገገሚያ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል። በዚህም መሠረት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከክልል አቀፍ ምርት ያለው ድርሻ በ2016 ከነበረበት 6.0 በመቶ በ2022 ወደ 10.1 በመቶ ከፍ እንዲል ታቅዷል።

30. **የ20.4 በመቶ የዘርፉን ተጨማሪ ዕሴት ዓመታዊ ዕድገት ለማሳካት በሁሉም ንዑስ ዘርፎች እና ከሁሉም ተዋናዮች የሚጠበቀው አጠቃላይ የአምሥት ዓመት የመዋዕለ - ንዋይ መጠን ግምት በወቅቱ የመግዥያ ዋጋ 575.5 ቢሊዮን ብር ነው።** ይህም ማለት በአማካይ በዘርፉ በዓመት የ115.1 ቢሊዮን ብር መዋዕለ-ንዋይ ይጠበቃል። ይህ መጠን በራስ አቅም ቤት የሚገነቡ አርሶ አደሮች እና የከተማ ነዋሪዎች የገንዘብ እና የጉልበት ግምት፣ የማሕበረሰብ የነጻ ጉልበት የመንገድ እና የአካባቢ ጥበቃ ግንባታዎች የጉልበት ግምትን ሁሉ ያጠቃልላል። የዘርፉ መዋዕለ - ንዋይ የሚፈስስባቸው ንዑስ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፤

    1. በራስ አቅም የሚሠሩ የገጠር ቤቶች

2. የገጠር ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም
3. የከተማ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ
4. የኮሜርሻል ሕንጻዎች ግንባታ
5. የተቋማት ሕንጻዎች ግንባታ
6. የመሠረተ - ልማት ግንባታ
    i. መስኖ
    ii. መንገድ እና ድልዲዮች
    iii. የማሕበራዊ መሠረተ - ልማት
        1. ትምህርት ቤቶች
        2. የጤና ተቋማት
    iv. የቱሪዝም ልማት ግንባታዎች
7. የኢንዱስትሪ ኮንስትራክሽን
    v. ውሃ
    vi. ኤነርጂ
    vii. ማዕድን እና ኳሪንግ
    viii. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የፋብሪካዎች ግንባታ
8. የቱሪዝም ልማት ግንባታዎች
9. ሌሎች የኮንስትራክሽን ሥራዎች

## 13.4. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

31. **የዘርፎች ትስስር፤** የኮንስትራክሽን ዘርፍ በአብዛኛዎቹ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ዘርፎች የግንባታ መሠረት የመሆኑን ያህል ከሌሎች ዘርፎች የሚፈልገው ግብዓት ትልቅ ነው። በመካከለኛ ጊዜ አብዛኛው የኮንስትራክሽን በተለይም የህንጻ ግንባታ ማጠናቀቂያ ግብዓቶች የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶች ሲሆኑ 70 በመቶ ያህሉ ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡ ናቸው። በረጅም ጊዜ ከተሽከርካሪ እስከ ከፍተኛ ማሽኖች የሚደርሱ መሣሪያዎች የከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶች ናቸው። ኢንዱስትሪው ከማዕድን ዘርፍ ግብዓት ይስዳል። በመሆኑም የዘርፉ ልማት ሲታሰብ የዘርፎች በግብዓትነት እና በተጠቃሚነት ተሳስረው መታቀድ ይኖርባቸዋል። በገበያ መርህ እሳቤ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሲነቃቃ እና በአካባቢው ለሚገኙ የግንባታ ግብዓቶች እንዲሁም ከውጭ ለሚገቡ አላቂ እና ቋሚ ግብዓቶች ፍላጎት በመፍጠር ለእነዚህ ምርቶች መመረት ምልክት እንደሚሰጥ ይታመናል። በእኛ አገር ሁኔታ ዘርፎች ሲሣያቸውን አይተው ከመንቃት ይልቅ ከውጭ ማስመጣት ይቀላቸዋል። ለዚህም የሲሚንቶ፣ የብረት፣ መስተዋት፣ ሴራሚክስ፣ የወለል ንጣፎች፣ የተዘጋጁ እምነ በረድ፣ ግራናይት የመሳሰሉ ለኮንስትራክሽን የሚውሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያው እስኪፈጥራቸው ከመጠበቅ በዕቅድ አመላክቶ መመረታቸውን በፖሊሲ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

32. **ትብብር፤** ለዘርፉ መዘመን የመንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የምርምር እና የትምህርት ተቋማት፣ የውጭ አጋሮች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትብብር ወሳኝ ሚና ይጫዎታል።

33. **የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፍ፤** በሥራ ላይ ያሉ የዘርፉ ሕጎችን በመፈተሽ አስቻይ የማድረግ ሥራ ይሠራል።
34. **ክትትል እና ግምገማ፤** በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለሚታዩ ከልክ ያለፈ መዘግየት እና የወጪ መናር፣ እንዲሁም የጥራት መጓደል መፍትሄው ችግርን በወቅቱ መፍታትን ግብ ያደረገ ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ማስፈን ነው።

# ምዕራፍ አሥራ አራት
# ቱሪዝም

## 14.1. የትኩረት መነሻ

### የቱሪዝም ፋይዳ

1. የሰው ልጅ ዋና የሕይወት ተሞክሮ እና የውሳኔ ልምምድ የሥራ እና የእረፍት ጊዜን በማመጣጠን ተድላ እና ደስታ የሞላበት ጤናማ ሕይወት መምራት ነው። በምግብ እና መጠጥ፣ በጨዋታ፣ በአብሮነት፣ በትርዒት፣ እና በትዕይንት ከሚገኙ የሀሴተ ነፍስ ምንጮች አብዛኛዎቹ ጉዞን (travelling) የሚያካትቱ ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልጋቸውም ናቸው። በተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት ትርጉም መሠረት ሰዎች በቋሚነት ከሚሠሩበት ወይም ከሚኖሩበት አካባቢ ውጪ በተከታታይ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በመጓዝ የሚፈጸሟቸው የመዝናናት፣ የቢዝነስ፣ የሙያ እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች በቱሪዝም ሥርዓት ይካተታሉ። የቱሪዝም ቁልፍ ባሕርይ ዜጋ ከቦታ ቦታ ተጉዞ ደስታ እና ጤና እንደ መጨረሻ ግብ የሚያገኙባቸው የሀሴት ምንጮች የሆኑ የቱሪዝም መስሕቦቸች ታይተው ገቢ የሚያመጡ፣ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ፣ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ፣ አዳዲስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉ ምክንያት የሚሆኑ፣ ከሌላው ዓለም ጋር መልካም ትውውቅን በመፍጠር ለማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ካፒታል መዳበር የሚያግዙ መሆናቸው ነው።

2. ቱሪስቶች አንድን መዳረሻ በተለይ የሚመርጡባቸው ሦስት ቀዳሚ ምክንያቶች እረፍትን ለማሳለፍ እና ለመዝናናት (vacation and leisure)፣ ጓደኛ እና ዘመድ ለመጠየቅ (visit to friends and relatives)፣ እና በንግድ ወይም በሥራ ወይም ሙያን መሠረት ያደረገ ጉዞ (business or profeesional travel) ናቸው። ዓለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ጓደኛ እና ዘመድ ለመጠየቅ የሚጓዙ ቱሪስቶች 40 በመቶ፣ ለእረፍት እና መዝናናት ዓላማ መዳረሻዎችን የሚመርጡ ቱሪስቶች 37 በመቶ፣ ለንግድ፣ ለሥራ እና ሙያዊ ጉዞ ዓላማ የሚገዙ ጎብኝዎች 20 በመቶ፣ እና በሌሎች ምክንያቶች የሚጓዙ 3 በመቶ ድርሻ አላቸው።

3. **ስዕል 14-1፤** ዓለም አቀፍ የቱሪስቶች የጉዞ ምክንያቶች




ምንጭ፤ Tourism: The Business of Hospitality and Travel, Cook, et al; Sixth Edition, 2018.

4. የቱሪዝም አንዱ ባህርይ ተጓዦች ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ጉዞ የሚያደርጉ ቢሆንም እነዚህ ዋና የጉዞ ምክንያቶች ለሌሎች የቱሪዝም ተግባራት (tourism activities) ፍላጎትን ይፈጥራሉ። የቱሪዝም ልማት ስትራቴጂ ሊያተኩርበት የሚገባው አንዱ ጉዳይም እንደ ጉባዔ የመሳሰሉ አጭር የቆይታ ጊዜ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች የሚጓዙ ቱሪስቶችን የቆይት ጊዜ ማራዘም የሚያስችሉ፣ እንዲሁም ለዘመድ እና ጓደኛ ለማየት ከሚጓዙ ቱሪስቶች የተሻለ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ምስህቦችን እና የቱሪዝም ምርቶችን መፍጠር ነው።

5. ዓለም አቀፍ ቱሪዝም ገቢ ቱሪዝም (inbound tourism) እና ወጪ ቱሪዝም (outbound tourism) አለው። ከገቢ ቱሪዝም ኢኮኖሚያዊ ገቢ እና የውጭ ምንዛሪ እንደሚገኝ ሁሉ በወጪ ቱሪዝም ምክንያት ዜጎች ለአገር

ኢኮኖሚ ሊጠቅም ይችል የነበረ ፍላጎትን ከአገር ያስወጣሉ፣ የውጭ ምንዛሪ ክምችትንም በመቀነስ የንግድ ሚዛን እንዲዛባ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ በ2015 ከገቢ ቱሪዝም የተገኘ ገቢ 1.53 ትሪሊየን የአሜሪካ ዶላር የነበረ ሲሆን ከዚህ ገቢ የተጣራ ተጠቃሚነት የሚወሰነው በወጪ ቱሪዝም አማካኝነት ዜጎች በውጭ አገራት የከፈሉት መጠን ግምት ውስጥ ከገባ በኋላ ነው። የአገር ውስጥ ቱሪዝም (domestic tourism) የሚበረታታበት አንዱ ምክንያትም ወጪ ቱሪዝምን በመቀነስ አገራዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ነው። በዚህ መሠረት የቱሪዝም ማኔጅመንት ዋና ትኩረት የአገር ውስጥ ቱሪዝምን፣ ወጪ ቱሪዝምን እና ገቢ ቱሪዝምን ከሚያካትተው ብሔራዊ ቱሪዝም (national tourism) ውስጥ የገቢ ቱሪዝም እና የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ወይም በጥቅሉ የውስጥ ቱሪዝምን (internal tourism) በተቻለ መጠን ማሳደግ ነው።

6. መልካም የራስ እሴትን ማሳወቅ እና ጠቃሚ የሌሎች አገራት ባህልን መማር በቱሪዝም የሚገኙ ፋይዳዎች ናቸው። መልካም የራስ እሴቶችን ለጎብኝዎች ማስተዋወቅ ለዘርፉ መስፋፋት ከሚያበረክተው አስተዋጾዖ በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ የማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ካፒታልን ያሳድጋል። በተለይ ከወጪ ቱሪዝም ዜጎች የሌሎችን አገራት የቴክኖሎጂ ጥበብ፣ መልካም የሥራ ባህል፣ እና የጊዜ አጠቃቀም በመማር ቱሪዝምን ለአገር ልማት ያለውን ፋይዳ ማስፋት ይቻላል። የዚህ ዓይነቱ ቱሪዝም ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሲባል ከሚደረግ ገንቢ የገቢ ንግድ ጋር ይስተካከላል። በአንጻሩ ጠቃሚ ያልሆኑ ምናልባትም አጠፊ እና በራዥ ባህሎች በቱሪዝም ሰበብ ሊሸጋገሩ ይችላሉ። የአገር ውስጥ የቱሪዝም ሀብቶችን በማነጽ ውድድር ከበዛበት የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ሥርዓት ስጥ መላካም ልምዶችን በመቀመር የተሻለ ተጠቃሚ የመሆን ግብን ለማሳካት ዓላማ ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት ትኩረት ይሰጣል።

## ዓለም አቀፋዊ የቱሪዝም ባሕርያት እና አቅጣጫ

7. ቱሪዝም በዓለም ላይ እያደገ ያለ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ መስተጋብር ሥርዓት ነው። የጎብኝዎች ብዛት በመዳረሻ በ1942 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር) 25 ሚሊዮን ብቻ የነበረ ሲሆን በ2015 ወደ 1.3 ቢሊዮን ተጓዥ ወይም በሰባት አስርት ዓመታት ውስጥ በ52 እጥፍ አድጓል። የቅርብ ጊዜ ለውጡ ሲታይ የተጓዥ ብዛት በ2002 ከነበረበት 972.8 ሚሊዮን ተጓዥ በ2015 ወደ 1.3 ቢሊየን ሰው፣ ወይም በ13 ዓመታት ውስጥ በ34.2በመቶ ጨምሯል። በተመሳሳይ ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ በ2002 ከነበረበት 989.1 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር በ2015 ወደ 1.53 ትሪሊየን ዶላር ወይም በ55.3 በመቶ ከፍ ብሏል።

8. የቱሪዝም መነሻ እና መዳረሻ በአብዛኛው ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የሚቆራኝ ነው። ወደ አሜሪካ የተጓዙ የአውሮፓ ቱሪስቶች ቁጥር እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1901 እስከ 1910 ድረስ 91.6 ከመቶ የነበረ ሲሆን ከ1999 እስከ 2010 በነበሩት ዓመታት ይህ ድርሻ ወደ 13.2 በመቶ አሽቆልቁሏል። በአንጻሩ በተመሳሳይ ጊዜ ወደ አሜሪካ የተጓዙ የኤሲያ ቱሪስቶች ከ3.7 በመቶ ወደ 34.8 በመቶ አድጓል። የአሜሪካ የቱሪስቶች ከፍተኛ መዳረሻ እየሆነች መምጣትም ምክንያቱ ኢኮኖሚዋ እያደገ እና የዓለም ኢኮኖሚ መሪነቱን እየያዘ መሄዱ ነው። በ2015 አሜሪካ ከዓለም የቱሪስት ቁጥር 5 በመቶ፣ የቱሪዝም ገቢ 12 በመቶ በመሸፈን በጎብኚ ቱሪስት ብዛት 3ኛ፣ በቱሪዝም ገቢ ደግም 1ኛ ነበረች። በተመሳሳይ ጊዜ በቱሪስት ብዛት በ8 በመቶ ድርሻ 2ኛ፣ በቱሪዝም ገቢ በ5 በመቶ ድርሻ 3ኛ የነበረች አገር ፈረንሳይ ናት። በአንጻሩ የአፍሪካ እና የላቲን አሜሪካ የቱሪዝም ድርሻ በገቢ ቱሪስቶች ብዛትም ሆነ በቱሪዝም ገቢ ብዙም ለውጥ ሳያሳይ ቆይቷል።

9. የቻይና ኢኮኖሚ በፍጥነት እያደገ መምጣት ከቻይና የሕዝብ ብዛት ጋር ተዳምሮ ቻይናን የቱሪዝም ምንጭ እያደረጋት መጥቷል። በአጸፋው የቻይና የገቢ ቱሪዝም እስከ ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ድረስ ሲድግ የነበረ ሲሆን ከኮቪድ 19 በኋላ በታየው መቀዛቀዝ የኤሲያ እና የፓስፊክ የቱሪዝም ገቢ ድርሻ በ2002 ከነበረበት 26 በመቶ በ2015 ወደ 22 በመቶ እንዲቀንስ አስተዋጽዖ አድርጓል።

10. ስዕል 14 -2ሀ፤ የቱሪስት ብዛት፣ የቱሪዝም ገቢ፣ እና የቱሪዝም ኤክስፖርት በ2015




ምንጭ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት (UN Tourism)

11. ስዕል 14 -2ለ፤ የቱሪስት ብዛት፣ የቱሪዝም ገቢ፣ እና የቱሪዝም ኤክስፖርት በ2010




ምንጭ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት (UN Tourism)

12. ቱሪዝም በጠንካራ እና በጥሩ የኢኮኖሚ መዋቅር ላይ ሲመሠረት የተሻለ ጥቅም ያስገኛል። በታዳጊ አገራት ቱሪዝም የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ፣ የሥራ ዕድል ለማስፋት፣ እና አገልግሎት ተኮር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ለማስፋፋት የሚያግዘውን ያህል ዓለም አቀፍ ጦርነት ወይም ግጭት፣ ቱሪስቶችን ያሳተፈ ወይም ዒላማ ያደረገ ሽብር፣ ቱሪስቶችን ዒላማ ያደረገ ዓለም አቀፍ የእገታ ወንጀል፣ የቱሪስት መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት የሚያወድም ተፈጥሮዓዊ ክስተት፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ በሚከሰትበት ጊዜ የመጀመሪያ ተጠቂ ዘርፍ በመሆኑ ለድህነት በፍጥነት መንገስ የተጋለጠ ነው። ከዚህ አንጻር በ2012 በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርኝ ወቅት የዓለም የቱሪስት ቅጥር በ72.3 በመቶ፣ የቱሪዝም ገቢ ደግሞ በ62.3 በመቶ የቀነሰ ሲሆን እስከ 2015 ድረስ የቱሪስት ብዛት እና የቱሪዝም ገቢ በቅድመ ኮቪድ 19 ወቅት በተለይም በ2011 የነበረውን አኀዝ ተቃረበ እንጂ አልደረሰበትም።

13. ስዕል 14-3፤ የዓለም ቱሪስት ብዛት በመዳረሻ (በሚሊዮን) እና የቱሪዝም ገቢ (በቢሊዮን ዶላር)




ምንጭ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት (UN Tourism)

14. በአገር ደረጃ በ2005 ዩክሬይን የ24.67 ሚሊዮን ቱሪስቶች መዳረሻ በመሆን 5.1 ቢሊዮን ዶላር ያገኘች ሲሆን በቀጣዩ ዓመት የክሬሚያ ግጭትን ተከትሎ የቱሪስት ቁጥር ወደ 12.7 ሚሊዮን፣ የቱሪዝም ገቢ ደግሞ ወደ 1.6 ቢሊዮን አሽቆልቁሏል። ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ክስተትእ በኋላ ቱሪዝም በብዙ አገራት እያስንሰራራ ቢሆንም በሩሲያ እና በዩክሬይን ጦርነት ምክንያት በ2014 ወደ ዩክሬይን የተጓዙ ቱሪስቶች ቁጥር ወደ 2.7 ሚሊዮን፣ ከቱሪዝም የሚገኝ ገቢ ደግሞ ወደ 800 ሚሊዮን ዶላር የበለጠ ቀንሷል። በተመሳሳይ በ2007 ከ33.73 ሚሊዮን ቱሪስቶች 8.4 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ታገኝ የነበረችው ሩሲያ በኮቪድ 19 ወቅት ወደ 6.36 ሚሊዮን ከወረደው የጎብኝ ብዛት የተገኘው 3.9 ቢሊዮን ዶላር የቱሪዝም ገቢ በ205ም ከ6.7 ቢሊዮን ዶላር በላይ ማለፍ አልቻለም። የኮቪድ 19 መነሻ በመሆን ውዝግብ ውስጥ የገባቸው ቻይና በ2002 የዓለምን የቱሪስት ገቢ 5 በመቶውን በመሸፈን ከዓለም 4ኛ የነበረች ሲሆን ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኋላ ዘርፉ ማገገም ባለመቻሉ በ2015 የዓለምን የቱሪስት ገቢ 2 በመቶ በመሸፈን ከ10ኛ ደረጃ በታች ሆናለች።

15. በሉላዊነት (globalization) ዘመን ቱሪዝም እንደ የአገሩ ፍልስፍና ለባሕል ዕድገት ፋይዳም የባሕል ወረራ ስጋትም ደቅኗል። በቱሪዝም የሰዎችን እንቅስቃሴ ተከትሎ የራስን በጎ ባሕል እና መልካም እሴቶች በማስተዋወቅ ከሚገኝ ዓለም አቀፍአዊ ጥቅም ትይዩዩ የባሕል እና እሴት ግጭቶችም ይስተዋላሉ። የምሥራቅ እና የምዕራብ የፖለቲካ እና የወታደራዊ ፍጥጫ ከኢኮኖሚ ፉክክር ባልተናነሰ ምናልባትም በበለጠ የእሴቶች ፉክክር ነው። በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፉክክር ውስጥ ትብብር የመኖሩን ያህል በባሕል እና እሴቶች በዘላቂነት የሚቻለው ስትራቴጂ መከባበር ነው።

16. ከእነዚህ ክስተቶች በመነሳት የወደፊት ዓለም አቀፍ ቱሪዝም የሚከተላቸው አቅጣጫዎች ተተንብየዋል፤
   1. በዓለም ላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መስፋት፣ የነፍስ ወከፍ ገቢ መጨመር፣ ይህንንም ተከትሎ የመዝናናት ፍላጎት ማደግ፣ እንዲሁም የመሠረተ ልማት መስፋፋት እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ በፍጥነት ማደግ የአገር ውስጥንም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ቱሪዝምን ከምንጊዜውም በላይ ይጨምረዋል፤
   2. የቱሪዝም እንቅስቃሴ መጨመር ዓለም አቀፍ እና የአገር ውስጥ ቱሪስት ፍላጎቶችን መሠረት ያደረጉ አዳዲስ የመዝናኛ እና የአገልግሎት ኢንዱስትሪዎች በአገራት ይስፋፋሉ፤
   3. እንደ ቻይና እና ሕንድ የመሳሰሉ የሕዝብ ብዛታቸው በኢኮኖሚ አቅም እየዳበረ እንደሚመጣ የሚጠበቁ አገራት የቱሪዝም ምንጮች ይሆናሉ፤
   4. የዓለም ሥነ ሕዝብ ለውጥ በቱሪዝም ላይ ለውጥ የሚያስከትል ሲሆን በተለይ የወደፊቱ የቱሪዝም ምንጭ የዕድሜ ባለፀጋዎች ይሆናሉ፤
   5. ቴክኖሎጂ መረጃን ቀላል በማድረግ ቱሪዝምን የሚያበረታታ ሲሆን እንደ ኮንፈረንስ ቱሪዝም ዓይነቶቹ ምድቦች ላይ እንቅስቃሴን ሊገድብ ይችላል።

17. የዓለም የወደፊት የቱሪዝም ገበያ ከሞላ ጎደል በሚከተሉት ምድቦች ላይ ያተኩራል፤
    1. የምቾት ቱሪዝም (slow tourism)፤
    2. የዝና ቱሪዝም (adventure tourism)፤
    3. የሕክምና ቱሪዝም (medical tourism)
    4. የሁለተኛ ቤት ቱሪዝም (Vocation and real estate tourism)
    5. የሕዋ ቱሪዝም (space tourism)፤
    6. የሀሽሽ ቱሪዝም (marijuana tourism)

18. ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች በወደፊት የቱሪዝም ሥርዓት ላይ ገዥ መርሆዎች ይሆናሉ፤
    1. ከተፈጥሮ ጋር የታረቀ እና የተስማማ ቱሪዝም
    2. የቀውስ ወቅት ቱሪዝም ዝግጁነት

## የኢትዮጵያ እና የአማራ ብሔራዊ ክልል የቱሪዝም አፈጻጸም

19. በኢትዮጵያ የቱሪስት ብዛት ከ2002 እስከ 2009 ባሉት ዓመታት ከ470 ሺህ ወደ 930 ሺህ በፍጥነት ያደገ ሲሆን ከቱሪዝም የሚገኘው ገቢ በ2003 ከተመዘገበው 800 ሚሊዮን ዶላር በ2009 ወደ 400 ሚሊዮን ዶላር ቀንሶ ታይቷል። በ2012 የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት እንደማንኛውም አገር የቱሪስት ፍሰት እስከ 270 ሺህ የወረደ ቢሆንም ከቱሪዝም የሚገኘው ገቢ በአንጻሩ ከሌላው ዓለም በተለየ ሁኔታ ጨምሮ ነበር። የዚህም ምክንያቱ የአገልግሎት ዋጋ መጨመር፣ እና የቱሪስቶች ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት ሊሆን ይችላል። በድህረ ወረርሽኝ ወቅት ከኤሲያ አገራት በተለየ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያን የጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር በ2015 ወደ 1.08 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም በቅድመ ወረርሽኝ ወቅት በ2011 ከነበረበት የ810 ሺህ ጎብኝ ብዛት የላቀ ነው።

20. ስዕል 14-4፤ የቱሪስት ብዛት እና የቱሪዝም ገቢ በኢትዮጵያ (2002 – 2015)




ምንጭ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት (UN Tourism)

21. በ2016 በአማራ ብሔራዊ ክልል መሠረተ ልማት የተሟላላቸው የቱሪስት መዳረሻዎች ብዛት 10 ነው። በአብዛኛው እነዚህ መዳረሻዎች መሳብ የቻሉት የውጭ አገር ቱሪስት 16,242 ሲሆን የአገር ውስጥ ቱሪስት ብዛት ደግሞ 5,725,856 ነበር። በአጠቃላይ ከዘርፉ በክልሉ የተገኘው ገቢ 2.44 ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከውጪ አገር ቱሪስቶች የተገኘው ገቢ 19 ሚሊዮን ዶላር ወይም 1 ቢሊዮን ብር እንደሆነ ይገመታል። በተለይ የክልሉ የውጭ አገር ቱሪስት ፍሰት ወደ ኢትዮጵያ ከገባው 1.44 ሚሊዮን የቱሪስት ፍሰት 1.4 በመቶ ብቻ መሆኑ ክልሉ እንደ ሀብት መሠረቱ ከዘርፉ የሚገባውን ያህል እየተጠቀመ እንዳልሆነ ማሳያ ነው።

22. የቱሪስት ቁጥር እና ከቱሪዝም የሚገኝ ገቢ በመጨመር ላይ ቢሆንም ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት የመልማት አቅም እና ከዓለም አቀፍ የዘርፉ ዕድገት አንጻር አፈጻጸሙ አበረታች አይደለም። በ2002 ከዓለም ቱሪስቶች ውስጥ ኢትዮጵያን መዳረሻ ያደረጉ ጎብኝዎች 0.05 በመቶ ያህሉ ብቻ የነበሩ ሲሆን ከ13 ዓመት በኋላ በ2015 የኢትዮጵያ ድርሻ 0.08 በመቶ ብቻ ነው። ይህ አኀዝ ከዓለም ጎብኝዎች ውስጥ 1 በመቶ የሚሆኑት ከሚጎበኟት ግብጽ ጋር ሲወዳደር የግብጽ በ13 እጥፍ ይልቃል። የቱሪዝም ገቢ ደረጃ የቱሪስት ቁጥር ደረጃ ነጸብራቅ በመሆኑ በ2015 1.3 ትሪሊየን ዶላር ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገቢ ውስጥ ኢትዮጵያ የነበራት ድርሻ 0.07 በመቶ ብቻ ነበር።

23. **ስዕል 14-5፤** የኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ጎብኝዎች እና የቱሪዝም ገቢ ድርሻ (2002 - 20015)




ምንጭ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት (UN Tourism)

24. የመዳረሻ አገራት የአገልግሎቶች ዋጋ መለያየት እንደተጠበቀ ሆኖ የጎብኝዎች የቆይታ ጊዜ ከአንድ ጎብኚ የሚገኘውን ገቢ ይወስናል። ኢትዮጵያ ላለፉት 13 ዓመታት ከአንድ ጎብኚ ያገኘችው ገቢ በአማካይ 1,170 ዶላር ሲሆን ይህም ከ1,113 ዶላር ዓለም አቀፍ አማካይ ገቢ ጋር ተቀራራቢ ነው። በ2015 በዓለም ላይ በነፍስ ወከፍ ጎብኚ ከፍተኛ ገቢ ከሚያገኙ አገራት አውስትራሊያ ($6,418)፣ ሊባኖስ ($3,246)፣ አሜሪካ ($2,845)፣ ሲሸልስ ($2,819)፣ እና ካናዳ ($2,477$) ቀዳሚዎቹ ናቸው።

25. **ስዕል 14-6፤** የቱሪዝም ገቢ በጎብኚ፤ የኢትዮጵያ እና የዓለም ንጽጽር (የአሜሪካ ዶላር)




ምንጭ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት (UN Tourism)

26. በአማራ ብሔራዊ ክልል የቱሪዝም ሀብት ልማት ዋና ዋና ችግሮች ሲጠቃለሉ በቅርቡ ግንባታቸው የተጠናቀቀ እና የተጀመሩ አዳዲስ የቱሪስት መስህቦች ለቱሪዝም ልማት ተስፋ ሰጪ ቢሆኑም የኢትዮጵያ እና የአማራ ክልል ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያሳየው የዓለምን የቱሪዝም ሥርዓት አቅጣጫ ግምት ውስጥ ያስገባ የቱሪዝም ልማት ዝግጁነት አልነበረም፤ የዓለም አቀፍ የቱሪዝም ፍላጎት ስፋት እና ዕድገት በሚጠይቀው ልክ የቱሪዝም ምርቶች እና አገልግሎቶች አልለሙም። በተለይም

1. ሰፊ የቱሪዝም ሀብት አቅም በክልሉ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ መሆናቸው ቢታወቅም ቀድመው ከተገነቡ እና በተፈጥሮ ከሚገኙ መስህቦች ባለፈ የክልሉን እና የአገሪቷን የቱሪዝም አቅም በሚመጥን ደረጃ ገና አልታነጹም፣
2. በክለሉ ነባር መስህቦችን በአሉበት ምናልባትም በተጎዱበት ደረጃ ከመጠቀም ውጪ የማደስ፣ እንዲሁም መስህቦችን በዘማናዊ መሠረተ ልማት ተደራሽ የማድረግ ጥረቶች ውስን ናቸው፤ በቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ በሆኑ አገራት በጥንታዊ የቱሪስት መስህቦቻቸው አማካኝነት የሚመጡ ጎብኝዎችን ቆይታ እና እርካታ ለመጨመር የሚያስችሉ በመስህቦቹ ዙሪያ የሚፈጥሯቸው የአዲሱ ትውልድ ሳቢ ትዕይንቶች እና የቱሪዝም ምርቶች በኢትዮጵያ በአጠቃላይ በአማራ ብሔራዊ ክልል በተለይ የተለመዱ አይደሉም፣
3. የቱሪዝም ልማትን ለአጭር ጊዜ የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ግቦች ከሚኖረው ፋይዳ በዘለለ የፖሊሲ አቋም የሚያስፈልገው እና ከጠንካራ የኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ለውጥ ጋር ያለው መስተጋብር በቅጡ አልተጤነም፣ እንዲሁም
4. የረጅም ዘመን የቱሪዝም ልማት አስተዳደር የመጣለትን ጎብኚ ከማስተናገድ አልፎ የዓለም የቱሪስት ፍላጎትን በሳይንሳዊ ሥነ ገበያ ተንትኖ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት ውስን ነው።

## 14-2. የቱሪዝም ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች

27. የክልሉን የቱሪዝም ሀብት አቅም፣ የዓለም አቀፍ የቱሪዝም ሥርዓት ባሕርያት፣ እና የወደፊት ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልል የቱሪዝም ልማት ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች

1. ክልላዊ የቱሪዝም ሀብት አቅሞችን ከአገራዊ እና ክልላዊ እሴቶች ጋር በማጣጣም ማነጽ፣
2. የተበታተኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በአዳዲስ ተጨማሪ መስህቦች፣ በመሠረተ ልማት እና የቱሪዝም ምርቶች አማካኝነት ወደ ቱሪዝም መስመሮች፣ ቀጠናዎች እና ጥብቅ ሥፍራዎች ማሳደግ፣
3. የቱሪዝም ልማትን ጽዱ እና ምቹ የመኖሪያ እና የሥራ አካባቢን ለዜጎች ከመፍጠር እና የዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በማቀናጀት ፍትሃዊ ቱሪዝምን ማረጋገጥ፣
4. ወጪ ቱሪዝምን የሚተካ እና ክልላዊ ምርታማነትን የሚያግዝ በጠንካራ ኢኮኖሚ መሠረት ላይ የቆመ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ቱሪዝም ማራመድ፣
5. ለሰፊ የዓለም የቱሪዝም ፍላጎት ትርጉም ያለው አቅርቦትን በሳይንሳዊ የገበያ ጥናት መርህ በማመቻቸት ከዓለም ቱሪዝም ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን ናቸው።

28. **ክልላዊ የቱሪዝም ሀብት አቅሞችን ከአገራዊ እና ክልላዊ እሴቶች ጋር በማጣጣም ማነጽ፣** የአማራ ብሔራዊ ክልል ለዋና ዋና የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ፍላጎቶች የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ሀብቶች አሉት። የቱሪዝም ልማቱ ነባሮቹን በማደስ፣ ከባቢያቸውን ጽዱ እና ማራኪ በማድረግ፣ በአቅራቢያቸው እና በዙሪያቸው ሌሎች ባሕላዊ እና ዘመናዊ መስሕቦችን በማስፋፋት ይጀምራል። ከተሞች የቱሪዝም መዳረሻ እንደመሆናቸው መጠን ከታሪካዊ አሻራዎቻቸው ጎን ለጎን "የእኛ ትውልድ" ምዕራፎች በንጽጽር የሚታዩበት ለኑሮ እና ለሥራ አመቺ የሆኑ ማስፋፊያዎች እና አዳዲስ ግንባታዎች በከተማ ልማት ግቦች አማካይነት ሲካሄዱ በተመሳሳይ ሁኔታ በውበታቸው እና በአገልግሎታቸው ተወዳዳሪ የቱሪዝም መስህብ መሆን ይችላሉ። አዳዲስ መዳረሻዎች እና መስህቦች በተጠና መንገድ መልማት እንዲችሉ በመሠረተ ልማት መምራት እና መግራት፣ በዓመት አንድ ጊዜ ከሚታዩት ወደ የሚዘወተሩት ማስፋፋት፣ የ13 ወር ፀጋን እና የክልሉን የተለያየ መልክዓ ምድር እና የአየር ንብረት ለዓመት ሙሉ ቱሪዝም በማነጽ የክልሉ እምቅ ሀብት በቱሪዝም ልማት አማካይነት ለአጠቃላይ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲውል ጥረት ይደረጋል።

29. **የተበታተኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በአዳዲስ ተጨማሪ መስህቦች፣ በመሠረተ ልማት እና የቱሪዝም ምርቶች አማካኝነት ወደ ቱሪዝም መስመሮች፣ ቀጠናዎች እና ጥብቅ ሥፍራዎች ማሳደግ፣** በክልሉ የሚገኙ ጉልህ የቱሪስት መስህቦች እና መዳረሻዎች የሚታወቁ እና ውስን ናቸው። በመዳረሻዎቹ መሃል ያልለሙ ለቱሪዝም

መዳረሻነት፣ እና መስህብነት ሊውሉ የሚችሉ ሀብቶች አሉ። እነዚህን ሀብቶች ማልማት፣ እርስ በእርሳቸው እና ከቀዳሚዎቹ ጋር መንገድን በመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ማገናኘት፣ እንዲሁም የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎቶችን የሚያሰፉ ማበረታቻዎችን ማቅረብ የቱሪስቶችን ቆይታ እና እርካታ ይጨምራል። የቱሪዝም ምርቶች የሚታዩ፣ የሚተገበሩ፣ ለምግብነት የሚውሉ፣ የሚሸመቱ በመሆናቸው ቱሪስቶችን ከማቆየት ባለፈ በጥራታቸው ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እና የአገር ስም የሚያስጠብቁ እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል። በምርት ሂደት ውስጥ መጥፎ ዕቃ እንዳለ ሁሉ ታይተው ወይም ቱሪስቶችን አጋጥመው የቱሪዝም ቢዝነስን የሚጎዱ ከቱሪዝም መጥፎ ምርቶች (bad tourism products) የሚመደቡ በመሆናቸው መልካም የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎቶችን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ያልሰለጠኑ እና ፈቃድ የሌላቸውን አስጎብኝዎች፣ የአካባቢ ብክለትን፣ ስርቆት እና ልመናን ማስቀረት ተገቢ ይሆናል።

30. **የቱሪዝም ልማትን ጽዱ እና ምቹ የመኖሪያ እና የሥራ አካባቢን ለዜጎች ከመፍጠር እና የዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በማቀናጀት ፍትሃዊ ቱሪዝምን ማረጋገጥ፤** ከተሞች እና የገጠር መንደሮች ውብ፣ ጽዱ እና ሳቢ ሆነው የሚታነጹት፣ የተራራ እና ሸለቆዎች እንዲሁም የአፍላጋት እና ቀላያት ማራኪ የመልከዓ ምድር ትዕይንቶች ላይ የመዝናኛ አገልግሎቶች እና የመዳረሻ ማሳለጫዎች የሚገነቡት፣ ደኖች እና ምንጮች የሚጠበቁት በቀዳሚነት የዜጎችን ብልጽግና የተሟላ እና ዘላቂ ለማድረግ ነው። ውበት ለራስ የመሆኑን ያህል በቱሪዝም ሥርዓት ውስጥ ደግሞ ተጎብኝቶ እና ታይቶ ገንዘብ ያስገኛል፣ ተጨማሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በሁሉም አካባቢዎች እንደ ሀብት መሠረታቸው በአማካይ ርቀት የፍትሃዊ ቱሪዝም ተደራሽነት ማረጋገጥ የፍትሃዊ ዘላቂ ልማት ግብ ነው።

31. **ወጪ ቱሪዝምን የሚተካ እና ክልላዊ ምርታማነትን የሚያግዝ በጠንካራ ኢኮኖሚ መሠረት ላይ የቆመ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ቱሪዝም ማራመድ፣** ቱሪዝም የሥራ ዕድል ይፈጥራል፣ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛል፣ በምርት እና አገልግሎት ዘርፎች ላይ ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ በመፍጠር የኢኮኖሚ ዕድገትን ያፋጥናል። በብሔራዊ ቱሪዝም ውስጥ ውስጣዊ ቱሪዝም (የገቢ ቱሪዝም እና አገር ውስጥ ቱሪዝም ድምር) እና ወጪ ቱሪዝም አለ። በተለይ የክልሉ እና የአገሪቷ ኢኮኖሚ እያደገ በሚመጣበት ወቅት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ሲጨምር ወጪ ቱሪዝም ገቢ ቱሪዝምን በመገዳደር ወይም በሙብለጥ እና የክፍያ ሚዛንን በማዛባት ከገቢ ቱሪዝም ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያቀጭጭ ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ በወጪ ቱሪዝም አማካይነት የዜጎች የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት ፍላጎት እንዲሸሽ በማድረግ አገር ውስጥ ኢኮኖሚን ሊያነቃቃ ይችል የነበረ አቅም እንዲወጣ ምክንያት ይሆናል። በሌላ በኩል ወጪ ቱሪዝም ለመዝናናት ከሚውል ይልቅ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ መልካም የሥራ ባሕል፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ የከተሞች ልማት፣ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም የሚደረጉ የቢዝነስ፣ የስልጠና፣እና የትምህርት ጉዞዎችን በሚያበረታታ ሁኔታ ሲቃኝ ለዕድገት አስተዋጽዖ ይኖረዋል። በዚህም መሠረት የብሔራዊ ወይም ክልላዊ የቱሪዝም ስትራቴጂ የውጭ ቱሪስቶች በስፋት የሚፈልጓቸውን ምርቶች በማቅረብ የገቢ ቱሪዝም አላባን ከፍ ከማድረግ ጎን ለጎን፣ በአገር ውስጥ ቱሪዝም (domestic tourism) ረገድ ዜጎች በውጭ አገር በስፋት የሚፈልጓቸውን እና የሚጓጉላቸውን የቱሪዝም ምርቶች እና አገልግሎቶች በክልሉ በማስፋፋት፣ እንዲሁም ከወጪ ቱሪዝም መካከል ለቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያግዙ የቱሪስት ምድቦች (tourist segments) ላይ በማተኮር ነው። የጨዋታ ፓርኮች፣ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ሰፊ እና ትላልቅ የገበያ ማዕከላት፣ እና የሕክምና ቱሪዝም በክልል እንዲሁም በአገር ደረጃ ሊተኩ የሚችሉ የቱሪዝም መስህቦች እና ምርቶች ናቸው።

32. ቱሪዝም የኢኮኖሚ ዕድገትን የማፋጠኑን ያህል በጠንካራ ኢኮኖሚ ላይ ሲመሠረት የበለጠ የቱሪዝም ገቢ ያስገኛል። በየደረጃው ጥራትን እያስጠበቀ በለሙ ከተሞች እና የገጠር አካባቢዎች ብልጽግናን የሚያረጋግጥ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተጎብኝቶ እና ታይቶ ተጨማሪ ገቢ ያስገኛል። ነገር ግን ቀላል የማይባል ዜጋው ኑሮ በቱሪዝም ልማት ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ እንቅስቃሴ በየወቅቱ በሚፈጠሩ ደፋቂ ኩነቶች ከሌላው ዘርፍ በበለጠ ተጠቂ ስለሚሆኑ የዘላቂ ቱሪዝም ልማት መሠረቱ መዋቅራዊ ሽግግርን ያረጋገጠ ኢኮኖሚ በመሆኑ አጠቃላይ የክልሉ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ይህን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

33. **ለሰፊ የዓለም የቱሪዝም ፍላጎት ትርጉም ያለው አቅርቦትን በሳይንሳዊ የሥነ ገበያ መርህ በማመቻቸት ከዓለም ቱሪዝም ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን፤** የቱሪዝም ኢኮኖሚ እንደማንኛውም ዘርፍ በፍላጎት እና አቅርቦት ሕግጋት ይመራል። ዘርፉ እንደ አገር ወጪ እና ገቢ፣ ትርፍ እና ኪሳራ፣ ዕዳ እና ምንዳዕ፣ እንዲሁም ተስፋ እና ሥጋት አለው። ከእነዚህ ክስተቶች መካከል ክልሉ ከዘርፉ ገቢውን፣ ትረፉን፣ ምንዳውን፣ እና ተስፋውን ባለው የመልማት አቅም ልክ ከፍ ለማድረግ የብዝሃ ዘርፍ ሳይንስን በመጠቀም ፍላጎት እና አቅርቦትን ያጣጣመ ትንተና ያስፈልገዋል። ቱሪስቶች ወደ አንድ መዳረሻ ለመጓዝ ዋና ዋና ምክንያቶች አሏቸው፤ በሚጓዙባቸው

መዳረሻዎች የሚመርጧቸው የቱሪዝም መስህብ ዓይነቶች እና የቱሪዝም ምርቶች አሉ፤ ከእነዚህ የተጓዦች ምርጫ መካከል የተጓዦችን የጊዜ ቆይታ ለማራዘም የበለጠ ሚና ያላቸው የቱሪዝም ምርቶች እና አገልግሎቶች አሉ። ገበር ስትራቴጂው የቱሪስት ቁጥርን በመጨመር እና የቱሪስት የቆይታ ጊዜን በማራዘም ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማሳደግ ሲሆን የቱሪዝም ማኔጅመንት እና ሥነ ግብይት (marketing) ተግባር የቱሪዝም መስህቦችን፣ መዳረሻዎችን፣ እና ምርቶችን በማስፋፋት የቱሪዝም ቁጥርን መጨመር እና የቱሪስት የቆይታ ጊዜን ማሳደግ ነው።

34. ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘን ፋይዳ ከፍ ለማድረግ የቱሪዝም ባህርያትን ማጥናት ይጠይቃል። ቱሪዝም በሰዎች ውሳኔ የሚፈጸም ተግባር በመሆኑ ብዙ የሰው ልጅ መስተጋብሮችን የሚዳስስ ነው። ከዚህ አንጻር የጎብኝዎችን ማንነት፣ የጉዞ ምክንያቶችን፣ የጉዞ መዳረሻ ምርጫ፣ በጉዞ ወቅት በስጋትነት የሚያዩዋቸው ጉዳዮች፣ በጉዞ ወቅት የሚመርጧቸው አስፈላጊ ነገሮች፣ የትራንስፖርት ዓይነት ምርጫ፣ የመቆያ ቦታ ምርጫ፣ በጉዟቸው ሊፈጽሟቸው ስላቀዷቸው ጉዳዮች፣ የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች ሊያሟሉ ስለሚችሉ አካላት፣ በሚጎበኟቸው አካባቢዎች ስለሚፈጥሯቸው ተጽዕኖዎች እና ለእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልስ በሚሰጠው የቱሪዝም ሥርዓት ወይም ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ የሥራ ዕድሎች እና አጠቃላይ ማሕበራዊ እንዲሁም አገራዊ ተጠቃሚነቶች ምን እንደሆኑ መለየት ያስፈልጋል።

35. በቱሪዝም ገበያ ውስጥ ፍላጎትን ለማመላከት የቱሪዝም ገበያን በሳይንሳዊ መንገድ ከፋፍሎ ማየት ተገቢ ይሆናል። ለዚህ ተግባርም አምሥት ደረጃዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፤
    1. አግባብነት ያለው የገበያ መከፋፈያ ሥልት መምረጥ፣
    2. የተከፋፈሉ የቱሪዝም ገበያዎችን ባህርይ የሚያሳዩ ዝርዝር መረጃዎችን መለየት፣
    3. የእያንዳንዱን የገበያ መደብ (tourism market segment) የወደፊት ስፋት መተንበይ፣
    4. የእያንዳንዱን የገበያ መደብ ከአጠቃላይ ፍላጎት ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ ማስላት፣
    5. የትኛው ወይም የትኞቹ የቱሪዝም ገበያ መደቦች እንደሚያዋጡ መወሰን እና ተገቢ የሥነ ገበያ ሥልት መቀየስ።

36. የቱሪዝም ገበያ ፍላጎትን የማመላከት ሂደት ከጉዞ ምክንያቶች ይጀምራል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዓለም ላይ ሦስት ዋና ዋና የቱሪስቶች የጉዞ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህም
    1. ጓደኛ እና ዘመድ ለመጎብኘት፣
    2. ለመዝናናት፣ እና
    3. ለቢዝነስ ወይም ከሙያ ጋር የተያያዙ ጉዞዎች ናቸው።

37. ከጉዞ ምክንያቶች በመቀጠል የቱሪዝም ፍላጎትን በማመላከት ምድብ (tourism markets segmentation) ለመስጠት የሚያስችሉ ጉዳዮች የተጓዦች ምርጫዎች ናቸው። ምርጫዎቹ በቱሪስቶች
    1. የፊዚዮሎጂካዊ ፍላጎቶች፣
    2. የደህንነት ፍላጎቶች፣
    3. የአብሮነት ፍላጎቶች፣ እና
    4. የልዩ ደንበኝነት ፍላጎቶች ይወሰናሉ።

38. እነዚህ ፍላጎቶች በተራቸው
    1. በጂኦግራፊ (የቱሪስት ፍላጎቶች እንደመጡበት አካባቢ ይለያያል)፣
    2. በሥነ ሕዝብ (ወጣቶች፣ የእድሜ ባለጸጋዎች፣ ያገቡ እና ያላገቡ የተለያየ ፍላጎት አላቸው)፣
    3. በሥነ ልቦና፣ እና
    4. በቱሪዝም ምርት ወይም አገልግሎት ፈርጆች ይለያያሉ።

39. ከላይ በሦስት ደረጃ የተለዩትን የቱሪስቶች ፍላጎት ማመላከቻ በማቀናጀት በማድረግ የተለዩ ዋና ዋና የጎብኚ ምድቦች (specialized tourist segmentations) መለየት የሚቻል ሲሆን ዋና ዋናዎቹም
    1. የቢዝነስ እና ሙያ ነክ ተጓዦች (business and professional travellers)፣
    2. የማበረታቻ ተጓዦች (incentive travelers)፣
    3. የማሕበረሰባዊ እና የቡድን ተጓዦች (Social, Military, Education, Religious and Fraternal - SMERFs )፣ የዕድሜ ባለጸጋ ተጓዦች (mature travellers)፣
    4. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተጓዦች (special interest tourism) ናቸው።

40. የጎብኚ ምድቦቹ የዓለም አቀፍ የቱሪዝም ፍላጎት አቅጣጫ የሚያመላክቱ ሲሆኑ በክልል እና በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ሀብቶችን ከአገራዊ እና ክልላዊ እሴቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ለማልማት እና ከዓለም አቀፍ የቱሪዝም ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ፍንጭ ይሰጣሉ።

41. **ስዕል 14 -6፤** የቱሪዝም ገበያ ፍላጎት እና አቅርቦት ወሳኝ ይዘቶች




ምንጭ፤ የCook, et al ሀሳቦችን በመቀመር የተዘጋጀ

42. ከአምሥቱ የጎብኚ ምድቦች መካከል የዕድሜ ባለጸጋ ተጓዦች በብዛት፣ በጉዞ ድግግሞሽ፣ በቡድን በመጓዝ፣ እና በቆይታ ጊዜ ርዝመት መስፈርቶች እያደገ ያለ ምድብ ነው። ይህ ከአጠቃላይ የአደጉ አገራት የሥነ ሕዝብ መዋቅር መቀየር ጋር የተያያዘ ሲሆን በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብዛት የተወለደው ትውልድ (baby-boomers) ክብረ ወሰን በሚሰብር ደረጃ ወደ ጡረታ እየተሸጋገረ በመሆኑ ነው። የዚህ ምድብ ቱሪስቶች ዋና ዓላማ ለመዝናናት እና ለማረፍ ሲሆን የምቾት ቱሪዝም ውስጥ የሚካተት ነው። ምድቡ በሁለተኛ ደረጃ ለቢዝነስ ዓላማ ጉዞ የሚያደርግ ነው።

43. የዕድሜ ባለፀጋ ተጓዦች የሐይቅ እና የወንዝ ዳርቻዎችን፣ ፀጥታን የተላበሱ የገጠር አካባቢ ማረፊያዎችን፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚያዘወትሩ ሲሆን፣ ጥቅጥቅ ደን አካባቢዎችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን በሁለተኛ ደረጃ ለቆይታ ይመርጣሉ። ከነዚህ ተጓዦች ምድብ መካከል 75 በመቶ የሚሆኑት ለጉዞቸቸው መኪና በተለይም የምቾት መዝናኛ መኪናን የሚፈልጉ ሲሆን በአብዛኛው የጥቅል ጉብኝት አቅርቦትን (package tour) ይመርጣሉ። ከዚህ ጉዞ ጋር አብረው የሚሄዱ ሌሎች የሳይኮሎጂካል ፍላጎቶች በየመዳረሻዎች እና መንገዶች ተደራሽ የሆነ የምግብ እና መጠጥ መስተንግዶዎች እና ከከተማ እስከ ፓርኮች ባሉ መሸጋገሪያዎች የመኝታ አገልግሎት ይፈልጋሉ። ከዘርፉ ልማት ዕቅድ አንጻር የምድቡ ተጓዦች መለያ ባሕርይ እያደገ ያለ ምድብ መሆኑ፣ ለመጓዝ ጊዜ እና ፍላጎቱ፣ እንዲሁም ሀብት እና ገቢ ያላቸው መሆኑ ነው። እነዚህ ተጓዦች ከማየት ይልቅ በመዳረሻዎች በድርጊት በመሳተፍ ማሳለፍን ይፈልጋሉ፤ በተናጠል ከመጓዝ ይልቅ ከልጆች እና ልጅ ልጆች ጋር መጓዝ እና መዝናናትን ያዘወትራሉ። ከደህንነት ፍላጎቶች አንጻር ይህ ምድብ እንክብካቤ የሚፈልግ በመሆኑ የሰለጠኑ የጉዞ ባለሙያዎች እና ከምቾት እስከ ጤና ላሉት ፍላጎቶች ዝግጁነት ይጠይቃል። ከዚህ አንጻር የአማራ ብሔራዊ ክልል የዚህ ምድብ ተጓዦች የሚመርጧቸውን መዳረሻዎች፣ መስሕቦች እና ምርቶች ለማቅረብ መነሻ ሀብቱ ያለው ሲሆን ቀሪው ጉዳይ ማነጽ፣ ማዘመን፣ ማስተሳሰር እና ማቀናጀት ነው።

44. የቢዝነስ እና ሙያ ነክ ጉዞ ምድብ ውስጥ ያሉ ጠቃሚ የቱሪዝም ልማት ምንጮች ናቸው። ከመለያ ባሕርያቶቻቸው መካከል 62 በመቶ የሚደርሱት እረፍትን ከቢዝነስ ጋር አስተሳስረው መጓዛቸው፣ ተደጋጋሚ

ጉዞ ማድረጋቸው እና በአብዛኛው በከተሞች በሆቴሎች ቆይታ የሚያደርጉ መሆናቸው ነው። ከዚህ አንጻር ከተሞችን ለጎብኚዎች ምቹ ማድረግ፣ ተጠቃሽ እና ታዋቂ የገበያ ማዕከላትን በመገንባት ቢዝነስን ዓለም አቀፋዊ ማድረግ፣ በዘርፉ ተወዳዳሪነትን ይጨምራል።

45. የማበረታቻ ተጓዦች የስብሰባ፣ የኩባንያዎች እና መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ማበረታቻ፣ የጉባዔዎች፣ እና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች የሚያካትቱ ሲሆን ኢትዮጵያ የብዙ ድፕሎማሲ ማዕከላት መገኛ እንደመሆኗ መጠን በእነዚህ ሰበብ አገር ውስጥ የሚገቡ ጎብኝዎችን ለማቆየት ከመሥራት በተጨማሪ እንደ ጣና ፎረም ዓይነቶቹ ጅምሮች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

46. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተጓዦች ቱሪዝም ምድብ ምድብ ከ15 በላይ ንዑስ ምድቦች ያሉበት ሲሆን ከዚህ በርካታ ፍላጎቶች ከሚጠቃለሉበት ምድብ መካከል በተለይ የሥነ ምሕዳር ቱሪዝም (ecotourism)፣ የሕክምና ቱሪዝም፣ የአርኪዎሎጂ ቱሪዝም፣ እንዲሁም ባሕላዊ እና የማይዳሰሱ መስህቦች ቱሪዝም ክልሉ በትኩረት ሊሠራባቸው የሚችሉ ንዑስ ምድቦች ናቸው። ምድቡ ከአገራዊ ጠቃሚ ባሕላዊ እሴቶች ጋር የሚጋጩ ፍላጎቶች ያሉበት በመሆኑም በፖሊሲ የሚገሩ ጉዳዮች ታሳቢ ይደረጋሉ።

47. በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ የቱሪዝም ምርት በማቅረብ ተወዳዳሪ የመሆን ግብ ዝግ ባይሆንም የቱሪዝም አቅርቦት በአብዛኛው በአሁናዊ እና የወደፊት የዓለም የቱሪዝም ሥርዓት አቅጣጫ ላይ ይመሠረታል።የቱሪዝም ምርት (tourism product) አቅርቦት መጓጓዣን፣ መስተንግዶን፣ ምግብ እና መጠጥ፣ መስህቦችን፣ እና መዳረሻዎችን የሚያካትት ነው። በቱሪዝም የአቅርቦት ሥርዓት ውስጥ ገዢው መርህ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሁሉንም ነገር ይሰትራል (One Stop Does It All) የሚለው ነው። አገልግሎቶች በአንድ ርከን ወይም በቀጥታ፣ በሁለት ርከን፣ ከዚህ ሲያልፍም በሦስት ርከን ለተገልጋይ ቱሪስቶች ሊቀርቡ ይችላሉ። የአንድ ርከን ወይም የቀጥታ አገልግሎት የአየር ጉዞ ቲኬት፣ የመኪና ኪራይ፣ የባቡር ጉዞ፣ የሎጂዎች እና የሪዞርቶች አገልግሎት፣ የምግብ ቤቶች፣ የፓርኮች እና ሌሎች መስህቦችን ለማስተባበር የተለያዩ የመሃል አገናኞች ሳያስፈልጉ በአንድ አካል በተለይም በድረ-ገጽ የሚጠናቀቅበት አሠራር ነው። ከመረጃ ቴክኖሎጂ ማደግ ጋር ተያይዞ ይህ አማራጭ በመስፋት ላይ ይፈኛል። የክልሉ የቱሪዝም ልማት ዋና ዓላማም አቅርቦትን ከዘመኑ ዓለም አቀፍ ፍላጎት እና የቴክኖሎጂ ለውጥ አቅጣጫ ጋር አብሮ ማዘመን ነው።

## 14.3. የትኩረት መስኮች

48. የቱሪዝም ዘርፍ የቀጣይ የአምሥት ዓመት ዕቅድ ሦስት ዋና ዋና የትኩረት መስኮች

1. የቱሪዝም መዳረሻ እና መስህቦች ልማት፣
2. የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት ጥራት፣
3. የቱሪዝም መሠረተ ልማት፣
4. ዘመናዊ የቱሪዝም መረጃ ሥርዓት፣ እና
5. የቱሪዝም ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ናቸው።

## 14. 4. ዓላማ እና ግቦች

49. የአምሥት ዓመት የቱሪዝም ልማት ዋና ዓላማ የቱሪስት መዳረሻዎችን እና መስህቦችን በማልማት እንዲሁም ብቁና ተወዳዳሪ የቱሪዝም አገልግሎቶችን በማስፋፋት የቱሪስት ፍሰትን እና ገቢን ማሳደግ፣ ክልሉ ከዘርፉ ሊያገኝ የሚችለውን ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከፍ ማድረግ ነው።

50. የዘርፉን ዕቅድ ዓላማ ለማሳካተም የሚከተሉት ግቦች ተለይተዋል፤

1. ሁሉንም የክልሉ የቱሪዝም ሀብት በዓይነት እና በቦታ በመለየት ለቱሪዝም መዋዕለ ንዋይ ዝግጁ ማድረግ
2. የክልሉን ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎችን ሙሉ በሙሉ ማደስ፣ የከባቢ መስህቦች ልማት ማረጋገጥ፣
3. አዲስ እና ነባር የቱሪዝም መዳረሻ እና መስህቦችን በመሠረተ ልማት ሙሉ በሙሉ ተደራሽ ማድረግ፣ እርስ በእርሳቸውም ማስተሳሰር፣
4. የክልሉን የቱሪስት መዳረሻዎች እና መስህቦች መረጃ የዘመኑን ቴክኖሎጂ ሥርዓት በመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽ ማድረግ፣ ማስተዋወቅ፣

5. የቱሪዝም ሥርዓትን ማዘመን፤ የሆቴሎችን ጥራት እና የመስተንግዶ ደረጃ ማሻሻል፣
6. የቱሪዝም የሰው ኃይል ሥልጠና በማጠናከር በዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማረጋገጥ፣ እና
7. የክልሉን አጠቃላይ የቱሪዝም ልማት የመረጃ ሥርዓት ማጠናከር እና ማዘመን ናቸው።

## 14.5. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

51. የቱሪዝም ልማት ዓላማ እና ግቦችን ዳር ለማድረስ የተለዩ የማስፈጸሚያ ሥልቶች
    1. የክልሉን የቱሪዝም ልማት የሀብት መሠረት ላይ በመመሥረት የቱሪዝም ልማት መስመሮች፣ ኮሪደሮች እና ቀጠናዎች በስፓሻል ፕላን ማመላከት፣
    2. የዘርፉን ኢንቨስትመንት በጥናቶች እና በመሠረተ ልማት መምራት፣
    3. እንደ መስኖ ግድብ፣ ትልልቅ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች፣ የከተማ መሠረተ ልማት አውታሮች፣ የመኖሪያ እና የቢዝነስ ግንባታዎች፣ እና ዘመናዊ የገጠር መኖሪያ ቤት ግንባታዎችን የመሳሰሉ የሌሎች ዘርፎች የልማት ግንባታዎች የቱሪዝም ምርቶችን በመፍጠር ከቱሪዝም ልማት ግቦች ጋር እንዲጣጣሙ ከዘርፎች ጋር በቅንጅት መሥራት፣
    4. የኢትዮጵያን ዲያስፖራ በትውልድ አገር ጉብኝት እና በሪል እስቴት ቱሪዝም ግንባታ ምድቦች ማሳተፍ፣
    5. በመዳረሻ፣ በምስህቦች፣ በመስተንግዶ፣ በልዩ ባሕላዊ ምግብ እና መጠጦች እንዲሁም በትራንስፖርት የሚገለጹ ተወዳዳሪ የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎቶች መረጃን ለዓለም ተደራሽ ማድረግ፣ እና
    6. ዛይንሳዊ የክትትል፣ የድጋፍ እና ግምገማ ሥርአት መዘርጋት ናቸው።

# ምዕራፍ አሥራ አምሥት

# ንግድ እና ገበያ ልማት

## 15.1. ሚና

1. ውስን ሀብት ላይ የተመሠረተ አቅርቦት በተሳለጠ መንገድ ከፍላጎት ጋር ተጣጥሞ እንዲዘልቅ ንግድ የማይተካ ሚና ይጫዎታል። የአቅርቦት እና የፍላጎት ሚዛን የሸማች ደህንነት (consumer welfare) ይረጋገጥ ዘንድ የነገራተ ምርት ዋጋዎች ማለትም ኪራይ፣ ወለድ፣ ምንዳዕ እና ደመወዝ፤ የሸቀጦች ዋጋ፣ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ምልክት (market signal) እንዲያንጸባርቁ ንግድ እና የንግድ ሥርዓት ወሳኝ ሚና አላቸው። የኢኮኖሚ ዕድገት የሸቀጦች እና የአገልግሎቶች ልውውጥ መብዛት፣ ማደግ፣ እና መራቀቅ ሲሆን ንግድ እና የንግድ ሥርዓት ምርታማነትን (productivity)፣ ቅልጥፍናን (efficiency)፣ የሥራ ክፍፍል (division of labor)፣ እና አትኩሮተ - ተግባርን ወይም መከረርን (specialization) በማሳለጥ የዕድገትን አቅጣጫ የመበየን አቅም አለው።

2. ንግድ ምርቱን የመምሰሉን ያህል፣ ምርትም የንግድ ሥርዓቱ ነጸብራቅ ይሆናል። ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ግብርና ምርት ጀምሮ የዘመናዊ ግብርና ውጤቶችን ከአምራች ወደ ሸማች ያደርሳል፤ በዚህም የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮችን የገበያ ተደራሽነት የማሳለጥ፣ የዘማናዊ ግብርና ውጤቶችን በበቂ መጠን ለሸማቾች እንዲደርስ በማደረግ የኑሮ ውድነትን ይከላከላል። የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት የመተካት ግብን በማሳካት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫዎታል። በቴክኖሎጂ ተመዳዳሪነት መርህ ፈጣን እድገት እንዲረጋገጥ ለቴክኖሎጂ ሽግግር አመች የሆኑ የካፒታል ምርቶች ገቢ ንግድን በማቀላጠፍ መዋቅራዊ ሽግግርን ያፋጥናል፤ ለዚህ ዓላማ የሚደረጉ የኢንቨስትመን ሥራዎችን ያበረታታል።

## 15.2. ክልል አቀፍ እና አገር አቀፍ የንግድ ሥርዓት ሁኔታ

3. በ2013 የብሔራዊ ሠራተኛ ኃይል እና ፍልሰት ጥናት መሠረት የንግድ ዘርፍ 598 ሺህ ለሚሆኑ የክልሉ ዜጎች የሥራ መስክ ነው። ከ2013 እስከ 2016 በነበሩት አራት ዓመታት የንገድ እና ሆቴሎች ተጨማሪ እሴት በዓመት በአማካይ

በ11.2 በመቶ አድጓል። በ2016 የበጀት ዓመት የእነዚህ ንዑስ ዘርፎች ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ምርት የነበረው ድርሻ 12.1 በመቶ ነው።

4. የአገር አቀፍም ሆነ የክልል አቀፍ የንግድ መዋቅር ለግብይት መሳለጥ፣ እና ለዋጋ ከትትል ያለው አመቺነት ዝቀተኛ ነው። ዘርፉ በአነስተኛ ተዋንያን የተሞላ በመሆኑ አቅራቢዎች (ቸርቻሪዎች) ትርፍን የሚሹት ከብዛት ሳይሆን ባላቸው አነስተኛ መጠን ላይ ዋጋ በመጨመር ሲከፋም በመቆለል ነው። ለዚህም አንዱ ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ነው። ገቢ ወይም ትርፍ ምርትን በብዛት በመሸጥ (economies of scale)፣ ወይም ጥቂት ምርትን በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ሊጨምር ይችላል፤ ። አነስተኛ አቅራቢ ከብዛት ተጠቃሚ ስለማይሆኑ ወይም ብዙ ማምረት እና መሸጥ ተጨማሪ ጥረት ምናልባትም ልፋትን ስለሚጠይቅ በውስን አቅርቦት ላይ ዋጋ በመጨመር ትርፍ ማረጋገጥን ይመርጣሉ። የአነስተኛ፣ ግን በርካታ አቅራቢዎች ያሉበት የገበያ ሥርዓት መንግሥት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ያልተገቡ የዋጋ ጭማሪዎችን ጨምሮ የዘርፉ ወሳኝ ጉዳዮችን ለማስተካከል ይቸገራል።

5. በደላላ ብዛት የተጨናነቀ ረጅም እና የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለት የግብይት ሥርዓቱ ቀልጣፋ እንዳይሆን፣ በውጤቱም የዋጋ ንረት እንዲከሰት አስተዋጽዖ ማድረጉ አልቀረም። የኬላ ላይ ቀረጥን ጨምሮ የባለ ድርሻ ተዋንያን መበራከት በአቅራቢዎች ወጪ መብዛት ምክንያት ሸማቹ ለኑሮ ውድነት የበለጠ ተጋላጭ እንዲሆን ያደርጋል። የዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ በዋጋ ላይ ያለው ሚና ለሸማቹ የዋጋ መረጃ ለማግኘት ከማገዝ ይልቅ አቅራቢዎች ዋጋን በምልዓት ከፍ አድርገው እንዲወስኑ ማገዙ አልቀረም።

## 15.3. የትኩረት አቅጣጫዎች

6. ከላይ የተጠቀሱትን የዘርፉን ሚናዎች እና የተስተዋሉ ተግዳሮቶች ግምት ውስጥ በማስገባት የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የንግድ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው፤
    1. ንግድን በማዘመን የዘመናዊ አገልግሎት እና የኢንዱስትሪያላዊነት አካል ማድረግ፣
    2. ትርፍን ከከፍተኛ የመሸጫ ዋጋ ሳይሆን ከምርት ወይም ከሽያጭ ብዛት (economies of scale) ማግኘትን ግብ ያደረጉ ከፍተኛ አቅም ያላቸው የዋና ዋና ምርቶች አቅራቢዎች እንዲቋቋሙ በማድረግ ገበያውን ማጥገብ፣
    3. ከአስመጪዎች ይልቅ የአግር ውስጥ ምርትን ንግድ የሚያሳልጡ አቅራቢዎችን፣ ከአስመጪዎችም የቴክኖሎጂ እና አምራች ካፒታል እቃዎችን የሚያስገቡ አስመጪዎችን በማበረታታት ንግድን የረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ማድረግ፣
    4. የፍጆታም ሆኑ የግብዓት እቃዎች እንደ ዓይነታቸው በአንድ ማዕከል ለሸማቾች የሚደርሱበትን የታላላቅ የከተማ ውስጥ ገባያዎችን (mall) በልዩ ሁኔታ በማስፋፋት ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓት መፍጠር፣
    5. የተሳለጠ የገበያ ሥርዓትን በመሠረተ-ልማት፣ በሕግ እና አሠራር መደገፍ።

## 15.4. የትኩረት መስኮች

7. በአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን ሁለት የዘርፉ የትኩረት መስኮች
    1. ዘመናዊ፣ተወዳዳሪ፣ህጋዊና ፍትሃዊ የንግድ ስርዓት፣ እና
    2. ዘመናዊ ተወዳዳሪና ፍትሐዊ የግብይት ስርዓት ናቸው።

8. ዘመናዊ፣ተወዳዳሪ፣ህጋዊና ፍትሃዊ የንግድ ስርዓትን ከመገንባት አንጻር በተደራጀ አግባብ ህግና ስርዓትን የሚያከብር እና ህገወጥነትን የሚጠየፍ የንግድና ሸማች ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት ታቅዷል።

9. ዘመናዊ ተወዳዳሪና ፍትሐዊ የግብይት ስርዓት ከማስፈን አኳያ የግብይት ተዋንያንን ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ፣ ሸማች ተኮር የግብት ስርዓትን በመከተል የኑሮ ውድነት ጫናን የመቀነስ፣ የግብይት አሠራሮችን የማዘመን፣ የኤክስፖርት ምርት መጠንና ጥራትን የበማሳደ፣ የውጪ ምንዛሬ ግኝትን የማሻሻል፣ የገበያ መዳረሻዎችን የማዘመን፣ማስፋትና ተደራሽነታቸውን የማረጋገጥ ግቦችን ማሳካት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው።

## 15.5. ዓላማ እና ግቦች

**10. ሠንጠረዥ 15-1፤ ዓላማ እና ግቦች**

| ዓላማ | ግብ |
|---|---|
| **1.** የንግድ መሠረቱን በማስፋትና ህጋዊ የንግድ ሽፋንን በማጠናከር የሸማቹን መብት ማስከበር | • ትኩረቱን ምርት በብዛት እና በመጠን በማቅረብ በኩል ተፅዕኖ ያላቸውን ንግድ ተዋንያን ላይ ያደረገ የንግድ መሰረቱን ከ 331,819 ወደ 728,836 ማሳደግ<br>• የንግድ ዉድድሩን በማጠናከርና የኢንስፔክሽን ስራዉን በማስፋት ህጋዊ የንግድ ሽፋኑን ከ46% ወደ 70% ማሳደግ፤<br>• ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት፡ |
| **2.** የገበያ መሠረተ ልማት በማስፋፋት ፣የግብይት ስርዓቱን በማዘመንና ሰንሰለቱን በማሳጠር ፣የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት እና የኤክስፖርት ግብይትን ማሳደግ | • የገበያ ተዋንያንን አቅም በማሳደግ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት በትስስር በማቅረብ የኑሮ ዉድነቱን ማረጋጋትና ገበያውን ማጥገብ፤<br>• ዘመናዊ የገበያ መሠረተ-ልማት እና የመረጃ ስርዓትን በመዘርጋት ግብይቱን ማሳለጥ<br>• የኤክስፖርት አሰራሩን በማጠናከርና የገበያ ትስስሩን በማቀላጠፍ በሰብልና በእንስሳት ዉጤቶች የወጭ ግብይት ማሳደግ |

## 15.6. የማስፈጸሚያ ስልቶች

11. የንግድ እና ገበያ ልማት ዕቅድን በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተነድፈዋል፤

- ቅንጅታዊ አሰራሩን በማሳደግ እና ህገ-ወጥነትን መከላከል
- የአገር ውስጥና ኤክስፖርትን ግይትን በጥራት፣በመጠንና በአይነት ማሳደግ
- የንግድ ሪፎርሙንና የህግ ማዕቀፎችን ማሻሻል፣ መተገበር
- ስራዎችን በፈጠራ እና በምርምር ማስደገፍ
- ተግባራትን በቴክኖሎጂ በማስገደፍ መፈፀም
- ተግባራትን በጠንካራ የቡድን ስሜትና የስራ ባህል መፈጸም
- ውጤታማነት፣ቅልጥፍና ችግር የመፍታት አቅምን ማሳደግ
- የፋይናንስ ውጤታማነት ሀብትን በቁጠባ እና ውጤት በሚያመጣ ተግባር መጠቀም
- ጠንካራ የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋት።

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

# የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ልማት

## 16.1. መነሻ

1. ትራንስፖርት እና ሎጂስትሪክስ የዘመናዊ ኢኮኖሚ ማሳለጫ፣ አራሱም ትልቅ ኢንዱስትሪ ነው። ስለ ኢንዱስትሪያላዊነት ሲታሰብ የትራንስፖርት እና ሎጂስትሪክስ ስፋት፣ የአገልግሎት ቅልጥፍና፣ እና ዓለም አቀፍ ተወዳሪነት ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ወሳኝ ባሕያት ናቸው። የማሳለጫ መንገዶች፣ ለወደብ ቅርብ መንገዶች፣ በአማካይ ርቀት የሚገነቡ ስታራቴጂካዊ ደረቅ ወደቦች፣ የባቡር እና የመርከብ ትራንስፖርት ሥርዓቶች መኖር እና ቅልጥፍና ተወዳዳሪነትን ይበይናሉ።

2. ትራንስፖርት መሠረተልማት፣ የማጓጓዣ መሣሪያዎች፣ ኃይል፣ እና ተያያዥ አገልግሎቶች የተካተቱበት ረጅም የእሴት ሰንሰለት ሥርዓት በመሆኑ ትልቅ ኢንዱስትሪም ነው። የትራንስፖርት ሥርዓት የማጓጓዣ ሥልቶች (የየብስ፣ የውሃ፣ የአየር)፣ የትራንስፖርት መሠረተልማትን (መንገድ፣ የባቡር ሃዲድ፣ የፈሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦች፣ ወደብ፣ የአየር ማረፊያዎች፣ የብስክሌት እና ስኩተር ማሳለጫዎች፣ የእግረኛ መተላለፊያዎች፣ የትራፊክ ምልክቶች)፣ የትራንስፖርት ማጓጓዣዎችን እና ኮንቴይነሮችን፣ ኦፐሬሽን (ማሽከርከር፣ ማብረር፣ መቅዘፍ፣ የትራፊክ ማኔጅመንት (ቁጥጥር እና ሲግናል)፣ ፕሮግራም (ማቀድ እና ማሳለጥ)፣ ማቀናጀት (ኢንተርሞዳል)፣ የተሽከርካሪዎች የኃይል ምንጭ፣ ቴክኖሎጂ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል የተካተተበት ሰፊ ሥርዓት ነው።

3. ሎጂስቲክስ የሚከተሉት ዋና ዋና አምዶች አሉት፤
    1. የምርት እና ዕቃዎች አያያዝ፣ ስትራቴጂካዊ መጋዘን፣ ድህረ ግብርና ምርት አያያዝ
    2. ምርትን ማሸግ (ፓኬጂንግ እና ዩኒታይዜሽን)
    3. አቀይቶ መሸጥ (ኢንቨንተሪ)
    4. ትራንስፖርት
    5. መረጃ እና ቁጥጥር።

4. በ2013 መረጃ መሠረት የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ በአማራ ብሔራዊ ክልል ለ122 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል። ከዚህም በተጨማሪ በ2016 የትራንስፖርት እና ኮምዩኒኬሽን ተጨማሪ እሴት ከአጠቃላይ ክልላዊ ምርት 6.5 በመቶ ድርሻ የነበረው ሲሆን ይህም ከአገልግሎት ንዑስ ዘርፎች መካከል ከንግድ እና ሆቴሎች ንዑስ ዘርፍ ቀጥሎ ከፍተኛው ድርሻ ነው። ከ2013 እስከ 2016 በነበሩት አራት ዓመታት የንዑስ ዘርፉ ተጨማሪ ዕሴት በ8.2 በመቶ አድጓል። በተመሳሳይ ወቅት አጠቃላይ የአገልግሎት ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት ምጣኔ 7.5 በመቶ ነበር።

5. የአማራ ብሔራዊ ክልል የሁሉም ዓይነት መልከዓ ምድር መገኛ ቢሆንም ከፍተኛ እና ተራራማ አካባቢዎች ስለሚበዙ ተወዳዳሪነትን ለማስፋት ከዓለም አቀፍ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሥርዓቶች ጋር የሚያገናኙ ስትራቴጂካዊ የትራንስፖርት እና የሊጂስትሪክስ ሥርዓቶችን መዘርጋት ያስፈልጋል።

## 16. 2. የትኩረት አቅጣጫ

6. የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ የትኩረት አቅጣጫ፤
    - ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን መሠረት ላደረገው የኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂካዊ ድጋፍ ማድረግ፣ በተለይም ግብዓትን እና ምርትን ተደራሽ ማድረግ፣
    - ለወጪ እና ገቢ ንግድ መሳለጥ ስትራቴጂካዊ የመንገድ ትራንስፖርት ኮሪደሮችን መለየት እና በፌደራል መንግሥት፣ እንዲሁም ከአጎራባች ክልሎች ጋር በጋራ ማልማት፣
    - ክልሎችን እና አጎራባች አገሮችን በመንገድ ትራንስፖርት በማገናኘት የቀጠናዊ ትስስርን ማጠናከር፣

- የከተሞችን ዕድገት ቀድሞ በመተንበይ እና በመተንተን የረጅም ዘመን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ፍላጎት ማቀድ፣ ለእድገት ደረጃቸው የሚመጥን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ መሠረት ልማቶችን መዘርጋት፣
- የገጠር ነዋሪዎች ወደ አንድ አዳጊ የከተማ ማዕከል ይሰባሰቡ ዘንድ ቀድሞ በተነደፈ ፕላን በትራንስፖርት መሠረተ-ልማት መምራት፣
- ለኢንዳስትሪያላዊነት የሚመጥን ክልላዊ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ መቅረጽ፣ በተለይም ክልላዊ የብዙሃን ትራንስፖርት (mass transport) ስትራቴጂ መንደፍ፣ ከፌደራል፣ ከቀጠና እና አህጉራዊ እቅዶች ጋር ማጣጣም እና በየደረጃው መተግበር፣
- የክልሉ ደረቅ ወደቦችን ሚና ከልማት ቀጠናዎች ጋር ማስተሳሰር
- ከተሞች እንደ ጂኦግራፊያዊ አመችነታቸው፣ የሀብት መሠረታቸው፣ እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው የደረቅ ወደብ፣ የአቪዬሽን፣ እና የባቡር ትራንስፖርት ማዕከላት እንዲሆኑ በረጅም ጊዜ ዕቅድ ማመላከት፣ በየደረጃው ወደ ተግባር ማሸጋገር፣
- ድህረ ምርት ብክነትን በዘመናዊ ክዘና መቀነስ
- በአስተሻሸግ ሥርዓት የንግድ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ እና
- በኢንሸንተሪ አገልግሎት ዋጋ ማረጋጋት ናቸው።

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

# ትምህርት

## 17.1. የትኩረት መነሻዎች

### ትምህርት ለምን?

1. ትምህርት በልዩ ሁኔታ እንዲታቀድ እና የተለየ የመንግሥት ትኩረት እንዲያገኝ የሚያደርጉ መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ፤

   - **የሕይወት ዘይቤ፤** እንደማናኛውም የዓለም አገራት ሁሉ በኢትዮጵያ እና በአማራ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት መዳረሻ ምንም ይሁን ምን ትምህርት ቤቶች ዜጎች ከመዋዕለ - ሕጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ፣ ከኮሌጅ እስከ ዩኒቨርሲቲ ባሉ ርከኖች ከዕለት ውሏቸው አብዛኛውን፣ ከዕድሜ ዘመናቸው ደግሞ ቀላል የማይባለውን ጊዜ እና የሕጻንነት፣ የወጣትነት፣ እና የአዋቂነት ዘመን የሕይወት ተሞክሮ የሚያሳልፉባቸው ተቋማት ናቸው። እነዚህ ተቋማት እንደ መማሪያ ቦታ ብቻ ሳይሆን ከቤት ቀጥሎ ለልጆች የተመቹ የመቆያ ስፍራዎች ማድረግ የተሻለ ኑሮ የመፍጠር አንድ አካል ነው።

   - **የዕውቀት ማሸጋገሪያ እና የፍትሃዊ ሀብት ክፍፍል ማረጋገጫ፤** ትምህርት ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ የዕውቀት ፈርጆች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገርበት፣ ወጣቶች በሕይወት ዘመናቸው ለሚመጥናቸው የሥራ መስክ እና ማሕበራዊ ስፍራ የገር እና የጠጣር ክህሎቶች (soft and hard skills) ማስጨበጫያ ሥርዓት ነው። በተለይ ማሽን የሰው ጉልበትን ብቻ ሳይሆን አስተሳብንም ጭምር በመተካት ላይ በሚገኝበት የዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘመን ትውልድ ካልተማረ ብቻ ሳይሆን በወሳኝ የትምህርት መስኮች ላይ አትኩሮ መወዳደር ካልቻለ ሥራ ማግኘት ጭምር አዳጋች ይሆናል። ለዚህም የሚመጥን የቴክኖሎጂ ዝግጁነት ማረጋገጥ የሚቻለው በትምህርት ሥርዓት ነው። ከዚህም ባለፈ ዜጎች እንደ ጥረታቸው መጠን ሀብት አፍርተው በፍትሃዊነት ሊኖሩ እንዲችሉ የሀብት መፍጠሪያ አቅምን በፍትሃዊነት ማዳረስ የሚቻለው በትምህርት ነው። በዚህም መሠረት፣ ትምህርት የእያንዳንዱን ዜጋ የኢኮኖሚ ደረጃ እና የማሕበራዊ ስፍራ (economic and social positions) የሚበየኑበት ሥርዓት ነው።

   - **የኢኮኖሚ እና የሥልጣኔ ተስተካካይነት ማረጋገጫ መሣሪያ፤** የኢኮኖሚ ተስተካካይነት የሚረጋገጠው በቴክኖሎጂ ተስተካካይነት መሆኑ እስከታመነ ድረስ የቴክኖሎጂ ዕውቀት በፍጥነት እና በስፋት መረጋገጥ የሚችለው በግብታዊነት እና በአጋጣሚ በተሳካላቸው ውስን ዜጎች ጥረት ይልቅ ቴክኒክን እና ለቴክኖሎጂ ፈጠራ መሠረት የሆኑ ሣይንሳዊ ሕግጋትን በትምህርት ሥርዓት ሕዝባዊ በማድረግ ነው። አገር ሲሰለጥን በሁለንተናዊ መመዘኛዎች ምን እንደሚመስል ከሩቅ አይቶ የስልጣኔ ተስተካካይነትን ማረጋገጥ የሚችል ትውልድ ማነጽ የሚቻለው በትምህርት ነው።

   - **የርትዕ ማሕበረሰብ መቅረጫ ተቋም/ሥርዓት፤** በዘመናዊ ማሕበረሰብ ውስጥ ትምህርት የቀጣዩ ትውልድ የሞራል ልዕልና፣ በተለይም የማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ፖለቲካዊ እሳቤ ደረጃ የሚቀረጽበት ሥርዓት ነው። የዕምነት ተቋማት፣ ማሕበረሰብ እና የሥራ ቦታዎች የትውልድ መቅረጫ ሥርዓታት አካል ናቸው። እነዚህን ተቋማት በምክንያት ተክቶ ትውልድ የመቅረጽ ኃላፊነት ያለበት የትምህርት ሥርዓት የርትዕ ማሕበረሰብ አምዶችን ሳይሸራርፍ ብቻ ሳይሆን በላቀ ደረጃ ማሸጋገር ይጠበቅበታል።

   - **ትልቅ ኢንዱስትሪ፤** መንግሥት ለትምህርት በሚመድበው በጀት፣ ወላጆች ለትምህርት በሚያወጡት ወጪ፣ የትምህርት ተቋማት በሚቀጥሩት የሰው ኃይል፣ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ለትምህርት ዘርፍ አምርቶ በሚያቀርባቸው ግብዓቶች ምክንያት ትምህርት ከኢኮኖሚ አንጻር አንድ ትልቅ ኢንዱስትሪ ነው። በገበያ ውስጥ ለሸቀጦች ጥራት የደረጃ ምደባ፣ ለመዲሃኒቶች የደህንነት ቁጥጥር፣ እና ለአንዳንድ ሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ከሚሰጠው ሥርዓት በላይ የሁሉም ነገር የጥራት ብቃት መሠረት በሆነው የትምህርት ኢንዱስትሪ ላይ የመንግሥት ሚና ወሳኝ ነው።

2. ትምሕርት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በየትኛውም ማሕበረሰብ ተተግባሪ ከሆኑት ፋይዳዎች በተጨማሪ በታዳጊ አገራት የተለይ ሚና ይጫወታል። ቅድመ - ኢንዱስትሪያላዊ ማሕበረሰብ ዛይንሳዊ አመለካከቶች እንዲያዳብር፣ ስለ ጤና አጠባበቅ፣ ስለ ዘመናዊ ሕክምና፣ ሥነ ተዋልዶ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው፣ ከሁሉም በላይ አገር ሲሰለጥን ምን እንደሚመስል ለማስተዋል እና ለለውጥ ለመትጋት ትምህርት ትልቅ መሣሪያ ነው። በሥነ ተዋልዶ ረገድ የቤተሰብ ምጣኔን በመጠቀም ያልተገራ የሕዝብ ብዛትን ለመገደብ ከመጣር በበለጠ ሴት ልጆች በትምሕርት ሁሉም ደረጃዎች እንዲያልፉ እና ለከፍተኛ ትምሕርት ማብቃት አንድ እንስት በሕይወት ዘመኗ ልትወልዳቸው የምትችለውን የልጆች መጠን በማዘግየት እና ትርጉም ባለው ደረጃ በመቀነስ የተሻለ ውጤት ያስገኛል። ዘላቂ የሴቶች ትምሕርት ለዘላቂ ዘመናዊ የሥራ ዕድል በር ስለሚከፍትም የቤተሰብ ምጣኔ በሴቶች የሥራ ፍላጎት ምክንያት ይስተካከላል።

## የአማራ ብሔራዊ ክልል የትምህርት ዘርፍ አፈጻጸም

3. ከ1988 እስከ 2015 በነበሩት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልል የትምህርት ሽፋን በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ፣ እና በሁለተኛ ደረጃ ትርጉም ባለው መጠን ጨምሯል። በትምሕርት ሚኒስቴር መረጃ መሠረት የክልሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ጥቅል ተሳትፎ በ2004 ከነበረበት በ2015 ወደ 55 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን ከአገር አቀፍ አፈጻጸም ጋር የተቀራረበ ነው። ይህ መርሃ ግብር የአፀደ ሕጻናት፣ የአቻ ለአቻ እና ማሕበረሰብ አቀፍ ትምህርትን የሚያካትት ነው። ከዚህ ውስጥ የክልሉ የመዋዕለ ሕጻናት የትምሕርት ሽፋን በ2015 የትምሕርት ዘመን 7.5 በመቶ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ምጣኔ ከአገር አቀፉ የ21.5 በመቶ ምጣኔ በጣም ያነሰ ነው።

4. ሠንጠረዥ 17-1፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት እና አጸደ ሕጻናት ጥቅል ተሳትፎ

| | **ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት** | | **አፀደ ሕጻናት** | |
|---|---|---|---|---|
| የትምሕርት ዓመት | አማራ ብ. ክልል | አገር አቀፍ | አማራ ብ. ክልል | አገር አቀፍ |
| 2004 | 15.5 (11.8) | 21.6 | 2.4 (2.2) | 5.3 |
| 2005 | 28.9 (22.1) | 26.1 | 2.5 (2.4) | 6.2 |
| 2006 | 41.9 (30.2) | 34.0 | 2.6 (2.4) | 6.6 |
| 2007 | 41.0 (38.8) | 39.0 | 2.0 (2.7) | 7.0 |
| 2008 | 52.3 (37.1) | 49.9 | 2.9 (2.8) | 8.0 |
| 2009 | 45.1 (37.0) | 45.9 | 2.9 (2.8) | 7.7 |
| 2010 | 46.6 (40.8) | 44.2 | 3.2 (3.1) | 8.6 |
| 2011 | 43.4 (38.4) | 40.7 | 3.7 (3.4) | 11.7 |
| 2012 | 41.9 (33.3) | 45.4 | 4.3 (3.8) | 10.4 |
| 2013 | 42.1 (32.5) | 36.7 | 4.2 (3.7) | 7.8 |
| 2014 | 45.8 (32.8) | 44 | 5.7 (4.8) | 11.1 |
| 2015 | 55 (38.3) | 50 | 7.5 (6.1) | 21.4 |
| 2016 | 55.5 | 57.8 | | |

ምንጭ፤ የኢፌዲሪ ትምሕርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የትምሕርት ስታትስቲክስ መጽሔት እና የአብክመ ትምሕርት ቢሮ
**ማስታዎሻ፤** በቅንፍ ውስጥ ያለው መረጃ ከአብክመ ትምሕርት ቢሮ የተገኘ ነው። የሁለቱ መረጃዎች ልዩነት የትምሕርት ሚኒስቴር እና የክልሉ ቢሮ የተጠቀሙበት የክልሉ የሥነ ሕዝብ መረጃ ምንጮች ልዩነት የፈጠረው ነው።

5. የአንደኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ (1 – 8) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ1988 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 22.3 በመቶ በ2007 በክልሉ ስሌት መሠረት ወደ 92.1 በመቶ አድጎ የነበረ ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን ወደ 69.3 በመቶ ወርዷል። ከ1988 እስከ 2004 ድረስ የክልሉ የአንደኛ ደረጃ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ከአገር አቀፉ ምጣኔ ያነሰ ቢሆንም ተቀራራቢ ነበር። ነገር ግን ከ2010 የትምህርት ዘመን በኋላ የክልሉ የትምሕርት ተሳትፎ ምጣኔ እየቀነሰ በመሄዱ በ2004 የትምሕርት ዘመን 3.5 የመቶኛ ነጥብ የነበረው ልዩነት በ2015 ወደ 27.6 የመቶኛ ነጥብ ሰፍቷል።

6. ስዕል 17-1፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (1 – 8) ጥቅል ተሳትፎ




ምንጭ፤ የአብክመ የትምሕርት ቢሮ እና የኢፌዲሪ የትምሕርት ሚኒስቴር መረጃዎችን በመጠቀም የተዘጋጀ

7. በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ1988 የትምሕርት ዘመን ከነበረበት 5.9 በመቶ በ2013 የትምህርት ዘመን 49.5 በመቶ ደርሶ ነበር። ነገር ግን፣ በክልሉ የትምሕርት ቢሮ ስሌት መሠረት በ2015 የትምህርት ዘመን ይህ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ወደ 38 በመቶ ወርዷል። በትምሕርት ሚኒስቴር መረጃ መሠረት የ2015 እና የ2016 የክልሉ የሁለተኛ ደረጃ የትምሕርት ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 56.2 በመቶ እና 50.4 በመቶ ናቸው።

8. ስዕል 17-2፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ




9. በአጠቃላይ በአለፉት አሥር ዓመታት የክልሉ አንደኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ጥቅል ተሳትፎ አበረታች፣ ነገር ግን ከአገር አቀፉ አማካይ ያነሰ ነበር። በተመሳሳይ ወቅት የክልሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ከአገር አቀፍ አማካይ ይልቅ ነበር። ነገር ግን በአለፉት ሦስት ዓመታት አፈጻጸም የሸፋን መቀነስ የታየበት ሲሆን አንዱ እና ዋናው ምክንያት በክልሉ የተከሰተው ግጭት ነው።

10. ከአስተዳደራዊ መረጃዎች በተጨማሪ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 ብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል እና ፍልሰት ዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው 3 ዓመት እና በላይ ዕድሜ ካለው የክልሉ ሕዝብ መካከል 21.5 ሚሊዮን ሕዝብ መካከል 50.8 በመቶ የሚሆነው ከማይምነት ነጻ ነው። ከ25 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ካለው

ሕዝብ ውስጥ 36.8 በመቶ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣ 7 በመቶ የሚሆነው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ 4.3 በመቶ የሚሆነው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በላይ ተሳትፎ ያለው ነው። የአገር አቀፉ ከማይምነት ነጻ የሆነ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በላይ ተሳትፎ ያለው ሕዝብ ምጣኔ አንደ ቅደም ተከተሉ 49.2 በመቶ፣ 38.7 በመቶ፣ 7.7 በመቶ፣ እና 4.4 በመቶ ናቸው።

11. የክልሉም ሆነ የአገሪቷ የዘርፉ የተሳትፎ አፈጻጸም ከሌሎች አገራት ጋር ሲነጻጸር በአፍሪካ ደረጃ እንኳ ዝቅተኛ ነው። በአንጻራዊነት ዝቅተኛ አፈጻጸም ኖሮትም የሚጣረሱ የሚመስሉ የከፍተኛ የተማረ የሰው ኃይል ሥራ አጥነት በአንድ በኩል፣ በከተማም ሆነ በገጠር ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በሌላ በኩል ይስተዋላል። በአገርም ሆነ በክልል ደረጃ የትምሕርት ጥራት መቀነስ የዘርፉ ትልቅ ሥጋት ሆኗል።

12. በአጠቃላይ በትምህርት እና ስልጠና ረገድ በ1980ዎቹ አጋማሽ ከነበረበት የሽፋን ደረጃ አንጻር በአሁኑ ወቅት የተሻለ አፈጻጸም ቢኖረውም መደረስ ከነበረበት የሽፋን ግብ አኳያ በተለይ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት እና በሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት አፈጻጸሞቹ አጥጋቢ አይደሉም። የአለፉት አራት ዓመታት ዝቅተኛ የትምሕርት ዘርፍ አፈጻጸም እንደ ሌሎች ዘርፎች አፈጻጸም ሁሉ በወቅቱ ከደረሱ ተደጋጋሚ ደፋቂ ኩነቶች በተለይም ከኮቪድ -19 ወረርሽኝ እና ከጦርነት ክስተቶች ጋር የተያያዙ መሆናቸው ግልጽ ነው። ነገር ግን የአፀደ ሕጻናት ትምሕርት ተሳትፎ ከግጭት በፊትም ዝቅተኛ አፈጻጸም ማሳየቱ ሕጻናትን ቀድሞ ማነጽ እና መቅረጽ ትኩረት እንዳልተሰተው አመላካች ነው። ከግጭት ክስተት በፊትም ለሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ተሳትፎ በተጠበቀው ልክ አለማደግ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት እንደ ምክንያትነት ቢጠቀስም ከመጀመሪያ ደረጃ ትምሕርት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ያለው የተማሪዎች ሽግግር የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች በሚገኙበት ሁኔታ ጭምር ዝቅተኛ መሆኑ፣ ወይም የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔ ከፍተኛ መሆኑ፣ እና የመድገም ምጣኔ እየጨመረ መምጣቱ ለትምሕርት ሽፋን ግብ አለመሳካት ከአቅርቦት በላይ ሌሎች መሠረታዊ ምክንያቶች እንዳሉ አመላካች ነው።

13. ከትምሕርት ሽፋን የሚልቀው አሳሳቢ ጉዳይ የትምሕርት ጥራት መጓደል ነው። በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ እየተስተዋለ ላለው የትምሕርት ጥራት መጓደል የግብዓት አቅርቦት ብቃት እና ጥራት መጓደል፣ ተገቢ እና ምቹ ባልሆነ ሥርዓተ ትምሕርት፣ እና በትምሕርት አስተዳደር ችግር እንደሆነ ይታመናል። ነገር ግን እነዚህ ቅርብ እና ለረጅም ዘመን የሚነሱ ምክንያቶች ምክንያት ናቸው።

14. በትምህርት ዘርፍ ሊነሱ የሚገባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች

    1. ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ7ኛው ክፈለ ዘመን ፊደላትን በማጥናት የጀመረችው፣ በክርስትና እና በእስልምና ዕምነቶች አሻሽላ የቀጠለችው እና በዳግማዊ አጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ማዘመን በጀመረችው ትምህርት ዛሬ ድረስ ስለምን በሽፋን ረገድ የሚዋዥቅ አፈጻጸም አሳየ?
    2. በአፍሪካ ደረጃ ዝቅተኛ የትምህርት ሽፋን ባለበት የኢትዮጵያ ሁኔታ የተማረ ሥራ አጥነት ስለምን ነገሰ?
    3. የተቀጠረው የተማረ ኃይል ስለምን በተማረው ትምህርት እና ክሕሎት ትርጉም ባለው ደረጃ ችግር መፍታት አቃተው፤ የጥራት መጓደልስ እንዴት ተፈጠረ?

15. በጥናት መዳበር እንዳለባቸው ታሳቢ በማድረግ ከሽፋን ዝቅተኛ መሆን በምክንያትነት ሊነሱ የሚችሉት ጉዳዮች ትምህርትን ለማስፋፋት ከክልላዊ እና አገራዊ ውስን የሀብት አቅም በላይ የማሕበረሰቡ በተለይም የገጠር ማሕበረሰብ ትምህርትን ከኋላቀርነት መላቀቂያ እና የችግር መፍቻ አድርጎ ያለመውሰድ፣ ለትምህርት ከልብ የመነጨ ፍላጎት አለመኖር ተጠቃሽ ነው። የአማራ ብሔራዊ መንግሥት ከፍተኛውን በጀት የሚመድበው ለትምህርት ሆኖ ሳለ ከፍተኛ የትምህርት ማቋረጥ ምጣኔ እና አጠቃላይ የሽፋን መቀነስ ከብዙ መገለጫዎች መካከል የፍላጎት ችግር ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

16. የተማረውን በቅጡ መቅጠር ያቃተበት ትልቁ ምክንያት የኢኮኖሚ መዋቅሩ በአንስተኛ ባለይዞታ ግብርና ላይ የተመሠረተ በመሆኑ እንደ አምራች ኢንዱስትሪ እና ዘመናዊ አገልግሎት ያሉ ዘርፎች የመቅጠር አቅም ውስን መሆን ነው። በአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሰው ኃይል ድርሻ በ2013 ከ3.3 በመቶ ያልበለጠ ነው።

17. የተቀጠረው ኃይል በአብዛኛው ከተግባር ጋር ያልተቆራኘ የመሆኑ ምስጢር ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እንደ ችግር ይነሳ የነበረው የጥራት ችግር ነው። መማር የግድ ለውጥ አያመጣም፤ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት ከደቡብ ምሥራቅ ኤሲያ አገራት የሚስተካከል የትምህርት ሽፋን ነበራቸው። ነገር ግን ትምህርት የመስፋፋቱን ያህል በኢኮኖሚ ዕድገት መግፋት አልቻሉም። ለዚህ ምክንያቱ የትምህርት የዘርፍ ስምሪት፣ የተማረ የሰው ኃይልን የሚያለማምድ፣ የሚቀጥር እና የሚያበቃ የኢኮኖሚ መዋቅር አልፈጠሩም።

18. በኢትዮጵያ የደቡብ ምሥራቅ አፍሪካ አገራትን ተሞክሮ በመውሰድ 70 በመቶ የከፍተኛ ትምህርት ቅበላን ለሳይንስ እና ምህንድስና ትምህርት እንዲሁም መወሰኑ እና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች መስፋፋታቸው ችግሩን አልቀረፈውም። የዚህ መሠረታዊ ችግሮች ሁለት ናቸው፤ ከማስፋፋት ግብ ጋር የሚጋጭ የጥራት ችግር፣ እና የኢኮኖሚ መዋቅር ለተማረ የሰው ኃይል የሚጋብዝ አለመሆን።

## የዘርፉ ተግዳሮቶች መገለጫዎች፤ የትምህርት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ

## አጠቃላይ እይታ

19. ልጆች ምን መማር እና ማወቅ እናዳለባቸው፣ ይህን ትምሕርት የት እና እንዴት እንደሚማሩት ዛሬ ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች የቀጣዩን ትውልድ የዕውቀት፣ የዕድገት፣ የማሕበራዊ ርትዕነት ደረጃ በእጅጉ ይወስናሉ። እነዚህ ውሳኔዎች በድምሩ አገር በዘርፉ ያፈሰሰችውን ሀብት አዋጭነት እና የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ውጤቶችን፣በአጠቃላይ በዓለም መድረክ የሚኖርን የአገር ደረጃ ይበይናሉ። በዚህም የትምህርት ሥርዓት አወቃቀር፣ አደረጃጀት፣ እና የሀብት ስርጭት ወይም አጠቃቀም የማሕበረሰብን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ደረጃ እና በአንድ አገር ውስጥ የሚኖርን የኃይል ተሳትፎ ሚዛን ይበይናል።

20. **የትምህርት ሥርዓት እንደ ምርት ሥርዓት** (Education production function)፤ ትምህርት እንደ ምርት ይመረታል፣ ይሰራጫል፣ ጥቅም ላይ ይውላል። በማምረት ሂደት ትምህርት ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ግብአቶችን ይፈልጋል። ዕውቀትን ከምር ፈልጎ ለሚመጣ ተማሪ የትምህርት ጥራት በዋናነት በእነዚህ ግብዓቶች ይወሰናል። ትምህርት እንደ ፍጆታ በማሕበረሰብ በተለይም በግለሰብ፣ በቢዝነስ፣ በመንግሥት እና በአገራት ይፈለጋል። እነዚህ ፍላጎቶች በኢንቨስትመንት፣ በማምረት እና በግብዓትነት ይገለጻሉ። የትምህርት ስርጭት ከፍላጎት እና አቅርቦት መስተጋብር ውጤትነት ባለፈ በመንግሥት የገበያ ስብራትን የማስተካከል እና ልማታዊ ሚና ይወሰናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎች ይነሳሉ፤

1. የትምህርት ቁሳዊ ወጪ፣ ስነ ልቦናዊ ጫና፣ እና የአማራጭ ምርጫ ወጪ (opportunity cost) ከፍተኛ ሆኖ ሳለ ማሕበረሰብ ለምን መማርን እና ማስተማርን ይመርጣል?
2. የትምህርት እሴቶች እንዴት ይፈጠሩ፣ እንዴት ይሰራጩ?
3. የፖለቲካ ሥርዓት ከትምህርት ጋር የተያያዙ የማሕበረሰብ ፍላጎቶች እና ግቦችን እንዴት ወደተጨባጭ ውጤቶች ይቀይራል?

21. **የትምህርት ሥርዓት ወሳኝ አካላት፤** ከተማሪዎች ተሳትፎ እስከ የመንግሥት የትምህርት አቅርቦት በሚደርሱ ሰፊ የትምህርት ሥርዓት ጉዳይ በዋናነት ሦስት ወይም አራት አካላት ይወስናሉ፤ የማሕበረሰብ መዋቅር (social structure)፣ ወላጅ (እና ተማሪ)፣ እንዲሁም መንግሥት። ወላጅ እና ተማሪ የትምህርት ፍላጎትን፣ መንግሥት የትምህርት ፍላጎትን እና አቅርቦትን፣ የማሕበረሰብ ተወካይ ቡድኖች ደግሞ በትምህርት ሥርዓት እንዲካተቱ የወል ፍላጎቶች እና አቅርቦትን ይወክላሉ።

22. **የወላጅ** (agents) **የትምህርት ውሳኔዎች፤** ወላጅ እንደ ግለሰብ ለትምህርት የሚያወጣውን ወጪ ግምት ውስጥ በማስገባት **የትምህርት ፍላጎትን** የሚወስኑ ስለልጁ ትምህርት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ (economic return) እና ማሕበራዊ ፋይዳ (social retun) የሚመለከቱ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል። በኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ረገድ የሚጠበቅ የተጣራ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም (expected net return to education)፣ በማሕበራዊ ጥቅም በኩል የራስ የሚላቸው መልካም እሴቶች እና ማሕበራዊ ደረጃ (social status) ናቸው።

23. **የመንግሥት የትምህርት ሚናዎች፤** በትምህርት ጉዳይ መንግሥት በፍላጎት እና በአቅርቦት በኩል ይሳተፋል። በፍላጎት ረገድ የመንግሥት ለትምህርት ያለው ቀጥተኛ ፍላጎት ለመንግሥት ዘርፍ በተለይም ለሲቪል ሰርቪስ የሚሆን የሰው ኃይል ነው። ትምህርት በግል ሊሰጥ የሚችል አገልግሎት ቢሆንም ሊሰጥ ከሚችለው ሰፊ

ማሕበራዊ ፋይዳ በመነሳት በትምህርት አቅርቦት ላይ መንግሥት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ (በፖሊሲ አማካይነት) ይሳተፋል፤ ይወስናል። መንግሥት ትምህርት ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን እንዲያሳካለት ይፈልጋል፤ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል። የኢኮኖሚ ዕድገት አንዱ ምንጭ ሰብዓዊ ካፒታል ሲሆን ይህም በትምህርት ላይ ይመሠረታል። ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል በተፈጠረ ሀብት መጠን እና ትምህርትን በፍትሃዊነት ተደራሽ በማድረግ ይረጋገጣል። በጥቅሉ የመንግሥት የትምህርት አቅርቦት ውሳኔ ባለው ሀብት መጠን፣ በታቀደ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እና በማሕበራዊ ግቦች ላይ ይመሠረታል።

24. **የተማሪ ውስጣዊ የትምህርት ፍላጎት** (implicit demand for education) **እና ተጽዕኖው፤** የተማሪው የትምህርት ፍላጎት ውሳኔ እንደ የትምህርት ደረጃው ይለያያል። በመጀመሪያዎቹ የሕጻንነት የተሳትፎ ዓመታት የትጋት ደረጃዎች የውስጥ ተሰጥዖን በማውጣት ረገድ በወላጅ እና በመምህራን በሚደረጉ ጥረቶች ይወሰናል። በመካከለኛ እና በአብዛኛው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወቅት የሚኖረው የተማሪዎቹ የትምህርት ዕውነተኛ ፍላጎት በትጋት የሚገለጽ ውስጣዊ ፍላጎት ሲሆን ይህም በሚጠበቅ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እና የሥነ ልቦና ጫና (psychological cost) ይወሰናል። ይህ ከተሳትፎ የሚልቅ ውስጣዊ ፍላጎት በትምህርት ጥራት ላይ እንደምታ አለው።

25. **የማሕበረሰብ የትምህርት ሥርዓት ሚና፤** በማሕበረሰብ ስም የሚጠየቁ ከእምነት፣ ማንነት እና ቋንቋ ጋር የሚያያዙ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲመለሱ የሚጠበቁ ጉዳዮች አሉ። እነዚህ ጉዳዮች ከእምነት ተቋማት እስከ ፖለቲካ ቡድኖች በሚደርሱ ኃይሎች አስተባባሪነት እና ግፊት በልጆቻቸው ትምህርት ተሳትፎ ላይ የሚወስኑ ወላጆች በፍላጎት በኩል፣ እንዲሁም ፍላጎቶችን የማቀራረብ ኃላፊነት የተሰጠው መንግሥት በአቅርቦት በኩል የቡድን መብት ጥያቄዎችን ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ይደረጋሉ። እነዚህ ውሳኔዎች በተማሪዎች ውስጣዊ የትምህርት ፍላጎት እና ምርጫዎች፣ እንዲሁም ከታቀደ ግብ አኳያ የሚመዘን ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

26. **የትምህርት ወሳኝ አካላት መስተጋብር እና ውጤቱ፤** የትምህርት ዕውነተኛ ፍላጎቶች እና አቅርቦቶች ለተማረ እና ለሰለጠነ የሰው ኃይል በሚኖር አቅርቦት እና ፍላጎት በሥራተኛ ገበያ (labor market) ላይ ይበየናል። በገበያ ውድድር እሳቤ የግሉ ዘርፍ የተማረ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚፈልግ ሲሆን በዋናነት የኢኮኖሚ መዋቅሩ እና የሚፈጥረው የሥራ ዕድል ምርታማነትን፣ የምንዳዕ መዋቅርን፣ እና የማህበረሰብ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራት ውሳኔዎችን በውጤቱም የክትመት ደረጃን ሳይቀር ይበይናሉ። ግለሰቦች የአንድን አገራዊ የኢኮኖሚ መዋቅር የመቀየር አቅሙ እንደሌላቸው ስለሚገነዘቡ በጊዜው ያለው የኢኮኖሚ መዋቅር የሚፈልገውን በስልጠና መስክ፣ በትምህርት ቆይታ፣ እና ክህሎት የሚገለጹ ዝግጅትን የሚመርጡ ሲሆን፣ በቴክኖሎጂ፣ በቁሳዊ ካፒታል፣ እና በሰብዓዊ ካፒታል አጠቃቀም ደረጃ የሚወሰነው የኢኮኖሚ መዋቅር የትምህርትን እሴት ወይም ፋይዳ ይበይናል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የትምህርት አቅርቦት እና ፍላጎት ከተመጣጠነ፣ በአደጉ አገራት ሌላ ቴክኖሎጂ ዘመም ፍላጎት እስካላደፈረሰው ድረስ የከፍተኛ ገቢ ኢኮኖሚ መመጣጠን ነጸብራቅ ሆኖ ሲቀጥል፣ በታዳጊ አገራት ለውጥ ፈላጊ ኃይል እስካላደፈረው ድረስ የአነስተኛ ገቢ ኢኮኖሚ መመጣጠን ነጸብራቅ ሆኖ ይቀጥላል።

27. እነዚህ በውድድር ኢኮኖሚ እሳቤዎች ላይ የቆሙ መመጣጠኖች በአደጉ አገራት እና ዝቅተኛ ገቢ በአላቸው አገራት የተሻለ የዕድገት ፍላጎት የመቀየር ዕጣ ይገጥማቸዋል። ነገር ግን ከእነዚህ ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣሙ ወይም የሚጣረሱ የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚ ውሳኔዎች፣ እና ማሕበረሰብን በሚወክሉ ቡድኖች የሚቀርቡ የጋራ ፍላጎቶች የመኖራቸው እውነታ ትምህርት ለለውጥ የሚኖረውን ፋይዳ ቀጥተኛ እና ተተግባሪ እናዳይሆን ያደርገዋል።

28. የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እና የፖለቲካ ኃይል ግንኙነቶች ውጤት የሆነው የማሕበረሰብ መዋቅር (social structure) ግምት ውስጥ ሲገባ የግለሰቦች የትምህርት ምርጫ እና በኢኮኖሚው እና ማሕበራዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ግለሰቦች በማሕበራዊ መዋቅሩ ባላቸው ደረጃ እና ቦታ ይወሰናል። ትምህርት በግለሰቦች ምርጫ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የዕምነት ተሰሚነት ባላቸው ኃይሎች ተጽዕኖ ሊወሰን ይችላል። ትምህርት እንደ ተቋም በማሕበረሰብ ማሕበረ - ኢኮኖሚ ግንኙነቶች ላይ እንደመመሥረቱ መጠን በውጤቱ እነዚህን መዋቅሮች ለማስቀጠል መሣሪያ ይሆናል።

29. ግለሰቦች በመንግሥት የማዳረስ ግብ እና በፖለቲካ ተጽዕኖ የማቻቻል ፍላጎቶችን በመቃወም ሌላ አማራጮችን ይፈልጋሉ። በተለይ በታዳጊ አገራት የውጭ ገበያን ታሳቢ ያደረጉ የግል ትምህርት ቤቶችን እስከ ማቋቋም እና በውጭ አገር ትምህርት ቤቶች ልኮ እስከማስተማር የሚደርስ ውሳኔ ይወስዳሉ። በዚህ ሁኔታ አገር ከትምህርት ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ልታጣ ትችላለች።

## የኢትዮጵያ/የአማራ ብሔራዊ ክልል የቅርብ ዘመን የትምሕርት ሁኔታ

30. ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ከአንድ ምዕተ ዓመት የዘለለ ዕድሜ አለው። ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በየሥርዓት ለውጡ የትምህርት ፖሊሲ ለውጦች ተደርገዋል። በትምህርት ሥርዓት ላይ የሚደረጉ የፖሊሲ ለውጦች ውጤታቸው መታየት የሚጀምረው እስከ አንድ ትውልድ ዕድሜ ዘግይቶ በመሆኑ የቅርብ የትምህርት ዘርፍ ውጤቶች ያለፉ የፖሊሲ ለውጦች ያስከተሏቸው ድምር ውጤቶች ናቸው። የኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ ወደ ተግባር ከገባ የአንድ ትውልድ ዕድሜ አሳልፏል። በየወቅቱ የተተገበሩ ዋና ዋና የትምህርት ፖሊሲ ለውጦች ሁሉም ህጻናት የመማር እድል ማግኘት ግዴታ መሆኑ፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ መደረጉ፣ እስከ አራተኛ ክፍል ድረሰ የአንድ መምህር (ሰልፍ ኮንቴይንድ) ሥርዓት መከተሉ እና ተማሪዎች እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ክፍሎችን ያለፈተና እንዲያልፉ መደረጉ፣ ስድስተኛ ክፍል ላይ ይሰጥ የነበረው የአንደኛ ደረጃ ብሔራዊ የምዘና ፈተና እንዲቀር መደረጉ፣ ወደ ዩኒቨርሲቱ የሚገቡ እና ወደ ቴክኒክ ትምህርት ቤቶች የሚገቡ ተማሪዎች ከ10ኛ ክፍል የሚለዩበት የብሔራዊ ፈተና መጀመሩ፣ የተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ምደባ እና የትምህርት መስክ ምርጫን በውጤት ከማስጠበቅ ይልቅ በእጣ መደልደል መጀመሩ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአንደኛ ዓመት መርሃ ግብር ይሰጡ የነበሩ የትምህርት ሽፋኖች እና ጥልቀቶች ወደ ሁለተኛ ደረጃ እንዲወርዱ እና የከፍተኛ ትምህርት የዲግሪ መርሃ ግብር የትምህርት ቆይታ በአንድ ዓመት እንዲቀንስ መደረጉ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የአንድ ለአምሥት አደረጃጀት መተግበሩ፣ በመጨረሻም 70 በመቶ የሚሆነው የከፍተኛ ትምህርት ቅበላ ለሳይንስ እና ምህንዲስና ዘርፎች እንዲሆን መደረጉን ያካትታሉ።

31. የእነዚህ የፖሊሲ ለውጦች መነሻ የየራሳቸው አመክንዮ ሊኖራቸው ቢችልም በዘርፉ አፈጻጸም ላይ ያስከተሏቸው ለውጦች እና ከሌሎች የዘርፍ አፈጻጸሞች እና ከማሕበረ ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በነበራቸው መስተጋብር በጋራ ያስከተሏቸው ውጤቶች ቢያንስ ሦስት መሠረታዊ ውጤቶችን አስከትለዋል፤
    1. ከአብዛኛው የዓለም አገራት በታች የሆነ የትምህርት ሽፋን፣
    2. ከፍተኛ የሆነ የተማረ ሥራ አጥነት ምጣኔ፣ እና
    3. የትምህርት የጥራት መጓደል።

32. የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ለዓመታት ወጣ ገባ መሆን እና በተለይ በገጠሩ አካባቢ የመንግሥትን ጉትጎታ የሚጠይቅ መሆኑ ትምህርትን እንደ አዋጭ ኢንቨስትመንት በወጥነት ያለመውሰድ አመለካከት እንዳለ ያሳያል። ይህ ሁኔታ ትምህርትን በማቋረጥ ወደ ትዳር በመግባት የቤት እመቤት መሆን፣ ይፋ ባልሆኑ የሥራ መስኮች መሰማራት፣ ወደ ውጪ አገር መፍለስ፣ እና ሥራ አጥ ሆኖ መኖር በመሳሰሉት ምርጫዎች ይገለጻል። ለዚህ ክስተት አንዱ ምክንያት ቀጥሎ የሚቀርበው የኢኮኖሚ መዋቅሩ የተማረ የሰው ኃይልን በበቂ ሁኔታ ማስተናገድ አለመቻል የፈጠረው በትምህርት ተስፋ ያለማድረግ ዝንባሌ ነው።

33. የመንግሥት የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት እና የኢኮኖሚ መዋቅሩ (የግሉ ዘርፍ) የሰው ኃይል ፍላጎት አለመጣጣም የተማረ ሥራ አጥ ፈጥሯል። የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት በፖሊሲ በተመላከቱ የመዋቅራዊ ለውጥ ግቦች ሊወሰን ይችላል። መንግሥት በሚጠበቀው የመዋቅራዊ ለውጥ እና የኢኮኖሚ ዕድገት ልክ በትምህርት ሥርዓቱ ቢያዘጋጅም የግሉ ዘርፍ ፍላጎት ለተወሰኑ መለስተኛ ሙያዎች ብቻ የሚበቃ በአብዛኛው በመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች (primary economic activities) ላይ ያተኮረ በሚሆንበት ጊዜ ለሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች (secondary, tertiary, and quaternary economic activities) የተዘጋጀ፣ ነገር ግን የውጭ አገር ገበያን ታሳቢ ያላደረገ የተማረ የሰው ኃይል ሥራ አጥ ይሆናል።

34. የከተማ ወላጅ ማሕበረሰብ የልጆቻቸውን ማሕበራዊ ስፍራ የሚበይኑበት ፍልስፍና ለከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት አነሳሽ የመሆኑን ያህል በሥራ ምርጫ ላይ አሉታዊ ጫና አሳድሯል። ልጅ ተምሮ ኮሌጅ በመግባት ለራሱ፣ ለቤተሰቡ እና ለአገሩ መጥቀም እንደሚኖርበት እና ሊደርስባቸው የሚገቡት መስኮች ጭምር በሕክምና፣ በምህንዲስና፣ እና በአውሮፕላን አብራሪነት ተወስነው ይነገራሉ። ይህ የወላጅ የትምህርት ፍልስፍና በውጭ ታላላቅ ዩኒቨርስቲዎች ሳይቀር ተወዳዳሪ መሆን የቻሉ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች እንዲፈጠሩ አስችሏል። ነገር ግን በሌላ መልኩ ይህ ፍልስፍና ተግዳሮትም ሆኖ ይታያል። በመጀመሪያ ደረጃ ዩኒቨርሲቲ ያልገባ እና

በመንግሥት ያልተቀጠረ ዜጋ ለትምህርት ያወጣው ጊዜ እና ወጪ እንደባከነ ይቆጠራል፤ በብዛትም ሥራ አጥ ሆኖ ይቀጥላል። እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ትምህርት ችግር መፍታት የሚያስችል ዕውቀት መቅሰሚያ ሳይሆን ለቅጥር በተለይም ለመንግሥት ኃላፊነት የሚያበቃ ሂደት ተደርጎ የመወሰዱ ዕውነታ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለኮሌጅ መግቢያ ፈተና ያልደረሱ የአንደኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሳይቀሩ ራስን በተማረ ሰብዕና ውስጥ አስገብተው በአካባቢያቸው የሚገኙ እንደ ግብርና እና ከፊል የጉልበት ሥራዎችን ንቀው ሥራ አጥ ይሆናሉ። ይህ ክስተት በእድሜ የገፉ አባቶች ብቻ ከሥራ ጋር በሚታገሉበት የግብርና ዘርፍ በመጀመሪያ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሚለካ ዕውቀት የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን የሚንቅ፣ ነገር ግን ለከፍተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ያልበቃ አጉል ትውልድ ፈጥሯል።

35. ከከፍተኛ ትምህርት የተመረቁ ወጣቶች ለከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የመንግሥት ሥራዎች እና ውስን የፋይናንስ ዘርፎች ካልሆነ በስተቀር ለትምህርት ዝግጅታቸው በሚመጥን ምንዳዕ እና ደመወዝ ሊቀጥራቸው የሚችል የኢኮኖሚ መዋቅር ስላልተፈጠረ የሙያ እና ሥራ እድል አለመጣጣም ጭምር የፈጠረው ሥራ አጥነት እንዲስፋፋ ሆኗል። በተለይም ለሣይንስ እና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በብዛት ቢያሰለጥኑም የግሉ ዘርፍ ይህን የተማረ ኃይል መቀጠር የሚችል የኢኮኖሚ መዋቅር አላረጋገጠም። ለማሳያ ያህል በአብዛኛው መሃንዲሶችን እና የቴክኒክ ምሩቃንን ሊቀጥር ይችል የነበረው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከአጠቃላይ ክልላዊ እና አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በክልል ደረጃ ከ8 በመቶ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ከ7 በመቶ ያልበለጠ ነው። በሰው ኃይል ቅጥር ድርሻም በ2013 የአማራ ብሔራዊ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ድርሻ 3.3 በመቶ ብቻ ነበር።

36. የትምህርት ጥራት ዋናው የሰብዓዊ ካፒታል አምድ ሲሆን ከብዙ አቅጣጫዎች ችግር ውስጥ ገብቷል። የመጀመሪያው ምክንያት በውስን ሀብት ትምህርትን በስፋት የማደረስ ግብ የፈጠረው ነው። የመንግሥት ትምህርት አቅርቦት ውሳኔዎችን ከሚበይኑ ጉዳዮች አንዱ የትምህርት ወጪን ለመሸፈን የሚያስችል ሀብት ነው። ሙሉ በሙሉ በተደራጁ በቂ ትምህርት ቤቶች፣ በተሟሉ የትምህርት ቁሳቁሶች፣ እና በተሟሉ ብቁ የሆኑ፣ ጥራት እና ተነሳሽነት ያላቸው ደስተኛ መምህራን ሁሉንም ለትምህርት የደረሰ ዜጋ ለማስተማር ከሀብት አንጻር ለአንድ ታዳጊ አገር አዳጋች በመሆኑ ምርጫው አንድም ከሽፋን ይልቅ ለጥራት ቅድሚያ መስጠት፣ ወይም ሁሉንም ለትምህርት የደረሰ ዜጋ ተደራሽ አድርጎ የጥራትን ችግር ማስታመም ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልልን ጨምሮ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ኢትዮጵያ ካላት ሕዝብ ብዛት እና የመልማት ፍላጎት አንጻር የተማረ የሰው ኃይል በቂ እንዳልሆነ ቢገመትም ካላት የኢኮኖሚ አቅም እና መዋቅር አንጻር ከጥራት ይልቅ ለሽፋን ያደላ ፖሊሲ ስትከተል ቆይታለች።

37. ለትምህርት ጥራት መጓደል ሁለተኛው ምክንያት በተማረ ሥራ አጥነት እና ዝቅተኛ ምንዳዕ ምክንያት ተማሪዎች ትምህርትን እንደ ጊዜ ማሳለፊያ መውሰዳቸው እና ጥራት የሚፈልገውን ትጋት እና ጠንክሮ መሥራት ችላ ማለታቸው ነው። ከዚህ አንጻር ጥቂት ለትምህርት ዓለም አቀፋዊ ግብ ሰጥተው የሚተጉ እና በአብዛኛው በግል እና በልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ወጣቶች የውጭ ዩኒቨርሲቲዎችን እና ሲመረቁም የውጭ አገር ገበያዎችን የሚያልሙ ናቸው። በትምህርት ረገድ ጥራት ያለው ትውልድ ከላይ ከላዩ ወደ ባዕድ አገር በፈለሰ ቁጥር የቀጣዩ ትውልዶች የትምህርት ጥራት በተከታታይ እየቀነሰ እንዲመጣ ያደርጋል።

38. ሌላው ከትምህርት ጥራት ጋር የሚያያዘው ጉዳይ ከማሕበረሰብ የቡድን ፍላጎት ውስጥ የተያያዙ የርዕዮተ ዓለም፣ የእምነት እና በራስ ቋንቋ የመማር የማንነት ፍላጎቶች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ መንጸባረቅ የፈጠሯቸው ተግዳሮቶች ናቸው። ወላጅ ማሕበረሰብ በገቢ አቅም፣ በማሕበራዊ እሴት፣ እና በማሕበራዊ ደረጃ ፍላጎቶቹ ወጥ ባለመሆናቸው መንግሥት በትምህርት አቅርቦት ላይ እነዚህን የፍላጎት መሠረቶች የማጣጣም ኃላፊነት ይወድቅበታል። እምነት ነክ ሥርዓታት ወጣቱ ፍልስፍናን አስቀድሞ እንዳይመራመር ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲደርስ የዕምነት አቋም ሸብቦታል። ሃይማኖታዊ እምነትን በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ሲጸረር የነበረው የደርግ መንግሥት ሲወድቅ በስፋት የተስተዋለው ማሕበረሰባዊ ክስተት በእምነት መትጋት ነው። በተለይም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ፉክክር በሚታይበት ሁኔታ የተማሪዎች በሃይማኖታዊ ዕምነት ልምምዶች ውስጥ ማለፍ ፍልስፍናን እና ሳይንሳዊ ምርምርን የምር እንዳይኖሩት ከማድረግ አልፎ በሥራ ዘመናቸው ሴኩዩላሪዝምን ከማስፈን ይልቅ የዕምነት ወገንተኝነት እንዲጫጫናቸው በር ከፍቷል።

39. ሌላው የማሕበረሰብ ቡድን ተጽዕኖ የቋንቋ እና ማንነት ፍላጎቶች ወጥ ሳይንሳዊ ቋንቋ እንዳይኖር ገድቧል። በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ጥቅም እንዳለው የዘርፉ ምሁራን የሚናገሩ ቢሆንም በተግባር ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጀምረው በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ሳይንሳዊ እና የቴክኖሊጂ ቋንቋ በመሆነው እንግሊዝኛ መሸጋገር ከፍተኛ መዝግየትን ይፈጥራል። በውጤቱም ከሳይንሱ ይልቅ ለቋንቋው በሚባክን ጊዜ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ይቀንሳል። በዚህም ምክንያት አቅም ያላቸው ወላጆች ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ የግል ትምህርት ቤቶች በማስገባት ልጆቻቸውን ለውጭ ገበያ ያመቻቻሉ።

40. በመጨረሻ የመንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ የትምህርት ተወዳዳሪነትን ገድቧል። ትምህርት በተፈጥሮው ውድድርን ይጠይቃል። ተመሳሳይ የትምህርት ዕድል ሰጥቶ ተመሳሳይ ምርት አይገኝም። ጥቂት ሃሳብ አፍላቂዎች፣ በርካታ አማካይ ተማሪ፣ እና ቀላል የማይባል ትምህርት መከሊቱ ያለሆነ ዜጋ መኖሩ ሃቅ ነው። ከበርካታ ትምህርት ቤት የገቡ ወጣት ትውልድ ውስጥ አገርን በሳይንሳዊ እና የቴክኖሎጂ እውቀት እና እንደ የሙያ ዝንባሌአቸው በየዘርፉ የለውጥ መሪ መሆን የሚችሉ ጥቂት ናቸው። ይህን አቅም ከብዛት በውድድር ሂደት አንጥሮ ለማውጣት የሚያስችል የትምህርት አሰጣጥ እና የመምህራን ጥራት ከሁሉም ዓይነት ትምህርት ቤት እና ከሁሉም መምህራን አይገኝም። ይህ መሆን የሚችለው ጥራት እና ዕውቀት መሸለም ሲቻል ነው። በሲቪል ሰርቪስ ተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅት ማስረጃ ሰርተፊኬት ያለው መምህር ደመወዙ ተመሳሳይ ነው። በትምህርት መስክ የተሰማራው የግሉ ዘርፍ ለምርጥ መምህራን የተሻለ ደመወዝ ከፍሎ የተሻለ የትምህርት ጥራት ሲያስገኝ የመንግሥት የትምህርት ሥርዓት ይህን የማድረግ የውድድር ሥርዓት የለውም።

## የኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የትምህርት ዘርፍ ልማት ውጣ ውረድ እና መሠረታዊ ምክንያቶች

41. የኢትዮጵያ እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልል የትምህርት ዘርፍ ችግር እንደ የፖለቲካ ሥርዓቱ ዓይነት ደረጃው ቢለያይም በሽፋን ወይም ተደራሽነት ማነስ፣ እና በጥራት ጉድለቶች የሚጠቃለል ነው። ለእነዚህ ችግሮች መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮችን ለመንቀስ በየዘመናቱ ጥናቶች ተደርገው የፋይናንስ እና የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች፣ ከእነዚህ የሚመነጩ የመምህራን ጥራት እና ትጋት ጉድለት፣ የግብዓቶች እጥረት፣ እና የሥርዓተ ትምህርት አግባብነት ችግር በዋናነት እየተነሱ በርካታ የትምህርት ፖሊሲ ለውጦች እና መገላባበጦች ተካሂደዋል። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሊተገበር የነበረው እና በትምህርት ማሕበረሰቡ ተቃውሞ የገጠመው ሥርዓተ ትምህርት በአውሮፓ በተለይም በጀርመን እንደ አገሩ ነባራዊ ሁኔታ ሥርቷል፤ አገር አሻግሯል። በደርግ ዘመን የተተገበረው ሥርዓተ ትምህርት እንደ አሜሪካ ባሉ አገራት ሠርቷል። በኢህአዴግ ዘመን የተተገበረው ሥርዓተ ትምህርት የአሜሪካ፣ የጀርመን፣ እና የደቡብ ኮሪያ የትመህርት ፖሊሲዎች ባህርያትን ከሞላ ጎደል ያካተተ ሲሆን ፖሊሲዎቹ በእነዚህ አገራት ሠርተዋል። ከሁሉም በላይ ግን ኢትዮጵያ በየዘመናቱ ተተግባሪ ይሆናሉ ተብለው የተለዩ የትምህርት ፖሊሲዎችን ተራ በተራ ስትሞክር ቆይታ የትምህርት አቅሟ አሁንም በሽፋን እና በጥራት ከአብዛኛው የአፍሪካ አገር ያነሰ አቋም ላይ ለመገኘቱ ከፖሊሲ በተለይም ከሥርዓተ ትምህርት ጉዳዮች የሚልቁ መሠረታዊ ምክንያቶች እንዳሉ አመላካች ነው።

42. ከችግሩ መሠረታዊ ምክንያቶች መካከል በዋናነት ሁለት ጉዳዮች ሊጠቀሱ ይችላሉ፤
    1. ትምህርት በየሥርዓቱ የርዕዮተ ዓለም ወይም የፖለቲካ ዓላማ እና ማራመጃ መሣሪያ በመደረጉ የተፈጠረ አለመስከን ወይም ግብ የለሽነት እና እሱን ተከትሎ የሚፈጠር ግጭት፣ እንዲሁም
    2. በፖሊሲ ደረጃ የሚጣረሱ የሽፋን እና የጥራት ግቦች ናቸው።

43. **ዓላማውን የሳተ የትምህርት ሥርዓት፤** በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ትርጉም ባለው ደረጃ ለዩኒቨርሲቲ የበቃው የማሕበረሰቡ የዕውቀት ቁንጮ ከአሥርት ዓመታት የሚልቅ ጊዜውን ያጠፋው በችግር ፈቺ ሣይንሳዊ ምርምር ላይ ሳይሆን ከሥርዓተ መንግሥት ተቃውሞ አልፎ በአንድ ርዕዮተ ዓለም እንኳ መግባባት በማያስችል አድካሚ የፖለቲካ ትግል ነው። ለትምህርት ዓላማ የተሰባሰበ ወጣት ንቅናቄ የወለደው የደርግ ሥርዓት ትምህርትን የሕብረተሰባዊ ርዕዮተ ዓለም ማራመጃ ሲያደርገው በውጤቱ አንደበተ ርትዕ ግን ከተግባር ጋር የተፋታ ትውልድ ተፈጠረ። ከዚህም በከፋ ሁኔታ ቀላል የማይባል ከዩኒቨርሲቲ አቋርጦ የወጣ ልሂቅ 17 ዓመት በልማት ሳይሆን በአውዳሚ ጦርነት ጊዜውን ፈጀ፤ ያፈራው ትውልድም ተኳሽ እንጂ ተመራማሪ አልነበረም። ኢህአዴግም የትምህርት ሥርዓቱ የወቅቱን ጫፍ የረገጠ የብሔር ፖለቲካ ማራመጃ፣ አንድ ለአምሥት አደረጃጀት ሳይቀር የዕለት ከዕለት ርዕዮት ማስረጫ በማድረጉ በአንድ ትውልድ ዕድሜ ለአገር አንድነት ሳይሆን ለብሔር ግጭት ውረድ እንውረድ የሚባባል የተሳለ ወጣት ተፈጠረ። ከዚህም በላይ የዴሞክራሲ

ግቡን በሳተ ሁኔታ ሴኪዩላሪዝምን በትምህርት ተቋማት ማስተግበር ስላልፈለገ ለችግሩ መፍቻ ተፈጥሮን ከመመርመር ይልቅ በዕምነት ተጽዕኖ ሥር የወደቀ አማኝም ሰባኪም የሆነ ትውልድ እንዲፈጠር አገዘ። እነዚህ ኩነቶች የአለፈውን ያልታደለ የትምህርት ፍኖት አስቀጥለው ዛሬም በትምህርት ገበታ ላይ መሆን የነበረበት ወጣት ብረት ይወለውላል።

44. **የሚጣረሱ የትምህርት ልማት ግቦች፤** ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት እስከ ኢህአዴግ ዘመን ድረስ ትምህርትን በሁሉም ደረጃ ለሁሉም ማሕበረሰብ ማዳረስ እና ጥራትን ማስጠበቅ የትምህርት ፖሊሲ ዋና ግቦች ናቸው። ከታዳጊ አገር የሀብት እና የመፈጸም አቅም እንዲሁም በሰው ልጅ ተፈጥሮ እና በጊዜ ላይ በሚመሠረት የትምህርት ልዩ ባሕርይ አንጻር ሁለቱ ግቦች አብረው አይሄዱም። ውስን ሀብት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በብቃት እና በጥራት በማዳረስ እና ብቃት ያላቸው መምህራንን በመቅጠር ጥራትን ማረጋገጥ ካለበት በአንዴ በሁሉም ደረጃ ለሁሉም ዜጋ ተመሳሳይ አገልግሎትን የማሳካት ግብ እውን ሊሆን አይችልም። ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ በማዳረስ ግብም ውስጥ ጥራትን ማስጠበቅ የሚቻለው በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ልዩ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ትምህርት ቤት የማቋቋም እና የልዩ ትምህርት ቤቶች መምህራንን በልዩ ማበረታቻ መቅጠር ሲቻል፣ እንዲሁም በሥርዓቱ ውስጥ በመንግሥት ድጋፍ የሚደረግላቸው የግል ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ ሲበረታታ ነው። እነዚህ አማራጮች በተለይ በደርግ ዘመን ዝግ የነበሩ ሲሆን የግል ትምህርት ቤቶች ተወርሰው ወደ መንግሥት ትምህርት ቤትነት ተቀይረዋል። የልዩ ትምህርት ቤቶች አማራጭ በተለይ በክልሉ ተስፋ ሰጪ ውጤት ቢያሳዩም የማስፋፋት እና በዚህ ሥርዓት የሚሰለጥኑ ተማሪዎችን ለክልሉ ልማት መልሶ የመጠቀም አስቻይ ሁኔታ ገና አልተፈጠረም።

45. ለእነዚህ ሁለት የትምህርት ሥርዓት መሠረታዊ ስብራቶች ማስረጃ የሚሆኑት በየዘመናቱ የተፈጠሩት የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ የተለዩት ችግሮች፣ የፖሊሲዎቹ የመቀያየር ድግግሞሽ መብዛት ናቸው። ኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት የትምህርት ሥርዓት ተሞክሮ አላት፤ ከሞላ ጎደል የተደራጀ ትምህርት በኢትዮጵያ የሳባ ፊደል በወቅቱ የነበሩትን ልሳናት የጽሁፍ ቋንቋ ካደረገበት እና መግባቢያ ሆኖ ማገልገል ከጀመረበት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን ይጀምራል። ከክርስትና እና እስልምና ዕምነቶች መስፋፋት በኋላም የቤተ ክህነት እና የመድረሳ ወይም የቁርዓን ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ሥርዓት መሠረት ጥለዋል። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የአገረ መንግሥት ግንባታን ካደላደሉ በኋላ የኢንዱስትሪ አብዮትን ተከትሎ በሣይንስ ትምህርት መስፋፋት እየታገዘ በአውሮፓ በፍጥነት እየተፈጠረ የነበረውን ቴክኖሎጂ ብዙም ሳይቆይ ወደ አገራቸው ማስገባት ጀምረው ነበር። በወቅቱ ፊደል ከቆጠረው የማሕበረሰብ ክፍል መካከል ይህን ቴክኖሎጂ ከመቃወም አልፎ የሚተረጉም እና የሚተገብር የሰው ኃይል አልነበረም። ይህን ሁኔታ ተከትሎ የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት ቤት የሆነው ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ በ1900 የተቋቋመ ሲሆን እስከ 1917 ድረስም ብቸኛው የአገሪቷ የመንግሥት ትምህርት ቤት ሆኖ ቆይቷል፤ በዚህ በወቅትም 3,000 ተማሪዎች ተምረውበታል።

46. የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትም በዚሁ ጥረት ገፍቶ የመጀመሪያውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማለትም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት በ1927 የተቋቋመ ሲሆን በዚህም ተፈሪ መኮንን (ኋላ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ) በመክፈቻ ንግግራቸው *"አገሩን የሚወድድ ሁሉ ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ ማገዝ፣ ልጆቹን ማስተማር፣ የጎረቤት ልጆች እንዲማሩ መደገፍ አለበት። መቶ ሺህ የተማሩ ዜጎች ይኖሩን ዘንድ በአንድ ተማሪ መጀመር አለብን፤ ሃያ ሺህ ትምህርት ቤቶች ይኖሩን ዘንድም ከአንድ ትምህርት ቤት ግንባታ መነሳት ይኖርብናል"* በማለት የዕድገት መውጫ መንገዱ የተማረ ሰው መሆኑን አስረግጠዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ የትምህርት በጀት የተያዘውም ልዩ የትምህርት ታክስ በተጣለበት በ1918 ነበር። እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ በኢትዮጵያ 22 ትምህርት ቤቶች የነበሩ ሲሆን 14 የሚሆኑት በአሜሪካዊያን እና ስዊድናዊያን ሚሲዮናዊያን ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ ነበሩ።

47. **የጣሊያን ወረራ ጥፋት ያነጣጠረበት የተማረ ሰብዓዊ አቅም እና የትምህርት ሥርዓት፤** የአምሥት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ቀዳሚ የጥፋት በትር ያረፈው ይቃወመኛል ብሎ ባሰበው ጥቂት የነቃ የማሕበረሰብ ክፍል ነው። ኢትዮጵያ ከነበራት ጥቂት የተማረ ዜጋ 3,000 የሚደርሰው በታቀደ ስልት ተገድሏል። ይባስ ብሎም ትምህርት ቤቶች ወድመዋል፤ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ የተጻፉ የማስተማሪያ መጻሕፍት ተቃጥለዋል። ኢትዮጵያ ስለ እድገቷ በሰለጠነ የሰው ኃይል ረገድ ከዜሮ መጀመር ነበረባት። የውጣ ውረዱ እርግማን ከዚህ ይጀምራል።

48. **ቁጭት የወለደው የትምህርት ሥርዓት፤** በጣሊያን ወረራ ጦርነት ወቅት ተቋርጦ የነበረው መደበኛ ትምህርት ከድል በኋላ በ1934 እንደገና የጀመረ ሲሆን አጼ ኃይለ ሥላሴ የትምህርት ቦርድ በአገር አቀፍ ደረጃ እና በክፍለ ሀገራት በማቋቋም እና ራሳቸው የቦርዱ ሰብሳቢ አድርገው በመሰየም በተዘዋዋሪም የትምህርት እና ስነ ጥበብ ሚኒስቴርን እስከ 1958 መርተዋል። በገቢ ንግድ ላይ የሚጣል የትምህርት አድ ቫሎረም ታክስ እና በመሬት ይዞታ ላይ የሚጣል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ታክስ በ1939 ተግባር ላይ ውሏል። አጠቃላይ የአገሪቷ ተማሪዎች ብዛትም በ1935 ከነበረበት 19,000 በ1947 ወደ 90,000 አድጎ ነበር።

49. **የተማረ የሰው ኃይል እጥረት የፈጠረው አዲስ የትምህርት ፖሊሲ፤** የ1940ዎቹ የትምህርት አፈጻጸም ከተነሳበት ዝቅተኛ መሠረት አኳያ እንደ ስኬት ሊቆጠር ቢችልም አገሪቷ ከሚያስፈልጋት የተማረ የሰው ኃይል አቅም እና እየጨመረ የመጣውን የመማር ፍላጎት ለማስተናገድ እጅግ ፈታኝ ሁኔታዎች ተፈጠሩ። ከትምህርት ቤቶች እና ከትምህርት ቁሳዊ ግባዓቶች እስከ መምህራን እጥረት የሚዘልቁ ችግሮች በቂ የፋይናንስ አቅም ላልነበራት አገር ፈተና ነበሩ። ለማሳያ ያህል የትምህርት እና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ከሚመድበው በጀት 20 በመቶ የሚሆነው የሚከፈለው ከውጭ አገር ለተቀጠሩ መምህራን ነበር። በዚህም ሁኔታ ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በተደረሰ የትብብር ስምምነት ከአሜሪካ በመጡ ባለሙያዎች የረጅም ዓመት የትምህርት ዘርፍ ልማት ዕቅድ ተነድፎ ወደ ትግበራ ተሸጋግሯል። በእቅዱ መሠረት በተለይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርትን እስከ አራተኛ ክፍል በመወሰን የማሕበረሰብ ችግሮችን በመፍታት ላይ ያተኮረ የማሕበረሰብ ትምህርት ቤቶችን (community schools) በማስፋፋት ላይ እንዲያተኩር፣ ለዚህም ዕድሚያቸው ከትምህርት ደረጃው የሚልቁ ተማሪዎችን ዕድሚያቸው ለክፍል ደረጃቸው ከሚመጥኑት ተማሪዎች ለይቶ በማስተማር እንዲተገበር የመፍተሄ አቀወጣጫ አስቀምጧል። ከዚህም ጎን ለጎን የመለስተኛ ሁለተኛ እና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ቅበላ በማስፋፋት ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ ነድፏል። በከፍተኛ ደረጃ ትምህርትም ለቴክኒክ፣ የንግድ ሥራ፣ ለሲቪል፣ ለኢንዱስትሪ፣ እና ኤሌክትሪክ ምህንድስናዎች ቅድሚያ በመስጠት እነዚህ ተቋማት ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ መክሯል። ከአሥር ዓመት በኋል ውጤቱ ሲገመገም ማጠቃለያው ዕቅዱን በታለመለት አግባብ ለመፈጸም መቸገር ሲሆን ይህም ዕቅዱን ወደ መሬት ለማውረድ ሥርዓት አልነበርም፣ ፕረቶችን ማቀናጀት አልተቻለም፣ የነበረው የአሠራር ሥርዓትም ቀልጣፋ አልነበረም፣ የትምህርት አፈጻጸም ከቁጥሩ ማነስ በከፋ የጥራቱ ጉዳይ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነበር።

50. **ከአፍሪካ አገራት ያነሰ የትምህርት አፈጻጸም የፈጠረው ቁጭት እና የፖሊሲ ለውጥ፤** ችግሮቹ በጣም ጎልተው የታዩት በትምህርት አፈጻጸሟ የተኩራራች የመሰለችው ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት እና ሣይንስ ኮንፈረንስ (UNESCO) የአፍሪካ የትምህርት ጉባዔ በ1953 ባዘጋጀችበት መድረክ አፈጻጸሟን ከሌሎች አፍሪካ አገራት አፈጻጸም ጋር ለማነጻጸር አጋጣሚው በተፈጠረበት ወቅት ነው። በወቅቱ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ከኒገር በስተቀር ሁሉም የአፍሪካ አገራት ከኢትዮጵያ የተሻለ አፈጻጸም ነበራቸው። የኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ 3.8 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህ እንደ ሞሪሺየስ እና ምዕራብ ናይጄሪያ መቶ በመቶ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ሃፍረት እና ቁጭት ፈጥሯል። በመለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋንም ከኢትዮጵያ ያነሰ ወይም እኩል ደረጃ የነበራቸው የአፍሪካ አገራት ስድስት ብቻ ነበሩ። የኢትዮጵያ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን 0.5 በመቶ የነበረ ሲሆን በተመሳሳይ ወቅት ጋና 29.4 በመቶ ደርሳ ነበር። በዚህ ሁኔታ ቁጭት የገባቸው ንጉሱ የዩኔስኮ ጉባኤ ምክረ ሃሳቦችን በመውሰድ የሃያ ዓመት የትምህርት ልማት ዕቅድ ተነድፎ ወደ ሥራ እንዲገባ ባዘዙት መሠረት ይሄው ተፈጻሚ ሆኖ ኢትዮጵያ የትምህርት ልማት ዕቅዷን በሁለተኛው እና ሦስተኛው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች (1955 - 1966) ውስጥ በማካተት በትጋት ለመሥራት ጥራለች።

51. **የአዲስ አበባ ኮንፈረንስ ግቦች አፈጻጸም ከዕቅድ በታች መሆን የፈጠረው የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ እና የተማሪ አብዮት፤** በአዲስ አበባው የአፍሪካ የትምህርት ኮንፈረንስ የታየው የኢትዮጵያ ዝቅተኛ አፈጻጸም በውስጥ እና በአጋር ድርጅቶች እንዲሁም አገራት የፈጠረው ስሜት ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት እንዲሰጠው አግዟል። በውጤቱም በ1966 መዳረሻ የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በአንደኛ ደረጃ 18 በመቶ፣ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 7 በመቶ፣ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ 3 በመቶ፣ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ 0.2 በመቶ ማድረስ ተችሏል። በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ሁሉንም በአገሪቱ የተቋቋሙ ኮሌጆች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሥር በማድረግ የተሠራው ሥራ ትልቅ ለውጥ የታየበት ነበር። በወቅቱ ከትምህርት ልማት አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ሁለት ጉዳዮች ትኩረትን የሚስቡ ነበሩ። የመጀመሪያው በአንድ አሥርት ዓመታት የተገኙት ውጤቶች ከመነሻው አንጻር ጉልህ የሚባሉ ቢሆንም ከተቀመጠው ግብ እና አገሪቷ ለምትፈልገው አጠቃላይ ልማት ከሚያስፈልገው የሰው ኃይል ዝግጅት አንጻር ዝቅተኛ ነበር። በዕቅዱ መሠረት በ1963 መደረስ የነበረበት የትምህርት ሽፋን በአንደኛ ደረጃ 71 በመቶ፣ በመለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ 15 በመቶ፣ እንዲሁም

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ 0.4 በመቶ ነበር። በዚህም መሠረት የትምህርት ሽፋን የአፈጻጸም ደረጃው በዕቅድ ከተቀመጠው ጋር ሲነጻጸር በአንደኛ ደረጃ 25.4 በመቶ፣ በመለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ 30 በመቶ፣ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ 50 በመቶ ነበር። ሁለተኛው ክስተት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከ1950ዎቹ ጀምሮ የትምህርት ጊዚያቸውን በማጠፍ ጭምር በፖለቲካ ንቅናቄ ላይ መጠመዳቸው እና ለልማት ግብዓትነት የታለመው የትምህርት ዓላማ ለአንድ አሥርት ዓመታት ያህል በግጭት እና ተቃርኖ የባከነ አቅም ነበር። በዚህ መሃል ንጉሳዊ መንግሥት የትምህርት ዘርፍ ክለሳ ጥናት እንዲደረግ አዘዘ።

52. የ1963 የትምህርት ዘርፍ ክለሳ ጥናት (Education Sector Review) በአብዛኛው ከዩኒቨርሲቲ የተውጣጡ 51 አባላትን ጨምሮ 81 አባላት ባሉት 14 ግብረ ኃይሎች የተደራጀ አካል የተጠና ሲሆን የጥናቱ ጥልቀት እና ስፋት በአገር ደረጃ እስከ አሁን ተጠቃሽ ነው። የጥናቱ ዓላማ

    1. የኢትዮጵያን የትምህርት እና ስልጠና ሥርዓት እና ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ እንዲሁም ባሕላዊ ልማት ለማፋጠን ያለውን አቅም መርምሮ ለመረዳት፣
    2. እንደ አስፈላጊነቱ የትምህርት እና ስልጠና ሥርዓቱ ለማሕበረሰቡ እና ለአገሪቷ ልማት መሻሻል የሚያግዘበትን የተሻለ አግባብ ለማመላከት፣
    3. ትምህርት አገራዊ ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር እንዲያግዝ የመፍትሄ ሃሳቦችን ማመላከት፣ እና
    4. የቅድሚያ ትኩረት በሚሰጣቸው የትምህርት እና ስልጠና ጥናቶችን እና ለዘርፉ የሚያስፈልግ መዋዕለ ንዋይ መለየት ናቸው።

53. በጥናቱ የተለዩ የትምህርት ዘርፍ ተግዳሮቶች

    1. ከውጭ የገባው የትምህርት ሥርዓት በባሕርይው የኢትዮጵያን ወጣት ማግለሉ፣
    2. ከአገሪቱ ማሕበረ - ኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታ ባፈነገጠ መልኩ ለልሂቃን ብቻ ተለክቶ የተሰፋ የትምህርት ሥርዓት መሆኑ፣
    3. በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ከፍተኛ ብክነት መታየቱ፣
    4. የትምህርት ዕድል ሥርጭት ፍትሃዊ አለመሆን፣ እና
    5. የትምህርት ሥርዓት አስተዳደር በከፍተኛ ደረጃ የተማከለ መሆኑ ናቸው።

54. የጥናቱ ድምዳሜዎች፤

    1. ትምህርት የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሕይዎት በቀጥታ በመቀየር የኢትዮጵያን መቀየር ስላለበት፣ በሥራ ላይ ያለው የትምህርት ሥርዓት መስተካከል እና መቀየር አለበት፤
    2. ትምህርት በተቻለ መጠን ለእያንዳንዱ ዜጋ መዳረስ እንዲችል የዘመኑን ቴክኖሎጂ መጠቀም፣ እና ሁሉንም የዘመናዊ እና ባሕላዊ የትምህርት ልምምዶችን በማካተት የማሕበራዊ እና የእምነት ተቋማት አቅምንም ጭምር መጠቀም ያስፈልጋል የሚሉ ናቸው።

55. የጥናቱ ዋና ምክረ ሀሳብ አዲስ የትምህርት መዋቅር ሥራ ላይ ማዋል ሲሆን በተለይም በርካት ተማሪዎችን እንደሚያሳትፍ ተስፋ የተደረገበትን የመሠረታዊ አቅም ትምህርት (Minimum Formation Education) መተግበር ነው። ዋና ይዘቱም የአራት ዓመት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በማስፋፋት ሕጻናት በመሕበረሰቡ ውስጥ የተሻለ አቅም ኖሯቸው የተሻለ ሕይወት መምራት እንዲችሉ መሠረታዊ ዕውቀት ማስጨበጥ፣ እና ትምህርታቸውን ወደ ቀጣይ ደረጃዎች ለመግፋት ለሚወስኑ ሕጻናት የተሻለ መሠረት ለመጣል ነው። በዚህም መሠረት በሁሉም ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ወደ ማሕበረሰቡ በመመለስ የተግባር አገልግሎት እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል።

56. የትምህርት ዘርፍ ክለሳ ጥናቱ በነበረው ጥልቀት እና ስፋት በትምህርት ዘርፍ ፖሊሲ የኢትዮጵያ የራስ አቅም የታየበት ቢሆንም ዘመኑ እያንዳንዱን የመንግሥት የፖሊሲ ርምጃ ለመቃወም ሰበብ ብቻ የሚፈለግበት ጊዜ ስለነበር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዑደት አራት ዓመት እንዲሆን ሀሳብ መቅረቡን ጨምሮ የፖሊሲ ብያኔዎቹ ከፍተኛ ተቃውሞ አስነስተው ለትግበራ ሳይበቃ ቀርቷል። በተለይም ሰነዱ ገና በይፋ ሳይወጣ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን ጥናቱ እነዲካሄድ ያዘዘውን መንግሥት ለማጥላላት ዓላማ ተጠቅመውበት በተለይም የድሃውን ልጅ ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዳይማር የሚገድብ የትምህርት ሥርዓት እንደሆነ በሕዝቡ ዘንድ በማሰራጨት ምክረ ሃሳቡ ፖሊሲ ሆኖ ከመተግበር ይልቅ ለአብዮቱ ግብታዊ ምክንያት ሆኖ የንጉሳዊ ሥርዓቱ እንዲቀየር አስተዋጽዖ አድርጓል።

57. የተማረ ኃይል በርካታ ውድ የትምህርት እና የልማት ዓመታትን አባክኖ ወይም ሰውቶ ያዋለደው አብዮት በረጅም፣ ፈታኝ፣ እና ውድ የትምህርት ሂደት የተፈጠሩ ጥቂት አመራር ላይ ያሉ ብሩህ አዕምሮዎችን ጨምሮ

በበርካታ ሺህ የሚቆጠሩ የተማሩ ወጣቶችን ፈጅቶ ለቀጣዮቹ አሥራ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያ ልማቷን በዕውቀት ሳይሆን በዘመቻ እና በመፈክር እንዲትመራ ተገደደች።

58. በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በቁጭት እና እልህ ጭምር የተፈጠረው የትምህርት አቅም በአብዛኛው በንቃት ላይ፣ በዋናነት ያመጣው ውጤትም የዘመውድ ሥርዓቱን መቀየር እና የመሬት ላራሹን ዓላማዎች ማቀንቀን እና በዘመቻ ማስፈጸም ነው። በትምህርት ጫፍ ላይ የደረሱ አቅሞች የተከማቹነት በዩኒቨርሲቲ፣ ዝቅ ሲልም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ደግሞ የአንድ አሥርት ዓመታት ጊዜ ያጠፉት በፖለቲካ ርዕዮት ላይ ነው። በውጤቱም የተፈጠረው የሰብዓዊ ካፒታል አምድ ችግር ፈቺ የሣይንስ ምርምር የሚጠይቀው ስክነት እና አስተውሎት ሳይሆን የወቅቱ ርዕዮተ ዓለም መለያ የሆነው ጽንፈኝነት፣ አክራሪነት፣ እና ግትርነት ነበር። ከዚህ አንጻር አገርን በዕውቀታቸው ደግፈው በልማት እንዲያሻግሩ ተስፋ የተጣለባቸው ወጣት ልሂቃን ስብስብ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ መንግሥትን ካዋለደ በኋላ እራሱ ባቀነቀነው ርዕዮት ቀላል የማይባለው ኃይል ሲገደል ቀላል የማይባል ሌላው አቅም በቀጣዮቹ አሥራ ሰባታ ዓመታት በአውዳሚ ጦርነት ውስጥ ተሳታፊ ሆኗል። ትግል የራሱ ግብ እና የታሪክ ብያኔ ቢኖረውም በጥፍር ተቁሞ ከተከማቸ ውድ ሰብዓዊ ካፒታል አኳያ ግን በእርግጥ ትልቅ ብክነት ነበር።

59. **አብዮታዊ መንግሥት፣ አብዮታዊ ትምህርት፤** የደርግ ሥርዓት በብዙ መልኩ የትምህርት ውጤት እንደሆነ ሁሉ ትምህርትን ለርዕዮተ - ዓለም ንቃት መሣሪያ አድርጎታል። የ1966 አብዮት በፈነዳበት ወቅት ግርድፍ የተሳትፎ ምጣኔ (gross enrollment ratio) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት 16 በመቶ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 4 በመቶ፣ በከፍተኛ ትምህርት ከ1 በመቶ በታች ነበር። ይህን መነሻ አቅም የተረከበው ሥርዓቱ ከ1966 ጀምሮ እስከ 1977 ድረስ አምሥት ብሔራዊ የልማት ፍልስፍናዎችን የተከተለ ሲሆን የኢትዮጵያ ትቅደም ፖሊሲ፣ የሕብረተሰባዊነት ፖሊሲ፣ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) መመሪያዎች፣ እና የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ፕሮተራም ናቸው። የትምህርት ሥርዓቱ እና ፖሊሲውም በዚሁ አግባብ የተቃኘ ነበር።

60. በሀምሌ 1966 "ኢትዮጵያ ትቅደም" መርህ የአብዮቱን መፈንዳት ባበሰረ ማግስት በወርሃ ነሀሴ ብሔራዊ የዕድገት በሕብረት የዕውቀት እና የሥራ ዘመቻ ፕሮግራም ታውጇል። በዚህም ከ10ኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ያሉ 60,000 የሚጠጉ ተማሪዎች በታህሳስ 1967 ወደ ለዘመቻ ተሰማርተዋል። በታሕሳስ 1967 ሕብረተሰባዊነት ታውጇል። የግል ትምህርት ቤቶች መወረስ፣ በ1968 ትምህርት ቤቶች በመንግሥት እና ሕዝብ መተዳዳራቸው፣ 1969 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ በትምህርት ረገድ የተደረጉ ለውጦች ናቸው። በዚህ ወቅት በዕድገት በሕብረት ዘመቻ 160,000 ዜጎች ማንበብ እና መጻፍ እንዲችሉ የተደረገ ቢሆንም፣ ከትምህርት ማስፋፋት በላይ የተማሩ ወጣቶችን የመሬት ላራሹ እና ሌሎች የሕብረተሰባዊነት ርዕዮት ነክ አዋጆችን እንዲያስፈጽሙ ተልዕኮ በመስጠት የተገለጸው የትምህርት ሥርዓትን የፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያ የማድረግ ግብ ጎልቶ ነበር።

61. በተለይም በ1968 የወጣው የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ነበሩት። ዋና ዓላማው አሮጌ ሥርዓትን በአዲስ መተካት እና ኋላ ቀር ማሕበረሰብን ወደ አዲስ የነቃ ሕብረተሰባዊ ማሕበተሰብ ማሻገር ነበር። በዚህ ፕሮግራም ስለ ትምህርት ብዙ ትንተና የተሰጠ ባይሆንም በጥቅሉ ማይምነትን ማጥፋት፣ ነጻ ትምህርት ለሰፊው ሕዝብ ማዳረስ፣ ሣይንስ እና ቴክኖሎጂ፣ ሥነ ጽሁፍ፣ እና ሥነ ጥበብብ ማስፋፋት፣ እንዲሁም ባሕልን ከውጭ አድሃሪ ባሕል ተጽዕኖ ማላቀቅ እንደ ግብ ተይዘዋል። በ1969 በወጣው የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት እንደ ዓላማ ከተያዙት ሦስት ግቦች በቀዳሚነት የተመላከተው ሕብረተሰባዊነትን ማስተማር፣ መተንተን፣ ማስረጽ እና እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችሉ ዘዴዎችን መቀመር ነው።

62. በ1971 የወጣው የብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባሕል ዕድገት ዘመቻ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል። ይህ ፕሮግራም ከርዕሰ - ብሔሩ ሰብሳቢነት እስከ ቀበሌ ገበሬ ማሕበራት አስፈጻሚነት በሚዘልቅ መዋቅር በተቋቋመው የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ የሚመራ ሲሆን በርዕዮተ ዓለም፣ በትምህርት፣ በሣይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና ባሕል ረገድ ሁለት የትኩረት አቅጣጫዎችን ነድፏል። እነዚህም ርዕዮት ዓለምን ማስረጽ፣ እና ጥራት ያለው ትምህርትን በሁሉም ደረጃ ማስፋፋት ናቸው። ፕሮግራሙ የአምሥት ዓመታት የአብዮት ጉዞ የትምህርት አፈጻጸም የገመገመ ሲሆን በተለይ ሥርዓተ ትምህርትን ለመቀየር እና የትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም ጥራትን ማረጋገት እንዳልተቻለ፣ እንዲሁም ከማይምነት ነጻ ከመሆን ግቦች ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ሽፋን ድረስ ያሉ ግቦች መስተጋብር እና ግንኙነቶች ገና ቅርጽ አለመያዛቸው፣

በዚህም ምክንያት ከልማት አንጻር የትምህርት ዋና አቅሙ ጥራት ማስጠበቁ በመሆኑ ለዚህ ችግር አፋጣኝ መፍትሄ መስገኘት እንደሚገባ ታምኗል።

63. ከዚህ የፕሮግራም ግምገማ እና የትኩረት አቅጣጫ በመነሳት የትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት አቅጣጫ ፖሊሲ በ1972 አውጥቷል። በፖሊሲ አቅጣጫ ሰነዱ መሠረት የትምህርት ዋና ዓላማው ዜጎችን ለምርት፣ ለሣይንሳዊ ዕውቀት፣ እና ለሕብረተሰባዊ ንቃተ ሕሊና ማዘጋጀት ነው። ሰውን እንደ ማሽን በፈለጉት አቅጣጫ ማሰማራት እና በፈለጉት የሰው ኃይል መጠን የፈለጉትን ያህል ምርት ማምረት ስለማይቻል በትምህርት ሂደት የሚያልፉ ዜጎችን ባሕርይ በአመለካከት (attitude)፣ በግንዛቤ (cognitive)፣ እና ሥነ ልቦና (psychomotor) መቅረጽ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ተወስዷል። እነዚህንም ባሕርያት እውን ለማድረግ የፖሊቴክኒክ ትምህርትን ማስፋፋት እንደ አማራጭ የተወሰደ ሲሆን የትምህርት ሥርዓቱ ምሁራዊ ዕውቀት (intelect)፣ ርዕዮተ ዓለም (idology)፣ ሙያ እና ቴክኒክ (vocational and technical)፣ ሥነ ውበት (aesthetic)፣ አካላዊ ብቃት (physical)፣ እንዲሁም የሥራ ትምህርት (labor education) ዋና አምዶች አድርጎ ይወስዳል። የፖሊቴክኒክ የትምህርት እና ሥልጠና ሥርዓቱ ሦስት ተደራሾች በተምህርት ዕድሜ ያሉ ወጣቶች፣ የትርፍ ጊዜ ተማሪዎች እና ሰልጣኞች እና ልዩ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የመግባት ጠባብ ዕድልን ጨምሮ አራት ደረጋዎች ነበሩት።

64. በ1971 የተተገበረው ሌላው ፕሮግራም የብሔራዊ መሠረተ ትምህርት ዘመቻ (National Literacy Campaign) ነው። የዚህ ፕሮግራም ዋና ግብ ትምህርትን ለሰፊው ሕዝብ በማዳረስ በ1979 ከማይምነት ነጻ የሆነ ማሕበረሰብ መፍጠር ነው። የደርግ መንግሥት ዕውቅና ካገኘባቸው ጥቂት የስኬት አፈጻጸሞች አንዱ ተጠቃሽ የዚህ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ፕሮግራም ነው።

65. የትምህርት ጥራት የማይታለፍ፣ ነገር ግን ከአሥር ዓመታት ልፋት በኋላ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ክስተት ሆኖ ቀጥሏል። በ1976 የትምህርት ሚኒስቴር እየወረደ የመጣውን የትምህርት ጥራት ሁኔታ በተለየ ትኩረት እንዲጠና ወስኖ በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ተሳታፊነት ወደ ተግባር ተሸጋግሮ ነበር። በሁሉም ንዑስ ዘርፎች የተጠቃለለ ሪፖርት መቅረብ ባይችልም የተማሪ - አስተማሪ ጥምርታ እየቀነሰ መሄድ፣ ከ36 በመቶ በላይ የሚሆኑ የአንደኛ ደረጃ መምህራን፣ 42 በመቶ የሚሆኑ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ምንም ዓይነት የመምህርነት ሥልጠና አለመውሰድ፣ እና 43 በመቶ የሚሆኑት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ከአንድ እና ሁለት ዓመት የዘለለ የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት አለመውሰዳቸው፣ የትምህርት ቤቶች መጨናነቅ፣ የትምህርት መሣሪያዎች እጥረት እና ደካማ የትምህርት አስተዳደር ዋና ችግሮች ሆነው ተለይተዋል። ይህን ችግር ጊዜ ወስዶ ለመቅረፍ ዝግጅቱ ከመጠናቀቁ በፊት የ1983ቱ ለውጥ ቀደመው።

## ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች

66. የአምሥት ዓመት የትምሕርት ዘርፍ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ከየሃያ አምሥት ዓመት የትምህርት ዘርፍ ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ የሚመሠረት ሲሆን፣ ዋና አቅጣጫዎቹም በተደራሽነት፣ በጥራት፣ በተተግባሪነት፣ እና በርትዕነት ላይ የሚመሠረት የትምሕርት ሥርዓት ማስፈን ነው። በተለይም በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይደረጋል፤
    1. ትምህርት ቤቶች በሂደት በተማሪዎች የሚወደዱ እና ለሁለንተናዊ ዕድገት ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ (ትምህርት ቤቶች ከቤት ቀጥሎ ለመማሪያ እና ማዘውተሪያ ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ)፣
    2. የትምህርት ተደራሽነት እና ሽፋንን ከጥራት እና ተጨባጭ ግብ ጋር ማመጣጠን (የተደራሽነት እና ጥራት ሚዛን የጠበቀ የትምህርት ሥርዓት ማስፈን)፣
    3. ከታች ማብቃት፣ ከላይ ማረቅ፣ እና መልሶ ማልማት፤ የትምህርት ሥርዓት የበቁ ዜጎች መቅረጫ መሆኑን ከሕጻንነት እስከ ወጣትነት በሚደረጉ ክትትሎች ማረጋገጥ (የሥነ ተዋልዶ፣ ጤና፣ ሥነ ምግብ ጉዳዮችን ያካተተ ትውልድን ከሥር የመቅረጽ ስትራቴጂ)፣ ማሰልጠን እና ዕውቀት በሚሸልም ምንዳዕ በኢኮኖሚው ውስጥ ማቆየት፣
    4. ትምህርትን ከኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር ማዘጋጀት፤ ስልጠና ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለግብርና ልማት፣ ለቱሪዝም ልማት፣ ለቴክኖሎጂ ልማት፣
    5. ትምሕርትን ምክንያታዊ እና ግብ ተኮር ማድረግ፤ ትምህርት በሣይንሳዊ እና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ችግሮችን በየደረጃው የመፍቻ ብቸኛ መሣሪያ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ማድረግ፣ ሣይንሳዊ ዕውቀትን ከግብረ ገብነት እና መልካም ባሕላዊ እሴቶች ጋር ማቀናጀት።

## ዋና ዋና ግቦች

67. የትምሀርት ዘርፍ ዋና ዓላማ
    - የትምህርት ሽፋንን በየደረጃው ማሳደግ፣
    - የትምህርት ተሳትፎን ብቻ ሳይሆን ዘላቂነትን በዓለም አቀፍ ምጣኔ ደረጃ ማሻሻል
    - ጥራት ያለው እና ለኢኮኖሚው በቂ የሆን የሰለጠነ የሰው ኃይል ማብቃት፣
    - የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ሽፋን ማሻሻል፣ በዋናነት ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ጥራት ማረጋገጥ።

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

68. የትምህርት ዘርፍ ዕቅድ የማስፈጸሚያ ስልቶች፤
    1. የትምሕርት ሽፋን እና ጥራት ግቦችን በመንግሥት፣ በግል ዘርፍ፣ እና በመንግሥት- የግል ዘርፍ ትብብር በሚደረጉ የሦስት ርከን ተሳትፎዎች በዘላቂነት ማረጋገጥ፣
        - በመንግሥት ድጋፍ የሚታገዝ ማብቃትን እና ሣይንሳዊ ዕውቀትን ማዕከል ያደረገ የግል ትምህርት ቤቶች ሥርዓት መዘርጋት፣ የትምህርት ጥራትን ማዕከል አድርገው ለሚሠሩ የግሉ ዘርፍ ተዋንያን ልዩ ማበረታቻ እና ድጋፍ ማድረግ፣
        - ልዩ ትምሕርት ቤቶችን በመንግሥት፣ በመንግሥት እና በግል ትብብር መገንባት፣
        - ከተግባር ጋር የተቀናጀ የጎልማሶች ትምሕርት ሥርዓት መተግበር፣
    2. የቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምሕርትን ከጤና፣ ከቅድመ - ወሊድ እና ድህረ - ወሊድ የእናቶች ክብካቤ፣ ከሥነ ምግብ፣ እና ከሕጻናት ክብካቤ ሥርዓቶች ጋር ማቀናጀት፣
    3. በትምሕርት ላይ ለሚደረግ የመንግሥት ወጪ ምርታማነት እና ቅልጥፍና ትኩረት መስጠት፣ ተጠቃሚ ማሕበረሰብን መሠረት ያደረገ ለመሠረተ-ልማት ግንባታ፣ ለትምሕርት ማበልፀጊያ፣ እና የተማሪዎች ምገባ ልዩ የትምህርት ታክስ ወይም መዋጮ ሥርዓት ማስፈን፣
    4. ለልዩ ትምህርት ቤቶች እና ለነጻ የትምህርት ዕድል ባለ ሀብቱን እና የውጭ አጋሮችን ያሳተፈ የትምህርት ፈንድ እና ፋውንዴሽን ማቋቋም፣
    5. ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን የሙያ ክህሎት በትምህርት ተቋማት እና በግሉ ዘርፍ ትብብር የሥራ ልምምድ (ኢንተርንሺፕ) ባሕል ማዳበር፣
    6. የዓለም አቀፍ የዕውቀት እና የቴክኖሎጂ አቅጣጫን ግምት ውስጥ ያስገባ የትምህርት ሥርዓት ማስረጽ፣
    7. ቀልጣፋ የትምህርት አስተዳደር ሥርዓት ማስፈን።

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

# ጤና

## 18.1. መግቢያ

2. በአማራ ብሔራዊ ክልል እና በኢትዮጵያ ወቅቱን የሚመጥን፣ የጤና ችግሮችና ባህሪያቸው ጋር የተናበበ፣ ለመንስኤዎቻቸው ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ የጤና ስርዓት መገንባት አስፈላጊ ነው። ለዚህም አማራ ክልል ጤና ቢሮ የ 25 አመት የጤና ፍኖተ ካርታ እና ከዚህም የሚቀዳ የአምሥት ዓመት የጤና ልማት ዕቅድ ከአገራዊ የጤና ፖሊሲ ጋር በማናበብ አዘጋጅቷል። የፍኖተ ካርታው እና የአምሥት ዓመት የጤና ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዋንኛ አላማውም ዘላቂና ለተግዳሮት አይበገሬ የጤና ስርዓት በክልሉ በመገንባት ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት በፍትሀዊነት ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ በማድረግ ጤናማ እና አምራች ዜጎችን መፍጠር ነው። በአማራ ክልል የሚስተዋሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች፣ ጎጅ ልማዳዊ አሰራሮች፣ ተፈጥራዊ አደጋዎች እና በየጊዜው የሚከሰቱ ግጭቶች በጤና ስርዓት ላይ ከፍተኛ ጫና በመፍጠር የቆየውን የጤና ተደራሽነት ችግር አባብሰውታል።

3. **ስለሆንም ይህ ፍኖተ ካርታ** እና ዕቅድ **ለመዘጋጀት** ዋና ዓላማ **እስካሁን የተመዘገቡትን መልካም ተሞክሮዎችን** ለማጠናከር፣ **እያደገ የመጣውን የማህበረሰብ የጤና ፍላጎትና ወቅታዊና ወደፊት ለሚከሰቱ ተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎችን ምላሽ ለመስጠት ፣ የጤና ስርዓቱ እና የስነ ህዝብ ቁጥር ጋር ማጣጣም ማስፈለጉ እና ከሀገራዊ ራዕይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር የሚጣጣም የጤና ስርዓት** ለመገንባት ነው።

## 18.2. የጤናው ዘርፍ ሁኔታ ትንተና

### የጤና መሰረተ-ልማት

4. የጤና መሰረተ-ልማት የጤና ስርዓት ከተገነባባቸው አንኳር ምሶሶዎች አንዱ ነው፡፡ በአማራ ክልል በአሁኑ ሰዓት 3725 ጤና ኬላዎች፣ 923 ጤና ጣቢያዎች፣ 72 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች፣ 20 አጠቃላይ ሆስፒታሎች እና 8 ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች፣ 10 ደም ባንኮች እና 2 ኦክስግን ፕላንቶች አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን በሃገር አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው ስታንዳርድ አንፃር የክልሉን የጤና አገልግሎት ሽፋን ጤና ኬላ 75%፣ የጤና ጣቢያ 98% እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 28% ደርሷል፡፡ በዚህ መሠረት በክልሉ ተጨማሪ 1,254 ጤና ኬላዎች ፣ 79 ጤና ጣቢያዎች እና 178 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ያስፈልጋሉ። ነገር ግን ፍትሀዊ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከተለመደው የጥምርታ ቀመር ባሻገር የክልሉን መልካ ምድራዊ አቀማመጥ እና የህዝብ አሰፋፈርን ታሳቢ ያደረገ የተቋማት ግንባታ አስፈላጊነት ታሳቢ መደረግ አለበት። በቀጣይ ሃያ አምስት አመታት የሚኖረውን የህዝብ ብዛት ዕድገትና ፍላጎትን ያማከለ የተቋማት ግንባታ ከክልሉ የሚጠበቅ ተጨማሪ ስራ ሲሆን በአገልግሎት ዘመን ያረጁ ተቋማትን በማደስና ለስራ ምቹ ማድረግ ይጠበቃል። አብዛኛው ተቋማት በሃገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን ደረጃ አያሟሉም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጤና ኬላ ሽፋን የተሰላው በነባሩ የጤና ኬላ ስታንዳርድ ሲሆን በአዲሱ የጤና ኤክስቴንሽን ፍኖተ- ካርታ የተቀመጠውን ስታንዳርድ ለሟሟላት ሰፊ ስራ ይቀራል። የአማራ ክልል ላለፉት አመታት በጦርነትና ግጭት ምክንያት በጤና ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስተናገደ ሲሆን ተቋማትን መልሶ መገንባትና ማደረጀት ከፍተኛ ሀብትና ርብርብ የሚጠይቅ ተጨማሪ የአጭር ዘመን ትኩረት ነው። በአማራ ብሄራዊ ክልል የግሉ ዘርፍ የመሰረተ-ልማት ተሳትፎ ስንመለከት ከሁለት ሺህ በላይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቢኖሩም ስርጭታቸው በከተማ አካባቢዎች ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በአጠቃላይ በክልሉ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት ለስራ ምቹ ከማድረግና የታካሚዎችን ደህንነት ከማረጋገጥ አንፃር ሰፊ ስራ የሚፈልግ ሲሆን ባዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የተደራጁ እንዲሆኑም ያስፈልጋል።

### የጤና ዘርፍ የሰው ሀብት

5. በአማራ ክልል በ2016 ዓ.ም በአጠቃላይ 70,752 የጤናው ዘርፍ ሰራተኛ ሲኖር ከዚህ ውስጥ 46,872 የተለያዩ የጤና ባለሞያዎች ይገኛሉ። ይህም ቢሆን ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን (UHC) ለማሳካት ከወጣው የህዝብ ጥምርታ አንጻር

(45 ለ10,000) የክልሉ የሰው ሀይል ጥምርታ (9 ለ 10,000) ዝቅተኛ ነው። እ.ኤ.አ 2021 (ዩኒሴፍ 2023) በክልሉ ውስጥ የጤና ሰራተኛው ከህዝብ ጋር ያለው ድርሻ 1,547 የህክምና ዶክተሮች ሲኖሩ ጥምርታውም (1፡16,000 ህዝብ)፣ 20,955 ነርሶች፣ ሚድዋይፎች እና የጤና መኮንኖች (1፡1,182 ህዝብ) እና 9716 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች (1፡2,548 ህዝብ) ክልሉን በማገልገል ላይ መሆናቸውን ያሳያል።

6. ሠንጠረዥ 178– 1፡ የአማራ ብሔራዊ ክልል የጤና ባለሙያ - ሕዝብ ጥምርታ (በ1 ሺህ ሕዝብ)፤ የአገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ንጽጽር




7. ይህ የሚያሳየ የጤና ባለሙያዎች ከፍተኛ እጥረት እና ያልተመጣጠነ ስርጭትና የሙያ ስብጥር መኖሩን ሲሆን፣ በተከሰተው ግጭት ምክንያት ችግሩ እየተባባሰ ሄዷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የፍላጎት ትንበያና ከባቢያዊ ስርጭት ፍትሃዊ ከማድረግ አኳያም ክፍተቶች ይታያሉ። የጤና ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማነስና በቂ የሆነና ተገቢነት ያለው ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና የሚያገኙበት እድል ተደራሽ አለመሆኑ፣ የጤና ባለሙያዎችን በስራ ቦታቸው በከፍተኛ ተነሳሽነት ከመስራትና ከመቆየት አንጻር ራቅ ባሉ አካባቢዎች ሲመደቡና የደህንነት ስጋቶች በሚኖሩበት ጊዜ ከፍተኛ የፍልሰት ችግር አለ።

8. በተጨማሪም ወሳኝ ለሆኑ የጤና አገልግሎቶች አቅርቦትና ጥራት አስፈላጊ የሆኑ ጤና ባለሙያዎችን ከመቅጠርና ከመመደብ አንጻር ከፍተኛ ክፍተት ይታያል። አልፎም የስራ አፈጻጸምን በጥራት ከመለካት፣ ተጠያቂነትን ከማስፈን፣ የጤና ባለሙያዎችን ህጋዊ፣ ስነምግባራዊና ሙያዊ ድንጋጌዎችን በማክበር የሚሰሩ መሆኑን ከማረጋገጥ አኳያ ክፍተቶች መኖራቸው ታይቷል። እንዲሁም የጤና ባለሙያውን በሥራ ላይ ከማቆየት አንጻር የእድገት መሰላልና ሌሎች የማበረታቻ ስልቶች ተሟልተው እየተገበሩ አይደለም። ስለሆነም የአገር አቀፍ ትንበያውንና ክልላዊ ሁኔታዎችን በመተንተን ለቀጣይ የሚያስፈልገውን የሰው ሃብት ትንበያ ፣ ውጤታማ የአፈጻጸም መለኪያ ስርዓቶችን በመዘርጋት አፈጻጸምን መሰረት ያደረገ እድገት፣ የትምህርት እድልና የማበረታቻ ስልቶችን መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመድኃኒት እና የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦት እና አግባባዊ አጠቃቀም

9. ጥራቱን የጠበቀ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የመድሀኒትና የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦት ወሳኝ ሚና አላቸው። ሆኖም ግን እንደ አማራ ክልል 72 በመቶ የመንግስት ተቋማት የተሟላ አቅርቦት ያላቸው ሲሆን ለላብራቶሪና

የዲያግኖስቲክ አገልግሎት የሚውሉ ግብአቶች አቅርቦት በጣም ዝቅተኛ ነው። ለጤና አገልግሎት ከሚውሉ የመድሀኒትና የመሣሪያ ግብአቶች በአብዛኛው ከውጪ ሀገር በግዢ በማስገባት የሚገኙ ሲሆን በሀገር ውስጥ አልፎም በክልሉ የሚመረቱ ግብአቶች ዝቅተኛ በመሆናቸው በሀገር ኢኮኖሚና በአቅርቦት ሰንሰለት ላይ ከፍተኛ ጫና አስከትሏል። የመድሀኒትና የህክምና መሣሪያ አቅርቦትና አግባባዊ አጠቃቀም ለማሻሻል በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

10. የአቅርቦት ስርዓቱን ለማሻሻል ከሚተገበሩ አሰራሮች መካከል እንደ ሀገር በመተግበር ላይ የሚገኘው የተቀናጀ የመድኃኒት አስተዳደር ስርዓት (IPLS)፣ በኮምፒውተር የታገዘ የመድሃኒት አስተዳደር ሥርዓት(Dagu)፣ ለኦዲት ምቹ የሆነ የፋርማሲ አገልግሎት (APTS)፣ የክሊኒካል ፋርማሲ አገልግሎት፣ በኮምፒውተር የታገዘ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ሥርዓት(MEMIS) ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ግን የአቅርቦት ሰንሰለት መቆራረጥ፣ የመድሀኒትና የህክምና ቅድመ ትንበያና ልየታ ክፍተት፣ ረጅም የሆነ የግዢ ስረዓት፣ የመድሀኒት ብክነትና አግባባዊ አጠቃቀም ችግር ፣ ጊዜውን የጠበቀ የህክምና መሣሪያዎች ጥገና አለማድረግ አልፎም በኤሌክትሮኒክስ የተደገፈ የክትትል እና የአስተዳደር ስረዓት አለመኖር አልፎም በመድሀኒት ክምችት አያያዝ ችግርና የመድኃኒት ማስውጋጃ ማዕከል አለመኖር ከሚጠቀሱ ተግዳሮቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ ባሻገር የባህላዊ መድሀኒቶችን በጥናትና ምርምር መደገፍና ማሳደግ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

11. ይህ በእንዲህ እንዳለ በአማራ ክልል በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ባለፉት አራት አመታት የጤና ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል። ከግጭቱ በፊት የተቀናጀ የፋርማሲዩቲካል ሎጂስቲክስ ሲስተም (IPLS) መተግበሩ አስፈላጊ የሆኑ የጤና ግበዓቶች አቅርቦት በወቅቱ ለማሰራጨት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ነገር ግን የጤና ግብዓቶች አቅርቦት ከውጭ በሚገቡ መድሃኒቶች ላይ በዋናነት የተመሰረተ መሆኑ እና ውስን የሆነ የግል ዘርፍ ተሳትፎ መኖሩ አሁንም ተግዳሮቶች ሆነው ቀጥለዋል። በክልሉ በተከሰተው ግጭት ምክኒያት የወደሙና የተዘረፉ ተቋማት መብዛት፣ የህክምና መሣሪያዎች ብልሽት፣ አልፎም በፀጥታ ችግር የመንገድ መዘጋት የአቅርቦት ሰንሰለቱንና የህክምና አገልግሎቱን ክፉኛ በማስተጓጎል በማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል።

## የጤና ፋይናንስ

12. የጤና ፋይናንስ ለጤና ስርአቱ ዋንኛ ምሰሶ ሲሆን የኢትዮጲያ መንግስት የተለያዩ ስትራቴጅክ ፍኖተ ካርታ በመንደፍ የጤና ፋይናንስ ዘርፍ በማጠናከር ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል። የጤና ፋይናንስ ዋንኛ አላማውም የውስጥ ገቢን በማሳደግ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ማዳረስ ነው። አማራ ክልልም ለጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሃገራችን በፈረመችው የአቡጃ ስምምነት መሰረት 15 በመቶ የክልሉን በጀት ለተከታታይ አመታት ለጤናው ዘርፍ የመደበ ሲሆን በተመሳሳይ የማህበረሰብ የጤና መድህ ሽፍን በወረዳ 100% ማሳካት ተችሏል። ነገር ግን ሃገራዊ የነብስ ወከፍ የጤና ወጪ ($33.6) የአለም ጤና ድርጅት ለሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ካስቀመጠው ስታንዳርድ ($86) እና ከአማካኝ ታዳጊ ሀገራት($66) ጋር ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛ ነው።

13. በተመሳሳይም ቀጥተኛ ከኪስ የሚወጣ የህክምና ውጭ (out-of-pocket expenditure) ከፍተኛ(30%) መሆን፣ የአጋር አካላት ተሳትፎ በሚፈለገው መልኩ አለማደግ፣ ዝቅተኛ ገቢ መኖር፣ ደካማ የሃብት ማሰባሰብ ስርዐት ፣ የወጪ ቆጣቢነት ባህል አለማደግ ፣ የፋይናንስ ስረዓቱ ዲጂታይዝ አለመሆን እና አዳዲስ ችግር ፈቺ የጤና የፋይናንስ ሪፎርምችን ነድፎ ተግባራዊ አለማድረግል ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው። አልፎም የግሉ ዘርፍ(2.5%) እና የጤና መድህን ለጤናው ዘርፍ(1%) ያላቸው አበርክቶ ዝቅተኛ መሆኑ ተጨማሪ ተግዳሮት ፈጥሯል።

## የጤና ዲጂታይዜሽን እና መረጃ ስርዓት

14. በአማራ ክልል እየተተገበሩ ያሉ የዲጂታል የጤና መረጃ ስርዓቶች ለጤናው ስርዓት አስተዳደር እና የአቅርቦት ሰንሰለት ቅልጥፍና ልዩ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛል። በክልሉ ቀልጣፋና ዘመናዊ የጤና ስረዐት ለመዘርጋት በተሰሩ ሰፊ ስራዎች የዲጂታል ጤና ስርአቶች በተለያየ የትግበራ ደርጃ ላይ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት በትግበራ ላይ ከሚገኙ የዲጂታል ጤና ስረዓቶች EMR-MRU፣ Full EMR፣ Dagu፣ eCHIS፣ EMR-ART በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። በመጀመሪያ አሀድ የጤና አገልግሎት ላይ የተተገበረው የeCHIS ሲስተም ከቤተሰብ የጤና ማህደር ምዝገባ ጀምሮ አሁን ከRMNCH ሞጁሎች ጋር ወደ 1,684 የጤና ኬላዎች ላይ ተስፋፍቷል። እ.ኤ.አ ከ 2018 ጀምሮ DHIS-2 በሁሉም የመንግስት ሆስፒታሎች እና አብዛኛዎቹ የጤና ማዕከላት ባጠቃላይ በ1,051 የጤና ተቋማት ላይ እየተተገበረ ይገኛል።

15. EMR (Electronic Medical Record) ስርዓት በ አምስት (7) ጤና ተቋማት ብቻ እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን በአንዳንድ በተጀመረባቸው ተቋማት ስረዓቱ በገጠመው እክሎች ምክኒያት የመቋረጥ ችግር ገጥሞታል። የ EMR-ART የኤች አይ ቪ ሕክምና ሥርዓት ደግሞ የART አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም የኤሌክትሮኒክስ ሎጂስቲክስ አስተዳደር መረጃ ስርዓት (eLMIS) የመድኃኒት አቅርቦቶችን እንደ ቪታስ(VITAS) ለመጋዘን፣ ዳጉ(DAGU) ለጤና ተቋማት ለክምችት አስተዳደር እና mBrana ለክትባት ስርጭት የመድሀኒትና ክትባት አቅርቦትን ለማሳለጥ በጥቅም ላይ የዋሉ ስረዓቶች ነው። የማስተር ፋሲሊቲ መመዝገቢያ ስዓት (MFR) በ2020 በክልሉ መተግበር የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከ8,700 በላይ የጤና ተቋማት ተካተዋል። የክልሉን የጤና አይሲቲ መሠረተ(ICT) ልማት ለማሳለጥ ሄልዝኔት-ቪፒኤን(Health Net-VPN) በ 847 የጤና ተቋማት ላይ ADSL እና 3G ቴክኖፐሎጂዎችን በመጠቀም ተዘርገቷል። ምንም እንኳን በክልሉ ከላይ ያሉት የዲጂታል ጤና ስረዓቶች መተግበር የጀመሩ ቢሆንም የዲጂታል መሠረተ ልማት አለመስፋፋት፣ የሰለጠነ ባለሞያ አለመኖር፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎትና ኢንተርኔት መቆራረጥ፣ የተቋማት የውስጥ አውታረ መረብ(LAN) ዝቅተኛ መሆን፣ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች አቅርቦት ማነስ የሚጠቀሱ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

## የጤና ምርምርና ፈጠራ ስራዎች

16. የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የህብረተሰቡን ጤና ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ሰፊ ጥናትና ምርምር በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል። የምርምር ዳይሬክቶሬቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አስቸኳይ የክልል ጉዳዮችን ለመፍታት፣ መፍትሄዎችን ቅድሚያ ለመስጠት ፣ ፈጠራን ለማስፋፋት እንዲሁም የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማሻሻል የባህል ህክምናን ጨምሮ ዋና ዋና ጉዳዮችን በመለየት ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ ይገኛል።

17. የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመረጃ አያያዝና ትንተና የላቀ ሲሆን ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ከጤና መለኪያዎችና ገምጋሚ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር እንደ አማራ ክልል ጤና አትላስ ያሉ ጠቃሚ ግብአቶችን በማልማት ላይ ይገኛል።

18. ከተቋሙ ዋና ተልእኮዎች መካከል ስልጠና እና አቅም ማሳደግ ተጠቃሾች ናቸው። ተቋሙ በአገልግሎት ላሉ የጤና ባለሞያዎች ስልጠናዎችን ይሰጣል እንዲሁም የተመራማሪዎቹን ክህሎት ለማሳደግ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በቅርበት ይሰራል። በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ፓሊሲ አወጣጥን ለማገዝ ተላላፊ በሽታዎችን፣ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን፣ አመጋገብን እና የጤና ስርዓቶችን ጨምሮ ሰፊ ጥናቶችን ያደርጋል። ተቋሙ ወሳኝ የጤና መረጃን በህትመቶቹ በኩል በማሰራጨት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል ። ትብብርን እና የእውቀት መጋራትን ለማጎልበት በብሔራዊ ሳይንሳዊ ኮንፈረንስ ላይ በንቃት ይሳተፋል።

19. ምንም እንኳን ሰፋፊ ስራዎች እየተተገበሩ ቢሆንም አብዛኛው የምርምር ስራዎች በፕሮጀክት የተደገፈ ሲሆን እርዳታ ለማግኘት ወይም ፈጠራን ለማጎልበት በምርምር ማዕከላት መካከል በትብብር መስራት ዙሪያ ጉልህ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። አልፎም ለዕቅድ እና ለፖሊሲ መተርጎም የተገደበ የማስረጃ አጠቃቀም ፣ የተካኑ ተመራማሪዎች እጥረት፣ በቴክኖሎጂ የተሟሉ ማዕከላት አለመኖር እና የጸጥታ ችግር ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

## የጤና አገልግሎት

20. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአማራ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ህብረተሰቡ በቀላሉ የሚያገኛቸው፣ ተደራሽ የሆኑ፣ ተቀባይነት ያላቸውና ዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ጥራት ያላቸው የጤና አገልግሎቶችን ለመስጠት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በ1998 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው እና በ2012 ዓ.ም የተከለሰው መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ፓኬጅ በጤና ማበልጸግ፣ በሽታ መከላከል፣ የፈውስ እና የመልሶ የማገገሚያ አገልግሎቶችን ያካተተ እንዲሆን ተደርጓል። በተጨማሪም በእያንዳንዱ የአገልግሎት አሰጣጥ እርከን የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ዝርዝርም የለየ ሲሆን የሆስፒታሎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ የሁለተኛ እና የሶስተኛ እርከን ክብካቤ ተደራሽነት እየተስፋፋ መጥቷል። የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ በአንድ ጤና ጣቢያ እና በስሩ ባሉ አምስት ጤና ኬላዎች

ለገጠር የማህበረሰብ ክፍል አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። በከተሞች አካባቢ ጤና ጣቢያዎች የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

21. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የጤና ማበልፀግ እና በሽታን መከላከልን ጨምሮ መሰረታዊ እና አጠቃላይ የጤና አገልግሎት ፓኬጆችን እየሰጠ ሲሆን ይህም የውሃ፣ ሳኒቴሽን፣ ሃይጅን እና የአካባቢ ጤና፣ የፈውስ እና የመልሶ ማገገም ክብካቤን ያካተቱ ናቸው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የህብረተሰቡን የጤና ፍላጎት ለማሟላት እና በአገልግሎት ጥራት ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለመፍታት በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት አሰጣጥን የማጠናከር በርካታ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። የድንገተኛ የወሊድ እና ጨቅላ ሕጻናት ህክምና ተደራሽነትን ለማሳደግ መንግስት በጤና ጣቢያዎች በቀዶ ህክምና የማዋለድ አገልግሎት መስጫዎችን በመገንባት እና አገልግሎቱን በማስፋት ላይ ይገኛል።

22. ለቅድመ ጤና ተቋም ፣ የአደጋ ጊዜ እና ወሳኝ ክብካቤ አገልግሎቶች ለመስጠት በአሁኑ ወቅት በክልሉ 612 የሚሰሩ፣ 270 የማይሰሩ በድምሩ 882 አምቡላንሶች ቢኖሩም ሁለንተናዊ የአደጋ ጊዜ ተደራሽነት ማዕከል እጥረት ፣ ደካማ የአምቡላንስ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት፣ በአምቡላንስ የመሰረታዊ የህይወት ድጋፍ አቅርቦቶች እጥረት እና በአምቡላንስ ውስጥ የሚሰሩ የህክምና ባለሙያዎች ቁጥር ዝቅተኛ መሆን የሚስተዋሉ ዋነኞቹ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ደህንነታቸው የተጠበቀ የደም እና የደም ተዋጽኦ አገልግሎት በክልሉ 10 ደም ባንኮች የሚሰጡና የሚያስተባብሩ ሲሆን በዓመት የሚሰበሰበው አጠቃላይ የደም መጠን በ2014 ዓ.ም ከ80,160 ዩኒት በ2015 ዓ.ም ወደ 83,447 ከፍ ብሏል፣ ይህም በዋናነት በበጎ ፈቃደኝነት ደም ለጋሾች 99% ድርሻ የሚይዝ ነው።

23. በየእርከኑ በሚገኙ ተቋማት ሁሉን አቀፍ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ውጤታማ፣ ሰዎችን ያማከለ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል። የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያዎችን ለማጎልበት የኢትዮጵያ የሆስፒታል አገልግሎቶች ትራንስፎርሜሽን መመሪያ እና የሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ተግባራዊ ሁነዋል። በ2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ የሆስፒታል አገልግሎቶች ትራንስፎርሜሽን መመሪያ መሠረት በክልል ደረጃ በሁሉም ምዕራፎች 62 በመቶ አማካይ የአፈፃፀም ውጤት ተመዝግቧል። ባለፉት ሁለት አመታት የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላትና በሆስፒታሎች አካባቢ የሚስተዋሉ እሮሮዎችን ለመቅረፍ በተመረጡ ሆስፒታሎች ላይ እየተተገበረ የሚገኘው የስረዓት ማነቆዎች ላይ ያተኮረ ሪፎርም (SBFR) መልካም እምርታዎችን እያስገኘ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የሆስፒታል አልጋ የመያዝ መጠን 75 በመቶ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት የነፍስ ወከፍ ቁጥር 1.8 ማድረስ ተችሏል።

24. በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢዎች ጥራቱን የጠበቀ የላቦራቶሪና ሌሎች ዲያግኖስቲክ ምርመራዎች አገልግሎት ለመስጠት ሰፊ ስራዎች እየተሰራ ቆይቷል፡፡ በክልሉ የህክምና ላቦራቶሪ ምርመራ የመገኘት ምጣኔ (Laboratory test availability) በ2016 ዓ.ም በጤና ጣቢያ ደረጃ 26 በመቶ እንዲሁም በሆስፒታሎች 64.5 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡ አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረግ እና ከማስፋት አንጻር የምርመራ መሳሪያዎች አለመገኘት፣ የግብዓቶች አለመሟላት፣ በቴክኖሎጅ ታግዞ የመስራትና የማላመድ እጥረት፣ በተዋረድ ለሚገኙ የጤና ተቋማት የሚደግፍና የሚከታተል ባለሙያ አለማሟላት በስራዉ ዘርፍ የተወሰኑ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ሆስፒታልን መሠረት ያደረጉ የስፔሻሊቲ እና የማገገሚያ አገልግሎቶች በዩኒቨርሲቲዎች እና በሌሎች ስፔሻሊቲ ሆስፒታሎች ተመድበው በ8 አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች አገልግሎት ይሰጣሉ። ምንም እንኳን በክልላችን ሁለት የአካል ተሃድሶ አገልግሎት ማዕከላት ያሉ ሲሆን በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ የሚደረግላቸው ድጋፍና ክትትል ዝቅተኛ ነው። የሕክምና መሳሪያዎች አቅርቦት እጥረት እና መቆራረጥ፣ ጠንካራ የመንግስት እና የግል አጋርነት አለመኖሩ የስፔሻሊቲ እና ሰብ ስፔሻሊቲ እንዲሁም የተሃድሶ አገልግሎቶች በቂ እንዳይሆን አድረጎታል። በተጨማሪም በጤናው ስርዓት ውስጥ የጤና አገልግሎት አቅርቦት፣ ግዥና የቁጥጥር ስርዓት በአንድ የአመራር ስርዓት ውስጥ መሆናቸው የአገልግሎት አቅርቦት ጥራትና ተጠያቂነትን ለማስፈን አስቸጋሪ አድርጎታል።

## የስነ ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ ህጻናት ጤና አገልግሎት አጠቃቀም

25. ጥራቱን የጠበቀ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ለማሻሻል የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ተቋማትን አቅም በማሳደግ አዳዲስ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለመጨመር የሚያስችሉ ስራዎች ሲሰሩ ቆይቷል፡፡ በዚህም የተነሳ በአማራ ክልል ባለፉት 10 አመታት በአማካኝ 84 በመቶ

የቤተሰብ እቅድ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ማድረስ ተችሏል። ይህም ከሀገርና አለም አቀፍ ግቦች አፈፃጸምጋር ሲወዳደር ክልሉ የአገልግሎት ተደራሽነትና ጥራትን አጠናክሮ መስራት እንዳለበት ያሳያል፡፡ የግብዓትና የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት ከሰው ሰራሽና ተፈጥራዊ ተግዳሮቶች በተጨማሪ በዋናነት ለአፈጻጸሙ ተግዳሮት መሆናቸውን እንደ ምክንያት ይነሳሉ፡፡

26. እንደ አማራ ክልል አጠቃላይ የነፍሰ ጡር እናቶች ህክምና ክትትል የጨመረ ቢሆንም ከ12 የእርግዝና ሳምንት በፊት የሚሰጥ የቅድመ ወሊድ ክትትል አፈፃጸም በጣም ዝቅተኛ ነው (ባልፉት አመታት ከ 25% ማሳለፍ አልተቻለም)። ባለፉት አስር አመታት በአማካኝ 69 በመቶ ነፍሰ ጡር እናቶች 4 ጊዜና ከዚያ በላይ ክትትል ተመዝግቧል፣ 61 በመቶ ለሚሆኑ እናቶች በሰለጠነ ባለሞያ የታገዘ የወሊድ አገልግሎት፣ 77 በመቶ ከወሊድ በኋላ በሰባት ቀን ውስጥ የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ተሰጥቷል። ሆኖም ግን ከአለም አቀፍና ሃገራዊ ግቦች ጋር ሲወዳደር አንደ ክልል የእናቶች ህክምና ተደራሽነትና ጥራት ላይ አጠናክሮ መስራት እንዳለበት ያሳያል። በተመሳሳይ በ 2015 ክልላዊ መረጃ እንደሚያሳየው በቀዶ ጥገና የወሊድን አገልግሎት ያገኙት 5 በመቶ ብቻ ሲሆን ይህ አፈጻጸም ከክልል ክልል አፈጻጸሙ ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል(ለምሳሌ 52 በመቶ አዲስ አበባ )።

27. የህፃናት ህመም እና ሞትን ዋና ዋና መንስኤዎችን ለመከላከል እና ለማከም በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል ። በዚህም መሰረት የህፃናት ክትባት እንደ ሃገርም ሆነ እንደ ክልል በከፍተኛ ትኩረት ተሰርቷል። እንደ አማራ ክልል ባለፉት 10 አመታት በአማካኝ 87 በመቶ ህፃናት ሙሉ ክትባት ሽፋን ማድረስ ተችላል።

28. ስዕል 18 – 2፤ በአማራ ክልል የስነ ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ ህጻናት ጤና አገልግሎት አጠቃቀም ከ 2007-2016




## ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች

29. በበሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር ፕሮግራም ረገድ ባለፉት ጊዜያት አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ላለፉት አስርት አመታት እንደ ኤች አይ ቪ፣ ቲቢ እና ወባ ባሉ ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰት ህመምና ሞት በከፍተኛ መጠን መቀነስ ተችሏል፡፡ ለኤችአይቪ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለይቶ በጥምር የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል/መቆጣጠር የባሕርይ ለውጥ ተግባቦት ስርጸት ፕሮግራሞች ከ88 በመቶ በላይ በመፈጸማቸው ካለፉት ጊዜያት ጋር ሲነጻጸር ትልቅ መሻሻል አሳይቷል፡፡ የተፈጠሩ የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችን ተከትሎ ክልሉ ሶስቱን የ95 በመቶ የኤች አይ ቪ ዒላማ በማሳካት ረገድ መሻሻል አሳይቷል፡፡ ኤች አይ ቪ በደማቸው ከሚኖሩ

ሰዎች ውስጥ 91 በመቶ የሚሆኑት የኤች አይ ቪ ሁኔታቸውን አውቀዋል፣ ከኤች አይ ቪ ጋር መኖራቸውን ካወቁት መካከል 99 በመቶ ያህሉ የጸረ ኤች አይ ቪ መድኃኒት መጠቀም የጀመሩ ሲሆን መድኃኒት መጠቀም ከጀመሩት መካከል 97 በመቶ የሚሆኑት በደማቸው ውስጥ የሚገኘው የቫይረስ መጠን መቀነስ አሳይቷል፡፡

30. ስዕል 18– 3፤ በ አማራ ክልል የ HIV/AIDS የህክምና አገልግሎት ዋና ዋና መለኪያዎች 2007-2016




31. በኢትዮጵያ ከ100,000 ህዝብ መካከል 119 የሚሆኑት የቲቢ በሽታ ይኖርባቸዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከፍተኛ የቲቢ በሽታ ጫና ከሚበዛባቸው 30 ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ስትሆን ከ5ቱ ከፍተኛ የሞት መንስኤ መካከል የቲቢ በሽታ አንዱ ነው። የ2016 በጀት አመት የአማራ ክልል አመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት እንደሚያሳየው የቲቢ ህክምና ሽፋን 66 በመቶ ማድረስ የተቻለ መሆኑ እና ይህ ሽፋን ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነው፡፡ እንዲሁም ሕክምና በትክክል ወስደው ያጠናቀቁ መጠን ወደ 96 በመቶ ማድረስ ተችሏል። የሳንባ ነቀርሳን የመለየት ምጣኔ ወደ 66 በመቶ ያደገ ሲሆን የህክምናው ስኬት ምጣኔ ደግሞ ከ90 በመቶ በላይ መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን መድሀኒት የተላመደ የቲቢ (DR-TB) በሽታ አሁንም የህብረተሰብ የጤና ችግር ሆኖ እንደቀጠለ ነው፡፡ የወባ ክስተት በተለይ በቆላማ አካባቢዎች ከግጭት እና ከአካባቢያዊ ለውጦች ጋር ተያይዞ ቁጥሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በቀጣይ ትኩረት የሚሻ ዋነኛ ችግር ሆኖ ቀጥሏል። የወባ በሽታን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንጻር እ.ኤ.አ በ2030 የወባ በሽታን የማጥፋት ፕሮግራም በተለያዩ የክልሉ ዞኖች በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

32. ስዕል 18 – 4፤ የክልሉ የወባ በሽታ ሳምንታዊ ክስተት ከ2012 እስከ 2016 የበጀት ዓመት ያሳየው አዝማምያ




## ትኩረት የሚሹ የሀሩራማ አካባቢ በሽታዎች

33. በኢትዮጵያ ከሚገኙ አሰራ ሁለት ሃሩራማ በሽታዎች ስምንቱ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰፊው የሚገኙበት ሲሆን እነሱም ትራኮማ፣ የሆድ ጥገኛ ትላትሎች፣ ብልሃርዝያ፣ዋራ፣ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ፣ ተላላፊ ያለሆነው ዝሆኔ፣ እከክና ሊሽማኒያሲስ በሽታዎች ናቸው፡፡ ሃሩራማ በሽታዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ክልሉ እየተከተላቸው ያሉ ስልቶች የህብረተሰብ አቀፍ የመድሃኒት ስርጭት እና ለበሽታዎቹ ተጠቂዎች ቀጥተኛ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ የበሽታዎቹን ስርጭት ለመግታት እና በወረርሽኝ ደረጃ እንዳይከሰቱ ለማድረግ የውሃ፣ ስነ-ጤናና ስነ-ንጽህና እንዲሁም የማህብረሰብ ባህሪ ለውጥ ማስረጽ ተግባራት በሁሉም ሃሩራማ በሽታዎች ይሰራሉ፡፡

34. በአጠቃላይ ክልሉ የኤድስ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የወባ በሽታ፣ የጉበት በሽታ እና ትኩረት የሚሹ ሃሩራማ በሽታዎችን ለማስወገድ እንዲሁም ውሃ ወለድ በሽታዎችን እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የዘላቂ ልማት 2030 ግቦችን ከማሳካት አንፃር እጅግ ወደ ኋላ ቀርቷል።

## ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች

**35.** ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ክስተት እየጨመረ ቢመጣም የስኳር በሽታ እና የልብና የደም ቧንቧ በሽታዎች ምርመራ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡት 54 በመቶ የሚሆኑት የጤና ተቋማት ብቻ ናቸው፡፡ የጡት እና የማህጸን ካንሰር በአዋቂዎች ላይ በጣም የተለመዱ የካንሰር ዓይነቶች ሲሆኑ ሪፖርት ከተደረጉት ዓመታዊ የጡት የካንሰር ሞት ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የሚሆኑት በሴቶች ላይ የሚከሰቱ ናቸው። የማህጸን በር ቅድመ ካንሰርና ካንሰር ልየታና ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ብዛት 352 (32%) ሲሆኑ በባለፉት አመታት የማህጸን በር ካንሰር ቅድመ ምርመራ የተደረገላቸዉ ሽፋን 12.5 በመቶ ሲሆኑ 5 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ቅድመ ካንሰር ምልክቱ ተገኝቶባቸዋል፡፡ ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ ስለ ካንሰር ምልክቶች ያለው ግንዛቤ ውስንነት፣ በቂ ቅድመ ምርመራ አለማድረግ፣ በወቅቱ ልየታና ህክምና አገልግሎት አለመጀመር እና በቂ የምርመራ እና ህክምና መስጫ ተቋማት አለመኖር ለከፍተኛ የሞት መጠን አጋላጭ ምክንያት ናቸው። በ2015 ዓ.ም የዓይን ሞራ ግርዶሽ የቀዶ ጥገና ምጣኔ (CSR) በተያያዘ ከአንድ ሚሊዮን ሰዎች 794 አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል።

36. ከላይ የተቀመጡ ቁጥሮች እንደሚያመለክቱት ክልሉ እንደ እኤአ 2030 ላይ እንዲሳኩ ከሚጠበቁት የዘላቂ ልማት ግቦች መካከል ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ያለጊዜው የሚያደርሱትን ሞት በመከላከል እና በህክምና በአንድ ሶስተኛ መቀነስ ከማሳካት አንጻር ወደ ኋላ መቅረቱን ያሳያል።

37. በአጠቃላይ በክልሉ የተሻሻለ የአገልግሎት ተጠቃሚነት እና የጤና ሁኔታ ቢኖርም የአገልግሎት ተደራሽነት፣ አሁንም የተጠቃሚነት እና በጤና ላይ የተገኘ ውጤት አናሳ መሆን ፣ በግጭት እና ድንገተኛ አደጋዎች የአገልግሎት መቆራረጥ በጤና ዘርፉ በከፍተት የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ በሌላ መልኩ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል በአካባቢ፣ በዕድሜ፣ በፆታ እና በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አሁንም ድረስ በጤና ደረጃና በአገልግሎት ተጠቃሚነት ረገድ ከፍተኛ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡

38. የህክምና ጥራት ጋር በተያያዘ አሁንም ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑ እና በጤና ተቋም ደረጃ የህክምና ግብዓቶችና ቁሳቁሶች አቅርቦትም ዝቅተኛ መሆን፤ የጤና የሰው ሀብት በቁጥርና በስብጥር ከተቀመጠው ስታንዳርድ በእጅጉ ያነሰ መሆኑ እና ለህክምና አገልግሎት ከኪስ የሚወጣው ገንዘብ መጠን ከፍተኛ በመሆን የአገልግሎት ማነቆዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የአማራ ክልል የጤና ስርዓት የጤና አገልግሎት በማሻሻል ረገድ እድገት እያስመዘገበ ቢሆንም ያሉትን ክፍተቶች ለመቅረፍ እና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት እና ስትራቴጂክ እቅድ ማውጣትን ይጠይቃል።

## የአደጋ ጊዜ ምላሽ አቅምና አስተዳደር

39. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተለያዩ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እና የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች ለተከታታይ አመታት ተጎድቷል። ባለፉት ሦስት ዓመታት፣ የጤና ዘርፉ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ የአገልግሎት ተደራሽነት እና የመቆራረጥ ፈተና ገጥሞታል፡፡ በክልሉ በተሰራ የጉዳት ዳሰሳ 863 ተቋማት ውስጥ 506(59.%) የጎዱና የተዘረፉ ተቋማት ተገኝተዋል።

40. በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ድርቅ እና ጎርፍ ሲሆኑ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ግጭት ፣ ተላላፊ በሽታዎች (እንደ ኮሌራ፣ እከክ፣ ኩፍኝ፣ ወባ፣ የእብድ ዉሻ በሽታ፣ አንትራክስ እና ኮቪድ-19) ፣ የእናቶች እና የጨቅላ ህፃናት

ሞት፣ ከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት፣ እና የሰብል ተባዮች የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እና አገልግሎት እንዲታወክ ምክኒያት ሆነዋል፡፡

41. በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት፣ ከኦሮሚያ ክልል በኦነግ ሸኔ ብሔር ተኮር ጥቃት እና በሰሜን ሸዋ ዞን እና በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን መካከል የተፈጠረው የውስጥ ግጭት ምክንያት ከ3.1 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸዉ መፈናቀላቸው ይታወሳል። በ2016 በድምሩ ከ3.1 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የተፈናቀሉ ሲሆን 2.3 ሚሊዮን የሚበልጡ ተፈናቃዮች ወደ ቤታቸው የተመለሱ ቢሆንም ከስደት የተመለሱ ተፈናቃዮች የተሟላ የጤና እና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማግኘት ባለመቻላቸው አሁንም ሰብዓዊ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

42. በጦርነትና ግጭት ምክኒያት የጤና ባለሙያዎች መፈናቀል የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድርዋል፡፡ በግጭትና በጦርነት የተጎዱ ሀገራት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጦርነት ከሚፈጥረው ጊዜያዊ የሞትና የቁስለት አደጋ ባሻገር በጤና እና ጤና ነክ አገልግሎቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይታወቃል። በጥናቶች በግልፅ እንደተቀመጠው በጦርነት ምክኒያት የአንድ ሰው ህይወት ሲጠፋ ተጨማሪ ከአምስት እስከ አስር የሚጠጉ ሰዎች የጤና ክብካቤ የሚያስፈልገው ጉዳት ይደርስባቸዋል። ይህ ደግሞ በተዳከመው የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተጨማሪ ጫና ያሳድራል። ጦርነትና ግጭት በጤናው ስረዓት ላይ በሚያሳርፈው ጫና  እናቶችና ህፃናት በዋናነት የሚጎዱ የህብረተሰቡ ክፍሎች ሲሆኑ በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች የእናቶች ሞት ምጣኔ በአማካይ ከ 15 በመቶ እስከ 25 በመቶ እንደሚጨምር በጥናቶች ተረጋግጧል። የመድሀኒትና የክትባት አቅርቦት ሰንሰለት በመቋረጡ ምክኒያት በህፃናት ላይ በክትባት መከላከል የሚቻሉ ህመሞችና ወረረሽኞች በብዛት ይከሰታሉ። በተጨማሪም በህፃናት ላይ የምግብ እጥረት ችግር ጉዳት ይደርሳል። ክልሉ የመጀመሪያውን የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በማቋቋም ከክሎች ቀዳሚ ሲሆን በዋናነት የድንገተኛ አደጋዎችና ክስተቶች ቅኝት ፣ ዝግጅት ፣ ምላሽ በመስጠት አልፎም የተሀድሶ ስራዎች በመስራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። ፈጠራ የታከለበት አሰራሮች እንደ የክልሉ የመረጃ ቋት አስተዳደር መዓከል(RDMC) እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የሪፓርት መሰብሰቢያ ዘዴ (Smart PHEM) በመተግበር የክልሉን የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር አሻሽሏል።በዞን ደረጃ የህብረተሰብ ድንገተኛ አደጋዎች ማስተባበሪያ ማዕከል በማዋቀር (PHEOC) ጊዜውን የጠበቀ የድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ ስረዓት ተገንብቷል። ሆኖም ግን ውስን የሆነ የማህበረሰብ ተሳትፎ ፣ የሀብት ማሰባሰብ ፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማነስ ፣ የባለሞያዎች ውስንነትና አቅም ማነስ የዘርፉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

## ዋና ዋና የጤና ተጽዕኖ አመልካቾች አፈፃጸም

43. ባለፉት አስርተ አመታት በጤና አገልግሎት ፍታዊነት ተደራሽነትና ጥራት በተሰራው ሰፊ እና አመርቂ ስራ በክልላችን ብሎም በሃገራችን ከፍተኛ የሆነ ጤና እምርታ ተመዝግቧል። ለማሳያ ያክል ከ 2000 እስከ 2022 እኤአ የእናቶች ሞት ምጣኔ ከነበረበት 871 ወደ 267  ቀንሷል (100፣000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት)። ነገር ግን የተላላፊ በሽታ ስርጭት እና የእናቶች እና የህፃናት የጤና ችግሮች በሚፈለገው መጠን መቀነስ አልተቻለም ይባሱን የተላላፊ በሽታዎች ወረርሽኝ በተዳጋጋሚ በክልላችን እየተከሰተ ይገኛል። ባለፉት ጥቂት አመታት እንደ ሀገር ሆነ እንደ ክልል ተላላፊ ያልሆኑ የጤና ህመሞች እና አደጋዎች እያደጉ የመጡ የጤና ስጋቶች ሆነዋል። በአማራ ክልል የተራዘመው የሰሜኑ ጦርነትና ከልላዊ ግጭት፣ ወረርሽኝ እና የበዛ የተፈጥሮ አደጋዎች በጤናው ስርዐትና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት ፈጥሯል። በዚህም የተነሳ ዋና ዋና የጤና ተጽዕኖ አመልካቾች አፈፃጸም ከሃገራችን እና አለም አቀፍ ግቦች ጋር ሲወዳደሩ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም።

44. ሠንጠረዥ 18 -1፡ ዋና ዋና የጤና ተጽዕኖ አመልካቾች አፈፃጸም በአማራ ክልል

| ዋና ዋና የጤና ተጽዕኖ አመልካቾች አፈፃጸም | ባለፉት አስረ አመታት ክልላዊ ና ሃገራዊ አፈፃጸም | | | | | | ሀገራዊ ዒላማዎችበ 2026 | አለማቀፋዊ-ዒላማዎች በ 2030 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2000 | 2005 | 2011 | 2016 | 2019 | 2022 | | |
| የእናቶች ሞት ምጣኔ* | 871 | 673 | 676 | 412 | 401 | 267 | 199 | 70 |
| አማካኝ የመኖር ዕድሜ ጣሪያ | 50.6 | | 62.9 | 66.8 | 67.8 | 68.7 | 70 | |
| ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን | | | | | | 0.38 | 0.58 | 0.8 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ5 ዓመት በታች የህጻናት ሞት ምጣኔ** | አማራ ክ | 183 | 154 | 108 | 85 | 69 | 69 | 44 | < 25 |
| | ኢትዮጵያ | 166 | 123 | 88 | 67 | 55 | 47 | | |
| እድሜያቸው ከአንድ አመት በታች የሆኑ ሕፃናት ሞት ምጣኔ** | አማራ ክ | 112 | 94 | 76 | 67 | 58 | 58 | 32 | NA |
| | ኢትዮጵያ | 97 | 77 | 59 | 48 | 43 | 34 | | |
| የጨቅላ ሕፃናት ሞት ምጣኔ** | አማራ ክ | 60 | 50 | 54 | 42 | 46 | 46 | 21 | NA |
| | ኢትዮጵያ | 48 | 39 | 37 | 29 | 33 | 26 | | |
| ከ 5 ዓመት በታች ህጻናት መቀንጨር መጠን (በመቶኛ) | አማራ ክ | 57 | 56.6 | 52 | 46.3 | 41.3 | 40 | 25 | <25 |
| | ኢትዮጵያ | 57.8 | 51.5 | 44.4 | 38.4 | 36.8 | 39 | | |
| ከ 5 ዓመት በታች ህጻናት መቀጨጭ መጠን (በመቶኛ) | አማራ ክ | 9.5 | 14.2 | 9.9 | 9.8 | 15 | 15 | 7.8 | <5 |
| | ኢትዮጵያ | 12.9 | 12.4 | 9.7 | 9.9 | 7.2 | 11 | | |

* የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ100,000 በህይወት ከተወለዱ ህጻናት **የ ህፃናት ሞት ምጣኔ በ1000 በህይወት ከተውለዱ ህጻናት፣
ከ 2000 _2019 ያሉ መረጃዎች ከ EDHS ፤ ከ 2022 _2026 መረጃ ከ ከ HSDIP እንዲሁም አለም አቀፍ ግቦች ከ SDG-2030 ተወስዳዋል

## የመንግስትና የግል አጋርነት (Public Private Partnership)

45. የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት ከ30-35 በመቶ የሚሆነውን የጤና አገልግሎት በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽዎ እያበረከተ ይገኛል። ሆኖም ግን ከተደራሽነት፣ ከጥራት እንዲሁም ከህክምና ዋጋ መናር ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ችግሮች ይታያሉ። መንግስት የግል ጤና ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቁና የሚስጡት አገልግሎት ጥራት ያለውና የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ አቅም ባገናዘበ መልኩ መሆን እንዲችል መቆጣጠርና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል። የግሉ ዘርፍ በጤና በኢንሹራንስ ማዕቀፎች እንዲሳተፉ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን መቅረጽና መተግበር በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ያለውን ተግዳሮት ለማሻሻል ይረዳል።

46. በተጨማሪም የግሉ ዘርፍ አንዳንድ የጤና አገልግሎቶችን ለምሳሌ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠይቁ የምርመራና ህክምና አገልግሎቶችን በትብብርና በጋራ ተጠቃሚነት ማቅረብ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል ። እንዲሁም በክልሉ ከሚገኙ አገራዊና አለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር ውጤናታማ አጋርነት መፍጠር ይገባል፡፡

## የባለብዙ ዘርፍ ትብብር

47. የጤናው ሴክተር ዘርፈ ብዙ እና ጠንካራ ተቋማዊ ትብብርን ይፈልጋል። ሴክተሮች ጤናን በሁሉም ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎቻቸው በማካተት ድጋፍና ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም በክልሉ ግን ጤና ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ሴክተሮች አንዱ መሆኑን በመገንዘብ እንዲሁም አስፈላጊ እና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራትን በዘርፈ ብዙ ትብብር ማዕቀፍ ከመከወን አንጻር ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ የጤናው ሴክተር በክልሉ የሚገኙ ሴክተሮችና ተቋማትን በመለየት አስፈላጊውን አጋርነት መፈጠርና የጤናው ዘርፍ ጉዳዮች ከሴክተሮች ፖሊሲና ስትራቴጅዎች ጋር የተመላከተና እየተተገበረ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

## የማህብረተሰብ ተሳትፎና ባለቤትነት

48. የጤና ዘርፍ ግቦችን ለማሳካት የማህበረሰብ ባለቤትነት ዋነኛው መርህ እና ስትራቴጂ ነው። በአማራ ብሔራዊ ክልል ከጤና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር ጋር ተያይዞ የማህበረሰቡ ተሳትፎ ከፍተኛ ነው። የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች

የሴቶች ልማት ቡድንን (WDG) ከማህበረሰቡ አባላት በመመልመል የማህብረሰቡን ተሳትፎና ባለቤትነትን ለማሳደግ ተሞክሯል። ነገር ግን የማህብረሰቡ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ሄዷል። ባለፉት ዓመታት በክልሉ ከተከሰቱት የፖለቲካ ነውጦች ፣ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች ጋር ተያይዞ የመጣውን የማህበረሰብ አቀፍ ተሳትፎ መቀዛቀዝ ለማሻሻል በአንዳንድ ወረዳዎች የጎጥ የማህበረሰብ ጤና አመራሮችን (Village Health Leaders) በማፍራት የማህበረሰብ ተሳትፎ የማጠናከር ስራ ተጀምሯል። ውጤታማ ስልቶችን በማስፋት መተግበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ አዳዲስ ዘዴዎችን መንደፍና መተግበር ህብረተሰቡ የራሱን ጤና እንዲያበለጽግና ለሴክተሩ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ተጨማሪ ስራዎች መስራት ይጠይቃል።

## 18.3. የትኩረት አቅጣጫዎች

49. የአማራ ብሔራዊ ክልል የጤና ዘርፍ ፍኖተ ካርታ እና ዋና ዕቅድ 12 የየትኩረትና የትግበራ አቅጣጫዎችን አመላክቷል፤
    1. የጤና መሠረተ ልማት ማሻሻል
    2. የክልሉን አሁናዊ እና የወደፊት ፍላጎት መሰረት ያደረገ የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ማሻሻል
    3. ፈጠራ የታከለበት እና አካታች የሆነ የጤና ፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት
    4. የጤናው ዘርፍ አመራር፣ አስተዳደር እና ተጠያቂነት ማጎልበት
    5. የመድኃኒት እና የህክምና መሳሪያዎች ተደራሽነት፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን በማሻሻል ቀጣይነት ማረጋገጥ
    6. የጤና ክብካቤ ጥራት፣ ደህንነት እና ፍትኃዊነት ማሻሻል
    7. የጤና ክብካቤ ደህንነት ማሻሻል
    8. ዲጂታል ጤና እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ
    9. የህዝብ ጤና ድንገተኛ አስተዳደር ስርዓትን የመቋቋም እና ውጤታማነትን ማሳድግ
    10. የጤና ምርምርን ማሳደግና የፈጠራ ስራዎችን ማፋጠን
    11. የማህበርሰብ ተሳትፎን ማሻሻል
    12. የጤና ቁጥጥርን ሥርዓት ማሻሻል።

## 18.4. ዋና ዋና ግቦች

- የጤና መሰረተ ልማት ተደራሽነትንና ደረጃን ማሻሻል
- የክልሉን የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ፍላጎት ማሟላት
- ስትራቴጂካዊ ግቦችን ለማሳካት ከሚያስፈልጉት መስፈርቶች ጋር ለማጣጣም የፖሊሲ እና መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን ማሻሻል
- የጤና ክብካቤ ደህንነት ማሻሻል
- የእናቶችን ፣ የጨቅላ ህጻናትን እና ህጻናትን ሞት ምጣኔን መቀነስ
- የኤችአይቪ/ኤድስ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የወባ በሽታ እና ትኩረት የሚሹ የሐሩራማ አካባቢዎች በሽታዎችን መከላከል እና ህክምና ማጠናከር
- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና ህክምና ማሻሻል
- የጥራት ያለው ፍትሃዊ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥን ማረጋገጥ
- የዲጂታል ጤና መሠረተ ልማት መገንባት እና የዲጂታል ጤና ሶሉሽኖች ትግበራ አጠቃቀም ማሳደግ
- ለሁሉም የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች ዝግጁነት እና ምላሽ መስጠትን ማረጋገጥ
- የቅኝት እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓትን ማሻሻል
- ዘመናዊ የሕክምና ማዕከላትን በስትራቴጂካዊ ቦታዎች ማቋቋምና ነባር የህክምና ተቋምትን ማዘመን

- የምርምር አቅምን እና ትብብርን ማጠናከር
- መረጃዎችን ማደራጀትና ለፖሊሲ ግብአት ማዋል
- በአሰራር እና በጤና ግብአቶች ላይ ፈጠራን ማበረታታት
- የሀገር በቀል ዕውቀትን እና ባህላዊ ህክምናን መጠበቅና ማሳደግ።

# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

# የማሕበራዊ እና ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች ልማት

## 19.1. የዘርፉ ሚና

50. በዚህ ዘርፍ የተካተተው የሴቶች፣ የህጻናት፣ የወጣቶች፣ የአረጋዉያን፣ የአካል ጉዳተኞች እና የስነህዘብ ጉዳይ ሲሆን ዘርፉ በክልሉ ውስጥ የሴቶችን፣ የሕፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋዊያንን እና የአካል ጉዳተኞችን መብቶችንና ጥቅሞችን ለማስከበር የሚረዱ የፖሊሲ ሀሳቦችን ማመንጨት፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ሲሆን በመብቶቻቸው ዙሪያ የተደነገጉ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች በክልሉ ተፈጻሚ ስለመሆናቸው ክትትል ማድረግ፣ በክልሉ የመንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ሪፖርቶች የሴቶችን፣ የሥርዓተ-ጾታን፣ ሕፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋዊያንንና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳዮች ለማካተት የሚያስችላቸውን ስልት በመንደፍ ተሳትፏቸውንና ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ ሚና አለው፡፡

51. ከዚህ በተጨማሪም መድልኦዎችንና የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሀሳቦች የማመንጨትና የመከታተል፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸው የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራዎችን የማከናወን፣ በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ሕገ-ወጥ ዝውውርና ፍልሰት፣ የጉልበት ብዝበዛ እና ሌሎች የመብት ጥሰቶችን ለመከላከል የሚረዱ የአሠራር ሥርዓቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመዘርጋት፣ ሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች እንዲሁም አረጋውያን በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ተሳትፏቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ለክልሉ መንግሥት ሀሳብ የማቀረብና የመከታተል፣ እንዲሁም የተለያዩ የክልሉ መንግሥት አካላት ሴቶችንና ወጣቶችን በውሳኔ ሰጭነት ቦታዎች በቂ ትኩረት ተሰጥቶ ስለመመደባቸው የመከታተል ሚና አለው፡፡

52. ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ ወጣቶችን፣ አረጋዊያንንና የአካል ጉዳተኞችን በነጻ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉ ሁለንተናዊ ድጋፍ የማድረግና የመከታተል እንዲሁም አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ሌሎች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ አሰራሮችን የመዘርጋት ሚና ይኖረዋል፡፡

53. በሌላ በኩል በዘርፉ ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ ወጣቶችን፣ አረጋዊያንንና አካልጉዳተኞችን ለሚያግዙና ለክልሉ ዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ሀብት በማፈላለግ ውጤታማ እንዲሆን የመከታተል እና የመደገፍ ስራ ይሰራል፡፡ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች ይወገዱ ዘንድ እንደሴተኛ አዳሪነትና ጎዳና ተዳዳሪነት ላሉ አስከፊ ችግሮች የተጋለጡ ወገኖችን የማደራጀትና የማቋቋም፣ የማኅበራዊ ጥበቃ ተቋማትን በማቋቋም ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል የማድረግ፣ የዜግነት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት እንዲዘረጋና የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር የመስራት እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጭ ድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት የመቀየስና የመተግበር ሚና አለው፡፡

54. ከዚህ በተጨማሪም ዘርፉ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በክልሉ እንዲስፋፋና ባህል እንዲሆን የማስተባበር፣ የበጎ ፈቃድ ማኅበራትን የማደራጀት፣ ድጋፍ የመስጠትና የመከታተል ሚና ያለው ሲሆን ወጣቶችን ከማኅበራዊ ጠንቆች፣ ከአደንዛዥ እጾችና አሉታዊ መጤ ባህሎች እንዲሁም ሌሎች ጤንነታቸውን ከሚጎዱ ነገሮች በመከላከል በሥነ- ምግባር የታነጹ፣ ንቁና ሀገር ወዳድ ዜጎች እንዲሆኑ እና ብሔራዊ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ሁሉ አገልግሎት እንዲሰጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የመስራትና ተፈጻሚነቱንም የመከታተል ሚና አለው፡፡ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ተቋማት በየደረጃው እንዲገነቡና የተገነቡ ማዕከላትንም በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች በባለቤትነት በመያዝ አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግና የሕግ ከለላ እንዲኖራቸው ድጋፍ የመስጠት ስራዎችንም ይሰራል፡፡ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የወጣቶች ልማት ፈንድ በማቋቋምና በማስተባበር የወጣቶችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ሚናም ይኖረዋል፡፡

55. በሌላ በኩል ዘርፉ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዩችን አስመልክቶ ጥናትና ምርምር የማካሄድ፣ መረጃዎችን የማደራጀት፣ ለተጠቃሚዎችም የማሰራጨት ሚና ያለው ሲሆን መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከብሔራዊው የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አፈጻጸም አኳያ የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎችንም የማስተባበርና የመምራት እንዲሁም ከነዚሁ አካላት ጋር በመቀናጀት የመስራት ሚና ይኖረዋል፡፡

## 19.2. የሁኔታ ትንተና

### ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

56. መንግስታት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈንና ሴቶችን ለማብቃት ቁልፍ የሆኑትን አብዛኛዎቹን የዓለም አቀፍ ስምምነቶችንና መገለጫዎችን የፈረሙ ሲሆን እኤአ በ1979 በሴቶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውንም ዓይነት መድልዎ የተፈረመው ስምምነት፣ እኤአ በ1993 በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማስወገድ የተፈረመው ድንጋጌ፣ እኤአ በ1994 የተካሄደው የስነ-ህዝብና ልማት ዓለም አቀፍ ጉባኤ እንዲሁም ዘላቂ የልማት ግቦች የሀገሪቱ የህግና የፖሊሲ አካል ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማሳካት በቤጅንግ የድርጊት መርሃ-ግብር (እኤአ በ1995) እንደቁልፍ ስትራቴጅ ተቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች ሊደረስባቸው ይችላሉ የተባሉ 17 ግቦችን የያዘ ሲሆን በተለይም ግብ 5 የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን በማራመድና ሴቶችን በማብቃት ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም ለጉዳዮቹ ትኩረት ሰጥተው የፈረሙ ሀገራት ለተግባራዊነታቸው ትኩረት ሰጥተው መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

57. በህጻናት መብቶች ስምምነት የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 1989 እ.ኤ.አ በተቀመጠው መሰረት ለህጻናት ልዩ እንክብካቤ የማድረጉ አስፈላጊነት በ1924 እ.ኤ.አ በወጣው የጄኔቫ ህጻናት መብቶች መግለጫ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤው በ1959 እ.ኤ.አ በተቀበለው የህጻናት መብቶች መግለጫ መመላከቱና በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች መግለጫ፣ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (በተለይ በአንቀጽ 23 እና 24)፣ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ቃልኪዳን በተለይ በአንቀጽ 10 እና የህጻናት ደህንነት በሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ተቋማትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ደንቦችና አግባብ ባላቸዉ ሰነዶች እውቅና አግኝቷል፡፡

58. በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መረጃ መሠረት ከአረጋዊያን አኳያ ዕድሜያቸው 60 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ በዓለማችን የሚገኙ አረጋውያን እ.ኤ.አ በ1950 ቁጥራቸው 200 ሚሊዮን፣ በ2000 ብዛታቸው 600 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በ2050 ደግሞ 2.1 ቢሊዮን እንደሚደርስ የትንበያ መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም ከዓለም ህዝብ እንደቅደም ተከተሉ 8 በመቶ፣ 10 በመቶ እና 22 በመቶ መሆኑን ያመላክታል፡፡

59. በ1994 ዓ.ም የወጣው የማድሪድ የአረጋዊያን የድርጊት መርሃግብር የፖለቲካ ድንጋጌ እና የማድሪድ ዓለም አቀፍ አረጋውያን ድርጊት መርሃ ግብር 3 አቅጣጫዎችና 18 ርዕሰ ጉዳዮች አሉት፡፡ ሰነዱ አረጋውያን በልማት የተሻለ ደህንነትና ጤንነት ወደ ሚረጋገጥበት የአረጋዊነት ዘመን እና ኢጋዥና ምቹ ሁኔታዎችን ማረጋገጥ በሚሉ አጀንዳዎች ላይ ትኩረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የመርሃ ግብሩ ተቀባይ አባል ሀገራት ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም በተመድ የጸደቁት 17ቱ የዘላቂ ልማት ግቦች በዋናነት አሳታፊና አካታች ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚደረገውን እንቅስቃሴ ከመሰረቱ ትኩረት የሰጡ እና አረጋውያንን በቀጥታ የሚመለከቱ ናቸው፡፡

60. በሌላ በኩል ከአካል ጉዳተኞች አኳያ አካል ጉዳት ማለት የአካል ክፍልን ማጣት ወይም የተግባር መገደብን የሚያመላክት ፅንሰ-ሀሳብ ሲሆን አካል ጉዳተኝነት ማለት ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ጋር እኩል ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚያደርግ የአካል ጉዳት፣ የአመለካከት ችግርና አካባቢያዊ መሰናክሎች ድምር ውጤት ነው። በዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን አንቀፅ 1 እንደተመላከተው አካል ጉዳተኝነት የረጅም ጊዜ አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስነአእምሮአዊ ወይም የስሜት ህዋሳት እክሎች ያሉባቸውን ወገኖች ያጠቃልላል። በዓለም ላይ የተለያየ ዓይነት አካል ጉዳተኝነት የሚያጋጥም ሲሆን ዓይነ-ስውርነት፣ መስማት መሳን፣ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት፣ ማየትና መስማት መሳን እንዲሁም ተደራራቢ የአካል ጉዳት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

61. የዓለም ጤና ድርጅት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2023 ያወጣው መረጃ እንደሚያመላክተው 1.3 ቢሊዮን ያህል ሰዎች የተለያየ ዓይነት የአካል ጉዳት ያጋጥማቸዋል። ይህ አሃዝ 16 በመቶ የሚሆነውን የዓለም ሕዝብ ቁጥር የሚወክል ሲሆን ይህም የአካል ጉዳት ከስድስት ሰዎች በአንዱ ላይ አለ ማለት ነው። እነዚህ ዜጎች ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ተያያዥ የጤና እክሎች የሚያጋጥማቸው መሆኑንም መረጃው ያሳያል። በሌላ በኩል የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባሕል ተቋም (ዩኔስኮ) መረጃ እንደሚያሳየው በታዳጊ

አገራት 90 በመቶ ያህል አካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርታቸውን አይከታተሉም። እ.ኤ.አ በ1998 ይፋ የሆነው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥናት የአካል ጉዳተኛ ጎልማሶች ዓለም አቀፋዊ የማንበብ ደረጃ 3 በመቶ ሲሆን የአካል ጉዳተኛ ሴቶች ደግሞ 1 በመቶ ብቻ መሆኑን አመላክቷል።

62. ከወጣቶች አኳያም በኢትዮጵያ የወጣቶች ፖሊሲ (1996) ላይ እንደተቀመጠው በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪክ ማሕበራት ከቆሙለት ዓላማና ከሚያከናውኑት ተግባር አኳያ ወጣትነት ለሚለው ፅንሰ ሃሳብ የተለያየ የዕድሜ ክልል ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከ15-24 ዓመት፣ የዓለም ጤና ድርጅት ከ10-24 ዓመት፣ የኢትዮጵያ የማሕበራዊ ደህንነትና ልማት ፖሊሲ ከ15-24 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝን ማንኛውንም ሰው ወጣት በማለት ይተረጉማሉ፡፡ የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎችን ስንመለከትም ወጣት የሚባለው የሕብረተሰብ ክፍል የተለያየ የዕድሜ ክልል ይዞ እናገኘዋለን፡፡ ለአብነት ያህልም በዑጋንዳ ከ12-30፣ በሞሪሸስ ከ14-29፣ በደቡብ አፍሪካ ከ14-28፣ በህንድ ከ15-35፣ በናይጄሪያ ከ18-35፣ በጅቡቲ ከ16-30 ያሉትን የዕድሜ ገደቦች ወጣትነትን ለመተርጐም ተጠቅመውበታል።

63. እንደ እ.ኤ.አ በ1800 የዓለም ሕዝብ ቁጥር 1 ቢሊዮን ገደማ የነበረ ሲሆን በ1950 የሕዝብ ብዛት በእጥፍ አድጎ 2.5 ቢሊዮን ደርሷል። ከ1950ዎቹ በኋላ የተሻለ የህክምና እና የንጽህና አጠባበቅ በመኖሩ የሚቾች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነሱ የዓለም የህዝብ ብዛት በ2000 ወደ 6 ቢሊዮን፣ በ2022 ወደ 8 ቢሊዮን፣ በ2024 ደግሞ ከ8.1 ቢሊዮን በላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ እንደ ተባበሩት መንግስታት ትንበያ በ 21ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የህዝብ ብዛት ወደ 10.4 ቢሊዮን ገደማ እንደሚደርስ ይገመታል። ይህ የህዝብ እድገት በሁሉም ሀገራት ተመሳሳይ ባለመሆኑ የሀገራት የስነ-ህዝብ ገጽታ የተለያየ እንዲሆን በማድረግ ለውስብስብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እየዳረጋቸው ይገኛል፡፡ በመሆኑም ሀገራት እንደ የሀገራቸው ነባራዊ ሁኔታ የተለያዩ የስነ-ህዝብ ፖሊሲዎችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ያደጉ አገሮች በአብዛኛው ዝቅተኛ የወሊድ ምጣኔ ያላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዙውን ጊዜ ለሕዝብ እርጅና፣ ለሠራተኛ ኃይል መቀነስ እና የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ስጋት ፈጥሮባቸዋል፡፡ ስለሆነም ብዙዎች ያደጉ ሀገራት ከችግሩ ለመውጣት የወሊድ መጠንን የሚያበረታታ ፖሊሲዎችን በመተግበር ላይ ይገኛሉ። በአንጻሩ ደግሞ በርካታ ታዳጊ ሀገሮች የውልደት ምጣኔያቸው ከፍተኛ በመሆኑ የሕዝብ ቁጥራቸው በፍጥነት እያደገ ይገኛል፡፡ ይህ ፈጣን እድገት ድህነትን፣ የምግብ ዋስትና እጦትን እና ስራ አጥነትን የሚያባብስ እንዲሁም በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ የወሊድ መጠንን የማያበረታታ ፖሊሲን በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡

64. የዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) እና የህዝብ ቁጥር እድገት የማይነጣጠሉ ናቸው። ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር ከድህነት፣ ረሃብ፣ ጤና፣ ትምህርት እና የአካባቢ ዘላቂነት ጋር በተያዙ በርካታ የዘላቂ ልማት ግቦች ላይ የሚደረገውን ግስጋሴ ሊያደናቅፍ ይችላል። በአንጻሩ በጾታ እኩልነት፣ በትምህርት እና በጤና አጠባበቅ ላይ ያተኮሩ እንዲሁም ዘላቂ ፍጆታ እና ምርትን የመሳሰሉ በርካታ ዘላቂ የልማት ግቦችን ማሳካት ደግሞ የወሊድ መጠን በመቀነስ የህዝብ ቁጥር እድገት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ስለሆነም እነዚህን ተለዋዋጭ የስነ ህዝብ ሁኔታዎችን በመረዳትና ያሉ ልዩነቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ችግሮችን ለመፍታት ዓለም አቀፍ ትብብር ያስፈልጋል።

## አህጉራዊ ሁኔታ

65. በአህጉር ደረጃ የአፍሪካ የሰብዓዊ እና የህዝቦች መብት ቻርተር እንዲሁም የአፍሪካ ሴቶች መብት የማፑቶ ፕሮቶኮል ለሴቶች ልዩ ትኩረትን ስጥቶ መስራትን በሚገባ ያሳያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የስርዓተ-ጾታ እኩልነት በአፍሪካ በሚል የተቀመጠው የሶልመን ድንጋጌ (እኤአ 2004) አገሮች የተቀመጡትን የሴቶች ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብሩ ይጠይቃል፡፡ በሌላ በኩል በአጀንዳ 2063 ላይ በአፍሪካ የሚካሄደው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ልማት ህዝብ ተኮር እንዲሆን መስራት፣ በተለይም ለሴቶች፣ ለህጻናትና ለወታቶች ልዩ ትኩረት መስጠት፣ በሁሉም የህይዎት ዘርፎች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በማረጋገጥ የሴቶችን ሚና ማጉላት፣ በሴቶች በህጻናትና በወጣቶች ላይ የሚደርሰውን ሁሉንም ዓይነት መድልዎ እና ጥቃት ማስወገድ ተገቢ መሆኑን አስቀምጧል፡፡

66. ከአረጋውያን አኳያ አረጋዊያንን ተጠቃሚ ለማድረግ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኔትወርክ የሚመሩበት የአሰራር መመሪያ መሰረት የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ያጸደቀው አጀንዳ 2063 የአፍሪካን መነሳሳትና የአህጉሪቱ መጻኢ እድል ላይ ያለመ ሰባት አጀንዳዎችን የያዘ ሲሆን እነኚህ አጀንዳዎች አረጋውያንን ተጠቃሚ እንደሚያደርጉ ይታመናል፡፡ ከአጀንዳዎቹ መካከል ዘላቂ ልማት፣ አካታች ማኅበረሰብ በመፍጠር የበለጸገች አፍሪካን እውን ማድረግ፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፣ ሠላማዊና ደህንነቷ የተጠበቀ አፍሪካን ማየት፣ በሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በህዝቦቿ ጥረት የበለጸገች አፍሪካን እውን ማድረግ የሚሉ ናቸው።

67. በአፍሪካ የአረጋዊያን ፕሮቶኮል ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች እያደገ የመጣውን የአረጋውያን ቁጥርና ፍላጎት እንዲሁም ይህንኑ ለማሳካት መንግስታት ፈጣን ተቋማዊ እርምጃ እንዲወስዱ በተለይም አረጋውያን ቋሚ ገቢ፣ ፍትሃዊ የሃብት ስርጭት፣ የሥራ እድል መስፋፋትና ተጠቃሚነት፣ ተገቢነት ያላቸው የጤና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ስለማድረግ፣ ከቤተሰብ ከመንግስት ከሲቪል ማህበረሰቦች እና ከግል ድርጅቶች መሠረታዊ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ማለትም ምግብ፣ ውሃ፣ አልባሳትና መጠለያ ተደራሽነት፣ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎችና አሳዳጊ የሌላቸው ህፃናትን ስለመንከባከብ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ጉልህ ሚና እና አስተዋጽኦ ስለማክበርና እውቅና ስለመስጠት፣ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ወቅት ያላቸውን ልዩ ፍላጎት ስለማስታወስ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች በመያዝ የወጣ ሲሆን ይህንን መሰረት አድርገዉ ሀገራት አካታችና ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ይደነግጋል፡፡

68. ከአካል ጉዳተኞች አኳያም በአፍሪካ ከ80 ሚሊዮን በላይ ሰዎች የተለያየ ዓይነት የአካል ጉዳት እንዳለባቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (2018/19 እኤአ) መረጃ ያሳያል። በአህጉሪቱ በተለይም በየጊዜው የሚከሰቱ አለመረጋጋቶች፣ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በርካቶችን ለአካልና ለአዕምሮ ጤና ጉዳት የሚዳርጉ ምክንያቶች ሆነው ይጠቀሳሉ። የአብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት ፈተናዎች የሆኑት የምጣኔ ሀብት እና የመሠረተ ልማት ችግሮች አካል ጉዳተኞችን የበለጠ ጫና ውስጥ የሚከቱ ከመሆናቸው ባሻገር ተገቢውን ድጋፍ እንዳያገኙ ተግዳሮት ሆነው ቆይተዋል።

69. ከስነ ህዝብ አኳያ የአፍሪካ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ በፈጣን እድገት ውስጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በልማት እድገት ላይ ጫና በማሳደር ላይ ይገኛል፡፡ የአፍሪካ አህጉር ከዓለም ህዝብ ቁጥር 17 በመቶ በላይ የሚሆነውን የሚይዝ ሲሆን ይህ ቁጥርም በከፍተኛ የእድገት መጠን እየጨመረ እንደሚሄድና በልማት እድገት ላይ ጫና እንደሚያሳድር ይጠበቃል። በዓለማችን በአብዛኛው ህዝባቸው በፍጥነት እያደገና የወጣት ቁጥራቸው እየጨመረ ያለው ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም የህዝብ ብዛት በ2050 ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ከእጥፍ በላይ እንደሚጨምር ይገመታል፡፡ እንደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ የህዝብ ብዛት በ2050 ወደ 2.5 ቢሊዮን እና በ2100 ደግሞ 40% ድርሻ በመሸፈን ወደ 4.3 ቢሊየን በላይ ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር የምግብ ዋስትና እጦት፣ ስራ አጥነት በተለይም የወጣቶች ስራ አጥነት፣ በቂ ያልሆነ መኖሪያ ቤት እና ለአካባቢ መራቆት አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

70. የአፍሪካ አጀንዳ 2063 የህዝብ ተለዋዋጭነት ለአህጉራዊ ብልጽግና ወሳኝ እንደሆነ አስቀምጧል። ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር የአጀንዳ 2063 ግቦችን ለማሳካት ሁለቱንም እድሎች (ትልቅ የሰው ኃይል) እና ተግዳሮቶችን (በሀብት፣ መሠረተ ልማት እና አገልግሎቶች ላይ ያለውን ጫና) ሊያመጣ እንደሚችል ያስቀምጣል። በተጨማሪም በጣም ወጣት ከሆኑት አህጉራት አንዷ መሆኗን በማስቀመጥ የሚከሰቱ ማኅበራዊ ብጥብጦችን ለመከላከል የወጣቶችን የሥራ አጥነት ችግር መፍታት እንደሚገባ ያስገነዝባል። በአጠቃላይ ከተጠቀሱት ችግሮች ለመውጣት የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ማስፋፋት፣ የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን ለሁሉም ማዳረስ፣ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች መፍጠር እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ ያተኮሩ አጠቃላይ ስልቶችን መከተል ያስፈልጋል።

### *ሀገራዊ ሁኔታ*

71. የህግ ማዕቀፎች /የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት እንዲሁም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996/ ሴቶች በጾታቸው ምክንያት በስራ ቅጥርና በክፍያ መድሎዎ እንዳይደረግባቸው ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ለሴቶች ጤና ጎጅ ናቸው ተብለው በተለዩ ስራዎች ሴቶችን ማሰማራት የተከለከለ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር 515/1997 ለተመሳሳይ ስራ ተመሳሳይ ክፍያ መኖር እንዳለበት ደንግጓል፡፡ እንዲሁም የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 455/1996 ደግሞ ሴቶች በመሬት የመጠቀም እኩል መብት እንዳላቸው ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩልመ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ኃላፊነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና የመንግስት ኤጀንሲዎች ከስልጣንና ተግባራቸው አኳያ የሴቶችን ጉዳይ አካተው እንዲሰሩም ይደነግጋል፡፡ ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲም የሴቶችን አቅም በማጎልበት ኢኮኖሚያ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ ድህነትንና የስርዓተ-ጾታ እኩልነት አለመስፈንን ለማስወገድ ታስቦ የተቀረጸ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሴቶች የልማትና የለውጥ ፓኬጅ የተቀረጸበት ዓላማ በሁሉም ዘርፍ የሴቶችን እኩል ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥና በሀገሪቱ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግባራት የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ነው፡፡ በመሆኑም የተቀመጡትን የህግ ማዕቀፎች ሳይሸራረፉ መተግበር ተገቢ ይሆናል፡፡

72. በሀገራችን ሴቶችን በሚመለከት የሚታዩ የተዛቡ አመለካከቶችን ለማስተካከል መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የተወሰኑትን ሴቶችን የሚመለከቱ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች በመቀበል በሀገሪቱ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35 ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 የሴቶች መብቶች መካተታቸው፣ ሕገ መንግስቱን ተከትሎም የሴቶችን መብት ለማስከበር የሚረዱ ራሱን ችሎ የሴቶች ጉዳይ ፖሊስን ጨምሮ ሊሎች ፖሊሲዎች፣ የቤተሰብ ህግ፣ የፍትሐብሔር እና የወንጀለኛ መቅጫ ህጉች መሻሻላቸው፣ ሌሎች ሕጐች፣ መመሪያዎችና ደንቦች መውጣታቸው፣ የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተል ተቋማዊ አደረጃጀት በሚኒስቴር ደረጃ ተዋቅሮ እስከ ወረዳ ድረስ መደራጀቱ፣ የሴቶች ልማት ፖኬጅ ተቀርጾ ሥራ ላይ መዋሉ፣ በተጨማሪም ለሴቶች ልዩ ድጋፍ እርምጃ እየተሰጠ መሆኑ፣ ወዘተ... የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

73. የሴቶችን የኢኮኖሚ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ ባለፉት ዓመታት የልማት ፕሮግራሞች በመቀረጻቸውና በመተግበራቸው፣ የግንዛቤና ንቅናቄ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስራዎች በመስራታቸውና የተለያዩ ግብዓቶች በመሟላታቸው በከተማና በገጠር ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም ሴቶችን በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ የሥራ ዘርፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነት መብት ከማረጋገጥ አኳያ የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ፣ የግብርና ዕድገትና የምግብ ዋስትናን በሚያረጋግጡ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ፣ በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ የሥራ መስኮች በመሰማራት ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና በአረንጓዴ ልማት ፕሮግራሞች ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ የሥራ ጫና በመቀነስ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች እንዲቀርቡላቸው፣ በተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ የቁጠባና ብድር አገልግሎት እንዲቀርብላቸው፣ የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉና የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው በማድረግ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግና በከተማ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ከሚገነቡ ቤቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡

74. ከላይ በኢኮኖሚው መስክ የተመዘገቡ ስኬቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማነቆ ሆነው ከሚታዩ ተግዳሮቶች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሱት ለሴቶች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በሚፈለገው መልኩ ተደራሽ አለመሆንና በምርታማነታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣ በግብርናና ከግብርና ውጪ ባሉ መስኮች የሚቀርበው የብድርና የግብዓት አቅርቦት በቂና ተደራሽ አለመሆን፣ የምርት ማቀነባበሪያና ጊዜና ጉልበት የሚቆጥቡ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ተደራሽ፣ ምቹና ዋጋቸው ተመጣጣኝ አለመሆን፤ በኢ-መደበኛ የንግድ መስኮች ላይ የተሰማሩ ሴቶችን ወደ መደበኛው የንግድ ስርዓት እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ድጋፍ አለመኖር፤ ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ በመርህ ደረጃ ቢቀመጥም በግል ተቋማትና በኢንዱስትሪዎች ተፈጻሚነቱ የሚፈለገውን ያክል አለመድረሱ፤ የሴቶች ኢንተርፕራይዞችን ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ብሎም ወደ ከፍተኛ ሽግግር እንዲያደርጉ የሚሰጠው ድጋፍ የተጠናከረ አለመሆን፣ የማምረቻና መሸጫ ቦታና በቂ የመሰረተ ልማት አውታሮች አለመስፋፋት፣ የገበያ ትስስር፣ ድጋፍና ክትትል ቀጣይነት ባለው መልኩ አለመቅረብ፣ የሴቶች የቁጠባ ባህል አለመዳበር፤ በኢኮኖሚ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ቀረጻ፣ ትግበራና ክትትልና ግምገማ ሂደት ሴቶችን ተሳታፊ በማድረግ ረገድ ውስንነት መኖር ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በማኑፋክቸሪንግና ኢንቨስትመንት ዘርፎች ያላቸው ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ፤ በኢንዱስትሪ የሥራ ቦታዎች የአካባቢ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ እንቅስቃሴዎች በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመሆን፣ በሥራ ቦታዎች ምቹ የስራ ሁኔታ አለመፈጠር እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማህበራት የሴት አባላት ቁጥር አነስተኛ መሆን ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው፡፡

75. በአጠቃላይ ሴቶችን በኢኮኖሚው ዘርፍ ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ በተሰሩ የተለያዩ ስራዎች ከድህነት ወለል በታች ያሉ ሴቶች ቁጥር በአንጻራዊነት መቀነሱን ያመላክታል፡፡ በተከናወኑ በርካታ ስራዎች የተመዘገቡ ውጤቶች ቢኖሩም ወደ ላቀ ደረጃ ከማሸጋገር አኳያ የአመለካከት ችግር፣ በየደረጃው ያለው አመራር ቁርጠኝነት ማነስ፣ በሁሉም አካላት የአቅም ውሱንነት መኖር፣ የተጠያቂነት አሰራር አለመጠናከር እንዲሁም ለሴቶች ተስማሚ አገልግሎቶች አለመስፋፋት ቁልፍ ችግሮች መሆናቸው ተለይቷል፡፡

76. የሴቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማጎልበት አንፃርም በዋነኛነት የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነትን ለማሳደግ፣ የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግና በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ማህበራዊ ጠንቆችን ለማስወገድ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተሰሩ ስራዎች አዎንታዊ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

77. ይሁን እንጂ በሴቶች ትምህርት ዙሪያ የህብረተሰቡ አመለካከት ሙሉ በሙሉ አለመቀየሩ፣ በቤት ውስጥ የስራ ጫናና በሚፈጸሙባቸው ጥቃቶች ምክንያት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ፣ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ ባለመሆኑ የሴት ተማሪዎች ተጠቃሚነት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ፣ በየትምህርት እርከኖቹ የሴቶች ትምህርት ማቋረጥና መድገም፣ የትምህርት ውጤታማነታቸው በሚፈለገዉ ደረጃ ላይ አለመድረስ፣ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ ካልተማሩ ሴቶች ቁጥር አንጻር ሲመዘን ዝቅተኛ መሆን፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት መስኮች የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፣ በቴክኒክና ሙያ የሚሰጡ ስልጠናዎች የሴቶችን ፍላጎት ያማከሉ አለመሆን እንዲሁም በየደረጃው ባሉ የትምህርት እርከኖች የሴት አመራሮች ቁጥር አነስተኛ መሆን በትምህርት ተሳትፎ ላይ የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

78. በጤናው ዘርፍም ከእናቶች የሞት መጠን አንጻር ሲታይ የጤና አገልግሎት ለሴቶች በተሟላ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸው፣ ተደራሽ በሆነባቸው አካባቢዎችም የሠለጠነ የሰው ኃይል፣ የመድሃኒትና ቁሳቁሶች እንዲሁም ሌሎች ግብዓቶች ችግሮች መኖር፤ በግንዛቤና አመለካከት ችግሮች፣ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት መጓደልና ሌሎች ምክንያቶች ሁሉም እናቶች በጤና ተቋማት አለመውለድና የድህረ ወሊድ ክትትል ዝቅተኛ መሆን፣ ለሴቶች/በተለይ ለታዳጊ ወጣት ሴቶች የሚሰጡ የተዋልዶ ጤናና ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች ተደራሽ ካለመሆናቸውም በተጨማሪ የመቀዛቀዝ ሁኔታ መኖር ተስተውለዋል፡፡

79. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጾታዊ ጥቃቶችን በመከላከልና በማስወገድ ረገድ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሟላ የባህሪ/የአመለካከት ለውጥ አለመምጣቱ፣ የህግ አፈፃፀም ክፍተት መኖርና የተፋጠነ ፍትህ አለማግኘት፣ ጥቃቱን/ድርጊቶቹን በሚፈፅሙ አካላት ላይ የሚተላለፉት የቅጣት ውሣኔዎች አስተማሪ አለመሆን፣ በጉዳዩ ዙሪያ በቂ መረጃዎች አለመኖራቸው፣ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ማዕከላት በቂ አለመሆናቸውና ያሉትም የተሟላ አገልግሎት አለመስጠት፤ ነጻ የህግ አገልግሎት ተደራሽ አለመሆን እንዲሁም ሴቶች ለተለያዩ ማህበራዊ ጠንቆችና ጎጂ መጤ ልማዶች ተጋላጭ መሆናቸው የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ልዩ ትኩረት ለሚሹ ሴቶች (አካል ጉዳተኞች፣ ጎዳና ተዳዳሪ፣ ሴተኛ አዳሪ፣ የአዕምሮ ህመም ያለባቸው፣ አረጋውያን፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ወዘተ) ልዩ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አገልግሎት በተቀናጀ ሁኔታ አለመጠናከር በክፍተት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

80. ከህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር አኳያ ችግሩ በተለይ በሴቶች ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ተከታታይነት ያላቸው የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎችን በማከናወን፣ ሴቶች በሀገር ውስጥ ባሉ የስራ አማራጮች እንዲሰማሩና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ፣ በህገ ወጥ አዘዋዋሪዎችና ደላላዎች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃዎችን በመውሰድና በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሌላ አገር የተሰደዱ ወገኖቻችን ወደ አገራቸው ተመልሰው በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ አዎንታዊ ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

81. ይሁን እንጅ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በመከላከል በአገር ውስጥ ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል በሴቶችና ማህበረሰቡ ዘንድ ያለው የተዛባ አመለካከት አለመቀረፍ፣ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ተሰማርተው በተደራጀ አግባብ ተጠቃሚ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎች የሚፈለገውን ያህል አለመፈጠራቸው፣ ከስደት የተመለሱትን የማቋቋምና የማጠናከር ስራዎች አጥጋቢ አለመሆናቸው እንዲሁም ህገወጥ አዘዋዋሪዎችና ደላላዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ዓይነታቸውን እየቀያየሩ መምጣትና ይህን ለመከላከል የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋት በዋናነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸዉ፡፡

82. የኢትዮጵያ ሴቶች የልማትና የለውጥ ስትረቴጅ (2009) እንደሚያመላክተው ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በተወሰዱ እርምጃዎችና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በፌደራል ደረጃ የሴቶች የውሳኔ ሰጭነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 38.8 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ 20.6 በመቶ፣ በአስፈጻሚ አካላት በከፍተኛ አመራር 13.3 በመቶ፣ በመካከለኛ አመራርነት ቦታ ላይ 22 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡

83. ይሁን እንጅ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ሚና በማሳደግ ከቤተሰብ ጀምሮ በየደረጃው በሚገኙ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማት ወደ አመራርነት እንዲመጡ በማድረግ ረገድ ሴቶች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምትና በራስ የመተማመን ብቃታቸው በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ የወንዶች የበላይነት አስተሳሰብ፣ ህብረተሰቡ በሴቶች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት፣ በሴቶች ውሳኔ ሰጭነት ዙሪያ በየደረጃው ያለው አመራር ቁርጠኝነት የሚፈለገውን ያህል አለመሆን እንዲሁም በአመራር ላይ ያሉ ሴቶች ተተኪዎችን በማፍራት ረገድ የሚጠበቅባቸውን ሚና አለመወጣት የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

84. ከህጻናት አኳያ ህፃናት የአንድ ህብረተሰብ መሠረት እንደ መሆናቸው ሁሉ እያንዳንዱ አገርና መንግስት እንደ ባህሉ ሁኔታ አትኩሮት በመስጠት ሊንከባከባቸው፣ መብታቸውንም ሊያስጠብቅላቸው ይገባል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የህዝብ ቁጥር የሚይዙት ህፃናት ናቸው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ሀገራችን በማህበራዊ ዘርፍ ትኩረት ሰጥታ ከምትሠራባቸው ዘርፎች አንዱ የህፃናት ጉዳይ ነው፡፡ ህፃናት የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጐች ከመሆናቸው አኳያ ሲታይ በእርግጥም የተለየ ትኩረት በመስጠት ሁለንተናዊ የሆነ ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ የተስተካከለ ስብዕና ይዘው እንዲያድጉና ብቁ ሀገር ተረካቢ ዜጐች እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል።

85. ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግስታት ድርጀት በሥራ ላይ የዋለውን የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር ተቀብላ በማፅደቅ ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህም መሠረት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በሀገሪቱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን ስልት በመቀየስ በህገ መንግስቱ የህፃናት መብቶችን በማካተት፣ የህፃናት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የቤተሰብ ህግ፣ የወንጀለኛና የፍታብሔር ህጎችን በማሻሻል፣ ከፌዴራል ጀምሮ በተዋረድ እስከ ወረዳ ድረስ መንግስታዊ መዋቅር በማቋቋም፣ ብሔራዊ የህፃናት ፖሊሲ፣ ብሔራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ፣ የትምህርትና የጤና ፖሊሲ የህጻናትን ጥቅም የሚያስከብሩ በማድረግ መንግስት የወሰዳቸው አበረታች እርምጃዎች በመሆናቸው ህጻናት በከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ዕድልና የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በማህበረሰቡ የሚደረግላቸው ድጋፍ እና እንክብካቤ፤ የህጻናት መሰረታዊ መብቶቻቸውና ደህንነታቸው መከበር እያደገ መጥቷል፡፡

86. ይሁን እንጂ ህብረተሰቡ የህጻናትን ጉዳይ የነገ ሃገር ተረካቢ አድርጎ ባለመመልከት፣ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ ባለማድረግ፣ ህጻናት በዕድሜያቸዉ በሚጠበቀው ልክ ትምህርት አለማግኘት፣ የተሟላ የጤና እንክብካቤ አለማግኘት፣ በልዩ ልዩ ጉዳዮች እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ አለመፍጠር፣ ምቹ ቤተሰብና አካባቢን መፍጠር አለመቻል፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይፈጸምባቸዉ አለማድረግ፣ ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትኩረት አለመስጠት፣ በተገቢው የአመጋገብ ስርአት አለመመገብ፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ከአከባቢያቸው ለቀው መሰደድ፣ በበይነ መረብ (ማህበራዊ ሚዲያዎች) ጥቃት መፈፀም፣ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛና የጎዳና ተዳዳሪነት በህፃናት የሚፈፀሙ ጥቃቶች እና የሚስተዋሉ አጠቃላይ ችግሮች በመሆናቸው በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡

87. የአረጋውያን ብሔራዊ የድርጊት መርሐ ግብር (2008-2017) እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ጥበቃ ምህዳርን ማስፋት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት የተለያዩ አንቀጾች ላይ ሰፍረው የሚገኙትን ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶችን ደረጃ በደረጃ የመተግበር ሂደት አንድ አካል ነው፡፡ በሕገ-መንግሥቱ የማኅበራዊ ጥበቃ ስርዓትን ለመዘርጋት መሠረት የሆኑ አንቀጾችን በተለይም በአንቀጽ 41 ሥር በዝርዝር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ በአንቀፅ 90 "የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል" በማለት መደንገጉ ለማኅበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ መቀረጽ ሕገ-መንግስታዊ መሠረት ነው፡፡

88. በኢትዮጵያ ያለው የአረጋውያን ቁጥር በ1999 ዓ.ም በህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት 3,568,810 እና በ2022 ማዕከላዊ ሲታስቲክስ ትንበያ መሰረት ደግሞ 5,329,180 የነበረ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የአገሪቱ ህዝብ 4.8 በመቶ እና 5.06 በመቶ እንደቅደም ተከተላቸው የሚወክል ነበር፡፡ የአረጋውያን ቁጥርና ተጋላጩነት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመሄድ ላይ በመሆኑ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲው የአረጋውያንን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆኑ፣ የአረጋውያን ጉዳይ ዓለም አቀፍ ትኩረት እየሳበ መምጣቱ በዓለም አቀፍና በአፍሪካ ደረጃ የአረጋውያን የድርጊት መርሃ-ግብር ወጥቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩ፣ እንዲሁም የአረጋውያን ችግሮች ስር እየሰደዱ በመምጣታቸውና ጧሪና ደጋፊ ያጡ አረጋውያን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ማደጉ፣ የአረጋውያንን ህይወት የሚፈታተኑ እና እንደ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የግሎባላይዜሽን እንዲሁም አዳዲስ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችን ለመቋቋም የተለየ ጥረት መጠየቁ፣ በዘርፉ ያሉ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች የተቀናጁና የተጣጣሙ እንዲሆን ለማድረግ የአደጋ ስጋትና ተጋላጭነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ምንጊዜም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡

89. በሌላ በኩል በኢትዮጳያ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ከተካሄደ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ምን ያህል አካል ጉዳተኞች እንዳሉ ትክክለኛ መረጃ ማግኘትን አዳጋች አድርጎታል። ይሁን እንጅ እንደ ዓለም ጤና ድርጅትና የዓለም ባንክ (2023) መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ 15 ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ የአካል ጉዳተኛ እንደሆነ

መረጃው የሚያመላክት ሲሆን ይህም ከጠቅላላው ህዝብ 17.6 በመቶ እንደሆነ ያሳያል፡፡ እነዚህ ዜጎች በጎጂ ልማዶችና በተዛባ አመለካከት እንዲሁም በሕግጋት እና በአፈጻጸማቸው ክፍተት ሳቢያ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እየተጋፈጡ እንደሆነም ይጠቁማሉ። በኢትዮጵያ ለአካል ጉዳተኞች የሚመጥን የመሠረተ ልማት አውታር ግንባታ አለመኖርና የአገልግሎት አሰጣጥ ጉድለት በርካቶችን ለከፍተኛ እንግልትና ለተጨማሪ የጤና እክል እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል።

90. ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ስምምነትን ተቀብላ የሕግ አካል ያደረገች ሲሆን የአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት እና የሕንፃ አዋጆችም ጸድቀው ወደ ስራ ተገብቷል። ከ60 በመቶ በላይ አካል ጉዳተኞችን ለቀጠረ ድርጅት ከታክስ እና ከቀረጥ ነፃ የሚያደርግ መመሪያ ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል። ይሁን እንጂ አካል ጉዳተኞችን እኩል ተሳታፊና ፍትሃዊ ተጠቃሚ ያደርጋሉ ተብለው የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሬት ላይ ወርደው በተጨባጭ ምን ለውጥ አመጡ አፈፃፀማቸውስ የሚለው አሁንም ድረስ የበርካቶች ጥያቄ ነው።

91. በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 5 እንደተደነገገው "መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለ ወላጅ ወይም ያለ አሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የአገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል" የሚል ድንጋጌም ተቀምጧል። በኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ቀደም ካሉት ዓመታት ከነበረው የተሻለ ግንዛቤ ቢፈጠርም አሁንም ቢሆን እንደ ሲዳ 2014 እኤአ የሃንዲካፕ ዓለም አቀፍ መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ ከ2.4 እስከ 4.8 ሚሊዮን (3 በመቶ) የሚገመት የአካል ጉዳተኞች ሕፃናት ብቻ የትምህርት ዕድል እንደሚያገኙ ያሳያል። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአካል ጉዳተኛ ህጻናት የትምህርት ዕድል እንደማያገኙና በዚህ ምክንያትም ለኢኮኖሚና ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡

92. ከወጣቶች አኳያ በኢትዮጵያ የወጣቶች ፖሊሲ (1996) ሰነድ ላይ እንደተመላከተው የተለያዩ ማኅበረሰቦችና ባህሎች ስለወጣትነት ያላቸው ግንዛቤ እና አመለካከት እንደየ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታቸው የሚለያይ በመሆኑ ለወጣትነት አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም አልተገኘለትም፡፡ ወጣትነትን በሕፃንነት የመጨረሻና በጐልማሳነት የመጀመሪያ ዕድሜዎች መካከል የሚገኙ አድርገው የሚተረጉሙ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በሕፃንነት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በኅብረተሰቡ ውስጥ የጐልማሳነት መገለጫ የሚባሉ ተግባራትን ማከናወን ሲጀምሩ ወጣት ብለው ይጠሯቸዋል፡፡ በሌላ በኩልም ከሥነ-ሕይወታዊ ዕድገት ጋር በማያያዝ በአካል መዳበርን፣ ለአካለ መጠን መድረስንና እነዚህን አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ለውጦችን የወጣትነት ዘመን ምልክት የሚያደርጉም አሉ፡፡ ከነዚህ ሁሉ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለፖሊሲ ዓላማ አመቺ ሆኖ የተገኘው በዕድሜ ላይ የተመሰረተ ትርጓሜ ነው፡፡

93. በፖሊሲው ላይ እንደተቀመጠው የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ሀገራችን ከተያያዘችው የልማት ግንባታ አንጻር ወጣቶችን አንቀሳቅሶ እምቅ አቅማቸውንና ችሎታቸውን ለመጠቀም ይቻል ዘንድ በዚህ የወጣቶች ፖሊሲ ወጣት ማለት ከ15-29 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡ እንደ ሀገራዊ ፖሊሲው ለአንድ አገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ልማት የሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ንቁ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ወጣቶች ደግሞ አዳዲስ ሀሳቦችን ለመቀበል እንዲሁም የፈጠራና የማምረት እምቅ አቅም ያላቸው በመሆኑ በሁሉም የልማት ዘርፎች ውስጥ የላቀ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ እምቅ ሀይላቸውንና ችሎታቸውን በተግባር ለማዋል ምቹ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ፍላጐቶቻቸውን እውን ለማድረግ የሚያስችሏቸው ሁኔታዎች ካልተፈጠሩላቸው ግን ፈጥነው ተስፋ በመቁረጥ እና ሁሉንም ነገር በመተው የኅብረተሰቡን እንቅስቃሴ በገለልተኛነት ከርቀት ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡ አልፈውም ለማኅበራዊ ጠንቆች ይጋለጣሉ፡፡ ስለሆነም በርካታ አገሮች ለወጣት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት በመስጠት በባለቤትነት የሚከታተሉ ተቋሞችን በማቋቋም፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በማውጣት የተደራጀና የተቀናጀ እንቅስቅሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

94. በአገራችን የወጣት ጉዳዮችና አደረጃጀት ተገቢው ትኩረት ካለማግኘቱ የተነሳ በወጣቶች፣ በቤተሰብ፣ በህበረተሰብ፣ በሌሎች ተባባሪ አካላት እና በመንግስት መካከል የጋራ ትብብርና ቅንጅት ተፈጥሮ በተፈለገው መጠን ሲሰራበት አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ከተቋቋሙበት ዓላማ አኳያ በተናጠል ባወጧቸው ፖሊሲዎች ውስጥ የወጣቶችን ችግሮች፣ ፍላጐቶችና ራዕዮች በተበታተነ ሁኔታ እየተገበሩ ቢገኙም እነዚህ ጥረቶች በተሟላና በተቀናጀ ሁኔታ እየተከናወኑ አይደሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ወጣቶች በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ብቃት ባለው መልኩ ተሳትፈው፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ልማትን በማፋጠን የራሳቸውንና የኅብረተሰባቸውን ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈርጀ-ብዙ ተግባራትን ለማከናወን ሁኔታዎች አልተመቻቹላቸውም፡፡

95. በመሆኑም የኢትዮጵያ ወጣቶች የልማትና የዕድገት ስትራቴጂ (2009) ላይ እንደተቀመጠው የወጣቶችንና የማኅበረሰቡን አመለካከት በመቀየር የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ኢኮኖሚ ማህበራዊ እና ፖለቲካ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ ወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚሉት ዋና ዋና ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

96. ከስነህዝብ አኳያ በሀገራችን የሚታየው የህዝብ ቁጥር ዕድገትና የሚከሰተው ችግር ከዓለም ዓቀፍ ሁኔታ የተለየ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ወቅት ፈጣን እድገት እያስመዘገበ ሲሆን ይህም በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ካላቸው አገሮች አንዷ ያደርጋታል። በዓለም ባንክ የተካሄዱ ጥናቶችና ትንበያዎች እንደሚያመለክቱት የሀገራችን ህዝብ በአማካይ 2.66 በመቶ በማደግ እአኤ በ2020 ቁጥሩ 115 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በ2023 ከ120 ሚሊዮን በላይ እንደሚሆንና ከናይጄሪያ ቀጥሎ በአፍሪካ ሁለተኛው ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ያላት ሀገር እንደሆነች መረጃው ያሳያል። መንግስት በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ ያለው የህዝብ ቁጥር ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ካልተጣጣመ ሊያስከትል የሚችለውን ችግርና ሀገራዊ አደጋ በመረዳት በ1985 ዓ.ም ብሔራዊ የስነ-ሕዝብ ፖሊሲ አውጥቶ ተግባራዊ በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በሀገራችን አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ከ15 ዓመት በታች ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የውልደት መጠን ቢቀንስም ቀጣይ የህዝብ ቁጥር እንደሚጨምር ያሳያል። ይህ ፈጣን እድገት አሁን ባሉት መሠረተ ልማቶች፣ ሃብቶች፣ ሊታረስ የሚችል መሬት እና ውሃ፣ እንዲሁም ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪ የውልደት ምጣኔ ከመቀነሱ ጋር ተያይዞ እየጨመረ ያለው የወጣት ቁጥር ለሀገሪቱ እድል ወይም ፈተና ይዞ ይመጣል፡፡ በመሆኑም ስራ አጥነትን እና ማህበራዊ አለመረጋጋትን ለመከላከል እንዲሁም ዕድሉን ወደ መልካም አጋጣሚ ለመለወጥ በትምህርት፣ በስራ እድል ፈጠራ፣ በጤና እንክብካቤ እና በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ያስፈልጋል። በእነዚህ ዙሪያ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶችን ከዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት እና የተሻሻለ መሠረተ ልማት ጋር ቅድሚያ የሚሰጥ ዘርፈ ብዙ አካሄድን መከተል ያስፈልጋል።

## ክልላዊ ሁኔታ

97. መንግስት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊና በፖለቲካው ዘርፍ ተሳታፊና ከውጤቱም ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህ ሂደትም ሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ከምንጊዜውም በበለጠ ንቁ ተሳታፊዎችና የውጤቱም ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ የፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ለአፈጻጸሙም አጋዥ የሆኑ አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በመፍጠር እንዲሁም አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት በተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኛል።

98. በስርዓተ ፆታ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት ሴቶች በሀገራችን ብሎም በክልላችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ሰፊ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የሚያሳይ ሲሆን በሕብረተሰቡ ውስጥ ሆነው በተለያዩ የማምረት ስራዎች፣ ወልዶ በማሳደግና በመንከባከብ ትውልድን እንዲቀጥል በማስቻል እና በማሕበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግባትራን በማከናወን ለልማቱ እያደረጉት ያለው አስተዋጽኦ ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ በክልላችን ሴቶች በአማካኝ በቀን ከ14 እስከ 17 ሰዓት በስራ ላይ እንደሚያሳልፉ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

99. ከላይ በሀገራዊ የሁኔታ ትንተናው ላይ የተጠቀሱት በሀገሪቱ እና በክልሉ ሕገ መንግስት ውስጥ የሴቶች መብቶች መካተታቸው፣ ሕገ መንግስቱን ተከትሎም መብታቸውን ለማስከበር የሚረዳ ፖሊሲዎች፣ የቤተሰብ ህግ፣ የፍትሐብሔር እና የወንጀለኛ መቅጫ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ የልማት ፓኬጆች፣ ልዩ ድጋፎች፣ አደረጃጀቶች ተቀርጸው ተግባራዊ እየተደረጉ ሲሆን እነዚህን መሰረት በማድረግ ባለፉት ዓመታት ብዙ ሊጠቀሱ የሚችሉ አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ አብዛኛዎቹ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያቅዷቸው እቅዶችና ፕሮጀክቶች ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ አካቶ በመተግበር በኩል ያለው አፈፃፀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ቀደም ሲል በሴቶች ላይ ይፈፀሙ የነበሩ የመብት ጥሰቶች /ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኃይል ጥቃቶች ሙሉ በሙሉ ባይወገዱም በየጊዜው እየቀነሱ የመጡ ሲሆን በቤት ውስጥ በሀብትና በንብረታቸው የማዘዝ ሁኔታ እና የውሳኔ ሰጭነት ሚናቸው እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ የትምህርት ተሳትፎና የጤና አገልግሎት ሽፋንም እያደገ መጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካና በመልካም አስተዳደር የተደራጀ እንቅስቃሴ በማድረግ ጥያቄዎቻቸውን የማንሳት ፍላጎትና ተሳትፏቸው በተለይም በገጠር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች ታይተዋል።

100. የ2014 የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ እንደሚያሳየው ጠቅላላ የክልሉ የከተሞች የስራ አጥነት ምጣኔ 20 በመቶ ሲሆን የወንዶች 10.8 በመቶ እንዲሁም የሴቶች 29.5 በመቶ እንደሆነና ይህም የሴቶች የስራ አጥነት ምጣኔ

ከወንዶች ከፍተኛ ብላጫ እንዳለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከሴቶች የስራ አጥነት ምጣኔ ከፍተኛነት ጋር ተያይዞ ሲታይ አሁንም ለሴቶች የሚፈጠው የስራ ዕድል በሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ መሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

101. በሌላ በኩል ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የቁጠባና የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን በዚህም መሰረት በባለፉት ዓመታት የብደር አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ የሴቶች የብድር ተጠቃሚነት ድረሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 73 በመቶ በ2016 63 በመቶ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ እንዲሁም የሴቶችን የቁጠባ ባህል ለማዳበር ባለፉት ዓመታት በተሰሩ የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችና በተዘረጉ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች የቁጠባ ባህላቸው እያደገ እንደመጣ መረጃው ያመላክታል፡፡ የብደር አገልግሎቱ ለመቀነሱም እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት አብዛኛው የንግድ እንቅስቃሴ መቀዛቀዙ፣ የሰሜኑ ጦርነት፣ በክልሉ እየተካሄደ ባለው ግጭት ጥቂት የማይባሉ የአበዳሪ ድርጅቶች ስራቸውን በሚጠበቀው ልክ ማከናወን ባለመቻላቸው እንዲሁም ሴቶች አካባቢያቸውን ለቀው በመሰደዳቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

102. የሴቶችን የኢኮኖሚ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ እንደክልል ባለፉት ዓመታት ሴቶችን በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ የሥራ ዘርፎች፣ በመሬት ባለቤትነት፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና በአረንጓዴ ልማት ፕሮግራሞች፣ በተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ የቁጠባና ብድር አገልግሎት እንዲቀርብላቸው፣ የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉና የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው በማድረግ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግና በከተማ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ከሚገነቡ ቤቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

103. ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ በባለፉት ሶስት ዓመታት 945,654(590,807 እማወራ እና 354,847 ባለትዳር) ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ ይህም ሴቶች የመሬት ባለቤት በመሆናቸው መሬታቸውን ለላቀ ኢኮኖሚ ጠቀሚታና ለዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ፣ የሴቶች መብት መከበርና ዋስትና ለማረጋገጥ እና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋቸዋል፡፡

104. ይሁን እንጅ ለሴቶች የሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የብድርና የግብዓት አቅርቦት፣ ጊዜና ጉልበት የሚቆጥቡ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ በንግድ ስራ ለተሰማሩ ሴቶች የሚደረገው ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን የሚሉት አሁንም ያልተፈቱ ችግሮች ናቸው፡፡

105. ከትምህርት አኳያ በ2015 በጀት ዓመት የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ መረጃ መሰረት በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ እና በመሰናዶ ትምህርት የስርዓተ-ፆታ ልዩነት አመልካች (የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ሲሰላ) እንደቅደም ተከተላቸው 1.04፣ 1.34 እና 1.19 ሲሆን ይህም ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው መረጃው ያሳያል፡፡ ከጤና አኳያ ደግሞ በኢትዮጵያ የስነህዝብና ጤና ጥናት (እኤአ 2019) መሰረት እኤአ በ2019 በአማራ ክልል በጤና ተቋም የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች 54.2 በመቶ ሲሆን የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ደግሞ 82.6 በመቶ እንደነበር መረጃው ያመላክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ ጤና ቢሮ የ2015 በጀት ዓመት መረጃ መሰረት በክልሉ የድህረ ወሊድ ክትትል ሽፋን 82.9 በመቶ እንደነበር መረጃው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን በትምህርት ተሳትፎም ይሁን በጤናው ዘርፍ ገና ብዙ መስራት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

106. በተቋሙ የ5 ዓመት ዕቅድ /2018-2022/ መረጃ መሰረት የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በተወሰዱ እርምጃዎችና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በክልል ምክር ቤት 36.71 በመቶ፣ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቶች 44.18 በመቶ፣ በወረዳ ምክር ቤቶች 49.7 በመቶ እና የቀበሌ ምክር ቤት 47.29 በመቶ ደርሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በ2016 በህግ ተርጓሚነት ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ በተሰራው ስራ በዳኝነት በክልል 21.42 በመቶ፣ በዞን 15.14 በመቶ፣ በወረዳ 27.99 በመቶ እንዲሁም በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች 36.9 በመቶ ሲሆን በአስፈጻሚዉ አካል የአመራር ሰጭነት ቦታ ላይ በክልል 17 በመቶ፣ በዞን 22.9 በመቶ እንዲሁም በወረዳ 21 በመቶ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

107. ይሁን እንጅ ሴቶችን ወደ አመራርነት ከማምጣት አኳያ የወንዶች አመለካከት ያልተቀረፈ መሆን፣ በየደረጃው የአመራር ቁርጠኝነት ማነስ፣ የሴቶች የራሳቸው ፍላጎት ማነስ፣ የሴት አደረጃጀቶች ጥንካሬ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ የወጡ ህጎች ተግባራዊ ባለመሆናቸው ተጠያቂነት አለመኖር፣ በአጠቃላይ በተዛባው የስርአተ ፆታ ግንኙነት፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካው ስር ሰዶ የቆየ ችግር በመኖሩ በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት ከፍተኛ ስራ መስራትን ይጠይቃል፡፡

108. ከህጻናት አኳያ ክልሉ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ስምምነቶችና እና የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር ሰነዶች እንዲሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት የሀገሪቱ የህግ አካል እንዲሆኑ የተደነገጉትን ህጎች መነሻ በማድረግ ለተፈጻሚነታቸው እየሰራ ይገኛል፡፡ በክልሉ የ2017 በጀት ዓመት የህዝብ ቁጥር ትንበያ መሰረት ከጠቅላላዉ ህዝብ ውስጥ 12.1 ሚሊዮን (50.5 በመቶ) የሚሆኑት ህጻናት ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ባለፉት ዓመታት ለችግር ተጋላጭ ከሆኑ ህጻናት አኳያ፣ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ምቹ ቤተሰብና አካባቢን ከመፍጠር፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ከመከላከል፣ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ፣ ከህጻናት የአመጋገብ ስርአት ሁኔታ፣ ከህፃናት ጉልበት ብዝበዛና ህገወጥ ዝውውር ከማገታት፣ የጎዳና ተዳዳሪነት ከመቀነስ እንዲሁም በህፃናት የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ከመከላከል አኳያ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

109. ለአብነት ያህልም የትምህርት ቢሮ የ2015 በጀት ዓመት መረጃ እንደሚያሳየው የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ-8ኛ)፣ የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-10ኛ) እና የመሰናዶ (ከ11ኛ-12ኛ) ትምህርት ንጥር የትምህርት ተሳትፎ እንደቅደም ተከተላቸው 64 በመቶ፣ 27.3 በመቶ እና 15.2 በመቶ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በጤና በኩል በኢትዮጵያ የስነህዝብና ጤና ጥናት (እኤአ 2019) መሰረት እኤአ በ2019 ሁሉንም ዓይነት ክትባት የወሰዱ ህጻናት ቁጥር 62.1 በመቶ እንደሆነና በክልሉ ያለው የመቀንጨር ምጣኔ ደግሞ 41.3 በመቶ ሲሆን ይህም ከሀገር አቀፉ 36.8 በመቶ የመቀንጨር ምጣኔ ከፍ ያለ እና አሳሳቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የስነህዝብና ጤና ጥናት (እኤአ 2016) መሰረት እኤአ በ2016 በክልሉ ያለው የጨቅላ ህጻናት ሞት ከ1000/67 ሲሆን ከ5 ዓመት በታች ያለው የህጻናት ሞት ደግሞ ከ1000/85 እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የበጀት ዓመታት ከትምህርትም ሆነ ከጤና አኳያ ከፍተኛ ስራ መስራትን ይጠይቃል፡፡

110. በሌላ በኩል ሴት የመንግስት ሰራተኞች ህፃናት ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉና እየተንከባከቡ ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ውጤታማ ስራ መስራት እንዲችሉ በመንግስት ተቋማት የህጻናት ማቆያዎችን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ባለፉት ዓመታት በክልል 22፣ በዞን 18 እና በወረዳ 29 በድምሩ 69 ማቋቋም ተችሏል፡፡ ይህም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 29 የ40 ማዕከላት ጭማሪ እንዳለው መረጃው ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 2 የማህበረሰብ የህጻናት ማቆያ ማዕከላትን ማቋቋም ተችሏል፡፡

111. በክልሉ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ምክንያት የተነሳ በርካታ ህጻናት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ህጻናት የአደጋ ተጋላጭ መጠናቸው ከፍተኛ በመሆኑ በቂ የሆነ መጠለያና ልብስ የማያገኙ፣ የተሟላ ምግብ የሌላቸው፣ ለስነ ልቦና ችግር እና ለአድሎና መገለል የተጋለጡ በመሆናቸው መንግስትና ህብረተሰቡ ድጋፍና እንክብካቤ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

112. ህጻናትን በነባርና በአዲስ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ የተለያዩ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ህጻናቱ በክበባት እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ህጻናት የዴሞክራሲ ስርአት ሂደትን እንዲለማመዱና በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ተቀርጸው እንዲያድጉ ለማድረግ የህጻናት ፓርላማ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ እስከ 2016 በጀት ዓመት በክልሉ 3,734 የህጻናት ፓርላማዎችን ማቋቋም የተቻለ ሲሆን በዚህም ህጻናት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ የህጻናት ጉዳይ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሲታይ ብዙ የሚቀረው በመሆኑ በቀጣይ የዕቅዱ ዘመን ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡

113. ከአረጋውያን አኳያ መንግስት አረጋዊያን የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በህገ መንግስቱ፣ በአፍሪካ ህዝቦች እና ሰብዓዊ መብቶች ቻርተር፣ የአፍሪካ አረጋዊያን ፕሮቶኮል ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 1182/2012 በማጽደቅ ወደ ስራ ተግብቷል፡፡ በሀገራችንም ሆነ በዓለም ደረጃ የከተሜነት እና የኢንዱስትሪ መስፋፋት እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማደግ የሰው ልጅ የአኗኗር ዘይቤ እንዲዘምን አድርጓል፡፡ በዚህም የሰዎች አማካይ የመኖሪያ ዕድሜ ጣሪያ ከፍ በማድረጉ የአረጋውያን ቁጥር በየዓመቱ እንዲጨምር ሆኗል፡፡

114. በ1999 የሀገር አቀፍ ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት 1,029,000 አረጋውያን በአማራ ክልል የነበሩ ሲሆን ይህ ቁጥር የጠቅላላ ህዝቡን 5.9 በመቶ እንደሚሸፍን እና 89.2 በመቶ አረጋውያን ደግሞ በገጠር እንደሚኖሩ መረጃ ያመላክታል፡፡ እንደ አማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ 2017 ዓ.ም ትንበያ መሰረት 1,466,543 አረጋውያን በክልላችን ያሉ ሲሆን ይህም ከጠቅላላው ህዝብ 6.14 በመቶ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያል፡፡

115. አረጋዊያን የራሳቸው የሆኑ መሰረታዊ መብቶች እና ፍላጎቶች ያሏቸው ሲሆን ከእነዚህም መካከል የምግብ፣ የመጠለያና የሕክምና አገልግሎቶች፣ የማኅበራዊ ዋስትና፣ የብድር፣ ትምህርትና ሥልጠና በእኩልነት የማግኘት፣

በመረጡትና በሚስማማቸው አካባቢ የመኖር፣ ራሳቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በንቃት የመሳተፍ፣ የሕግ ጥበቃ የማግኘት፣ የግል እምነትን የማራመድና የመንፈሳዊ አገልግሎቶችን የማግኘት፣ በክብር የመኖር፣ በምንም መስፈርት ልዩነት ሳይደረግባቸው በእኩልነት የመታየት እንዲሁም በራሳቸው አደረጃጀቶች እነዚህን መብቶች ማስጠበቅ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጅ መሰረታዊ መብቶቻቸውና ፍላጎቶቻቸው በተሟላ ሁኔታ እየተከበረ እና እየተጠበቀ ባለመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

116. ከአካል ጉዳተኞች አኳያ አካል ጉዳተኝነት እንደ ልዩ መጥፎ ዕድል ተደርጎ የሚቆጠርበት አስተሳሰብ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ የግንዛቤና የአመለካከት ችግር በመሆኑ አካል ጉዳተኞች ፍፁም መስራት እንደማይችሉ በማሰብ ራሳቸውና ቤተሰባቸውን እንዲረዱና በልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዕድል ያልነበራቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ የክልሉ መንግስት የእነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች መብት በማስከበር በሀገሪቱ ልማት እኩል ተሣታፊነትንና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በህገ መንግስቱ፣ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶችን ተቀብሎ ከማጽደቅና በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ከማካተት ጀምሮ የተለያዩ አዋጆችንና የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን በማውጣትና የድርጊት መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀት የተለያዩ ተግባራት ሲያከናወን ቆይቷል፡፡

117. የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር በሚመለከት በተቋሙ የ5 ዓመት ዕቅድ ሰነድ ላይ እንደተመላከተው በክልላችን ወደ 4 ሚሊዮን የሚጠጋ አካል ጉዳተኛ እንደሚገኝ ይገመታል፡፡ ምንም እንኳ አካል ጉዳተኛ ሰዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እና በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካው እና በሌሎች ሴክተሮች ውስጥ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ቢገኙም አሁንም ካለባቸው አካላዊ፣ አእምሮአዊ ወይም የስሜት ህዋሳት እክል የተነሳ ከፍተኛ ለሆነ መድሎ ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡ ለዚህ መድሎ በዋነኝነት እንደምክንያት ወይም መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው ደግሞ ህብረተሰቡ ስለአካል ጉዳተኞች ያለው የአመለካከት ችግር እና የግንዛቤ እጥረት ነው፡፡

118. በመሆኑም በመንግስት አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካው እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ ለማድረግ ባለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

119. ከወጣቶች አኳያ መንግስት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊና በፖለቲካው ዘርፍ ተሳታፊና ከውጤቱም ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህም ወጣቶችን ንቁ ተሳታፊና የውጤቱም ፍትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን፣ አሰራሮችን በመዘርጋት እና ግብዓቶችን በማሟላት በተግባራዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ይገኛል።

120. በክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የ2017 በጀት ዓመት የህዝብ ትንበያ መሰረት በክልሉ እድሜያቸዉ ከ15-29 የዕድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ወጣቶች ቁጥር 7.22 ሚሊዮን (30.23 በመቶ) የሚሆነውን የህብረተሰብ ክፍል እንደሚሸፍን መረጃው ያመላክታል፡፡ ወጣቶች አዳዲስ ሃሳቦችን ከማፍለቅና ከመቀበልም ባሻገር የማምረት እምቅ አቅም ባለቤቶች በመሆናቸው ለአንድ ሃገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ልማት ዕድገት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

121. ወጣቶች በሚፈልጉት የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀት ስር በመሆን መብትና ጥቅማቸውን ህገ-መንግስቱ ባስቀመጠላቸው አግባብ እንዲጠይቁ በተለያዩ የወጣት አደረጃጀቶች ውስጥ ባለፉት አራት አመታት 2.35 ሚሊዮን ወጣቶች በነባርና በአዲስ አደረጃጀቶች ውስጥ እንዲደራጁ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 9,408 የወጣት አደረጃጀት መሪዎች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ያለድምጽ እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በመንግስት እቅዶች፣ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በመሳተፍ ለተግባራዊነቱ የድርሻቸውን ማበርከት የቻሉ ሲሆን በዚህም ጥቂት የማይባሉ ወጣቶች መብት እና ጥቅሞቻቸው ማስከበር ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም በርካታ ወጣቶችን በሚፈለገው ደረጃ አለማደራጀት፤ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ወቅታዊና ተገቢ ምላሽ አለመስጠት፣ ለችግሮቻቸው ራሳቸውን የመፍትሄ አካል አድርገው አለመውሰድ፣ በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች በተለይ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ያለድምጽ በቋሚነትና በሚፈለገው መጠን አለማሳተፍ፣ በመንግስት አመራሮችና በአስፈፃሚ አካላት ለወጣቱ የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆን፣ ወጣት ተኮር የዉይይትና የተሳትፎ መድረኮች /ኮንፈረንሶች/ ማነስ ማነቆ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

122. በኢኮኖሚ ዘርፍ የወጣቱ ዋነኛና አንገብጋቢ በሆነው የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በገጠርና በከተማ የሚገኙ ወጣቶች የስራ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ፣ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡና ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ጅምር ለውጦች ቢኖሩም ለወጣቶች በተለየ አግባብ ምቹ የብድር ስርዓት አለመፍጠር፣

የአካባቢ ፀጋዎችን በአግባቡ ለይቶ መጠቀም አለመቻል፣ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ችግር እንዲሁም የቴክኖሎጂና የግብዓት አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን ለስራ እድል ፈጠራ ተግዳሮት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

123. በማህበራዊ ዘርፍም ብቁ፣ ጤናማና አምራች ዜጋ የሆነ ትውልድ መፍጠር ለአንድ ሃገር የልማት ዕድገት በሚደረገው ርብርብ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የወጣቶችን አስተሳሰብ ለመገንባትና አመለካከታቸውን ለመቀየር፣ ማህበራዊ ኃላፊነታቸዉን እንዲያጎለብቱ ለማድረግ፣ የማህረሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት እንዲሁም በልማቱ የድርሻቸዉን መወጣት እንዲችሉ በክረምትና በበጋ በተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በማሳተፍ ለክልሉ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ተደርጓል፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ የክልሉ ባህል እየሆነ በመምጣቱ የወጣቶች ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ በወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ጠቀሜታውን ተገንዝቦ በትኩረት ይዞ በመስራት በኩል ውስንነቶች ይታዩበታል፡፡ ከወጣት ማዕከላት አኳያ ባለፉት ዓመታት 487 የወጣት ማዕከላትን መገንባት የተቻለ ሲሆን በዚህም በርካታ ወጣቶችን በማዕከላቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን የወጣት ማዕከላት ተደራሽነት ዝቅተኛ ነው፡፡

124. በመሆኑም የወጣቶች ችግር ሰፊ፣ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ በመሆኑና በአንድ ተቋም ብቻ ችግሮችን መፍታት ስለማይቻል በሁሉም የመንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የወጣቶችን ጉዳይ በፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና እቅዶች አካትተው በመስራት የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ በየደረጃው የሚገኙ ሁሉም አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተዉ ሊሰሩ ይገባል፡፡

125. በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታ በዘርፉ በተከናወኑት ስራዎች በርካታ ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም የግንዛቤ ፈጠራና ማሳደግ ስራዎች እና አገልግሎቶች ለህብረተሰቡ በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ አለመሆን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ የኃይል ጥቃቶች እና መጤ ልማዶች መበራከት፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የትብብርና ቅንጅት ስራ የተጠናከረ አለመሆን፣ የድጋፍ የክትትል እና የተጠያቂነት ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ ፖሊሲዎች የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አለመሻሻላቸው፣ ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎች በዘርፉ በስፋት አለመከናወናቸው እና የተጠኑ የጥናት ግኝቶች በአግባቡ ተግባራዊ አለመደረጋቸው፣ በሴቶች ህጻናት ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ዙሪያ ያለው የመረጃ ስርዓት አለመዘርጋቱና አለመጠናከሩ፣ አዳዲስ ተሞክሮዎችን አለመቀመርና አለመተግበር፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተደራሽ አለመሆን እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የህብት እጥረት በዘርፉ የተስተዋሉ ዋና ዋና ክፍተቶች ናቸው፡፡

126. ከስነህዝብ አኳያ የአማራ ክልል ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ከሚታይባቸው የአገራችን ክልሎች አንዱ ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በ1987 ዓ.ም 14.2 ሚሊየን የነበረው የክልሉ የህዝብ ቁጥር በ1999 ዓ.ም ከ12 ዓመት በኋላ በተደረገው ብሔራዊ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት 17.2 ሚሊዮን መድረሱ ታውቋል(ማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሰ፣ 2010)፡፡ የአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ በ2017 ዓ.ም ባወጣው የትንበያ መረጃ መሠረት የክልሉ የሕዝብ ብዛት 23.8 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ አብዛኛዎቹ በመውለድ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ይህ ህዝብ በ2029 ወደ 27.6 ሚሊየን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ በክልሉ የከተሜነት መስፋፋት እየጨመረ ቢሆንም በ2017 ዓ.ም 77.2% (18.44 ሚሊየን) የሚሆነው ህዝብ በገጠር አካባቢ የሚኖር ሲሆን በዋነኝነት በግብርና ላይ የተሰማራ ነው(ማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ፣ እኤአ2013)። በክልሉ በስራ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ እድሜያቸው ከ15-64 ዓመት 56.3% (13.45 ሚሊየን) በመሆናቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች የሚገኙበት ክልል ነው፡፡ በመሆኑም በአገር አቀፍ ደረጃ እንደታየው በክልሉ የህዝብ ስብጥር ለውጡ እድል ወይም ፈተና ይዞ የሚመጣ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በክልሉ ለሚታዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች መንስኤ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለዚህ የክልሉን ከስነ ህዝብ ጋር የተያያዙ ችግሮች ለመፍታት ዘላቂና ህዝብ ተኮር እቅዶችን አካታች በሆነ መልኩ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

127. የስነ ህዝብን ጉዳዮችን ከዘላቂ የልማት ግቦች ትግበራ ጋር ማቀናጀት ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ወሳኝ ያደርገዋል። በፍጥነት የህዝብ ቁጥር መጨመር ሊያስከትሉ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅእኖዎች በመቅረፍ የስነ-ሕዝብ ቱሩፋቱን ጥቅም ላይ ለማዋል ትምህርትን፣ የጤና እንክብካቤን፣ የቤተሰብ ምጣኔን ጨምሮ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማትን ማስተዋወቅና መተግበር እንደሚገባ አጀንዳ 2063ም በተዘዋዋሪ እና በግልፅ ያስቀምጣል።

128. በአጠቃላይ በሁኔታ ትንተናው እንደተመላከተው በዘርፉ ያለው ውክልና፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት አነስተኛ እንደሆነ ታይቷል፡፡ ባለፉት ዓመታት በርካታ ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው የተዛባ አመለካከት ያልተቀረፈ እንደሆነና በእየተቋማቱ ያለው የአካቶ ትግበራም ቢሆን እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

129. በመሆኑም የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋዊያንን እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብት በማስከበር እኩል ተሣታፊነትንና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም የእነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ የሠብዓዊ መብትና የልማት አጀንዳ መሆኑን በመገንዘብ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ በየደረጃው ከሚገኝ የሚመለከተው አካል ሁሉ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች በተለያዩ የሰላምና ጸጥታ ችግሮች ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ጠጠቂ በመሆናቸው ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዕቅድ ዓመታቱ ለስነህዝብ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ቤደረጃው ካለ የሚመለከተው አካል ሁሉ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

## 19.3. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- ተጠቃሚነት፣ ተሳትፎና ውክልና አነስተኛ መሆን
- የተዛባ የአመለካከት ችግርና የተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ደካማ መሆን
- የአካቶ ትግበራ ውስንነት
- የትኩረት መስኮች
- ተጠቃሚነትን፣ ተሳትፎንና ውክልናን ማሳደግ
- የህጻናት ደህንነትና ጥበቃ
- የማህበራዊ ጉዳይ ጥበቃን ማሳደግ
- የህዝብ እድገትና ልማቱ ማጣጣም

## 19.4. የትኩረት አቅጣጫዎች

130. የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተፈጥሮአዊ፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩላቸው ማድረግ፣ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዙሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተፈረሙ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችና ቃልኪዳኖችን ተግባራዊነት የማረጋገጥ፣ በሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ከባህልና ወግ ተቃራኒ የሆኑ መጤ ባህሎች፣ ሱሰኝነት፣ ብዝበዛና አድሎዎች፣ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን የማስቀረት፣ የሴቶች፣ ህፃናትና አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን በነፃ ፍላጎት የመደራጀት መብት የማረጋገጥ እንዲሁም ለሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የተሰጡ ሁለንተናዊ መብቶችን በህበረተሰቡ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና እንዲከበሩ የሚያስችሉ ስራዎችን መስራት፣ የሴቶች፣ ሴክተር ዘለል ጉዳዮችን ተቋማት አካተው እንዲያቅዱና እንዲተገብሩ መከታተልና መደገፍ፣ የስብዕና ልማት ማዕከላትንና ማዘውተሪያ ስፍራዎች በማስፋፋት ህጋዊነታቸውን ማረጋገጥ፣ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያድርጉ ፀጋዎችን በመለየት ተጠቃሚነታቸዉን ማጠናከር፣ ወጣቶች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸዉ ተከታታይ የሙያ ድጋፎችን ማድረግ፣ የወጣቱን ሰብዓዊ ሀብት፣ ዕውቀትና ክህሎት በማበልፀግ ቴክኖሎጂ የመጠቀምና የማፍለቅ አቅሙን ማጎልበት፣ የሰው ሃብትን በማልማት ክልሉን ከስነ ህዝብ ቱሩፋት አዎንታዊ ተጠቃሚ ማድረግ እንዲሁም የሥነ-ህዝብና ወሳኝ ኩነት መረጃ ምዝገባና የመረጃ አያያዝን ማጐልበት የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡

## 19.5. ዓላማ

131. ለስነህዘብና ልማት ትኩረት በመስጠት የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንን እና የሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነት እና ውክል በማረጋገጥ መብታቸውን ማስከበር፣

## 19.6. ዋና ዋና ግቦች

132. የሴቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብትና ደህንነት ከማረጋገጥ አኳያ የሴቶች አካላዊ ጥቃት ምጣኔ ከ24% ወደ 14%፣ የወሲባዊ ጥቃት ምጣኔን ከ10% ወደ 5%፣ የህፃናት ጋብቻ ምጣኔ ከ43% ወደ 15%፣ የሴቶች የቤት ውስጥ ጥቃት ምጣኔን ከ35% ወደ 20%፣ የሴት ልጅ ግርዛት ምጣኔ ከ62% ወደ 30%፣ የህፃናት አካላዊ ጥቃት ምጣኔን ወደ 20% መቀነስ እንዲሁም የህፃናት ወሲባዊ ጥቃት ምጣኔን ወደ 20% ዝቅ ማድረግ የሚሉ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

133. በሌላ በኩል ከሴት ልጅ ግርዛት ነፃ የወጡ ቀበሌዎችን ከ66% ወደ 86%፣ ከሴት ልጅ ገርዛት ነጻ  የወጡ ወረዳዎችን ወደ 20 የማሳደግ ስራ የሚሰራ ሲሆን ከህፃናት ጋብቻ ነፃ የወጡ ቀበሌዎችን ከ35% ወደ 70% እንዲሁም ከህፃናት ጋብቻ ነፃ የወጡ ወረዳዎችን ወደ 15 የማሳደግ ስራም ተግባዊ ይደረጋል፡፡ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህጻናት አገልግሎት የሚሰጡ 3 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በአዲስ እንዲቋቋሙ የማድረግ፣ 1 የሴቶች የተሃድሶና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል የማቋቋም፣ አረጋውያንን እና አካል ጉዳተኞችን በነባርና በአዲስ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ የማድረግ፣ 50 አዲስ የህጻናት ማቆያዎች እንዲቋቋሙ የማድረግ፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምጣኔ ከነበረበት 55% ወደ 40% ዝቅ የማድረግ፣ 1 የህፃናት የተሃድሶ መስጫ ማዕከል እንዲቋቋም ማድረግ እንዲሁም ወደ ጎዳና የሚወጡ ህፃናትን ቁጥር የመቀነስ ስራዎች በከፍተኛ ትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል።

134. ከዚህ በተጨማሪም አካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት ዕድል እና የአካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦች የስነልቦና፣ የማህበራዊ እና ሌሎች የተሃድሶ አገልግሎቶች እንዲያገኙ የማድረግ ስራም የሚተገበር ይሆናል፡፡

135. የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንን እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያም የህፃናት ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የኢኮኖሚ ማጠናከሪያ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን ህፃናት የቤተሰብ ተኮር፣ የማህበረሰብ አቀፍ እና የተቋማዊ እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በሴቶች ልማት ህብረት እና በራስ አገዝ ቡድን እንዲቆጥቡ የማድረግ፣ ለሴቶች የጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጅ አቅርቦትንና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የሴቶችን የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት መብት ማረጋገጥ፣ መብት 19 የአረጋዊያን የገቢ ማስገኛ ማዕከላት እና 1 ሞዴል የአካል ጉዳተኞች የገቢ ማስገኛ ማዕከል የመገንባት፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በማህበረሰብ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት (CCC) በተሰበሰበ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሁኑ የማድረግ እንዲሁም  የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚዎችን፣ ለምኖ አዳሪዎችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችን እና ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን የማቋቋም ስራ ይሰራል፡፡

136. በዕቅድ ዘመኑ 15,000 ሴቶች ለአመራር ብቁ የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አኳያም የሴቶች የቤት ውስጥ የስራ ጫና ከነበረበት 15% ወደ 10% ዝቅ የማድረግ እንዲሁም የስርዓተ ፆታ እኩልነት ያረጋገጡ ቀበሌዎች ከነበረበት 16% ወደ 30% እንዲያድግ የማድረግ ስራዎች በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን ከመዘርጋትና አገልግሎቶችን ከማስፋፋት አንጻርም የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት (CCC) ከነበረበት 96.22% ወደ 100% እንዲያድግ ማድረግ፡፡

137. የሴቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዊያን ተቋማዊነትና ተጠያቂነት ስርዓት ማጎልበትን በተመለከተ ሁሉም ተቋማት በአካቶ ትግበራ ተቋማዊ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓትን ለማሳደግም ፕሮጀክት በመቅረጽ፣ በጥምረቶች (CCC) አማካኝነት እና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ገቢ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡

138. በእቅድ ዘመኑ 4.3 ሚሊዮን አዲስ ወጣቶች በፍላጎታቸውና በመረጧቸው መስኮች በአዲስና በነባር አደረጃጀቶች እንዲደራጁ የማደረግ ግብ የተቀመጠ ሲሆን የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ከማረጋገጥ አኳያ በህግ አውጪ ወደ 20 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ ወደ 36 በመቶ እና በህግ አስፈፃሚ ወደ 20 በመቶ የማድረስ እንዲሁም ወጣቶችን በተለያዩ የንቅናቄ መድረኮች በየደረጃው የማሳተፍ ግብ ተቀምጧል፡፡

139. ከዚህ በተጨማሪም ስራ ፈላጊ ወጣቶች የስራ ባህል ግንዛቤ በመፍጠር ወጣቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው እና የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በበጋ እና በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወጣቶችን በማሰማራት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ የስብዕና ልማት ማዕከላትን ከ483 ወደ 813 በማሳደግ በማዕከላት ተጠቃሚ የሚሆኑ ወጣቶችን ከ6.8 ሚሊዮን ወደ 10.2 ሚሊዮን የማድረስ፣ የሁሉንም ተቋማት የመፈፀም አቅም በማጎልበት የወጣቶች ጉዳይ አካቶ መተግበርን ከነበረበት 55 በመቶ ወደ 75 በመቶ የማድረስ ግቦችንም ለማሳካት ይሰራል፡፡

## 19.7. የማስፈጸሚያ ስልቶች

*ማብቃት*

140. ሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዩች ተጠቃሚና ተሳታፊነታቸው እንዲረጋገጥ የግንዛቤ እና የንቅናቄ ስራዎች መስራት፣

የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መስጠት፣ አደረጃጀቶችን ማቋቋምና ማጠናከር፣ በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ማመቻቸት፣

## አካቶ ትግበራ

141. ተቋማት የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንን እና የስነ-ህዝብ ጉዳይን በፕሮግራሞቻቸው፣ በፕሮጀክቶቻቸው፣ በዕቅዶቻቸውና በሪፖርታቸው እንዲያካትቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ የተቋማትን አቅም መገንባት፣ የመመዘን ስራዎችን መስራት፣

## ትብብርና ቅንጅት

142. ከመንግስታዊና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ፎረሞች፣ ጥምረቶች፣ ምክር ቤቶች፣ ከአጋር አካላት፣ የፋይናንስ እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በትብብርና በቅንጅት በመስራት በዘርፉ የሚኖረውን ውክልና፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

## ተሳትፎና ተጠቃሚነት

143. በዘርፉ የሚኖረውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ሀገራዊ ትስስር የሚፈጠርበት ነፃና ጠንካራ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሚያስችል የልማት ፈንድ ማቋቋም የሚሉት የዘርፉ የ5 ዓመታት ዕቅድ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

# ምዕራፍ ሃያ

# የገጠር ልማት

## 20.1. መነሻ

1. በ2013 ብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ጥናት መሠረት በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው 23,202,770 ሕዝብ ውስጥ 18,664,014 ወይም ከአጠቃላይ የክልሉ ሕዝብ 80.4 በመቶ የገጠር ነዋሪ ነው። በክልሉ ከሚኖረው 11,076,385 አጠቃላይ የሠራተኛ ኃይልም 9,134,334 ወይም 82.5 በመቶ የሚሆነው የሚኖረው በገጠር ነው። በገጠር ከሚኖረው የሠራተኛ ኃይል ውስጥ 7,092,986 ወይም የገጠር ሠራተኛን 77.7 በመቶ የሚሆነው የተሰማራው በግብርና ዘርፍ በተለይም በአብዛኛው በአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ነው። በከተማ የሚኖር አርሶ አደር ወይም ገበሬን ጨምሮ በክልሉ በግብርና እና ተያያዥ ዘርፎች የተሰማራው የሰው ኃይል ከአጠቃላይ የክልሉ ሠራተኛ ኃይል 66.4 በመቶ ነው። የግብርና እና ተያያዥ ዘርፎች ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ምርት ያላቸው ድርሻ 52 በመቶ ሲሆን አብዛኛው የዘርፉ እሴት ከገጠር እንደሚመነጭ ይታወቃል።

2. በከጠር የሚኖረው ሕዝብ ለልማት ተደራሽነት ከፍተኛ እንደምታ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ መገለጫዎች አሉት፤
   - በ2008 መረጃ መሠረት ከድህነት ወለል በታች ያለው የገጠር ሕዝብ ምጣኔ በከተማ ካለው ይበልጣል፤ የከተማ የድህነት ምጣኔ 11.6 በመቶ፣ የገጠር የድህነት ምጣኔ 28.8 በመቶ፣
   - የገጠር የፈርጀ ብዙ ድህነት ምጣኔ ከገቢ ድህነት ምጣኔ የከፋ ሲሆን በትርፍ አምራች ዞኖች እና ወረዳዎች ይበልጥ ይከፋል፣
   - ለወትሮው አነስተኛ የነበረው የገጠር ሥራ አጥነት ምጣኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ 5.1 በመቶ ደርሷል፤ ይህ ማለት 467,101 የሚሆን የገጠር ሠራተኛ ኃይል ሥራ ፈላጊ ሲሆን በከተሞች ከሚኖረው ሥራ አጥ በቁጥር በ42,291 ሰው ይበልጣል፣
   - በገጠር በሥራ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ ኃይል መካከል 55.6 በመቶ የሚሆነው ያልተማረ ወይም መደበኛ ትምህርት ያልተከታተለ ነው (48.4 በመቶ ያህሉ ምንም ዓይነት ትምህርት ያልተማረ፣ 31.1 በመቶ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የወሰደ፣ 4.9 በመቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተከታተለ፣ 2.3 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ከሁለተኛ ደረጃ ተምህርት በላይ የተከታተለ ነው)፣
   - የሠራተኛ ምርታማነት ከአፍሪካ አገራት ጋር ሲወዳደር እንደ አገር 8 አገራትን ብቻ የሚበልጥ ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር የሠራተኛ ኃይል ምርታማነት ከከተማው በግማሽ ያንሳል፣
   - ከ60 ዓመት በፊት በነበረው የምርታማነት ንጽጽር 70 በመቶ የሚሆነው የገጠር ሠራተኛ ኃይል ትርፍ ወይም ስውር ሥራ አጥ ነው
   - በአማራ ብሔራዊ ክልል ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት በአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛው ምጣኔ ነው፣
   - እንደ ውሃ፣ መብራት፣ እና መንገድ፣ እና ጥራት ያለው ትምህርት፣ እና የጤና ክብካቤ በማዕከል ለመስጠት የሚያስችሉ የተሻሻሉ ትምህርት ቤቶችን እና የጤና ተቋማትን የመሳሰሉ ማሕበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት በገጠር፣ በተለይም ከከተማ የመሠረተ ልማቶች ተደራሽነት ምጣኔ ጋር ሲወዳደሩ ዝቅተኛ ናቸው፣
   - የገጠር የመኖሪያ አሰፋፈር ለእርሻ መሬት እና ለግጦሽ ቦታ ቅርበት ሲባል የተበታተኑ በመሆናቸው ለመሠረተ ልማት ዝርጋታ እና ተደራሽነት አመቺ አይደሉም፣
   - በገጠር ለወደፊት ከትመት መነሻ በሚሆኑ ደረጃ የሚቆረቆሩ አዳዲስ የገጠር ከተሞች በፕላን ያልተመሩ እና የወደፊቶቹን ከተሞች ተግዳሮቶች ከአሁኑ የሚያመላክቱ ናቸው፣
   - የገጠሩ ማሕበረሰብ ለኃይል ምንጭነት፣ ለግንባታ፣ ለመሥሪያ ቁሳቁሶች በአካባቢው የወል ደንን የሚጠቀም በመሆኑ እና የእህል ሰብል እርሻን መሠረት ያደረገ ለረጅም ዘመን መሬትን ያለማቋረጥ የሚጠቀም የግብርና ሥልት ስለሚጠቀም የአኗኗር ዘይቤው ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ አይደለም፣

- የኢኮኖሚ መሠረቱ በዋናነት ግብርና፣ የማምረቻ አቅሙ በእንስሳት ጉልበት ላይ የተመሠረተ እና ለዘመናት ያልተሻሻለ ሥልት፣ የህብት መሠረት የሆነው የመሬት ይዞታው በአብዛኛው የተበጣጠሰ እና ለዘመናዊ ግብርና የማያመች ነው።

3. ለችግሮቹ መፍትሄ ሰጥቶ የገጠሩን ማሕበረሰብ ኑሮ ማሻሻል እንዳይቻል ስለ ገጠር ልማት የተያዙ የቆዩ አመለካከቶች እና ስትራቴጂዎች አስተዋጽዖ አድርገዋል። የእነዚህ መገለጫዎችም
    - የገጠሩን ማሕበረሰብ የኑሮ መሠረት ከግብርና በተለይም ከአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ጋር የማያያዝ አመለካከት እና ተግባር ነው። ከግብርና ውጪ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሠረት የሚሆኑ ሀብቶች እና በስልጠና ሲታገዝ በራሱ የልማት አቅም የሚሆን ሰው ባለበት አካባቢን ለእርሻ ሥራ ባለው አመቺነት ብቻ የመልማት አቅሙን በመወሰን ለግብርና ሥራ አመች ባለሆኑ አካባቢዎች የሚኖር ማሕበረሰብ በድህነት እንዲኖር አስተዋጽዖ አድርጓል፤
    - የገጠር ነዋሪ ተግባር የሆነው ግብርና ላልተማረ አርሶ አድር የሚተው እንጂ በትምህርት የተገኘ ዕውቀት ግብርናን የማይቀይር፣ የተማረም የማይሰማራበት ዘርፍ አድርጎ የማየት ችግር፣
    - የዛሬው ገጠር የነገ ከተማ፤ የዛሬው የበለጸገ ገጠር የነገው የበለጸገ ከተማ እንደሆነ ግምት ውስጥ ባለማስገባት የገጠር መሬት በከተማ እስከሚከለል ድረስ የገጠር መንደሮችን በከተማ ልማት አቅባብ ያለማነጽ እና ቀድሞ በዕቅድ ያለመምራት ችግር ናቸው።

## 20.2. የትኩረት አቅጣጫዎች

4. የገጠር ልማት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች
    - የገጠር ሥልተ ምርትን ማሻሻል፣ በተለይም ድህነትን የሚጠየፍ እና በጥረቱ ከድህነት ለመላቀቅ የሚቆጭ ማሕበረሰብ በመፍጠር በራስ ጥረት እና በራስ መተማመን ከበለጸጉ ማሕበረሰቦች ጋር መስተካከል እንዲያልም፣ እና እንዲደርስ ማመላከት፣ መደገፍ፣ መግፋት
    - በክልሉ በከተማ እና በገጠር የተመጣጠነ ልማት ማረጋገጥ፣
    - በገጠር የኢኮኖሚ ዕድገት ከአካባቢ ጥበቃ እና መልካም ባሕላዊ እሴቶች ተመጋግቦ እንዲዘልቅ ማሳለጥ።

## 20.3. ዓላማዎች

5. የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የገጠር ልማት ዋና ዓላማዎች
    - የተሻሻለ እና ጥራት ያለው ኑሮ በገጠር ማረጋገጥ
    - ዘመናዊ መሠረተ ልማትን በተማከለ ሁኔታ እና በጥራት ማዳረስ
    - የቤተሰብ ገቢ ምንጭን ማስፋት እና ማሳደግ
    - የገጠር አካባቢን መልሶ ማልማት
    - ለገጠር - ከተማ ሽግግር ምቹ መሠረት መጣል

## 20.4. የትኩረት መስኮች

6. የገጠር ልማት የትኩረት መስኮች
    - አምራች የገጠር መሠረተ ልማትን ማስፋፋት እና ማዘመን
    - ምርታማነትን በገጠር መጨመር እና የኢንቨስትመነት አማራጮችን ማስፋት
    - አዋጭ የደን ልማት እና የአፈር ጥበቃ ሥራዎች
    - ለመኖር ምቹ የሆነ እና የጸዳ ቤት፣ ለመኖር ምቹ የሆነ እና የጸዳ አካባቢ

## 20.5. ሥልቶች

7. የገጠር ልማት ዕቅድ የማስፈጸሚያ ሥልቶች

- በገጠር ልማት ወይም የገጠር ሽግግር ከተሳካላቸው አገራት ልምድ በመቀመር ከቀበሌዎች እና ጎጦች የሚጀመር፣ በማዕከላት እና በዙሪያው ገጠር መካከል የተሳሰረ ልማትን፣ የተቀናጀ እና ሁሉን አቀፍ የገጠር ልማትን፣ የሰፈራ ማዕከላት ልማትን ታሳቢ ያደረገ፣ በገጠር ነዋሮዎች፣ በመንግሥት እና በአልሚዎች ትብብር የሚካሄድ የገጠር ልማት ንቅናቄ መፍጠር፣
- ትብብር፤ ታታሪነትን እና በራስ የመተማመን ባህርያትን ለጋራ እጣ ፋንታ እና ብልጽግና በፍፁም መደጋገፍ የመሥራት ባሕል ማስረጽ፣
- የሀብት ምንጭ የእርሻ መሬት ብቻ አይደለም- ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች
- በመካከለኛ ጊዜ ስልጡን የገጠር መኖሪያ ለመገንባት፣ ለረጅም ጊዜ የከተማ ልማት ጥሩ መሠረት ለመጣል በገጠር ባለ ሁለት ፍኖት ሥልት መከተል፤
    1. ማዕከል እና ዙሪያ ገብ፣ የወደፊት ከተማነትን ታሳቢ ያደረገ የሰበት ማዕከል መፍጠር- ገና ለከተማ ማዕከልነት ያልበቁ ማዕከላትን በመምረጥ በዙሪያው ያሉ ጎጦች በሳቢ ምክንያቶች እንዲሰባሰቡባቸው ማድረግ - ቀድሞ በፕላን መምራት
    2. ለከተማነት ባይበቁም የገጠር መሠረተ ልማትን በአማካይ ቦታ ለማዳረስ የሚያስችሉ ጎጦችን በመለየት ማልማት
- በየገጠር ኢንተርፕራይዝ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ የባሕል ልማት ተሃዲሶ እና ንቃት፣ የጎጦች ማስተካከል እና ማዋዋጥ፣ በገቢ ማዳደግ፣ የምርት መሠረትን በመቀየር እና በገጠር አመራር ንቃት በሚደረጉ እንቅስቃቄዎች ማሕበረሰብን ማሳተፍ፣ እና
- ከመንገር ባለፈ ማሳየትን እና አብሮ መሥራትን ያስቀደመ የማስተማር ሥልት መከተል።

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

# የከተማ ልማት

## 21.1. መነሻዎች

1. ክትመት የማይቀር ክስተት ነው። ከተሞች የቀጣዮቹ ዘመናት የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ፣ የባሕላዊ እና የፖለቲካዊ ማዕከላት ናቸው። በአማራ ብሔራዊ ክልል ሁኔታ አሁን ያለው የክትመት አካሄድ ከቀጠለ ከ15 እስከ 17 ዓመታት በሚደርስ ጊዜ ውስጥ የክልሉ የከተማ ሕዝብ ቁጥር ለመጀመሪያ ጊዜ የገጠሩን ሕዝብ ቁጥር ይበልጣል፤ የከተማ ሕዝብ ብዛትም በዚያው ልክ ያድጋል። ይህም ማለት ከተሞች ለኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ፣ የፍትህ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች (functions) እና መስተጋብሮች እንደሚኖራቸው ዝግጁነት የጉስቁልና ወይም የብልጽግና፣ የኋላቀርነት ወይም የሥልጣኔ መገለጫ የመሆን መንታ ዕድል አላቸው። ይህን የሚወስነው ይህ ትውልድ የቀጣዮቹን ትውልዶች መዳረሻ ተንብዮ ዛሬ ላይ የሚወስዳቸው የቅድመ - ዝግጅት ርምጃዎች የከተሞችን የስልጣኔ እና የብልጽግና ማዕከልነት በማድረግ አቅም ነው።

2. የቀጣዮቹ ሃያ አምሥት ዓመታት የከተማ ልማት ዋና ዓላማ ከተሞችን ምቹ እና ዘላቂ የመኖሪያ እና የሥራ አውዶች ማድረግ ሲሆን መሣሪያውም የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ የከተማ ፕላን ነው። በከተማ ፕላን ተደራሽ የሚያደርጓቸው ቁልፍ ጉዳዮች የበለጠ ትኩረት ይሻሉ።

## 21.2. አፈጻጸም

3. በተቋሙ የ10 ዓመት (2013-2022) እቅድ በ8 የትኩረት መስኮች እና በ71 ዋና ዋና ግቦች እንዲሁም ግቦችን ለመለካት በተቀረፁ 172 የአፈፃፀም መለኪያዎች (KPIs) ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን ባለፉት 4 ዓመታት በ7 የትኩረት መስኮች ማለትም ዘመናዊ የከተማ ፕላን እና መሬት አስተዳደር፣ ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር፣ የተቀናጀ የከተማ መሠረተ ልማት፣ የከተሞች መልካም አስተዳደርና ፋይናንስ፣ የከተማ ፅዳትና አረንጓዴ ልማት፣ የከተማ ሴፍቲኔትና ምግብ ዋስትና፣ ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግንባታ የትኩረት መስኮች እንዲሁም ከሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያ በ56 ግቦች እና በ119 የአፈፃፀም መለኪያዎች (KPIs) ከነውን /አፈፃፀም የተመዘገበ ሲሆን በ15 ግቦች እና በ53 የአፈፃፀም መለኪያዎች (KPIs) ምንም ከነውን /አፈፃፀም አልተመዘገበም፡፡

4. በነዚህ ዓመታት ከታቀዱ ዋና ዋና ግቦች መካከል በአብዛኛዎቹ አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ከከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ስራዎች አኳያ የክልል ልማት ፕላን ዝግጅት እና የከተማ ትስስር ፕላን ዝግጅት አፈፃፀም (48%)፤ ከመሬት ልማትና አስተዳደር ስራዎች አኳያ ለከፊል ሰነድ አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት (35.62%)፣ ህገ ወጥ ግንባታና መሬት ወረራን መከላከልና መቆጣጠር (26.38%)፣ የከተማ መሬት በጨረታ ማስተላለፍ (24.20%)፤ ከቤት ልማትና አስተዳደር ስራዎች አኳያ የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት (33%)፣ በሪል ስቴት የመኖሪያ ቤት ግንባታ (7.25%)፣ የመንግስት ቤቶችን በዘመናዊ የመረጃ ቋት ማደራጀት (28.04%)፤ ከከተሞች መልካም አስተዳደርና ፋይናንስ ስራዎች አኳያ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥና የተገልጋይ እርካታ እንዲሁም የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ምዘና (47.09%)፣ ለገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና መስጠት (45.10%)፣ የከተሞች ፋይናንስ አሰባሰብና አጠቃቀም (39.60%)፤ ከከተማ ፅዳትና አረንጓዴ ልማት አኳያ ቆሻሻን ከምንጩ የመለየት መልሶ የመጠቀም እና የሚወገደውን በተገቢው ቦታ ማስወገድን ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች (3.57%) እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ዘርፍ አኳያ የመንግስት ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር (19.57%) እና የግንባታ ግብዓት ጥራት ፍተሻ (15.34%) ወዘተ ከተቀመጠው ግብ እና ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር ሲታዩ በሚፈለገው ልክ ያልተከናወኑ (ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸው) ናቸው፡፡

5. ከመሬትና ቤት ልማት አኳያ የደቀቁ የከተማ አካባቢዎችን መልሶ ማልማት እና በመልሶ ማልማት የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣ ከመሰረተ ልማት ስራዎች አኳያ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ፣ ዘመናዊ ቄራ፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ፣ ከፅዳትና አረንጓዴ ልማት አኳያ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ያዘጋጁ ከተሞች፣ ከኮንስትራክሽን ዘርፍ አኳያ በምርምር የተገኙ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ተጠቃሚ የማድረስ ስራዎች አፈፃፀም ያልተመዘገበባቸው ናቸው፡፡

## 21.2. ስትራቴጅክ ጉዳዮች

6. እንደ ከተሞችና መሰረተ ልማት ተቋም ለክልሉ የ25 ዓመት የማክሮ ሌብል እቅድ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ የትኩረት መስኮችንና ዋና ዋና መዳረሻ ግቦችን እንዲሁም ማስፈፀሚያ ስልቶችን የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን ለአብነትም 8 ዋና ዋና የትኩረት መስኮች እና 12 ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፡፡ እንዲሁም በከተሞች የሚታየውን የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በዘላቂነት ከመፍታት አኳያ የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ፣ አገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን፣ ወረቀት አልባ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ ሲስተም ልማት እና ዲጂታይዜሽን ላይ ያተኮሩ ስትራቴጅክ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡

7. የከተሞችን እድገትና ልማት ከማፋጠን አኳያ ስማርት ከተሞች (smart cities)፣ የከተማ ቁጥር እድገት እና ደረጃ ሽግግር፣ የከተማ ነዋሪ ህዝብ እድገት ምጣኔ፣ የከተሞች ፋይናንስ ልማት፣ ክልላዊ የከተሞች እርስ በርስ ትስስር ፕላን ዝግጅት፣ የከተሞች የልማት ቀጠና (ግሮውዝ ኮሪደር) ልየታ፣ አዳዲስ የኢኮኖሚ፣ የቴክኖሎጅ፣ የቱሪዝም፣ የታሪክ (ሂስቶሪካል ሲቲስ)፣ የኢንደስትሪ፣ የንግድ ማዕከል፣ የባህል ማዕከል (compacted cities) የኛ ትውልድ ከተሞች ከተሞች ግንባታ ላይ ያተኮሩ ስትራቴጅክ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡

8. ከከተማ ፕላን አኳያ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ከተሞች 100% በተዘጋጀላቸው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ልማትና አገልግሎቶች ቅንጅትና ትግበራ ፕላን እንዲመሩ ይደረጋል፡፡ ይህም ማለት ሁሉም የክልሉ ከተሞች በሀገር አቀፍ የከተሞች አመሰራረትና ቅንጅት ፕላን (National Urban Development Spatial Plan)፣ የከተማ ልማትን በሚያቀናጅ የክልል ልማት ፕላን (Regional Development Spatial Plan) እና የኢኮኖሚ ትስስር ያላቸዉ አከባቢዎች በትስስር ፕላን (City Cluster Development Plan) እንዲመሩ ማድረግ ለዚህም መነሻ የሚሆነው Regional Development Spatial Plan እና City Cluster Development Plan በሚመለከተው አካል በቀጣይ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንደሚደረግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

9. ከከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር አኳያ 4ቱ ዋና ዋና ተግባራት (functions) ማለትም የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን (land use plan)፣ የመብት ፈጠራና አቅርቦ (land tenure)፣ መሬት ልማት እና ገቢ የማመንጭት (land dev,t & land value tax) እንዲሁም መሬት የማጣራት፣ የማረጋገጥና ብቁ የሆኑትን የመመዝገብ (cadastor) ስራዎች እርስ በርስ ተመጋግበው እንዲዘምኑ በማድረግ የከተማ መሬትን ከዝርፊያና ከንጥቂያ በማላቀቅ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊ እና ወጪ ቆጣቢ መሆነ መንገድ ለላቀ ልማት ማዋል የሚያስችል ስርዓት ዝርጋታ ዋና ስትራቴጅክ ጉዳይ ይሆናል፡፡

10. ከቤት ልማት አኳያ 1,303,917 ቤቶች ውዝፍ (Backlog) እጥረትን ጨምሮ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በከተማ ህዝብ ብዛት መጨመር ምክንያት የሚመጣ የ919,598 ቤቶች ፍላጎት እና በእርጅና ምክንያት መታደስ ያለባቸው 189,792 ቤቶች በመሆናቸው በአጠቃላይ የ2,413,307 ቤቶች ፍላጎት ይኖራል ተብሎ ይገመታል፡፡ በመሆኑም የቤት አቅርቦት ችግር በስፋት በሚታይባቸው ከተሞች በመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በግሉ ዘርፍ እና በህዝብ አጋርነትና ተሳትፎ ተደራሽ እና ወጭ ቆጣቢ የቤት ልማት ስትራቴጅዎን ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም vertical development ላይ በማተኮር በትንሽ መሬት በርካታ ቤቶችን /የጋራ ህንፃዎችን (mixed use apartments) ማልማት ላይ ያተኮረ የቤት ልማት ስትራቴጅን መከተል ሌላው ስትራቴግክ ጉዳይ ነው፡፡

11. ከመሰረተ ልማት አቅርቦት አኳያ በመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በህዝብ አጋርነትና ተሳትፎ ፍትሃዊነትን ባረጋገጠ አኳኋን የተቀናጀ፣ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ፣ ተደራሽና ወጭ ቆጣቢ የሆነ፣ ዘርፈ ብዙ የመሰረተ ልማት አቅርቦት እና አስተዳደር (በዋናነት የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነትና ጥገናን) ስርዓት ዝርጋታ ላይ ያተኮሩ ስትራቴጅካዊ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡

12. ከከተማ ፅዳትና ውበት አኳያ ውጤታማ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያዝና አወጋገድ ስርዓት በመዘርጋት የከተሞችን ገፅታ በዘላቂነት ለመቀየር እንዲቻል በህዝቡ ላይ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ማምጣትን ዋና ግብ አድርጎ ውብ ፅዱ ለኑሮ ተስማሚና አረንጓዴ ከተሞች ግንባታን እውን የሚያደርጉ ስትራቴጅካዊ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡

13. ከምግብ ዋስትና እና ስራ እድል ፈጠራ አኳያ የከተማ ምግብ ዋስትና እና የስራ እድል ፈጠራ ተሞክሮ ፕሮግራሙ ወደ ሌለባቸው ሌሎች ከተሞች እንዴት ይስፋፋ እና በራስ አቅም ከድህነት እንዴት ፈጥነን እንውጣ የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ ስትራቴጅክ ጉዳይ ለመለየት ተሞክሯል፡፡

14. በአጠቃላይ ከአሰራር ስርዓት መዘመን እና የማይለዋወጡ የከተማ ልማት ተቋማትን ከመገንባት ጋር ተያይዞ በተለይም ከስማት ሲቲና ከከተማ መሬት ካዳስተር እንዲሁም አዳዲስ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ ማዕከል ከተሞች ምስረታ ጋር ተያይዞ የአደረጃጀት ለውጥ የሚያመጡ፣ የግህና የአሰራር ማሻሻልና አዳዲስ የህግ ማዕቀፎች ዝግጅትን የሚፈልጉ እንዲሁም በየስራ ዘርፉ ተፈላጊና የከተማ እድገትና ልማትን የሚመራና ዲሲፕሊንድ የሆነ አመራርና ባለሙያ ስምሪት እንዲኖር የሚያስገድዱ ዋና ዋና ችግሮች የተለዩ ሲሆን እነዚህን ግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ዘመናዊ የመረጃና የአሰራር ሥርዓት ዝርጋታ እና ኢንስቲቲዩሽን ግንባታ ላይ ትኩረት ያደረጉ ስትራቴጅዎች ተለይተዋል፡፡

## 21.3. የትኩረት መስኮች

15. ዋና ዋና የከተማ ልማት የትኩረት መስኮች፤

- የከተሞች መልካም አስተዳደርና ፋይናንስ
- ዘመናዊ የከተማ ፕላን እና መሬት አስተዳደር
- ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር
- የተቀናጀ ምርታማና ዘላቂ የከተማ መሠረተ ልማት
- የከተማ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት
- የከተማ ምግብ ዋስትና እና ሴፍቲኔት
- ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እና ኢንስቲቲዩሽን ግንባታ

## 21.4. የከተማ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች

16. ዋናው የከተሞች የትኩረት አቅጣጫ ከተሞችን በፕላን መምራት እና የፕላን ተፈጻሚነትን ማረጋገጥ ነው። ዝርዝር አቅጣጫዎችም

    1. ከተሞችን እንደሀብት መሠረታቸው የልማት ማዕከላት ማድረግ
    2. የከተሞችን መስፋፋት ቀድሞ የሚመራ የከተማ ፕላን እንዲኖር ማድረግ
    3. በዜጎች ተሳትፎ የሚገነቡ ዘላቂ የመኖሪያ ቤቶችን ማስፋፋት
    4. የከተማ መሠረተ ልማትን ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና ጥራት ማረጋገጥ
    5. በከተሞች የምግብ ዋስትናን ጨምሮ ማሕበራዊ ጥበቃን (social protection) ማረጋገጥ
    6. ከተሞች ለኑሮ ምቹ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ፣ ውብ፣ ጽዱና አረንጓዴ እንዲሆኑ ማድረግ
    7. ዘመናዊ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደርን ማስፈን
    8. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን በማዘመን መልካም አስተዳደርን ማስፈን
    9. ዘመናዊ የከተማ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ማስፈን

17. **የከተሞች መጠን፣ ቅርጽ እና ስርጭት፤** ነባር ከተሞችን ማዘመን፣ መልሶ ማልማት፣ እና ማስፋፋት የሚቀጥል ሲሆን በእነዚህ ከተሞች ሊኖር የሚችለውን ሕዝብ ብዛት ከጂኦግራፊያዊ አመችነት፣ ከኢኮኖሚ መሠረት ዘላቂነት፣ ከመሠረተልማት ተደራሽነት፣ ከገጠር - ከተማ ስብጥር እና መስተጋብር አስፈላጊነት፣ እንዲሁም ከከተሞች ያልተማከለ ቀጠናዊ ስርጭት አኳያ በሪጂዮፖሊታን፣ በዞን፣ እና በወረዳዎች ሊኖሩ የሚገባቸውን የከተማ ብዛት እና በእነዚህ ከተሞች ሊኖር የሚችለውን ሕዝብ ብዛት በመካከለኛ እና ረጅም ጊዜ ዕቅድ የሚመላከት ይሆናል። በተለይም ክትመት የኢኮኖሚ አውድ ይሆናል ሲባል የኢኮኖሚ ዕድገት ፍትሃዊ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት በከተሞች ፍትሃዊ ስርጭት የሚወሰን በመሆኑ የከተሞች ስርጭት ከሪጂዮፖሊታን እስከ አነስተኛ ከተሞች አብሮ የመልማት ግብን ታሳቢ ያደረገ አወቃቀር በየአካባቢው እንደ ሀብት መሠረቱ ማዋቀት ተገቢ ይሆናል።

18. **የከተሞች የኢኮኖሚ መሠረት፤** በእውቀት እና ቴክኖሎጂ የሚመራ ኢኮኖሚን በመዋቅራዊ ለውጥ አማካኝነት ማረጋገጥ የረጅም ዘመን ዓላማ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ አንጻር ከተሞች እንደ ሀብት መሠረታቸው የበለጠ በሚታወቁበት መስክ ዝግጅት ያደርጋሉ። የሥራ ዕድል ግቦች ከመዋቅራዊ ግቦች አንጻር በየትኛው ዘርፎች የትኞቹ ከተሞች መተግበር እንዳለባቸው በፕላን ይመላከታሉ። ለዚህም ዝግጁነት የስልጠና፣ የመሬት እና ተያያዥ ሀብቶች ልማት ዕቅድ ይነድፋሉ፣ ይተገብራሉ።

19. **የከተማ፣ የኢንዱስትሪ፣ እና የገጠር መስተጋብር፤** የዘመናዊ አገልግሎት ዘርፎች፣ የአምራች ኢንዱስትሪ እና የከተማ ግንኙነት፣ የኢንዱስትሪ መንደር እና የከተማ ልዩነት፣ የከተማ እና የገጠር የኢኮኖሚ መስተጋብር ምን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው። ከተሞች ምቹ መኖሪያ መሆን ካለባቸው ከብክለት የጸዱ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን የከተማ ማሕበረሰብ የሥራ ዕድል ማግኘት ይችል ዘንድ የአምራች ኢንዱስትሪዎች

ግንባታ አስፈላጊ ይሆናል። ይህን ሚዛን በጠበቀ መልኩ የከተሞች እና የኢንዱስትሪ መንደሮች በትራንስፖርት እና በመኖሪያ ቤት አቅርቦት መስተጋብር የሚመጣጠን ይሆናል። በሌላ በኩል የገጠር እና የከተማ መስተጋብር ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅ በመሆኑ መሬትን በመሳሰሉ ሀብቶች፣ በግብርና ምርት አቅርቦት፣ በኢንዱስትሪ ምርት ፍላጎት፣ እና በሠራተኛ ኃይል ረገድ የሚኖሩ ፍላጎት እና አቅርቦቶች በፖሊሲ እና በፕላን ይመላከታሉ።

20. **የከተማ መሠረተ ልማቶች፤** የከተማ መሠረተልማት የኢኮኖሚ ግቦችን፣ የሕዝብ ብዛትን፣ የከተሞች መስፋፋትን. እና የቴክኖሎጂ ለውጦችን ተከትሎ የሚያድግ እና የሚሰፋ በመሆኑ በኢህ ልክ የረጅም ጊዜ ፍላጎትን፣ እና ተተግባሪነትን በጊዜ ሠሌዳ የሚያመላክት ዕቅድ እና የከተማ ፕላን ይነደፋል። በተለይም የኢኮኖሚ ግቦችን፣ በማሕበራዊ ግቦች ረገድ የትምህርት፣ የጤና፣ የባሕል ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣም የረጅም ጊዜ ዝግጁነት ይደረጋል።

21. **ለመኖሪያ ምቹ የሆኑ ከተሞች፣** የማሕበራዊ መሠረተ ልማቶች፣ ጽዱ እና አረንጓዴ ከተሞች ከሌሎች ግቦች ጋር ተጣጥመው መዝለቅ ይኖርባቸዋል።

22. **የመኖሪያ ቤት ፍላጎት፤** የመኖሪያ ቤት ፍላጎት እና ተደራሽነት የከተማ ልማት አንድ አምድ በመሆኑ ፍትሃዊ የቤት ተደራሽነትን በማረጋገጥ እና ሁሉንም የቤት ባለቤት በማድረግ አመለካከቶች መካከል ያለውን ተጨባጭ ልዩነት በስትራቴጂ የሚመለስ ይሆናል። በተለይም ጥራት ያላቸው የቤት አልሚዎችን ወደ መስኩ በማስገባት ቤት ማልማት አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ እንዲሆን፣ ግለሰቦች ከቤት ግንባታ ይልቅ በሚያዋጣቸው መስክ እንዲተጉ በማድረግ የሥራ ክፍፍልን እና ስልጠትን ወይም ቅልጥፍናን እና ምርታማነትን የማበረታታት አቅጣጫ ይወሰዳል።

23. **ፍትህ እና መልካም አስተዳደር፤** የከተሞች አገልግሎት አሰጣጥ ዝመና፣ የወሳኝ ኩነቶች አገልግሎት፣ ኢ-ገቨርናንስ በጊዜ ሰሌዳ ተመላክተው በከተሞች ይተገበራሉ። የከተማ የመንግሥት እና የሕዝብ ተቋማት ለሕዝባቸው መልካም አክልጋይ ይሆናሉ።

24. **የከተማ ሀብት፤** ሀብትን ማስተዳደር የማይችል ከተማ ለመልማት የሚቸገር በመሆኑ የከተሞች የሀብት መሠረታቸውን በማጤን በዘመናዊ መንገድ ቆጥሮ መያዝ እና መጠበቅ እንዲችሉ ሥርዓት ይዘረጋል።

25. የከተማ ፕላን እና ተተግባሪነት፤ የከተማ ፕልን ስፓሻል ፕላን፣ የከተማ ማስተር ፕላን፣ የከተማ - ገጠር መስተጋብር በተለይም ለነገ ስልጡን ከተሞች መነሻ የሚሆኑ ስልጡን የገጠር መንደሮችን ባካተተ መልኩ ይተገበራል። የከተማ ፕላን ሕግ ነው። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ከፕላን ተደራሽነት እና ክፍተት በላይ ተተግባሪነት ትልቅ ተግዳሮት ሆኗል። በከተሞች በርካታ ቤቶች አንዴ ከተገነቡ በኋላ ለማፍረስ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫናው ከባድ ስለሚሆን በማጽደቅ ሕገወጥነትን ማበረታታት የተለመደ አማራጭ ነው። ይህ በቀጣዮቹ ዓመታት የከተማ ልማት ዕቅድ መቀጠል ያለበት ልምምድ አይደለም። የከተማ ፕላን እንደ ሕግ መከበር የሚኖርበት ሲሆን ሕገ-ወጥ ግንባታን አስተማሪ በሆነ ርምጃ ቀድሞ የመከላከል ሥልት ተተግባሪ ይሆናል።

26. የከተማ መረጃ ሥርዓት፤ የከተማ ልማት ዕቅድ፣ እንዲሁም የከተማ ፕላን በአግባቡ ተተግባሪ የሚሆኑት በተጨበጠ ዘመናዊ መረጃ ላይ በመመሥረት ነው። ከተሞች የሀብት መሠረት እስከ መሠረተልማት እና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮች፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ ልውውጦች በዘመናዊ መረጃ መያዝ ቁልፍ ተግባር ይሆናል።

## ክፍል አምሥት

# የለሙ እና የሚታነጹ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ አቅሞች


| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሃያ ሁለት | **የሚታነጹ ቁሳዊ አቅሞች** |
| ምዕራፍ ሃያ ሦስት | **መሠረተ - ልማት** |
| ምዕራፍ ሃያ አራት | **ሥነ ሕዝብ፣ ሰብዓዊ ካፒታል እና የሰው ሀብት ልማት** |
| ምዕራፍ ሃያ አምሥት | **ሣይንስ እና ቴክኖሎጂ** |

# መግቢያ

1. **በአማራ ብሔራዊ ክልልም ሆነ በኢትዮጵያ የማሕበረሰብ ዕድገት ደረጃ በትውልዶች በሚቆጠር የጊዜ ርዘመት ሊታሰብ የሚችል ግብ አገራዊ እና ክልላዊ አቅሞችን መሬትን መሠረት ካደረገ ተፈጥሮአዊ አቅም ማሸንን መሠረት ወደ አደረገ የቁሳዊ ካፒታል አቅም፣ ከዚህ ሲያልፍም ዕውቀትን መሠረት ወደ አደረገ የሰብዓዊ ካፒታል አቅም፣ እና በመጨረሻም የሥርዓታት ርትዕነትን መሠረት ወደ አደረገ የማሕበራዊ ካፒታል አቅም ማሸጋገር ነው።** በዚህ ሂደትም ማሕበረሰብ ከግብርና መሠረተ - ሕይወት ወደ ኢንዱስትሪያላዊ ማሕበረሰብ፣ ቀጥሎም በዕውቀት ወደሚመራ የለማ ማሕበረሰብ፣ በመጨረሻም የልማት ጥረቶች ሁሉ የመጨረሻ ግብ ሰው የመሆን እውነታ ወደ የሚከበርበት የበለጸገ ማሕበረሰብ እንደሚሸጋገር ታሳቢ ይደረጋል። ነገር ግን ከኋላ ገስግሶ የመልማት ጥቅሙ ቀድመው የበለጸጉ ማሕበረሰቦች ማሕበረሰብ ሲሰለጥን ምን እንደሚመስል ከፊታቸው የሚያሳያቸው ባለመኖሩ በረጅም ጊዜ ሂደት የወጡ እና የወረዱበትን አስቸጋሪ ጉዞ መድገም ሳያስፈልግ ለሁሉም ደረጃዎች ግብ መሳካት ውጥኖችን ቀድሞ በመጀመር እና የቅድም ተከተሎችን የጊዜ ርዝመት በማሳጠር በአቋራጭ ተስተካካይነትን ማረጋገጥ ነው።

2. **የዚህ በትውልድ በሚለካ የረጅም ጊዜ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የተመሠረተ የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ የሚያድግ፣ የሚሰፋ፣ የሚራቀቅ፣ እና የማይነጥፍ ሀብት በአቋራጭ መፍጠር የሚያስችል በቁሳዊ ካፒታል፣ በሰብዓዊ ካፒታል፣ እና በቴክኖሎጂ የሚገለጽ አቅም መፍጠር ነው።** ፍትሃዊ ተደራሽነትን ያማከለ የሰብዓዊ ልማት መነሻ በኢኮኖሚ አቅም የሚለካ ሀብት ነው። የኢኮኖሚ አቅም በረጅም ጊዜ ሂደት በፈጣን እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ይረጋገጣል። በነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት የሚለካ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ በመካከለኛ እና መለስተኛ የረጅም ጊዜ የነፍስ ወከፍ ቁሳዊ ካፒታል እና የምርታማነት ዕድገት ሲሆን፣ ዘለግ ባለ የረጅም ጊዜ (ምናልባትም በሁለት ትውልድ) ደግሞ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው።

3. **የታቀደው የቁሳዊ ካፒታል ለዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ ከክልላዊ ምርት አንጻር ከተመላከተው ምጣኔ በላይ በሚኖረው ምርታማነት እና የቅልጥፍና ደረጃ በእጅጉ ስለሚወሰን እነዚህ ቁልፍ ባሕርያት በመዋዕለ ንዋይ መረጣ እና ስምሪት፣ በጊዜ እና ገንዘብ አጠቃቀም፣ እንዲሁም በሙሉ አቅም ለማምረት በሚያስችሉ የግብዓቶች አቅርቦት እንዲረጋገጡ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል።** ቁሳዊ ካፒታል ከመሠረተ - ልማት አቅም፣ ፋብሪካ ውስጥ እስከ የሚገኙ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ የአገልግሎት ዘርፍ ማሳለጫ ሕንፃዎች፣ መሣሪያዎች እና ቁሶች፣ እንዲሁም ተሽከርካሪዎች ያሉትን ያጠቃልላል። ቁሳዊ ካፒታል ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው ፋይዳ በአብዛኛው ከሠራተኛ ኃይል ጋር ባለው ተገቢ ምጥጥን (capital – labor ratio)፣ ምርታማነት (productivity) እና ቅልጥፍና (efficiency) ሲሆን የቁሳዊ ካፒታል ቅልጥፍና አንድ ብር ዋጋ ያለው ተጨማሪ ዕሴት ለመፍጠር የሚያስፈልገው የካፒታል መጠን የብር ዋጋ ነው። ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች እንደ ባሕርያቸው የተለያየ ደረጃ እና መጠን ያለው ቁሳዊ ካፒታል የሚጠቀሙ ቢሆንም የካፒታል ቅልጥፍና ከዘርፎች እና ከንዑስ ዘርፎች መካከል በትኩረት መስክነት በሚደረግ ምርጫ እና ተገቢ የመዋዕለ - ንዋይ ስምሪት ይወሰናል። የቀጣዮቹን አምሥት ዓመታት እና በተከታዮቹ የአምሥት ዓመታት የልማት ዕቅዶች የተመላከቱ ግቦችን ለማሳካት በየደረጃው ክትትል የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መዋዕለ - ንዋይ ወደ ተፈላጊው ዘርፍ መፍሰሱን እና በተገቢው ቅልጥፍና መከናወኑን፣ እንዲሁም የተገነቡ ቁሳዊ ሀብቶች በሙሉ አቅማቸው ማምረት መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው።

4. **የቁሳዊ ካፒታል የምርታማነት ደረጃ በግብዓትነት በሚያገለግለው የዘርፍ ብዛት እና በውስጡ በያዘው የቴክኖሎጂ ምጥቀት ደረጃ ስለሚወሰን፣ በቴክኖሎጂ የመስተካከል እና የመወዳደር ግብ ለማሳካት የተወጠነው ስትራቴጂ የቁሳዊ ካፒታል አቅምን ቴክኖሎጂ - ገብ በሆኑ ዘርፎች በላቀ ደረጃ በመፍጠር ነው።** ከዚህ አንጻር እንደ መሠረተ-ልማት ዓይነቶቹ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞች ለበርካታ የኢኮኖሚ ተዋናያን እና ዘርፎች በሚኖራቸው ፋይዳ ወሳኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ። በምርት ሂደት ውስጥ በግብዓትነት የሚያገለግሉ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞች በሁሉም ዘርፎች የሚኖራቸው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ በበርካታ ዘርፎች በአላቂ እና ቋሚ ግብዓትነት በሚኖራቸው ሚና እና በሚጠቀሙት የረቀቀ ቴክኖሎጂ - ገብ ግብዓት ምክንያት በአምራች ኢንዱስትሪ በተለይም በከፍተኛ የብረታ-ብረት እና የዐረብ ብረት፣ ማሽነሪ፣ እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ፣ ዘርፎች እና ንዑስ ዘርፎች ላይ ትልቅ አቅም ይፈጠራል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በራሱ እንደ አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ፣ ከዚህም ባለፈ በሁሉም ዘርፎች በሚኖረው የማሳለጥ ሚና እንደ ትልቅ የቴክኖሎጂ አቅም ትኩረት ይሰጠዋል።

5. **የቁሳዊ ካፒታልም ሆነ ተያያዥ የቴክኖሎጂ አቅሞችን መፍጠር የሚቻለው እና በምርት እና አገልግሎት ሂደት ውስጥ በተገቢው ደረጃ አገልግሎት ላይ መዋላቸው የሚረጋገጠው በሰብዓዊ ካፒታል ላይ በሚደረግ መዋዕለ -ንዋይ በመሆኑ በትምህርት፣ በጤና እና አመለካከት ዙሪያ በሚሠሩ ሥራዎች በዕውቀት የታነፀ ርትዕ እና አልሚ ትውልድ እንዲፈጠር ጥረት ይደረጋል።** የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት ለስኬት የሚበቃው የሰው ኃይል በተገቢ ዘርፎች በተለይም በሣይንስ እና ቴክኖሎጂ በብቃት እና በጥራት ሲሰለጥን ነው። ቴክኖሎጂ ባለ ሁለት ስለት ጎራዴ ነው። ለዚህም ሣይንሳዊ ዕውቀት ለመልካም የማሕበረሰባዊ ብልጽግና እንዲውል በማሕበረሰቡ በተለይም በወጣቱ ትውልድ ላይ ትልቅ የመልካም ስብዕና ግንባታ ሥራ ይሠራል።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

# የሚታነጹ ቁሳዊ እና የማይዳሰሱ አቅሞች

### የክልሉ የልማት አቅሞች

1. ክልሉ ለሁሉም ዓይነት የኢኮኖሚ ዘርፎች ልማት ምቹ የሆኑና ከሞላ ጎደል ሁሉም ዓይነት መሠረታዊ የተፈጥሮ ሀብት አቅሞች ያሉት ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ ያሉትን ዕምቅ የልማት አቅሞች ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ በመለየትና በማልማት እና የክልሉን ሀብት በስፋት ተጠቅሞ ኢኮኖሚውን ማሳደግ ያስችላል፡፡ ከዚህ አኳያ የአማራ ክልል በብዙ ዕምቅ ሀብቶች ተነፃ ጻሪ ጠቀሜታ /Comparative Advantage/ ያለው በመሆኑ ያሉትን ፀጋዎች በአግባቡ በመለየትና ለልማት በማዋል ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ እና የህዝቡን የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በክልሉ የሚገኙ ዕምቅ አቅሞች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡
2. **ሰብዓዊ ሀብት፡-** በክልሉ ያለዉ የህዝብ ቁጥር ሲታይ እጅግ በጣም ግዙፍና ትልቅ የልማት አቅም ሊሆን የሚችል ሲሆን እንደ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ ትንበያ መረጃ በ2017 ዓ/ም በክልሉ 11,884,006 (49.78 በመቶ) ወንድ እና 11,994,993 (50.23 በመቶ) ሴት በድምሩ 23,878,999 የሚኖር ሲሆን ህዝብ ይኖራል ተብሎ የሚገመት ሲሆን በወጣት የእድሜ ስብጥር ( 15 – 64 ) ያለው አምራች ሰብዓዊ ሀብት ከአጠቃላይ የክልሉ ህዝብ 56.32 በመቶ (13,449,286) የሚሆነውን ይይዛል፡፡ ይህ ትኩስ ሀይል የልማት አለኝታ ሊሆን የሚችል እና ከዚህም ጎን ለጎን ክልሉን የቀጣይ የስነ ህዝብ ትሩፋት ተጋሪ በመሆኑ እንደ አንድ የእድገት አቅም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
3. **የመሬት ሀብት፡-** ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት (ILRI) በተገኘው መረጃ መሰረት በአማራ ክልል ለግብርና ተስማሚ የሆኑ 17 የአፈር አይነቶች የሚገኝ ሲሆን ይህም ክልሉን ለግብርናዉ ዘርፍ ቀዳሚ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡
4. **የውኃ ሀብት፡-** እንደሚታወቀው ውኃ ለመጠጥ፣ ለመስኖ ልማት፣ ለእንስሳት ሀብት ልማት፣ ለዓሳ እርባታ፣ ለብዝሀ ህይዎት ጥበቃ፣ ለመጓጓዣ፣ ለቱሪስት መስህብነትና ለመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያገለግላል፡፡ ስለሆነም ወደፊት የሚታሰበውን ዘላቂ ልማት ከማረጋገጥ አንፃር ያለንን የውኃ ሀብት ዕምቅ አቅም መለየትና በዘላቂነት መጠቀም የሚቻልበትን ሥልት መቀየስ አስፈላጊ ነው፡፡ ክልላችን ከሀገሪቱ የገጽ ምድር የውሃ ሀብት ከፍተኛውን/60 በመቶ/ ሚሆነውን የውሃ መጠን ያመነጫል፡፡ ክልሉ እንደ አባይ፣ ተከዜ ወዘተ … የመሳሰሉ ተፋሰሶች የሚገኙበት የበርካታ ወንዞች ባለቤት ሲሆን በአጠቃላይ 44.8 ቢሊዮን ሜትር ኩዩቢክ የገጸምድር ውኃና ሰፊ የከርሰ ምድር ውኃ አለዉ፡፡ በተጨማሪም በክልሉ 1,677 የሚደርሱ ዓመቱን በሙሉ የሚፈሱ እና 297 በክረምት ብቻ የሚፈሱ ወንዞች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም በዓመት ወደ 35 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ይገኛል፡፡
5. **የማዕድን ሀብት፡-** ማዕድን ለአንድ ሀገር የገቢ ምንጭነት፣ ለኢንዱስትሪ ግብአትነት፣ ለመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለዉጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን ሃገራችንም በኢንዱስትሪ ግንባታ በምታደርገው ጉዞ ቀላል የማይባል ድርሻ አለዉ፡፡ በክልላችን በርካታ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ የኢንዱስትሪ፣ የከበሩ፣የብረትና ብረት ነክ፣ የኮንስትራክሽንና የኢነርጂ ማዕድናት እንዳሉ የተደረጉ ጥናቶች የሚያመላክቱ ሲሆን ይህም በክልሉ በዚህ ዘርፍ ለሚሰማሩ እና ማልማት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ እና ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም በክልሉ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት አሲዳማ አፈርን ለማከም ጥቅም ላይ የሚውለውን ኖራ ድንጋይ ጨምሮ እንደ ጀሶ ድንጋይ (ጂፕሰም)፣ ሲልካ ሳንድ፣ ፑሚስ፣ ካኦሊን፣ ሸክላ አፈርና የመሳሰሉ ማዕድናት ፣ ኦፓል፣ አምበር እና ጃስፐር ያሉ የከበሩ ማዕድናት፣ ብረት ነክ ማዕድናት፣ የወርቅ ክምችት ፣ እንደ ድንጋይ ከሰል ያሉ

የኢነርጂ ግብዓት የሚያገለግሉ ማዕድናት፣ ኦይል ሼል /ነዳጅ አዘል አለት/፣ ለግንባታ የሚያገለግሉ እንደ እምነበረድ፣ ግራናይት፣ ሳንድስቶን፣ ነጭ ድንጋይ፣ ጥቁር ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ቀይ አሸዋ (Scoria) እና ለዘመናዊ ህንፃ ማስዋቢያ በጣም ተፈላጊ የሆነው የጥርብ ድንጋይ በክልሉ በተለያዩ ዎረዳዎች ይገኛሉ፡፡

6. **የቱሪዝም ሀብት፡-** የቱሪዝም ልማት የኢኮኖሚ እድገትን ለማሳደግ፣ ድህነትን ለመቅረፍ፣ የስራ እድል ለመፍጠር እና የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል እንደ አንድ ጠቃሚ ስትራቴጂ ጥቅም ላይ ይውላል። የአማራ ክልል በሁሉም የቱሪዝም ዓይነቶች የተፈጥሮ፣ ቅርስ ወይም የባህል ቱሪዝም በበቂ ሁኔታ የበለፀገ ነው፡፡ በክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በመንከባከብ፣ በማስተዋወቅ እና በማስፋፋት ለቱሪዝም ዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠትና ከቱሪዝም ዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ማግኘት እና ማህበራዊ ልማትን ማረጋገጥ ይቻላል። የአማራ ክልል ሠፊ የቆዳ ስፋት ያለው፣ ብርቅዬና ድንቅዬ የዱር እንስሳት፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች፣ ገዳማትና አድባራት፣ሀይቆች፣ ፍል ዉሀዎች፣ፓርኮች፣የትግል ቦታዎች፣ ባህላዊ እሴቶች እና ሌሎች የቱሪስት መስህብ ሃብቶች ያሉት አካባቢ ነው። በሚዳሰሱ እና በማይዳሰሱ ቅረሶች ሀገሪቱ በዩኔስኮ ለዓለም ቅርስነት ያስመዘገበቻቸው እንደ የላል-ይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣የጭስ አባይ ፏፏቴ፣ የጎንደር ቤተመንግስታት፣ጮቄ ምርጥ የቱሪዝም መንደር፣የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ እና የጣና ሃይቅ በክልሉ ይገኛሉ፡፡ ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል የጥምቀት በዓል ፣ የመስቀል በዓል ፣ እንዲሁም የልደት በዓል በሀገራችን ብሎም በክልላችን በድምቀት የሚከበሩ ሲሆን ይህም የክልሉ ድንቅ የቱሪዝም እምቅ ሀብት ነዉ፡፡ በተጨማሪም በክልሉ ከሚገኙ የዱር እንስሳት መካከል ዋልያ፣ ቀይቀበሮ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ የምኒሊክ ድኩላ፣ ሚዳቋ፣ነብር፣ አቦሸማኔ፣ ቆቅ የተለያዩ ዝርያ ያላቸው አዕዋፋት እና ሌሎችም የሚገኙበት በመሆኑ በቱሪዝም ዘርፉም ትልቅ አቅም ያለዉ ክልል በመሆኑ በቱሪዝም ዘርፉ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

7. **ቁሳዊ የካፒታል አቅሞች፡-** አብዛኛቹ የተገነቡ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞች በመሠረተ ልማትና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትን ለማካሄድ የተገነቡ ህንፃዎች እንዲሁም የመስኖ መሠረተ ልማቶች፣ የኢንዱስትሪ መንደሮችና የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የኢነርጂ መሠረተ ልማት የመሳሰሉት ለዕድገት መነሻ አቅሞች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

8. በአማራ ብሔራዊ ክልልም ሆነ በኢትዮጵያ የማሕበረሰብ ዕድገት ደረጃ በትውልዶች በሚቆጠር የጊዜ ርዘመት ሊታሰብ የሚችል ግብ አገራዊ እና ክልላዊ አቅሞችን መሬትን መሠረት ካደረገ ተፈጥሮአዊ አቅም ማሸንን መሠረት ወደ አደረገ የቁሳዊ ካፒታል አቅም፣ ከዚህ ሲያልፍም ዕውቀትን መሠረት ወደ አደረገ የሰብዓዊ ካፒታል አቅም፣ እና በመጨረሻም የሥርዓታት ርትዕነትን መሠረት ወደ አደረገ የማሕበራዊ ካፒታል አቅም ማሸጋገር ነው። በዚህ ሂደትም ማሕበረሰብ ከግብርና መሠረተ - ሕይወት ወደ ኢንዱስትሪያላዊ ማሕበረሰብ፣ ቀጥሎም በዕውቀት ወደሚመራ የለማ ማሕበረሰብ፣ በመጨረሻም የልማት ፕረቶች ሁሉ የመጨረሻ ግብ ሰው የመሆን እውነታ ወደሚከበርበት የበለጸገ ማሕበረሰብ እንደሚሸጋገር ታሳቢ ይደረጋል። ነገር ግን ከኋላ ገስግሶ የመልማት ጥቅሙ ቀድመው የበለጸጉ ማሕበረሰቦች ማሕበረሰብ ሲሰለጥን ምን እንደሚመስል ከፊታቸው የሚያሳያቸው ባለመኖሩ በረጅም ጊዜ ሂደት የወጡ እና የወረዱበትን አስቸጋሪ ጉዞ መድገም ሳያስፈልግ ለሁሉም ደረጃዎች ግብ መሳካት ውጥኖችን ቀድሞ በመጀመር እና የቅደም ተከተሎችን የጊዜ ርዝመት በማሳጠር በአቋራጭ ተስተካካይነትን ማረጋገጥ ነው።

9. የዚህ በትውልድ በሚለካ የረጅም ጊዜ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የተመሠረተ የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ የሚያድግ፣ የሚሰፋ፣ የሚራቀቅ፣ እና የማይነጥፍ ሀብት በአቋራጭ መፍጠር የሚያስችል በቁሳዊ ካፒታል፣ በሰብዓዊ ካፒታል፣ እና በቴክኖሎጂ የሚገለጽ አቅም መፍጠር ነው። ፍትሃዊ ተደራሽነትን ያማከለ የሰብዓዊ ልማት መነሻ በኢኮኖሚ አቅም የሚለካ ሀብት ነው። የኢኮኖሚ አቅም በረጅም ጊዜ ሂደት በፈጣን እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ይረጋገጣል። በነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት የሚለካ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ በመካከለኛ እና መለስተኛ የረጅም ጊዜ የነፍስ ወከፍ ቁሳዊ ካፒታል እና የምርታማነት ዕድገት ሲሆን፣ ዘለግ ባለ የረጅም ጊዜ (ምናልባትም በሁለት ትውልድ) ደግሞ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው።

10. የታቀደው የቁሳዊ ካፒታል ለዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ ከክልላዊ ምርት አንጻር ከተመላከተው ምጣኔ በላይ በሚኖረው ምርታማነት እና የቅልጥፍና ደረጃ በእጅጉ ስለሚወሰን እነዚህ ቁልፍ ባሕርያት በመዋዕለ ንዋይ መረጣ እና ስምሪት፣ በጊዜ እና ገንዘብ አጠቃቀም፣ እንዲሁም በሙሉ አቅም ለማምረት በሚያስችሉ የግብዓቶች አቅርቦት እንዲረጋገጡ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል። ቁሳዊ ካፒታል ከመሠረተ - ልማት አቅም፣ ፋብሪካ ውስጥ እስከ የሚገኙ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ የአገልግሎት ዘርፍ ማሳለጫ ሕንፃዎች፣ መሣሪያዎች እና ቁሶች፣ እንዲሁም ተሽከርካሪዎች ያሉትን ያጠቃልላል። ቁሳዊ ካፒታል ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው ፋይዳ በአብዛኛው ከሠራተኛ ኃይል ጋር ባለው ተገቢ ምጥጥን (capital – labor ratio)፣ ምርታማነት (productivity) እና ቅልጥፍና (efficiency) ሲሆን የቁሳዊ ካፒታል ቅልጥፍና አንድ ብር ዋጋ ያለው ተጨማሪ ዕሴት ለመፍጠር የሚያስፈልገው የካፒታል መጠን የብር ዋጋ ነው። ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች እንደ ባሕርያቸው የተለያየ ደረጃ እና መጠን ያለው ቁሳዊ ካፒታል የሚጠቀሙ ቢሆንም የካፒታል ቅልጥፍና ከዘርፎች እና ከንዑስ ዘርፎች መካከል በትኩረት መስከነት በሚደረግ ምርጫ እና ተገቢ የመዋዕለ - ንዋይ ስምሪት ይወሰናል። የቀጣዮቹን አምሥት ዓመታት እና በተከታዮቹ የአምሥት ዓመታት የልማት ዕቅዶች የተመላከቱ ግቦችን ለማሳካት በየደረጃው ክትትል የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መዋዕለ - ንዋይ ወደ ተፈላጊው ዘርፍ መፍሰሱን እና በተገቢው ቅልጥፍና መከናወኑን፣ እንዲሁም የተገነቡ ቁሳዊ ሀብቶች በሙሉ አቅማቸው ማምረት መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው።
11. የቁሳዊ ካፒታል የምርታማነት ደረጃ በግብዓትነት በሚያገለግለው የዘርፍ ብዛት እና በውስጡ በያዘው የቴክኖሎጂ ምጥቀት ደረጃ ስለሚወሰን፣ በቴክኖሎጂ የመስተካከል እና የመወዳደር ግብ ለማሳካት የተወጠነው ስትራቴጂ የቁሳዊ ካፒታል አቅምን ቴክኖሎጂ - ገብ በሆኑ ዘርፎች በላቀ ደረጃ በመፍጠር ነው። ከዚህ አንጻር እንደ መሠረተ-ልማት ዓይነቶቹ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞች ለበርካታ የኢኮኖሚ ተዋናያን እና ዘርፎች በሚኖራቸው ፋይዳ ወሳኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ። በምርት ሂደት ውስጥ በግብዓትነት የሚያገለግሉ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞች በሁሉም ዘርፎች የሚኖራቸው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ በበርካታ ዘርፎች በአላቂ እና ቋሚ ግብዓትነት በሚኖራቸው ሚና እና በሚጠቀሙት የረቀቀ ቴክኖሎጂ - ገብ ግብዓት ምክንያት በአምራች ኢንዱስትሪ በተለይም በከፍተኛ የብረታ-ብረት እና የዐረብ ብረት፣ ማሽነሪ፣ እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ፣ ዘርፎች እና ንዑስ ዘርፎች ላይ ትልቅ አቅም ይፈጠራል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በራሱ እንደ አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ፣ ከዚህም ባለፈ በሁሉም ዘርፎች በሚኖረው የማሳለጥ ሚና እንደ ትልቅ የቴክኖሎጂ አቅም ትኩረት ይሰጠዋል።
12. የቁሳዊ ካፒታልም ሆነ ተያያዥ የቴክኖሎጂ አቅሞችን መፍጠር የሚቻለው እና በምርት እና አገልግሎት ሂደት ውስጥ በተገቢው ደረጃ አገልግሎት ላይ መዋላቸው የሚረጋገጠው በሰብዓዊ ካፒታል ላይ በሚደረግ መዋዕለ -ንዋይ በመሆኑ በትምህርት፣ በጤና እና አመለካከት ዙሪያ በሚሠሩ ሥራዎች በዕውቀት የታነፀ ርትዕ እና አልሚ ትውልድ እንዲፈጠር ጥረት ይደረጋል። የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት ለስኬት የሚበቃው የሰው ኃይል በተገቢ ዘርፎች በተለይም በሣይንስ እና ቴክኖሎጂ በብቃት እና በጥራት ሲሰለጥን ነው። ቴክኖሎጂ ባለ ሁለት ስለት ጎራዴ ነው። ለዚህም ሣይንሳዊ ዕውቀት ለመልካም የማሕበረሰባዊ ብልጽግና እንዲውል በማሕበረሰቡ በተለይም በወጣቱ ትውልድ ላይ ትልቅ የመልካም ስብዕና ግንባታ ሥራ ይሠራል።

## ቁሳዊ የማምረቻ ካፒታል አቅሞች

13. በአሁኑ ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ በገቢ ንግድ በሚገለጽ ከፍተኛ ፍላጎት እና በወጪ ንግድ በሚገለጸው አቅርቦት መካከል ያለው የሰፋ ልዩነት በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ደረጃ በአብዛኛው የቁሳዊ ማምረቻ ካፒታል አቅም ልዩነት ነጸብራቅ ሲሆን፣ የቀጣዮቹ ዓመታት የዕቅዱ የመጀመሪያ ርምጃ የእነዚህን አቅም ልዩነት ማጥበብ ነው። የ20 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ዋጋ ያላቸው የገቢ ዕቃዎች የሚፈበረኩት የተራቀቀ ቴክኖሎጂ በሚጠቀም ቁሳዊ የካፒታል አቅም

ሲሆን ይህን ወጪ በመጠኑም ቢሆን (4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር) ለመሸፈን ኢትዮጵያ ለዓለም የምታቀርበው ምርት የሚመረተው ከሞላ ጎደል በበሬ ጫንቃ አቅም ነው። በብሔራዊ የሀብት ማጠቃለያ (National Accounts) በእኩል የዶላር ዋጋ የተመዘገቡ የቁሳዊ ካፒታል መጠኖች እኩል የማምረት አቅም ላይኖራቸው የመቻሉ ምስጢር የቁሳዊ ካፒታል ወሳኙ አቅም መጠኑ እና ዋጋው ሳይሆን ምርታማነቱ ነው። በመካከለኛ ጊዜ የመሠረተ ልማት አቅሞችን እና የቁሳዊ ካፒታል አቅምን በማስፋፋት ብቻ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ እና ክልላዊ ገቢን ትርጉም ባለው ደረጃ ከፍ ማድረግ ይቻላል። ከዚህ አንጻር በግብርናው ዘርፍ በበሬ ላይ የተመሠረተ አስተራረስን ወደ ሜካናይዜሽን መቀየር እና በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እንደ ምግብ፣ ጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ እንዲሁም የኮንስትራክሽን ግብዓቶች የመሳሰሉትን መሠረታዊ የገቢ ዕቃዎች ለመተካት የሚያስችሉ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞችን መገንባት ተገቢ ነው። ነገር ግን ዘላቂ እና የማይቀለበስ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ ለሚያስችሉ፣ የተራቀቁ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን ለሚጠቀሙ የብረታ ብረት እና ማሽነሪ እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ አቅሞች መሠረት ይጣላል።

# ምዕራፍ ሃያ ሦስት

# መሠረተ ልማት

## 23.1. መነሻ

6. **በትክክለኛ መረጣ እና ዘርፍ - ተኮር ድልድል መሠረተ - ልማት ለዕድገት እና ልማት ሦስት እጥፍ ዕድል ይሰጣል።** አንድደኛ፣ በመሠረተ-ልማት ዝርጋታ ወቅት ዜጎች ተቀጥረው ገቢ ያገኛሉ፤ በሚፈጠረውም የፍላጎት ማድግ እንደ ግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪ ያሉ አምራች ዘርፎች፣ እንዲሁም አገልግሎት ዘርፎች በአጸፋው እንዲነቃቁ ያደርጋል። ሁለተኛ፣ በተለይም የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማት ሲስፋፋ መነሻው ምርት እና ምርታመነትን መጨመር በመሆኑ የእነዚህ አቅሞች መገንባት የመዋዕለ - ንዋይ ፍሰትን በመጨመር፣ የተገነቡ እና የሚገነቡ የኢኮኖሚ ተቋማት የምርታማነት እንዲጨመር ያደርጋል። ሦስተኛ፣ በመሠረተ-ልማት አውታሮች ውስጥ በሂደት የሚያድግ ቴክኖሎጂ ስላለ፣ እንዲሁም እንደ ኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዓይነቶቹ የመሠረተ-ልማት አውታሮች በአዳጊ እና ተለዋዋጭ ቴክኖሎጂ የሚመሩ በመሆናቸው በዲጂታላይዜሽን ከታገዘ ዘመናዊ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ (e-Governance) እስከ ዘመናዊ የፋይናንስ አገልግሎት (FinTech) የሚደርሱ የማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎችን በማሳለጥ ምርታማነት እንዲመነደግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

7. **የውሃ እና ኃይል፣ የመስኖ፣ የመንገድ እና ሎጂስትክስ አገልግሎት፣ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የመሠረተ-ልማት አውታሮች ግንባታ በዕቅዱ ለዘርፎች በተሰጠው ትኩረት ልክ ቅልጥፍናን እና ምርታማነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ይገነባሉ፣ ይቀርባሉ።** ፈጣን የግብርና ልማት ሲታሰብ የመስኖ ልማት፣ ምርትን ከማሳ ወደ ገበያ ለመጓጓዝ የሚያግዙ መንገዶች፣ ለግብርና ሜካናይዜሽን የሚውሉ ማሽኖች በቀላሉ ወደ ማሳ የሚደርሱበት አማካይ የማሳ ውስጥ መንገድ፣ ለእንስሳት ሀብት ልማት የሚውል የውሃ፣ የእንስሳት ጤና እና የኳራንቲን አገልግሎት ማሳለጫ የመሠረተ-ልማት ግንባታዎች ያስፈልጋሉ። በኮመርሻል ግበርና የተመረቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች እና የወጪ ንግድ ምርቶች፣ ከውጭ የሚገቡ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች፣ እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ክልሉን ከሌኮች ክልሎች እንዲሁም ከወደብ በአቋራጭ ርቀት የሚያገናኙ መንገዶች እና የባቡር ሃድድ ልማቶች ያስፈልጋሉ። የማይቆራረጥ እና በቂ የኃይል አቅርቦት ለታቀደው የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት እና ዘመናዊ ግብርና፣ የዘላቂ ከተማ ልማት፣ እና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ወሳኝ መሠረተ-ልማት ነው። አገራዊ የኃይል አቅርቦትን የማሳደግ ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በክልሉ አቅም ሊሠሩ የሚችሉ አማራጭ የኃይል ምንጮች መገንባት ታሳቢ ተደርጓል።

8. **የከተማ መሠረተ ልማት አውታሮች የወቅቱን ችግር ከመሸንገል ባለፈ የሰለጠኑ አገራት ከተሞች የተጓዙበትን ረጅም እና ከችግር የመማር ሂደት መድገም ሳያስፈልግ በሩቅ እይታ ለዘመኑ የሚመጥኑ ሆነው መገንባት አለባቸው።** የከተሞችን ዕድገት ቀድሞ በመተንበይ እና በመተንተን የረጅም ዘመን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ፍላጎት ማቀድ፣ ለእድገት ደረጃቸው የሚመጥን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ መሠረት ልማቶችን መዘርጋት፤ ከተሞች እንደ ጂኦግራፊያዊ አመችነታቸው፣ የሀብት መሠረታቸው፣ እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው የደረቅ ወደብ፣ የአቪዬሽን፣ እና የባቡር ትራንስፖርት ማዕከላት እንዲሆኑ በረጅም ጊዜ ዕቅድ ማመላከት፣ በየደረጃው ወደ ተግባር ማሸጋገር የከተማ መሠረተ-ልማትን ተገቢ ሚና ያረጋግጣል። ትውልድ የሚቀረጽባቸው የትምህርት ተቋማት እና የጤና ተቋማት ቀድመው በዕቅድ እንዲመላከቱ፣ ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩም እንዲገነቡ ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

9. **የገጠር መሠረተ ልማቶች ቀልጣፋ አገልግሎትን እና የወደፊት ዘመናዊ ክትመትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በአማካይ ማዕከላት እንዲሰጡ ይደረጋል።** በሰለጠነው ዓለም ደረጃ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ቀጥር በአንድ ከተማ ሊስተናገድ የሚችል ነው። የከሰፊው የአማራ ክልል መሬት ውስጥ በከተማም ሆነ በገጠር ለሰው መኖሪያነት የዋለው ከ4 በመቶ አይበልጥም። ነገር ግን 80 በመቶ የሚሆነው የክልሉ የገጠር ነዋሪ አሰፋፈር ለእርሻ ማሳ ያለውን ቅርበት ተከትሎ የመሠረተ-ልማት አገልግሎት ተደራሽነትን በሚገድብ ሆኔታ የተበታተነ ነው። ይህን ሁኔታ መልክ ለማስያዝ የግዳጅ መንደር ምስረታ ሳይስፈልግ ቀድሞ በተጠና የወደፊት ከተማነትን ታሳቢ ያደረገ ዕቅድ የመሠረተ-ልማትን በማስፋፋት የገጠር መሠረተ-ልማትን ቀልጣፋ የማድረግ እና የወደፊት ከተሞችን ቀድሞ የመግራት ጣምራ ግቦችን ማሳካት ይቻላል።

## 23.2. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

1. የመሰረተ ልማት አቅርቦት የተቀናጀ፣ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ፣ ተደራሽና ወጪ ቆጣቢ አለመሆንና የአስተዳደር ስርዓቱን በሚጠበቀው ደረጃ አጠናክሮ አለማስቀጠል፣ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት አለመጠናቀቅ፣ ግንባታ ዘርፍ የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ዉስንነት መኖር፣ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት አለመስፋፋት፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጂስቲክስ አገልግሎት አለመዘርጋቱ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ የአሽከርካሪና የተሽከርካሪ ብቃት ዝቅተኛ መሆን፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የተመረጡ ዋና ዋና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ናቸው፡፡
2. የመጠጥ ዉሃ ሽፋን በሚጠበቀው ደረጃ አለማደግ፣ የዉሃ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ ከፍተኛ መሆን፣ የዉሃ ብክነት በሚጠበቀው ደረጃ አለመቀነስ፣ አዳዲስ ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በበቂ ሁኔታ ማምረት እና ማሰራጨት አለመቻል፣ የግሉ ዘርፍ በኃይል ማመንጨትና በኃይል ማስተላለፍ ላይ መዋዕለ ንዋዩን እንዲያፈስ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩ እንዲሁም የመስኖ መሰረተ ልማት አለመስፋፋት፣ በቆላማ አካባቢዎች ሁሉን አቀፍ ልማት አለመስፋፋት፣ የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የአገልግሎት ዘርፎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ማዘመንና መደገፍ የሚችል የቴክኖሎጅ አቅም አለመኖር እንዲሁም የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ ዝቀተኛ መሆን የሚሉት በዘርፉ የተለዩ ዋና ዋና ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 23.3. የትኩረት መስኮች

3. የመሠረተ ልማት ዘርፍ የትኩረት መስኮች የሚከተሉት ናቸው፤
   - የመሰረተ ልማት ጥራት፣ ፍትሃዊነት፣ ተደራሽነትና ዘላቂነት
   - የመሰረተ ልማት ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት
   - አማራጭ የኢነርጅ አቅርቦት
   - የመሰተረ ልማት የቴክኖሎጂ አቅርቦት
   - የህብረተሰብና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

## 23.4. የትኩረት አቅጣጫዎች

4. የመሠረተ ልማት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና ጥራት ማረጋገጥ፣ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን መሳደግ፣ የግል ባለሃብቱንና የህብረተሰቡን በዘርፉ ላይ ያለውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የፋይናንስ አቅምን ማሳደግ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር መዘርጋት፣ ችግር ፈቺ የሆነ የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፣ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች የአየር ንብረት ለውጥን ግምት ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም የአካባቢ አየር ንብረትን በዘላቂነት ለመጠበቅ ታዳሽ ኢነርጂዎችን በስፋት መጠቀም ተግባራትን በትኩረት መስራት የሚሉት ናቸው።

5. የልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ የመስኖ መሰረተ ልማት አቅርቦትን ማረጋገጥ፣ የመንግስት ወጪ ሊቀንሱና ሊቆጥቡ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ጥናት፣ ምርምርና ስልጠናን የሚያስተባብርና የሚመራ ጠንካራ ክልላዊ ተቋም ማቋቋም፣ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣ ምቹ የኢኖቬሽን ስነ-ምህዳር ሽፋንን ማሳደግ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የቴክኖሎጅ መሰረተ ልማቶችን መዘርጋት፣ የቴክኖሎጅ ማበልጸግ፣ ማላመድ እና ማሸጋገር የመሰረተ ልማት ዘርፉ ሰፊ ቀጣይነት ያለው፣ ምርታማ የሆነ ፍትሃዊ ገቢ የሚፈጥር፣ የስራ ዕድል እንዲፈጥር ማድረግ እንዲሁም የዘርፉን የመፈፀምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተለይተዋል፡፡

## 23.5. ዓላማ እና ግቦች

### ዓላማ

6. የመሠረተ ልማቱን የተቀናጀ፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ በማድረግ አገልግሎቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ አስተማማኝና ጥራት ያለው እንዲሆን ማድረግ፤

### ዋና ዋና ግቦች

7. የከተሞችን የፋይናንስ አስተዳደር እና የሃብት አጠቃቀም በማሳደግ በ2022 ለመሰረተ-ልማት አቅርቦትና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ቢያንስ 70% በራሳቸው አቅም እንዲሸፍኑ ማድረግ፣ በክልሉ ከተሞች የመንገድ መሰረተ ልማት በ2016 ካለበት 18,535 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 29,850 ኪ.ሜ እንዲደርስ ማድረግ፣ በከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሰረተ ልማት ዝርጋታ በ2016 ከነበረበት 6,731.57 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 10,841 ኪ.ሜ ማሳደግ፣ የመንገድ መብራት አቅርቦት መሰረተ ልማት በ2016 ከነበረበት 4,577.1 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 7,371 ኪ.ሜ ማድረስ፣ የገበያ ማዕከላት ግንባታ በቁጥር በ2016 ከነበረበት 132 በ2022 ወደ 213 ለማድረስ እንዲሁም የመስሪያና መሸጫ ሼድ ግንባታ በቁጥር በ2016 ከነበረበት 20,324 ወደ 32,732 ማድረስ እንዲሁም በሁሉም ከተማ አስተዳደሮች የእሳትና ድንገተኛ አደጋ አገልግሎት እና ዘመናዊ የቄራ አገልግሎት ሽፋን 100 በመቶ እንዲደርስ የማድረግ ግቦች በዕቅድ ዘመኑ ተይዘዋል፡፡

8. ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ጋር በተያያዘ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን 2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 252 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 312 ማሳደግ፣ የደረቅ ጭነት ወደቦችንም 2015 ካለበት 3 በ 2022 ወደ 7 የማሳደግ፣ የአትክትና ፍራፍሬ እና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል ቀዝቃዛ መጋዘኖች ከ2 ወደ 8 የማሳደግ፣ ደረጃውን የጠበቀ የወጭና ገቢ እቃዎች ማቆያ መጋዘኖች አሁን ካለበት ከ0 ወደ 24 ማሳደግ እንዲሁም የአየር ትራንስፖርት መዳረሻዎች አሁን ካለበት 4 ወደ 8 ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር መስራት፣ ዘመናዊ የውሃ ትራንስፖርት ወደብ ግንባታ ከ0 ወደ 2 ለማሳደግ፣ የመንገድ ትራፊክ አደጋን በ10 ሽህ ተሽከርካሪ 2015 ካለበት 32% በ2022 ወደ 23% ለመቀነስ፣ በትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰውን የሰው ሞት በአማካኝ በየዓመቱ ከነበረበት 772 በ50% መቀነስ፣ ከ50 ሺህ ህዝብ በላይ ነዋሪ ባላቸው 30 ከተሞች የብዙሃን እና ሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎት የማስፋፋት፣ የገቢ እቃዎች ከደረቅ ወደብ ላይ ቆይታን ከ30 ወደ 10 ቀን የመቀነስ እንዲሁም ወጪ እቃዎች ከተመረቱበት አካባቢ መጋዘን ተጭነው ወደ ወደብ የሚደርሱበትን ጊዜ ከ30 ወደ 15 ቀን የመቀነስ  የማሳደግ ግቦች ተይዘዋል፡፡

9. የክልሉን አጠቃላይ የመንገድ ዝርጋታ በ2015 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 31,392.89 ኪ.ሜ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 51,665.06 ኪ.ሜ የማሳደግ ግብ የተቀመጠ ሲሆን የመንገድ ጥግግትን በ1000 ካሬ ኪ/ሜትር በ2015 ከነበረበት ከ 171.89 ኪ/ሜትር ወደ 282.94 ኪ/ሜትር እና በ1000 ህዝብ ከነበረበት ከ1.35 ኪ/ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 2.03 ኪ/ሜትር ለማድረስ፣ በቅርብ ከሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ ያለው አማካይ ርቀት በኪ/ሜትር በ2015 ከነበረበት ከ2.95 ኪ/ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1.77 ኪ.ሜትር ዝቅ ለማድረግ እንዲሁም በቅርብ ከሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ የሚወስደው አማካይ የእግር ጉዞ በሰዓት በ2015 ከነበረበት ከ 35.43 ደቂቃ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 21.21 ደቂቃ ዝቅ ለማድረግ ይሰራል፡፡

10. የመደበኛ መንገድ ግንባታን በ2015 ከተደረሰበት 4921.2 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 7375.20 ኪ.ሜ ለማድረስ፣ የወረዳ ገጠር መንገድ ጥገናን በ2015 ከተደረሰበት 21,902.05 ወደ 70,000 ኪ/ሜ ለማሳደግ፣ የመንገድ ተደራሽ ባልሆኑ አካባቢዎች በመቀናጀ በጀት የእግረኛ ተንጠልጣይ ድልድዮችን ግንባታ በ2015 ከተደረሰበት 21 ወደ 86 የማሳደግ፣ ለመንገድ ግንባታና ጥገና ከወረዳ ም/ቤትና ከህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚሰበሰበውን ሀብት በ2015 ከተደረሰበት ብር 2,210,343,840 በ2022 ወደ ብር 6,449,595,083 የማሳደግ፣ እስከ 2022 ድረስ በአምስት መስመሮች በፌደራል መንግስት የበጀት ድጋፍ 873 ኪ/ሜ የከፍያ የፍጥነት መንገድ እንዲገነባ የማድረግ፣ በፌደራል በጀት ድጋፍ በክልሉ እስከ 2022 በጀት ዓመት ድረስ 10 ከፍተኛ ድልድዮችን የመገንባት ስራ በግብ ተይዘው ይከናወናሉ፡፡

11. ከጠቅላላው የክልል ውስጥ ምርት ውሃ ለኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የገንዘብ መጠን በ2017 ከተደረሰበት 2.24 ቢሊየን በ2022 ወደ 4.48 ቢሊየን የማድረስ ግብ ተይዟል፡፡ የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በ2017 ከነበረበት 78.22% በዕቅድ ዘመኑ ወደ 90.05% ለማድረስ፣ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በ2017 ከተደረሰበት 78.84% በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 90.01% ለማድረስ እንዲሁም በአጠቃላይ በተሻሻለው የአቅርቦት ስታንዳርድ መሠረት ክልላዊ የመጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2017 ከተደረሰበት 78.84% በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 90.01% ለማድረስ የሚሰራ ሲሆን የብልሽት ምጣኔን በ2017 ከነበረበት 22.4% በዕቅድ ዘመኑ ወደ 6.9% ዝቅ ማድረግ፣ የሚባክነውን ውሃ መጠን በ2017 ከነበረበት 22.05% በዕቅድ ዘመኑ ወደ 15% ዝቅ ማድረግ፣ በከተሞች ባለመስመር ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ግንባታ በ2017 ከነበረበት 23% ወደ በ2022 ዓ.ም ወደ 60% ለማሳደግ ግብ የተቀመጠ ሲሆን የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃና ማጣሪያ ግንባታ ብዛት በ2017 ከነበረበት ብዛት 11 በ2022 ወደ 20 የማድረስ  ስራም ይሰራል፡፡ በ2022 ሁሉም የገጠር መንደሮች የመፀዳጃ ቤት ተጠቃሚ እንዲሆኑም ለማድረግ ግቦችም ተይዘዋል፡፡

12. በሌላ በኩል የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ስርጭት ሽፋን በ2017 ተደረሰበት 73.02 % በ2022 ወደ 100% የማሳደግ፣ የቤተሰብና የተቋማት የባዮ ጋዝ ዳይጀስተር ፕላንቶችን በመገንባት የተጠቃሚነትን ቁጥር በ2017

ከተደረሰበት 19,000 በ2022 ወደ 38,727 የማሳደግ፣ የተቋም ባዮ ጋዝ ዳይጀስተር ፕላንት ለመገንባት በቁጥር በ2017 ከተደረሰበት 5 ባዮ ጋዝ ዳይጀስተር ፕላንት በ2022 ወደ 150 የማሳደግ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ምንጮችና ቴክኖሎጆዎችን ሽፋን ለማሳደግ በገጠር መንደሮችና አነስተኛ ከተሞች የተለያዩ አማራጭ የኢነርጂ ኃይል ሽፋን በ2017 ከተደረሰበት 10.5 ሜጋ ዋት በ2022 ወደ 12.5 ሜጋ ዋት የማሳደግ እንዲሁም የሶላር ስርጭትን በ2017 በቁጥር ከተደረሰበት 532,318 በ2022 ወደ 657,318 ማሳደግ ግቦችን በከፍተኛ ትኩረት ተፈጻሚ ለማድረግ ተይዘዋል፡፡

13. የሚገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ቁጥር 2015 ከነበረበት 6,148 በ2022 ወደ 7,748 በማሳደግ የሚለማውን መሬት ከ260,269 ሄ/ር ወደ 413,419 ሄ/ር ለማድረስ የሚሰራ ሲሆን ግንባታቸው በፌደራል የተጀመሩ 22,310 ሄ/ር የሚያለሙ 7 ሜጋ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በማጠናቀቅ ወደ ልማት ማስገባት፣ ጥናትና ዲዛይናቸው በፌደራል የተጀመሩ 183,000 ሄ/ር የሚያለሙ 5 ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ከክልሉ የሚጠበቀውን ድርሻ መወጣት፣ የሚቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎችን ማህበር ቁጥር 2015 ከነበረበት 1,600 በ2022 ወደ 2,185 ማሳደግ፣ የቆላማ አካባቢዎችን ሁሉን አቀፍ ልማት በማስፋፋት የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸሙን ከ0 ወደ 10% ማሳደግ የሚሉት ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

14. በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ እና ብቁ የሰው ኃይል መገንባት፣ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን በመለየት ማልማት፣ ከሀገር ውስጥ እና ከሌሎች ዓለም አቀፍ አገራት ጋር በመቀናጀት በዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የልምድ ልውውጥ ተሞክሮ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን ሀገር በቀል እዉቀቶችን መሰብሰብ፤ ማዘመን፤ እና ለማስተላለፍ፣ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ የቴክኖሎጂ ፅንሰ ሀሳብ እና የተግባር ልምምዶችን በማካተት የዘርፉን ተጠቃሚ ለማሳደግ፣ የክልሉን የቴክኖሎጂ ፍላጎት የሚመልስ በሰው ሀይልና በቴክኖሎጂ የበለጸገ ተቋም ለመገንባት፣ አዳዲስ የስራ ፈጣሪዎችን (ስታርት አፕ) እና አጋር ተቋማትን በማስተሳሰር ዘላቂ የቴኖሎጂና የእውቀት ሽግግር ለመፍጠር፣ ክልላዊ የተደራጀ ደህንነቱ የተጠበቀ የተማከለ ዋና እና መጠባበቂያ ዳታ ማዕከላትን ለማስገንባት፣ ክልላዊ የተደራጀ የቴክኖሎጅ እና ኢኖቬሽን ፓርክ ለመገንባት እንዲሁም የቴሌኮሚኒኬሽን እና የሃይል አቅርቦት መሰረተ ልማቶች ሽፋንን ለማስፋፋት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

## 23.6. የማስፈፀሚያ ሥልቶች

15. ክልላዊ የመሠረተልማት ቅንጅት ማስተር ፕላንና ማስፈጸሚያ ስታንዳርዶች ማዘጋጀት፣ የመሠረተልማት አገልግሎቶች አቅርቦት በመሠረተልማት የቅንጅት ዲዛይን ጋይድላይን መነሻነት በተቀናጀ ፕላን እንዲመራ ማድረግ፣ የመሠረተ-ልማት ፈንድ እንዲቋቋም ማድረግ፣ የሎጂስቲክስ ማዕከላት እንዲገነቡ ማድረግ፣ የመንግስት፣ የግል ባለሃብቱን እና የአጋር አካላትን ተሳትፎ ማጠናከር፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት የመሰረተ ልማት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ፣ የመሰረተልማት አገልግሎቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ማፈላለግ፣ የፌደራል መንግስት በክልሉ መሠረተልማት ፕሮጀክቶች ላይ ያለውን ድርሻ ማሳደግ፣ የተዘረጉ የህብረተሰብ ተሳትፎ አሰራሮችን ማጠናከር፣ በአሠራር ሥራን ማሳለጥ የሚያስችሉ የቴክኖሎጅ የህግ ማዕቀፎች፣ ስታንዳርዶች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ የአሠራር ልምዶችና የመሳሰሉት ማደራጀትና እነዚህ በተሟሉበት ሁኔታ ሥራን መሥራት የሚችል በቴክኖሎጅ ዕውቀትና ክህሎት የሠለጠነና የበቃ የሰው ኃይልና ተቋም ማፍራት፣ ችግር ፈች የሆነ የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፣ እንዲሁም በዘርፉ የማሰልጠኛና የምርመራ ተቋማትን እንዲኖር ማድረግና ያሉትን ማጠናከር የሚሉት ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ሥልቶች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሃያ አራት

# ቴክኖሎጂ

### 24.1. መነሻ

## የቴክኖሎጂ ምንነት

1. **ቴክኖሎጂ የሀሳብ እና የተግባረ ዕድ (ቴክኒክ) ቅንጅት ውጤት ነው።** በመሠረታዊነት በምርት ሂደት የቴክኖሎጂ ፋይዳ ውስን ምርት የሚያስገኙ ውስን መነሻ የተፈጥሮ ቁሳዊ  አቅምን ገደብ በሌለው የሰው ልጅ ዕውቀት በማትባት ገደብ የሌለው ምርት በማምረት የሚያድጉ ፍላጎቶችን ማሟላት እና ሰብዓዊነትን ማስቀጠል ነው። የተጠረበ የድንጋይ መሣሪያ ምናልባትም የመጀመሪያው ማሽን ነው። መጥረብ በድንጋይ ማሽን ውስጥ የሰረገ ወይም የተጫነ (imbodied) ሀሳብ (idea) ወይም ዕውቀት (knowledge) ነው። ዛሬ ላይ በሃያ አንደኛው ክፍለ- ዘመን በአንድ በኩል መንኮራኩር በሚባል ግዙፍ ግዑዝ ማሽን ላይ ወደ ጠፈር የሚያደርስ፣ የእጅ መዳፍ በምታክል ትንሽ የተንቀሳቃሽ ብልጥ ስልክ ቀፎ ማሽን ላይ በሰው ሠራሽ አስተውሎት (artificial intelligence) እንደ ሰው የሚያስብ  ቻትጂ.ፒ.ቲ (ChatGPT- Chat Generative Pretrained Transformer) የተሰገ የሰው ልጅ ሃሳብ እና ዕውቀት ተጭኖባቸዋል። በዚህ የሚሊዮን ዓመታት ዘመን ውስጥ የሰው ልጅ ያደረገው አዝጋሚ ለውጥ (evolution) የቴክኖሎጂ ለውጥ ነጸብራቅ ነው።

## የቴክኖሎጂ ዕድገት

2. የቴክኖሎጂ ዕድገት የሀሳብ ዕድገት እና በውጤቱም የቁሳዊ ካፒታል (ማሽን) መሻሻል ነው። በምርት ሂደት ውስጥ ቴክኖሎጂ የማሽኖች ወይም የመሣሪያዎች፣ የግብዓቶች፣ የኃይል፣ የምርት ሥርዓት እና የሀሳብ መስተጋብራዊ ሥርዓት (system) ነው። በማሽን፣ በግብዓቶች፣ በኃይል ምንጮች፣ እና የምርት ሥርዓት መሻሻል ውስጥ የሀሳብ መሻሻሎች አሉ። የቴክኖሎጂ ዕድገት በእነዚህ አምዶች የሚደረጉ የሀሳቦች ክምችት (stock of ideas) ዕድገት ነው። በዚህ የሀሳብ መሻሻል ማሽኖች፣ ግብዓቶች፣ የኃይል ምንጮች፣ እና የኦቶሜሽን ሥርዓት ይሻሻላሉ፣ በውጤቱም የምርት እና የኑሮ መሻሻልን ያስገኛሉ።

3. በሰው ልጅ የረጅም ታሪክ እና በዘመናት በሚለኩ የአገራት የኢኮኖሚ ለውጥ ተሞክሮ እንደተስተዋለው እመርታ መፍጠር የቻሉ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ሁለገብ (general purpose) ቴክኖሎጂዎች ናቸው።
    - **እሳት፤** ሰው እስከአሁን ያልተካው ታላቁ የቴክኖሎጂ ግኝቱ እሳትን መቆጣጠር ነው። እሳት ለሰው ልጅ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል፣ ለብርሃን ምንጭነት፣ እና ለዘመናት ለፈጠራቸው በርካታ ግኝቶች መሠረታዊ የኃይል ምንጭ ነው።
    - **ቋንቋ እና ተግባቦት፤** የቋንቋ ቴክኖሎጂ በምልክት ከመግባባት በፊደል እስከተደገፈ የማህበረሰብ መቅረጫ የረቀቀ ስነ ጽሁፍ፣ ሥነ - ጥበብ፣ ፎክሎር፣ እንዲሁም የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ መግባቢያነት ያደገ ሲሆን ዋና ባህርይው ተጽዕኖው ሁለንተናዊ መሆኑ ነው።
    - **የማሽን እና የኦቶሜሽን ሥርዓት፤** የማሽን ጽንሰ - ሃሳብ በየትኛውም ዘርፍ ተተግባሪ ነው። ከመቆፈሪያ ዶማ እስከ መንኮራኩር እንዲሁም የእጅ ስልክ የተሸከሙት የቴክኖሎጂ ምጥቀት ደረጃ እና ዓላማ ቢለያይም ያው ማሽን ናቸው። ማሽንን በኦቶሜሽን የፋብሪካ ሥርዓት ምርትን በገፍ እንዲያመርት የማድረግ ሥልት ደረጃው ቢለያይም  በየትኛውም የኢንዱስትሪ ዘርፍ መተግበር ይቻላል።
    - **ኃይል፤ በ**መሠረታዊው የፊዚክስ ጽንሰ - ሃሳብ ሥራ ለመሥራት ኃይል ያስፈልጋል። የሥራ መጠን በኃይል ግብዓት መጠን ይወሰናል። ለሁሉም ዓይነት እንቅስቃሴዎች የተለያየ የኃይል ምንጭ መፍጠር ውድ እና አስቸጋሪም ነው። ሰው የፈጠራቸው የተሳኩ የኃይል ምንጮች በተለይም እንፋሎት፣ ነዳጅ እና ኤሌክትሪክ በየትኛውም መስክ ተተግባሪ አቅሞች ናቸው።
    - **ግብዓት፤** በዚህ ዘርፍ የተደረጉ የቴክኖሎጂ ለውጦች ለእያንዳንዱ ምርት በሚሆኑ ግብዓቶች ላይ ከማተኮር ይልቅ ለበርካታ ተግባራት የሚውሉ የማዕድን፣ የኬሚካል እና ሌሎች ሰው ሠራሽ ግብዓቶችን የማምረት ሥልት፣ በእያንዳንዱ የእንስሳት እና የአዝርዕት ዓይነት ግብዓት ከማተኮር ይልቅ ለሁሉም በሚጠቅም የማዳበሪያ እና የዘረ-መል ቴክኖሎጂ ላይ መሥራት፣ ለዘመናት

ከማይሻሻሉ ቋሚ ግብዓቶች ይልቅ አዳጊ እና ውስብስብ መካከለኛ ግብዓቶች (intermediate inputs) ላይ ማተኮር ለፈጣን ቴክኖሎጂ ዕድገት እና ኢኮኖሚ አቀፍ ተጽዕኖ ምክንያት ሆኗል።

- **የቢዝነስ ማኔጅመንት ሥርዓት፤** ለግል ፍጆታ የተቋቋመ የማምረቻ ተቋም በቤተሰብ ወደሚተዳደር ቢዝነስ፣ ከፍ ሲልም ዕውቀት ባላቸው ተቀጣሪ የቢዝነስ ባለሙያዎች የመምራት ዘይቤ እና የአንድን ኢኮኖሚ የማምረት አቅም ለማሳደግ የሚያስችለው የኮርፖሬት ሥርዓት በአብዛኞዎቹ የኢኮኖሚ ዘርፎች ተተግባሪ ነው።
- **ፋይናንስ አሳላጭነት ሥርዓት (financial intermediary)፤** የልማት አንዱ ትልቅ ተግዳሮት ሀሳብን ወደ ቴክኒክ በመቀየር ምርት ለማምረት የፋይናንስ ፍላጎትን በራስ ቁጠባ መወጣት አለመቻል ነው። የፋይናንስ ተቋማት የፋይናንስ አቅርቦትን ማሳለጥ እና ሥጋትን የመቀነስ ሥርዓት በየትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ለሚደረግ ቢዝነስ ተተግባሪ የሆነ ግኝት ነው።

4. ሁለገብ ቴክኖሎጂዎች የኢኮኖሚ ዕድገት እና አጠቃላይ መዋቅራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ ውስን ተመጋጋቢ አቻ ቴክኖሎጂዎች ያስፈልጓቸዋል። የሰው ልጅ የመጀመሪያው ማሽን የተጠረበ፣ የተወቀረ፣ የሾለ፣ ድንጋይ ነው። ይህ ማሽን መቁረጥ፣ መቆፈር፣ እና መፍጨት ይችላል። የኃይል ምንጩ የሰው ጉልበት ነው። በመቁረጥ፣ በማሾል፣ በመውቀር፣ በመቆፈር ጥበቦች ሰው ማምረት፣ ምግብ ማሰናዳት፣ መጠለያ መሥራት፣ የመከላከያ አቅም መገንባት ችሏል።

5. የዘማናት የቴክኖሎጂ ዕድገት እንደሚያሳየው ለዛሬው በዓይነት የበዛ ረቂቅ ቴክኖሎጂ መሠረት የሆነው፣ ቴክኖሎጂዎች በጥቂት ሁለገብ እና ተመጋጋቢ አቅጣጫዎች መሻሻላቸው ነው። በተለይም በዘመን ሂደት
   1. ማሽን ከተጠረበ እና ከሾለ ድንጋይ በሰው ጉልበት ወደሚዘወሩ አነስተኛ የእንጨት እና የብረት የሥራ ማቃለያዎች (ዶማ፣ መጥረቢያ፣ ማረሻ፣ ቢላዋ፣ ጦር፣ ጎራዴ)፣ በመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅትም ከብረት እና የአረብ ብረት ወደተሠሩ ኢንጂኖች ተሻሽሏል፤
   2. የማሽኖቹ የኃይል ምንጭ ከሰው ጉልበት ወደ እንስሳት ጉልበት፣ የእንፋሎት ኃይል፣ የኤሌክትሪክ እና የነዳጅ ኃይል አድጓል፤
   3. ግብዓቶቹ ከእንስሳት እና የሰብል ውጤቶች ወደ ማዕድናት፣ በማዕድናት ረገድም ከብረታ ብረት ወደ ከፊል ኤሌክትሪክ አስተላላፊ፣ እና ሰው ሠራሽ ፔትሮ ኬሚካሎች ተሻሽለዋል፤
   4. የአመራረት ሥልቱ የእጅን ማሽኖችን የማቃናት፣ የመጠምዘዝ፣ የማጠፍ፣ የመዘርጋት፣ የማውረድ፣ የማውጣት እና የማሽከርከር ሚና በኦቶሜሽን ሥርዓት በመተካት  በአንዴ ብዙ ማምረት የሚያስችል የፋብሪካ እና የኦቶሚሽን ሥርዓት ማስፈን ወደ መቻል፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ማሽኖችን የሰውን ልጅ አስተውሎት (intelligence) መተካት በሚያስችል ደረጃ አሻሽሏል።
   5. የቢዝነስ አስተዳደር እና ፋይናንስ ሥርዓት የቴክኖሎጂ ሀሳብ እና ዕውቀት ያላቸው ግለሰቦችን የፋይናንስ ፍላጎት ገዳቢ ከሆነው በራስ አቅም የሚጠራቀም ቁጠባ ወደ ባንክ ብድር አሳድጎታል።

6. የቴክኖሎጂ ዓይነቶች ከነጠላ ወደ ብዙ አቅጣጫዎች ባደጉ ቁጥር የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ እና ብልጽግና እየተሻሻሉ መጥተዋል። በዘመነ ሰው ሠራሽ አስተውሎት ማሽን በሥራ መስክ ሰውን ሲተካ ሥራ አጥነትን ይፈጥራል ወይስ የሰው ልጅ ጉልበት እና አስጨናቂ የአዕምሮ ሥራዎች ከመሥራት ወደ የማያደክሙ የአገልግሎት ዘርፎች እንዲሰማራ ተጨማሪ ዕድል ይፈጥራል የሚሉት ጥያቄዎች ወደፊት የሚታዩ ናቸው።

7. በመጀመሪያው የእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት የማሽን፣ የኃይል፣ የግብዓት፣ እና በአጠቃላይ የኦቶሚሽን ሥርዓት በጥልቀት የተተገበረው በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪው ቢሆንም ከስተቱን የኢንዱስትሪ አብዮት የሚያደርገው ፈጠራዎቹ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪው ያመጡት ለውጥ ሳይሆን ማሽንን፣ ኃይልን፣ እና ግብዓትን በማዘመን በኦቶሚሽን የፋብሪካ ሥርዓት የሰውን ጉልበት ተክቶ በገፍ የማምረት ቴክኖሎጂ በሌሎችም ዘርፎች ተተግባሪ ስለነበረ ነው። በዚያን ዘመን የለውጥ መሠረት የሆኑት ጥቂት ግን ለበርካታ ዘርፎች መዘመን ምክንያት የሆኑ ግኝቶች መካከል ግንባር ቀደሞቹ
   1. የብረት ማቅለጫ እና የብረታ ብረት ሥራ
   2. የእንፋሎት ኢንጂን
   3. የጥጥ መፍተያ ማሽን
   4. የሸክላ ወይም የሴራሚክስ ሥራ
   5. ለኬሚካል ኢንዱስትሪ መሠረት የጣለው የሰው ሠራሽ ቀለም ናቸው።

8. በተመሳሳይ በሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት በአገረ አሜሪካ ትኩረት ተሰጥቷቸው የበለጸጉ እና ሌላውን ዘርፍ ያነቃነቁ የቴክኖሎጂ ዘርፎች
   1. የአረብ ብረት (ስቲል) እና ማሽን
   2. የባቡር ትራንስፖርት
   3. ነዳጅ
   4. ኬሚካል እና
   5. የባንክ አገልግሎት ናቸው።

9. በሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት ኤሌክትሪክሲቲ እና ኤሌክትሮማግኔቲዝም በሣይንሱ ዓለም በአውሮፓ በግንባር ቀደምትነት በቮልታ፣ አምፒር እና ፋራዳይ ምርምር እውን መሆን የኤሌክትሪክ ጀነሬተር እና የኤሌክተሪክ ሞተር እንዲፈለሰፉ በር ከፈተ። በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ የዘመናችን የዕለት ተዕለት ተግባራት እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚታገዙ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣ ዘመናዊ ሕክምና፣ እና የመከላከያ አቅም መሠረት የኤሌክትሪክ መፈጠር፣ የጀነሬተሮች እና የኤሌክትሪክ ሞተሮች መፈልሰፍ ነው።

10. የዘመናችን የቴክኖሎጂ አብዮት የዲጂታል ቴክኖሎጂ ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን በ20ኛው ክፍለ-ዘመን የነበሩ ጅማሮዎችን በማበልጸግ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ማሽኖችን የሰውን ልጅ አስተውሎት (intelligence) መተካት በሚያስችል ደረጃ በማሻሻል ላይ ይገኛል። ይህ የዘማናችን የቴክኖሎጂ ጥግ ሰው ሠራሽ አስተውሎት (artificial intelligence - AI) ሲሆን ቴክኖሎጂው የሰውን ጉልበት መተካት ብቻ ሳይሆን የሰውን ልጅን የመማር (learning)፣ በምክንያት የመተንተን (reasoning)፣ ችግሮችን የመፍታት፣ በእይታ ቁሳዊ ነገሮችን የመለየት እና የመተርጎም (perception)፣ የመበየን እና ቋንቋን የመጠቀም ወይም በቋንቋ የመግባባት ልዩ አዕምሮአዊ ችሎታዎችን ተክቶ ማከናወን የሚያስችል ሥርዓት ነው። ይህ ቴክኖሎጂ በአንድ በኩል ኦፐንኤ.አይ. (OpenAI) እና ማይክሮሶፍት (Microsoft) በሌላ በኩል ጉግል (Google)፣ በቅርቡ የተዋወቀው የዲፕሲክ (DeepSeek) አውዶች ሕዋዊ እና አሊባባ በተሰኙ ሥርዓት-አውዶች የሚካሄድ ሲሆን በሦስት ግቦች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል፤
    1. ብርቱ ሰው ሠራሽ አስተውሎት (Strong AI ወይም Artificial General Intelligence – AGI)
    2. ተግባረ- ሰው ሠራሽ አስተውሎት (Applied AI)
    3. ምስለ - እዕምሮ (Cognitive Simulation)

11. የብርቱ ሰው ሠራሽ አስተውሎት (ጠንካራ ኤአይ) ግብ ከሰው ባላተናነሰ ሁኔታ የሚያስቡ ወይም ከሰው ልጅ ጋር የሚፎካከሩ ማሽኖችን መሥራት ነው። ይህ ግብ በተለይ የሰውን ልጅ ህልውና በሚያሰጋ መልኩ በጦርነት ተግባር ላይ ሊውል ስለሚችል አወዛጋቢ የቴክኖሎጂ ግንባር ቢሆንም ከመልካም ግኝቶቹ የተሳካለት ከሰው ልጅ ጋር በቋንቋ መግባበት የሚያስችለው ሥርዓት በተለይም የትልቅ ቋንቋ ሞደል (Large Language Model) ነው። በ2022 የተለቀቀው የቻትጂፒቲ፣ በ2023 የተለቀቀው 4ኛው ትውልድ ቻትጂፒቲ (ChatGPT_4) ትልቅ ስኬቶች ናቸው። የሰውን ማንነት በፊቱ የሚለዩ ሶፍትዌር፣ ተጠቃሚዎች በኢንተርኔት የሚፈልጉትን ጉዳይ የሚገምቱ እና ቀድመው ሀሳብ የሚያቀርቡ መተግሪዎች፣ ደንበኞች ለመግዛት የሚፈልጓቸውን እና የሚጇቸውን ምርት እና አገልግሎቶች ለይተው የሚያስተዋውቁ የኢንተርኔት መተግበሪያ ሥርዓቶች፣ እንዲሁም የአፕል ሲሪ (Apple's Siri) እና የጉግል መፈለጊያን የመሳሰሉ የተፈጥሮ ቋንቋ ማቀነባበሪያዎች የእነዚህ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው።

12. የሰው ሠራሽ አስተውሎት ምናልባትም የሰው ልጅ በዘመኑ ያሳካው ትልቁ የቴክኖሎጂ ግኝት ነው። በአለፉት 10 ሺህ ዓመታት የሰው ልጅ እሳት መቆጣጠርን ወይም ማልማትን ያስከነዳ ግኝት ኖሮት አያውቅም። የዘርፉ አልሚዎች ሰው ሠራሽ አስተውሎት ከእሳት እና ከኮረንቲ የበለጠ የሰው ልጅ የፈጠረው ታላቁ ግኝት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ይህን አመለካከት በሚደግፍ መልኩ በ2024 ጉግል በጥናት ውጤት ደረጃ ያስተዋወቀው በኳንተም ስሌት ላይ የተመሠረተው አዲሱ የኮምፒውተር ችፕ (computer chip) በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ፈጣን የሚባለው ኮምፒውተር አስልቶ ለመጨረስ አሥር ሴፕቲሊዮን (septillion) ወይም $10 \times 10^{24}$ ዓመታት የሚፈጅበትን ተግባረ - ሂሳብ በ5 ደቂቃ ውስጥ ማጠናቀቅ የሚችል ነው። ይህ የስሌት አቅም ሳይንስ በተለይም ፊዚክስ የደረሰበትን የዘመኑ የመጨረሻው ዕውቀት ማለትም የደቃቅ ቁስአካል ተፈጥሮ (ፓርቲክል ፊዚክስ) ላይ በመመሥረት ዕውን የሆነ የቴክኖሎጂ ግኝት ነው። ይህ ዊሎው (Willow) የተሰኘ የኮምፒውተር ችፕ የቀጣይ ትውልድ ኮምፒውተሮች የኳንተም ኮምፒውተሮች እንደሚሆኑ አመላክቷል።

## የቴክኖሎጂ ፋይዳ

13. **ቴክኖሎጂ የአሻጋሪ ኢኮኖሚ ዕድገት እና ልማት ምንጭ ነው።** በንድፈ ሃሳብ ደረጃ፣ በነባር ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ ቁሳዊ ካፒታሎችን ማስፋፋት በመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚ ዕድገትን ያረጋግጣል። ይህ የሚሳካው ነባር ቴክኖሎጂን ለሠራተኛ ኃይል ለምርት በቂ በሆነ ደረጃ በማስታጠቅ እና በማዳረስ ሂደት ነው። ካፒታል በሰው ኃይል ዕድገት ምጣኔ ልክ እኩል በሚያድግበት የመመጣጠን ደረጃ ወቅት (steady state) ገቢን ከሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔ በላይ ማሳደግ የሚቻለው በማይነጥፍ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው።

14. በአማራ ብሔራዊ ክልል ድህነትን ትርጉም የለሽ ማድረግ የሚያስችል ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ሲታቀድ ለመካከለኛ ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ የሚሆነውን በመጠን እና በጥራት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የካፒታል አቅም ከማሳደግ ጎን ለጎን ለማይነጥፍ የቴክኖሎጂ ዕድገት መሠረት የሚጣል መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው። ኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች በምርት ሂደት የሰው ኃይል የታጠቃቸው የካፒታል እና የቴክኖሎጂ ጥምር አቅሞች ናቸው። በመካከለኛ ጊዜ በዝቅተኛ ምጣኔ ላይ የሚገኘውን የካፒታል መጠን በፍጥነት በመስፋፋት እና የካፒታል - የሰው ኃይል ጥምርታን በተከታታይ ከፍ በማድረግ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ይቻላል። ካፒታል እና የሰው ኃይል በእኩል ምጣኔ ማደግ በሚጀምሩበት የረጅም ጊዜ አውድ ውስጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከሕዝብ ዕድገት ምጣኔ በላይ ማሳደግ ስለሚያዳግት የነፍስ ወከፍ ገቢን ማሳደግ፣ የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ እና ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ አይቻልም። ካፒታል በሰው ኃይል ዕድገት ምጣኔ ልክ እኩል በሚያድግበት የመመጣጠን ደረጃ ወቅት ገቢን ከሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔ በላይ ማሳደግ የሚቻለው በማይነጥፍ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው።

15. **ቴክኖሎጂ ፈጣን እና የማይቀለበስ የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን ማረጋገጥ የሚችለው ከመዋቅራዊ ግቦች ጋር ሲጣጣም ነው።** በሜካናይዜሽን፣ በኃይል፣ በግብዓት፣ እና በኦቶሜሽን ቅንጅት በሚገለጽ የምርት ሥርዓት ውስጥ በእነዚህ አምዶች የሚደረጉ የሀሳብ ለውጦች ከአንዱ ይልቅ በሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ በተሻለ ፍጥነት እና በማያባራ ሂደት የቴክኖሎጂ ለውጥ፣ በሂደቱም የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት ያስገኛሉ። እነዚህ የፈጣን ዕድገት ለውጥ ምንጭ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ወይም ንዑስ ዘርፎች ሁለት ዋና ዋና ባሕርያት ውስብስብ እና በየጊዜው የሚሻሻሉ መካከለኛ ግብዓቶች የሚጠቀሙ መሆናቸው፣ እና በእነዚህ ዘርፎች የሚፈጠሩ አቅሞች ለሌሎች ዘርፎች እና ንዑስ ዘርፎች መነቃቃት አጋዥ መሆናቸው ነው። እስከ አሁን ድረስ ባለው የቴክኖሎጂ እና የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ የዚህ ዓይነት ገዢ እና ንቅናቄ ፈጣሪ ባሕርይ ያላቸው ዘርፎች ውስን የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ - ዘርፎች ናቸው። የቴክኖሎጂ ስፋት በኢኮኖሚ ስፋት ልክ የሚወሰን በመሆኑ ከሰፊው የዓለም የቴክኖሎጂ ጣቃ ሥልታዊ በሆነ መንገድ መጥኖ የሚደረግ የቴክኖሎጂ ዕድገት ግብ በእነዚህ አንቀሳቃሽ ወይም ለጥልቅ መዋቅራዊ ለውጥ ምንጭ በሆኑ ንዑስ ዘርፎች ላይ መሆን ይገባዋል።

16. ከዚህ አንጻር የአማራ ብሔራዊ ክልል የልማት ዕቅድ እሳቤ በግል ዘርፍም ሆነ በመንግሥት በመዋዕለ - ንዋይ ስምሪት፣ በመሠረተ - ልማት አቅርቦት እና ዝራጋታ፣ በማበረታቻ አሰጣጥ፣ በሰው ኃይል ስልጠና፣ እና በሥራ ፈጠራ የትኩረት ትኩረት የሚሰጣቸው ለጥልቅ መዋቅራዊ ለውጥ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ዘርፎች ሲሆን ዋና መስፈርቱ ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚኖራቸው ተግባራዊ ሚና ነው። የፍብረካ ምሕንድስና እና የዲጂታል ቴክኖሎጂ የሰው ኃይል ስልጠና የትኩረት መስኮች ሲደረጉም ዋና ግባቸው የተመረጡ ስትራቴጂካዊ ዘርፎችን ለማዘመን ነው።

17. **የቴክኖሎጂ ዕድገት በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢኮኖሚ እና የስልጣኔ ተስተካካይነት ማረጋገጫ ነው።** በዓለም አቀፍ ደረጃ በነፍስ ወከፍ ገቢ መለኪያ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገራት በምትመደበው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የአማራ ብሔራዊ ክልል ገቢ በ25 ዓመታት ከከፍተኛ ገቢ አገራት ተስተካካይ የማድረግ ትልም የሚሳካው በፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው። በዓለም ላይ በአገራት መካካል በገቢ አቅም የሚገለጽ ከፍተኛ ልዩነት ይስተዋላል። ይህ የገቢ ልዩነት በሌሎች የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ፣ እና የፖለቲካ ፈርጆች ይንጸባረቃል። የሁሉም ልዩነቶች መሠረት የአቅሞች ልዩነት ሲሆን ገዢው የልዩነት ምንጭ የቴክኖሎጂ ልዩነት ነው። የኢኮኖሚ እና አጠቃላይ የሥልጣኔ ተስተካካይነት የሚረጋገጠው በፈጣን የቴክኖሎጂ ለውጥ እውን በሚሆን የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት ነው። ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት በዘመናዊ ግብርና ከሌላው ዓለም የተሻለ ገቢ የነበራቸው ቻይና እና ምዕራብ አውሮፓ ለተሻለ ገቢያቸው ምንጩ የተሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ነው። በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን እንግሊዝ ከገቢ ባሻገር በሁለንተናዊ አቅም ዓለምን የመራችው በቴክኖሎጂ እውቀት የኢንዱስትሪ አብዮት ስላሳካች ነው። ከፈረንሳይ እስከ ጀርመን ያሉ የአውሮፓ አገራት እና ጃፓን የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን ከእንግሊዝ ጋር የረጋገጡት በእንግሊዝ ቴክኖሎጂ ላይ ተመሥርተው ባስፋፉት የቴክኖሎጂ

ማላመድ እና ማሻሻል ንቅናቄ ነው። አሜሪካ ከተስተካካይነት ባለፈ የዓለም ልዕለ - ኃይልነት ደረጃን የተቆናጠጠችው ቴክኖሎጂን በምርምር እና ልማት በመደገፍ የተስተካካይነት መዛሪያ ስላደረገች ነው። በአሁኑ ወቅት የዓለማችን የአገራት የኢኮኖሚ እና የኃያልነት ፉክክር በዋናነት በአሜሪካ እና በቻይና የሚካሄድ ሲሆን ዋና የመፎካከሪያው ሻሙላ ቴክኖሎጂ በተለይም የዲጂታል ቴክኖሎጂ ነው።

18. **ቴክኖሎጂ የሰው ልጅ በአዝጋሚ ለውጥ በሚለካ የረጅም ዘመን ታሪኩ እንደ ዝርያ የመጥፋት ስጋቶችን ጨምሮ የገጠሙትን ችግሮች በመፍታት ለዛሬው ሰብዓዊ ልዕልና (humanity) የበቃበት መሣሪያውም፣ ከደመ-ነፍስ ዝውተራ የላቀ ተግባሩ ማሳያ እና ሰው የመሆን ማንነቱም ነው።** የሰው ልጅ በደረሰበት የዕውቀት አድማስ ልክ የሚገጥሙት ችግሮች እንደ ዝርያ በዓለም ላይ ከመጥፋት ስጋት እስከ መራብ፣ መታረዝ፣ መታመም እና ውስን ዕድሜ ይደርሳሉ። ሰው ከ1.4 ሚሊዮን ዓመታት በፊት እሳትን የመቆጣጠር ጥበብን የመሰለ የመከላከያ አቅም በመፍጠር በሌሎች ኃያል እንስሳት ጥቃት ከመጥፋት ድኗል። እሳትን መቆጣጠር ለበርካታ የሰው ልጅ ፍላጎቶች መፍትሄ መሆን ስለቻለ እስከ አሁን የእሳት አጠቃቀም ግኝትን ያስከነዳ የሰው ልጅ አብዮት የለም። የሰው ልጅ ፍላጎቶች እንደ የዕደገት ደረጃው በውስን የተፈጥሮ ሀብት እና ቁሳዊ አቅም እንዲሁም በየዘመናቱ ከሚፈጠሩት ውስጣዊ እና ውጫዊ አዳዲስ ተግዳሮቶች ፊት የሚሰፉ፣ የሚያድጉ፣ የሚራቀቁ፣ የሚወሳሰቡ እና የሚገዝፉ ናቸው። የማልተስ ንድፈ-ሃሳብ እንደሚያስተምረው እነዚህን ፍላጎቶች ማሟላት ሲያቅት የሰው ልጅ በቸነፈር፣ በጦርነት፣ እና በወረርሽኝ (positive checks) ፍላጎት እና አቅርቦት እስከሚመጣጠን ድረስ ሲበልግ በዝተው ሲጠርር እንደሚያልቁት አጋዘኖች ሁሉ መቋቋም ወደቻሉ ጥቂቶች ደረጃ ይወርዳል። የሰው ልጅ ከማልተስ ሚርት እና ከሳላዎች እና አጋዘኖች እጣ ያመለጠው ውስኑን ቁሳዊ የተፈጥሮ ካፒታል በማይነጥፍ ዕውቀት በፈጠረው የቴክኖሎጂ ስለት እና ባትረፈረፈው ምርት ነው። ሰው ለመግባቢያ ቋንቋን የፈጠረው፣ ቋንቋውንም በፊደል እና በስነ - ጽሁፍ ያዳበረው ሀሳብን ወደ ወደ ተግባር ቀይሮ ነው። ይህ ሀሳብን ወይም ዕውቀትን ወደ ተግባር የመቀየር የሰው ልጅ ሥልት በአሥራ 17ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓውያኖቹ ቴክኖሎጂ ብለው ሰይመውታል። ቴክኖሎጂ በግሪክ ቋንቋ የቴክኒክ ዕውቀት ወይም ጥናት ማለት ነው። ቴክኖሎጂ በሳይንሳዊ ዕውቀት መመሪት ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ገዢ ትርጉሙ ሰው የሚገጥሙትን ችግሮች እና ተግዳሮቶች ለመፍታት ሳይንሳዊ እውቀት እና ጥበብን ወደ ተግባር የሚቀይርበት ዘዴ ነው።

19. በሃያ አንደኛው ክፍለ - ዘመን እንደ አገር የኢትዮጵያ እንደ ክልል የአማራ ብሔራዊ ክልል ችግር ድህነት እና ኋላቀርነት ነው። እስከ ሰባተኛው ክፍለ-ዘመን የታሪክ መታጠፊያ ድረስ ኢትዮጵያ በስልጣኔ ትቀድማቸው የነበሩ ወይም ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የነበሩ አገሮች በስልጣኔ ርቀው የመገኘታቸው ምስጢር በእነዚህ ማሕበረሰቦች ሳይንስ-መር ቴክኖሎጂ መመንደጉ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ከመቸንከር በታች በግጭት አዙሪት ማሽቆልቆሉ ነው። የክልሉ ድህነት እና ኋላቀርነት ትብታብ የሚፈታው በፈጣን እና የረጅም ጊዜ አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ነው። የፈጣን እና አሻጋሪ ዕድገት ምንጭ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው። በመሆኑም፣ የኢኮኖሚ ተስተካካይነት እና ተወዳዳሪነት ግብ የሚረጋገጠው በማያሻማ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት እና ተወዳዳሪነት ግብ ነው።

## የቴክኖሎጂ ምንጭ

## የዘመናት የሰው ልጅ እና የማሕበረሰቦች ጥረት

20. የየዘመናቱ የቴክኖሎጂ ደረጃዎች በቀዳሚዎቹ በርካታ ዘመናት የተከማቹ የሳይንስ እውቀት እና የቴክኖሎጂ አቅም ውጤቶች ናቸው። እሳትን ለላቀ ጥቅም ማዋል የ1.4 ሚሊዮን ዓመታት ዕድሜ አለው፤ ፈጣሪውም ሆሞ አውስትራሎፒቲከስ (Homo australopithecus) ነው። የእሳት ጥቅም አንዱ ፈርጅ በሆነው የብርሃን ዕድገት አቅጣጫ ማገዶ ጨራሽ የሆነውን ከእሳት የሚገኝ ብርሃን በፓሊዮሊቲክ ሕዝቦች (Paleolithic people) የእንስሳት ሞራን መጠቀም የሚችል የድንጋይ ኩራዝ በመሥራት የኃይል ብክነትን በ22 እጥፍ የቀነሱት ከ42 ሺህ እስከ 17 ሺህ ዓመታት በፊት ነው። ባቢሎኒያውያን የዚህን ዘዴ የኃይል ምንጭ በሰሊጥ ዘይት በመተካት ብክነትን በግማሽ የቀነሱት ወይም ቅልጥፍናን በእጥፍ ያሳደጉት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1750 ነው። ፍልስፍና በናኘበት የግሪክ ስልጣኔ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ348 ዓመት በፊት ፕሌቶ ሃሳቦቹን ለመጻፍ የተጠቀመበት የሻማ መብራት ከሰሊጥ ዘይት ይልቅ በእጥፍ ኃይል ቆጣቢ ነበር። ከዚያ በኋላ የሻማን ብርሃን የመስጠት አቅም በእጥፍ በጨመረው እና የዓሳ ነባሪን ቁጥር ባመናመነው የዓሣ ነባሪ ዘይት ለመተካት 1800 ዓመታት ፈጅቷል። እኤአ በ1859 በአሜሪካ የመጀመሪያው አዋጭ ድፍድፍ ነዳጅ መገኘትን ተከትሎ ከቀዳሚው 20 በመቶ የብርሃን ድምቀት መስጠት የቻለው እና የዓሳ ነባሪን ዘር ከመጥፋት የታደገው የናፍጣ

ኩራዝ ጥቅም ላይ ውሏል። እኤአ በ1879 ቶማስ ኤዲሰን የፈጠረው የኤሌክትሪክ አምፑል የናፍጣ ኩራዝን 16 እጥፍ የብርሃን ድምቀት ይሰጣል። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው የፍሎረሰንት መብራት የኤዲሰንን አምፑል የብርሃን ድምቀት 26 እጥፍ ይሆናል። በረጅሙ ዘመን እሳቤ የፍሎረሰንት መብራት የብርሃን ድምቀት ወይራ አንድደን የምናገኘውን የብርሃን ድምቀት 143 ሺህ እጥፍ ይሆናል።

## ሣይንስ

21. ቴክኖሎጂ በሰው ልጅ የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ሁሉ ለችግር መፍቻነት ከመዋሉ አንጻር ቴክኖሎጂ መደበኛ ሳይንስን ይቀድማል፤ የሰው ልጅም በተፈጥሮው ቴክኖሎጂስት ነው። ከቅርብ ዘመን ታሪክ አኳያ የ18ኛው ክፍለ-ዘመን የእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት በመሠረቱ የቴክኖሎጂ አብዮት ነው። ይህ የቴክኖሎጂ አብዮት በእንግሊዝ በተቀናጀ ሁኔታ በሚካሄድ መደበኛ ሳይንሳዊ ጥናት ባይመራም ከእንግሊዝ ቀድመው የነበሩ የቻይና፣ የመካከለኛው ምሥራቅ እና አካባቢው፣ እና በኋላም የጣሊያን ዓይነቶቹ የአውሮፓ አገራት የዘመናት የሳይንሳዊ ዕውቀት እና የክህሎት ክምችት (buildup) እና የዚህ ክምችት በዚያን ወቅት ለለውጥ ወሳኝ ደረጃ ላይ መድረስ (breakthrough)፣ እንዲሁም ለግለሰቦች የፈጠራ ነጻነት በመስጠት ረገድ የእንግሊዝ ለዚህ አጋጣሚ የተሻለ ዝግጁነት ላይ መገኘት ናቸው።

22. **ከሳይንቲስት እስከ መሪ የሚደርሱ ባለርዕዮች የቴክኖሎጂ አዋላጆች ናቸው።** በ1620 ፍራንሲስ ባኮን የተባለ እንግሊዛዊ ፈላስፋ ሣይንሳዊ ዕውቀት የሰው ልጅ ተፈጥሮን ከመቆጣጠር ያላነሰ ሚና እንዲኖረው የሚያድርግ መሆኑን ተንብዮ ነበር። ከዚያ ወዲህ በነበሩት ምዓት - ዓመታት የሰው ልጅ በወረርሽኝ፣ በርሃብ እና ቸነፈር እንዲሁም በድህነት ይማቅቅ ስለነበር የባኮን ርዕይ ተምኔታዊ እንደሆነ ተቆጥሮ ነበር። ላለፉት 5 ሺህ ዓመታት ከባኮን ትንበያ በኋላ ባሉት 340 ዓመታትን ያህል ሣይንሳዊ ግኝት እና ለውጥ አልተስተዋለም። በ1963 የአሜሪካው ፕሬዚደንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ አስበናቸው እና አልመናቸው የማናውቃቸው አሥር በሮች በሣይንስ ተከፍተዋል በማለት አብስረዋል። እንደ አውቶሞቢል፣ ማቀዝቀዥያ፣ ቴሌቪዥን፣ ስልክ በግለሰቦች በቀላሉ የሚገዙ ዕቃዎች መሆን ችለዋል። የሰውን ልጅ በአጋጣሚ ካልሆነ የመያልፈው የሳንባ ነቀርሳ፣ የሳንባ ምች፣ እና የተስቦ ወረርሽኝ በጸረ-ተሕዋሲያን መዲሃኒት መከላከል እና የሰውን ሕይወት መታደግ ተቻለ። አሜሪካኖች የዓለም የመጨረሻው አስፈሪ መሣሪያ የሆነውን ኒኩሊየር ታጠቁ፤ ጨረቃ ላይ መውጣት ለሰው ልጅ ቀላል ሆነ። ይህ የሆነው ሳይንሳዊ ምርምር ባዋለደው ቴክኖሎጂ ነው።

23. ሳይንሳዊ ምርምር በአውሮፓ በስፋት ከመጀመሩ በፊት እስከ መጀመሪያው የእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት ድረስ ጉልህ የቴክኖሎጂ ግኝቶች የግለሰቦች የተናጠል ፈጠራ ውጤቶች ነበሩ። በአሜሪካም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት የነበረው የቴክኖሎጂ ሞዴል በግለሰቦች ላይ የተመሠረተ ነበር። በኢንዱስትሪ አብዮት ማግስት ዩኒቨርሲቲዎች እና ሌሎች የምርምር ተቋማት ለቀዳሚዎቹ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ሳይንሳዊ ትንታኔ ከመስጠት አልፈው ቴክኖሎጂን በሀሳብ የመምራት አቅም መፍጠር ችለዋል። በዚህም ከኋላ የመጡ ሜሪካን የመሰሉ አገራት ቴክኖሎጂን በመደበኛ ትምህርት እና ሳይንሳዊ ጥናት በመደገፍ ከበፊተኞቹ የበለጠ ማፋጠን ችለዋል።

24. **በጥቂት ግለሰቦች በአጋጣሚ ይገኝ የነበረውን አዝጋሚ እና ውስን ቴክኖሎጂ ሣይንስ የተፈጥሮ ሕግጋትን በማስቀመጥ በፍጥነት፣ በስፋት እና በጥራት እንዲሳካ አስችሏል።** ቴክኖሎጂ የተደራጀ የሣይንስ ጥናትን በቀደመባቸው ዘመናት የቴክኖሎጂ ግኝቶች ብግለሰቦች የሚሳኩት በብዙ ጥረት እና ዳሰሳ በዕድል ነበር። ሣይንስ የተሳኩ የቴክኖሎጂ ግኝቶችን ከመተንተን ባለፈ ተፈጥሮ ለቴክኖሎጂ ፈጠራ አመቺ የሆነ የራሷ ሥርዓት ያላት መሆኑን ለመግለጽ ሞክሯል፤ በብዙ ደረጃም ተሳክቶለታል። በዚህም የተፈጥሮ ሣይንስ በተለይም የቁሳዊ ሣይንስ (physical science) ገዢ የተፈጥሮ ሕግጋትን ለይቷል። ቴክኖሎጂ በጥቂት ደፋር ግለሰቦች በዳሰሳ ይገኝ ከነበረበት አዝጋሚ አካሄድ ይልቅ የሣይንስ ሕግጋቱን በመከተል እና ሀሳብን ከቴክኒክ ጋር በማገናኘት ከዕለት ዕለት የሰው ልጅ ኑሮ ማቃለያ የሰውን ልጅ ሕይወት እስከሚታደጉ የተራቀቁ የሕክምና መሣሪያዎች የሚደርሱ የቴክኖሎጂ ግኝቶች በስፋት እና በፍጥነት እንዲሳኩ ማድረግ ተችሏል።

25. **የሣይንስ ዋና ትኩረት በውስን ጥረት ጠቃሚ ሥራ ማከናወን የሚያስችሉ አጎልባቾችን ወይም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማዋለድ የሚችሉ የተፈጥሮ ሥርዓቶችን ወይም ሕግጋትን መለየት ነው።** የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር ይብዛም ይነስም ሥራ (work) መሥራት አለበት። ሥራ ለመሥራት ማውጣት፣ ማውረድ፣ መሳብ፣ መግፋት አለበት። የእነዚህ የግፋ-ሳብ ጥረቶች (forces/efforts) ኃይል (energy) ወይም በሰዓት ሲለካ ጉልበት (power) ያስፈልጋቸዋል። አንድ አማካይ ጎልማሳ ከሚበላው ምግብ 10 ሜጋ ጁውል የኬሚካል

ኃይል በቀን ያስፈልገዋል። ከዚህ ኃይል ውስጥ የተወሰነውን ሥራ ይሠራበታል። የሰው ልጅ ትልቁ ችሎታው ለሌሎች እንስሳት ተወስኖ ከተሰጠው የደመነፍስ ዝውተራ ወጥቶ በጥልቀት በማሰብ ከምግብ ያገኘትን ውስን የኬሚካል ኃይል ጠቃሚ ሥራ ለመሥራት ወደሚያስችል የኃይል ዓይነት መቀየር ነው። አንድን የኃይል ዓይነት ወደ ሌላ የተሻለ ሥራ መሥራት የሚያስችል የኃይል ዓይነት መቀየሪያ አቅም በማሽኖች እና በሥልቶች የሚገለጽ ቴክኖሎጂ ነው። ከጥቅል የተፈጥሮ ሕግ በርካታ የቴክኖሎጂ አቅሞች መፍጠር የሚቻለው በሣይንሳዊ ምርምር ነው።

26. ቁሳዊ ሣይንስ በተለይም ፊዚክስ እስከ አሁን በደረሰበት ንድፈ - ሃሳብ በሕዋ (universe) ውስጥ ያሉ ማንኛውም የነገራት መስተጋብሮች የሚዳኙት በአራት ግፋሳቦች (forces) ነው። ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው የቁስአካላዊ ስበት (gravitational force) ሲሆን ይህን ሕግ በመከተል በተደነገጉ የኒውተን መሠረታዊ የተፈጥሮ ሕግጋት በአብዛኛው በዓይን በሚታዩ ከድልዲይ እስከ ግድብ፣ ከየብስ ትራንስፖረት እስከ ጠፈር ሳቴላይት እና መንኮራኩር የሚደርሱ ቴክኖሎጂዎች መሳካት ችለዋል።

27. ከ18ኛው ክፍለ-ዘመን ወዲህ የመጀመሪያውን የኢንዱስትሪ አብዮት ተከትሎ የሁለተኛው ኢንዱስትሪ አብዮት ሞተር የሆኑት የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተሳኩት ሣይንስ የኤሌክትሮማግኔጢስ ግፋሳብ (electromagnetic forces) ሕግጋትን በማግኘቱ ነው። በየቀኑ እንደ ዘበት የምናስተውላቸው በእቃዎች ንክኪ የሚፈጠሩ እሳት መሰል ብልጭታዎች ሁለት ባሕርያት እንዳሏቸው ቤንጃሚን ፍራንክሊን አሳወቀ፤ እነዚህንም ቀናሽ እና ጨማሪ ሙሊቶች (negative and positive charges) የሚሉ ስያሜዎችን ሰጣቸው። ከእሱ በ30 ዓመት ዕድሜ የሚያንሰው ቻርለስ ኩሎምብ በሁለት የኤሌክትሪክ ሙሊቶች መካከል የሚፈጠረውን የመሳሳብ ወይም የመገፋፋት መጠን መለካት የሚያስችል ቀመር ፈጠረ። ይህን ሀሳብ ካርል ጋውስ አስፋፍቶ በእቃዎች ላይ የሚገኝን የኤሌክትሪክ ሙሊቶች መጠን የሚለካ ቀመር ይፋ አደረገ። እነዚህን ሀሳቦች መሠረት በማድረግ የኤልክትሪክ ሙሊቶች ካፓሲተር በተሰኘ መሣሪያ ተጠራቅመው እና ተይዘው ሥራ መሥራት የሚያስችል የኤሌክትሪክ ኃይል (electric potential) መሆን እንደሚችሉ በሙከራ ተረጋገጠ። ካፓሲተር የፎቶግራፍ ፍላሽ፣ የመኪና የአደጋ መከላከያ (አይር ባግ) ሥጋት መለያ (ሴንሰር)፣ የሌዘር ማተሚያዎች፣ ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ እንዲሁም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውላል። በቀጣዮቹ ዓመታት የኤሌክትሪክ ኃይልን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ መውሰድ እንደሚቻል በሙከራ ተረጋገጠ።

28. **ኤሌክትሪክሲቲ ማግኔጢስን እንደሚፈጥር ሁሉ፣ ማግኔጢስም ኤሌክትሪክ መፍጠር ይችላል የምትል አንድ የፊዚክስ ንድፈ-ሃሳብ ለበርካታ የቴክኖሎጂ ትግበራዎች ውላ የሰውን ልጅ ሕይወት በእጅጉ ቀይራለች።** በ1820 ሀንስ ኦርስቴድ የተባለ ደንማርካዊ ኮረንቲ ማግኔጢስ እንደሚፈጥር ተገነዘበ። ይህን ግኝት ተከትሎ እንግሊዛዊው ማይክል ፋራዳይ ማግኔጢስ በአጸፋው ኮረንቲ መፍጠር እንደሚችል በምርምር አረጋገጠ። የዚህ የኤሌክትሮማግኔጢስ ጥምር ባሕርይ ሥርዓት መገኘት በዋናነት ጄኔሬተር፣ የኤሌክትሪክ ሞተር ወይም ዲናሞ፣ እንዲሁም ትራንስፎርመር እንዲፈጠሩ በር የከፈተ ሲሆን ከእነዚህ የሚመነጩ የኤሌክትሮኒክስ የትግበራ ውጤቶች ለቁጥር የሚያታክቱ ናቸው። በጤናው ዘርፍ የምናውቀው ኤም.አር. አይ. (Magnetic Resonance Imaging) የኤሌክትሮማግኔቲዝም የሳይንስ ግኝት ቀጥተኛ የቴክኖሎጂ ትግበራ ውጤት ነው።

29. ጀምስ ማክስዌል የተባለ ስኮትላንዳዊ የፊዚክስ ሳይንቲስት በቀዳሚዎቹ ሕግጋት ላይ ተመስርቶ ማግኔጢስን በተለያየ ፍጥነት በማንቀሳቀስ ኮረንቲን ማግኘት እንደተቻለ ሁሉ፣ የኤሌክትሪክ አውዶችን በተለዋዋጭ ፍጥነት በመቀያየር ሩቅ ርቀት መናኘት የሚችሉ የኤሌክትሮማግኔቲክ ሞገዶችን (electromagnetic waves) መፍጠር እንደሚቻል አረጋግጧል። ይህ ግኝት ሁለት ፋይዳዎችን አስገኝቷል። የመጀመሪያው ፋይዳ የራዲዮ እና የቴሌቪዥን መገናኛዎችን፣ የማይክሮዌቭ፣ የኤክስ-ሬይ እና ካት ስካን መሣሪያዎችን የመሳሰሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አስገኝቷል። ሁለተኛው ፋይዳ የምናየው ነጭ ብርሃን ራሱ የብዙ ቀለማት ስብጥር የሆነ የኤሌክትሮማግኔት ሞገድ መሆኑን፣ ከሚታየው ብርሃን የሚልቁ በሰው ልጅ ዓይን የተፈጥሮ አቅም የማይታዩ ሞገዶች እንዳሉት ማመላከቱ ነው።

30. የእነ አልበርት አነስታይን ዘመን የሆነው 20ኛው ክፍለ ዘመን ብርሃን (እና ሌሎችም ኤልክትሮማግኔቲክ ሞገዶች) የሞገድ (wave) እና የቁስ (photons) ጥምር ባህርያት ያሉት መሆኑን ያረጋገጠ እና ይህም ለኳንተም ፊሲክስ፣ ለኒኩሊየር እና የደቂቅ ቁስ ፊሲክስ (particle physics) ምርምሮች በር ከፍቷል። በዚህ ደረጃ ያሉ የተፈጥሮ ባሕርያት ጠንካራ የደቂቅ ቁስ ግፋሳቦች (strong nuclear forces) እና ልል የደቂቅ ቁስ ግፋሳቦች (weak nuclear forces) በተሰኙ መስተጋብሮች የሚጠቃለሉ ናቸው። በትግበራ ደረጃ ኳንተም ፊሲክስ የመጪዎቹ ልዕለ-ኮምፒውተሮች መሠረት ይሆናል። የደቂቅ ቁስ ቴክኖሎጂ (nano technology) በተለይ

በሕክምናው ዘርፍ እመርታ ያስገኛል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል። ከዚህ ባለፈ የዚህ የደቂቅ ቁስ ምርምር የዩኒቨርስን አፈጣጠር ለማወቅ የሚተጋ ነው። በንድፈ ሃሳቡ መሠረት ዛሬ የምናስተውላቸው ትልልቅ ከዋክብት፣ እና ዓለማት ዩኒቨርስ ሲፈጥር የተፈጠሩ ሳይሆኑ በብዙ የብርሃን ዓመታት አድገው እዚህ የደረሱ ግዑዛን ናቸው። ዩኒቨርስ ሲፈጠር የነበሩት ቁሶች ደቂቅ ቁሶች ወይም ንዑስ ቁሶች (ሰብ ፓርቲክልስ) እንደነበሩ በንድፈ ሃሳብ ያስቀምጣል። በቅርቡ ከላይ በተገለጹት እና እስከ አሁን ተፈጥሮን ይገዛሉ ተብለው ከሚታሰቡት የቁሶች ስበት (gravitational forces)፣ የኤሌክትሮማግኔቲክ ስበት (electomagenetic forces)፣ የጠንካራ ደቂቅ ቁስ ስበት (strong nuclear forces)፣ እና የልል ደቂቅ ቁስ ስበት (weak nuclear forces) አራት ግፋሳቦች የማይገለጹ የቁሶች ባሕርያት ታይተዋል። ይህ ማለት ሌላ ተጨማሪ ግፋሳብ መኖሩን ያመላክታል። ሳይንስ ይህን መለየት ከቻለ የሰው ልጅ የቴክኖሎጂ ደረጃ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ወደሚችልበት ከፍታ ያደርሰዋል ተብሎ ይጠበቃል። ሣይንስ በዘርፉ ላይ ጥናት እያደረገ ሲሆን ቴክኖሎጂም እየጠበቀ ነው። ሣይንስ ቴክኖሎጂን ይመራል። የምዕራቡ ዓለም ባሕል በጥቅሉ በተለይ ከመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ በዓይን ከሚታዩ ግዙፍ ከዋክብት ጀምሮ ከሚያጠናው ሜካኒካል ፊዚክስ በዓይን ወደማይታዩት የኤሌክትሮማግኔጢስ፣ ሲያልፍም ደቂቅ ቁሶች በሳይንስ እየተመራ ሲራቀቅ የእኛ ባሕል በዓይን የሚታዩትን የእነሱ ግኝቶች አድንቆ የማይታየውን ለመንፈሳዊ ትንታኔ ትቶታል።

*ሥርዓታት*

31. **ለአንድ አገር የቴክኖሎጂ ዕድገት በመንግሥት እና ማሕበረሰብ መናበብ የሚገለጹ ሥርዓታት ሚና አይተኬ ሲሆን ዋናው መሣሪያም የቴክኖሎጂ እና የሣይንስ ፖሊሲ ነው።** ትርጉም ያለው የቴክኖሎጂ ግስጋሴ የተካሄደው በአንደኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት በእንግሊዝ ነው። አብዛኛዎቹ የአውሮፓ አገራት ለሰማንያ ዓመታት በሃይማኖት ሰበብ በተነሳ ጦርነት ሲተራመሱ እንግሊዝ የመጨረሻዎቹን ሠላሳ ዓመታት ለሥርዓታት ማሻሻያ የጥሞና ጊዜ ወስዳ ነበር። በዚህ ወቅት በመጀመሪያ ደረጃ የግጭቱ መቆም፣ ከዚያም ሲያልፍ በእንግሊዝ የመንግሥት እና ዕምነት መለያየት (secularism)፣ የጠቅላይነት ሥርዓት ማክተም እና የጠንካራ የፓርላማ ሥርዓት መስፈን፣ ለጥበበኛ ስደተኞች መጠጊያ መሆን እና ጥበብን የሚያበረታታ ሥርዓት መስፍን፣ እንዲሁም የእጅ ባለሙያዎችን የመጨረሻ የማሕበረሰብ ደረጃ ከሚሰጠው ከፋፋይ የማሕበረሰብ አስተሳሰብ በመላቀቅ ሣይንሳዊ እውቀትን እና ቴክኖሎጂን ሕዝባዊ ማድረጉ ለእንግሊዝ የቴክኖሎጂ ግስጋሴ መሠረት ጥሏል። በወቅቱ በእንግሊዝ ዕውን የሆኑት የቴክኖሎጂ ግኝቶች የተሳኩት ካልተማረው እና ከታችኛው የማሕበረሰብ ክፍል ነበር።

32. የእንግሊዝ መንግሥት ለነጻ የሣይንሳዊ ዕውቀት እና ፈጠራ የሰጠው ከለላ የኢንዱስትሪ አብዮትን አዋልዷል። በሌሎች አውሮፓ አገራት በዘመኑ የካቶሊክ አስተምህሮት ሣይንስ እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ከጥንቆላ እና አስማት በከፋ ይወገዝ በነበረበት ዘመን የእንግሊዝ መንግሥት በሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ረገድ የግለሰብ ነጻነት በማስፈኑ እና ከሌላው አካባቢ ተሳድደው ለሚመጡ የዕደ - ጥበብ ባለሙያዎች እና ነጋዴዎች መጠጊያ በመሆኑ ፈጠራ ከጥቂት ልሂቃን ይልቅ ከብዙሃኑ ሕዝብ እንዲገኝ አድርጓል። በሌሎች የአውሮፓ አገራት በተለይም የፈረንሳይ መንግሥት የእንግሊዝ ማሽን ሠራተኞችን በከፍተኛ ደመወዝ በማስኮብለል ጭምር ቴክኖሎጂ ወደ ፈረንሳይ እንዲገባ አድርጓል። የጀርመን መንግሥት የቴክኒክ እና የቢዝነስ ማኔጅመንት ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት የቴክኖሎጂ ሽግግርን ሕዝባዊ እና ዘመናዊ ማድረግ ችሏል። የአሜሪካ መንግሥት ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ምርምር ትርጉም ባለው ደረጃ ድጋፍ ማድረግ የጀመረው በታላቁ የኢኮኖሚ ውድቀት (the Great Depression) ወቅት እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ነው። በተለይም በመጀመሪያዎቹ የጦርነት ዓመታት ድጋፉ በመከላከያ ዘርፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ከጦርነቱ በኋላ የመንግሥት ድጋፍ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ባተኮሩ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ምርምሮች ላይም ተስፋፍቷል።

33. የአሜሪካ መንግሥት ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ምርምር ትርጉም ባለው ደረጃ ድጋፍ ማድረግ የጀመረው በታላቁ የኢኮኖሚ ውድቀት (the Great Depression) ወቅት እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ነው። በተለይም በመጀመሪያዎቹ የጦርነት ዓመታት ድጋፉ በመከላከያ ዘርፍ ላይ ያተኮረ ነበር። ከጦርነቱ በኋላ የመንግሥት ድጋፍ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ባተኮሩ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ምርምሮች ላይም ተስፋፍቷል። በተለይ በጦርነቱ ወቅት የሳይንሳዊ ምርምር እና ልማት ቢሮ (Office of Scientific Research and Development) የተቋቋመ ሲሆን ግቡ
    - ሳይንቲስቶችን እና መሃንዲሶችን በጦርነቱ ጥረት ላይ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ማስተባበር፣
    - የመንግሥት - ኢንዱስትሪ - ዩኒቨርሲቲ ትብብርን መፍጠር እና ውጤታማ ማድረግ፣ እና

- ሳይንቲስቶች እና መሃንዲሶች በመንግሥት አማካሪነት ያልተገደበ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ነበር።

34. በፕሬዚደንት ትሩማን ጊዜ "ሳይንስ፤ ገደብ የለሹ የለውጥ ግንባር" (Science the Endless Frontier) በሚል መርህ ከወታደራዊ ግቦች በተጨማሪ ለሥራ ፈጠራ፣ ጤና እና የኢኮኖሚ እድገት በሚያግዝበት ደረጃ እውቅና ተሰጥቶታል፤ ለዚህም መንግሥት ለሣይንስ ማሕበራዊ ኮንትራት ወስዷል፤ በተግባር ደረጃም ብሔራዊ የጤና ኢንስቲትዩት፣ ብሔራዊ የሣይንስ ፋውንዴሽን፣ ብሔራዊ የሥነ-በረራ እና የሕዋ ምርምር አስተዳደር (National Aeronautics and Space Adminstration)፣ የብሔራዊ የሣይንስ ምርምር ቢሮ፣ የኤነርጂ ዲፓርትመንትን የመሳሰሉ ተቋማት መሥርቷል። በሮናልድ ሬገን ዘመን መንግሥት ከቀዝቃዛው ጦርነት ጋር በተያያዘ የመከላከያ ቴክኖሎጂዎች ላይ የተኮረ ሲሆን በ1980ዎቹ መጨረሻ የአባቱ ጆርጅ ቡሽ መንግሥት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ለመሠረታዊ ሲቪል ኢንዱስትሪ ትኩረት በመስጠት የከፊል ኤልክትሪክ አስተላላፊ ቴክኖሎጂ ምርምር የሚያካሂድ የትብብር ማዕቀፍ (Semiconductor research cooperation) ተመሠረተ። በክሊንተን ጊዜ ይህ ምርምር በእጅጉ ተስፋፋ። ይህም በከፍተኛ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም፣ እና በመንግሥት ጥናት እና ምርምር የተገኙ የፈጠራ መብቶችን ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠው ስምምነት በሥራ ላይ ዋለ።

35. ይህ በመንግሥት ድጋፍ እና ዩኒቨርሲቲዎች ጥናት እና ምርምር ከተገኘ በኋላ ለትግበራ ወደ የግሉ ዘርፍ የሚተላለፍ ቴክኖሎጂ ውጫዊ (exogenous) ቴክኖሎጂ በአሁኑ ዘመን የግል አምራች ተቋማት ስለተርፋቸው ሲሉ በራሳቸው ምርምር እና ልማት ማዕቀፍ እያሳደጉት ይገኛሉ። ይህም በምጣኔ ሀብት ሣይንስ አስተምህሮት ውስጥ የውስጥ ቴክኖሎጂ-መር እድገት ንድፈ ሃሳብ (endogenous growth theory) መሠረት ሆኗል። በዚህም መሠረት የቴክኖሎጂ ሞደል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ከነበረው የግለሰቦች ፈጠራ በሳይንስ ምርምር ተደግፎ ወደሚፈጠር የቀጥተኛ ቴክኖሎጂ ሞዴል (linear technological model)፣ በመጨረሻም ቴክኖሎጂን በየምርት ተቋማት እያሻሻሉ፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እያዋዋጡ፣ ከቁሳዊ ምርት ባሻገርም እንደ ሶፍትዌር የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎችን በቀጥታ እያመረቱ ወደሚመነጠቅ ቴክኖሎጂ ሞዴል ተሸጋግሯል። የቴክኖሎጂ ሞዴል በትርፍ ላይ በተመሠረቱ ተቋማት በሚመራበት በዚህ ዘመን የመንግሥት ፖሊሲ ቴክኖሎጂን በሚመሩ አገራት እና ቴክኖሎጂን ለማስተላለፍ በሚጥሩ አገራት መካከል ልዩነት አለው፤ በቴክኖሎጂ መሪ አገራት ቴክኖሎጂን የመግራት ፖሊሲ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ለማደግ ለሚታትሩ አገራት ደግሞ የመንግሥት ፖሊሲ ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሕዝቡን በተለይም ወጣቱን በሣይንሳዊ እና ቴክኒካዊ ዕውቀት ዝግጁ ማድረግ ነው።

## የዘመኑ ቴክኖሎጂ ፋይዳ እና ስጋት

36. **ቴክኖሎጂ ባለ ሁለት ስለት ጎራዴ ነው።** ሣይንስ እና ቴክኖሎጂ የሚያለማውን ያህል አጥፊም ነው፤ ብክለት እና የኒኩሊየር አውዳሚነት ትልቅ የሰብዓዊ ፍጡር ስጋቶች ናቸው። አዲሱ የሰው ሠራሽ አስተውሎት የሰውን ልጅ በሥራ መስክ ከመተካት በጦር ሜዳ መስክ ጥቅም ላይ ውሎ የሰው ዘር እስከማጥፋት አደጋ ሊያደርስ ይችላል። ከሠራተኛ አንጻር ቴክኖሎጂ ሦስት ውጤቶች ሊያስከትል ይችላል፤
   - ሠራተኞችን ባሉበት የሥራ መስክ የበለጠ ምርታማ ማድረግ፣
   - በአንድ የማምረት ሂደት ሠራተኞች ቢተኩም ሌላ ተያያዥ የሥራ መስክ እንዲፈጠር ማገዝ፣
   - ሠራተኞችን ሙሉ በሙሉ መተካት

37. ከ1980ዎቹ ጀምሮ የኮምፒተሮች እና የዲጂታል መሣሪያዎች መፈጠር ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ዕድሎችን እንደሚያሰፋ ተገምቶ ነበር። በአሜሪካ በ1960 ከ25 እስከ 54 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ሠራተኞች መካከል 6 በመቶ ያህሉ ከሥራ ውጪ ወይም ከሠራተኛ ኃይል ውጪ ሆነው ነበር። በአሁኑ ወቅት ይህ ምጣኔ 12 በመቶ ደርሷል። የዚህ ምክንያት ከቴክኖሎጂ ለውጥ ጋር ተያይዞ የኮሌጅ ትምህርት የሌላቸው ዜጎች ደህና ምንዳዕ ማግኘት ባለመቻላቸው ነው። የምንዳዕ እና ደመወዝ መዋቅር የዲጂታል ቴክኖሎጂን ለተማሩ ጥቂት የኮምፒውተር ሳይንቲስቶች፣ መሃንዲሶች እና የፋይናንስ ባለሙያዎች ባደላ መልኩ ከፍተኛ ልዩነት የሚታይበት ሆነ። በዚህም ምክንያት በአሜሪካ ባለ ሁለት ርከን ማሕበረሰብ እየተፈጠረ ይገኛል።

38. የኮምፒውተሮች ጥሩው ነገር ያዘዟቸውን መሥራታቸው ነው፤ የኮምፒውተሮች መጥፎው ነገር ያዘዟቸውን መሥራታቸው ነው። በአሜሪካ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የሠራተኛ ገቢ ከአጠቃላይ ብሔራዊ ገቢ ከ67-70

በመቶ ድርሻ የነበረው ሲሆን ቀሪው የካፒታል ድርሻ ነበር። በ2019፣ የሠራተኛ ገቢ ከብሔራዊ ገቢ ያለው ድርሻ ከ60 በመቶ ያነሰ ነው።

39. በቴክኖሎጂ በገፉ እና በፉክክር ላይ ባሉ አገራት ውስጥ በቴክኖሎጂ አልሚዎች እና ምሁራን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የየሚመለከታቸው ልሂቃን የሚነሳው ውይይት እና ክርክር በዘመነ ሰው ሠራሽ አስተውሎት ዕድል እና ስጋቶች የመኖራቸው ጉዳይ ነው። አንዱ የስጋት አቅጣጫ
    - ሰውን በመተካት ሥራ አጥነትን ማበራከት፣
    - የሰውን የግል ነጻነት መጋፋት ወይም መሳጣት (invading privacy)፣ እና
    - የወጣቶችን አስተሳሰብ እና አመለካከት በማይጠቅም እና አጥፊ በሆነ ደረጃ መሰቀዝ እና መቆጣጠርን ያካትታል።

40. በቴክኖሎጂ የገፉ አገራት የዘርፉ ክርክር ቴክኖሎጂን ለላቀ ማሕበራዊ ጥቅም ለመግራት ልምድ የሚወሰድበት ነው። በክርክሩ ነጥሮ የሚወጣው ገዢ ጉዳይ ቴክኖሎጂን በአግባቡ መሳፈር እና መግራት እንጂ ማስቆም የማይቻል መሆኑ ነው። የሰው ልጅ ትልቁ አቅሙ የዕውቀት የሰላ ጎራዴውን መቆጣጠር መቻሉ ነው። ዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ማሕበራዊ ጉዳት የሚያስከትሉ ሆነው ቢገኙ እንኳ የዚህ ችግር መፍትሄም የተሻለ ጠቃሚ ቴክኖሎጂ መፍጠር ነው። የቴክኖሎጂ መሪነቱን በጨበጡ አገራት የመንግሥታት ሚና በፖሊሲያቸው የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን ቴክኖሎጂ ለሰው ልጅ በሚጠቅም ሁኔታ ምርት እና አገልግሎቶችን ማምረት እንዲያስችሉ መግራት ነው። ቴክኖሎጂ የሰውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ እና አቅም የሚያሰፋ መሆን አለበት። የዘመኑ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ የሠራተኛን አቅም ማስፋት፣ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ እና በምርታማነት ዕድገት የመጣን ተጨማሪ ሀብት የሠራተኛን ክፍያ በማሳደግ ሁለንተናዊ አብሮ ማደግን ማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ መቃኘት ይኖርበታል።

41. **በሰው ሠራሽ አስተውሎት እድል እና ስጋት ጉዳይ የቴክኖሎጂ ተከታይ አገራት ሚና ከቴክኖሎጂው መሪ አገራት ሚና የተለየ ነው።** የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት እስከ አሁን ባለው የቴክኖሎጂ ክምችት ላይ በመመሥረት የሚረጋገጥ በመሆኑ በኢኮኖሚ ዕድገት ለመመንጠቅ በቴክኖሎጂ ርካብ ላይ ለመቆናጠጥ የሚጥሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገራት በቴክኖሎጂ የገፉ አገራት የቴክኖሎጂ ፉክክር አቅጣጫን በቅጡ በመረዳት በኢኮኖሚያቸው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ተስፋ እና ሥጋት በመቃኘት ዝግጁ መሆን ነው። ቴክኖሎጂ ለማሕበረሰብ ጠቃሚ ይሆን ዘንድ ቴክኖሎጂን ወይም ማሽንን ለማስቆም ከመሞከር ወይም ቆሞ የሚሆነውን ከመጠበቅ ይልቅ ከማሽኑ ጋር መፍጠን እና መስተካከል ነው።

42. የቴክኖሎጂ ዕድገት ለማሕበረሰብ የጠቀመበት ልምድ አለ። በ20ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ በአሜሪካ የተስፋፋው የአውቶሞቢል ኢንዱስትሪ (Ford Motor Company, General Motors) አዲስ በኤሌክትሪክ የሚሠራ ማሽን መፈጠሩን ተከትሎ ቀልጣፋ ፋብሪካዎች ማስፋፋት በመቻሉ እና የተሻሻሉ የመኪና ሞዴሎች በማስተዋወቁ የሠራተኛ ቅጥር እና ምንዳዕ ለተማረውም ሆነ ላልተማረው አድጓል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ (እኤአ) ድረስ የኮሌጅ ምሩቃንም ሆነ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምንዳዕ በተመሳሳይ ምጣኔ ጨመረ። ቴክኖሎጂ ምርታማነትን ሲጨምር የአምራች ተቋማት ለሠራተኛ ኃይል ፍላጎት በመጨመሩ ምንዳዕ ጨምሯል። የዚህን ዘመን ቴክኖሎጂም ለማህበረሰብ የጋራ ተጠቃሚነት ለመግራት ፖሊሲ ሚና አለው።

43. ቴክኖሎጂን በተለይም የዘመኑን የዲጂታል ቴክኖሎጂ አብዮት ለተሻለ ማሕበራዊ ፋይዳ ለመግራት ርትዕ ማሕበረሰብ ያስፈልጋል። የዘርፉ ምሁራን እንዳሉት የኮምፒውተር ጥሩው ነገር ያዘዙትን መሥራቱ ነው፤ የኮምፒውተር መጥፎው ነገር ያዘዙትን መሥራቱ ነው።

## የኢትዮጵያ/የአማራ ብሔራዊ ክልል የቴክኖሎጂ ደረጃ እና ተግዳሮቶች

44. የዓለም ጥቅል የቴክኖሎጂ አድማስ ጥግ ከፍተኛውን አገራዊ ምርት በሚያመርቱ እና ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ባላቸው አገራት ይወከላል። የአንድ አገር ካፒታል የማምረቻ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ አቅሞች (physical and human capital) ድምር ነው። ቴክኖሎጂ በእያንዳንዱ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ አቅም የሰረገ (embodied) እና የእነዚህን ነገራት - ምርቶች የማምረት አቅም የሚወስን የሀሳቦች ክምችት ነው። አገራት በአንዳንድ ውስን ስትራቴጂካዊ የቴክኖሎጂ ዓይነቶች ቀዳሚ ሊሆኑ ቢችሉም የአገራት ቴክኖሎጂ በማምረት አቅም ሲለካ አገራቱ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ሀብታቸውን በሙሉ አቅም ሲጠቀሙ ሊያመርቱ የሚችሉት የሙሉ አቅም ምርት

(potential GDP) ነው። ከዚህ አንጻር የዓለም ጥቅል የቴክኖሎጂ አድማስ ጥግ በዓለም ከፍተኛው አገራዊ ምርት እና የነፍስ ወከፍ ገቢ ሊመላከት ይችላል።

45. የአንድ አገር የቴክኖሎጂ ስፋት እና ጥልቀት በኢኮኖሚው ስፋት እና የዘርፎች እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች ውስብስብነት ይወሰናል። ሰፊ፣ እና ውስብስብ ግብዓቶችን የሚጠቀም ኢኮኖሚ በተገማች እና የተረጋጋ የኢኮኖሚ እድገት፣ እንዲሁም በርትዕ መዋቅራዊ ለውጥ የታጀበ አስገምጋሚ (vibrant) ኢኮኖሚ ነው። በዚህም ምክንያት የፈጣን እና ፈርጀ-ብዙ ቴክኖሎጂ ልማት የፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና አሻጋሪ መዋቅራዊ ለውጥ፣ በሂደትም የመዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጫ መሣሪያ የመሆኑን ያህል የተሳካ መዋቅራዊ ለውጥ ማረጋገጥ የቻለ ውስብስብ ኢኮኖሚ የፈርጀ-ብዙ ቴክኖሎጂ አድማስ ማሳያ ነው።

46. በአጠቃላይ አገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም እና ስርጸት ደረጃ በአምሥት ዋና ዋና መለኪያዎች ማመላከት ይቻላል፤

- አገራዊ የማምረት አቅም- የነፍስ ወከፍ ገቢ፣ አማካይ የሠራተኛ ምርታማነት፣
- የከፍተኛ እና መካከለኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ንዑስ ዘርፎች ከአገራዊ ኢኮኖሚ ያላቸው ድርሻ፣
- የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ደረጃ (digital intensity)
- የዘርፎች የቴክኖሎጂ ትስስር (technological connectedness)
- የቴክኖሎጂ ፈጠራ እና ሽግግር ደረጃ።

47. የአገራት የቴክኖሎጂ አቅም የማምረት አቅም ሲሆን ይህ የማምረት አቅም በአማካይ አገራዊ ምርት (potential GDP) በተለይም በነፍስ ወከፍ የሠራተኛ ገቢ ይለካል። የዓለምን ቴክኖሎጂ እንደምትመራ የሚታመንላት አገር አሜሪካ በ2015 የነበራት አገራዊ ምርት በነፍስ ወከፍ ሠራተኛ በ2013 የመግዛት አቅም 151,847 ዶላር ሲሆን ይህም በቴክኖሎጂ እየተገዳደረቻት ካለችው ቻይና አኃዝ በ3.6 እጥፍ ይበልጣል። በተመሳሳይ ወቅት የኢትዮጵያ አገራዊ ምርት በነፍስ ወከፍ ሠራተኛ በ2013 የመግዛት አቅም 5,855 ዶላር ነበር። ይህም ማለት አንድ አማካይ አሜሪካዊ ሠራተኛ በቀን የሚያመርተውን ለማምረት አንድ አማካይ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ 26 ቀናት ይፈጅበታል። ኢትዮጵያ በአማካይ የሠራተኛ ምርታማነት ከአፍሪካ የምትበልጣቸው አገራት ስምንት ብቻ ናቸው። ለዚህ አንዱ ምክንያት አብዛኛው ማሕበረሰብ ቴክኖሎጂ ገብ ባልሆነ ግብርና ላይ የተሰማራ መሆኑ ነው። በ2015 የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ 33 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህም ከኒዠር እና ሴራ ሊዮን ቀጥሎ በዓለም ላይ 3ኛው ከፍተኛ የግብርና ዘርፍ ድርሻ ምጣኔ ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልል የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ 52 በመቶ የነበረ በመሆኑ አማካይ የሠራተኛ ምርታማነት ከአገራዊ አማካይ ምርታማነት እንደሚያንስ ይጠበቃል። በዚህ አመክንዮ መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል ኢኮኖሚ ከዓለም የቴክኖሎጂ አድማስ በጣም ሩቅ ነው።

48. ስዕል 24 – 1፤ የቴክኖሎጂ አድማስ በአገራዊ የሠራተኛ ምርታማነት



ምንጭ፤ የዓለም ባንክ መረጃን በመጠቀም የተቀነባበረ

49. የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት የሚንጸባረቅበት ሌላው መስፈርት በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ የመካከለኛ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ንዑስ ዘርፎች የተጨማሪ እሴት ድርሻ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ቴክኖሎጂን በስፋት የሚጠቀመው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በክልሉ ከ8 በመቶ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ7 በመቶ አለመብለጡ የክልሉን እና የአገሪቷን የቴክኖሎጂ ደረጃ ያመለክታል። ከዚህም ውስጥ የመካከለኛ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ንዑስ ዘርፎች ድርሻ 16 በመቶ፣ የከፍተኛ ማሽን እና የትራንስፖርት ዕቃዎች ድርሻ 5.5፣ እንዲሁም የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ድርሻ 10 በመቶ ብቻ መሆኑ በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የተጀመሩ የኢንዱስትሪ ውጥኖች ለጥልቅ መዋቅራዊ ለውጥ የሚያስፈልገውን ቴክኖሎጂ ደረጃ ያልያዙ መሆናቸውን ያሳያል።

50. ሠንጠረዥ 24-1፤ የኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋቅር ከዋና ዋና የዓለም አገራት መዋቅር ጋር ያለው ንጽጽር

| | የአምራች ኢንዱስትሪ ድርሻ ከአገራዊ ምርት | | የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ድርሻ ከአምራች ኢንዱስትሪ በመቶኛ (2013)* | | | | | | የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2013 የዶላር የመግዛት አቅም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መረጃ ከተያዘበት ከፍተኛው | 2013 | መካከለኛ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ | ማሽነሪ እና ትራንስፖርት | ኬሚካል | ጨርቃጨርቅ | ምግብ እና መጠጥ | ሌሎች | |
| **ኢትዮጵያ** | **7.1** | **4.6** | **16.1** | **5.5** | **10.6** | **10** | **36.6** | **37.3** | **2,628** |
| ሲንጋፖር | 27.1 | 20.3 | 81.8 | 61.5 | 20.0 | 0.1 | 3.6 | 14.8 | 131,864 |
| ስዊዘርላንድ | 19.8 | 19.1 | 68.0 | 28.8 | 36.7 | 0.6 | 7.3 | 26.6 | 81,603 |
| ደንማርክ | 18.1 | 12.5 | 56.7 | 26.2 | 26.0 | 1.1 | 12.3 | 34.4 | 69,879 |
| ጀርመን | 24.8 | 18.9 | 60.6 | 40.3 | 10.9 | 1.1 | 8.2 | 39.5 | 61,940 |
| ፈረንሳይ | 22.7 | 9 | 51.7 | 30.8 | 15.6 | 2.6 | 18.8 | 32.7 | 53,835 |
| ደ. ኮሪያ | 28.2 | 25.5 | 63.6 | 48.2 | 11.8 | 2.9 | 6.7 | 30.5 | 48,571 |
| ጃፓን | 23.5 | 20.9 | 56.1 | 42.7 | 11.9 | 1.5 | 13.5 | 30.4 | 44,549 |
| ቻይና | 32.5 | 27.5 | 41.5 | 24.5 | 10.8 | 10 | 11.8 | 42.8 | 20,407 |
| ቦትስዋና | 11.6 | 5.2 | 28.0 | 17.6 | 11.1 | 5.5 | 28.1 | 37.7 | 16,664 |
| ደ. አፍሪካ | 24.8 | 12.9 | 24.0 | 14.6 | 7.0 | 1.8 | 22.3 | 54.4 | 14,173 |
| ኢንዶኔዥያ | 32.0 | 19.2 | 30.1 | 13.2 | 12.2 | 12.9 | 28.9 | 35.6 | 12,897 |
| ናይጀሪያ | 21.1 | 14.6 | 33.4 | 7.0 | 25.5 | 11 | 30.0 | 25.8 | 5,624 |
| ዛምቢያ | 33.3 | 8.3 | 9.7 | 5.0 | 8.7 | 1.1 | 30.9 | 58.3 | 3,527 |
| ዚምባብዌ | 26.9 | 12.4 | 9.6 | 1.3 | 6.5 | 2.8 | 65.4 | 24.0 | 3,276 |

ምንጭ፤ የዓለም ባንክ ድረ-ገጽ የአገራት መረጃዎች፣ 2023

51. የአማራ ብሔራዊ ክልል ውስን ከሆነው የአገር አቀፍ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የአምራች ተቋማት ብዛት ያለው ድርሻ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ቀጥሎ በርቀት ሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በተለይ ቴክኖሎጂ ገብ በሆኑት የብረታ ብረት እና ማሽን፣ እንደዲሁም የኬሚካል ኢንዱስትሪ ያለው ድርሻ በ2.7 በመቶ ብቻ መወሰኑ ትኩረት የሚሻ ነው። በ2015 የአዲስ አባባ ከተማ መስተዳድር የብረታ ብረታ እና ማሽን ፋብሪካዎች አገር አቀፍ ድርሻ 56.8 በመቶ፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ድርሻ 47.3 በመቶ ነው። በተመሳሳይ ዓመት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የብረታ ብረት እና ማሽን ኢንዱስትሪዎች ድርሻ 29.7 በመቶ፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ከአገር አቀፍ የንዑስ ዘርፉ ተቋማት ብዛት የነበረው ድርሻ ደግሞ 42.6 በመቶ ነው።

52. የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ደረጃ (digital intensity) ደህንነታቸው በተጠበቀ የኢነትርኔት አገልግሎት እና በኢነተርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ ምጣኔ ሊገለጽ ይችላል። ኢትዮጵያ በ2014 ደህንነቱ የተረጋገጠ ኢንተርኔት አገልግሎት ለሚሊዮን ሕዝብ 17.5 ሲሆን ይህ አኀዝ በዓለም ላይ ከፍተኛ ከተባሉት ምጣኔዎች ማለትም የደንማርክ 261,268 የሲንጋፖር 228,648 የኔዘርላንድ 194,963 እና የአሜሪካ 187,747፣ እንዲሁም አቻ ከሚባሉት የኬንያ 297 በአጠቃላይም ከሰሃራ በታች ያሉ አፍሪካ አገራት አማካይ 794 አንጻር በጣም አነስተኛ ነው። ኢንተርኔት የሚጠቀም ሕዝብ ምጣኔ ከዲጂታል ቴክኖሎጂ ፋይዳ አንጻር ከምርታማነት ጋር ላይያያዝ ይችላል። ኢንተርኔት ለግለሰቦች መዝናኛ ወይም ለቢዝነስ አገልግሎት ሊውል ይችላል። ለማሳያም የተባበሩት የአረብ ኤመሬቶች (ዩኤኢ)፣ ኳታር፣ ሳዑድ አረቢያ እና ባሕሬን 100 ከመቶ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ ምጣኔ አላቸው። በ2014 ኖርዌ፣ ላክሰምበርግ፣ ደንማርክ፣ ደቡብ ኮሪያ እና አሜሪካ ከ97 በመቶ በላይ የሆነ የበኢነትርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ ምጣኔ ነበራቸው። ኬንያ፣ ርዋንዳ፣ በአጠቃላይም ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ

አገራት የኢንተርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ ምጣኔ እንደ ቅድም ተከተላቸው 40.8 በመቶ፣ 34.4 በመቶ፣ እና 33.6 በመቶ ነው። በተመሳሳይ ወቅት የኢትዮጵያ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ ምጣኔ 19.4 በመቶ ነበር።

53. ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 የሠራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ብሔራዊ ዳሰሳ መረጃ መሠረት ኮምፒውተር መጠቀም የሚችል ከአሥር ዓመት ዕድሜ በላይ ያለ ሕዝብ ምጣኔ 8.9 በመቶ፣ ኢንተርኔት መጠቀም የሚችል ሕዝብ 14.6 በመቶ ሲሆን፣ በአንጻሩ ተንቀሳቃሽ ስልክ ያለው ሕዝብ ብዛት ምጣኔ 73.8 በመቶ ነበር። በተመሳሳይ አሥር ዓመት ዕድሜ በላይ ከሚሆነው የክልሉ የሠራተኛ ኃይል መካከል 8.5 በመቶ ኮምፒውተር መጠቀም የሚችል፣ 11.1 በመቶ ኢንተርኔት መጠቀም የሚችል፣ እና 77.1 በመቶ የሚሆነው ተንቀሳቃሽ ስልክ ነበረው። የክልሉ የኮምፒውተር እና ኢንተርኔት ተጠቃሚ ሕዝብ እና ሠራተኛ ኃይል ምጣኔ ከአገር አቀፍ ምጣኔ ከ1 እስከ 2 መቶኛ ነጥብ ያነሰ ሲሆን፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ ያለው የክልሉ ሕዝብ እና ሠራተኛ ኃይል ምጣኔ ከአገር አቀፉ ምጣኔ በ10 የመቶኛ ነጥብ የላቀ ነው።

54. *ሠንጠረዥ 24-2፤ የዲጂታል ዕውቀት ሥርጸት (Digital Literacy) ደረጃ*

| | ከ10 ዓመት በላይ ያለ ሕዝብ | |
|---|---|---|
| | አማራ ብ. ክልል (ከ17.6 ሚ.) | ኢትዮጵያ (ከ70 ሚ.) |
| ኮምፒውተር መጠቀም የሚችል | 8.9 | 9.9 |
| ኢንተርኔት የሚጠቀም | 14.6 | 16.7 |
| ሞባይል ስልክ ያለው | 73.8 | 63.8 |
| | ከ10 ዓመት በላይ ያለ ሠራተኛ | |
| | አማራ ብ. ክልል (ከ11.1 ሚ.) | ኢትዮጵያ (ከ41.6 ሚ.) |
| ኮምፒውተር መጠቀም የሚችል | 8.5 | 9.7 |
| ኢንተርኔት የሚጠቀም | 14.1 | 16.2 |
| ሞባይል ስልክ ያለው | 77.1 | 67.2 |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 የሠራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ

55. በዘርፎች የቴክኖሎጂ ትስስር (technological connectedness) መስፈርት የክልሉም ሆነ የአገር አቀፍ የቴክኖሎጂ የዘርፍ ስምሪቶች በመሠረታዊ ማሽን፣ በመለዋወጫ፣ በኃይል አቅርቦት፣ በማዕድና እና ሰው ሠራሽ ግብዓቶች የተሳሰሩ አይደሉም። ለዚህ ማሳያዎቹ ማሽኖችን ከውጭ ለማስገባት በውጭ ምንዛሪ እጥረት መፈተን እና መዘግየት፣ ማሽን ተሟልቶ ወደ ሥራ ሲገባ በኃይል አቅርቦት እና ከውጭ መግባት ባለባቸው ጥሬ ዕቃዎች እጥረት ምክንያት ከ54 በመቶ በላይ በሙሉ አቅም ማምረት አለመቻል ናቸው። ስለዚህ በአገር ውስጥ ያሉ የማምረቻ ተቋማት ከባሕላዊው የገጠር ሥልተ ምርት በስተቀር በማሽን፣ በኃይል አቅርቦት፣ በሰው ሠራሽ እና የማዕድን ግብዓት እንዲሁም በኦቶሜሽን ቴክኖሎጂ ተሳስረው የተቋቋሙ አይደሉም።

56. በቴክኖሎጂ ፈጠራ እና ሽግግር ረገድ ከውጭ የማይገቡ በራስ አቅም የሚሠሩ የቴክኖሎጂ አቅሞች በአብዛኛው በግብርና ዘርፍ በሞፈር እና ቀንበር (ማረሻ እና ወገል የብረታብረት ምርቶችን ጨምሮ)፣ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የሸማኔ ዕቃ፣ በኬሚካል ኢንዱስትሪ አረቄ፣ ጠላ እና ጠጅ፣ እንዲሁም መለስተኛ የጽዳት ኬሚካሎች፣ በሴራሚክ ኢንዱስትሪ የሸክላ ሥራዎች ላይ ለዘመናት ቆሟል። ከውጭ የገቡ ቴክኖሎጂዎች በአገር ደረጃ በቁጥር ሲታሰቡ በርካታ ቢሆኑም የራስ ከመሆን ይልቅ በማሽን፣ በመለዋወጫ፣ እና በግብዓት ቴክኖሎጂዎቹ በተፈጠሩበት አገር ባላቸው ዕጣ ፋንታ ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።

57. በቴክኖሎጂ ረገድ አራት መሠረታዊ ተግዳሮቶችን መለየት ይቻላል፤

1. **በእቅድ፣ በፖሊሲ፣ እና በተግባር የሚንጸባረቁት የመዋቅራዊ ለውጥ ግብ መነሻዎች ከቴክኖሎጂ ተስተካካይነት ግብ ጋር የተጣጣሙ አለመሆን፤** ዘርፎች ወይም ንዑስ ዘርፎች ሲመረጡ የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ቴክኖሎጂ ገብ በተለይም አዳጊ እና ውስብስብ መካከለኛ ግብዓቶችን የሚጠቀሙ በመሆናቸው እና ለሌሎች ዘርፎች መነቃቃት በሁለገብነት ስለሚያገለግሉ ነው። ይህ የመዋቅራዊ ግብን

ከቴክኖሎጂ አቅም መትባት ጋር የማያያዝ ጉዳይ በዕቅድ፣ ወይም በአፈጻጸም ጊዜ ግምት ውስጥ ሳይገባ የመዋዕለ ንዋይ ስምሪቶች በዘፈቀደ የሚመሩ ይሆናሉ።

2. **የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሽን ከውጭ አስገብቶ ማምረት ከመቻል ግብ ጋር ማያያዝ፤** ማሽን ቴክኖሎጂ ተሸካሚ እንጂ በራሱ ቴክኖሎጂ አይደለም። መሸንን አገር ውስጥ አስገብቶ ማምረት ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን መጠቀም በቴክኖሎጂው መጠቀም እንጂ ቴክኖሎጂን ማሸጋገር አይደለም። ቴክኖሎጂ ተሸጋገረ የሚባለው ሀሳቡን በአገር ውስጥ አቅም ወደ ተግባር ማስገባት፣ ማለማመድ እና በመጨረሻም መፍጠር እና መወዳዳር ሲቻል ነው። በኢትዮጵያ እና በአማራ ብሔራዊ ክልል ደረጃ ትልቁ የቴክኖሎጂ ጉድለት ሀሳብን ወደ ቴክኒክ ቀይሮ የመተግበር ችግር ነው።

3. **በወሳኝ የቴክኖሎጂ ዘርፎች በሠለጠነ የሰው ኃይል እና በኢንዱስትሪያላዊ ባለሀብት የሚገለጽ የቴክኖሎጂ ዝግጁነት ውስን መሆን፤** ከክልሉ እና ከአገሪቷ የኢኮኖሚ መዋቅር፣ ከትምህርት እና የስልጠና ሥርዓት፣ እንዲሁም ከአገር ውስጥ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ባሕል የሚመነጭ የቴክኖሎጂስት እና የኢንዱስትሪያሊስት እጥረት በስፋት አለ። ሀሳብን ወደ ቴክኒክ ቀይሮ የመተግበር ችግር ያለው በትምህርት ቤቶች ሰልጥኖ በወጣው የሰው ኃይል ጭምር ነው። ለዚህ አንዱ ዋና ችግር የኢንዱስትሪ እና የትምህርት ወይም ማሰልጠኛ ተቋማት ትስስር አለመኖር ነው። ይህ በተምህርት ፖሊሲው የተቀመጠ ቢሆንም ለዕውቀት የሚገባውን ዋጋ ሰጥቶ የረቀቀ ግን ለአብዛኛው የአገር ውስጥ ባለሀብት በማይታወቁ ወይም በአጭር ጊዜ ትርፍ በማያስገኙ ስትራቴጂካዊ ኢንዱስትሪዎች መግባት የሚደፍር አልሚ ውስን በመሆኑ ነው።

4. **እንደ ማሕበረሰብ ሣይንሳዊ እና የቴክኖሎጂ ዕውቀትን የችግሮቹ መፍቻ አድርጎ የመቀበል እና ለዚህም የመትጋት ወይም የማበረታታት ባህል ዝቅተኛ መሆን፣** ዕውቀትን ወደ ቴክኒክ የሚቀይር የሰለጠን የሰው ኃይልም ሆነ ቴክኖሎጂን በስፋት የሚጠቀም የኢኮኖሚ መስክ ላይ የሚሰማራ የአገር በቀል አልሚ እጥረት መሠረታዊ መነሻ በሳይንሳዊ እና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ችግር መፍቻነት የሚያምን ማሕበረሰብ ወሳኝ በሆነ መጠን እና ጥልቀት ባለመፈጠሩ፣ እና የሰለጠነው የሰው ኃይልም ሆነ አልሚው የዚህ ማሕበረሰብ አካል መሆኑ ነው። የተማረው ወይም የሰለጠነው የሰው ኃይል በመንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ተቀጥሮ መሥራትን ግብ አድርጎ የሚማር፣ አገራዊ አልሚው ደግሞ የአጭር ጊዜ ትርፍ በሚያስገኙ በብዛትም የማቀባበል ሚና ባላቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሠማራትን የሚመርጥ፣ በአጠቃለይ ሁለቱም አካላት ቴክኖሎጂ ምርት ማትረፍረፍ ከሚችልባቸው አፈር እና ብረት ጋር መታገልን የሚሸሹ ናቸው።

## 24.2. የረጅም ዘመን የቴክኖሎጂ ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫዎች

58. የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ-ካርታ ዋና ስትራቴጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነትን ማረጋገጥ ነው። የኢኮኖሚ ተስተካካይነት የሚረጋገጠው በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ሲሆን የፈጣን ግን አሻጋሪ የሆነ የረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ደግሞ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው።

59. የቴክኖሎጂ ተስተካካይነትን ለማረጋገጥ አራት መሠረታዊ ፍኖቶችን ለመከተል አቅጣጫ ተይዟል፤

- **መሪ ዘርፎች፣ መሪ አቅሞች፤** በሁሉም ዘርፎች ቴክኖሎጂን በአንዴ ለማሸጋገር፣ ለመማር፣ እና ለማልማት ከመሞከር ይልቅ ክልሉ እና አገሪቷ ተወዳዳሪ ሊሆኑ በሚችሉባቸው ዘርፎች፣ ከሁሉም በላይ ለብዙ ዘርፎች ልማት መነቃነቅ በሚያግዙ ዘርፎች ላይ ማተኮር፣
- **የተቀናጁ እና የተሳሰሩ አቅሞች፤** የተመረጡ መዋዕለ - ቴክኖሎጂዎችን በመሠረታዊ የማሽን ቴክኖሎጂ፣ በኃይል ምንጭ፣ በግብዓት እና በአመራረት ሥርዓት (አቶሜሽን ርቅቀት) ጫፍ እስከ ጫፍ የማስተሳሰር ስልት መከተል፣
- **በአቋራጭ ከዓለም የቴክኖሎጂ ጫፍ የመጀመር ስልት፤** የቴክኖሎጂ ተስተካካይነትን ለማረጋገጥ በአንድ በኩል መሠረታዊ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችን በማሟላት፣ በዋናነት ግን በማሽን ቴክኖሎጂ፣ በኃይል ምንጭ፣ በግብዓት እና በአመራረት ሥልት ዓለም ከደረሰበት ቴክኖሎጂ ጋር መላመድ፣ እና

- **ሕዝባዊ መሠረት ያለው ቴክኖሎጂ፤** በሥርዓተ - ትምህርት በሚደገፍ የሳይንስ ዕውቀት ቴክኖሎጂን ሕዝባዊ ማድረግ።

60. **መሪ ዘርፎች እና መሪ አቅሞች፤** የረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት ስኬት ታሪክ እንደሚያሳየው ቴክኖሎጂ በበርካታ ዘርፎች ናኝቶ የበዛ ቢመስልም በአራት ዋና ዋና ፍኖቶች ሲያድግ ቆይቷል፤ በሁሉን አቀፍ ማምረቻ ማሽኖች፣ በኃይል ምንጭ፣ በግብዓቶች፣ እና በአሠራር ሥርዓት። ቴክኖሎጂ በራሱ አይቆምም፤ የሚቆምበት ቁሳዊ ካፒታል ያስፈልገዋል። በቴክኖሎጂ የተቡ እና የተሳሉ ቁሳዊ ካፒታሎች ዓላማቸው ምርት ማምረት ነው። በሁሉም ዘርፍ ተፈላጊ የሆኑ በቴክኖሎጂ የተቡ ቁሳዊ ካፒታሎች መካከል ማሽኖች ናቸው። ማሽኖች የሚፈበረኩት በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው። ስለሆነም ማሽኖችን እና ልዕለ - ማሽኖችን (ማሽን አምራች ማሽኖችን) የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመሠረታዊነት ትኩረት የሚሰጠው ኢንዱስትሪ ነው። ማሽን የማምረቻ አቅም የመሆኑን ያህል ዘላቂ እና አዋጭ የኃይል ምንጭ እና ግብዓቶች ይጠይቃል። ማሽኖችን ለማምረት የብረት እና የከፊል ኮረንቲ አስተላላፊ ማዕድናት ልማት፣ ለሰው ሠራሽ ግብዓት ምርት አቅም የሚሆኑ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚያተኩርባቸው መስኮች ናቸው። የኃይል ምንጭ በየዘመኑ ከእንጨት ከሚገኝ እሳት ጀምሮ እስከ ኤሌክትሪክ ኃይል የገዘፈ ሲሆን ዘላቂነቱን ከብክለት በጸዳ እና ከዘመኑ የዘላቂ አረንጓዴ ልማት ግቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ ማልማት ይጠይቃል። የአመራረት ሥርዓት በአንድ ሰው ከሚከናወኑ የተናጠል የዕደ ጥበብ ውጥኖች በፋብሪካ ሥርዓት በአንዴ ብዙ ማምረት ወደሚያስችል የኦቶሜሽን ሥርዓት፣ ከዚህም ባለፈ የሰው ጉልበት ብቻ ሳይሆን አስተሳሰብን በሚተኩ ማሽኖች የማምረት ሥልት ተሸጋግሯል።

61. በመሆኑም የቀጣዮቹ የረጅም ጊዜ እና የመካከለኛ የልማት ዕቅዶች የቴክኖሎጂ የትኩረት አቅጣጫ ዋና የትኩረት መስክ በሆኑት
    - የአምራች ማሺኖች እና በልዕለ- ማሽኖች ቴክኖሎጂ እና አጠቃላይ የፍብረካ ምህንዲስና፣
    - የዘላቂ እና አዋጭ የኃይል ምንጮች ቴክኖሎጂ፣
    - የማዕድናት ልማት እና ሰው ሠራሽ የኬሚካል ግብዓቶች ቴክኖሎጂ፣
    - የባዮ ቴክኖሎጂ እና የዘረ መል ምሕንዲስና (genetic engineering)፣ እንዲሁም
    - በሁሉም ወሳኝ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ እና የመንግሥት አገልግሎቶች ተተግባሪ በሆነው የዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅም ለመፍጠር በትኩረት መሥራት ነው።

62. የተቀናጁ እና የተሳሰሩ አቅሞች፤ በቴክኖሎጂ ግስጋሴ ልማትን ለማፋጠን ሁለት ሥርዓታት ወሳኝ ናቸው፤
    - ማሽንን፣ ግብዓትን እና ኃይልን አቀናጅቶ ገደብ የለሽ ምርት ማምረት የሚያስችል የፋብሪካ የኦቶሜሽን ሥርዓት
    - ዕድገት በቴክኖሎጂ እንዲረጋገጥ የሚያግዝ በማህበረሰብ፣ በዕምነት ተቋማት፣ እና በፖለቲካ ልሂቃን ዝግጁነት የሚገለጽ ሥርዓት።

63. ቴክኒካል በሆነው የማምረት ሂደት የማምረቻ አቅሞች በኃይል እጥረት ከተፈተኑ፣ የግብዓት እጥረት ካጋጠማቸው ወይም ከውጭ የሚገቡ ከሆነ ቴክኖሎጂ ዘላቂ እድገትን ሊያረጋግጥ አይችልም። በተለይም የኢኮኖሚ ዕድገት ነባር ምርቶችን በስፋት በማምረት የሚረጋገጥ ሳይሆን ነባር ምርቶችን በአዲስ ምርቶች በመተካት የሚገኝ ነው። አዲስ ምርቶች በአዲስ ቴክኖሎጂ መመረት ይኖርባቸዋል። የቴክኖሎጂ ለውጥ የሚረጋገጠው ነባር የማምረቻ ማሽኖችን በአዳዲስ ማሽኖች ከመተካት በፈጠነ ድግግሞሽ ውስብስብ እና የረቀቁ መካከለኛ ግብዓቶችን (intermediate inputs) በመጠቀም ነው። የተለዋዋጭ እና የተራቀቀ የቴክኖሎጂ ዕድገት ምንጮች ግብአቶች ናቸው። እነዚህን ግብዓቶች ከውጭ ለዘመናት የሚያስገባ አገር የቴክኖሎጂ ጥገኛ እንጂ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ ሊሆን አይችልም። ከዚህ አንጻር ማሽኖችን ከመፈብረክ ባለፈ ግብዓቶችን በራስ የቴክኖሎጂ አቅም ማምረት የፋብሪካ የግብዓት ችግር ከመቅረፍ እጅግ በዘለለ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ማረጋገጫ ሥልት ነው።

64. በሌላ በኩል ለሳይንሳዊ ዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ቀናዒ የሆነ ማሕበረሰብ ለጠቃሚ ቴክኖሎጂ ሽግግር ወሳኝ የመሆኑ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምርት እና ቴክኖሎጂዎቻቸው በአዲስ የሚተኩባቸው ኩባንያዎች ተጽዕኖም ለዕድገት እንቅፋት መሆኑ አይቀርም። በአገራችን በቴክኖሎጂ እና በምርት ከፍተኛ የጊዜ ታካኪነት አለ። በእነዚህ ዓይነቶቹ ተግዳሮቶች ምክንያት አሮጌው ቴክኖሎጂ በአዲስ ሲተካ አዲሱ ቴክኖሎጂ የሚተኩትን

ምርቶች ማካካስ ካልቻለ ዕድገት አዝጋሚ ይሆናል። የዚህ ዓይነት ዝንባሌዎችን የሚያርም የመንግሥት ፖሊሲ የርትዕ ሥርዓታት አካል ነው።

65. **በአቋራጭ ከዓለም የቴክኖሎጂ ጫፍ የመጀመር ስልት፤**ቴክኖሎጂ የማሻሻሎች ድምር ወጤት ነው። የቴክኖሎጂ እድገት በጥቅሉ በማሽን ሥርዓት (machine systems)፣ በኃይል ምንጭ (energy)፣ በግብዓት (inputs)፣ እና በእነዚህ አቅሞች በሰረጉ (embodied) ሃሳቦች (ideas) ለውጥ ሊገለጽ ይችላል። ማሽን ከተጠረበ ዲንጋይ ወደ ቀላል የብረታ ብረት መሣሪያዎች፣ በእንፋሎት ኃይል የሚሠሩ ኢንጂኖች፣ ኮምፒውተሮች፣ እና ሮቦቶች ተሻሽሏል። የኃይል ምንጭ በእንጨት ላይ ከተመሠረተ እሳት፣ የእንስሳት እና የአትክልት ውጤቶች (ሞራ እና ዘይት)፣ የእንስሳት ጉልበት፣ እንፋሎት፣ ኮረንቲ እና ነዳጅ አድጓል። ግብዓቶች ከተራ ዲንጋይ፣ እስከ የእንስሳት እና የአዝርዕት ውጤቶች፣ ብረት፣ ብረታ ብረት፣ የዓረብ ብረት፣ ሃይድሮ ካርበን፣ ከፊል ከረንቲ አስተላላፊ (semiconductors) ተሻሽሏል። ሃሳብ የሰውን ልጅ እጅ እና ጉልበት ከመተካት ጀምሮ የሰውን ልጅ አስተሳሰብ (intelligence) በማሽኖች እስከ መተካት ደርሷል። ከኋላ ገስግሶ በቴክኖሎጂ የመስተካከል አመክንዮ ትክክል የሚሆነውም በቴክኖሎጂ ቀዳሚ የሆኑ አገራት በበርካታ ክፍለ - ዘመናት ያለፉበትን የቴክኖሎጂ ርክን ሁሉ በመድገም ሳይሆን ከመጨረሻው የቴክኖሎጂ ምህዋር በመንጠላጠል እና በማግባት ነው። በዚህም መሠረት ለፍብረካ ምህንድስና መሠረት በሆኑት ዘመናዊ ማሽኖች ቴክኖሎጂ፣ በኃይል አቅርቦት ረገድ ከአየር ንብረት ጋር የተጣጣመ የኤሌክትሪክ ኃይል ቴክኖሎጂ፣ በግብዓት ረገድ ለዘመናዊ ፍብረካ፣ ለኬሚካል ኢንዱስትሪ እና ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት (ብረት፣ ከፊል ኮረንቲ አስተላላፊ- semiconductors) እና ሰው ሠራሽ ግብአቶች፣ እንዲሁም የዲጂታል ቴክኖሎጂ ከጫፍ የሚጀመርባቸው ቴክኖሎጂዎች ናቸው።

66. **ሕዝባዊ መሠረት ያለው የቴክኖሎጂ ዝግጁነት፤** ቴክኖሎጂ ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው የሚያስፈልግበት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፤ የመጀመሪያው ምክንያት ለቴክኖሎጂ ፈጠራ መክሊቱ ያላቸው የሰላ አዕምሮ ባለቤቶች እና ቴክኖሎጂውን ከፈጠራ እና ከማላመድ ባለፈ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወደ ቢዝነስ ለመቀየር የአልሚነት (አንተርፐረነርሺፐ) ተሰጥዖ ያላቸው ዝጎች የሚገኙት ከጥቂት ልሂቃን ይልቅ ከብዙው እና ሰፊው ሕዝብ መሃል ስለሆነ ነው። ሁለተኛው ምክንያት የኢኮኖሚ ዕድገት በውስን ለጥልቅ መዋቅራዊ ለውጥ አስተዋጽዖ ባላቸው ዘርፎች መሪነት የሚለኮስ ቢሆንም በምልዓተ ዘርፎች ንቅናቄ የሚረጋገጥ በመሆኑ እና በእነዚህ ዘርፎች የተሰማራው ሰፊ የኢኮኖሚ ተዋናይ ሕዝብ በቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትም ሆነ ፈጣሪነት ተሳታፊ መሆን ስላለበት ነው።

67. ሕዝባዊ መሠረት ያለው የቴክኖሎጂ ዝግጁነት ማረጋገጫ መንገድ ለቴክኖሎጂ ሽግግር አዋጭ በሆኑ ዘርፎች የሚያተኩር የሳይንስ እና የቴክኒክ ትምህርትን አባካኝ ባለሆነ መልኩ በመሳፋፋት ነው። በተሞክሮ ደረጃ የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ስኬት ምንጭ በጥቂት ወሳኝ ዘርፎች (የብረት ማቅለጫ እና የብረታ ብረት ሥራ፣ የእንፋሎት ኢንጂን፣ የጥጥ መፍተያ ማሽን፣ የሸክላ ወይም የሴራሚክስ ሥራ፣ እና ለኬሚካል ኢንዱስትሪ መሠረት የጣለው የሰው ሠራሽ ቀለም) የቴክኖሎጂ ፈጠራን ማሳካት የቻሉት ትምህርት ቤት ያልገቡ ወይም በትምህርታቸው እምብዛም ያልገፉ ነገር ግን በመንግሥት ፖሊሲ የትችላላችሁ ነጻነት የተሰጣቸው የታችኛው ማሕበረሰብ አካል ናቸው። በቀሪው አውሮፓ እና በጃፓን በተቀጣጠለው፣ በኋላም አሜሪካንን ለልዕለ- ኃይልነት ባበቃው በሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የቴክኖሎጂ ሕዝባዊ መሠረትነት የተረጋገጠው ቴክኖሎጂን በሳይንስ እና የቴክኒክ ትምህርት በትምህርት ቤቶች በማዳረስ ነው። በትምህርት ሥርዓት የተፈጠሩ ባለምጡቅ አዕምሮ አቅሞችን በማሰባሰብ ቴክኖሎጂን በምርምር እንዲያፋጥኑ በማድረግ አሜሪካ ተሳክቶላታል። የደቡብ ምሥራቅ አገራት በተለይም የደቡብ ኮሪያ ልምድ የሚያሳየው የቴክኖሎጂ ዝግጁነት ተገቢ ትምህርትን ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግን ይጠይቃል።

68. ቴክኖሎጂን በትምህርት ሥርዓት ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ በመሠረታዊነት በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የችግር መፍቻ ብቸኛ ቁልፍነት የሚያምን ማሕበረሰብ መፍጠር ይጠይቃል። ቴክኖሎጂን በፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭነት ማሕበረሰብን ለመሻገር እንዲቻል ከሚያስፈልጉት የቁሳዊ ካፒታል እና የሰለጠነ የሰው ኃይል ዝግጁነት በተጨማሪ እና በበለጠ ቴክኖሎጂን ለችግሩ መፍቻነት የሚቀበል፣ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ጥረቶችን የሚያቅፍ እና የሚያበረታታ ማሕበረሰባዊ መሠረተ - እሴቶች (sympathetic social ethos) መገንባት መቻልን ታሳቢ ያደርጋል።

## 24.3. የቴክኖሎጂ ዝግጁነት (Technological Readiness)

69. የ21ኛው ክፍለ - ዘመን የቴክኖሎጂ ግንዛቤ ከመሣሪያዎች (tools)፣ እና ማሽኖች በላይ ዘዴዎችን (means)፣ ሂደትን (process) እና ሃሳብን (ideas) የሚያጠቃልል ሲሆን የዚህ የመካከለኛ እና የረጅም ዘመን እቅድ ትግበራ ሲታሰብ አንዱ ወሳኝ ጉዳይ በአንድ በኩል ቴክኖሎጂን የእለት ከእለት ችግሮችን መፍቻ መሣሪያ የማድረግ፣ እና ጠንክሮ ከመስራት ባሻገር እና በበለጠ በጥበብ እና በሥርዓት የመሥራት ባሕል ማስረጽ ነው። የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን በሚያስገኛቸው ጥቅሞች ወይም እድሎች እና የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን በሚፈጠሩባቸው ማሕበረሰብ ባሕል እና እሴቶች መካከል ከፍተኛ መስተጋብር ይስተዋላል። በዕቅድ ዘመኑ ከቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ ርብርብ የሚደረግባቸው ሦስት ዋና ዋና ማሕበራዊ ጉዳዮች ችግርን ከመፍታት የመነጨ ማሕበረሰባዊ የቴክኖሎጂ ፍላጎትን መፍጠር፣ ለኢኖቬሽን የሚያግዙ የቁሳዊ ካፒታል እና የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅም መፍጠር፣ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ፕረቶችን የሚያቅፍ እና የሚያበረታታ ማሕበረሰባዊ መሠረተ - እሴቶች (sympathetic social ethos) መፍጠር ናቸው።

70. ታዳጊ አገራት ጊዜ ያለፈባቸውን ቴክኖሎጂዎች መጠቀም ሳያስፈልጋቸው በርካታ የቴክኖሎጂ ርከኖችን በመዝለል ወደ ቴክኖሎጂ አድማስ ጥግ መድረስ ይችላሉ። ይህን ለማሳካት መሠረታዊ የሚባሉ መነሻዎች ያስፈልጋሉ፤

- መነሻ የሰለጠነ የሰው ኃይል
- መሠረታዊ መሠረተ-ልማት
- መነሻ መሠረታዊ የቴክኖሎጂ ልምምድ
- ተስማሚ የመንግሥት ፖሊሲ

71. በፈጠራ የሚዳብር ቴክኖሎጂ ለማበረታታት

- የግል ጥናት እና ልማት (ሪሰርች እና ዲቨሎፐመንት)
- የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማበረታታት እና መደጎም
- የረቀቁ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ካላቸው አገራት የሚመነጭ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ - ንዋይን ማበረታታት
- በተመረጡ ስትራቴጂካዊ ቴክኖሎጂዎች ላይ የመንግሥት ምርምር እና ልማት ማካሄድ
- ጠንካራ የፈጠራ መብት ጥበቃ ማድረግ
- ከውጭ አገር መንግሥታት፣ ከፍተኛ የምርምር ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በተመረጡ የቴክኖሎጂ ልማቶች ላይ አብሮ መሥራት

72. መረጃ በተለይ ቢግ ዴታ ለዘመኑ የቴክኖሎጂ አድማስ ሽግግር ወሳኝ የዝግጁነት ማረጋገጫ ነው። ሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚሠራው የቢግ ዴታ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ነው።

73. ትምህርት መስፋፋት የሚኖርበት ለቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት እና ምርታማነት ወይም ቅልጥፍና ዓላማ ብቻ ሳይሆን በዘመነ - ዲጂታል ቴክኖሎጂ ያልተማረ የሠራተኛ ኃይል ሥራ ማግኘት ስለሚከብደው እና ሥራ አጥነት ከሚታሰበው በላይ ሊስፋፋ ስለሚችል ነው። ቴክኖሎጂ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ቢሆንም የሠራተኛ እና በአጠቃላይ የማሕበረሰብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጡ ጉዳይ ቀጥተኛ ከመሆን ይልቅ የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ይወስኑታል።

### ዓላማ

74. የሃያ አምሥቱ የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ ዓመቱ ሣይንስ እና የቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ዋና ዓላማ በዋናነት ዓለም አቀፋዊ የቴክኖሎጂ ተስተካካይነት ማረጋገጥ፣ በዚህም የኢኮኖሚ ተስተካካይነት ግቦችን ማሳካት ነው።

75. የሃያ አምሥት ዓመት የቴክኖሎጂ መዳረሻ ዓላማ በየአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች እንዲተገበሩ በተያዙ ንዑስ ዓላማዎች ላይ የሚመሠረት ሲሆን ንዑስ ዓላማዎቹም

- በአንድ ትውልድ ዘመን በማሽን ቴክኖሎጂ፣ በአማራጭ የኃየል አቅርቦት፣ በስትራቴጂካዊ ግብዓት፣ በዘረ መል ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም በዲጂታል ቴክኖሎጂ አስተማማኝ ሽግግር ማድረግ እና መወዳደር፣
- በቀጣዮቹ አሥር ዓመታት በማሽን ቴክኖሎጂ፣ በአማራጭ የኃየል አቅርቦት፣ በስትራቴጂካዊ ግብዓት፣ በዘረ መል ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም በዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ የሚያስችሉ ክልላዊ የኢንዱስትሪ መሠረቶች መጣል፣ እንዲሁም
- በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት በማሽን ቴክኖሎጂ በተለይም በፍብረካ ምህንድስና፣ በአማራጭ የኃየል አቅርቦት በተለይም በኤሌክትሮ ሜካኒካል እና አማራጭ የኃይል ቴክኖሎጂ፣ በስትራቴጂካዊ ግብዓት በተለይም በስትራቴጂካዊ ማዕድናት ልማት ቴክኖሎጂ፣ በዘረ መል ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም በኦቶሜሽን በተለይም በጂታል ቴክኖሎጂ የበቃ የሰው ኃይል ዝግጅት ማድረግ፣ እና
- ለቴክኖሎጂ መሠረት የሚሆን በቴክኖሎጂ የሚያምን በሣይንሳዊ ዕውቀት የበለጸገ ርትዕ ወጣት ትውልድ መፍጠር ናቸው።

## 24.4. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

76. የቴክኖሎጂ ግቦች ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች

- በተግባር ስልጠና የሚደገፍ ብዙሃን ወጣቶችን ያማከለ ሰፊ የፋብሪኬሽን ኢንጂነሪንግ እና ኢኖቬሽን ንቅናቄ የመፍጠር፣
- በከፍተኛ ልዩ የንድፈ-ሃሳብ እና የተግባር ስልጠና፣ የኢንዱስትሪዎች ምርምር እና ልማት (research and development) የሚደገፍ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎች ሽግግር መሠረት የመጣል፣ እና
- የዲጂታላይዜሽን ተወዳዳሪነት ማበልጸጊያ ማዕከል እና የአይቲ ኢንዱስትሪ ልማት የማስፋፋት አቅጣጫዎችን መከተል፣
- ቴክኖሎጂን እና ስልጠናን ከተጨበጠ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ግብ እና ከፕሮጀክቶች ጋር በማስተሳሰር ተተግባሪነቱን ማረጋገጥ፣
- በቴክኖሎጂ ቀዳሚ ዕውቀት እና ተሞክሮ ካላቸው ወዳጅ አገራት ጋር በሽርክና እና በትብብር በሚደረግ መዋዕለ ንዋይ ቴክኖሎጂን በቋሚነት ማሸጋገር፣
- የሣይንስ ትምህርትን ከተግባር ጋር በሚያስተሳስር፣ ችግር ፈቺነትን ማዕከል ባደረገ ንቅናቄ የማሕበረሰብ ባሕል አካል እንዲሆን ንቅናቄ መፍጠር፣
- ልዩ ችሎታዎችን በማሰባሰብ ማነጽ እና ማቆየት የሚችል ተወዳዳሪ የሣይንስ እና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ምርምር ማዕከል ወይም የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋም፣
- በዋናነት የሜካናይዜሽን፣ የኃይል፣ የግብዓት፣ የኦቶሜሽን (ዲጂታላይዜሽን) ቴክኖሎጂዎችን እና ለዚህ ቴክኖሎጂ ሕዝባዊ መሠረት የሚጥል የሣይንስ ዕውቀትን የሚያስተባብር የሣይንስ እና ቴክኖሎጂ መንግሥታዊ ተቋም (ምናልባትም ቢሮ) ማቋቋም ናቸው።

# ምዕራፍ ሃያ አምሥት

# ሰብዓዊ ካፒታል እና የሰው ሀብት ልማት

## 25.1. መነሻ

### ሚና

1. የልማት ወሳኙ ግብዓትም ሆነ የልማት ግብ ሰው ነው። የረጅም ዘመን ኢኮኖሚ ዕድገትን ከሚወስኑት ቁሳዊ ካፒታል፣ እና ቴክኖሎጂ ጋር ሦስተኛው እና ወሳኙ ነገረ-ምርት (factor of production) የሰው ኃይል በተለይም ሰብዓዊ ካፒታል ነው። ሰው የኃይል ምንጭ (ጉልበት) ከመሆን በላይ የለማ ካፒታል እና ቴክኖሎጂን (ዕውቀት እና ሀሳብ) የሚያስገኝ ከምርት ሥርዓት አንጻር ልዕለ ግብዓት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

2. ይፋ በሆኑ የፌደራል ተቋማት መረጃዎች መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል በ2013 የዳሰሳ ጥናት ወቅት ከ23 ሚሊዮን የሚልቅ ሕዝብ የነበረው ሲሆን ይህ ኃይል ለልማት ትልቅ መነሻ አቅም ነው። ነገር ግን፣ የታቀደውን የአሻጋሪ ኢኮኖሚ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ግቦች ዕውን ለማድረግ ከሚጠበቀው ሚና አኳያ የሰው ኃይል በተወዳዳሪ ሰብዓዊ ካፒታል ደረጃ መታነጽ ይኖርበታል። የሰብዓዊ ካፒታል ሚና በሕዝብ ብዛት፣ በተጨባጭ ሣይንሳዊ ዕውቀት፣ በጤና፣ እና በማሕበራዊ ርትዕነት ደረጃዎች ይወሰናል። እነዚህ የሰብዓዊ ካፒታል አምዶች ሲሟሉ ኢኮኖሚው የሚፈልጋቸው ወሳኝ አቅሞች የሚሆኑትን ያህል ያልሰለጠነ የሰው ኃይል በበዛበት ሁኔታ ሠራተኛ ኃይል አቅም መሆኑ ወርቶ ሥራ አጥነትን መቀነስ በራሱ አንድ ፈታኝ ግብ ይሆናል። ለዚህም ሲባል በትምሕርት እና ስልጠና የሚደረጉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ዝግጁነቶች ወሳኝ ይሆናሉ።

### የሕዝብ ብዛት እንደ ሀብት

3. ብዙ ሕዝብ የብዙ መክሊቶች እና ዕውቀት ምንጭ ነው። ዕውቀት ከመሠረታዊ ግንዛቤ እስከ ምጡቅ አዕምሮ ይናኛል። ለተራቀቁ የቴክኖሎጂ አቅሞች የሚሆኑ ጥልቅ ሣይንሳዊ ዕውቀቶች ሊመነጩ የሚችሉት ከጥቂት ባለመክሊቶች ብቻ ነው። የእነዚህን ባለምጡቅ ዓይምሮ ባለቤቶች ትርጉም ባለው መጠን የማግኘት ዕድል የሚሰፋው ከጥቂት ሕዝብ ይልቅ ከብዙ ሕዝብ ነው። ማይምነት በነገሰበት ማሕበረሰብ ውስጥ የሕዝብ ብዛት በውስን ሀብት ፊት ተግዳሮት ቢሆንም፣ በዕውቀት ሲታነጽ እና ከዓለም ሥልጣኔ ጋር ሲተሳሰር የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ብሎም የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ይሆናል። ከዚህ በተያያዘ በተለይ የአማራ ብሔራዊ ክልልም ሆነ ኢትዮጵያ የወጣት ኃይል ቁጥር በዘመን አንዴ ብቻ ከፍተኛ ምጣኔ ለሚደርስበት የስነ-ሕዝብ ሽግግር እየቀረቡ ናቸው። የሥነ - ሕዝብ ሽግግር ትሩፋት (demographic dividend) ከፍ ባለ ደረጃ መረጋገጥ የሚቻለው ይህን ትውልድ በርትዕ ሣይንሳዊ ዕውቀት በማነጽ ነው። በአጠቃላይ በዕውቀት የታነጸ፣ ጤናማ፣ እና ርትዕ ወጣት የሠራተኛ ኃይል ከሥራ ዕድል ጋር ሲገናኝ በአዘቦት ወቅት በኢኮኖሚ ፖሊሲ ከሚገኝ የኢኮኖሚ ልማት በሚልቅ ልማት የሚገለጽ የሥነ ሕዝብ ሽግግር ቱሩፋት ማረጋገጥ ይቻላል።

### ሣይንሳዊ ዕውቀት

4. የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ቴክኖሎጂ የመሆኑን ያህል ቴክኖሎጂ በትምሕርት የሚስፋፋ ዕውቀት የወለደው የሀሳቦች ክምችት ነው። እውቀት ከቁሳዊ ካፒታል በተለየ የማይነጥፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ነው። ዕውቀት ለዕድገት ባለው አስተዋጽዖ ከቁሳዊ ካፒታል የሚለይበት ባሕርያት አሉት፤
   1. የቁሳዊ ካፒታል ሲስፋፋ ተጨማሪ ምርት የመቀነሱን ያህል ዕውቀት በተከማቸ መጠን የበለጠ የዕውቀት ክምችትን በመጥራት እያንዳንዱ ተጨማሪ ዕውቀት የሚያስገኘው ተጨማሪ ምርት እንዲያድግ የማድረግ (increasing returns to scale) ባሕርይ አለው።
   2. ዕውቀት አንዴ ከተፈጠረ በኋላ ከቁሳዊ ካፒታል በተለየ ሁኔታ በተመሳሳይ ጊዜ ለብዙ ዘርፍ ዕውቀትን መጠቀም በቻለ ተዋንያን ሁሉ በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል ይችላል።
   3. ቁሳዊ ካፒታል በአከማቹት ቁጥር በእልቀት የሚፈተነውን እና ተጨማሪ ካፒታል ለማከማቸት እዳ የሚሆነውን ያህል፣ ዕውቀት በአከማቹት ቁጥር ሌላ ዕውቀት ይሻል፣ ሲከማችም ይተባል፤ ቁሳዊ ካፒታል ይተካካል፤ በአንጻሩ ዕውቀት አቻ ይፈልጋል።
   4. በከፍተኛ ደረጃ የተፈጠረ ዕውቀትን ወደታች በማውረድ ተግባራዊ ለማድረግ ይህን የሚተገብር የሰለጠነ የሰው ኃይል ይጠይቃል።

5. እነዚህ ባህርያት ከሰብዓዊ ሀብት የሚገኝ ዕውቀት የማይነጥፍ ሀብት ምንጭ የመሆኑን እውነታ ያጠናክራሉ።

## ጤናማ የሠራተኛ ኃይል

6. ጤንነት እንደ የመጨረሻ ማሕበረሰባዊ ግብ የሚረጋገጠው ሀብት በመፍጠር ሲሆን ሀብትን የሚፈጥር የሠራተኛ ኃይል ደግሞ ጤናማ መሆን አለበት። በዚህ አግባብ ጤና ዋና የልማት ግብ እና ትልቅ የሀብት መፍጠሪያ የሰብዓዊ ካፒታል አቅም ነው። ከሰብዓዊ ካፒታል አኳያ ጤናማ ትውልድ ከተለመደው የጤና ትርጓሜ በዘለለ በደባል ሱሶች ያልተበረዘ እና ያልቆዘመ፣ እንዲሁም በወንጀል እና ሥርዓት አልበኝነት ያልተተበተበ ሊሆን ይገባዋል።

## ርትዕ ሠራተኛ ኃይል

7. ሰብዓዊ ካፒታልን ከቁሳዊ ካፒታል የሚለየው ዋና ባሕርይ ሰብዓዊ ካፒታል እንደ ቁሳዊ ካፒታል በቋሚነት መቆጠር አለመቻሉ እና በምርት ሂደት ሊያስገኘው የሚችለው ውጤት አንጻራዊ መሆኑ ነው። ሰው ሲያደፍጥ አፍራሽ ነው፤ ሰው ሲለግም ምርት ዜሮ ነው፤ ሰው በአዘቦት ጊዜ የተለመደ ውጤት ያስገኛል። ነገር ግን ሰው ሲቆጭ አንዱ እንደ ሺህ ያመርታል፤ የዚህ ዕቅድ ተስፋ ቁጭትን ለልማት የማነጽ ተስፋ ነው።

## የክልሉ የሰብዓዊ ሀብት ሁኔታ

### ስነ ሕዝብ

8. በ2005 የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ (የአሁኑ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት) ትንበያ መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ብዛት የዚህ ዕቅድ መነሻ ዓመት በሆነው 2017 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር) 23,879,000 ነው። ይህ ትንበያ መሠረት ያደረገው የ1999 የሕዝብ ቆጠራ ውጤት፤ የ1992፣ የ1997፣ እና 2003 የሥነ ሕዝብ እና የጤና ዳሰሳ ጥናቶች፣ እንዲሁም የ2004 የድህረ ቆጠራ ዳሰሳ ጥናት (ኢንተርሴንሳል ጥናት) ነው። ነገር ግን፣ ይህ ትንበያ መሠረት ያደረገባቸው መነሻዎች የአማራ ብሔራዊ ክልል በምክንያት ጥያቄ ያነሳባቸው ናቸው። በተለይም የ1999 የሕዝብ ቆጠራ ውጤት በሥነ ሕዝብ ባሕርይ ለመግለጽ ከሚያስቸግሩ ግብታዊ ክስተቶች መካከል የክልሉ ሕዝብ የዕድገት ምጣኔ ከሌሎች ክልሎች በተለየ ሁኔታ መቀነሱ እና በዚህም ምክንያት የክልሉ ሕዝብ ብዛት ከአገር አቀፍ ሕዝብ ያለው ድርሻ በከፍተኛ ምጣኔ መቀነሱ ተጠቃሾች ናቸው።

9. በ1999 የሕዝብ ቆጠራ መሠረት የክልሉ ሕዝብ የዕድገት ምጣኔ ከሌሎች ክልሎች በተለየ ሁኔታ ቀንሷል። የሕዝብ ቆጠራ ውጤቱ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ከ1986 እስከ 1999 በነበሩት ዓመታት በ1.68 በመቶ እንደጨመረ ያሳየ ሲሆን የሕዝብ ብዛቱ በዚህ ዝቅተኛ ምጣኔ ደረጃ ያደገ ሌላ ክልል አልነበረም። በተመሳሳይ ወቅት የአገሪቷ ሕዝብ ያደገበት ምጣኔ 2.49 በመቶ ነበር።

10. ሠንጠረዥ 25-1፤ የክልሎች የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ (%)

| | 1986-1999 | 1999-00 | 2000-01 | 2011-12 |
|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 2.45 | 2.22 | 1.99 | 1.82 |
| አፋር | 2.20 | 2.09 | 3.03 | 2.31 |
| አማራ | 1.68 | 2.35 | 2.17 | 1.59 |
| ኦሮሚያ | 2.86 | 3.09 | 2.84 | 2.42 |
| ሶማሊ | 2.52 | 1.57 | 2.66 | 2.51 |
| ቤጉ | 2.89 | 3.57 | 3.20 | 2.75 |
| ደብብሕ | 2.86 | 2.81 | 2.56 | 2.31 |
| ጋምቤላ | 4.03 | 4.23 | 4.06 | 3.24 |
| ሐረሪ | 2.58 | 3.83 | 3.16 | 2.72 |
| አዲስ አበባ | 1.99 | 1.90 | 2.11 | 2.36 |
| ድሬ ዳዋ | 2.37 | 3.80 | 3.10 | 2.84 |
| **ኢትዮጵያ** | **2.49** | **2.67** | **2.55** | **2.19** |

*ምንጭ፤ የማዕከላዊ ስታትስቲካል ኤጀንሲ (የ1986፣ 1999 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ፤ የ2005 ትንበያ)*

11. የክልሉ ሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔ መቀነስም የክልሉ ሕዝብ ብዛት ከአገር አቀፉ ሕዝብ ብዛት የነበረው ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ አድርጓል። በዚህ ምጣኔ መሠረት የክልሉ ሕዝብ ብዛት ከአገር አቀፍ ሕዝብ ብዛት ድርሻ በ1986 ከነበረው 25.8 በመቶ በ1999 ወደ 23.3 በመቶ የቀነሰ ሲሆን፣ በትንበያው መሠረትም በ2012 ይህ ድርሻ ወደ 22 በመቶ ዝቅ ብሏል።

12. ስዕል 25-1፤ የአማራ ክልል ሕዝብ ብዛት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ያለው ድርሻ በመቶኛ




ምንጭ፡- የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የ1986 እና 1999 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርት፣ የ2005 ትንበያ

13. የ2004 ኢንተርሴንሳል ሪፖርት የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ከ1999 እስከ 2004 ባሉት ዓመታት በዝቅተኛ ምጣኔ 1.9 በመቶ፣ በከፍተኛው ምጣኔ 2.7 በመቶ፣ በናሙናው አማካይ (ፖይንት ኤስቲሜይት) በ2.3 በመቶ እንዳደገ ሪፖርት አድርጓል። የሕዝብ ብዛት ትንበያ በመሠረታዊነት የወሊድ፣ የሞት፣ ወዘተ ምጣኔዎችን ግምት ቢያስገባም በጥቅል በሁለት ጉዳዮች ላይ ይመሠረታል፤ መነሻ የሕዝብ ብዛት እና የዕድገት ምጣኔ። የ2005 ትንበያ የተጠቀመበት የዕድገት ምጣኔ በዳሰሳ ጥናቱ የተገኘውን ከ2.3 በመቶ የሚጀምረውን ሲሆን መነሻ የሕዝብ ብዛት ግን በ1.7 በመቶ ሲያድግ የነበረውን መጠን ነው። በ1999 የክልል የሕዝብ ቆጠራን መሠረት ያደረገው የሕዝብ ብዛት የሚያመላክተው በ1986 እስከ 1999 ሕዝቡ በ1.7 በመቶ ሲያድግ እንደነበረ ሲሆን ይህም ዝቅተኛ ምጣኔ ጥያቄ ቀርቦበታል። ዋናው ጭብጥ በኋላ በኢንተርሴንሳል ጥናት እንደታየው በ1999 እና 2004 መካከል የአማራ ክልል ሕዝብ በአማካይ በ2.3 በመቶ ሲያድግ ከነበረ በቀዳሚዎቹ አሥራ አራት ዓመታት በ1.7 በመቶ እያደገ እንደነበረ ሊያሳይ የሚችል የሥነ ሕዝብ አመክንዮ ሊኖር አለመቻሉ ነው።

14. ስዕል 25-2፤ ወጥ ያልሆነው የማ.ስ.ኤ. የአማራ ሕዝብ የዕድገት ምጣኔ



ምንጭ፡- የማዕከላዊ ስታትስቲካል ኤጀንሲ (የ1986፣ 1999 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ፤ የ2005 ትንበያ)

15. በዚህም ምክንያት የ2005 ትንበያ ባስገኘው የሕዝብ ብዛት እና ከ1986 እስከ 1999 በነበሩት ዓመታት የአማራ ክልል ሕዝብ ቢያንስ ከ1999 በኋላ ባደገበት የ2.3 በመቶ ማደጉን ግምት ውስጥ ያስገባ ማስተካከያ ቢደረግበት ኖሮ ሊሆን በሚችለው የሕዝብ ብዛት መካከል 1999 ላይ የ1.5 ሚሊዮን፣ 2013 ላይ ደግሞ የ2.1 ሚሊዮን ልዩነት ተስተውሏል። ከፊል መፍትሄ ብቻ የሰጠው የ2005 የሥነ ሕዝብ ትንበያ እስከ የ1999 የሕዝብ ቆጠራ የተጠቀመባቸውን እና ጥያቄ የቀረበባቸውን የሥነ ሕዝብ መሠረታዊያን (ፈርቲሊቲ፣ ሎንጀቪቲ ወዘተ) በመጠቀሙ የአማራ ክልል ሕዝብ የዕድገት ምጣኔ ከ2005 በኋላም ከአገር አቀፉ አማካይ በጣም የነሰ እንዲሆን አድርጎታል፤ በዚህም ምክንያት የክልሉ ሕዝብ ብዛት ከአገር አቀፍ ሕዝብ ያለው ድርሻ በከፍተኛ ምጣኔ ቀንሷል።

16. ስዕል 25-3፤ የተተነበየ የክልሎች የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ (በመቶኛ)




ምንጭ፥ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ትንበያን መሠረት በማድረግ የተሰላ

17. ስዕል 25-4፤ የክልሎች የሕዝብ ብዛት ከአገር አቀፍ ሕዝብ ብዛት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ (የተተነበየ)



18. በዚህ ሁኔታ የሕዝብ ብዛትን መሠረት ያደረጉ የልማት ዕቅድ ግቦችን ለዕውነት በቅበ ደረጃ ለማስላት የቅርብ ዓመታት የሥነ ሕዝብ አመልካቾችን መዳሰስ አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል ዳሰሳ ጥናት በተጨማሪ መረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውሏል። በተለይ በ2013 የብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል ጥናት ውጤት  መሠረት በተመሳሳይ ዓመት የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ብዛት ግምት 23,202,770 ነው። ይህ ቁጥር በ2004 ትንበያ በ2013 ይኖራል ተብሎ ከተተነበየው 22,537,000 ሕዝብ በ665,770 ይበልጣል። ይህ ልዩነት የልማት ዕቅዱ ትግበራ በሚጀምርበት 2018 ወደ  1,040,485 ይሰፋል። በሁለቱ መረጃዎች የተሰሉ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔዎቹም በተመሳሳይ ልዩነት ያሳያሉ።

19. ስዕል 25-5፤ የአማራ ሕዝብ ብዛት የዕድገት ምጣኔ በ2005 የሥነ ሕዝብ ትንበያ እና በ2013 የብሔራዊ ሠራተኛ ኃይል የዳሰሳ ጥናት ትንበያ መሠረት




20. ሠንጠረዥ 25-2፤ የአማራ ሕዝብ ብዛት የዕድገት ምጣኔ በልማት ዕቅድ ዘመን (በ2005 የሥነ ሕዝብ ትንበያ እና በ2013 የብሔራዊ ሠራተኛ ኃይል የዳሰሳ ጥናት ትንበያ መሠረት ንጽጽር)

| የልማት ዕቅድ ዘመናት | የ2005 ትንበያ | በ2013 የሰው ኃይል ዳሰሳ ጥናት መረጃ የተከለሰ |
|---|---|---|
| 2018-2022 | 1.31 | 1.55 |
| 2023-2027 | 1.18 | 1.39 |
| 2028-2032 | 1.05 | 1.24 |
| 2033-2037 | 0.95 | 1.12 |
| 2038-2042 | 0.86 | 1.01 |

21. ለሃያ አምሥት ዓመት የልማት ፍኖተ ካርታ እና ለተከታታይ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች ግብዓትነት የዋለው የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ እና ብዛት በ2013 የብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል እና ፍልሰት ዳሰሳ ጥናትን መሠረት በማድረግ የተከለሰው ነው።

## የሠራተኛ ኃይል

22. በ2013 የብሔራዊ ሠራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ጥናት መሠረት በ2013 ከነበረው  የአማራ ብሔራዊ ክልል 23,202,770 ሕዝብ መካከል ዕድሜው 10 ዓመት እና በላይ የሆነ ሕዝብ ብዛት 17,597,652፣ ወይም የአጠቃላይ ሕዝቡን 75.8 በመቶ ነበር። ከዚህ ሕዝብ መካከልም የኢኮኖሚ ተሳትፎ ዝግጁነት የነበረው

ሕዝብ (economically active population) ብዛት 11,968,296 የነበረ ሲሆን በዕድሜ ክልሉ ካለው ሕዝብ የነበረው ምጣኔ (activity rate) 68 በመቶ ነው። ይህ የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ ከ64.7 በመቶ አገር አቀፍ ምጣኔ የላቀ ነው። የክልሉ የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ በገጠር 68.3 በመቶ፣ በከተማ ደግሞ 66.7 በመቶ ነው። በጾታ ረገድ የወንዶች የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ 77.7 በመቶ ሲሆን፣ የሴቶች ለሥራ ዝግጁነት ምጣኔ 58.4 በመቶ ነው። የገጠር የወንዶች የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ ከከተማው ምጣኔ የሚበልጥ ሲሆን፣ የከተማ የሴቶች የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ ደግሞ ከገጠሩ ምጣኔ ይበልጣል። የሴቶች የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ ከወንዶች የሥራ ዝግጁነት ምጣኔ፣ እንዲሁም የገጠር ሴቶች የኢኮኖሚ ተሳትፎ ዝግጁነት ምጣኔ ከከተማው ምጣኔ ለማነሱ አንዱ ምክንያት በአብዛኛው የገጠር ሴቶች ወደ ትዳር በመግባት ከሠራተኛ ኃይል ማዕቀፍ ውጪ ስለሚሆኑ ነው።

23. በኢኮኖሚ ተሳትፎ ዝግጁነት ረገድ የሚታዩ ጉልህ ጉዳዮች፤
    1. የኢኮኖሚ ተሳትፎ ዝግጁነት ምጣኔ በ10-14 ዕድሜ ክልል ዝቅተኛ ምጣኔ ጀምሮ እስከ 35 – 39 የዕድሜ ክልል ይጨምራል፣ ከዚህ ዕድሜ ክልል በኋላ በተዋረድ ይቀንሳል፤ በአጠቃላይ ከ25 እስከ 59 ዓመት ዕድሜ ክልል የኢኮኖሚ ተሳትፎ ከፍተኛ ነው።
    2. የሴቶች የኢኮኖሚ ተሳትፎ ዝግጁነት ምጣኔ በከተማም ሆነ በገጠር ከወንዶች ምጣኔ ያነሰ ነው።
    3. ዕድሜአቸው ከ10 እስከ 19 የሚደርሱ 2,439,923 ወጣቶች ለሥራ ዝግጁ መሆናቸው፣ ከእነዚህ መካከልም 2,325,559 የሚሆኑት በሥራ ላይ ያሉ፣ 114,364 ያህሉ ደግሞ ሥራ ፈላጊ መሆናቸው አብዛኛዎቹ በትምሕርት ገበታ ላይ መገኘት የነበረባቸው መሆኑን ያመላክታል።

24. ሠንጠረዥ 25-3፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ የሥራ ተሳትፎ ደረጃ (በመቶኛ)

| | **ጠቅላላ** | | | **ከተማ** | | | **ገጠር** | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የዕድሜ ክልል | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት |
| **10 ዓመት እና በላይ** | **68.0** | **77.7** | **58.4** | **66.7** | **74.0** | **60.5** | **68.3** | **78.6** | **57.8** |
| 10-14 | 40.8 | 46.6 | 35.1 | 13.7 | 14.0 | 13.3 | 45.0 | 51.6 | 38.5 |
| 15-19 | 54.1 | 57.5 | 50.3 | 35.5 | 35.0 | 35.9 | 58.5 | 61.5 | 54.9 |
| 20-24 | 76.2 | 81.5 | 71.1 | 74.1 | 73.4 | 74.5 | 77.0 | 83.5 | 69.4 |
| 25-29 | 84.1 | 95.1 | 74.7 | 87.0 | 97.1 | 79.3 | 82.8 | 94.3 | 72.4 |
| 30-34 | 85.0 | 97.7 | 73.6 | 91.2 | 97.4 | 83.5 | 82.6 | 97.8 | 70.6 |
| 35-39 | 85.1 | 98.5 | 74.3 | 89.9 | 97.6 | 83.0 | 83.6 | 98.8 | 71.8 |
| 40-44 | 83.2 | 97.1 | 68.0 | 87.0 | 96.6 | 74.5 | 82.3 | 97.2 | 66.7 |
| 45-49 | 83.9 | 98.7 | 69.7 | 88.7 | 98.3 | 79.9 | 83.0 | 98.8 | 67.7 |
| 50-54 | 82.0 | 96.3 | 69.1 | 77.5 | 96.1 | 61.5 | 82.9 | 96.4 | 70.6 |
| 55-59 | 75.6 | 94.2 | 52.4 | 73.9 | 92.4 | 51.0 | 75.9 | 94.5 | 52.7 |
| 60-64 | 72.6 | 93.6 | 49.5 | 53.4 | 77.3 | 34.7 | 75.1 | 95.3 | 51.9 |
| 65+ | 44.8 | 63.8 | 18.8 | 36.9 | 56.5 | 18.9 | 46.1 | 64.7 | 18.8 |
| **15-29** | **69.7** | **75.2** | **64.4** | **67.0** | **71.1** | **64.3** | **70.6** | **76.3** | **64.4** |
| **15-64** | **76.3** | **86.5** | **66.5** | **75.7** | **84.3** | **68.6** | **76.5** | **87.0** | **65.8** |

ምንጭ፤ የ2013 የብሔራዊ ሠራተኛ ኃይል እና የፍለሰት ዳሰሳ ጥናት፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት

25. በሌላ በኩል፣ ዕድሜው 10 እና በላይ ከሆነው ሕዝብ መካከል 5,629,356 ወይም የዕድሜ ክልሉን 32 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ለሥራ ዝግጁ ያልሆነ (economically inactive) ሕዝብ ነበር። ለሥራ ዝግጁ ካልሆኑት ዜጎች መካከል 65.3 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። በአገር አቀፍ ደረጃም ለሥራ ዝግጁ ካልሆኑ ዜጎች ውስጥ 61.5 በመቶ ሴቶች ናቸው። ለሥራ ዝግጁ ላለመሆን ከተጠቀሱት ምክንያቶች መካከል በትምሕርት ገበታ ላይ መገኘት ዋናው ምክንያት ሲሆን የክልሉን ለሥራ ዝግጁ ያልሆኑ ዜጎች 51.1 በመቶ ይሸፍናል። በጾታ ረገድ 72.7 በመቶ የሚሆኑት ለሥራ ዝግጁ ያልሆኑ የክልሉ ወንዶች እና 39.9 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች በትምሕርት ላይ የሚገኙ ናቸው። ለሥራ ዝግጁ ላለመሆን ሁለተኛው ከፍተኛ ምክንያት ለራስ ፍጆታ

በሚውል የቤት ውስጥ ሥራ መሰማራት ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ለሥራ ዝግጁ ያልሆኑ የክልሉ ዜጎች ውስጥ 21.7 በመቶ፣ በተለይም ከሴቶች መካከል 32 በመቶ ይሸፍናል።

26. ሠንጠረዥ 25-4፤ ከ10 ዓመት ዕድሜ በላይ ሆነው ለሥራ ዝግጁ ያልሆኑ (inactive population) ዜጎች ስርጭት በምክንያት

| | | አማራ ብሔራዊ ክልል | | | ኢትዮጵያ* | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት |
| | ጠቅላላ ብዛት | 5,629,356 | 1,952,461 | 3,676,895 | 24,718,714 | 9,524,359 | 15,194,355 |
| የምክንያቶች ድርሻ (%) | የቤት ውስጥ ሥራ | 21.7 | 2.3 | 32.0 | 19.2 | 4.3 | 28.5 |
| | እርግዝና | 4.0 | 0.0 | 6.1 | 4.5 | 0.0 | 7.4 |
| | ትምሕርት | 51.1 | 72.7 | 39.7 | 54.1 | 71.7 | 43.1 |
| | አካል ጉዳት | 1.1 | 2.0 | 0.6 | 1.2 | 1.7 | 1.0 |
| | ሕመም | 6.7 | 6.9 | 6.7 | 4.1 | 4.5 | 3.8 |
| | የዕድሜ ማነስ | 4.8 | 6.3 | 4.0 | 6.4 | 7.7 | 5.6 |
| | የዕድሜ መግፋት | 9.6 | 8.3 | 10.3 | 8.6 | 7.1 | 9.5 |
| | ጡረታ | 0.1 | 0.1 | 0.1 | 0.4 | 0.6 | 0.3 |
| | የሃዋላ ገቢ | 0.1 | 0.2 | 0.0 | 0.4 | 0.5 | 0.3 |
| | ኮቪድ-19 | 0.0 | 0.0 | 0.0 | 0.1 | 0.1 | 0.1 |
| | ሌላ | 0.7 | 1.2 | 0.5 | 1.0 | 1.9 | 0.4 |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 ብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል እና ፍልሰት ዳሰሳ ጥናት
*የትግራይ ብሔራዊ ክልል መረጃን አይጨምርም።

27. ከ10 – 14 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች እና ከ15 – 19 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ወጣቶች በትምሕርት ገበታ ላይ መገኘት ያለባቸው ሲሆን፣ በትዳር ምክንያት ከሠራተኛ ኃይል የሚወጡ ሴት ወጣቶች ጉዳይ የትምሕርት እና የሥራ ተሳትፎአቸውን ማሳደግ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው በተጨማሪ ለዘላቂ የሥነ ሕዝብ ምጣኔ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

28. ለሥራ ዝግጁ ከሆነው ሕዝብ መካከል 11,076,385 ወይም (92.5 በመቶ) በሥራ ላይ የሚገኝ ሲሆን ቀሪው 891,911 (7.5 በመቶ) ሥራ ፈላጊ ነው። በሥራ ላይ ከሚገኘው የሰው ኃይል መካከል 82.5 በመቶ የሚሆነው በገጠር አካባቢ የሚኖር ነው። በጾታ ረገድ፣ 58.6 በመቶ የሚሆኑት የክልሉ ሠራተኞች ወንዶች ናቸው። የሴቶች የሥራ ተሳትፎ ከገጠር ይልቅ በከተሞች የተሻለ ነው፤ በሥራ ላይ ከሚገኘው የሰው ኃይል መካከል የሴቶች ድርሻ በከተሞች 44.9 በመቶ ሲሆን፣ በገጠር ደግሞ 40.7 በመቶ ነው። ለገጠር የሴቶች የሥራ ስምሪት ድርሻ ከወንዶች አንጻር ማነስ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች በትዳር ምክንያት ከሠራተኛ ኃይል ማዕቀፍ ውጪ መሆን እና ከወንዶች የበለጠ የሥራ አጥነት ምጣኔ ናቸው።

29. በ2013 የሠራተኛ ኃይል ዳሰሳ ጥናት መሠረት የክልሉ የሥራ አጥነት ምጣኔ ከ10 ዓመት እና በላይ ላለው ለሥራ ዝግጁ የሆነ ሠራተኛ ኃይል 7.5 በመቶ ሲሆን በጾታ ረገድ የወንዶች ምጣኔ 4.7 በመቶ፣ የሴቶች ደግሞ 11 በመቶ ነበር። የክልሉ የሥራ አጥነት ምጣኔ በከተማ በሁለቱም ጾታዎች 17.9 በመቶ፣ በወንዶች 11.3 በመቶ፣ እና በሴቶች 24.9 በመቶ ነበር። የገጠር የሥራ አጥነት ምጣኔ 4.9 በመቶ ሲሆን ነገር ግን በሥራ አጥ ብዛት የገጠሩ ከከተማው በ42,291 ይበልጣል።

30. ከ15- 64 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ካለው የክልሉ የሠራተኛ ኃይል፣ የሥራ አጥ ምጣኔ በሁለቱም ጾታዎች 8.3 በመቶ፣ በወንዶች 5 በመቶ፣ እና በሴቶች 12.4 በመቶ ነበር። በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በሁለቱም ጾታዎች 18.3 በመቶ፣ በወንዶች 11 በመቶ፣ በሴቶች ደግሞ 25.6 በመቶ ሲሆን፣ የገጠር የሁለቱም ጾታዎች የሥራ አጥነት ምጣኔ 5.4 በመቶ ነበር።

31. ከ15 – 29 ዕድሜ ክልል ውስጥ ካለው ወጣት የሰው ኃይል መካከል 11.7 በመቶ የሚሆነው ሥራ ፈላጊ የነበረ ሲሆን የሴቶች ሥራ አጥነት ምጣኔ (16 በመቶ) የወንዶችን የሥራ አጥነት ምጣኔ (7.9 በመቶ) እጥፍ ነበር። የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ በከተማ በሁለቱም ጾታዎች 23.6 በመቶ፣ በገጠር ደግሞ 8 በመቶ ነበር። የከተማ ሥራ አጥነት ምጣኔ ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች የመቅጠር አቅም ውስንነትን የሚያመላክት ሲሆን፣ በተለይ የገጠር የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ የቤተሰብ ግብርና ባለበት ሁኔታ ከፍተኛ መሆኑ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

32. ሠንጠረዥ 25-5፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የሥራ አጥነት ምጣኔ በዕድሜ ክልል እና በጂኦግራፊ (በመቶኛ)

| የዕድሜ ክልል | ክልል አቀፍ | | | ከተማ | | | ገጠር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት | ሁለቱም ጾታዎች | ወንድ | ሴት |
| **10 ዓመት እና በላይ** | **7.5** | **4.7** | **11.0** | **17.9** | **11.3** | **24.9** | **4.9** | **3.3** | **7.0** |
| 10-14 | 2.8 | 3.51 | 1.9 | 12.2 | 15.2 | 8.9 | 2.4 | 3.0 | 1.6 |
| 15-19 | 8.7 | 7.2 | 10.7 | 20.8 | 18.9 | 22.1 | 7.0 | 6.0 | 8.4 |
| 20-24 | 14.4 | 9.6 | 19.9 | 32.1 | 23.5 | 36.9 | 8.5 | 6.7 | 11.0 |
| 25-29 | 11.8 | 7.0 | 16.9 | 18.7 | 11.8 | 25.0 | 8.5 | 5.0 | 12.5 |
| 30-34 | 6.6 | 3.2 | 10.7 | 13.8 | 6.3 | 24.8 | 3.5 | 1.6 | 5.6 |
| 35-39 | 6.0 | 2.6 | 9.7 | 13.0 | 7.0 | 19.4 | 3.7 | 1.1 | 6.4 |
| 40-44 | 5.9 | 3.7 | 9.2 | 13.4 | 7.2 | 24.1 | 4.1 | 2.9 | 5.9 |
| 45-49 | 4.5 | 1.5 | 8.5 | 13.8 | 9.8 | 18.3 | 2.6 | 0.0 | 6.3 |
| 50-54 | 6.1 | 4.4 | 8.3 | 15.2 | 11.0 | 20.8 | 4.5 | 3.2 | 6.1 |
| 55-59 | 3.5 | 2.3 | 6.2 | 10.1 | 8.0 | 15.0 | 2.4 | 1.3 | 4.7 |
| 60-64 | 4.0 | 2.2 | 7.8 | 15.2 | 13.0 | 19.0 | 3.0 | 1.2 | 6.6 |
| 65+ | 2.9 | 3.3 | 0.7 | 10.2 | 12.4 | 3.9 | 1.9 | 2.3 | 0.0 |
| **15-29** | **11.7** | **7.9** | **16.0** | **23.6** | **16.3** | **29.0** | **8.0** | **5.9** | **10.6** |
| **15-64** | **8.3** | **5.0** | **12.4** | **18.3** | **11.1** | **25.6** | **5.4** | **3.5** | **8.0** |

ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2013 ብሔራዊ የሠራተኛ ኃይል እና ፍልሰት ዳሰሳ ጥናት

## የምርታማነት ግቦች እና የሰው ኃይል ፍላጎት

33. የረጅም ዘመን የሰው ኃይል ፍላጎት መነሻ ምርታማነት እና ቅልጥፍና ነው። ጥቅል የሰው ኃይል ፍላጎትን ለመወሰን እንደ መነሻ የሚወሰዱ ሁለት ክልላዊ ዕውነታዎች፤

1. እንደ አገር አቀፉ ሁሉ የክልሉ ሠራተኛ ኃይል ምርታማነት ከዓለም አቀፍ የሠራተኛ ምርታማነት አኳያ ዝቅተኛ መሆኑ፣ እና
2. ቢያንስ ባለፉት ስድስት አሥርት ዓመታት በፊት ከነበረው የኢትዮጵያ ግብርና ዘርፍ የሠራተኛ ምርታማነት እንጻር በአሁኑ ወቅት በገጠር ከሚገኘው የዘርፉ የሰው ኃይል ከሁለት - ሦስተኛ በላይ የሚሆነው በስውር ሥራ አጥነት ሊካተት የሚችል ትርፍ ሠራተኛ መሆኑ ናቸው።

34. በኢትዮጵያም ሆነ በአማራ ብሔራዊ ክልል አብዛኛው የሰው ኃይል የተሰማራበት መስክ ግብርና እንደመሆኑ እና የዘርፉ ምርታማነትም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ እንደመሆኑ መጠን በዓለም አቀፍ የሰው ኃይል ምርታማነት መስፈርት አሁን ያለው የሰው ኃይል በቀጣዮቹ ዓመታት የታሰበውን ፈጣን ዕድገት ለማረጋገጥ በቂ ነው። በሥራ ላይ ያለው ሠራተኛ እንደ አሜሪካ አማካይ ሠራተኛ ከሠራ አሁን የሚያመርተውን ምርት ሃያ ስድስት እጥፍ፣ እንደ ቻይና አማካይ ሠራተኛ ከሠራ ደግሞ አሁን በማምረት ላይ ያለውን ምርት ሰባት እጥፍ ማምረት ይችላል። ነገር ግን፣ የሠራተኛ ምርታማነት ከመዋቅራዊ ለውጥ፣ ከካፒታል- ሠራተኛ ጥምርታ እና ከሰው ኃይል ሥልጠና ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚው የሚጠቀመው የሰው ኃይል በብዛት ላይ የተመሠረተ መሆኑ አይቀርም። የፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ዋና የትኩረት አቅጣጭ ቅልጥፍና እና ምርታማነትን ማሳደግ ነው ሲባል የሠራተኛ ምርታማነትን ማሳደግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጣዮቹ

አምሥት ዓመታት የሽግግር ወቅት በ2.7 በመቶ ምጣኔ የሚያድግ የሠራተኛ ኃይል ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማለት በቀጣዩ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ መጨረሻ እስከ 12.6 ሚሊዮን የሚደርስ ሠራተኛ በኢኮኖሚ ውስጥ እንደሚያስፈልግ ወይም እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ በተከታዮቹ ሃያ ዓመታት የሚኖረው የሠራተኛ መጠን በመዋቅራዊ ሽግግር ስኬት ደረጃ የሚወሰን ሲሆን በተለይ የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የወጪ ፍልሰት መቀነስ፣ እና የገቢ ፍልሰት መጨመር የሚፈጥሩት የሥራ ፈጠራ ግብ የሠራተኛ ፍላጎትን መጠን ከቅልጥፍና ግብ በላይ ሊያሳድጉት እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

## የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ እና የዘርፎች የሰው ኃይል ስምሪት

35. የዘርፎችን የረጅም ጊዜ የሰው ኃይል ፍላጎት የሚወስነው የመዋቅራዊ ለውጥ ግብ ነው፡፡ በቀጣዮቹ ሃያ አምሥት ዓመታት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በጥቅሉ ከገጠር ወደ ከተማ፣ በዘርፍ ረገድም ከግብርና ወደ አምራች ኢንዱስትሪ እና ዘመናዊ አገልግሎት ዘርፎች ሽግግር እንዲያደርግ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች የሰው ኃይል ድርሻ በ2013 ከነበረበት 66.4 በመቶ በ2042 ወደ 30 በመቶ እንዲቀንስ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች የሰው ኃይል ድርሻ በ2013 ከነበሩበት፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው 3.3 በመቶ እና 27.7 በመቶ በ2042 ወደ 21 በመቶ እና 43.9 በመቶ እንዲጨምሩ ይጠበቃል፡፡

36. ሠንጠረዥ 25-6፤ የዘርፎች የሰው ኃይል ስምሪት ድርሻ ከአጠቃላይ የሰው ኃይል (በመቶኛ)

| | 2013 | 2022 | 2027 | 2032 | 2037 | 2042 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 66.4 | 57.1 | 52.5 | 46.0 | 37.4 | 30.0 |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 3.3 | 6.9 | 10.3 | 14.9 | 17.5 | 21.0 |
| ሌሎች ኢንዱስትሪዎች | 2.8 | 3.4 | 3.8 | 4.3 | 5.2 | 5.1 |
| አገልግሎት | 27.5 | 30.4 | 31.7 | 33.6 | 38.0 | 43.9 |

## የሰው ኃይል አቅርቦት

37. የልማት ዕቅዱን ለማሳካት ከሚያስፈልገው የሰው ኃይል ውስጥ በአቅርቦት በኩል የሚጠበቀው ክፍተት የሰለጠነ የሰው ኃይል ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ለተፈጠረው የተማረ ወጣት ሥራ አጥ ከትምህርት ፖሊሲ ክፍተት ይልቅ ለተማረው ወጣት በተማረበት ዘርፍ በቂ የሥራ መስክ ኢኮኖሚው መፍጠር አለመቻሉ ዋና ምክንያት ነው፡፡ በዚህ የልማት እቅድ የትግበራ ወቅት የትምህርት እና የስልጠና የትኩረት አቅጣጫዎች ትምህርት እና ስልጠና በዕቅዱ ከተያዘው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የኢኮኖሚውን የዕድገት ፍጥነት እንዲመሩ የተለዩ ዘርፎች በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ የሰው ኃይል ይፈልጋሉ፡፡ ዕውቀት በተከማቸበት የሚከማች በመሆኑ በቴክኖሎጂ የገፉ አገራት ተርታ የመስተካከል ግብ ሊሳካ የሚችለው ዕውቀትን በሁሉም ዘርፍ አዲስ ቴክኖሎጂ በመፍጠር ተግባር ላይ በማሰማራት ሳይሆን የስልጠና ትኩረትን ለቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያግዝ መልኩ በመቃኘት ይሆናል፡፡ የሥልጠና ተቋማት በተማከለ እና የዘርፎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ፣ የዘርፎችን የማሰልጠን ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ ይተገበራል፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

38. የሰብዓዊ ሀብት እና የሠራተኛ ኃይል የትኩረት አቅጣጫ
    1. በሃያ አምሥት ዓመት ሂደት ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ዓይነት እና መጠን በበቂ ሁኔታ ማፍራት፣ ይህም ከ4.0 በመቶ የሥራ አጥነት ምጣኔ ግብ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ትኩረት መስጠት፣
    2. ዋና ቀጣሪ የግል ዘርፉ መሆኑን ማረጋገጥ፣
    3. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ ክህሎት እና እውቀትን በተግባር ሥልጠና፣ እና በቅጥር ሥርዓታቸው እንዲያበረታቱ ማድረግ፥
    4. የስልጠና ዓይነት፣ ስምሪት፣ እና ጥራት ከዕቅዱ የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ እና ግቦች ጋር እንዲጣጣም ከዘርፎች ፍላጎት አንጻር በጋራ ማቀድ እና መተግበር፣
    5. የባለ ሦስት ደረጃ የስልጠና ሥርዓት ማስፈን፤

- ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግር የማድረግ፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ሀሳብ የማፍለቅ እና የማበልጸግ ሚና ያለው ዝንባሌው፣ አቅም እና ክህሎቱ ያላቸው ወጣቶች ከትምሕርት ቤቶች ተመርጠው የሚሰለጥኑበት ከሁለት እስከ ሦስት በሚደርሱ የክልሉ አካባቢዎች ፋካልቲዎች የሚኖሩት አንድ ታላቅ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋም፣
- የመካከለኛ ደረጃ የቴክኒክ ባለሙያዎች የሚያሰለጥኑ ቁጥራቸው የተመጠነ ልዩ ፖሊቴክኒኮች ማደራጀት፣ እና
- በልዩ ልዩ ንዑስ ዘርፎች እና ንዑሰ-ንዑሳን ዘርፎች የሙያ፣ የቴክኒክ፣ እና ቮኬሽናል ተግባራዊ ስልጠና እንደ የአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚሰጥባቸው ማዕከላት ማደራጀት።

6. የልማት ዘርፎች በእውቀት እና ክህሎት ይመሩ ዘንድ ስልጠናን ከዘርፎች ልዩ ፍላጎት ጋር ማጣጣም፣
    - ለዘመናዊ ግብርና የሚሆን የሰው ኃይል ማዘጋጀት፣
    - በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በኮንስትራክሽን እና ሌሎች ልዩ ልዩ የከተማ እና የገጠር ኢንተርፕራይዞች የሚሆን የሰው ኃይል አቅም መፍጠር፣
    - በቴክኖሎጂ፣ በተለይም በፋብሪኬሽን ምህንድስና እና ዲጂታል ቴክኖሎጂ ጥልቅ ሥልጠና አትኩሮ መሥራት።
7. ሥልጠናን ልምድ ከውጭ ከማሸጋገር ግብ ጋር ማቀናጀት፣ በመንግሥት እና በግል ዘርፍ ትብብር የመዋቅራዊ ለወተግባር ተኮር ማድረግ፣
8. የተበታተኑ የተናጠል ሥልጠናዎችን በማዕከል መምራት እና መግራት።

## ክፍል ስድስት

# የልማት ፋይናንስ

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሃያ ስድስት | **መዋዕለ ንዋይ፣ ቁጠባ እና የፋይናንስ ዘርፍ ልማት** |
| ምዕራፍ ሃያ ሰባት | **የመንግሥት ፋይናንስ** |

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

# መዋዕለ ንዋይ፣ ቁጠባ እና የፋይናንስ ዘርፍ ልማት

## 26. 1. መነሻዎች

### ሚና

1. **መዋዕለ-ንዋይ (investment) የዕቅዱ ማስፈጸሚያ እና ማረጋገጫ ዋና መሣሪያ ነው።** የዕቅዱ ግንባር ቀደም ግብ ፈጣን እና ዘላቂ (የነፍስ ወከፍ) ኢኮኖሚ ዕድገት ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጩ በመካከለኛ ጊዜ የነፍስ ወከፍ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ካፒታል ዕድገት፣ በረጅም ጊዜ ደግሞ ቴክኖሎጂ ዕድገት ነው። የቴክኖሎጂ አቅም የሀሳቦች ክምችት፣ የቴክኖሎጂ ዕድገትም የሀሳቦች ዕድገት ነው። ቁሳዊም ሆነ ሰብዓዊ ካፒታል የሚፈጠረው፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂን በፈጠራ ለማሳደግ በምርምር የሚተጉ ዜጎች ማፍራት የሚቻለው በመዋዕለ ንዋይ ነው። ከአሻጋሪ ዕድገት አንጻር የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት የሚሰነው በመዋዕለ ንዋይ ስምሪት በሚረጋገጥ መዋቅራዊ ለውጥ ነው።

2. **መዋዕለ ንዋይ የስትራቴጂካዊ ውሳኔዎች እና የፖሊሲ ግብ ማስፈጸሚያ መሣሪያም ነው።** የኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ አፍታ አለው፤ ፈጥኖ ሀብትን ወደ ልማት በማስገባት መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም የመቼ እና እንዴት ጥያቄዎች የሚመለሱት በፈጣን የመዋዕለ-ንዋይ ውሳኔ ነው። መዋዕለ ንዋይ በልቶ ከማደር በላይ ለሆኑ የሉዓላዊነት፣ እኩልነት፣ ኃያልነት ግቦች ማረጋገጫ መሣሪያ ነው። በአጭር የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ መዋዕለ ንዋይ-የጥቅል ኢኮኖሚ መዛባት ምንጭም መፍትሄም ሊሆን ይችላል፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል እና ገቢ መፍጠሪያ፣ በሂደቱም የማክሮ ኢኮኖሚ ማትጊያ ሆኖ ያገለግላል። መዋዕለ-ንዋይ የገንዘብ ፖሊሲ ከገንዘብ ኢኮኖሚው ውጪ ባሉ ዘርፎች (አምራች እና አገልግሎት ዘርፎች) ተጽዕኖ ለመፍጠር (transmission mechanism) ዋናው ድልዲይ ነው። ስለዚህ መዋዕለ -ንዋይ ከአጭር ጊዜ የፖሊሲ መሣሪያነት እስከ የረጅም ዘመን የዕድገት ምንጭነት ምን፣ ለማን፣ ስንት፣ ለምን፣ በማን፣ መቼ፣ የት፣ እና እንዴት የዕቅድ ጥያቄዎች መልስ መስጪያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል።

3. **ጥራት ያለው መዋዕለ ንዋይ ጥራት ያለው አገራዊ ቁጠባ ያስፈልገዋል።** መዋዕለ-ንዋይ በአንድ ወቅት ከተመረተው ገቢ ውስጥ የፍጆታ ወጪን በመቀነስ ስለነገ የማሕበራዊ ደህንነት እና ኢኮኖሚያዊ አቅም የዛሬን ምቾት ቀንሶ የማምረቻ አቅሞችን ወይም ካፒታል ለመጨመር የሚደረግ ወጪ ነው። ይህ ማለት ጥራት ያለው መዋዕለ ንዋይ ጥራት ያለው ቁጠባ ያስፈልገዋል።

4. **ለኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያላቸው የአጭር እና የረጅም ጊዜ የፋይናንስ ምንጮች ቢኖሩም የዘላቂ ፋይናንስ ምንጭ አገራዊ ቁጠባ ነው።** የቤተሰብ ወይም ግለሰቦች ቁጠባ፣ የግልቢዝነሶች ቁጠባ፣ የማሕበራት ቁጠባ፣ የመንግሥት ቁጠባ፣ እንዲሁም ብድር እና እርዳታ የልማት ፋይናንስ ምንጮች ናቸው። በመሠረቱ አበዳሪ እና እርዳታ ሰጪ በሌለበት ሁኔታ ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍጆታ (consumption) መታቀብ ነው። ብድር እና እርዳታም ጥቅም ላይ ሲውል ዞሮ ዞሮ በሌላ አገር አንድ አካል ከፍጆታ የተረፈው ወይም የቆጠበው (foreign saving) ነው። የዝቅተኛ ገቢ - ዝቅተኛ ቁጠባ - ዝቅተኛ መዋዕለ ንዋይ- ዝቅተኛ ምርታማነት - ዝቅተኛ ገቢ የድህነት አዙሪት ለመስበር ስትራቴጂካዊ መንገድ ጥራት ያለው ቁጠባ ማረጋገጥ እና መዋዕለ ንዋይን ምርታማ በማድረግ ወይም ምርታማ በሆኑ ዘርፎች ላይ በማዋል ነው። ቁጠባው ሁሉ መዋዕለ-ንዋይን ባያረጋግጥም መዋዕለ-ንዋይ ግን የግድ ቁጠባ ይፈልጋል። በክልሉ ክልል አቀፍ የቁጠባ መጠን መረጃ ባይኖርም በአገር አቀፍ ደረጃ በመጠኑም በጥራቱም ውስን ነው። ለአለፉትት 15 ዓመታት ፈጣን ዕድገት አገራዊ ቁጠባ የማይናቅ ሚና ቢጫዎትም በወሳኝነት ግን የውጭ ብድር እና እርዳታ ሚና ጉልህ ነበር። እንደ ዘርፉ ጥናት ብድር እና ርዳታ በታዳጊ አገራት ልማት ላይ ያመጣው ለውጥ ያልታየው አብሮት የሚመጣ አሳሪ ቅድመ ሁኔታ መኖሩ፣ የአገር ውስጥ ቁጠባን የሚያዘናጋ በመሆኑ፣ በዚህም ምክንያት ብድር እና እርዳታ ሲቆም እድገት የሚቆም በመሆኑ፣ እንዲሁም በራስ ጥረት ያልተገኘ ሀብት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አገራት ለምርታማነት የሚኖራቸው ትኩረት ዝቅተኛ ስለሚሆን፣ በውጤቱም የተፈለገውን ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ስለማያረጋግጥ ነው። ነገር ግን እርዳታ እና ብድርን እንደ መራር መዲሃኒት ወስዶ ለአሻጋሪ ዕድገት በብልሃት ማዋል እንደሚቻል የደቡብ ኮሪያ ተሞክሮ ያሳያል። ይህም ሆኖ የዘላቂ ዕድገት ምንጩ አገራዊ ቁጣባ ነው።

5. **የፋይናንስ ተቋማት የአስተማማኝ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጫ ተቋማት ናቸው።** የፋይናንስ ተቋማት ቀዳሚ ሚና የተበታተነ የግለሰቦች እና የቢዝነስ ቁጠባን በማሰባሰብ ትርጉም ባለው መዋለ ንዋይ ለሚያፈሱ

ባለመከሊት አልሚዎች በብድር መልክ ፋይናንስን ማሳለጥ ነው። መዋዕል ንዋይ በባሕርይው ሥጋት ያለበት መስክ ነው። አልሚዎች ስጋትን በመፍራት ተገቢ መዋዕለ ንዋይ ከማፍሰስ እንዳይታቀቡ የፋይናንስ ተቋማት ዋስትና (insurance) በመስጠት አልሚዎችን ያደፋፍራሉ።

6. **በአማራ ክልል ደረጃ የፋይናንስ ተቋማት ሚና በየግለሰቦች እና ቢዝነስ እጅ የሚገኝ የተበታተነ ሀብት ከማሰባሰብ ግብ ያለፈ ነው።** በክልል እና በአገር አቀፍ የሚኖረው አብዛኛው ማሕበረሰብ ከኢኮኖሚ መዋቅሩ በመነሳት ሀብት የሚቆጥበው በእህል እና ጥራጥሬ፣ በእንስሳት፣ እና ከፍ ሲልም ከከበሩ ማዕድናት በተሠሩ ጌጣጌጦች ነው። ይህ ማሕበረሰብ ገንዘብን (money) የሚፈልገው ለመገበያያ ዓላማ ሲሆን ትርፍ ገንዘብ ሲኖርም የሚያስቀምጠው በቤቱ ነው። እነዚህ በየግለሰቦች ቤት የሚገኙ ሀብቶች አንድም መጠናቸው አነስተኛ በመሆኑ፣ ሁለትም በገንዘብ መልክ ስለማይገኙ ወደ ልማት ከመግባት ይልቅ ለቤተሰባዊ ፍጆታ ብቻ ያገለግላሉ። የፋይናንስ ተቋማት በየግለሰቦች እጅ የሚገኙ በተናጠል ለልማት ብዙም ፋይዳ የሌላቸው እና በመጨረሻም ለፍጆታ የሚውሉ ሀብቶችን ለልማት ጥቅል ላይ ሊውሉ በሚችሉበት አግባብ  በማሰባሰብ እና የቢዝነስ መከሊት ላለቸው አልሚዎች በማበደር ፋይናንስን የማሳለጥ (financial intermediation) ሚና ይጫወታሉ።

## አፈጻጸም እና ተግዳሮቶች

### መዋዕለ ንዋይ

7. ከ2006 እስከ 2016 ባሉት የበጀት ዓመታት ለ26,118 ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷል። ከእነዚህም መካከል የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ድርሻ 45.3 በመቶ ነው። አጠቃላይ የመዋዕለ ንዋይ ፈቃድ ጥያቄዎች ብዛት እስከ 2015 የጨመረ ሲሆን ከ2010 በኋላ ያሉት ዓመታት አጎዘች መዋዠቅ የሚታይባቸው ናቸው። ለዚህ መውጣት እና መወውረድ ቅርብ ምክንያቶቹ የኮቪድ - 19 ወረርሽኝ እና ተከታታይ ግጭቶች ናቸው። በ2015 ከፍተኛ የመዋዕለ ንዋይ ፈቃድ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም በ2016 የተመዘገበው ፍላጎት ከአራት ዓመታት በፊት በ2012 ተጠይቆ ከነበረው ያነሰ ነው።

8. ከመዋዕለ ንዋይ ፈቃድ ጥያቄዎች የአማራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ2006 ከነበረበት 33 በመቶ በ2010 ወደ 50 በመቶ ጨምሮ የነበረ ሲሆን እስከ 2015 ድረስም ከ44 በመቶ በላይ ሆኖ ቆይቷል። ነገር ግን በ2016 የበጀት ዓመት የዘርፉ የመዋዕለ ንዋይ ፍላጎት ድርሻ ከ2009 በፊት ወደነበረበት ማለትም 37 በመቶ ቀንሷል። ይ

9. ስዕል 25- 1፤ የመዋዕለ ንዋይ ጥያቄ የቀረቡ ፕሮጀክቶች ብዛት




ምንጭ፤ አብክመ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ

10. በምጣኔ ሀብት ሣይንስ ትንታኔ እና መረጃ መሠረት በገበያ በሚመራ የትኛውም አገር ኢኮኖሚ ውስጥ በመዋዠቅ የሚታወቀው የጥቅል ኢኮኖሚ አመልካች መዋዕለ ንዋይ ነው። በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የዚህ ዓይነቱ መዋዠቅ የሚከሰተው የአልሚዎች (investors) የቢዝነስ ውሳኔ በስጋት እና በተስፋ መሃል መዋለል ምክንያት ነው። ወደ ልማት የመግባት እና ወደ ምርት የመሸጋገር ጉዳይ እነደተጠበቀ ሆኖ የመዋዕለ ንዋይ ፈቃድ ጥያቄ መጠን በራሱ አልሚዎች ስለ ኢኮኖሚው ያላቸውን ተስፋ እና ስጋት አመላካች ነው።

11. በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የመዋዕለ ንዋይ ፈቃድ ካስገቡት መካከል 30 በመቶ፣ ወይም በዘርፉ የመዋዕለ ንዋይ ፈቃድ ከጠየቁት መካከል 24.3 በመቶ የሚሆኑት መሬት ተላልፎላቸዋል። መሬት ከተላለፈላቸው አልሚዎች መካከል በአምሥት ዓመት ውስጥ ከነበረው ብዛት 42.7 በመቶ የሚሆኑት ወደ ማምረት ተሸጋግረዋል። በአለፉት ቅርብ ዓመታት ወደ ማምረት ከተሸጋገሩት የአምራች ኢንዱስትሪዎች ከብዛት 8.1 በመቶ ድርሻ ያላቸው ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 83.4 በመቶ የካፒታል ድርሻ እና 50.4 በመቶ የሰው ኃይል ድርሻ ነበራቸው። ከአጠቃላይ ብዛት 68.2 በመቶ ድርሻ ያላቸው አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ከካፒታል 2.6 በመቶ፣ ከሰው ኃይል ደግሞ 29.3 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። በተመሳሳይ 23.6 በመቶ የብዛት ድርሻ የነበራቸው መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች 14.1 በመቶ የካፒታል፣ እና 20.3 በመቶ የሰው ኃይል ድርሻ ነበራቸው።

12. ሠንጠረዥ 26-1፡ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች መዋዕለ ንዋይ ስርጭት በኢንዱስትሪ ደረጃ (በመቶኛ)

| | ብዛት | ካፒታል | የሰው ኃይል |
|---|---|---|---|
| አነስተኛ | 68.2 | 2.6 | 29.3 |
| መካከለኛ | 23.6 | 14.1 | 20.3 |
| ከፍተኛ | 8.1 | 83.4 | 50.4 |

ምንጭ፤ አብክመ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ

13. እንደሚጠበቀው አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ሲወዳደሩ ከካፒታል ይልቅ በሰው ኃይል ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የአነስተኛ፣ መካከለኛ፣ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች አማካይ የሰው ኃይል ቅጥር በተቋም 9 ሰው፣ 18 ሰው እና 127 ሰው ሲሆን የእነዚህ ደረጃዎች አማካይ የካፒታል መጠን በኢንዱስትሪ፣ እንደ ቅድም ተከተላቸው፣ 1.2 ሚሊዮን ብር፣ 18.8 ሚሊዮን ብር፣ እና 322 ሚሊዮን ብር ነው። አማካይ የካፒታል - ሰው ኃይል ጥምርታ የአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች 134 ሺህ ብር፣ የመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች 1 ሚሊዮን ብር፣ እና የከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች 2.5 ሚሊዮን ብር ነው። በጥቅሉ ሲታይ በቅርብ ወደ ማምረት የገቡት የክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ድርጅቶች በካፒታል አቅም ሲለካ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ቀጥሎ ትልቅ የሚባሉ ናቸው።

14. ሠንጠረዥ 26- 2፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ድርጅቶች መጠን በካፒታል እና በሰው ኃይል

| ኢንዱስትሪ | ብዛት | ካፒታል (ሚሊዮን ብር) | የሰው ኃይል | ካፒታል በኢንዱስትሪ | የሰው ኃይል በኢንዱስትሪ | ካፒታል - ሰው ኃይል ጥምርታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አነስተኛ | 2362 | 2,790.8 | 20753 | 1,181,544 | 9 | 134,477 |
| መካከለኛ | 817 | 15,319.0 | 14388 | 18,750,355 | 18 | 1,064,709 |
| ከፍተኛ | 282 | 90,809 | 35756 | 322,017,730 | 127 | 2,539,686 |
| ሁሉም | 3,461 | 108,919 | 70,897 | 31,470,340 | 20 | 1,536,297 |

ምንጭ፤ አብክመ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ

15. በንዑስ ዘርፎች ረገድ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ (አግሮ ፕሮሰሲንግ) ድርጅቶች በካፒታል መጠን 46.3 በመቶ ደርሻ በመያዝ እና በአማካይ በድርጅት 42.6 ሚሊዮን ብር ካፒታል በማስመዝገብ በመጠን ከሌሎቹ ንዑስ ዘርፎች ልቆ ታይቷል። የሰው ኃይል ከመቅጠር አንጻር የጨርቃጨርቅ ዘርፍ የተሻለ ድርሻ አላቸው። አማካይ የጨርቃጨርቅ ዘርፍ የሰው ኃይል መጠን በድርጅት 265 ሲሆን ይህ የሌሎችን ንዑስ ዘርፎች የመቅጠር አቅም ከእጥፍ በላይ ነው። የዓለም የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ቅጥር በፋብሪካ ከቦታ ቦታ፣ ከምርት ዓይነት፣ እና ከኦቶሜሽን ደረጃ አንጻር የተለያየ ቢሆንም በአማካይ ከ100 እስከ 200 ሰው ይደርሳል። ከዚህ አንጻር የአማራ ክልል የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች በቁጥር ውስን ከመሆናቸው በስተቀር በመጠን ደረጃ ከዓለም አቀፍ አማካይ የሚበልጡ ናቸው። ተወዳዳሪነትን እና ቅልጥፍናን፣ እንዲሁም የምርት አማራጮችን ለማብዛት ውስን ምርት የሚያመርቱ ትላልቅ ግን ጥቂት ፋብሪካዎችን ከማበረታታት ይልቅ ከ100 እስከ 250 ሰው ሊቀጥሩ የሚችሉ በርከት ያሉ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችን ማበረታታት ተገቢ ይሆናል።
16. ሠንጠረዥ 26-3፤ የመዋዕለ ንዋይ ስርጭት በንዑስ ዘርፎች

| | የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ | ጨርቃ ጨርቅ | ብረታ ብረት | ኬሚካል እና የግንባታ ግብዓት |
|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 777 | 892 | 1402 | 390 |
| ካፒታል (ሚ. ብር) | 50,423 | 14,124 | 20,254 | 24,119 |
| የሰው ኃይል | 17,323 | 24,191 | 13,696 | 15,669 |
| | | **ድርሻ በመቶኛ** | | |
| ከብዛት | 22.5 | 25.8 | 40.5 | 11.3 |
| ከካፒታል መጠን | 46.3 | 13.0 | 18.6 | 22.1 |
| ከሰው ኃይል | 24.4 | 34.1 | 19.3 | 22.1 |
| | | **የመጠን ምጣኔዎች** | | |
| ካፒታል በድርጅት | 42,619 | 30,318 | 35,569 | 21,298 |
| የሰው ኃይል በድርጅት | 94 | 265 | 102 | 111 |

*ምንጭ፤ አብክመ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ*

17. ለክልሉ አነስተኛ የመዋዕለ ንዋይ አፈጻጸም ወቅታዊ ግጭት ያስከተለው የፀጥታ ችግር፣ የመሬት አቅርቦት አለመሳለጥ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። መሠረታዊው ጉዳይ ግን የጸጥታ ችግር ባልነበረበት ጊዜም የመዋዕለ ንዋይ አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው። መሬት እንደልብ ለአልሚዎች ከተላለፈ በኋላም በክልሉ ሳይለሙ ታጥረው ሙት ካፒታል ሆነው የተቀመጡ ሀብቶች ብዙ ናቸው። የነዚህ መገለጫ ከፀጥታ እና መሬት ከማስተላለፍ ችግር የዘለለ ነው። በአገርም ሆነ በክልል ደረጃ በዘርፉ ያሉ ነባር ሁኔታዎች ሲጠቃለሉ
    - እስከ 2010 ድረስ ለአገር ውስጥ አልሚዎች ከተፈቀዱት ፕሮጀክቶች መካከል ወደ ማምረት የተሸጋገሩት 9.8 በመቶ የነበሩ ሲሆን በአንጻሩ በተመሳሳይ ጊዜ ፈቃድ ካገኙ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ ንዋይ አልሚዎች ውስጥ 54 በመቶ የሚሆኑት ወደ ማምረት ተሸጋግረዋል፤
    - የአገር ውስጥ አልሚዎች ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ይልቅ በአገልግሎት ዘርፎች የሚያተኩሩትን ያህል፣ የውጭ አገር አልሚዎች በአብዛኛው (71 በመቶ) በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አተኩረዋል፤ ከዚህ ባለፈ በሁለተኛ ደረጃ በግብርና ላይ ተሰማርተዋል፤
    - የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ ንዋይ ፋብሪካዎች በአገር ውስጥ አልሚዎች ከተቋቋሙ ፋብሪካዎች በመጠን የሚልቁ ሲሆን በካፒታል 8 እጥፍ በሰው ኃይል ቅጥር ደግሞ በ3 እጥፍ ይበልጧቸዋል።

18. ከዚህ አኳያ መሠረታዊው የክልሉ እና የአገሪቷ የመዋዕለ ንዋይ ችግሮች በሦስት ሊጠቃለሉ ይችላሉ፤
    - የመዋዕለ ንዋይ ስምሪት ከስትራቴጂካዊ መሪ ዕቅድ ያልመነጨ እና ዘፈቀዳዊ መሆን፣
    - የአልሚዎች መረጣ በጥናት ላይ ያልተመሠረተ መሆን፣
    - ለእውነተኛ አልሚዎች የሚደረግ ድጋፍ ውስን መሆን እና ይልቁንም በተንዛዛ ቢሮክራሲ የሚገለጽ፣ ቁጥጥር ላይ ማተኮር፣ በአንጻሩ መሬት ወስደው በማያለሙ ወቅት እና ኪራይ ጠባቂዎች ላይ የሚወሰድ ርምጃ የላላ መሆን።

### ቁጠባ

19. በአማራ ብሔራዊ ክልል የቁጠባ ባሕል ያልዳበረ በመሆኑ ጥረት ይጠይቃል። ከመሠረታዊ ፍጆታ የተረፈው ለበዓላት ድግስ ይውላል። ከዚህ የተረፈውም በእህል እና ጥራትሬ፣ እንዲሁም በቁም ከብት የሚያዝ በመሆኑ ለኢኮኖሚው ወሳኝ አስተዋጽዕዖ ሳደርግ ይቀራል። ዋና መሣሪያው የቁጠባን ጥቅም ከማስረዳት ባለፈ ለቁጠባ ገገር ምክንያት የሚሆን ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ግቦች ለማሕበረሰቡ መፍጠር ነው። በተለይ በገጠሩ አካባቢ መኖር ሕይወትን ለማትረፍ አንድ እንጀራ በልቶ ከማደር በላይ መሆኑን ከተሻሻለ የቤት አሠራር እና አያያዝ ጀምሮ ማመላከት ያሻል። የመሬት ታክስ ለትምህርት ዓይነት የፊስካል ፖሊሲዎች ተዘዋዋሪ ቁጠባ ማረጋገጫ መንገዶች ናቸው። ለአካባቢ ልማት የሚሆን ገንዘብ በጭራ (በጋማ እና በቁም ከብት እንስሳት) ሊከፈል ይችላል። 52 በመቶ የሚሆነው የግብርና ዘርፍ በቁጠባም ሆነ በታክስ ገቢ ለፋይናንስ ያለው አስተዋጽዖ ዝቅተኛ ከሆነ ከግብርና ውጪ ካለው ውስን ዘርፍ በሚሰበሰብ ሰፊውን ገጠር በራስ አቅም ለማልማት አስቸጋሪ ነው።

### የፋይናንስ ተቋማት

20. ከክልሉ ጋር ቅርብ ትስስር ያላቸው ባንኮች መኖር ለፋይናንሻል ቁጠባ ግቦች መሳካት ትልቅ አበርክቶ ይኖራቸዋል። በዓለፉት ከሁለት አሥርት ዓመታት የዘለለ ወቅት በተለይ የአማራ ብድር እና ቁጠባ ተቋም (የአሁኑ ፀደይ ባንክ) ከክልሉ የኢኮኖሚ መዋቅር ጋር የሚጣጣም የብድር እና ቁጠባ ሥልት ይዞ መንቀሳቀሱ የቁጠባ ባሕልን አስፋፍቷል። ነገር ግን ከቁጠባ በላይ ልማት መረጋገጫ መንገዱ ጥራት ያለው መዋዕለ ንዋይ በመሆኑ በክልሉ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ለተመረጡ ስትራቴጂካዊ ዘርፎች የረጅም ጊዜ ብድር ማመቻቸት እንዲችሉ ማድረግ ይገባል። ከዚህ አንጻር ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ክልል በቀል ባንኮች እንደ ፖሊሲ ባንክ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

## 26. 2. የትኩረት አቅጣጫዎች

21. የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ የመዋዕለ ንዋይ የትኩረት አቅጣጫ የመዋዕለ-ንዋይ ስምሪት ምክንያታዊ እና መነሻ ያለው ማድረግ፣ በተለይም የመዋዕለ ንዋይ መፍላንት በካፒታል መጠን፣ በዘርፍ ስምሪት፣ በምንጭ ለመወሰን በሚከተሉት መነሻዎች ላይ መመሥረት፤

- የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ
- የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ ፍላጎት
- የቴክኖሎጂ ግብ
- የስትራቴጂካዊ አቅም ግቦች
- የተመጣጠነ ቀጠናዊ ልማት ግብ፣
- የሀብት መሠረት፥ እንዲሁም
- የሥራ ዕድል ፈጠራ ግቦች ናቸው።

22. የፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት እና የመዋቅራዊ ሽግግር ግቦች በተለይ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ በዘመናዊ ግብርና፣ እና በአይቲ ቴክኖሎጂ ላይ በግንባር ቀደምትነት ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰሰት እንደሚኖር ያመለክታል። የማዕድን፣ የቱሪዝም፣ የሰብዓዊ ሀብት፣ እንዲሁም የመሠረተ-ልማት ዘርፎች ሌሎቹ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰሰት የትኩረት መስኮች ናቸው። በአምራች ኢንዱስትሪ ረገድ የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የመዋዕለ-ንዋይ የትኩረት ምርቶች ገቢ ንግድን መተካት የሚያስችሉ የምግብ ማቀነባበሪያ፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የመዲሃኒት እና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ሲሆኑ፣ ከዚህ ጎን ለጎን ለብረታ ብረት እና ማሽን ቴክኖሎጂ፣ ለግብዓት ቴክኖሎጂ፣ ለአማራጭ የኃይል አቅርቦት፣ እና ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር መሠረት በሚጥሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ትኩረት ተደርጎ ይሠራል።ይህም ማለት ለከፍተኛ የማሽን እና የፋብሪኬሽን ኢንጂኔሪንግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሶፍት ዌር እና ሀርድ ዌር ምርቶች መሠረት ለመጣል ዝግጅት የሚደረግ ይሆናል። የመዋዕለ ንዋይ ሥምሪቱም ይህን ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል። በዘመናዊ ግብርና በምግብ ራስን መቻል ግብ የሚሳካው በኮመርሻል ግብርና በሚደረግ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰሰት ነው።

23. የመዋዕለ-ንዋይ ዋና ስትራቴጂ የአገር ውስጥ ኢንዳስትሪያሊስቶችን መፍጠር፣ በስትራቴጂካዊ መስኮች የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ነው። የአገር ውስጥ አልሚ፣ የልማት ድርጅቶች፣ የውጭ አገር አልሚዎች እንደ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ይሳተፋሉ።

## 26.3. የመዋዕለ ንዋይ ግቦች

24. በአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን የታለመውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማሳካት በወቅቱ የገበያ ዋጋ 5.77 ትሪሊዮን ብር መዋዕለ ንዋይ ያስፈልጋል። ይህ በ2008 ቋሚ ዋጋ ሲሰላ 966.7 ቢሊዮን ብር ይሆናል። ይህም የክልሉን የመንግሥት የካፒታል በጀት፣ የአርሶ አደሩን የግብርና ዘርፍ ስምሪት ይሸፍናል።

25. ሠንጠረዥ 26-4፤ የመዋዕለ ንዋይ ግቦች

| | መነሻ | አመላካች እቅድ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | 2018-2022 |
| አገራዊ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ (በሚሊዮን ብር) | 1,581,569 | 1,959,122 | 2,426,803 | 3,006,130 | 3,723,753 | 4,612,687 | |
| የመዋዕለ ንዋይ ምጣኔ (ከክልላዊ ምርት በመቶኛ) | | 31.0 | 35.9 | 36.7 | 37.5 | 39.0 | 36.0 |
| **መዋዕለ ንዋይ በወቅቱ የገበያ ዋጋ (በሚሊዮን ብር)** | | **607,930** | **870,512** | **1,102,044** | **1,395,157** | **1,798,948** | **5,774,591** |
| የግል እና የልማት ድርጅቶች መዋዕለ ንዋይ (በሚሊዮን ብር) | | 522,356 | 751,259 | 921,496 | 1,151,177 | 1,496,400 | 4,842,687 |
| የመንግሥት የካፒታል ወጪ (ሚሊዮን ብር) | | *85,574* | *119,253* | *180,548* | *243,980* | *302,548* | *85,574* |
| | | | ተጨማሪ መረጃ | | | | |
| ዲፍሌተር (2008=1) | 4.1 | 4.6 | 5.1 | 5.7 | 6.4 | 7.2 | |
| በ2008 ቋሚ ዋጋ (በሚሊዮን ብር) | | 133,563 | 170,761 | 193,017 | 218,173 | 251,176 | 966,690 |

## 26.4. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

26. የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የመዋዕለ ንዋይ ዕቅድ ግቦች የማስፈጸሚያ ስልቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- የመዋዕለ ንዋይ ስምሪቶች በታቀደ ዘርፍ እና ቦታ ከመረተልማት፣ ከሰው ኃይል፣ እና ከግብዓት አቅርቦት ጋር ተመሳክረው ይፈጸማሉ፤
- አልሚዎች በማልማት ብቃታቸው ተወዳድረው እና ተመርጠው በተመረጡ ዘርፎች በተለዩ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች በተቆረጠ የማስጀመሪያ እና የማጠናቀቂያ ጊዜ፣ በታቀደ የምርት ግብ ውል መሠረት ይሰማራሉ።
- ልዩ ማበረታቻዎች ይታቀዳሉ፤ መፍትሄን በጊዜ የመስጠት ግብ ያለው ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ከተጠያቂነት ጋር ይሰፍናል፤
- ሁሉንም የክልሉን መዋዕለ ንዋይ ስምሪቶች በማዕከል የሚመራ የመዋዕለ ንዋይ ተቋም ይመሠረታል፤
- በክህሎት፣ በስነ ምግባር፣ እና በአገልጋይነታቸው የተመሰከረላቸው ሙያተኞች የሚመሩት የመዋዕለ ንዋይ አሳላጭ ቢሮክራሲ ይፈጠራል፤ እንዲሁም
- የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ የመዋዕለ ንዋይ ትብብር ቋሚ የምክክር ጉባዔ ይቋቋማል።

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

# የመንግሥት ፋይናንስ

## 27.1. መግቢያ

1. የመንግሥት ፋይናንስ የመንግሥት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ዋና መሣሪያ ነው። መንግሥት ከሕዝብ ጋር በገባው ማሕበራዊ ኮንትራት መሠረት በፖሊሲው ሦስት ዋና ዋና ግቦችን ያሳካል፤ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማሕበራዊ ፍትህ፣ እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ። የዚህ የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ እነዚህ ግቦች በተሻለ ደረጃ እንዲሳኩ ማድረግ ነው።

2. የመንግሥት የፋይናንስ አቅም ሥራ ለመሥራት እንደተከማቸ የጉልበት አቅም ይቆጠራል። ይህ አቅም እንደዋለበት የዘርፍ ስምሪት ሊባክን፣ በመጠኑ ሊያለማ፣ ወይም ባለው ሀብት እና የዕውቀት ደረጃ ከፍተኛ ሥራ ሊሠራበት ይችላል። ይህ የሚረጋገጠው በምደባ ወቅት የኢኮኖሚ ዕድገትን በማነቃነቅ ደረጃ የተሻለ አቅም ባላቸው ዘርፎች እና በትንሽ ጥረት አብዛኛውን ማሕበረሰብ ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ ዘርፎች ላይ መሆኑን በማረጋገጥ፣ የአፈጻጸም ወቅት የሀብት እና የጊዜ ብክነትን በመቀነስ፣ እና ጥራትን በማስጠበቅ ቅልጥፍናን በማረጋገጥ ነው።

3. መንግሥት ሊፈጽማቸው ያቀዳቸውን ተግባራት ዳር ለማድረስ በሕገ-መንግሥት የተሰጡት ሁለት የመንግሥት ፋይናንስ ሥልጣኖች ያሉት ሲሆን እነዚህም ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን (power of taxation) እና ፋይናንስን ወጪ የማድረግ ሥልጣን (power of expenditure) ናቸው። ኢትዮጵያ የፌደራል የመንግሥት አወቃቀር የምትከተል አገር እንደመሆኗ በፌደራል መንግሥት እና ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሚደረጉ ገቢ የመሰብሰብ እና ወጪ የማድረግ ሥልጣኖች (fiscal assignments) በሕገ-መንግሥቱ ከአንቀጽ 94 እስከ አንቀጽ 100 ድረስ ባሉት ይዘቶች ተደንግገዋል።

4. የፋይናንስ ወጪን የሚመለከተው የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 94 አምሥት ዋና ዋና የመንግሥት ወጪ መርሆዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህም

    1. የራስ የውስጥ አስተዳደር ነጻነት (autonomy)፣
    2. ወጪን በራስ አቅም መሸፈን መቻል (self-sufficiency/equity0፣
    3. በአንድ የጋራ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ማሕበረሰብ ውስጥ ማሕበራዊ አንድነትን ማጠናከር (social cohesion)፣
    4. የተመጣጠነ ቀጠናዊ ወይም ክልላዊ ልማት ማረጋገጥ (balanced regional development)፣ እና
    5. ተጠያቂነት (accountability) ናቸው።

5. በአንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 1 "የፌዴራሉ መንግሥት እና ክልሎች በሕግ የተሰጧቸውን ኃላፊነቶች እና ተግባሮች ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በየበኩላቸው ይሸፍናሉ፤ ሆኖም ማንኛውም ክልል በውክልና ለሚፈጽመው ተግባር የሚያስፈልገው ወጪ ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ውክልናውን በሰጠው ወገን ይሸፈናል።" በሚለው ድንጋጌ ውስጥ የውስጥ አስተዳደር ነጻነት፣ እና ራስን የመቻል ልምምድ መርሆዎች ተንጸባርቀዋል። በአንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 2 "የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች የተመጣጠነ ዕድገት እንቅፋት ካልሆነ በስተቀር ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋም እና ለልማትማስፋፊያ ለክልሎች ብድርም ሆነ እርዳታ ሊሰጥ ይችላል። የፌዴራሉ መንግሥት ክልሎች ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ በሚመለከት ኦዲት እና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል።" በሚለው ድንጋጌ ውስጥ ደግሞ ማሕበረሰባዊ አንድነት፣ የተመጣጠነ የክልሎች ልማት፣ እና ተጠያቂነት ተንጸባርቀዋል።

6. የገቢ መሰብሰብ ሥልጣን በአገር ደረጃ

    1. የፌዴራል መንግሥት የታክስ እና የግብር ሥልጣን፣ የክልል፣
    2. የክልል መስተዳድሮች የታክስ እና የግብር ሥልጣን፣ እና

3. የጋራ የታክስ እና የግብር ሥልጣን ተብለው በሕገ-መንግሥቱ አንቀጾች 96 – 98 የተደነገጉ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች ያልተካተቱ የታክስ እና የግብር ሥልጣኖች በፌዴሬሽን ምክር ቤት እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው እንደሚወሰኑ በአንቀጽ 99 ተመላክቷል።

7. ታክስ እና ግብር ፍትሃዊ መሆን አለበት። ይህም በጎንዮሽ ፍትሃዊነት (horizontal equity) እና በተዋረድ ፍትሃዊነት (vertical equity) ይገለጻል። የዚህ ፍትሃዊነት መርህ ዋና ዓላማ ፍትሃዊነት በራሱ ግብ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ የሚሰበሰብ የታክስ እና ግብር ገቢ ከዜጎች ገቢ ጋር ሳይመጣጠን ቀርቶ ቢዝነስን በመጉዳት የኢኮኖሚ ዕድገት ግብን እንዳያስተጓጉል፣ የታክስ መሠረቱን በመሸርሸር ሊሰበሰብ የሚችለውን የታክስ እና ግብር መጠንም እንዳያቀጭጭ ሲባል ነው። ይህም በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 100 ሥር ባሉት አንቀጾች ተደንግጎ ይገኛል፤
   1. "ክልሎች እና የፌዴራሉ መንግሥት ታክስ እና ግብር በሚጥሉበተ ጊዜ የሚጠየቀው ታክስ እና ግብር ከምንጩ ጋር የተያያዘ እና በአግባቡ ተጠንቶ የተወሰነ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።"
   2. "በመካከላቸው የሚኖረውን መልካም ግንኙነት የማይጎዳና ከሚቀርበው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።"
   3. ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግሥትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን አይኖራቸውም።"

## 27.2. የመንግሥት ፋይናንስ ወጪ እና ገቢ አፈጻጸም ትንተና

### የመንግሥት ወጪ

8. **በአለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የልማት ወጪ በተለይ በአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የተከሰተውን የዋጋ ንረት ጫና ተቋቁሞ ዕቅዶችን ማስፈጸም በሚያስችል ደረጃ ሲያድግ ቆይቷል።** በ2015 የበጀት ዓመት የአማራ ብሔራዊ መንግሥት አጠቃላይ የፋይናንስ ወጪ 103.2 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን የክልሉ መንግሥት ወጪ ከ1987 ጀምሮ ላለፉት 28 ዓመት በ116 እጥፍ፣ ወይም በ19.9 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት ጨምሯል። ይህ ወጪ በ2008 የመግዛት አቅም ሲመዘን በ5 እጥፍ የጨመረ ሲሆን፣ ይህም  በዓመት በአማካይ በ6.9 በመቶ ሲያድግ እንደነበረ ያሳያል። ከአጠቃላይ የ19.9 በመቶ ዓመታዊ አማካይ የመንግሥት ወጪ ዕድገት ውስጥ 13 የመቶኛ ነጥብ የዋጋ ንረት ዕድገት ያመጣው ነው።

9. ስዕል 27 – 1፤ የመንግሥት አጠቃላይ ወጪ በጊዘው እና በቋሚ ዋጋ፤ 1987 - 2015




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

10. በሦስቱ አሥርት ዓመታት ውስጥ የመደበኛ ወጪ በ20 በመቶ፣ የካፒታል ወጪ ደግሞ በ21.8 በመቶ ተቀራራቢ ምጣኔ አድገዋል። በ2008 የመግዛት አቅም ስሌት መሠረት የመደበኛ ወጪ በ7 በመቶ፣ የካፒታል ወጪ ደግሞ በ8.7 በመቶ አድገዋል። በመግዛት አቅም ከተሰላው የ6.9 በመቶ አጠቃላይ የመንግሥት ወጪ ዕድገት ውስጥ የመደበኛ ወጪ 5.5 የመቶኛ ነጥብ፣ እና የካፒታል ወጪ ደግሞ የ1.4 መቶኛ ነጥብ ዕድገት ድርሻ ነበራቸው። የካፒታል ወጪ ከአጠቃላይ ወጪ ድርሻ ቋሚ ያልነበረ ሲሆን በአጠቃላይ የ28 ዓመታት አማካይ ድርሻ 19.4 በመቶ ነው። ይህ ማለት የመደበኛ ወጪ ከአጠቃላይ ወጪ መጠን አነስተኛ መሆን ከ6.9 በመቶ ዕድገት ውስጥ የ1.4 በመቶ ወይም የአጠቃላይ ዕድገቱን 20.3 በመቶ ብቻ እንዲይዝ አድርጎታል።

11. የካፒታል ወጪ ከአጠቃላይ የመንግሥት ወጪ የነበረው ድርሻ መዋዠቅ ይታይበታል። ይህ ከፕሮጀክቶች ዑደት ጋር ሊያያዝ ቢችልም በአብዛኛው ግጭት እና አለመረጋጋት በተከሰተባቸው ዘመናት ዝቅተኛ የካፒታል በጀት ድልድል ተስተውሏል። እስከ 10.5 በመቶ ድረስ የወረደ የካፒታል በጀት ድርሻ የተመዘገበው በ1997 ምርጫ ማግስት በ1998 ነው። በአጠቃላይ ከ1994 እስከ 2001 የበጀት ዓመታት የካፒታል በጀት ድርሻ ከ20 በመቶ በታች ነበር። በክልሉ ከፍተኛ የካፒታል በጀት ምደባ የተመዘገበው በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን የመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ሲሆን በተለይ በ2005 የተመዘገበው የ30.1 በመቶ ድርሻ ከሁሉም ዓመታት ከፍተኛው ነው። አለመረጋጋት መከሰት ከጀመረበት 2013 ጀምሮ የካፒታል በጀት ድርሻ ከ20 በመቶ በታች ወርዷል። ይህ የሚያሳየው ግጭት እና አለመረጋጋት በቀጥታ ውድመትም ሆነ በሚመደብ በጀት ውስንነት ምክንያት የሚጎዳው የሕዝብ ልማትን መሆኑን ነው።

12. ስዕል 27 – 2፤ የአብክመ የካፒታል ወጪ ከአጠቃላይ የክልሉ የመንግሥት ወጪ ያለው ድርሻ




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ

13. **በአለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት በነበሩት ሁሉም ጊዜያት ለትምህርት የተመደበው በጀት ድርሻ ከሁሉም ሌሎች ዘርፎች የበጀት ድርሻ ምጣኔ ይልቃል። ከጠቅላላ የመንግሥት ወጪ ውስጥ የትምህርት ዘርፍ ድርሻ ከ1987 – 1997 በነበሩት ዓመታት 47.4 በመቶ፣** ከ1998 – 2002 በነበሩት የተፋጠነ እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ (Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty - PASDEP) ዘመን 55.5 በመቶ፣ ከ2003 – 2009 በነበረው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (Growth and Transformation Plan - GTP) ዘመን 41.4 በመቶ፣ እና ከ2010 – 2015 ባሉት የለውጡ መንግሥት ዓመታት 50.2 በመቶ በጀት ነበር።

14. ስዕል 27-3፤ ከጠቅላላ የመንግሥት ወጪ የዘርፎች ድርሻ፤ 1987 – 2015




| | 1987 - 1997 | 1998 - 2002 | 2003 - 2009 | 2010-2015 |
|---|---|---|---|---|
| ጤና | 16.5 | 15.2 | 16.3 | 22.6 |
| ትምህርት | 47.4 | 55.5 | 41.4 | 50.2 |
| ግብርና | 21.5 | 20.0 | 13.3 | 13.0 |
| ውሃ | 6.2 | 4.1 | 11.9 | 6.4 |
| መንገድ | 8.5 | 5.2 | 17.1 | 7.8 |

ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

15. በተለይ በመደበኛ ወጪ ረገድ የትምህርት ዘርፍ ድርሻ በሁሉም ዓመታት ከ54 በመቶ በላይ ሲሆን በ2003 የበጀት ዓመት 63 በመቶ ደርሶ ነበር። የመማር ማስተማር ተግባር በእጅጉ በተፈተነበት በ2015 የበጀት ዓመት ጭምር የዘርፉ የመደበኛ ወጪ ድርሻ 60.6 በመቶ ነው። እስከ 2004 የበጀት ዓመት ድረስ ከ20 እስከ 25.6 በመቶ በሚደርስ ድርሻ ከትምህርት ቀጥሎ ከፍተኛ በጀት የሚደብለት የነበረው የግብርና ዘርፍ ድርሻ እየቀነሰ መጥቶ በ2015 ወደ 11.4 በመቶ ደርሷል። በአንጻሩ ከ2004 በፊት በመደበኛ በጀት ድርሻ በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኝ የነበረው የጤና ዘርፍ የመደበኛ በጀት ድርሻ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በ2015 የበጀት ዓመት 25.6 በመቶ ድርሻ በመውሰድ ከትምህርት ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃን ይዟል። ከዘርፎች መካከል ከመደበኛ በጀት ከ3 በመቶ ያልዘለለ ድርሻ የነበራቸው ውሃ እና መንገድ ናቸው።

16. ስዕል 27 – 4፤ የዘርፎች የመደበኛ ወጪ ድርሻ፤ 1987 – 2015




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

17. በመደበኛ ወጪ ረገድ ትምህርት ልማትን በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መምራት ከመጀመሩ በፊት እና በሁሉም የዕቅድ ዘመናት ወጥ እና ተመሳሳይ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። የግብርና ዘርፍ በግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ትግበራ የመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት እና በ1998 በተጀመረው የፈጣን እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ

ወቅት የግብርና ልማት ወኪሎችን ማሰማራትን በሚጨምረው ከፍተኛ ትኩረት ምክንያት ከትምህርት ቀጥሎ ከፍተኛውን የበጀት ድርሻ ወስዷል። በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዘመን እና እስከ 2015 ባሉት የለውጥ ዓመታት የዘርፉ የመደበኛ ወጪ ድርሻ የቀነሰ ሲሆን በአንጻሩ የጤና ድርሻ ጨምሮ ታይቷል።

18. ስዕል 27 – 5፡ የዘርፎች የመደበኛ ወጪ አማካይ ድርሻ በዕቅድ ዘመናት




| | ጤና | ትምህርት | ግብርና | ውሃ | መንገድ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1987 - 1997 | 18.2 | 58.0 | 21.4 | 1.2 | 1.2 |
| 1998 - 2002 | 14.6 | 60.7 | 22.4 | 1.3 | 1.0 |
| 2003 - 2009 | 20.2 | 59.2 | 17.7 | 1.5 | 1.4 |
| 2010-2015 | 25.2 | 58.3 | 13.8 | 1.2 | 1.5 |

ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

19. ከ187 እስከ 2002 በነበሩት ዓመታት የግብርና፣ የመንገድ፣ እና የውሃ ዘርፎች የካፒታል በጀት ድልድል በየዓመቱ ወይም ሁለት ዓመታት የመተካካት ሁኔታ ቢኖረውም በአማካይ የተመጣጠነ ድርሻ ነበረው። በዚህ ወቅት የትምህርት የካፒታል ወጪ ድርሻ ከፍ እና ዝቅ የማለት ባህርይ ቢስተዋልበትም በአማካይ ከሌሎች ዘርፎች ድርሻ የበለጠ ነበር። በአንጻሩ በተመሳሳይ ወቅት የጤና ዘርፍ ድርሻ እስከ 1999 ድረስ ከሁሉም ዘርፎች ያነሰ ደርሻ ነበረው። ይህም በመከላከል ላይ ያተኮረው ፖሊሲ እንደ ሆስፒታል ያሉ የጤና ተቋማትን ማስፋፋት የማያበረታታ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል። ነገር ግን በአብዛኛው ከ2003 የበጀት ዓመት ጀምሮ የመንገድ እና የውሃ ዘርፎች በአማካይ 71.3 በመቶ የሚሆነውን የካፒታል ወጪ ድርሻ የወሰዱ ሲሆን፣ የትምህርት፣ ጤና እና የግብርና ዘርፎች ቀሪውን 28.7 በመቶ ድርሻ ወስደዋል።

20. ስዕል 27 -6፤ የዘርፎች የካፒታል ወጪ ድርሻ፤ 1987 - 2015




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

21. የካፒታል በጀት ድልድል ለውጦች የትኩረት አቅጣጫ ለውጥን ያመላክታሉ። ከ1987 – 1997 በነበሩት ዓመታት ትምህርት፣ ግብርና እና መንገድ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው በመሆኑ ከ22 እስከ 25.7 በመቶ በሚሆን ድርሻ ከፍተኛ የካፒታል በጀት ተጠቃሚ ነበሩ። ከ1998 እስከ 2002 በነበሩት የዕቅድ ዓመታት ከትምህርት ቀጥሎ መንገድ፣ ጤና እና ውሃ ተመጣጣኝ ትኩረት የተሰጣቸው ዘርፎች ለመሆናቸው የበጀት ድልድሉ ፍንጭ ይሰጣል። በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን እና ከ2010 ለውጥ በኋላ ከአምሥቱ ዘርፎች ለመንገድ እና ውሃ ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን የትምህርት፣ የጤና እና የግብርና ዘርፎች የካፒታል በጀት ድርሻ በዘርፎቹ ከፍተኛ የመደበኛ ወጪ ድርሻ መተካቱን ያመለክታል። ይህ ማለት በቀዳሚዎቹ የልማት ዓመታት በእነዚህ ዘርፎች የተስፋፉት የማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የመሠረተ- ልማት አውታሮች መደበኛ ወጪ እየሰፋ መምጣቱን ያመለክታል።

22. ስዕል 27 - 7፤ የካፒታል በጀት የዘርፎች ድርሻ በዕቅድ ዘመን




| | ጤና | ትምህርት | ግብርና | ውሃ | መንገድ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1987 - 1997 | 13.5 | 25.7 | 22.0 | 16.6 | 22.2 |
| 1998 - 2002 | 19.3 | 31.3 | 9.0 | 18.1 | 22.3 |
| 2003 - 2009 | 9.8 | 11.2 | 6.5 | 28.9 | 43.6 |
| 2010-2015 | 10.0 | 10.3 | 9.7 | 32.1 | 37.8 |

ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

## የመንግሥት ገቢ

23. የአማራ ብሔራዊ ክልል አጠቃላይ ገቢ ከ1987 ከነበረበት 715 ሚሊዮን ብር በ2015 85.27 ቢሊዮን ብር ደርሷል። ይህ ማለት በ28 ዓመታት ውስጥ አጠቃላይ የመንግሥት ገቢ በ119 እጥፍ ወይም በዓመት በአማካይ በ19.7 በመቶ ሲያድግ ቆይቷል። በተመሳሳይ ወቅት የመንግሥት የታክስ ገቢ በ1987 ከነበረበት 82 ሚሊዮን ብር በ2015 ወደ 31.76 ቢሊዮን ብር ደርሷል። ይህ ማለት የክልሉ የታክስ ገቢ ለአለፉት 28 ዓመታት በ386 እጥፍ ወይም በየዓመቱ በአማካይ በ25.2 በመቶ ሲያድግ ቆይቷል። ይህ የክልል የታክስ ገቢ እድገት ምጣኔ ከአጠቃላይ ገቢ ዕድገት ምጣኔ መብለጡ የመንግሥት በገቢ ራስን የመቻል ጥረት በተፈለገው መጠን ባይሆንም በጥሩ አቅጣጫ ላይ እንደሚገኝ አመላካች ነው።

24. ስዕል 27– 8፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል ገቢ፤ 1987 - 2016




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

25. በ1987 የበጀት ዓመት ክልሉ ከአጠቃላይ ገቢው 11.5 በመቶ ያህሉን በክልሉ በተሰበሰበ የታክስ የሸፈነ ሲሆን በ2015 የበጀት ዓመት 37.5 በመቶ የሚሆነውን ጠቅላላ ገቢ በራስ አቅም በተሰበሰብ የታክስ ገቢ መሸፈን ችሏል። የክልሉ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ ገቢ አነስተኛ ድርሻ የነበረበት ዓመት በ2000 በጀት ዓመት ሲሆን የዚህ ምክንያት የክልሉ የታክስ ገቢ በ32.9 በመቶ ባደገበት ሁኔታ ከሌሎች ምንጮች የተገኘው ገቢ ከዚህ በላቀ 49.6 በመቶ አድጎ ስለነበረ ነው።

26. ስዕል 27 - 9፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ፤ 1987 - 2016




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

27. የክልሉ በገቢ ራስን የመቻል ጥረት አበረታች ቢሆንም በሚገባው ደረጃ አለመሆኑን የሚያመላክተው የታክስ ገቢ - ክልላዊ ምርት ጥምርታ ዝቅተኛ የመሆኑ ዕውነታ ነው። በ1990 የበጀት ዓመት የክልሉ የታክስ ገቢ - ክልላዊ ምርት ጥምርታ 1 በመቶ ያህል የነበረ ሲሆን በ2016 የበጀት ዓመት ወደ 2.1 በመቶ ከመውረዱ በፊት በ2015 የበጀት ዓመት በሦስት እጥፍ አድጎ 2.9 በመቶ ደርሶ ነበር። ይህ አመስተኛ ምጣኔ በአንድ በኩል የኢኮኖሚው መዋቅሩ እና የፊስካል ፖሊሲው የፈጠረው ነው። የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት ከክልላዊ ምርት የነበረው ድርሻ በ2008 58.3 በመቶ በ2016 ደግሞ 51.9 በመቶ ነው። ይህ አኀዝ በአገር ደረጃ ከታየ

በዓለም ከፍተኛው ምጣኔ ነው። በዓለም ላይ ከፍተኛ የግብርና፣ ደን እና ዓሳ ተጨማሪ ዕሴት የአገራዊ ምርት ድርሻ ያላቸው አገራት ኒዠር (47.8 በመቶ)፣ ኮሞሮስ (37.2 በመቶ)፣ እና ኢትዮጵያ (35.8 በመቶ) ናቸው። የአማራ ብሔራዊ ክልልን ጨምሮ በኢትዮጵያ የግብርናው ዘርፍ ትርጉም ያለው የግብርና ገቢ ግብር እንደማይከፍል ይታወቃል። በዚህ ሁኔታ የታክስ መጠንን ከጥቅል ክልላዊ ምርት አንጻር አስልቶ የግበርና ዘርፍ የአገራዊ ምርት ድርሻ አነስተኛ ከሆኑ አገራት ጋር አወዳድሮ አፈጻጸሙን በዝቅተኛነት መፈረጅ አመክንዮአዊ አይሆንም። ከዚህ ይልቅ የታክስ ገቢን ከግብርና ዘርፍ ውጪ ካለው አገራዊ ምርት ጋር በማነጻጸር የሚወሰደው የታክስ - አገራዊ ምርት ጥምርታ የተሻለ ተተግባሪ ምጣኔ ይሰጣል። በዚህም መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል የታክስ ገቢ ከግብርና ዘርፍ ውጪ ካለው አገራዊ ምርት አንጻር ያለው ትምርታ በ2015 የበጀት ዓመት 6.8 በመቶ ደርሷል።

28. የክልሉ የታክስ ገቢ ከግብርናው ዘርፍ ውጪ ከሆነው አገራዊ ምርት የነበረው ድርሻ በ2016 የበጀት ዓመት ወደ 4.5 በመቶ ቀንሷል። የክልሉ ኢኮኖሚ በ5.5 በመቶ ባደገበት ሁኔታ ለታክስ ገቢ እና የታክስ - ክልላዊ ምርት ምጣኔ መቀነስ ከአለመረጋጋት በተጨማሪ አንዱ ምክንያት ታክስ በከፍተኛ ደረጃ የማይሰበሰብበት የግብርናው ዘርፍ ከቀዳሚዎቹ አምሥት ዓመታት የ2.8 በመቶ አማካይ ምጣኔ  በላይ በ4.8 በመቶ ሲያድግ ከፍተኛ የታክስ ገቢ የሚያስገኘው የአገልግሎት ዘርፉ ከቀዳሚዎቹ አምሥት ዓመታት የ7.8 በመቶ አማካይ የዕድገት ምጣኔ ባነሰ በ6.5 በመቶ ምጣኔ ማደጉ ነው።

29. ስዕል 27 – 10፤ የታክስ ገቢ - ክልላዊ ምርት ጥምርታ፤ 1990 - 2016




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዝብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

30. ይህም ሆኖ የክልሉ የታክስ ገቢ ከግብርና ውጪ ካለው ክልላዊ ምርት አንጻር እስከ አሁን የተደረሰበት የ6.8 በመቶ ምጣኔ ዝቅተኛ ነው። ክልሉ ይህ ምጣኔ እስከ 15 በመቶ እስከሚደርስ ድረስ የታክስ ገቢ የማሳደግ አቅም አለው። ይህን ምጣኔ በቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት ወደ 9 በመቶ ማሳደግ በ12 በመቶ የዋጋ ንረት እሳቤ የታክስ ገቢን በ2022 ከአሥር አጥፍ በላይ እስከ 415 ቢሊዮን ብር ማሳደግ ያስችላል።

31. የዋጋ ንረት በሚፈታተነው ኢኮኖሚ ውስጥ የገቢ መጠን ማደግ ብቻ ሳይሆን ከዋጋ ንረቱ አንጻር የመግዛት አቅሙ ትኩረት ሊደረግበት የሚሻ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር በተለይ ከ2009 የበጀት ዓመት ጀምሮ አጠቃላይ ገቢ፣ የታክስ ገቢ፣ እና ሌሎች ገቢዎች የጨመሩ ቢሆንም የሌሎች ገቢዎች ዕድገት ከዋጋ ንረት ምጣኔ በታች በመሆኑ ጠቅላላ ገቢ በ2008 የብር የመግዛት አቅም ሲሰላ እንዲቀንስ አድርጎታል። ነገር ግን የክልሉ የታክስ ገቢ ከዋጋ ንረት በላይ በሆነ ምጣኔ በማደጉ የጠቅላላ ገቢ ልማት የማስፈጸም አቅም ሌሎች ገቢዎች በቀነሱበት ደረጃ እንዳይወርድ አድርጎታል።

32. ስዕል 27 – ΙΙ፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግሥት ገቢ በ2008 የብር መግዛት አቅም




ምንጭ፤ የአብክመ የገንዘብ ቢሮ መረጃን በመጠቀም የተሰላ

## የመንግሥት ፋይናንስ አፈጻጸም ዋና ዋና ጭብጦች

33. ከመረጃዎች ትንተና በመነሳት የአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግስት ፋይናንስ አፈጻጸም ዋና ዋና ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፤

1. በአለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት በተለይም በተለምዶ ድሃ ተኮር በሚባሉት የትምህርት፣ የመንገድ፣ የውሃ፣ የግብርና፣ እና የጤና ዘርፎች በመንግሥት ወጪ የሚደገፍ ከፍተኛ የልማት እንቅስቃሴ ተካሂዷል፤
2. መዋቅራዊ ሽግግር በዕቅድ ደረጃ አንኳር የትኩረት አቅጣጫ በሆነባቸው ዓመታት ሳይቀር ለመዋቅራዊ ሽግግር መሠረት በሚጥሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች ወጣቶች ተሰማርተው የፍብሪካ ምሕንድስና እና የዘመናዊ በተለይም የዲጂታል ቴክኖሎጂ ልምምዶች ማድረግ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ የተደረገው በበጀት የሚገለጽ ድጋፍ በጣም ውስን ነው፤
3. ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የወጣባቸው ትምህርትን ጨምሮ የእነዚህ አምሥት ዘርፎች በምርታማነት እና ቅልጥፍና የሚገለጽ ውጤታማነት በአስተዳደራዊ መረጃ በዘለለ በሣይንሳዊ መንገድ በተጽዕኖ ትንተና (impact evaluation) በአግባቡ ስላልተጠና የወደፊት የመንግሥት ወጪ አቅጣጫዎችን ለማመላከት ተግዳሮት ይፈጥራል፤ ይሁን እንጂ የተገኙት ውስን መረጃዎች በፕሮጀክቶች መዘግየት፣ በተጨማሪ ወጪ መናር፣ በጥራት መጓደል፣ እና በተለይም በትምህርት ዘርፍ በተማረ የሰው ኃይል ብክነት የሚገለጹ የመንግሥት ወጪ የምርታማነት እና ቅልጥፍና መጓደሎች ይስተዋላሉ፤
4. የክልሉ የመንግሥት መደበኛ ወጪ ከክልላዊ ምርት በ2013 የበጀት ዓመት በ7.3 በመቶ፣ በ2016 የበጀት ዓመት በ6.4 በመቶ አነዝ ከ8.8 በመቶ የኢትዮጵያ አነዝም ሆነ ከ15.5 በመቶ ከሳሃራ በታች ያሉ አገራት አነዝ ያነሰ መሆኑ መንግሥት ተጨማሪ የሰው ኃይል ለመቅጠር የሚያስችለው ቢመስልም ይህ በአመዛኙ ከግሉ ዘርፍ አንጻር የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ዝቅተኛ መሆን ጋር የተያያዘም ነው፤
5. የክልሉ የታክስ ገቢ እያደገ ቢመጣም ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ያህል ለመሰብሰብም ሆነ ፍትሃዊ የታክስ አስተዳደር ለማስፈን በጥናት ላይ የተመሠረተ እና አማራጭ የታክስ እና ታክስ ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን የሚያመላክት የፊስካል ፖሊሲ እና ሥርዓት በቅጡ አልተዘረጋም፤ እንዲሁም
6. ከየትኛውም ምንጭ እና በየትኛውም መስመር ወደ ክልሉ የሚፈስሱ የፋይናንስ ሀብቶች በክልሉ ኢኮኖሚ ላያ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ የክልሉ የፋይናንስ ሀብት እንደመሆናቸው መጠን የእነዚህን ሀብቶች መጠን እና ስምሪት እንዲሁም አፈጻጸም በመረጃ መሰነድ እና መከታተል ጠቃሚ ቢሆንም እነዚህን መረጃዎች ለመሰነድ የሚያስችል የተቀናጀ የዘመናዊ መርጃ ሥርዓት ይጎድላል።

## 27.3. የመንግሥት ፋይናንስ የትኩረት አቅጣጫዎች

34. ከላይ ከተለዩአት ጭብጦች በመነሳት የቀጣዮቹ አምሥት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግሥት ፋይናንስ የትኮረት አቅጣጫዎች
    1. የመንግሥት ወጪን የትኩረት መስክ ለሆኑት ዘርፎች በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ሕዝባዊ መሠረት ለመጣል ለሚደረጉ የፍብረካ ምሕንድስና እና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ልማቶች ጭምር ትኩረት በሚሰጥ አግባብ መደልደል፣
    2. የመንግሥት ወጪን የዘርፎች ስምሪት ምርታማነት እና ቅልጥፍና በአግባቡ እና በጊዜ መገምገም፣ ውጤታማነታቸውንም በገለልተኛ አካል ጥናት መፈተሽ፣
    3. የመንግሥት መደበኛ ወጪን የመንግሥት ማሕበረሰብ አገልግሎትን በተወዳዳሪ ሲቪል ሰርቪስ ከማላቅ ግቦች ጋር ማናበብ፣
    4. የመንግሥት ገቢን በሕዝብ ተሳትፎ፣ በተጠቃሚነት ደረጃ በሚጣሉ ተጨባጭ ፕሮጀክቶችን ማዕከል ያደረጉ የፋይናንስ፣ የዓይነት እና የጉልበት መዋጮዎችን ያካተቱ የፊስካል ፖሊሲዎችን ማስፈን፣ እና
    5. የተቀናጀ ዘመናዊ የመንግሥት ፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ማስፈን ናቸው።

## 27.4. የፋይናንስ ወጪ እና ገቢ አመላካች ግቦች

35. የበክልሉ በአምሥት ዓመቱ ዕቅድ ዘመን ዋና ዋና ግቦች የሚከተሉት ናቸው፤
    1. 2.6 ትሪሊየን ብር ወጪ ያስፈልጋል። ከዚህ ውስጥ 931.9 ቢሊዮን ብር የካፒታል ወጪ ነው። ይህን ወጪ ለመሸፈን ከሚያስፈልጉት የገቢ ምንጮች መካከል ከታክስ ገቢ 1.167 ትሪሊዮን ብር እንደሚሰበሰብ ታቅዷል።

36. ሠንጠረዥ 26 – 1፤ የመንግሥት ወጪ እና ገቢ ዕቅድ፤ 2018 - 2022

| | | 2018 | **2018 -22** | ዓመታዊ አማካይ |
|---|---|---|---|---|
| የታክስ ገቢ | በ2008 ቋሚ ዋጋ | 24,103,583,859 | **214,466,944,674** | 42,893,388,935 |
| | በጊዜው ዋጋ | 97,956,086,866 | **1,167,035,475,117** | 233,407,095,023 |
| የመንግሥት መደበኛ ወጪ | በ2008 ቋሚ ዋጋ | 34,433,691,227 | **282,356,526,026** | 56,471,305,205 |
| | በጊዜው ዋጋ | 156,729,738,986 | **1,706,189,159,426** | 341,237,831,885 |
| የመንግሥት የካፒታል ወጪ | በ2008 ቋሚ ዋጋ | 14,805,266,001 | **161,229,132,298** | 186,380,876,937 |
| | በጊዜው ዋጋ | 85,574,437,486 | **931,904,384,685** | 32,245,826,460 |
| ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ | በ2008 ቋሚ ዋጋ | 49,238,957,228 | **443,585,658,324** | 242,852,182,142 |
| | በጊዜው ዋጋ | 242,304,176,472 | **2,638,093,544,111** | 373,483,658,345 |

2. በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ ማለትም በ2022 የታክስ -ክልላዊ ምርት ምጣኔን 9 በመቶ ይደርሳል።
3. የታክስ ገቢ ጠቅላላ የመንግሥት ወጪን የመሸፈን ምጣኔ በ2015 ከነበረበት 30.8 በመቶ በ2022 ወደ 45 በመቶ ያድጋል።
4. ሁሉን የክልሉ የፋይናንስ መረጃዎች በዘመናዊ የተቀናጀ የመረጃ ሥርዓት ይሰነዳሉ።

## 27.5. የማስፈጸሚያ ሥልቶች

1. ዋና ዋና ሥልቶች
    1. በጥናት ላይ የተመሠረተ የታክስ አሰባሰብ መከተል፣
    2. በፊስካል ፖሊሲ አማካኝነት በተለይ ከክልላዊ ምርት ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ ካለው የግብርናው ዘርፍ ለገጠር ልማት የሚሆን ሀብት ማሰባሰብ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፤ የገጠር ትምህርት የመሬት ታክስ፣ የአካባቢ ጥበቃ የእንስሳት ሀብት ታክስ፣ በጉልበት የሚተመን የልማት መዋጮ፤
    3. ተተግባሪ ስትራቴጂካዊ ፕሮጀክቶችን እና የአካባቢ ልማትን ማዕከል ያደረገ ሕዝባዊ መዋጮ (crowdfunding) መጠቀም፣
    4. ፕሮጀክቶች ወደ ልማት ጸድቀው ወደ ልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭነት እና የተተግባሪነት ጥናት ማካሄድ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማሕበረሰብ እና በባለ ድርሻ አካላት ማስተቸት።

# ክፍል ሰባት

# ሥርዓታት


| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሃያ ስምንት | **ሥርዓታት እና ልማት** |
| ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ | **የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፍ** |
| ምዕራፍ ሠላሳ | **ባሕል፣ እሴቶች እና ወጎች ለልማት** |
| ምዕራፍ ሠላሳ አንድ | **የመንግሥት ተቋማት እና አመራር ሚና** |

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

# ሥርዓታት እና ልማት፤ እንደ መግቢያ

## 28.1. የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች

1. በምጣኔ ሀብት ሣይንስ በተለይም በኢኮኖሚ ዕድገት ንድፈ ሃሳብ መሠረት ቁሳዊ ካፒታል፣ ሰብዓዊ ካፒታል፣ እና ቴክኖሎጂ የአገራትን በነፍስ ወከፍ ገቢ መበላለጥ የሚወስኑ ነገራት ምርት ሲሆኑ፣ የማያቋርጥ የረጅም ጊዜ የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ምንጭ ግን የተከታታይ የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው። የአንድ አገር ያልዳበረ ኢኮኖሚ ከሚኖረው የሠራተኛ ኃይል አንጻር በነፍስ ወከፍ ዝቅተኛ ቁሳዊ ካፒታል ይኖረዋል። እያንዳንዱን የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ በቁሳዊ ካፒታል ለማስታጠቅ በሚደረግ የመካከለኛ ጊዜ ሂደት ምርታማነት ይጨምራል፣ የነፍስ ወከፍ ገቢም በዚያው መጠን ያድጋል። በእንደዚህ ዓይነት ካፒታልን የማስረጽ ርምጃ የነፍስ ወከፍ ገቢን ማሳደግ የሚቻለው ካለው የሰው ኃይል በላይ ካፒታልን ማስፋፋት ተጨማሪ ምርታማነት እና ተጨማሪ የነፍስ ወከፍ ዕድገት በማምጣት ረገድ ትርጉም የለሽ እስከሚሆን ድረስ ነው። በዚህ የቁሳዊ ካፒታል እና የሠራተኛ ኃይል መመጣጠን ውስጥ የነፍስ ወከፍ ገቢን ማሳደግ የሚቻለው ካፒታልን በመጨመር ሳይሆን አሠራርን በመቀየር፣ ነባር የማምረቻ ካፒታልን በአዲስ የተሻለ የማምረት አቅም ባለው ካፒታል ለምሣሌ አዲስ ማሽን በመተካት፣ ነባር መካከለኛ ግብዓቶችን በአዲስ የተራቀቁ ግብዓቶች በመተካት ነው፤ ይህ ክስተትም የቴክኖሎጂ ዕድገት ይባላል።

2. በኢኮኖሚ የገፉ አገራት ተጨማሪ የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ለማምጣት አዲስ ቴክኖሎጂ በመፍጠር የቴክኖሎጂን አድማስ መግፋት የሚኖርባቸው ሲሆን በኢኮኖሚ ተስተካካይነትን ለማረጋገጥ የሚተጉ ታዳጊ አገራት በቴክኖሎጂ ለውጥ ብቻ ሊረጋገጥ የሚችለውን የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ቀድመው የተፈጠሩ ቴክኖሎጂዎችን በመማር ማስመዝገብ ይችላሉ። በዚህ ንድፈ ሃሳብ እና በተሞክሮም በተረጋገጠው መሠረት ከኋላ የኢኮኖሚ ዕድገት ግስጋሴን የሚጀምሩ አገራት ቀዳሚዎቹ ካደጉበት ፍጥነት በላይ ያድጋሉ፤ በኢኮኖሚ ዕድገት ለመመንጠቅ ወይም መዋቅራዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ ከቀዳሚዎቹ አገራት ያነሰ ጊዜ ይፈጅባቸዋል። ይህ ሁኔታ የኢኮኖሚ ተስተካካይነትን የሚያረጋግጥ ሲሆን በዚህ ደረጃ የሚገኙ አገራት የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገትን ማስመዝገብ የሚችሉት የቴክኖሎጂ አድማስ ጥግ ላይ ከሚገኙ አገራት ጋር በቴክኖሎጂ በመወዳደር ነው።

3. ቁሳዊ ካፒታል በቁጠባ እና መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ይከማቻል። ሰብዓዊ ካፒታል እና ቴክኖሎጂ በትምሕርት ላይ በሚደረግ መዋዕለ ንዋይ እና ትጋት፣ ጥናት እና ምርምር ይፈጠራል። ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሳካ፣ በውጤቱም ማሕበረሰባዊ ብልጽግና እንዲረጋገጥ እንደ ማሕበረሰብ መቆጠብ፣ ቁጠባን እና በአንድ ወቅት ከሌሎች ምንጮች የተገኘን የልማት ፋይናንስ ለመዋቅራዊ ሽግግር መሳካት ቁልፍ ሚና ባላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ልማት በማዋል የተሻሉ የማምረቻ አቅሞችን መገንባት፣ የረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ የሆነውን የቴክኖሎጂ ዕውቀት መሻት እና ለዚህም በትምሕርት፣ በስልጠና እና በምርምር መትጋት ቁልፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጫ ርምጃዎች ናቸው። ይህን ማድረግ የቻለ አገር የኢኮኖሚ ተስተካካይነት (economic convergence) ማረጋገጥ ይችላል።

4. ነገር ግን፣ የኢኮኖሚ ተስተካካይነት ፍጹም እና ቀጥተኛ ሳይሆን በሌሎች መነሻ ጉዳዮች የሚወሰን (conditional convergence) ነው። በልማት ሂደት የመቆጠብ፣ መዋዕለ ንዋይ የማፍሰስ፣ የመማር እና የመመራመር አስፈላጊነትን የተረዱ ድሃ አገራት በርካታ ቢሆኑም ከድህነት ወጥተው ለዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተስተካካይነት የበቁት በጣም ጥቂቶች ናቸው። እንደ አገር ከኢትዮጵያ፣ እንደ ክልል ከአማራ ብሔራዊ ክልል አኳያም የእነዚህ ርምጃዎች አስፈላጊነት ታውቆ ያደረ ጉዳይ መሆኑ ከቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጀምሮ እስከ ቅርብ ዘመኑ የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ድረስ በነበሩ የልማት ዕቅድ ሰነዶች መመላከታቸው ማስረጃ ነው። ከዚህ የልማት ዕቅድ አንጻር ትልቁ ጥያቄ የእነዚህን ጉዳዮች አስፈላጊነት ከሰባት አሥርት ዓመታት በፊት ጀምረው በመለየት ወደ ተግባር የገቡ የልማት ዕቅዶች ስለምን አገርን ወደ ብልጽግና ማሸጋገር አቃታቸው የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ የየዘመናቱ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ የሰጡት መልስ 'የአፈጻጸም ችግር' የሚል ነው። በእርግጥም ለዕቅዶቹ ግብ ዳር አለመድረስ ዋናው ምክንያት ዕቅዱን ወደ ተግባር ለማሸጋገር ማሕበረሰብ እና መንግሥት የገነቧቸው የማስፈጸሚያ ሥልቶች በቂ አልነበሩም፤ ሲከፋም በአጋጣሚ ሳይሆን በምክንያት ገዳቢ ነበሩ። እነዚህ ሥልቶች የመፈጸሚያ እና የማስፈጸሚያ ሕግጋት ወይም ሥርዓታት ናቸው። እነዚህ ሥርዓታት የቁሳዊ ካፒታል፣ የሰብዓዊ ካፒታል እና

የቴክኖሎጂ አቅሞችን መጠን እና ጥራት፣ በተለይም እነዚህን አቅሞች ለመገንባት የሚደረጉ የቁጠባ፣ የመዋዕለ ንዋይ፣ እና የትምሕርት ውሳኔዎችን የሚበይኑ የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረታዊያን ናቸው።

## 28.2. ሥርዓታት፤ የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረታዊያን

5. እንደ ካፒታል፣ እና ቴክኖሎጂ ካሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ቅርብ በያኝ ለውጤዎች (growth correlates) የሚያልፉ የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚበይኑ የዕድገት መሠረታዊያን (growth fundamentals) ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ባሕል፣ ሥርዓታት፣ እና ዕድል ይጠቀሳሉ። ነገር ግን፣ ከእነዚህ የዕድገት መሠረታዊያን መካከል የሌሎቹን የዕድገት መሠረታዊያን ተጽዕኖ በማጉላትም ሆነ በመድፈቅ የአንድን አገር ድሃ ወይም ሀብታም የመሆን ዕጣ ፋንታ ለመበየን ገዢ የሆኑት ሥርዓታት ናቸው።

6. ሥርዓታት ማሕበረሰብ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ እና ማሕበራዊ ሕይወቱ ለሚውስዳቸው ውሳኔዎች፣ ርምጃዎች፣ እና መስተጋብሮች የሚገዛባቸው የጋራ መርሆዎች ወይም ሕግጋት ናቸው። ሥርዓታት
    1. የማሕበረሰብ የኢኮኖሚ ውሳኔዎችን እና ግንኙነቶችን የሚበይኑ **የኢኮኖሚ ሥርዓታት**፣
    2. ምን ዓይነት የኢኮኖሚ ሥርዓታት መኖር እንዳለባቸው ከመወሰን፣ የፖለቲካ ሥልጣን ሊኖረው የሚገባውን ኃይል እስከ መሰየም የሚደርስ ሚና ያለው **የፖለቲካ ሥርዓት**፣
    3. በማሕበረሰብ ዓለማዊ እና መንፈሳዊ አመለካከት ላይ ብያኔ የሚሰጡ **የዕምነት ሥርዓታት**፣
    4. ከማሕበራዊ ግንኙነት እስከ የኢኮኖሚ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጪነት ደረጃ ብያኔ የሚሰጡ **የቤተሰብ ሥርዓታት**፣
    5. የማሕበረሰብን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ሥነ ዜጋ፣ አመለካከት፣ እና እሴት የሚቀርጽ **የትምሕርት ሥርዓት**፣ እንዲሁም
    6. በቅርቡ እውቅና እያገኙ የመጡ **የጤና፣ የስፖርት፣ እና የሚዲያ ሥርዓታት** የሚካተቱበት ሰፊ አውድ ነው።

7. እነዚህ ሥርዓታት የማሕበረሰብን በመወሰን፣ በመፈጸም፣ በማስፈጸም የሚገለጹ መስተጋብቶችን የሚገሩ ሕግጋት ሲሆኑ የኢኮኖሚ ውጤቶችን፣ እና የልማት ግቦችን ተፈጻሚነት ይወስናሉ። ሥርዓታት የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያረጋግጥ የማበረታቻ መዋቅር ሊፈጥሩ፣ የኢኮኖሚ ለውጥን ሊገድቡ፣ ወይም የኢኮኖሚ ውድቀትን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከዚህ አንጻር፣ በቁጠባ እና መዋዕለ ንዋይ፣ በትምሕርት ተሳትፎ የሚገነቡ የቁሳዊ እና የሰብዓዊ ካፒታሎች፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂ ቅርብ ቴክኒካዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ መሆናቸው ቢታወቅም፣ እነዚህን አቅሞች ለመፍጠር እና አቀናጅቶ አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ በአፈጻጸም የሚገለጹ አስቻይ የኢኮኖሚ ሥርዓታት፣ እና አስቻይ የኢኮኖሚ ሥርዓታቱን የሚያሰፍን የፖለቲካ ሥርዓት የዕድገት መሠረታዊያን ናቸው።

8. ከሥርዓታት መካከል የአንድን አገር የድህነት ወይም የብልጽግና ዕጣ ፋንታ በመወሰን ረገድ የኢኮኖሚ ሥርዓታት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። የኢኮኖሚ ሥርዓታት ዋና ባሕርይ ተተዋናያን ከመረጡት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚገኝን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መበየን ነው። ግለሰቦች ለመቆጠብ፣ በመዋዕለ ንዋይ ለመሰማራት፣ ለመማር፣ ቴክኖሎጂን ለመቅሰም እና ለማሻሻል ከዚህ ውሳኔ የሚገኝ ጥቅም መኖር ያለበት ሲሆን ይህ የሚረጋገጠው በኢኮኖሚ ሥርዓታቱ ነው። በአንድ አገር የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ መሠላል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንደየደረጃው ከተፈጥሮ ሀብቶች በተለይም ከመሬት፣ ከማዕድናት እና ደን ከሚገኝ ኪራይ፤ ከለማ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ካፒታል በሚገኝ ምንዳዕ፣ ወለድ እና ትርፍ፤ እንዲሁም ከዕውቀት እና ቴክኖሎጂ በሚገኝ ምንዳዕ እና ትርፍ ይገለጻል። የማምረቻ አቅሞች እና መሠረቶች መሬት እና ማዕድን ከመሳሰሉ የተፈጥሮ ካፒታል ወደ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ካፒታል፣ ዕውቀት እና ተጠቃሽ ቴክኖሎጂ በዳበሩ ቁጥር የኢኮኖሚ ጥቅም ያድጋል፤ አገራዊ ኢኮኖሚ ይገዝፋል፤ የነፍስ ወከፍ ገቢም በዚያው መጠን ይሻሻላል፤ ሁለንተናዊ ብልጽግና ይረጋገጣል።

9. ፖለቲካ እና የፖለቲካ ሥርዓት ምን ዓይነት የኢኮኖሚ ሥርዓታት መስፈን እንዳለበት ይበይናል። አገራት በሚፈጥሯቸው የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ሥርዓታት ዓይነት የብልጽግና ደረጃቸው ይወሰናል። ከአንድ የኢኮኖሚ ሥርዓተ መሠረት ወደ ሌላው ሥርዓተ መሠረት ለመሸጋገር የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ እና ተሃድሶ አስፈላጊ ይሆናል። ነገር ግን፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ሥርዓት በታሕታይ እና ላዕላይ መዋቅር በጥቅም የተሳሰሩ በመሆናቸው ለለውጥ ዳተኛ ይሆናሉ።

10. ሥርዓታት በማሕበረሰብ ባሕል ሊወሰኑ ይችላሉ። ተራማጅ ባሕል ተራማጅ ሥርዓታትን፣ ኀታች ባሕል ኀታች ሥርዓታትን ሊያዋልድ ይችላል። በእርግጥ፣ ገዢ ሕግጋት፣ መመሪያዎች እና ሕጋዊ ትዕዛዞች ከመሳሰሉ ዘመናዊ ሥርዓታት ጎን ለጎን ወይም በአመዛኙ በባሕል ልምምድ ውስጥ የሚጠቃለሉ እና ሥር የሰደዱ ማሕበራዊ ስምምነቶች፣ ወጎች፣ እና ልማዶች የባሕላዊ ሥርዓታት አካል ናቸው። ከዚህ አንጻር፣ ሥርዓታት የሰው ልጅ በረጅም ታሪኩ በሂደት ያዳበራቸው የማሕበረሰብን ባሕርይ የሚቀርጹ፣ የሚገሩ፣ እና የሚዳኙ ሕግጋት፣ ደንቦች፣አሠራሮች፣ ወጎች፣ እና የጋራ ስምምነቶች ናቸው። ማሕበረሰብ ሲሻሻል እነዚህ ሥርዓታትም አብረው ይሻሻላሉ፤ ለማሕበረሰብ መሻሻልም አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

11. ከሥርዓታት ውስጥ በማሕበረሰብ ዕምነት፣ ወግ እና ልማድ የሚገለጸው ክፍል ዛሬ በኢኮኖሚ የበለጸጉ አገራትን ጭምር ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በአስከፊ ድህነት እና የግጭት አዙሪቶች ውስጥ አስገብቷቸው ያውቃል። የሰው ልጅ የዕድገት ደረጃ ከተፈጥሮ ጋር ባለው መስተጋብር በተለይም ለሚገጥሙት ችግሮቹ መፍቻ በሚኖረው ግንዛቤ እና ተግባር ይገለጻል። በጥንት ዘመን በየትኛውም የዓለም ክፍል ጎርፍ ሲያጠቃው ለጎርፍ አደጋ መፍትሄ ብሎ የወሰደው ለጎርፍ እና ውሃ ሙላት መገዛት እና እንስሳትን በመስዋዕትነት ማቅረብ ነበር። ፀሐይ ወጥታ ስትገባ እና በረጅሙ የበጋ ዘመን ጨለማ ሲነግስ ለፀሐይ አምላክ ተገዝቷል። ሰደድ እሳት የማይጋፉት አጥፊ ባላንጋራ ሲሆን ለእሳትም ገብሯል። ችግር፣ ርሃብ እና ቸነፈር ከአቅሙ በላይ ሲሆኑ ለአርባ ቀን ዕድል፣ ለጥንቆላ፣ ለድግምት እና መተት፣ እንዲሁም ለአስማት እጅ ሰጥቷል። ሌላው ቀርቶ በዘመናችን የችግር ምንጭን ለሰይጣን፣ የመፍትሄ ኃይልን ያለምንም ጥረት ለፈጣሪ ተዓምራዊ ጣልቃ ገብነት ሰጥቶ ይኖራል።

12. በዚህ ሁሉ ሂደት ችግርን እና መፍትሄን ከራስ የማራቅ እና ለውጫዊ አካል የመስጠት ልምምዶች አሉ። ቀላል ከሚመስለው ጉዳይ ለመጀመር አንዳንድ ማሕበረሰቦች ከእጃቸው የወደቀን ዕቃ ጣልኩት፣ ሌሎች ደግሞ ወደቀብኝ ይላሉ። አንዳንድ ማሕበረሰቦች ከቆመ ግድግዳ ጋር የተጋጨን ሕጻን ሲያለቅስ ጥፋቱ የግዑዙ ቋሚ ግድግዳ ሳይሆን የሕፃኑ መሆኑን ነግረው እንዲጠነቀቅ ይመክራሉ፤ ሌሎች ማሕበረሰቦች ልጁን ለመሸንገል ግዑዙን ግድግዳ በጥፊም በቡጢም ይበቀላሉ። በዚህ ሁሉ ልምምድ አንዳንድ ማሕበረሰቦች ልጆቻቸው የችግሮቻቸው መፍትሄ ከራሳቸው ብቻ እንደሚመጣ ሲያስተምሩ፣ ሌሎች ማሕበረሰቦች ልጆቻቸው ለችግሮቻቸው ሌሎችን እና ሌላ ውጫዊ ኃይልን ሲያማርሩ እንዲኖሩ በጧት ይቀርጿቸዋል። ይህ ከፍ ሲል ለጥፋት የዳረገ የሰው ልጅ ስህተቶች ምንጭ የማይታይ ሰይጣን፣ መፍትሄው ደግሞ ከራስ ጥረት በላይ ፈጣሪ እንደሆነ ይሰብካሉ፤ የአስተምሕሮቶቹ ምንጮች ግን ፈጣሪ የማሰብ ችሎታን ለሰው ልጅ መስጠቱን ያስነብባሉ።

13. እንደ ማሕበራዊ ሣይንስ ትንታኔ ከባሕል የሚመዘዝ ስለ ጊዜ ሁለት ዓይነት አመለካከት ያላቸው ማሕበረሰቦች አሉ። ጊዜ ትናንት፣ ዛሬ፣ የቅርብ ነገ፣ እና የሩቅ ነገ ወይም ከሞት በኋላ ያለ ነገ ተብሎ በአራት ቢከፈል፣ አንዳንድ ማሕበረሰቦች በማይቆጣጠሩት ትናንት ምናልባትም በአያቶቻቸው እና በቅድመ አያቶቻቸው ታሪክ እና ከሞት በኋላ ባለው የሩቅ ነገ ላይ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ። በሌላ በኩል ሌሎች ማሕበረሰቦች የዛሬ ጊዜያቸውን በሚቆጣጠሩት የቅርብ ነገ በተለይም በልጆቻቸው ዘመን ላይ ለውጥ ለማምጣት ይተጉበታል።

14. እነዚህ አመለካከቶች የማሕበረሰብን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ እና የትምሕርት ሥርዓታት በራሳቸው መንገድ ይቀርጻሉ፤ ወይም የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ እና የትምሕርት ሥርዓታት የእነዚህ ማሕበረሰባዊ እሴቶች ነጸብራቅ ይሆናሉ። ከፍ ባለ ደረጃ የቅርብ ዘመናት የዕምነት ሥርዓታት የፊውዳሊዝምን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥርዓታት አስጠባቂ ሆነዋል። በአጸፋው፣ የፖለቲካ ሥርዓቱ ለእምነት ሥርዓታት የኢኮኖሚ እና የማሕበራዊ ልዕልና ተጠቃሚነት ዋስትናን ችሯል። የፊውዳሊዝም ሥርዓት በቁጠባ እና በመዋዕለ ንዋይ የሚከማች፣ በትምሕርት - ወለድ እውቀት እና ቴክኖሎጂ የሚተባ የማምረቻ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ካፒታል ለማከማቸት የተፈጠረ ሳይሆን የተፈጥሮ ሀብትን በተለይም መሬትን የሀብት ምንጭ ያደረገ በኪራይ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ነበር። ይህን ሥርዓት በመቀየር ማሕበረሰብን ወደተሻለ ብልጽግና የሚያሸጋግር ሥርዓት ለመፍጠር ፊውዳሊዝም መቀየር ነበረበት። ነገር ግን፣ የፊውዳሊዝም ሥርዓት ወይም ሥልተ ምርት ቢቀየር በለውጡ ምክንያት ጥቅም የሚያጣው የፊውዳሉ የፖለቲካ ልሂቅ ነው። የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የዕምነት፣ የቤተሰብ፣ የትምሕርት፣ እና በዚህ ዘመን ደግሞ የሚዲያ ሥርዓታት በሚተራመሱበት አውድ ለኢኮኖሚ ዕድገት እና ሁለንተናዊ ብልጽግና መሠረት የሚሆን ገዢ ሥርዓት መለየት እና የዚህን ገዢ ሥርዓት ቅርጽ፣ ይዘት፣ እና ተግባር መለየት የልማት ትልቁ ጥያቄ ነው።

## 28.3. የፖለቲካ ሥርዓት እንደ ገዢ ሥርዓት

15. ስለማሕበረሰብ ብልጽግና ሲወሳ ሀብት መፍጠሪያው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው። ምናልባትም የሁሉም ሥርዓታት ማጠንጠኛ የኢኮኖሚ ጥቅም ነው። በኢኮኖሚ ዕድገት የሚረጋገጥ ብልጽግና የኢኮኖሚ ሥርዓታትን ጨምሮ አስቻይ የሆኑ ሥርዓታት ያስፈልጉታል። የሥርዓታት ለውጥ ለአሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት በር ይከፍት ዘንድ ከሥርዓታት ውስጥ ቀድሞ መቀየር ያለበት እና ለሌሎች የሥርዓታት ዓይነቶች መለወጥ የላቀ ሚና ያለው የፖለቲካ ሥርዓት ነው። ለዚህ ምክንያትቱ፣
    10. የፖለቲካ ሥርዓት ራሱን ቀይሮ ሌሎች ሥርዓታትን ለመቀየር የሚያጣው የኢኮኖሚ ጥቅም ስላለ፣ ይህንንም ጥቅም ለማስጠበቅ ጉልበት ስላለው የኢኮኖሚ ሥርዓትን ለመቀየር ከፍተኛው ዳተኝነት የሚመነጨው ከዚህ ሥርዓት በመሆኑ፣ እና
    11. በዘመናዊ አስተሳሰብ የኢኮኖሚ ዕድገትን እና በአጠቃላይ የብልጽግና ግቦችን በማረጋገጥ ረገድ የሌሎችን ሥርዓታት የመነተት አቅም ሥርዓታቱን በማዘመን፣ ወይም ተከታይ በማሳጣት፣ ወይም በመጨፍለቅ አሸንፎ ማሕበረሰብን ወደ የሚደፍቀው ሳይሆን ወደ የሚያሻግረው ሥርዓት ይተምም ዘንድ ለማስተባበር ኃላፊነት እና አቅም ስላለው ነው።

16. በአገራት ተሞክሮ የቅድመ - ስልጣኔ ማሕበረሰብ የሥርዓታት ትርምስ መልክ ለማስያዝ የማስተባበር ኃላፊነት የወሰዱት ጥቂት የማሕበረሰብ ክፍሎች በተለይም የፖለቲካ መሪዎች ናቸው። በዓለም ደረጃ በአብዛኛው ማሕበረሰብ የተስተዋለው የማሕበረሰብ እና በሰፊው አውድም ሲታይ የፖለቲካ መሪዎች ማሕበረሰቡ የሚያምንበትን ባሕል የበለጠ ተጠቃሚ እንዲያደርጋቸው ከመጠቀም ባለፈ ለለውጥ አለመትጋታቸው ከሰው ልጅ ረጅም ታሪክ ውስጥ ሰው በመከራ ያሳለፋቸው ዘመናት ይገዝፋሉ። በተለይ በጥንታዊ፣ በባሪያ አሳዳሪ፣ እና በፊውዳሊዝም ሥርዓተ ማሕበራት የነበሩ የፖለቲካ ልሂቃን ሦስት ኃይል ነበራቸው፤ የፖለቲካ ኃይል፣ የዕምነት ተቋማት ኃይል፣ እና የኢኮኖሚ ኃይል። የአገራት ሀብት መሠረት የሆነው መሬት የገዥዎች ሲሆን መሪዎች የሀብት የበላይነት አላቸው። ይህን የሀብት የበላይነት ለማስጠበቅ የፖለቲካ ኃይልን ይጠቀማሉ። ሕዝብ በፖለቲካ አመራሩ ላይ እንዳያምጽ የዕምነት መሪነትን ደርበው አልያም ስዩመ - እግዚአብሔር ሆነው፣ ለዚህም መቀባት ውለታ ለቤተ-እምነት ሥርዓቶች ሢሶ መሬት ሰጥተው ማሕበረሰቡ ድሃ እና ሀብታም ያለ እና የሚኖር፣ ድሃ ሀብትን የሚሻው በሰማይ ቤት መሆኑን አሳምነው እንዲገዙ ረድቷቸዋል።

17. በ12ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ በተለይም በአሁኗ ጣሊያን የተጀመረው ከግሪክ እና ከመካከለኛው ምሥራቅ የተወሰዱ ፍልስፍና እና በአጠቃላይ የተሃዲሶ (renaissance)፣ ይህን ተከትሎ በእንግሊዝ ያቆጠቆጠው የመንግሥት ከኃይማኖት መለየትን ያሰፈኑ፣ ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዕድል የሰጠ ፓርላሜንታዊ ሥርዓት መስፈን፣ ይህንንም ሥርዓት ተከትሎ ሕዝባዊ መሠረት ያለው የቴክኖሎጂ ፈጠራ ያዋለደው የኢንዱስትሪ አብዮት የረጅሙን የአውሮፓ የግጭት እና የድህነት አዙሪት የሰበሩ ተከታታይ እና ድምር ክስተቶች ናቸው።

18. ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ ባሉ ዘመናት የማሕበረሰቦችን እና የአገራትን የብልጽግና ፍኖት (growth trajectory) ልዩነት የፈጠረው በእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት በጥቂት ዝቅተኛ ማሕበረሰብ አባላት በዳሰሳ የተገኙትን ውስን ግን አስደናቂ እና ዓይን ገላጭ የቴክኖሎጂ ግኝቶች በቴክኒክ እና በሳይንሳዊ ትምህርት ለማሕበረሰባቸው በማዳረስ በተጉ እና ከመጠቀም ያላለፈ ጥረት ባላደረጉ መካከል በነበረ ልዩነት ነው። የሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት እና የዘመናችን ሦስተኛው ወይም የዲጂታል ቴክኖሎጂ አብዮት የሣይንሳዊ ዕውቀት መር ቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው።

19. ከዚህ መረዳት የሚቻለው የሥርዓታት ዋና ባሕርይ ካለፈው ታሪካቸው ጋር በእጅጉ የተቆራኙ መሆናቸው እና ለመቀየርም አስቸጋሪ መሆናቸው ነው። ለዚህ ዋና ምክንያት ከሥርዓታቱ መካከል በተለይ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ሥርዓታት በእጅጉ የተቆራኙ እና የቁርኝታቸው ማጠንጠኛ በለውጥ የሚታጣ ጥቅም ያለ መሆኑ ነው። ገዢ ሥርዓት የፖለቲካ ሥልጣን የያዙ ኃይሎችን የግል እና ቡድናዊ ጥቅም እስካስጠበቀ ድረስ በፈጣን ዕድገት ማሕበረሰብን የሚያበለጽግ ሌላ ሥርዓት መፍጠር የእነዚህን ቡድኖች ጥቅም ያሳጣል። በዚህ ሁኔታ ሁለት መንታ ሥርዓታት ይኖራሉ፤ የብልጽግና ኢኮኖሚክስ ወይም የድህነት ኢኮኖሚክስ፤ የዚህ ነጸብራቅም የብልጽግና ፖለቲካ ወይም የድህነት ፖለቲካ። እነዚህ ሥርዓታት የማሕበረሰብ ምርጫዎች ናቸው። ማሕበረሰብ ከሚያበለጽገው ይልቅ የሚኮንነውን ሥርዓት እንዲመርጥ ከዚህ ኪራይ የሚያተርፉ የፖለቲካ ልሂቃን ከኢኮኖሚ በመለስ ያሉ በዚህ ትውልድ የማይፈቱ የትናንት ታሪክን በማንሳት፣ በማንነት ዙሪያ የሚያተኩሩ ስሜት ቀስቃሽ አጀንዳዎችን በመቆስቆስ የለውጥ ጥያቄን ያዳፍናሉ። ለውጥ በባሕሪው አሮጌውን በአዲስ ይተካል፤ የፖለቲካ ሥርዓት በማሕበረሰብ ውስጥ ማን ሥልጣን ይዞ መቆየት እንዳለበት እና ይህን ሥልጣን ለምን ዓላማ ማዋል እንዳለበት

ይበይናል። በዚህ ምክንያት፣ የማሕበረሰብ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ ለውጥ ሲታሰብ ስለ ማሕበረሰብ እና አገር ብልጽግና ሲባል የራስ የሚለውን ጥቅም አሳልፎ የሰጠ (selfless) የፖለቲካ መሪ ወይም መሪ ትውልድ ማግኘት ለጥቂት አገራት ብቻ የተሳካ በዕድል ጭምር የሚፈጠር አጋጣሚ ነው። የዚህ ዓይነት መሪ ትውልድ ስልጣን፣ ሕዝባዊ ቅንነት (ወገንተኝነት)፣ እና አቅም ያስፈልጉታል።

## 28.4. ሥርዓታት እና ልማት በኢትዮጵያ

20. ለአለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልልን ጨምሮ በኢትዮጵያ ገዢ (dominant) የኢኮኖሚያዊ ጥቅም መሠረት መሬት ሲሆን አላባውም ከእሴት ይልቅ ወደ ኪራይ ያዘነበለ ነው። የሰለጠነው ዓለም ይህን ከፊውዳል ሥርዓት ጋር የተያያዘ ሥርዓት ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ቀይሮታል። በኢትዮጵያ በፊውዳሉ ሥርዓት ወቅት ለልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትልቅ ተግዳሮት የነበረ ሕልውናን ከመሬት ባለቤትነት ጋር የሚያያይዝ ሥርዓት በሶሻሊዝም ዘመን እና በኢሕአዴግ አገዛዝ ወቅት ቀጥሏል። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1949 ወደ ትግበራ የገባው የመጀመሪያው የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ  አፈጻጸም ግምገማ የለያቸው ሦስት አበይት ተግዳሮቶች ለለውጥ ዳተኛ የሆነ ከባሕላዊ አመራረት እና አጠቃቀም (ሥልተ ምርት) ለመላቀቅ ፍላጎት የሌለው ማሕበረሰብ ('entrenched traditional society')፣ የመሬት ሥሪት፣ እና ወደ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ልማት ለመሰማራት ፍላጎት እና ዕውቀት ያለው የግል ዘርፍ አለመኖር ናቸው። በወቅቱ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው ማሕበረሰብ የተሰማራበት ከመሬት ጋር የተያያዘ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ነጠላ ሥልተ ምርት አንድ የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። በልማት ዕቅዱ ግብ መሠረት የልማት ፋይናንስ ተመቻችቶለት ወደ አምራች እና ዘመናዊ ግብርና እንዲገባ የተጠበቀው የግል ዘርፍ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነውን የፋይናንስ ብድር በከተሞች ሕንጻ የሠራበት ሲሆን ይህ ከሕንጻዎች በሚገኝ ኪራይ ላይ የተንጠለጠለ ሌላ የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። ባንኮች የረጅም ዘመን ግን ዘላቂ ፋይዳ ላላቸው የአምራች ኢንዱስትሪ፣ ለግብርና፣ እና ለትምሕርት ብድር ከማመቻቸት ይልቅ የአጭር ጊዜ አቋራጭ ጥቅም ለሚያስገኙ የከተማ ውስጥ የቤቶች ግንባታ፣ ከፍ ካለም ለሆቴል አገልግሎቶች ብድር የሚያመቻቹ ሲሆን ይህም ሌላው የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው።

21. ሥርዓታት ይደጋገፋሉ፤ ሕልውናቸውም ከኢኮኖሚ ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሥርዓቶቹ በሌሎች በተለይም በፖለቲካ ሥርዓታት የተደገፉ ናቸው። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት መሬትን ወደተሻለ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ጥቅም ለማሸጋገር ሪፎርም እንዳይደረግ የከለከለው በፓርላማ ጭምር መቀመጫ የነበረው የመሬት ከበርቴው እና ምስለኔው ሲሆን፣ ለዚህ ምክንያቱ ሪፎርሙ ከመሬት የሚገኝ ከጭሰኛ የሚሰበሰብ ኪራይ ስለሚያሳጣው ነው። በ1966ቱ አብዮት ወቅትም የማርክሲዝም - ሌኒኒዝም አስተምህሮት እንደሚተነትነው በወዛደሩ ትርፍ የሥራ ሰዓት ላብ እና ደም ከተከማቸ የኢንዱስትሪ ፋብሪካ አቅም ወይም ካፒታል ይልቅ መሬት ሊሞቱለት የሚገባ ዋናው የማታገያ አጀንዳ ነበር።  የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም የሚኩራራበት የአብዮት ትሩፋት መሬትን በገጠር ለተወለደ ዜጋ ሁሉ በፍትሃዊነት ማከፋፈል ሲሆን፣ የተመሰረተውም ካርል ማርክስ በጠበቀው መልኩ በዳበረ ካፒታል ላይ ሳይሆን ከመሬት ከሚሰበሰብ የኮታ ዕህል ነበር።

22. ኢሕአዴግ በርዕዮት ዓለም ደረጃ የድጋፍ መሠረቱ አርሶ አደር፣ በሕግ በተለይም በሕገ-መንግሥት ለድርድር የማይቀርብ የመንግሥት ሀብት መሬት፣ በፖሊሲ ደረጃ የኢኮኖሚ ፖሊሲው በአነስተኛ የመሬት ባለይዞታ አርሶ አደር ላይ የተመሠረተ ግብርና - መር የኢንዱስትሪ ልማት ነበር። በአምራች ኢንዱስትሪ እና በኮመርሻል ግብርና ሊሰማራ ለሚችለው የግሉ ዘርፍ የተነፈገው ድጋፍ፣ እና በርዕዮት ዓለም ጭምር ምሁራንን ለአጋርነት በማያበቃ ወላዋይነት እንዲሁም ትምክሕተኝነት የተሰጠ ፍረጃ በተዘዋዋሪም ቢሆን የፖለቲካ ሥርዓቱ ለለማ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ካፒታል፣ እንዲሁም ዕውቀት ትኩረት እንዳልሰጠ፤ ከዚህም ባለፈ የፖለቲካ አጋር ካልሆነ መደብ የሚመጣ የልማት አቅም የፖለቲካ ሥልጣንን ሊያሳጣ እንደሚችል መስጋቱን የሚያሳይ ነው።

23. የመሬት ሊዝ ሥርዓት ተግባራዊ የሆነበት አመክንዮ መንግሥት እንደሚያምነው አገሪቷ ያላት ውድ ሀብት መሬት ስለሆነ መንግሥት ከሊዝ ከሚያገኘው ገቢ ልማትን ለማፋጠን ነው። ከመሬት ኪራይ መሰብሰብ በተቋም እንደ ሥርዓት የተጀመረው በመንግሥት ነው። በዚህም እንዴት የኢኮኖሚ ሥርዓታት በፖለቲካ ሥርዓት እንደሚቀረጹ ማስተዋል ይቻላል። የሊዝ ገቢ ከፍ ለማድረግ ሲባል በእንቁጥ እንቁጥ ለጨረታ የሚቀርብ መሬት የመሬትን ኪራይ አናረው። መሬትን በምርት ሂደት በግብዓትነት ተጠቅሞ ምርት ከማትረፍረፍ ይልቅ መሬትን በከፍተኛ የሊዝ ዋጋም ቢሆን ገዝቶ እንደ ጥሬት እያጠሩ ማስቀመጥ እና ማገላበጥ የበለጠ አዋጭ ስትራቴጂ ሆነ። ይህን በፖለቲካ ሥርዓቱ ድጋፍ ውድ እንዲሆን የተደረገ የመሬት ሀብት  ዕድሉን ያገኘ ሁሉ ለመቀራመት አላመነታም፤ የመንግሥት

በይፋ፣ የመንግሥት ኃላፊ እና ባለሙያ በስውር፣ ባለሀብቱ፣ የመኖሪያ ቤት ፈላጊ ዜጋ፣ ደላላው፣ እና የዕምነት ተቋማት ጭምር ከምንም ነገር በላይ መሬት ለማግኘት ተፎካከሩ።

24. ኢሕአዴግ በዚህ ሁኔታ አገር እና ሕዝብን የሚያሻግር የኢኮኖሚ ልማት እንደማይረጋገጥ የተረዳው ከሁለት አሥርት ዓመታት በኋላ ነው። መሬትን ለተሻለ ፋይዳ በተለይም ለአምራች ዘርፎች ልማት በማዋል ለውጥ ለማምጣት በማሰብ የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነድፎ ወደ ተግባር ተሸጋገረ። የግሉ ዘርፍ በአጭር ጊዜ በማይደፍራቸው በአምራች ኢንዱስትሪ እና ለእነዚህ ዘርፎች ልማት መሠረት በሆኑ የመሠረተ ልማት ዘርፎች መንግሥት በቀጥታ ተሰማራ። በአንጻራዊነት የግሉ ዘርፍ ሊገባበት በሚችለው ኮሜርሻል ግብርና ደግሞ የግሉ ዘርፍ እንዲሰማራ ተደረገ። በተለይ በግብርና ዘርፍ በሰፋፊ እርሻዎች የተሰማሩ አልሚዎች ነጻ በሚባል የሊዝ ዋጋ ምጣኔ የተረከቡትን መሬት አስይዘው ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ብድር ማግኘት እንዲችሉ ተመቻቸ። በአጠቃላይ በአምራች ዘርፎች ለሚሰማሩ አልሚዎች የረጅም ጊዜ ብድር ለማመቻቸት የግል የንግድ ባንኮች ከሚያበድሩት ገንዘብ ውስጥ 27 በመቶ የሚሆነውን በኢትዮጵያ ልማት ባንክ እንዲያስቀምጡ ፖሊሲ ወጣ። ለዚህ ከፍተኛ የመዋቅራዊ ሽግግር ግብ የሚመጥን የሰለጠነ የሰው ኃይል ይኖር ዘንድ የትምሕርት ሥርዓቱ በተለይም ለተፈጥሮ ሣይንስ እና ቴክኖሎጂ ትኩረት ሰጠ። በዚህም የቴክኒክ እና ሙያ ትምሕርት ቤቶች ወይም ኮሌጆች በስፋት ተከፈቱ፤ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲ ቁጥር በአጭር ጊዜ ከሁለት በአሥርት በሚቆጠሩ ደረጃ አደገ፤ የከፍተኛ ትምሕርት የተማሪዎች ቅበላ 70 በመቶ የሚሆነው ለተፈጥሮ ሣይንስ እና ቴክኖሎጂ እንዲሆን ተወሰነ። እነዚህ ሁሉ በፖለቲካ ሥርዓቱ የተመቻቹ የኢኮኖሚ ሥርዓታት ሲሆኑ ትክክለኛ ርምጃ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

25. የፖለቲካ ሥርዓቱ ግልጽ እና ትክክል ከሚመስሉት አሳላጭ የኢኮኖሚ ሥርዓታት ውስጥ የተጠቀማቸው የማስፈጸሚያ ሥልቶች ነበሩ፤ እንደ ስኳር ፋብሪካ፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ የከፍተኛ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ፣ በከፍተኛ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሮ - ሜካኒካል ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ዕውቀት እና የክሕሎት ልምድ የሚጠይቁ በመሆናቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ መወዳደር የሚችሉ ተቋራጮች መሳተፍ ሲኖርባቸው ለፖለቲካ ሥርዓቱ ታማኝ ለሆኑ አካላት እጅ ማፍታቻ እና መበልጸጊያነት ተሰጡ። በግብርናው ዘርፍ ከለጋስ ማበረታቻ ጋር የተሰማሩትም በውድድር ሥርዓት ሳያልፉ በፖለቲካ ታማኝነት ተመረጡ። ውጤቱ በሁሉም መስክ ውድቀት እንጂ ስኬት አልተመዘገበም። የመዋቅራዊ ሽግግር እንደሚያረጋግጥ የተጠበቀው እውቀት መር ኢኮኖሚ በሣይንስ እና ቴክኖሎጂ የተመረቁ ወጣቶችን መቅጠር ስላልቻለ የተማረ ሥራ አጥነት ነገሰ፤ የኢኮኖሚ መዋቅሩ ከዕውቀት ይልቅ ለቁሳዊ ግብዓቶች እና መሬት የበለጠ ዋጋ ሰጠ። ከሁሉም በላይ ትምሕርት ዋናው ምናልባትም ብቸኛው ከድህነት የማምለጫ መሣሪያ ለመሆኑ የተያዘው እምነት ተሸረሸረ።

26. እነዚህ ምልክቶች በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጀመሪያዎቹ ሁለተ የትግበራ ዓመታት እየታዩ ነበር። ይህ አካሄድ አጥፊ እንደሚሆን የተገነዘቡ እንዳንድ ከፍተኛ አመራሮች "ኢሕአዴግ ካለው የትግል ልምድ በጦርነት የመሸነፍ እና የመውደቅ ሥጋት የለነትም። የኢሕአዴግ ትልቁ የወቅቱ ፈተና ሙስና ነው። ወይ በሙስና አረንቋ ውስጥ እንበሰብሳለን፤ ወይም በትግላችን ከዚህ አረንቋ ተመንጥቀን እንወጣለን" በማለት ስጋታቸውን ገልጸው ነበር። ነገር ግን፣ የዚህ ዓይነት የሙሰኛ ሥርዓት አደገኛነት የገባቸው እነዚህ ጥቂት አመራሮች ይህን ስጋት ለመቀልበስ የሚያስችለው የፖለቲካ ጉልበታቸው እና የማስፈጸሚያ በትራቸው በአብዛኛው የሙስናው አካል ስለነበር ይህን ለማስቆም ዘግይተው ነበር።

27. ከዚህ ሁነት ሦስት አበይት የሥርዓታት ባሕርያትን መገንዘብ ይቻላል፤ በመጀመሪያ፣ ሥርዓታት የኢኮኖሚ ተዋንያንን ባሕርይ እና የሚጠብቁትን የኢኮኖሚ ጥቅም ወይም አላባ ይወስናል። በዚህም ምክንያት የሥርዓታት ባሕርይ የአንድን አገር ስኬት ወይም ውድቀት ይበይናል። መልካም የኢኮኖሚ ሥርዓት በሌላ የፖለቲካ ሥርዓት ላይሳካ፣ ጥሩ የትምሥርት ሥርዓት በመጥፎ የኢኮኖሚ ወይም የፖለቲካ ሥርዓት ምክንያት ከትሩፋት ይልቅ ወደ ዕዳ እና ሥጋት የደላ ትውልድ ሊቀርጽ፣ በውጤቱም የረጅም ጊዜ የመልማት ተስፋን ሊያደበዝዝ ይችላል። ሁለተኛ፣ የኢኮኖሚ ሥርዓታትን የሚያሰፍን፣ የሚያስጠብቅ፣ እና የሚቀይር የፖለቲካ ሥርዓት የመሆኑን ያህል አሠራራቸውንም ለውጤታማነትም ሆነ ለውድቀት በሚበቁበት ዕድል ላይ ብያኔ የሚሰጠው የፖለቲካ ሥርዓት ነው። በተለይ የፖለቲካ አመራር የሕዝብን አጀንዳ የሚያስጠብቁ ስለሕዝብ ታጋዮች ወይም የራሳቸውን እና በዙሪያቸው ያለ ጠባብ የፖለቲካ መሠረት ጥቅም የሚያስጠብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ወይም የሚቆጣጠሩ በሕግ አውጪ፣ በአስፈጻሚ፣ እና በሕግ ተርጓሚ መዋቅሮች የሚሰየሙ የፖለቲካ ሥርዓታት ናቸው። ሦስተኛ፣ የፖለቲካ ተቋማት አሻጋሪ አጀንዳዎችን በተገቢ የኢኮኖሚ እና የትምሕርት ሥርዓታት በማስፈጸም፣ እምነት እና ቤተሰብ የመሳሰሉ ተጓዳኝ ሥርዓታትን በማስተባበር ከልማት ጎን በማሰለፍ ማሕበረሰብን ለማስተዳደር (govern) እና ሥርዓት ለማስያዝ (regulate) ሥልጣን (power) እና አቅም (capacity) ያስፈልገዋል።

28. በአለፉት ዘመናት በኢትዮጵያ ለተወጡኑ የልማት ዕቅዶች ዳር አለመድረስ የግጭት ታሪክ አንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ የባህል ጉዳይ እንደ መሠረታዊ የዕድገት አፈጻጸም ተግዳሮት ተጠቃሽ ሊሆን ይችላል። ባሕል ወይም እሴት በዘመን ሂደት የሚቀየር ግን ረጅም ሂደት ነው። ባሕልን በመቀየር ሂደት በትምህርት የሚገኝ ሳይንሳዊ ዕውቀት የስልጣኔ አቋራጭ መንገድ ተደርጎ ስለሚወሰድ የትምሕርት ሥርዓቱም ሌላው የልማት አፈጻጸም ገላጭ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሳይንሳዊ ዕውቀት አገር እና ማሕበረሰብ ሲሰለጥን ምን እንደሚመስል አይቶ ለመተግበር የሚያስችል መሣሪያ ነው። በትምህርት የሚገኝን ሳይንሳዊ ዕውቀት አሻጋሪነት በመገንዘብ ከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ጥረት ተደርጓል። የትምህርት ሥርዓት በተለያዩ ምክንያቶች የሚጠበቅበትን አስተዋጽዖ ሳያደርግ ዛሬ ላይ ደርሷል። የትናንት ወጣት በእምነት አስተምህሮቶች፣ በማሕበረሰብ፣ እና ሥራ አጥነት ባልበዛበት የሥራ ቦታ ማንነቱ ሲቀረጽ ቆይቷል። ዛሬ የወጣቱን አስተሳሰብ የሚቀርጹ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች፣ የዕምነት አስተምህሮቶች፣ የፖለቲካ አውዶች፣ ማሕበራዊ ማንቂያ (ሶሻል ሚዲያ)፣ እና አልባሌ መዋያ ቦታዎች ናቸው። የትምህርት ሥርዓት ከሁሉም የማንነት መቅረጫ አውዶች ተወዳድሮ እና በልጦ የተሻለ አሻጋሪ፣ እና ርትዕ ትውልድ የመፍጠር ኃላፊነት ነበረበት። ነገር ግን፣ ከሥርዓታቱ መካከል ይህን ሁሉ ማስተባበር የነበረበት የፖለቲካ ሥርዓቱ ቁልፉን ድርሻ ይወስዳል። በርካታ ተዋንያን ካሉበት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ በተለይ የመንግሥትነት ኃላፊነት የወሰደ መሪ ትውልድ ይህን ለማድረግ ሥልጣን እና በርካታ አቅሞች ነበሩት፤ ከመንግሥት ቢሮ እስከ ትምህርት ቤት ሴኪዩላር ሥርዓት የማስፈን፣ ሕግን የመጠቀም፣ በሕዝባዊ አደረጃጀት ማሕበረሰብን የማንቃት እና በልማት የማትጋት፣ መልካም ዜጋን መርጦ በሲቪል ሰርቪስ የመቅጠር፣ ሀብት የመሰብሰብ፣ የክልሉን እና የአገሪቷን የሀብት ፍሰት አቅጣጫ የመወሰን መሣሪያዎች የመንግሥት ነበሩ፤ የጎደለው ከራስ እና ከራስ ቡድን በላይ ለሕዝብ መስዋዕት የመሆን ገዢ የሆነ አመለካከት እና ተግባር ነው።

29. ከዚህ አኳያ፣ የዚህ የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ከአለፉት የልማት ዕቅዶች በተለየ ሁኔታ ለውጥ እንደሚገኝበት የሚጠብቀው ከአዳዲስ ቴክኒካዊ እይታዎች በላይ ስለ አገራዊ ለውጥ እና ዘላቂ ጥቅም የራስ እና ጠባብ ቡድናዊ ጥቅምን አሳልፎ በመስጠት ስለለውጥ ለትጋት በምልዓት የወሰነ እና የተናበበ ዕድለኛ መሪ ትውልድ የመፈጠርን ዕድል ነው። ክፉ ዕጣ የሚመስልን አስከፊ ድህነት ከተሻገሩ አገራት ልምድ መማር እንደሚቻለው፣ አገርን ለማሻገር ይህ መሪ ትውልድ ራሱ ተቆጭቶ ሕዝብን ለለውጥ ማሰለፍ፤ በለውጥ፣ ለለውጥም በዕውቀት ኃይል ከማመን የዕድገት ቴክኒካዊ ዝርዝርን እስከ መረዳት የሚደርስ ቁርጠኛ የፖለቲካ አመራር መሆን ይጠበቅበታል።

## 28.5. የሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ታሳቢ የሚያደርገው የሥርዓታት ሚና

30. በሃያ አምሥት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ እና ይህ ፍኖተ ካርታ በሚተገበርባቸው ተከታታይ የአምሥት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዶች የተመላከቱት የልማት ግቦች በቴክኒክ ደረጃ፣ እና በአገራት ተሞክሮ ረገድ መተግበር የሚችሉ ናቸው። እነዚህን ዓላማዎች፣ እና ግቦች ዳር በማድረስ በተለይም በአንድ ትውልድ ለማረጋገጥ የተወጠነውን የዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት፣ ሁለንተናዊ ብልጽግና ርዕይ ዕውን ለማድረግ የሥርዓታት ሚና ከፍተኛ ነው። ይህ የልማት ዕቅድ የሚከተሉትን የሥርዓታት አቅጣጫ ታሳቢ ያደርጋል፤

1. ፈጣን፣ አሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት የሚያሳልጡ በፖሊሲ የተደገፉ የኢኮኖሚ ሥርዓታት ይሰፍናሉ።
2. ሽፋንን ከጥራት ጋር ያገናዘበ፣ ቀልጣፋ፣ ምርታማ፣ ግብ እና ውጤት - ተኮር የሆነ፤ ትውልድን ለዘመኑ የዓለም ትሩፋት እና ስጋት በብቃት የሚያዘጋጅ፣ አገር ሲሰለጥን ምን እንደሚመስል ከሩቅ አይቶ ሕዝብ የሚያሻግር፣ መልካም እሴቶች የተላበሰ ርትዕ ትውልድ የሚቀርጽ የትምሕርት ሥርዓት ይሰፍናል።
3. የመንግሥት ሚና ሁሉን ነገር ማሟላት የሚችል ሉአላዊ ኃይል ሳይሆን ማሕበረሰብ ራሱን ችሎ፣ ጥሮ እና ግሮ ማግኘት እንዲችል የሚያስተባብር፣ የሚያሳልጥ፣ አመቺ አውድ የሚፈጥር መሆኑን፤ የጠንካራ እና በራሱ የሚብቃቃ መንግሥት መሠረት ጠንካራ እና በራሱ የሚብቃቃ ሕዝብ መሆኑን፤ ዴሞክራሲ መብትን መጠየቅ እና መጠቀም ብቻ ሳይሆን ግዴታን መወጣት መሆኑን፤ ዕምነት የግል ነው ሲባል ዕምነት ለተከታዩ ምልዑ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት በልብ እና በቤት የሚተገበር እንጂ ለፉክክር አደባባይ ቀርቦ የግጭት ምንጭ መነሻ አለመሆኑን፤ እኩልነት በፍትሃዊ ተሳትፎ በሚገኝ ሀብት እና ብልጽግና እንጂ የሚጥሩ ነፍሶችን ጠልፎ በመጣል እኩል በመደህየት አለመሆኑን የሚረዳ እና የሚቀበል ማሕበረሰብ፤ ማሕበረሰቡ ዕውቀት እና ጥበብን በመሻት በጥረቱ እና በላቡ እንዲበለጽግ የሚያበረታቱ የዕምነት አስተምሕሮቶች በምልዓት የሚገለጹበት የማሕበረሰብ አቀፍ ተቋማት እና የዕምነት ሥርዓታት ይሰፍናሉ።

4. የማሕበረሰቡን ጤና እና ደህንነት፣ አካላዊ እና መንፈሳዊ ብቃት የሚጠብቁ የጤና እና ስፖርት ሥርዓታት ይበለጽጋሉ።
5. ስለ ማሕበረሰብ እና አገር ልማት መልካሙን አቅጣጫ የሚያሳዩ የሚዲያ ክፍሎች የዘመኑን ዛብ የለቀቀ የመገናኛ አውድ ተጠቅመው በምክንያትም ሆነ በግደለሽነት አፍራሽ ሚና የሚጫዎቱ ሚዲያዎችን ትርጉም የለሽ የሚያደርጉበት የሕዝብ ወገንተኛ የሚዲያ ሥርዓት ይጠናከራል።
6. ርትዕ ማሕበረሰብ ከርትዕ ቤተሰብ የሚመነጭ መሆኑን በመረዳት ለራስ፣ ለቤተሰብ፣ ለማሕበረሰብ እና ለአገር የሚያስብ እና የሚተጋ ትውልድ እንዲፈጠር ከጠባብ የቤተሰብ እና ቡድን ግብ ያለፈ አገራዊ እና ሰው የመሆን የጋራነትን ከሩቅ በማሳየት ትውልድ የሚቀርጽ የቤተሰብ ሥርዓት ይፈጠራል።
7. ጎታች ኃይሎችን አሸንፎ ከላይ የተጠቀሱትን ሥርዓታት ማስተባበር እና በትክክለኛ የለውጥ ጎዳና ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚችል፣ ለዚህም ከራስ እና ከጠባብ ቡድናዊ ፍላጎት በላይ ስለ አገር ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ መሪ ትውልድ የሚዘውረው፣ በሕግ የበላይነት እና በማሕበራዊ ፍትሕ የሚገለጽ፣ በሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ የሰመረ አመራር የሚሰጥ የፖለቲካ ሥርዓት ይሰፍናል።

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

# የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፍ

## 29.1. የዘርፉ ሚና

በሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት የሕግ የበላይነትን በማስከበር ሰላምና ደህንነትን ማስፈን የመንግስት ተቀዳሚ ኃላፊነት ነው፡፡ የሕግ የበላይነት፣ሰላምና ደህንነት ሰርቶ ለመኖር፣ ወልዶ ለመሳም፣ ነግዶ ለማትረፍ፣ ተምሮ ለመለወጥ እና አገርና ህዝብን ለማገልገል፣ ሁለንተናዊ ልማትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማፍጠን ድህነትንና ኋላቀርነትን በመቀነስ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ ለማሻሻል አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የህግ፣ ዳኝነትና ፍትሕ ተቋማት ዋነኛ ዓላማ በስልጣን ክልላቸዉ የሚኖረዉን የፍትህ ፍላጎትና አቅርቦት ምጥጥን (equilibrium) ማረጋገጥ ሲሆን የዘርፉ ተቋማት ባልተጠናከሩበት ሁኔታ የህግ የበላይነትን ማስፈኝም ሆነ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ሁለንተናዊ ልማት ማሳካት አይቻልም፡፡ የህግና ፍትህ ጉዳዮች በየትኛዉም የሰዉ ልጅ የዕድገት ምዕራፍ አስፈላጊ እና ቁልፍ ጉዳዮች ቢሆኑም በአንድ አገር ዉስጥ መዋቅራዊ ሽግግር እየተረጋገጠ፣ ከተሞች እየሰፉ፣ ትምህርትና ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ፣ የዜጎች-ዜጎች/ የዜጎች-መንግስት መስተጋብር እየተቀየረ እና የዜጎች ገቢ እየጨመረ በሄደ ቁጥር አስፈላጊነታቸዉ ይጨምራል፡፡ በተለያየ የዕድገት ምዕራፍ አልፈዉ አሁን በብልፅግና ማማ ላይ ያሉ አገራት ልምድ እንደሚያሳየዉ ኢኮኖሚ ሲያድግ እና ማህበረሰብ ሲሰለጥን አዳዲስ የህግና ፍትህ ፍላጎቶች ይፈጠራሉ፣ ነባር ፍላጎቶች ይቀየራሉ፡፡ አገር እየሰለጠነ በሄደ ቁጥር ግልፅ፣ ቀላልና ተገማች ህግ፤ የዜጎች/ ነዋሪዎች ሰላምና ደህንነት፤ ጠንካራ የንብረት መብቶች ጥበቃ፤ ውጤታማ የውል ማስፈፀሚያ ስርዓት፤ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት የህዝብ አስተዳደር፤ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ወጪ ቆጣቢ የዳኝነትና የፍትህ ስርዓት ወዘተ በአንድ አገር ወይም አካባቢ ለመነገድ እና ኢንቨስት ለማድረግ ብቻ ሳይሆን በቋሚነት ለመኖር ወይም በጊዜያዊነት ለመቆየት (ለምሳሌ፡- ቱሪዝም) እንደቅድመ ሁኔታ ይቆጠራሉ፡፡ የህግና ፍትህ አስተዳዳር ዉድድር በበዛበት ዘመነ-ሉላዊነት ወሳኝ የምርት አቅሞችን የሚባሉትን መሬት፣ ካፒታል፣ (የተማረ) የሰዉ ሀይል ሰዉ፣ እና አንተርፕርነርሽፕ በአግባቡ ለመጠቀም፣ ለመሳብ እና ለማቆየት የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በዚህ ዘመን በዓለም አገራት የሚስተዋለዉ የሕዝብ አስተዳደር ዘይቤ እንደሚያስረዳዉ መንግስት ሕግ ከማስከበር፣ ሰላምና ደህንነትን ከማስፈን ባሻገር በአገር ሁለንተናዊ ልማትና እድገት የሚጫወተው ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ መጥቷል፡፡ በተለይም በታዳጊ አገራት የመንግስታት ሚና ጎላ ብሎ የሚታይ ሲሆን መንግስታት የገበያ ክፍተትን ለመሙላት በኢኮኖሚው ውስጥ ሃብት የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ እያደገ እና እየሰፋ መጥቷል፡፡ መንግስታት ከተለመደዉ ነባር መንግስታዊ ተግባራት በተጨማሪ አዳዲስ አኮኖሚ ነክ ሚናዎችን እየተወጡ መምጣታቸዉን ተከትሎ የዳኝነት እና የፍትሕ ተቋማት ኃላፊነት ከወትሮው በተለዬ መልኩ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በመሆኑም ልማትና እድገትን ለማረጋገጥ የሚታሰብ ማንኛውም ትልም የዳኝነት እና ፍትሕ ዘርፍ ተግባራትን ማጠንጠኛ ማዕከል ማድረግ እና የዘርፉን ሚና ታሳቢ ብቻ አድርጎ ከመቀጠር ባሻገር በየዕለት ከዕለት ጥረት ውስጥ ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ የሚለኩ ግቦችና ተግባራት ተቀምጠዉለት ክትትል፣ ግምገማ እና ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ከሚስተዋሉ አዳዲስ ችግሮች እና ፍላጎቶች በመነሳት በታሪክ ከተጣባን የድህነትና ግጭት አዙሪት በመዉጣት በአንድ ትውልድ በዓለም ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ የመገንባት እና ሁለንተናዊ ብልጽግና የማሳካት ርዕይ ያለዉ የ25 ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ዕቅድ (2018-2042) ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ አዘጋጅቷል፡፡ የዕድገት ፍኖተ-ካርታዉ በአምሥት የአምሥት ዓመት የልማት ዕቅዶች የሚተገበር ሆኖ ሦስት ግልፅ ርከኖችን (የኢኮኖሚ መረጋጋትና ማገገም፣ የመመንጠቅ እና የመበልጸግ) እና በየጊዜዉ ሊደርስበት የሚችለዉን የኢኮኖሚ ዕድገትና ማህበረሰባዊ ለዉጥ የሚያመላክት ሲሆን በየዕድገቱ እርከን ሰፊ የፍትህ ፍላጎት መጨመር ብቻ ሳይሆን ለዉጥ ይኖራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በተለይም የግብርና መዘመንና የገጠር ህይወት መሻሻል፣ የከተሞች መስፋፋትና ከተሜነት፣ የኢንዱስትተሪ መስፋፋትና አስተዳዳር፣

የሰራተኛ ስምሪት ለዉጥ፣ የማዕድን ሀብት ልማትና ተጠቃሚነት፣ የቴክነሎጂ ፈጠራ ወይም ማላመድና መጠቀም፣ የኮንስትራክሽን አስተዳዳር እና ቁጥጥር፣ የቱሪዝም ልማትና ተጠቃሚነት፣ የንግድና ገበያ ልማት፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አስተዳዳርና ቁጥጥር ወዘተ ያለ ጠንካራ፣ ተገማች እና ዉጤታማ የህግ፣ የፍትህና የዳኝነት አስተዳደር የታለመላቸዉን ግብ ሊመቱ አይችሉም፣ ከተሳኩ ደግሞ አዳዲስ የህግና የፍትህ ፍላጎቶች ይዘዉ ይመጣሉ፡፡ የህግና የፍትህ ተቋማት ለተጨማሪ እና አዳዲስ ፍላጎቶች መልስ መስጠት ካልቻሉ የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ይከሰትና የፍትህ ክፍተት (justice gap) ይፈጠራል፡፡ ይህም ክልሉን ወደግጭት አዙሪት ይመልሳል፤ ዕድገትን፣ ልማትን እና የማህበረሰብ ለዉጥ ይጎትታል፡፡ የዚህ የዳኝነት እና ፍትህ ዘርፍ ዕቅድ ዓላማም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ፍትህ ቢሮ፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ማረሚያ ቤቶች፣ እና ተያያዥ ተቋማት ከክልሉ የልማት ርዕይ ጋር የተንሰላሰለ እና እየታሰበ ያለዉን የኢኮኖሚ እድገት እና የማህበረሰብ ለዉጥ የሚሸከም የዳኝነትና ፍትህ ስርዓት መገንባት ማስቻል ነዉ፡

በአጠቃላይ የዳኝነትና የፍትሕ ዘርፍ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት ከሌላ ተቋም የማይገኝ፣ የማይተካ እና የመጨረሻ አማራጭ በመሆኑ ዘርፉ ሰዎች ሁሉ ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ ያገኟቸው መብቶች ብቻ ሳይሆኑ በአንድ አገር ሁለንተናዊ ልማት እና እድገት ለማረጋገጥ ልዩ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በዚህ ዘርፍ የሚሰጠው አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በመንግስት ብቻ የሚሰጥ እና የዘርፉ ተቋማት በቅንጅት ካልሰሩ የደንበኞችን እርካታ ማሳደግም ሆነ በክልሉ ልማትና እድገት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ አይቻላቸዉም፡፡ የፍትሕ አገልግሎት የቅብብሎሽ ስራ በመሆኑ አንደኛው ተቋም ያለ ሌላኛው ተቋም የላቀ የፍትሕ አገልግሎት ለመስጠት የሚያዳግተው በመሆኑ ለየተቋማቱ በሕግ የተሰጠው ነጻነትና ገለልተኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ ቅንጅታዊ አሰራርን መከተል የውዴታ ግዴታ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሌላዉ በዘርፉ ተቋማት ትኩረት የሚሻዉ ጉዳይ የህግ ብዝሃነት እና የመሰረተ ማህበረሰብ ፍትህ አገልግሎት ሲሆን የህብረሰብን ተሳትፎ ከማረጋገጥ እና የህዝብን አቅም ከመጠቀም አንፃር ያላቸዉ ሚና ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት ሊሰራበት ይገባል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የዘርፉ ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ተገማች፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት የተላበሰ፣ እርካታን ያረጋገጠ እና አመኔታ የተቸረው ለማድረግ አገልግሎትን በኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓትን መዘርጋት ይደር የማይባል ተግባር ነዉ፡፡

## 29.2. የዘርፉ ዓለማቀፋዊ እና አህጉራዊ ሁኔታ

የዳበረ የሕግና ፍትህ ሥርዓት ከድህነትና ግጭት አዙሪት ለመዉጣት ብሎም የተሳካ የኦኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እና ርትዕ ማህበረሰብ ለመፍጠር በያኝ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በአለም ላይ አንድ ቢሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በየዓመቱ አዳዲስ የሕግ እና የፍትሕ ችግር የሚገጥማቸው መሆኑን የሔግ የህግ ፈጠራ ኢንስቲትዩት በ2020 (እ.ኤ.አ) ያጠናው ጥናት ይጠቁማል፡፡ በጥናቱ መሰረት 70% በላይ የሚሆኑ ሰዎች አጥጋቢ መፍትሄ አያገኙም፣ ቀሪዎቹ 30% ሰዎች ደግሞ መብታቸውን ለማስከበር ምን አይነት የህግ እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ እውቀቱ የላቸውም፡፡ ይህም በበርካታ ሀገራት ህዝቡ በህግና ፍትህ ሥርዓቱ ላይ ዝቅተኛ ዕምነት እንዲኖረውና በመንግስት እና በህዝብ መካከል የሰመረ ግንኙነት እንዳይኖር አድርጓል፡፡ ችግሮቹ ይበልጥ ጎልተው የሚታዩት በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ነው፡፡

በአለም አቀፉ የፍትህ ፐሮጀክት (World Justice Project) ጥናት መሰረት ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ዓመታት በዓለም ሀገራት ከፍተኛ የሆነ የህግ የበላይነት መሸርሸር እና የፍትህ ክፍተት ተመዝግቧል፡ ፡ የመንግስትን ስልጣን በህግ የተገደበ ከማድረግ፣ ሙስናን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር ከመዘርጋት፣ ለመሰረታዊ መብቶች ጥበቃ ከማድረግ፣ የህዝብ ሰላም እና ደህንነት ከማረጋገጥ፣ የተሻሻለ የህግ ቁጥጥርና ትግበራን ዕውን ከማድረግ እንዲሁም ውጤታማ የወንጀል፣ ፍትሃብሄር እና አስተዳዳር ፍትህ አስተዳዳር ከመዘርጋትና ከመተግበር አንፃር መጠነ ሰፊ ውስንነቶች ተስተውለዋል፡፡ በጥናቱ የመንግስት፣ የሲቪል ማህበራት፣ የዓለማቀፍ ተቋማት፣ የሚዲያ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ትኩረት ማነስ በምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡ ግጭትና የፖለቲካ አለመግባባት ሲከሰት ችግሩ እየከፋ እንደሚሄድ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡

አለም አቀፉ የፍትህ ፕሮጀክት እ.አ.አ. በ2024 ባወጣው የዓለም ሃገራትን የህግ የበላይነት ደረጃ የ142 ሀገራት ደረጃ መሰረት ዴንማርክ፣ኖርዌይ፣ፊላንድ፣ሲዊዲ፣ ጀርመን የመሳሳሉ ያሉ አገራት የህግ የበላይነትን የጋራ ባሕል መገለጫ በማድረግ እና ለዜጐቻቸውን ፍትህ በማስፈን፣ ዘላቂ ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያለውን ደረጃ ተቆናጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ሀይቲ፣አፍጋኒስታን፣ካምቦዲያ እና ቬንዚዮላ የመሳሰሉ አገራት ስር የሰደደ የህግ የበላይነትን ያላረጋገጡ፣ ሰፊ የፍትህ ክፍተት የሚስተዋልባቸው፣ የመንግስትና ህዝብ ጥቅም የማይከበርባቸው ሀገራት በሚል ከ138-142ኛ ያለውን የመጨረሻ ደረጃዎችን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ከአፍሪካ አገራት መካከል ሩዋንዳ፣ ናሚቢያ እና ሞሪሸየስ የህግ በበላይነትና ፍትህ አሰጣጥ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ሲሆን በተቃራኒው ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ሱዳንና እና ካሜሩን በህግ ዝቅተኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ አገራት እንደሆኑ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

ዝቅተኛ የሕግ የበላይነትና የፍትህ ችግሮች የሚስተዋሉባቸው አገራት ለንግድና ኢንቨስትመንት አመቺ አለመሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በአለም አቀፉ የ2020 የንግድ አሰራር ቀላልነት መለኪያ (Ease of Doing Business Index) ኒው ዚላንድ (86.8)፣ ሲንጋፖር (86.2)፣ ቻይና (85.3)፣ ዴንማርክ (85.3) እና ደቡብ ኮሪያ (84.0) በማስመዝገብ ለንግድና ኢንቨስትመነት ምቹ ሁኔታን መፍጠር ችለዋል፡፡ በሌላ በኩል ሶማሊያ (20.0)፣ ኤርትራ (21.6)፣ ቬንዚዮላ (30.2)፣ የመን (31.8) እና ሊቢያ (32.7) ደግሞ በንግድና ኢንቨስትመንት የኢኮኖሚ ዘርፍ መሰማራት ከባድ የሆነባቸው እና ምቹ ሁኔታ የሌላቸው አገራት በመሆን የመጨረሻዎቹን ደረጃዎች አስመዝግበዋል፡፡ በእነዚህ ሀገራት እንደስራ አጥነት እና ኑሮ ዉድነት የመሳሰሉ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መቅረፍ አዳጋች በመሆኑ የድህነትን እና የግጭት አዙሪትን መስበር አልቻሉም፡ ፡

ከዚህ አዙሪት ለመዉጣት በበርካታ አገራት **"ህግና ፍትህ የሰላም፣ ኢኮኖሚ ልማት፣ የማህበረሰብ ለዉጥ ዉጤት ናቸዉ ወይስ ምክንያት"** ከሚለዉ የቆየ ንድፈ ሐሳብዊ ክርክር እየወጡ ህጎችን እና የዳኝነትና ፍትህ ተቋማትን ማጠናከር የኢኮኖሚ እድገትና ማህበረ-ፖለቲካ ለዉጥ ለማምጣት ቁልፍ መሳሪያዎች ተደርገዉ ይቆጠራሉ፡፡ የዳኝነትና ፍትህ ዘርፉ ከግጭት ለመዉጣትና ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ያለዉን ሚና በተመለከተ የሰላምና ግጭት አፈታት ባለሙያ የሆኑት አሚር አብደላ እና ማሬ ሰነጼ በ2023 (እ.ኤ.አ) ለዘርፉ ባስተዋወቁት ሞዴል አሁናዊ ግጭት ዉስጥ ያሉ አገራት የፍትህና ዳኝነት ዘርፉን በማጠናከር እና በመጠቀም በአጭር ጊዜ ከአሉታዊ ሰላም (negative peace) ወጥተዉ ወደ አዎንታዊ ሰላም (positive peace) መመለስ ብሎም ግጭትን ከማስተዳደር (conflict management) ወጥተዉ ወደ ግጭትን መፍታት (conflict resolution) ከዛም ወደ ግጭትን ወደመለወጥ (conflict transformation) ማሸጋገር እንደሚችሉ የበርካታ አገራትን ልምድ እንደማስረጃ በማቅረብ አስደርተዋል፡፡

የህግና የፍትህ አስተዳዳር ለብቻዉ የቆመና በራሱ የሚመዘን ብቻ ሳይሆን ለንብረት መብት ጥበቃ በማድረግ፣ የግብይት ወጪን በመቀነስ እና ዉሎችን በማስፈጸም ለኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ጉልህ ሚና የሚጫወትና የአገራት የእድገት ልዩነት ሚስጥር ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ፡፡ በዚህም ለምሳሌ በብራዚል የተደረገ ጥናት የፍርድ ቤት አገልግሎት መሻሻል 10% ኢንቨስትመንትን እንደሚጨምር ያሳየ ሲሆን የሕግ የበላይነት መረጋገጥ ደግሞ 3 እጥፍ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚጨምር ያመላክታሉ፡፡ እንደ አለምአቀፍ ገንዘብ ድርጅት (IMF) ሪፖርት ደግሞ በሕግ የበላይት መለኪያ አንድ ነጥብ መሻሻል ከ 3% እስከ 4% የኢኮኖሚ ዕድገት ማሻሻልን ያመጣል፡፡ የዓለም ባንክ እ.ኤ.አ 2024-2025 ባወጣዉ ሪፖርት በፍ/ቤት ዉጤታማነት መለኪ ብቻ 25 % ላይ የነበረች አገር አፈጻጸም ወደ አማካኝ ወይም 50% መምጣት የአንድን አገር ኢኮኖሚ (GDP) በየአመቱ በ 0.28 % እንደሚሳድግ ይገልጻል፡፡ እንደ OECD & UNODC ሪፖርት አነስተኛ ሙስና እና ጠንካራ የሕግ የበላይት ያላቸዉ አገራት በእነዚህ መለኪያዎች ደካማ አፈጻጸም ካላቸዉ አገራት ከ2 እስከ 3 እጥፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸዉ መሆኑን ይገልጻል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የዳኝነትና ፍትህ አካላት ያላቸዉ ሚና በተ.መ.ድ የ2030 የዘላቂ የልማት ግቦች (ግብ 16)፣ በአፍሪካ አጀንዳ 2063 (ግብ 3 እና 4) እና በበርካታ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና ህገ-መንግስታት በግልፅ የተመላከተ ሲሆን ባለፉት አስርት ዓመታት ኢትዮጵያን ጨምሮ በበርካታ ሀገራት በአለም ባንክ እና ሌሎች ዓለምአቀፍ ተቋማት የሚደገፉ ሰፊ የህግ፣ የፍርድ ቤቶችና ፍትህ ተቋማት ሪፎርም ፕሮግራሞች ሲካሄዱ ቆይቷል፡፡ በዚህም ሂደት በአፍሪካ ሞዴል የሚሆኑ ጅምር የህግና ፍትህ ስርዓቶች እየተፈጠሩ ሲሆን ደቡብ አፍሪካ (ለህግና ፍትህ ተደራሽነት፣ የማረሚያ ቤት አስተዳዳር እና የታራሚዎች አያያዝ)፣ ሩዋንዳ (ለዲጂታል ፍትህ፣ ማህበረሰብ ተኮር የፍትህ አስተዳዳር እና የአስተዳደር ፍትህ ስርዓት)፣ ኬንያ (ለነፃ የህግ ድጋፍ እና አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች)፣ ጋና (ለነፃ የህግ ድጋፍ ተቋማት መስፋፋት እና ለተፋጠነ ፍትህ) እና ቦትስዋና (ለግልፅ እና ቀልጣፋ የዳኝነት ስርዓት፣ የፖሊስ አገልግሎት፣ የአስተዳደር ፍትህ ስርዓት) የተሻለ ልምድ የሚወሰድባቸዉ ሀገራት እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በእነዚህ ሀገራት የምዕራቡን ዓለም ህጎች እና የፍትህ ተቋማት አደረጃጀቶችን ልምድ በመዉሰድ ነፃ፣ ገለልተኛ፣ ሙያዊ፣ ዉጤታማ እና ለስራ ምቹ የሆኑ የፍትህ ተቋማትን ከመገንባት ጎን ለጎን የማህበረሰብ እና የገበያ መሰረት ያላቸዉን የተለያዩ ባህላዊ እና ዘመናዊ አማራጭ የፍትህ አስተዳዳር ዘዴዎችን በመጠቀም ዉጤቶችን አስመዝግበዋል፡፡ ሌላዉ እና የፍትህ አስተዳዳሩን ለማዘመን የተጠቀሙት ቴክኖሎጂን ሲሆን የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል፣ ውሳኔ አሰጣጥን ለማቀላጠፍ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ እና የዉስጥና የዉጭ ትብብርን ለማጠናከር ጉልህ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

### 29.3. የዘርፉ ሀገራዊ ሁኔታ

ኢትዮጵያ በረጅሙ የሕዝብ አስተዳደር ታሪኳ በባሕላዊ የሕግና የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ስትተዳደር የቆየች ቢሆንም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ወዲህ ዘመናዊ ሕግ ማውጣት፣ ሕግ አስፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ አካላትን አቋቁማለች፡፡ የተማከለ ቅርጸ-መንግስት እና አስተዳደር በመከተል በፖሊስ፣ በዓቃቤ ሕግ እና በፍርድ ቤቶች የፍትህ አገልግሎቶች ሲሰጡ የቆዩ ቢሆንም ያልተማከለ ቅርጸ-መንግስት እና አስተዳደር መከተል ከጀመረችበት 1983 ዓ.ም ወዲህ የፍትሕ አገልግሎት በፌደራል እና በክልል መንግስታት ደረጃ ስርዓት ተበጅቶላቸው ሕግ የማውጣት፣ የማስፈጸም እና የመተርም ተግባራት በፌደራል እና በክልል መንግስታት ደረጃ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በአገሪቱ የተስተዋለውን የኢኮኖሚ እድገት እና የማህበረሰብ ለውጥ ተከትሎ ለመጡት አዳዲስ የፍትህ ፍላጎቶች ተገቢ ምላሽ መስጠት ረገድ የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ጉልህ ሚና ያልተወጣ ስለመሆኑ እና በአገሪቱ መጠነ ሰፊ የፍትሕ አገልግሎት እንጓሉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

በዘርፉ የሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች በአገሪቱ የህግ የበላይነትና የህግ ተገዢነት ችግሮች እንዲሰፉ እና እንዲንሰራፉ በማድረግ ለንግድና ኢንቨስትመንት አመቺ ካልሆኑ አገራት ተርታ እንድትመደብ እና በዓለም ዝቅተኛ የሰላም ደረጃ ካላቸው አገራት አንዷ እንድትሆን አድርጓል፡፡ በ2024 ዓለም አቀፉ የሰላ ጠቋሚ መረጃ (Global Peace Index) መሰረት ኢትዮጵያ ከ163 የዓለም አገራ144ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠች ሲሆን በ2016 ዓ.ም ከነበረችበት129ኛ ደረጃ እና በ2023 ከነበረችበት 131ኛ ደረጃ አንፃር ሲታይ እየጨመረ የሚሄድ ማሽቆልቆል አስመዝግባለች፡፡ እ.አ.አ በ2020 ይፋ በተደረገው አለም አቀፍ የንግድ አሰራር ቀላልነት መለኪያ (Ease of Doing Business Index) መሰረትም ኢትዮጵያ በ48.0 ነጥብ ከ190 ሀገራት 159ኛ ደረጃን በመያዝ ዝቅተኛ የአፈፃፀም ደረጃ ያላት መሆኑ ተገልጾ ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ መደላድል የሚፈጥሩ የሕግ ማዕቀፎች እና የአሰራር ሥርዓቶችን እንድትዘረጋ ጠንከር ያሉ ምክረ ሀሳቦች ተመላክተዋል፡፡

እ.ኤ.አ 2020 የተደረገ የፍትህ ፍላጎቶች እና እርካታ ጥናት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ 7.4 ሚሊዮን ወይም 40% የሚሆነው ህዝብ በአመት በየአራት ዓመቱ ቢያንስ አንድ አስቸጋሪ እና ከባድ የህግና የፍትህ ጉዳይ የሚያገጥመው ሲሆን ከእነዚህ መካከል 2.2 ሚሊዮን ወይም 30% የሚሆኑት የህግ ጉዳዮች ፍትሃዊ ምላሽ የሚያገኙ ሲያገኙ ቀሪዎቹ 5.2 ሚሊዮን ወይም 70% ጉዳዮች ፍትሃዊ እና ምክንያታዊ ምላሽ አያገኙም፡፡ ይህም በአገሪቱ ትልቅ የፍትህ ክፍተት (justice gap) መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ በመሬት ዙሪያ የሚነሱ

አለመግባባቶች፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ ከጎረቤቶች ጋር የሚፈጠር አለመግባባት፣ የቤተሰብ አለመግባባት እና የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ከብድርና ገንዘብ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች፣ የሰራተኛ እና አሰሪ አለመግባባቶች በተደጋጋሚ የሚከሰቱ እና የፍትህ ጥያቄ የሚሹ ጉዳዮች ስለመሆናቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል የሔግ የህግ ፈጠራ ኢንስቲትዩት ጥናት እንደሚጠቁመው ከ2015-2019 (እ.ኤ.አ) ባሉት አራት ዓመታት ውስጥ ከ8.2 እስከ 8.7 ሚሊዮን የሚደርሱ ከመሬት ጋር የተያያዙ ግጭቶች የተከሰቱ መሆኑን በማውሳት ከ5.7 እስከ 6 ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች የወንጀል ሰለባ ሲሆኑ ከ3.2 እስከ 3.4 ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች ደግሞ በጉረቤት ግጭት አጋጥሟቸዋል፡፡ እነዚህ የሕግ እና የፍትሕ ጥያቄዎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ በተለያየ መንገድ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሲሆን አንዳንዶች አርሶ አደሩንና በመደበኛ ትምህርት ያላለፈውን፣ ሌሎች ሴቶችንና ህፃናትን፣ የከተማ ነዋሪዎችን፣የፋብሪካ ሰራተኞችን እና ቀጣሪ ባለሃብቶችን የሚመለከቱ ናቸው ፡፡

በኢትዮጵያ ሽምግልናን የመሳሰሉ ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አማራጭ የፍትሕ ማግኛ መንገዶች በመሆናቸው ብዛት ያለው የማኅበረሰብ ክፍል ይገለገልባቸዋል፡፡ የሚከተለው ሰንጠረዥ በኢትዮጵያ ከ2015-2019 (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ውስጥ ሰዎች የሕግ እና የፍትሕ ጉዳያቸውን ለመፍታት የተለያዩ አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም መፍትሄ ለማግኘት ጥረት ያደረጉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ብዙዎቹ ሽማግልናን እና ድርድርን ምርጫቸው ያደረጉ መሆኑንም ይጠቁማል፡፡

በኢትዮጵያ ከ2015-2019 (እ.ኤ.አ) በማኅበረሰቡ አገልግሎት ላይ የዋሉ ዋና ዋና የአለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች

| የክርክር/ግጭት መፍቻ ዘዴ | ፍትሕ ጥያቄ ያቀረቡ ሰዎች በመቶኛ |
|---|---|
| የአካባቢ ሽማግሌ | 43 |
| ድርድር | 26 |
| የቤተሰብ አስታራቂ | 23 |
| የአካባቢ አስተዳዳር | 18 |
| መደበኛ ፍርድ ቤት | 18 |
| ፖሊስ | 15 |
| ጉረቤት አስማሚ | 13 |
| ጓደኛ | 8 |
| ማህበራዊ ፍርድ ቤት | 5 |
| የሃይማኖት አባት | 3 |
| የህግ ባለሙያ/ ጠበቃ | 1 |
| አስተዳዳራዊ ጉባዔ | 1 |
| የሃይማት ፍርድ ቤት | 1 |

**ምንጭ፡** የሔግ የህግ ፈጠራ ኢንስቲትዩት የ2022 ጥናት፣ ገፅ 76

በጥናቱ ከተሳተፉ ሰዎች መካከል 43% የሚሆኑትና የገጠማቸውን የሕግና የፍትፍ ጥያቄ ለመፍታት የአካባቢ ሽማግሌዎችን (village elders) ድጋፍ የሚሹ መሆኑ ከመረጋገጡም ባሻገር በዚህ አይነት ሂደት የሚያገኝ የፍትህ አገልግሎት በመደበኛ የፍትህ ተቋማት ከሚሰጠው የፍትሕ አገልግሎት የተሻለ ጥራት እና ጥቅም ያለው ስለመሆኑ እምነት ያላቸው መሆኑን ከፍ ሲል የተገለተው ሰንጠረዥ ያስረዳልአለው፡፡ ይህ ቢሆንም ቅሉ ከሌሎች አገሮች ልምድ በተለዬ መልኩ በኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሕግ ጉዳዮች በመደበኛው ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ሲሆን ከማህበራዊ እስከ ሰበር ሰሚ ድረስ የሚደርሱ መሆኑን ጥናቶቹ ያስረዳሉ የሚደርሱ

ሲሆን ጥናቶች ያሳያሉ፤ 80% የሚሆኑት ከባባድ የሕግ ጥያቄዎች (most serious legal problems) ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ይመጣሉ፡፡

በፍትህ ዘርፉ በሚስተዋሉ ችግሮች እና ሰፊ በሆነ የፍትሕ ክፍተት ምክንያት በሀገሪቱ የህግ የበላይነትና የህግ ተገዢነት ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ ሄደዋል፡፡ የአለም የፍትሕ ፕሮግራም የ2024 (እ.ኤ.አ) የህግ የበላይነት ጠቋሚ መሰረት ከ142 የአለም ሀገራት 130ኛ ስትሆን ከ34ቱ ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች 30ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

የኢትዮጵያ የህግ የበላይነት ደረጃ 2024 (እ.ኤ.አ)

| መለኪያ | ዓለም አቀፍ ደረጃ | ከሰሃራ በታች አፍሪካ ደረጃ |
|---|---|---|
| በመንግስት ስልጣን ላይ ያሉ ገደቦች | 130/142 | 32/34 |
| የሙስና ችግሮች | 90/142 | 12/34 |
| የመንግስት አሰራር ግልፅነትና ተደራሽነት | 136/142 | 33/34 |
| መሰረታዊ መብቶች | 137/142 | 34/34 |
| የህዝብ ሰላም እና ደህንነት | 129/142 | 27/34 |
| የቁጥጥር ትግበራ | 132/142 | 30/34 |
| የፍትሃብሄር ፍትሕ | 121/142 | 28/34 |
| የወንጀል ፍትሕ | 104/142 | 22/34 |

**ምንጭ፡** የዓለም የፍትሕ ፕሮግራም፣ 2024 (እ.ኤ.አ)

ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው ከሙስና እና ደካማ የወንጀል ፍትህ አስተዳዳር በአገሪቱ የህግ የበላይነት አለመረጋገጥ እና የሕግ ተገዥነት ባህሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና እየቀነሰ እንዲሄድ አድርጎል፡፡

የዘርፉ ተቋማት እየተስተዋለ ያለውን የሰላም፣ የሕግ የበላይነት አለመረጋገጥ ችግር እና ሰፊ የሆነ የፍትሕ ክፍተት ለመቅረፍ የተለያዩ የሪፎርም ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በተለይም ከ1990ዎቹ ጀምሮ እስከ 2010 ዓ.ም ሲተገበር የነበረዉ የፍትሕ ስርዓት ማሻሻያ እና ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የተተገበረዉ የሕግ ማሻሻያ ፤ የዳኝነት ፣ የፍትህ ፣ የዴሞክራሲና የሕግ አስከባሪና የሴኩሪቲ ተቋማት ሪፎርም በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን በእነዚህም የማይቁ ዉጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ይሁን እንጅ ከተጠቀሱት ማሻሻያዎችም በኋላ የሕብተሰቡ የፍትህ እርካ ማምጣት አለመቻን ጥናቶች ስለሚያሳዩ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ በመሰረታዊነት ለመለወጥ በማሳብ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ለ 3 ዓመታት ተግባራዊ የሚደረግ የዳኝነትና የፍትህ አካላት የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በዚህ ዕቅድ የተገልጋይ እርካታ ጥናት ማካሄድ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ ውይይት ማድረግ፣ የፍርድ ቤቶች ነፃነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነት በማጠናከር፣ ተደራሽነትን በማሳደግ፣ የህግ ዕውቀትን በማዳበር፤ የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ የሚደርጉ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ፣ የፍድ ቤት መር አስማሚነት ስርዓትን በማጠናከር፣ ነጻ የሕግ አገልግሎት መስጫ ሥርዓትን በመዘርጋት፣ የፍትህዊነት ይስተዋልባቸው የነበሩ ሕጎችን በማሻሻል፣ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓትን በመቅረጽ፣ መሰረተ-ማኅበረሰብ የፍትሕ አገልግሎት ለመስጠት የሚያግዝ ጥናት በማከናወንና ምክረ ሀሳቦችን በማመንጨት፣ የንቃተ ሕግ እና የሕግ ተገዥነትን ለማዳበር፣ የተቋማትና አሰራር እና አደረጃጀት የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን በማውጣት እና መሰል ስር ነቀል የለውጥ ስራዎችን በመተግበር የህዝብ አመኔታ የተቸራቸው የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፍ ተቋማትን ለመገንባት ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ይኛል፡፡

የዳኝነትና የፍትህ ዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ እርምጃዎች ሲወሰዱ ቢቆዩም ዘርፉ አሁንም ያልተሻገራቸዉ ችግሮች አሉ፡፡ ፍትሃዊና ተገማች የሕግ አወጣጥ ስርዓት አለመኖር፣ የተደራሽነት

ችግር፣ የፍጥነት ችግር፣ የተገማችነት ችግር፣ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግር፣ የአካታችነት ችግር፣ የመሠረተ ልማት ችግር፣ ብቁ የሰው ኃይል እጥረትና የባለሙያዎች በብዛት መልቀቅ ችግር፣ የነጻነትና የተጠያቂነት ተመዛዝኖ ያለመኖር ችግር እና የፕሮፌሽናሊዝም አለመዳበር ተጠቃሽ ችግሮች ናቸዉ፡፡

በመሆኑም የክልላችን የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፍ ተቋማት በአገር ደረጃ ከተመዘገቡ ስኬቶችን እና ውድቀቶች ትምህርት በመቅሰም በክልሉ ጠንካራ የሕግ ሥርዓት ለመገንባት አልመው ሊተጉ ይገባል፡፡

## 29.4. የዘርፉ ክልላዊ ሁኔታ

### 29.4.1. ስለዳኝነትና ፍትህ ዘርፍ በጠቅላላው

የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፍ ተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት በሕግ በመደንገግ፣ ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ የሰው ሐብት አስተዳደር ሥርዓታቸውን በማዘመን የመፈጸም አቅምን ለማሻሻል ባለፉት ሶስት አስርት አመታት ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት ነጻ እና ገለልተኛ ሆነው ከመቋቋማቸውም ባሻገር ሶስተኛው የመንግስት አካል ሆነው ተደራጅተዋል፡፡ ሌሎቹ የፍትሕ ዘርፍ ተቋማትም በሕግ ተቋቁመው ለክልሉ ሕዝብና መንግስት የፍትሕ አገልግሎት እየሠጡ ይገኛሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ የአደረጃጀት፣ የተደራሽነት፣ የጥራት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማ የፍትሕ አገልግሎት በመስጠት ረገድ የዘርፉ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ነበሩ ለማለት አያስደፍርም፡፡ አለም አቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ የፍትሕ አገልግሎት በመስጠት እና እያደገ የመጣውን የክልሉን ሕዝብ የፍትሕ ፍላጎት በማሟላት ረገድ ስኬታማ ተቋማት ናቸው ለማለት ያዳግታል፡፡

መሰረታዊው ችግር የዘርፉን ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት ከሚቋቋሙበት ወይም ከሚደራጁበት መሰረታዊ ዓላማ እና ከአለምአቀፍ ተሞክሮዎችና መርሆዎች አንጻር በሕግ በአግባቡ መለየት አለመቻል እና ሙያዊ የሆኑ ተቋማትን ገንብቶ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎት መስጠት አለመቻል ሲሆን ውጤታማነታቸውን ከፍ ለማድረግ የተቋማቱን አደረጃጀት ማጠናከር እና ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስራ መስራትን ይጠይቃል፡፡

ሳይንሳዊ የጥናትና ምርምር ሀሳቦችን በማፍለቅ ጠቃሚ ምክረ ሀሳብ ያፈልቃሉ ተብለው የተቋቋሙት የዘርፉ የስልጠናና የምርምር ተቋማትም በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ናቸው፡፡ የዘርፉን ተቋማት የፍትሕ አገልግሎት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ችግር ይስተዋላል፡፡ የዘርፉን ተቋማት የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥ ወረቀት አልባ በማድረግ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች እና ጥራት ያለው አገልግሎት አሰጣጥን እውን ማድረግ ይገባል፡፡ መሰረተ-ማኅበረሰብ የሆኑ አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ሥርዓቶችን በአደረጃጀትና በሰው ሀይል በማጠናከር ለዜጎች አማራጭ መፍትሄ ማግኛ ዘዴዎችን ማስፋት ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

የፍትሕ አገልግሎት በአንዱ የዘርፉ ተቋም ተጀምሮ እዚያው የሚያልቅ ሳይሆን የሌላኛውን የዘርፉን ተቋም ትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ የዘርፉ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ደካማነት ለዘርፉ ውጤታማነት ትልቅ ጋሬጣ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የዘርፉ ተቋማት በሕግ የተሰጣቸው ነጻነትና ገለልተኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጋራ ተቀናጅቶና ተባብሮ በመስራት የላቀ የፍትሕ አገልግሎትን እውን ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በክልል ደረጃ ተቀናጅቶ በመስራት ረገድ ይስተዋል የነበረውን የመገፋፋት ችግር ይቀርፋል በሚል ከነሐሴ 03 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፍትሕ ተቋማት የጋራ መድረክ (Joined up Justice) ለመተግበር ሙከራዎች የነበሩ ቢሆንም ከዕቅድ በዘለለ ተጨባጭ ስራዎች ሳይሰሩ ቆይተዋል፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት እና ዉጤታማ ቅንጅታዊ አሰራሩን ለመተግበር ታስቦ መስከረም 23 ቀን 2017 ዓ.ም በዘፉ ተቋማት መካከል በተፈረመ የመግባቢያ ቻርተር የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት የትብብር መድረክ ከመመስረቱም በላይ መድረኩን በበላይነት የሚያስተባብር ጽ/ቤት ተቋቁሞና የጋራ ዕቅድ ወጦ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የትብብር መድረኩ ሥራ በስምምነት ቻርተር ከመሰራት አልፎ በአዋጅ ቁጥር 297/2017 የሕግ እዉቅና ተሰጦታል፡፡ ይህም በክልሉ የመጀመሪያ

የሆነ እና ለፌዴራልና ለሌሎች ክልሎች የዳኝነትና ፍትሕ ተቋማት ተምሳሌት የሚሆን ነዉ፡፡ የተቋማቱ አንኳር ችግሮች ተለይተው ችግሮቹን ከስር መሰረታቸው ለመቅረፍ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በ2017 በጀት አመት ብቻ በትብብር መድረኩ የጋራ እና በተቋማት የተናጠል ጥረት አጠቃላይ የዘርፋን ዉጤታማነት ሊያሳድጉ አልፎም በክልል ደረጃ የሕግ የበላይነትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ሊቀርፉ የሚችሉ የሕግ ማዕቀፎች የፀደቁ ሲሆን ለአብነት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 292/2017፣ የክልሉ የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 293/2017 ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 294/2017፣ የተሻሻለዉ የአማራ ክልል ማረሚያ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 295/2017፣ የአማራ ክልል ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ ቁጥር 297/2017፣ የአማራ ክልል የባህል ፍ/ቤቶች ለማቋቋምና እዉቅና ለመስጠት የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 298/2017 ፣የአማራ ክልል የፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት እንደገና ማቋቋሚ አዋጅ ቁጥር 299/2017 እና የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 17/2017 ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

አጠቃላይ በዘርፉ የተገኙ ዉጤቶችና የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በክልሉ የታቀደውን የ25 ዓመት የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት እቅድ የሚሸከም የዳኝነት እና የፍትሕ ለመገንባት ለሚደረገው ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ እና የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፍ ተቋማት የጋራ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ ለዘርፉ ዕቅድ መነሻ የሚሆን የዘርፉ ተቋማቱት አፈጻጸም የሁኔታ ግምገማ እንደሚከተለው ተዳሷል፡፡

### 29.4.2. የዳኝነት አገልግሎት፡ ፍርድ ቤቶች

በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግስት 3ኛው የመንግስት አካል የሆኑ ነጻ እና ገለልተኛ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመዋል፡፡ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 እና የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 282/2014 በክልሉ ውስጥ ነጻ እና ገለልተኛ የሆኑ ፍርድ ቤቶች ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማችና ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ ያረጋገጡ እና በህዝብ ዘንድ አመኔታ የተቸራቸው ፍርድ ቤቶች የመገንባትን አስፈላጊነት ያትታሉ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅርቡ የጀመረውን ሥር ነቀል የዳኝነት ትራንስፎርሜሽን የሚሸከሙ ፍርድ ቤቶችን ለመገንባት ያለመ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የማጠናከሪያ አዋጅ ቁጥር 297/2017 በክልሉ ፍርድ ቤት መጽደቁ የላቀ የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት ፍርድ ቤቶች ለሁለንተናዊ ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት አይነተኛ ሚና እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡ የክልሉ ፍርድ ቤቶች አፈጻጸም አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ተዳሷል፡፡

**የሰው ሐይል ልማትና ተቋም ግንባታ ስራ፡** ከ2003 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም ባሉት 14 ተከታታይ ዓመታት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሰው ሀይል ልማትና ጠንካራ ተቋም ግንባታ ልዩ ትኩረት ሰጥተው ለመስራት ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት የፍርድ ቤቶችን አመራሮች፣ ዳኞች፣ የጉባኤ ተሿሚዎች እና የአስተዳደር ሰራተኞችን የመፈጸም አቅም ለማጎልበት ያለሙ በርካታ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች ከመስጠታቸውም ባሻገር የረዥም ጊዜ የትምህርት ፕሮግራሞችን በማመቻቸት በርካቶች የትምህርት ዝግጅታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡ የፍርድ ቤቶችን አመራሮች በሚመለከት የሴት አመራሮች ቁጥር አነስተኛ መሆን በአንኳር ችግርነት ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ የክልሉን ፍርድ ቤቶች ነጻነትና ገለልተኝነት የሚያጠናክሩ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የዳኞች የዘመናት ጥያቄ የነበረው የዳኞች ከለላና ጥበቃ በህግ እውቅና ማግኘቱ የዳኝነት ነጻነትንና ገለልተኝነትን በማረጋገጥ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የሰው ሐይል ልማት እና የተቋም ግንባታ ስራው በፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተጨባጭ ለውጦች ያመጣ መሆኑ እሙን ቢሆንም ሊቀረፉ የሚገባቸው አንኳር ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ የሰው ሐይሉ ብቃት፣ ክህሎት እና ሥነ-ምግባር ሊፈተሽ የሚገባው በመሆኑ ስልት ቀይሶ መስራትን ይጠይቃል፡፡ የሥነ-ምግባር ችግር በተለያየ ጊዜ የሚነሳ በመሆኑ የችግሩን ጥልቀትና ስፋት ለመለየ እና መፍትሄ ማፍለቅ ላይ በአንክሮ ማጤን ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቶች ነጻነት ላይ የሚቃጡ ጣልቃ ገብነቶች፣ የፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች ለመፈጸም እና ለማስፈጸም የእምቢተኝነት አዝማሚያ

እያደገ መምጣት፣ የፋይናንስና የሰው ሐይል አስተዳደር ነጻነት ምሉዕ አለመሆን እና መሰል አንኳር ችግሮች የተቋም ግንባታ ስራውን ፈታኝ አድርጎታል፡፡ የዘርፉን ተቋማት ችግሮች ለመቅረፍ ያስችላል ተብሎ የተቋቋመው የክልሉ የፍትሕ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት የልህቀት ማዕከል ከመሆን ይልቅ የራሱን ችግሮች እንኳን ለመፍታት አቅም ተስኖት ቆይቷል፡፡ ይህንን መሰረታዊ ችግር ለመፍታት በተወሰደ የሪፎርም አቅጣጫ ለውጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሆነ የፍትሕ እና ሕግ ኢንስቲትዩት በአዋጅ ቁጥር 299/2017 እንደገና መቋቋሙ የዘርፉን የሰው ሀይል ልማት ችግር ይቀርፋል ተብሎ እምነት ተጥሎበታል፡፡

**የዳኝነት የአገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡** የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎቶችን በመክፈት፣ ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤቶችን በመክፈት፣ የተዘዋዋሪ ችሎት ቀጠናዎችን በማስፋት እና ድግግሞሽን በማሳደግ፣ የፐላዝማ ችሎት አገልግሎት በመስጠት፣ በርካታ ቅጻ ቅጾችን በመቅረጽ ባለጉዳዮች በነጻ እንዲገለገሉበት በማድረግ፣ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ቅድሚያ አገልግሎት የሚያገኙበትን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋትና መሰል እርምጃዎችን በመውሰድ የዳኝነት አገልግሎትን ተደራሽነት ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ አመርቂ ውጤቶች ታይተዋል፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጀመሩ የዲጂታላይዜሽን ስራዎች ሲጠናቀቁ ደግሞ ተደራሽነትን ይበልጥ ያሰፋል የሚል እምነት ተይዞ በርብርብ እየተሰራ ነው፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ ባጋጠመው የጸጥታ መደፍረስ ምክንያት ተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት መቋረጡ፣ በብዙ ቦታዎች የነበረው የፐላዝማ ችሎት አገልግሎት ማቋረጥ፣ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች የዋጋ ንረት እና መሰል ችግሮች የዳኝነት አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ረገድ በቁልፍ ተግዳሮትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ክልሉ ሲወረድ ሲዋረድ የመጡ ባሕላዊ የአለመግባባት መፍቻ ሥርዓቶች ባለቤት ቢሆንም ለመሰረተ-ማኅበረሰብ አማራጭ የፍትሕ አገልግሎት የተሰጠው ዝቅተኛ ትኩረት ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት ረገድ ትልቅ ጋሬጣ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ችግሩን በመረዳት በጠቅላይ ፍርድ ቤት በኩል ተዘጋጅቶ በክልሉ ምክር ቤት የጸደቀው በአማራ ብሔራዊ ክልል የባሕል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም እና እውቅና ለመስጠት የወጣው አዋጅ ቁጥር 298/2017 ዓ.ም ተግባራዊ ሲሆን የዳኝነት አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በተጨማሪም እንደ ፍ/ቤት መር አስማሚነት እና የግልግል ዳኝነት ያሉ አማራጭ ያለመግባባት መፍቻ መንገዶችን በማጠናከር ከንግድና ኢንቨስትመንት የሚነሱ ክርክሮችን በአፋጣኝና በጥራት እልባት እንዲገኙ በማድረግ ለኢንቨስትመንትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የፍ/ቤቱን የማይተካ ሚና ለመጫዎት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም የግልግል ዳኝነት ማሰልጠኛ እና የግልግል ዳኝነት ፋሲሊቲዎችን የያዘ ሕንጻ ለመገንባት ከባ/ዳር ከተማ አስተዳደር ቦታ በማስፈቀድ ከክልል አልፎ አገራዊ ፋይዳ ያለዉን ይህንን ፕሮጀክት እዉን ለማድረግ ታስቦ እየተሰራ ነዉ፡፡

**የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍና እና ጥራት፡** ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች እና በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስታት መሰረት የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአንድ በኩል የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት መስጠት ሚዛናዊ ሆነው ሊተገበሩ ይገባል፡፡ ባለፉት ዓመታት የጉዳዮች የመጨናነቅ መጠን፣ የማጥራት መጠን፣ የዳኞች የመዝገብ ጥምርታ፣ የውሳኔዎች የመጽናት፣ የመሻር እና የመሻሻል ምጣኔ ስታንዳርዶችን በመቅረጽ የዳኝነት አገልግሎትን ቅልጥፍናና ጥራትን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች በመሰራታቸው ምክንያት ተጨባጭ ለውጦች ተመዝግበዋል፣ ለአብነት ያህልም ከ2017 በጀት አመት ጀምሮ የሰበር ችሎት የቀረቡለትን መዛግብት በዕለቱ እልባት የመስጠት ደረጃ ላይ መድረሱ እና ለዉሳኔ የተቀጠሩ መዛግብትን በትናንሽ ምክንያቶች ሳይቀር አልተመረመረም በሚል ይሰጥ የነበረው ተለዋጭ ቀጠሮና ትዕዛዝ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ቀርቷል ማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱ ቅልጥፍናን አምጥቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ዓመታትን ይፈጁ የነበሩ መዛግብት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ የመጡ ቢሆንም በተለያዩ ውስጣዊና ውጪያዊ ምክንያቶች ረዥም ጊዜ የሚያስቆጥሩ መዛግብት በየደረጃው በሚገኙ ፍርደ ቤቶች ያሉ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ቅልጥፍናን በማምጣት ረገድ የተመዘገበውን ለውጥ ያህል የዳኝነት አገልግሎት ጥራት ላይ አመርቂ ውጤት አልተመዘገበም፡፡ የፍርድ ጥራት ችግር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይደለም፤ በተለይ ደግሞ የወረዳ ፍርድ ቤቶች የፍርድ ጥራት ችግር ሰፊ መሆኑን ሪፖርቶች አመላክተዋል፡፡ ሀሰተኛ ምስክርነት፣

ሀሰተኛ ሰነዶች፣ የካበተ ልምድ፣ ክህሎትና ሥነ ምግባር ያላቸው ዳኞች ፍልሰት እና አልፎ አልፎም የባለሙያዎች ብልሹ ሥነ ምግባር ፍትህን በማዛባትና የፍርድ ጥራት ችግርን በማጉላት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ስለሆነም በአንድ በኩል የሰው ሐብት ልማት ስራዎቻችን ላይ ትኩረት ማድረግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሀሰተኛ ምስክርነትና ሀሰተኛ ሰነድን በሚመለከት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በርብርብ መስራትን ይጠይቃል፡፡

**የሙያ ሥነ-ምግባርን ማሻሻልና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡** የዳኝነት ሙያ ሰፊ የመወሰን ስልጣን የሚያጎናጽፍ በመሆኑ ከፍ ባለ ሥነ-ምግባር ካልተከወነ በስተቀር በሰዎች ሕይወት፣ ነጻነትና የንብረት መብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል፡ ባለፉት ዓመታት የሙያ ሥነ-ምግባርን ለማሻሻል የሕግ ማዕቀፎችን ከማዘጋጀት ጀምሮ የተለያዩ አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል፡፡ ለአብነት ያህልም የዳኞች አስተዳደር አብይ ጉባኤ እና ንዑስ ጉባኤዎች ተቋቁመዋል፤ የፍርድ መርማሪ እና የሕግ ኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ተመድበዋል፡፡ የፍርድ ምርመራ እና የሕግ ኢንስፔክሽን ሥራው የራሱ የሆነ ውስንነት ቢኖርበትም የሚስተዋሉ የፍርድ አሰጣጥ እንከኖችን በመለየትና የሙያ ሥነ ምግባርን በማሻሻል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በቀጣይ አደረጃጀቱን ለማስተካከል ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ የሥነ ምግባር ችግር የተስተዋለባቸው ዳኞች፣ የጉባኤ ተሿሚዎች እና የአስተዳደር ሠራተኞች ከቀላል እስከ ከባድ የዲሰፕሊን ቅጣት ተላልፎባቸዋል፡፡ በቀጣይም የሥነ ምግባር ችግርን በሚመለከት ቀላል፣ ሚስጥራዊነቱ እና ደህንነቱ ተጠበቀ የቅሬታ መቀበያ ሥርዓት በመዘርጋት፣ የቅሬታ ማቅረቢያ ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ፣ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ በመስጠት የህዝብ አመኔታ የተቸራቸው ፍርድ ቤቶች ለመገንባት ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡

**የዳኝነት አገልግሎትን በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግን በተመለከተ፡** ዲጂታላይዜሽን አገልግሎት ተደራሽነትን፣ ቅልጥፍናን እና ጥራትን በማረጋገጥ እንግልትና ውጣ ውረድን መቀነሱ አያጠራጥርም፡፡ በአገር አቀፍ ብሎም በክልል ደረጃ የታቀደው የፍትህ ትራንስፎርሜሽን እቅድ አንዱ ምሰሶ የዳኝነት እና የፍትሕ ዘርፉን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የክልላችን ፍርድ ቤቶች ወደ ኋላ የቀረ መሆኑ ተገምግሞና ታምኖበት በክልሉ መንግስት ልዩ ትኩረት ተደርጎ የዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ሥራው እየተፋጠነ ይገኛል፣ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች እና የፌደራል ተቋማትም የለሙና የበለጸጉ ሶፍትዌሮችን ሳይቀር ለጠቅላይ ፍርደ ቤት አበርክተዋል፡፡ በ2017 በጀት አመት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ከ400 ሚሊየን ብር በላይ ዋጋ ያለዉ የዲጅታላይይሽን ፕሮጄክት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመዋዋል ወደ ሥራ የገባ ሲሆን ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሙሉ በሙሉ መተግበር ሲጀምር የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል የተገልጋዮችን እርካታ እና የህዝቡን አመኔታ ከፍ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፡** የፍትሕ አገልግሎት በአንዱ ተቋም ተጀምሮ እዚያው የሚያልቅ አይደለም፡፡ ይልቁንም የዘርፉን ተቋማት ቅንጅትና የእርስ በእስርስ ትብብር ይጠይቃል፡፡ በባለፉት ዓመታት በተለይም ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የዘርፉ ተቋማት ተቀናጅቶ ለመስራት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም ግን በዘርፉ ተቋማት መካከል መገፋፋትና መወቃቀስ ተስተውሏል፡፡ ተቋማቱ ከዕቅድ በዘለለም በቅንጅት ሥራ ይሄ ነዉ የሚባል ተጨባጭ ዉጤት አላመጡም፡፡ በዚህ ረገድ ያለውን ችግር ለመቅረፍ በማሰብ ከመስከረም 2017 ዓ.ም ጀምሮ የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት የትብብር መድረክን በመመስረት፣ የመግባቢያ ቻርተር በመፈራረም፣ የጋራ ዓመታዊ እቅድ በማቀድ፣ የጋራ ጉዳዮችን በግልጽ በመለየት ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የትብብር መድረኩ የራሱ ጽ/ቤት እና ኃላፊ ተመድቦለታል፤ የትብብር መድረኩንም ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበላይነት እንዲመራው በቅርቡ በፀደቀው የክልሉ ፍርድ ቤቶች የማጠናከሪያ አዋጅ የሕግ መሰረት እንዲኖረዉ፣ዘላቂና ተቋማዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በትብብር መድረኩ ላይ የማይገኝ የዘርፉ ተቋማት ኃላፊ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ጭምር በጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ቅንጅታዊ አሰራሩ ገና ከጅምሩ አመርቂ ውጤት እያሳየ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

**የተገልጋዮችን እርካታ ማረጋገጥ እና የህዝብ አመኔታ ማትረፍን በተመለከተ፡** የፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ግብ በሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት የተገልጋዮችን እርካታ ማረጋገጥ እና የህዝብ አመኔታን ማግኘት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ምንም እንኳን ብዙ መስራት ቢጠይቅም መሻሻሎች ታይተዋል፡፡ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ተገልጋዮች እርካታ 64.5% ነው፡፡ የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን፣

ቅልጥፍናን፣ ተገማችነትንና ጥራትን በማረጋገጥ እንዲሁም የህዝቡንና ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማሳደግ የተገልጋዮችን እርካታ ለማረጋገጥ እና የህዝቡን እምነት ከፍ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 29.4.3. ፍትሕ ቢሮ እና የዐቃቢ ህግ አገልግሎት

ፍትሕ ቢሮ ፍትሐዊ እና ተገማች ሕጎችን በማርቀቅ፣ ጥራት ያለው ምርመራ በማከናዎን፣ የሕጎችን አፈጻፀም በመከታተል፣ ውጤታማ የሕግ ምክር እና የዓቃቤ ሕግ አገልግሎት በመስጠት፤ የሕዝብ እና መንግስት ጥቅም ለማስጠበቅ የተቋቋመ ሲሆን፣

**አደረጃጀት፣ ከአደረጃጀት አኳያ፡** ከቀደሙ በተሻለ የአስተዳደር ዘርፍ፣ ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ ዘርፍ፣ የሕግ እና ፍትሕ ዘርፍ፣ ተብለው የሚታወቁ ሦስት አደረጃጀቶች አሉት፡፡ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ዘርፍ ነፃ ሆኖ ካለመቋቋሙ በተጨማሪ በሌሎች ሁለት ዘርፎችም መዋቅራዊ የአደረጃጀት ክፍተቶች አሉበት (ለምሳሌ፣ የሰነዶች፣ ጠበቆች እና ሲቭል ማሕበረሰብ ድርጅቶች፣ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ትብብር ጥምረት ጽ/ቤት፣ ሐብት ማስመለስ እና ጉባኤ ጽ/ቤት)፡፡

**የሰው ኃብት ልማት እና አስተዳደር፡** የቢሮው አስተዳደር ዘርፍ የሰው ኃብት ልማት፣ የዓቃቢያነ-ሕግ ጉባኤ ጽ/ቤት፣ የዕቅድ እና በጀት፣ ግዥ፣ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር፣ ኦዲት፣ ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤትን ያካተተ ሲሆን ከሰው ሐብት ልማት አኳያ ቢሮው 1790 ዓቃብያነ-ሕግ (1246 ወንድ፣ 544 ሴት) እና 1850 አስተዳደር ሰራተኞች (ወንድ 899 ሴት 951) ድምር 3640 የሰው ኃይል አለው፡፡ ከሰው ኃይል አስተዳደር አኳያ የአጭር እና እረጅም ጊዜ ስልጠናዎች በሰፊው የሚሰጡ ቢሆንም ዓቃቤያነ-ሕግ ከማበረታቻ ስርዓት ችግር ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ቁጥር በየአመቱ ይለቃሉ፤ የብቃት እና ስነ-ምግባር ችግሮችም ይስተዋላሉ፡፡

**የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አፈጻፀም፡** ይህ ዘርፍ የፀረ-ሙስና ወንጀል ጉዳዮች፣ የመደበኛ ወንጀል ጉዳዮች፣ የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች እና የሐብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬትን የያዘ ሲሆን ዋና ስልጣን እና ተግባሩም ወንጀል ምርመራን መምራት፣ የክስ እና ክርክር አገልግሎት፣ በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስ እና በሂደቱ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ከመድረሳቸው በፊት የማጥራት እና ውሳኔ (gate keeper to the judiciary) መስጠትን የሚያጠቃልል ሲሆን የመዝገብ ማጥራት ተግባርን በተመለከተ በተከታታይ 98.95 ፐርሰንት አስመዝግቧል፡፡ ወንጀለኛን ከስሶ ከማስቀጣት ምጣኔ አኳያ በቀጥታ ክስ 94.46 ፐርሰንት ላይ የደረሰ ሲሆን የይግባኝ እና ሰበር ማሸነፍ ምጣኔ ደግሞ 72.09 ፐርሰንት ላይ ይገኛል፡፡ ይሕ ዘርፍ ካሉበት በርካታ ዉስብስብ ችግሮች አንጻር የተመዘገበዉ ዉጤት ሲታይ አፈጻጸሙ ጥሩ ደረጃ ላይ ቢሆንም ምርመራን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ከመምራት ጀምሮ የወንጀል እና ወንጀለኛ መረጃ አያያዝ፣ ከፖሊስ እና ፍርድ ቤት ጋር የመረጃ ልውውጥ እና ትስስር አለመፍጠር፣ የምርመራ ጥራት ችግርን አለመሻገር ፣ መዝገቦች መቋረጥ ምጣኔን አለመቀነስ ፣ የክስ እና የክርክር ጥራት ችግር በዘላቂነት አለመፍታት፣ የኤግዚቢት አያያዝ፤ አስተዳደርና አመላለስ ላይ የሚታየዉን ችግር በዘለቄታ አለመፍታት፣ የገንዘብ ቅጣት በተገቢዉ ሁኔታ አለማስፈጸም፣ በወንጀል ምክንት የተወሰደን ንብረት በተፈለገዉ ደረጃ አለማስመለስ እና በዘርፉ ላይ የሚታዩ የአደረጃጀት ችግሮችን አለማስካከል ዋናዋና ችግሮች ስለሆኑ እነዚህን ችግሮች ሊፈታ የሚችል ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**የሕግ እና ፍትሕ አግልግሎት፣** ይሕ ዘርፍ የሕግ ማርቀቅ፣ ምክር እና ማጠቃለል አገልግሎት፣ የፍትሐብሄር ፍትሕ አገልግሎት፣ የሰነዶች፣ ጠበቆች እና ሲቭል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባ፣ ማረጋገጥ እና ክትትል አገልግሎት፣ የሰብአዊ መብት ክትትል አገልግሎትን ለክልሉ ሕዝብ እና መንግስት የሚሰጥ ሲሆን የክልሉ መንግስት ዋና የሕግ እና ፍትሕ ዘርፍ አማካሪ በመሆን ከሚወጡ ሕጎች ፍትሐዊነት ጀምሮ እስከ አፈጻጸም ድረስ የክልሉን መንግስት እና ሕዝብ ጥቅም እና መብት መከበሩን በማረጋገጥ ላይ መልካም ተግባራትን በመፈፀም ልይ ይገኛል፡፡ የዚህ ዘርፍ በፍትሕብሄር ፍትሕ ጉዳዮች የመዝገብ ማጥራት 98.47 ፐርሰንት ሲሆን የማሸነፍ ምጣኔ 89.36 ፐርሰንት ላይ ደርሷል፡፡ ፍታብሄር ጉዳይ ለብልሸቱ በርካታ ተዋንያን ያሉበት ከመሆኑ አንጻር እነህን ችግሮች በማለፍ መዝገቦችን በፍጥነት የመወሰንና ተከራክሮ የማሸነፍ ምጣኔ ዉጤት ሲታይ መልካም የሚባል ቢሆንም፤ ጉዳዮችን በድርድር/በአማራጭ የፍትሕ ስርዓት አለመቋጨት፣ ነጻ-የህግ አገልግሎትን

በስፋት ከመስጠት አኳያ ክፍተቶች ሰፊ ናቸው፡፡ የሕግ ማርቀቅ ስራዎችን በተመለከተ ጥራታቸዉን የጠበቁ ህጎችን የማዘጋጀት ስራ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ህጎችን ከማጠቃለል፣ የሕጎች ተፈጻሚነትን ከመከታተል እና ከጥራት መጠበቅ አኳያ ችግሮች አሉ፡፡ ጠበቆች በፍትህ ስርአቱ ውስጥ አወንታዊ ሚና እንድኖራቸዉ በስርአት የማስተዳደር ዉስንነት ይስተዋላል፡፡ የሰነዶች ምዝገባ እና የማረጋገጥ ተግባር፣ የሲቨል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን የመመዝገብ እና የመከታተል ተግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል የታየበት ተግባር ቢሆንም ጥብቅ እና ወጥ የአሰራርና የአደረጃጀት ስርአት ዘርግቶ የአገልግሎቱ ጥራት እና ቅልጥፍናን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ሰብአዊ መብትን ከማሳወቅ፣ ከማክበር፣ ከማስከበር እና ከማሟላት አኳያ መልካም ጅምሮች ቢኖሩም ክፍተቶች ሰፊ ናቸው፡፡

መሰረተ ልማት፣ መሰረተ ልማትን በተመለከተ ቢሮው በዞን መምሪያ ደረጃ የተሻለ የሕንፃ መሰረተ-ልማት በማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ በክልል ደረጃም የቢሮ እድሳትና ተያያዥ ግብአቶችን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነዉ፡፡ በወረዳ ደረጃም አንዳንድ ወረዳወች ደረጃቸዉን የጠበቁ ቢሮወች በመገንባት ወደ ስራ የገቡ አሉ፡፡ ይሁን እንጅ ከቢሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ ሁሉም ተቋሞቻችን የቢሮ እና ሌሎች የግብአት ችግሮች በተፈለገዉ ደረጃ አልተፈታም፡፡ ከበጀት አንጻርም ወረዳዎች ላይ የከፋ ቢሆንም በቢሮ እና በዞኖች ላይ ያለዉ የበጀት ችግር ከፍተኛ ነዉ፡፡

### 29.4.4. ፖሊስ እና የፖሊስ አገልግሎት

በአማራ ክልላዊ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ቁጥር 13 ሀምሌ 04/2006ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 216/2006ዓ.ም ላይ በርካታ ተግባራትን እንዲያከናውን ለኮሚሽኑ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በአዋጁ ከተሰጡት ዋና ዋና ተልዕኮዎች ወንጀልን መከላከልና ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ የወንጀል ምርመራ ማጣራትና የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓት እንዲሻሻል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ሲሆን ኮሚሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮው ለመወጣት ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ የፖሊስ መዋቅር በመዘርጋት ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ በሁሉም የዞን ከተሞችና ከተማ አስተዳደሮች የፖሊስ መምሪያዎች በሁሉም የክልሉ ወረዳዎች እና ንዑስ ወረዳዎች የፖሊስ ጽ/በቶችን በመክፈትና በቀበሌ ደረጃ በህብረተሰብ ተሳትፎ ማዕከላትን አስገንብቶ የሰው ኃይል በመመደብ ተደራሽ የሆነ ፖሊሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ቀደምት ተቋም ነው፡፡ በወንጀል መከላከል ስራዎች ሰላምና ፀጥታ በማረጋገጥ በኩል ዘርፈ ብዙ ውጤቶችን ማምጣት የተቻለ ሲሆን በ1994 ዓ.ም የጎጥ ወንጀል መከላከል ስራን በመጀመር ለህብረተሱ ተደራሽና አሳታፊ የወንጀል መከላከል ስራን በመጀመርና ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ፍልስፍናን በክልሉ በመተግበር ህዘብ ባሳተፈ የወንጀል መከላከል ተግባር በሃገር አቀፍ ደረጃ የተሞከሮ ማዕከል በመሆንና ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን ትርጉም ባለው ደረጃ በመቀነስ በሰላምና ፀጥታ ስራዎች ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡ ነገር ግን ላለፉት አምስት ዓመታት ጀምሮ እንደሃገር በተከሰተው የኮረና ወረርሽኝ በሽታ፣ በሃሪቱ በተከሰተው የሰሜኑ ግጭትና ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በክልሉ በተከሰተው ውስጣዊ ግጭት ምክንያቶች ከዚህ ቀደም የነበሩ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ስራዎች በአብዛኛው የክልሉ ቀበሌዎች አገልግሎቱ የተቋርጠና የፖሊስ አገልግሎት ህግ ማስከበር ተልዕኮ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በሚፈለገው ልክ ውጤት ማምጣት ባለመቻሉ አገልግሎቱን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ልዩ ትኩረት በመስጠት ማጠናከር ይገባል፡፡

ሁለተኛው የፖሊስ ተልዕኮ የወንጀል ምርመራ ሲሆን ከወንጀል መከላከሉ ባሻገር ወንጀልና የትራፊክ አደጋ ከተፈፀመ በኋላ አጥፊውን ከንፁሀን በመለየት የድህረ ወንጀል መከላከል አላማ ያለው የወንጀል ፍትህን ማረጋገጥ ሲሆን ዘመናዊ የምርመራ አቅሞችን ከመጠቀም አንፃርም ከፍተኛ ወጪ በማውጣት የፎረንሲክ ላብራቶሪ በማቋቋም የአሻራ ምርመራ፣ የሰነድና ሌሎች ባዮሎጂካል የቴክኒክ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ለምርመራ ሥራው ጉልህ አስተዋፅኦ ማበርከት ተችሏል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አገልግሎት ፈላጊው በሚጠብቀው ልክ የምርመራ አገልግሎት ጥራት፣ አቅምና ቅልጥፍና ማሻሻል ባለመቻሉ አፈፃፀሙ በሚፈለገው ልክ ማደግ አልቻለም ዋና ዋና እንቅፋቶችም የምርመራ ባለሙያዎች አቅም ውስንነትና ሥነ ምግባር ችግር፣ የቢሮና የግብዓት ችግር፣ የምርመራ አቅምና ጥራት መለኪያዎች ችግር መኖር ለምርመራ ውጤታማነት ከፍተኛ

እንቅፋት በመሆናቸው ዘርፉ በሰው አቅምና በሎጀስቲክስ ግብዓት በማጠናከር ተደራሽ የሆነ ፍትህ መዘርጋት ይገባል፡፡

ስለሆነም የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ህብረተሰቡ ያለ ምንም የደህንነት ስጋት ወደ ልማቱ እንዲያተኩር በማድረግ የክልሉ ሰላምና ፀጥታም አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ የነገ የማይባል ቀዳሚ ተግባር ለመወጣት ፖሊስ ህብረተሰቡን በማሳተፍና አጋር በማድረግ ተቋሙ የተቋቋማበትን አላማ ለማሳካት ትኩረት ሰጥቶ በመስራት በህበረተሰቡ ዘንድ ታማኝነት ያለው ተቋም በመፍጠር ከጊዜ ወደ ጊዜ በአፈፃፀም ሁኔታውም ሆነ በይዘቱ እየተወሳሰበ የመጣውን የወንጀል ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት አስቀድሞ ለመከላከል ተቋሙ ጊዜውን በሚመጥን መልኩ በሰው ኃይልና በቴክኖሎጅ በማደራጀትና በማዘመን ችግሮችንና ነባራዊ ሁኔየታውን በአግባቡ በመተንተን አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው፡፡

ስለዚህ የህግ የበላይነትን በማስፈን ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ የወጡ የመንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ ለውጤት ጠንክሮ መስራት እንደሚገባ ግልፅ አቅጣጫ በመያዝ ካለፉት የስትራቴጂክ እቅዶች አተገባበር ላይ የታዩ የህግ የበላይነት ማስከበር ክፍተቶችን በማረም የክልላችን ህዝብ ለሰላምና ደህንነት እያሳየ ያለውን ተሳትፎና የህግ መከበር ፍላጎት ይዞ ለማስቀጠልና ከሁሉም የፍትህ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን የሚገባ ይሆናል፡፡

### 29.4.5. ማረሚያ ቤቶች፡ ማረም፣ ማነፅ እና መልሶ መቀላቀል

የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር -176/2010 ሲሆን ከኮሚሽነሩንና ም/ኮሚሽነር መተጨማሪ በ12 ዳይሬክተሮች የተዋቀረ ሲሆን በዋናነት በዋናነት ታራሚዎችን የማረም እና ማነጽ ሀላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው ፡፡ በአጠቃላይ በሠላሳ አንድ ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ሲሆን ከ2013 እስከ 2016 ዓ.ም በተወሰደ ዳታ እንደታየው በአመት በአማካኝ 18,285 ታራሚዎችና እና ታሳሪዎች በተጨማሪም 104 ህጻናትም ከወላጆቻቸው ጋር በማረሚያ ቤት ይታሰራሉ፡፡ በአባላትና ሰራተኞች ስነ-ምግባር ለማስተካካል በሚቀርቡ ጥቆማዎች መሰረት 100% እና ታራሚዎች የሚፈጥሩትን የስነ ምግባር ግድፈት ተመጣጣኝ የእርምት ቅጣት ይሰጣል፡፡ ለታራሚዎች በልዩ ሁኔታ በየዓመቱ 4264 የስነልቦና እና ማህበራዊ የምክር አገልግሎት 235,908 ደግሞ በቡድንና በተናጠል የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በየዓመቱ በአማካኝ 2322 የቀለም ትምህርት፣ 5110 የቴክኒክና ሙያ፤ 3555 ደግሞ የግብርና ስልጠና ይሰጣል፡፡ በዚህ መሰረት ማረሚያ ቤቱ በየዓመቱ በአማካኝ 9,397,430.75 ብር ከግብርና 35,170,339 ብር፣ ከዕደጥበብ በአጠቃላይ 178,271,079 ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

ውጤታማ መዋቅራዊ ማሻሻያ ማድረግ እና የሰው ኃይሉንም በቁጥርና በጥራት የተሟላ እንዲሆን ማድረግ አለመቻሉ ከው ጭ የሚደርስን የህገወጦች ጥቃት መከላከል ባለመቻሉ ታራሚዎች ከእስር እንዲያመልጡ መሆኑ፤ በአመክሮና በይቅርታ አሰጣጥ በተለይም ከዕርቅ አፈጻጸም ጋር ተየይዞ የሚነሱ በርካታ ችግሮችን ለመፍታት የሚችል አደረጃጀትን በጥናት ላይ በመመስረት የተሸለ አሰራር መዘርጋት አለመቻሉ፣ የማረሚያ ቤቶች ግንባታ ከተማ ው ስጥ መሆናቸው ና ለማረም ማነፁ እስታንዳርዱን የጠበቀና የሰለጠነ፤ አምራች ዜጋ ለመፍጠር ምቹ አለመሆኑ፡፡ ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ከወጡ በኋላ ከማህበረሰቡ ጋር በጥሩ ሁኔታ እንዲቀላቀሉ ማድረግ (reintegration) የሚስችል አሰራር አለመዘርጋት እንደ ክፍተት የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለሁሉም ታራሚ አንድ አይነት የማረም እና የማነጽ አማራጮች መተግበራቸው እና የወጣት ጥፋተኞችና አዋቂዎች በአንድ ግቢ ውስጥ ተቀላቅለው መኖራቸው የባህሪ ለውጥ ስራውን የበለጠ እንዲወሳሰብ ያደረገው መሆኑ፣ የህጻናት ጸባይ ማረሚያ እና የአእምሮ ህመምተኞች መገገሚያ ተቋም የሌለ መሆኑ ወዘተ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

ለታራሚዎች አመክሮ፤ ይቅርታና የማይድን በሽታ ለተያዙ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያው እና አተገባበሩ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ በመሆኑ በታራሚዎችና በማረሚያ ቤቱ መካከል አለመግባባት መንስኤ በመሆኑ መመሪያው አተገባበር ለአባላት ስነ-ምግባር ብልሽት መንስኤ ሆኗል፡፡ የፌደራል ኬዞች እና የመከላከያ አባላት ታራሚዎች

ይቅርታ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተሞልቶ ቢላክም የሚፈቀደው በፌደራል መንግስት በመሆኑ በአንድ ማረሚያ ቤት የተለያየ አሰራር መኖሩ ለቅሬታ ምንጭ መሆኑ፤ ዋስትና ተከልክለው ወይም ዋስትና ያላቀረቡ ተጠርጣሪዎች ወይም በጊዜ ቀጠሮ ወደ ማረሚያ ቤት ከገቡ በኋላ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እያደረጉ ለፍርድ ቤት ያለማሳወቅና ተረስተው የሚቀሩበት ሁኔታ መኖር፣ በመሰረታዊ ፍላጎትና በጤና አገልግሎት የበጀት ችግር በመኖሩ የተሟላ አገልግሎት ያለመስጠት፣ ታራሚው ለማረሚያ ቤቶች ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኝ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሮ ወደ ስራ ያለመግባት፣ ታራሚን ከማረምና ከማነፅ አኳያ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያለማድረግና ታራሚው በማረሚያ ቤት እስከ መገዳደል የሚደርስ ህገ-ወጥ ድርጊት መፈፀሙ በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ያሉ ተጠርጣሪዎችን በዝውውር ወደ ሌላ ማረሚያ ቤት መላክ እና በችሎት ክርክር በቀጠሮው ከተቀየሩበት ማረሚያ ቤት ያለመቅረብ፣ ተቋሙ የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ ባለመሆኑ በስነ-ምግባር ችግር በማረሚያ ቤቱ መግባት የሌለባቸው የተከለከሉ ነገሮች እየገቡ ለሁከትና ብጥብጥ መንስኤ ከመሆናቸው ም በተጨማሪ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የማረም ስልት ተግባራዊ አለማደረግ የመሳሰሉ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡

## 29.5. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

### ርዕይ፣

- በ2022 ዓ.ም ሰላም እና የህግ የበላይነት ያረጋገጠ፣ ተደራሽ፣ ውጤታማና የህዝብ አመኔታ ያተረፈ የዳኝነት እና ፍትሕ ስርዓት ተፈጥሮ ማየት፣
- በ2027 ቴክኖሎጂ መር ውጤታማ የዳኝነት እና ፍትህ ስርዓት ተገንብቶ ማየት፣
- በ2042 በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነ የዳኝነት እና ፍትሕ ስርዓት ተፈጥሮ ማየት፣

### ተልዕኮ፣

- ወንጀል መከላከል እና ተፈፅሞ ሲገኝ ጥራት ያለው ምርመራ በማከናወን ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ በማቅረብ የክልሉን እና የነዋሪዎችን ሰላም እና ደሕንነት ማረጋገጥ፣
- ፍትሐዊ እና ተገማች ሕጎችን በማርቀቅ፣ የሕጎችን አፈጻፀም በመከታተል፣ ውጤታማ የሕግ ምክር እና የዓቃቤ ሕግ አገልግሎት በመስጠት፤ የሕዝብ እና መንግስት ጥቅም ማስጠበቅ፣
- የዳኝነት ነፃነትን እና ገለልተኝነትን በማረጋገጥ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች፣ ጥራት ያለው እና ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፣
- በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎችን ሰብአዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ ማስተዳደር፤ ውጤታማ የማረም እና የማነፅ ስራ መስራት፣ ደጋጋሚነትን መከላከል፣ ሰላማዊ እና አምራች ዜጋ በማድረግ ወደ ህብረተሰቡ መልሶ መቀላቀል፣
- የዘርፉን የሰው ኃይል እና ተቋማዊ አቅም በመገንባት፣ በቴክኖሎጅ የተደገፈ እና ቅንጅታዊ አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ፣ ሰብአዊ መብትን ማዕከል ያደረገ፣ ውጤታማ የዳኝነት እና የፍትሕ አገልግሎት በመስጠት የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣

### እሴቶች፣

- የሕግ የበላይነት፣
- ሰብአዊ ክብር፣
- ሙያዊ ብቃት እና ስነ-ምግባር፣
- ነጻነት እና ገለልተኝነት፣
- ግልፅነትና ተጠያቂነት፣
- ቅንጅታዊ አሰራር፣
- ምርምርና ፈጠራ፣

### ቁልፍ ችግሮች፣

በሕግ እና ፍትሕ ተቋማት የሚስተዋሉት ቁልፍ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተደራሽነት ችግር፣
- የተገማችነት ችግር፣
- የፍትሕ መጓደል፣

- ☞ የደሕንነት ስጋት፣
- ☞ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት፣

## የችግሮች መንስዔዎች፣

- ☞ ተቋማዊ ነጻነት እና የሙያዊ ገለልተኛነት በተሟላ ሁኔታ አለመኖር፣
- ☞ ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን፣
- ☞ ሙያዊ ብቃት ችግር፣
- ☞ የስነ-ምግባር እና ተጠያቂነት ችግር፣
- ☞ የመሰረተ-ልማት እና ግብአት ችግር መኖር፣
- ☞ የአመራር ቁርጠኝነት እና ብቃት ችግር፣
- ☞ ዝቅተኛ ቴክኖሎጅ አጠቃቀም፣
- ☞ ቅንጅታዊ አሰራር ውስንነት፣
- ☞ ዝቅተኛ የሕብረተሰብ አሳታፊነት፣
- ☞ የሕብረተሰብ እሴት መሸርሸር

## የትኩረት መስክ፣

በስትራቴጅክ ዕቅዱ የዳኝነት እና ፍትሕ ተቋማት ተልዕኮዎቻቸውን በተናጠል እና በቅንጅት ሲፈፅሙ ትኩረት ሊሰጡባቸው የሚገቡ ሶስት (3) ዋና ዋና የትኩረት መስኮች እንደሚከተለዉ ተለይተዋል፡፡

### ☞ የሕግ የበላይነት እና የዳኝነት ነጻነት፣

የህግ የበላይነትና ተገዢነት ችግሮች የክልሉ ሰላም እና ዕድገት ቁልፍና አሁናዊ ማነቆዎች ናቸዉ፡፡ የክልሉ ህዝብ ትልቅ እሴት እና መገለጫ የሆነዉ የሕግ ተገዥነት ባሕል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ ይገኛል፡፡ ችግሩ በግለሰቦች፣ በመንግስት አካላት እንዲሁም በዕምነትና ባህላዊ ተቋማት በስፋት ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ የዳኝነት ነፃነትን ማለትም ፍርድ ቤቶች በራሳቸዉ የውስጥ ጉዳይ (ለምሳሌ፡- የሰዉ ሃይልና በጀት) የመወሰን፣ ዳኞች በቀረበላቸዉ ጉዳይ ላይ ያለ ተፅዕኖ ዉሳኔ የመስጠት እና የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መከበር ላይ ሰፊ ዉስንነቶች ይስተዋላሉ፡፡ ከላይ በሁኔታ ትንተናዉ እንደተገለፀዉ ነፃነቱ የተጠበቀ፣ ገለልተኛ እና ተጠያቂነት የተረጋገጠበት ጠንካራ የዳኝነት አካል መኖር በሶስቱ የመንግስት አካላት ሊኖር የሚገባዉን የሥልጣን ክፍፍል እና ዴሞክራሲያዊ አሰራር ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ለህግ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ተወዳዳሪ አኮኖሚ ለመገንባት እጅግ አስፈላጊ ሁኔታ ነዉ፡፡ ከሙያዊ እና ተቋማዊ ነፃነት ጋር የተያያዙ ችግሮች ከፍርድ ቤቶችና ዳኞች በተጨማሪ በሌሎች የፍትህ ተቋማትና ባለሙያዎች ዘንድ (ለምሳሌ፡- አቃብያን ህግና ፖሊስ) በስፋት የሚስተዋሉ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል እንደነፃነትና ገለልተኝነት ሁሉ ለዳኝነትና ፍትህ ዘርፉ አስፈላጊ የሆነዉ እና ዉስንነቶች የሚስተዋሉበት ጉዳይ የተጠያቂነት ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዳኝነትና ፍትህ ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመሰረታዊነት መፍታት እና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚቻለዉ በዘርፉ ያለዉን ተቋማዊ ቁመና ማሻሻል ሲቻል ነዉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የተሟላ ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነት ማረጋገጥ እና ህብረተሰቡ በፍትህ ስርአቱ ላይ ያለዉን አመኔታ ማሳደግ ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነዉ፡፡

በመሆኑም በክልሉ ፍትሐዊ እና ተገማች የህግ አወጣጥ ስርዓትን በማረጋገጥ፣ የዳኝነት ነፃነት እና ገለልተኝነትን ማረጋገጥ፣ የወንጀል መከላከል እና የህዝብ ደህንነት ስራዎችን በማጠናከር እና የወንጀል፣ የፍትሐብሄር እና የአስተዳደር ፍትሕ አስተዳደር ውጤታማነትን በማሳደግ ሕግ እንደ ቀጪ እና የሚፈራ ብቻ ሳይሆን እንደ ጠቃሚ ባሕልና ስርዓት እንዲወሰድ በማድረግ የህግ የበላይነትንና የዳኝነት ነፃነት የክልሉ የኢኮኖሚ እድገት እና ማህበራዊ ለዉጥ መሰረት እንዲሆኑ ማድረግ የስትራቴጅክ ዕቅዱ ዋነኛ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

### ☞ የላቀ ፍትሕ አገልግሎት

ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ፍትሕን በእኩልነት እና በምቹ ሁኔታ ማግኘት የሚችሉት በዳኝነትና ፍትህ ዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በአግባቡ መለየትና አስቻይ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ሲቻል ነዉ፡፡ ከላይ በሁኔታ ትንተናዉ እንደተገለፀዉ በክልሉ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን

(ማለትም ቅልጥፍና፣ ጥራት፣ ተደራሽነት፣ ግልጽነት፣ ፍትሃዊነት ወዘተ) ዙሪያ ከሚስተዋለዉ ሰፊ ክፍተት አንፃር የዘርፉ ተቋማት ተቋማዊ አሰራራቸዉን በማሻሻል፣ ለህግና ስነምግባር ደንቦች በመገዛት እና ቅንጅታዊ አሰራርን ባህል በማድረግ የህብረተሰቡን እርካታና አመኔታ በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ ሊሰሩ ይገባል፡፡ በዚህ ዙሪያ በዘርፉ ተቋማት ከሚስተዋሉ ችግሮች በመነሳት የዘርፉን የሰው ሐብት ልማት እና ተቋማዊ አቅም ግንባታ በማሻሻል፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሳደግ፣ ተቋማትን በቅንጅታዊ አሰራር በማስተሳሰር፣ በዘርፉ ሙስናን መከላከል እና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ ለጠቋሚዎች፣ ተጎጂዎች እና ምስክሮች የሚሰጠዉን ጥበቃ በማሻሻል፣ እና የፍርደኞችን ማረም፣ ማነፅ እና መልሶ መቀላቀል ተግባራትን አፈፃፀም በማሻሻል በክልሉ የላቀ ፍትሕ አገልግሎት ማረጋገጥ ሁለተኛ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

☞ **የፍትሕ ተደራሽነት እና ሰብአዊ መብት፣**

የፍትሕ ተደራሽነት ህብረተሰቡ ህጎችን በቀላሉ የሚያገኝበትና የሚረዳበትን፣ አከራካሪ ጉዳዮች ሲገጥሙት በህግ ባለሙያ የሚታገዝበትን እና የዳኝነትና ፍትህ ተቋማትን በቅርቡና በቀላሉ የሚያገኝበትን ሁኔታ የሚያጠቃልል ቁልፍ የዘርፉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ሌላዉና ትኩረት የሚሻዉ ጉዳይ የፍትህ ስርዓቱን ሰዉና ሰብዓዊነት ተኮር የማድረግና ህገ መንግስቱን እና አገሪቱ የፈረመቻቸዉን ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች መሰረት በማድረግ ሰብአዊ መብትን የማሳዎቅ፣ የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ተግባር ነዉ፡፡ በክልሉ የፍትህ ተደራሽነት እና ሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ሁሉን አቀፍ የህግ አገልግሎትን ማሻሻል እና አማራጭ የፍትሕ እርምጃዎችን ማጠናከር አስፈላጊ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ ከተለመዱት የዘርፉ ተቋማት በተጨማሪ በጠበቆች፣ ነገረፈጆችና ሌሎች አካላት የሚሰጠዉን የህግ አገልግሎት በማሻሻል ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች እና ጥራት ያለዉ የዳኝነትና ፍትሕ አገልግሎት ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የዳኝነትና ፍትህ ተቋማቱ በመንግስት የሚቋቋሙና የሚደራጁ ይሁን እንጂ የተቋማቱ አገልግሎት ዋና ተጠቃሚ ህብረተሰቡ ነዉ፡፡ በአንድ በኩል ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ እና እየተወሳሰበ ከመጣዉ የፍትህ ፍላጎት አንፃር በሌላ በኩል የክልሉ ህዝብ ካለዉ የዳበረ የህግና የፍትህ ልምምድ አንፃር በዘርፉ የህብረተሰቡን ቀጥተኛ ተሳትፎና ድጋፍ ማረጋገጥ እና የዳኝነትና ፍትህ ስርዓቱን ሰዉ እና ሰብዓዊነት ተኮር ማድረግ ልዩ ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የዳኝነትና ፍትሕ ስርዓቱ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የሚገነባ፣ የህብረተሰብ መሰረት ያለዉ፣ ሰዉ ተኮር እና ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና መጠበቅ የሚተጋ ማድረግ ሶስተኛዉ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## 29.6. የስትራቴጅክ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ግቦችና ተግባራት

### 29.6.1. የስትራቴጅያዊ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

የትኩረት መስኮችን መነሻ በማድረግ የዳኝነት እና ፍትሕ ዘርፍ ዕቅድ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፡፡

**የትኩረት መስክ አንድ፡ የሕግ የበላይነት እና የዳኝነት ነጻነት፣**

☞ ፍትሐዊ እና ተገማች የህግ አወጣጥ ስርዓት ማረጋገጥ፣
☞ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
☞ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ዉጤታማነት ማረጋገጥ፣
☞ የፍትሐብሄር ፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ዉጤታማነት ማረጋገጥ፣
☞ የአስተዳደር ፍትሕ ስርዓት ዉጤታማነት ማረጋገጥ፣

**የትኩረት መስክ ሁለት፡ የላቀ ፍትሕ አገልግሎት**

☞ የአገልግሎት ቅልጥፍና እና ጥራት በማሻሻል የተገልጋይ እርካታን በዘላቂነት ማሳደግ፣
☞ ውጤታማ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣
☞ ተቋማዊ አቅም ግንባታ እና የሰው ሐብት ልማት ማጠናከር፣
☞ ቅንጅታዊ አሰራር ማሳደግ፣

- ☞ ለተጎጂዎች፣ ጠቋሚዎች  እና ምስክሮች የሚደረግ ጥበቃን ማጠናከር፣
- ☞ ፍርደኞችን የማረም፣ ማነፅ እና መልሶ መቀላቀል ስራዎችን  ማጠናከር፣
- ☞ ስነ-ምግባርን መገንባት፣ሙስናን መከላከል እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

**የትኩረት መስክ ሦስት፡ የፍትሕ ተደራሽነት እና ሰብአዊ መብት፣**

- ☞ የሕግ አገልግሎት ውጤታማነት ማረጋገጥ፣
- ☞ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና የሕግ ግንዛቤ ማረጋገጥ፣
- ☞ ብዝሃ-ሕግ እና አማራጭ ፍትሕ ስርዓቶችን ማጠናከር፣
- ☞ ሰብአዊ መብትን የማሳዎቅ፣ ማክበር፣ማስከበር እና ማሟላት ስራዎችን ማጠናከር፣
- ☞ የሴቶች፣ሕፃናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

### 29.6.2. ስትራቴጅክ ግቦች እና ተግባራት፣

የዳኝነትና  እና የፍትሕ ዘርፍ ዋና ዋና ስትራቴጅክ ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ግብ አንድ፡ ፍትሐዊ እና ተገማች የህግ አወጣጥ ስርዓት ማረጋገጥ፣**

ይህ ግብ የህግ የበላይት እና ህጋዊ አሰራር መሰረት ሲሆን በስትራቴጂክ ዘመኑ በጥናት ላይ የተመሰረተ የህግ አወጣጥ ስርዓት በመተግበር፣ የህግ አወጣጥ ጥራት መለኪያ ስርዓት በማዘጋጀት፣ በክልሉ እና በፌደራል የሚወጡ ህጎችን በማጠቃለል እና ለተጠቃሚው ተደራሽ በማድረግ፣ በሕግ አወጣጥ ስርዓቱ የማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማረጋገጥ እና ተያያዥ ተግባራትን በማከናወን በክልሉ ፍትሃዊና ተገማች የህግ አወጣጥ ስርዓት እንዲኖር በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

ግብ ሁለት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

በዕቅድ ዘመኑ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኝነትን እና ተጠያቂነት ማረጋገጥ ለሕግ የበላይነትን መስፈን እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ብሎም ዜጎች እና ባለሃብቶች በፍትህ ስርዓቱ ላይ ዕምነት እንዲኖራቸዉ ለማድረግ ካለዉ ልዩ ሚና አንፃር ልዩ ትኩረት የሚሰጠዉ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ህገ-መንግስቱን፣ ሌሎች ህጎችን እና አለማቀፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ የበጀት እና የሰው ኃብት አስተዳዳር ነፃነትን ጨምሮ የፍርድ ቤቶችን ተቋማዊ ነጻነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች እና የአሰራር ስርዓት በማጠናከር፣ የዳኞችንና ፍርድ ቤት ባለሙያዎችን ግለሰባዊ እና ውስጣዊ የሙያ ነጻነት የሚያረጋግጡ የህግ እና አሰራር ስርአቶችን በማሳደግ እና ከአድሎአዊ እና ወገንተኝነት የፀዳ የዳኝነት አገልግሎት ለማስፈን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በማጠናከር፣ የፍርድ ቤቶችን፣ የዳኞችን፣ የጉባኤ ተሿሚ እና የአስተዳደር ሰራተኞችን ተጠያቂነት የሚያረጋግጡ የሕግ ማዕቀፎች እና አሰራሮችን በማሻሻል እና ተያያዥ ተግባራትን በማጠናከር የተሟላ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን  በክልሉ ስርዓታዊ የማድረግ ስራ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

**ግብ ሶስት፡ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ዉጤታማነት ማረጋገጥ፣**

የወንጀል ፍትህ አስተዳዳር ሰፊ የወንጀል መከላከል፣ የወንጀል ምርመራ፣ የክስ ዝግጅት እና የፍርድ ቤት ክርክር ተግባራትን የያዘ ልዩ የአሰራር ስርዓት፣ የመረጃ አያያዝ፣ የቴክኖሎጂ እገዛ፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና የብዙ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚጠይቅ ለህግ የበላይነት፣ ሰላምና ዕድገት መሰረት የሆነ የፍትህ ዘርፍ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል በዘርፉ የሚከናወኑ ተግባራት የተጠርጣሪን፣ ተከሳሽን፣ የወንጀል ተጎጅዎችን፣ ምስክሮችን፣ ጠቋሚዎችን እና ሌሎችን አካላት ሰብዓዊ መብቶች ያከበሩ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ወጥ፣ የተሟላ እና ከዓለማቀፍ መለኪያዎች ጋር የተጣጣመ ስርዓት መንባት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በስትራቴጅክ ዕቅዱ ክልል አቀፍ የወንጀል መከላከል ስትራቴጅ በማዘጋጀት፣ ማሕበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ስትራቴጅ በማሻሻል እና በመተግበር፣ ውጤታማ የመንገድ ትራፊክ አደጋን መከላከል ስርዓት በመዘርጋት፣ በወንጀል መከላከል የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማረጋገጥ፣ መረጃ መር የቅድመ ወንጀል መከላከል አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ወንጀል መከላከልን ዓላማ ያደረግ የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት የወንጀል ህግ አፈጻጸም ውጤታማነትን በማሳደግ፣ የወንጀል መንስኤ እና ተጋላጭነትን በጥናት በመለየት የመከላከያ አማራጮችን በመተግበር፣

በቴክኖሎጅ የታገዘ የወንጀል መከላከል ስልት ተግባራዊ በማድረግ እና ወንጀል-ጠል ትውልድ ለመፍጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ዉጤታማ የወንጀል መከላከል እና የህዝብ ደህንነት ማረጋገጥ ስራዎች በልዩ ትኩረት የሚሰሩ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ ዉጤታማ የወንጀል ምርመራ እና የዐቃቤ-ሕግ አገልግሎትን (የወንጀል ክስና ክርክርን) ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማለትም ተግባራት የዳኝነትና ፍትህ ዘርፉ ተቋማትን የተናጠልና ቅንጅታዊ ትኩረት የሚጠይቁ ይሆናል፡፡ በተለይም የወንጀል ምርምራ እና የዓቃቤ ሕግ ዘርፎች ሙያዊ እና ተቋማዊ ነፃነት የሚያረጋግጡ የአደረጃጀት እና አሰራር ስርዓቶች መፍጠር፣ የወንጀል ጥቆማ እና ምርመራ የሚመራበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣ ፎረንሲክ እና ቴክኖሎጂ መር የወንጀል ምርምራ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ ውስብስብ እና ከባድ ወንጀሎችን ለማጣራት የሚያስችሉ ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ ከፍተኛ የሕዝብ እና የመንግስት ጥቅም ያለባቸውን የወንጀል ጉዳዩች ቅድሚያ እና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራበት የምርመራ ስርዓት መዘርጋት፣ የወንጀል ምርመራ ጥራት እና አቅም መለኪያ ስርዓት መዘርጋት፣ መረጃ መር እና ቅድመ-ገቢር የወንጀል ምርመራ ጥበብ መከተል፣ የወንጀል እና ወንጀለኛ መረጃ ምዝገባ ስርዓት መዘርጋት፣ የመዝገብ ውሳኔ፣ ክስ፣ ክርክር ጥራትን እንዲሁም የማስቀጣት አቅምን ማሳደግ፣ የንብረት ማስመለስ አደረጃጀት እና የአሰራር ስርዓትን ማሳደግ፣ የኤግዚቢት አስተዳደር እና አወሳሰን ስርዓት መዘርጋት፣ የቅጣት የአፈጻጸም እና ክትትል ስርዓት መቅረጽ እና መተግባር፣ እና የተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ እና ምስክር አቀራረብ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊነቱን በውጤታማነት መምራት ዉጤታማ የወንጀል ምርመራ፣ ክስና ክርክርን ለማድረግ ቁልፍ ተግባራት ተብለዉ ተለይተዋል፡፡

**ግብ አራት፡ የፍትሐብሄር ፍትሕ አስተዳደር ስርዓት ዉጤታማነት ማረጋገጥ፣**

በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ በክልሉ ዉጤታማ የፍትሐብሄር ፍትሕ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር የክልሉን ህዝብና መንግስት ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት ተለይተዉ የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ በዚህም ክልላዊ የፍትሐብሄር ፍትሕ ስትራቴጅ ማዘጋጀት እና መተግበር፣ የክልሉን ሕዝብ እና መንግስት ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮችን በመለየት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መተግበር፣ ጥራት ያለው የውል ሰነድ ዝግጅት፣ ረቂቅ ውል ምርመራ፣ ምክር አገልግሎት የሚሰጥበትን አሰራር ማሻሻል፣ የውል አስተዳደር እና አፈጻጸም ሂደትን መከታተል እና በውጤታማነት መምራት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፣ የሰነዶች፣ ጠበቆች እና ሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባ እና ማረጋገጥ አደረጃጀትን ማሳደግ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የፍርድ አፈጻጸም ውጤታማነትን የሚያረጋግጥ የአደረጃጀት እና አሰራር ስርአት መዘርጋት እና መተግበር፣ ዓቃቤ ሕግ በፍትሐብሄር ጉዳዮች ላይ የሚኖረውን ተግባር እና ኃላፊነት በተመለከተ በጥናት ላይ ተመስርቶ አሰራር ማሻሻል፣ እና ከገጠር እና ከተማ መሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክር መንስኤዎችን በጥናት ለይቶ ልዩ መፍትሔ የሚሰጥ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ የሚሉት የዕቅድ ዘመኑ ቁልፍ ተግባራት ተደርገዉ ተለይተዋል፡፡

**ግብ አምስት፡ የአስተዳደር ፍትሕ ስርዓት ዉጤታማነት ማረጋገጥ፣**

የአስተዳደር ፍትሕ ጉዳይ በክልሉም ሆነ በአገር ደረጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልዩ ትኩረት እየተቸረዉ የመጣ ዘርፍ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ በክልሉ የሚገኙ የአስተዳደር አካላት መመሪያ ሲያወጡም ሆነ አስተዳደራዊ ውሳኔን ሲወስኑ ሊከተሏቸዉ ስለሚገባ ስነ-ስርዓታቶች እና ከዚህ ዉጭ ተደርገዉ ሲገኙ ደግሞ ስለሚኖረዉ የተጠያቂነትና ማስተካከያ ስርዓት በተመለከተ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በክልሉ የአስተዳደር ፍትሕን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስራዎች ማለትም የአስተዳደር ፍትሕ ስርዓትን የማስተዋወቅ እና የማስረፅ ተግባራትን የመፈፀም፣ የአስተዳደር ፍትሕ ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚያስችል መዋቅር የመዘርጋት፣ መመሪያዎችን በዘላቂነት የመመርመር እና የመመዝገብ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት፣ የአስተዳደር መመሪያዎች እና ውሳኔዎች የፍርድ ቤት ክለሳ ስርዓትን የማጠናከር፣ በክልሉ አጠቃላይ የህጎችን ተፈጻሚነት የመከታተል፣ የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ስራቸውን በሕግ አግባብ መስራታቸውን የሕግ ተፈፃሚነት ኦዲት ማድረግ እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ፣ ቴክኖሎጅ መር የመመሪያዎች ተደራሽነት አፈጻጸም መኖሩን የመከታተል፣ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶችን (administrative tribunals) ማጠናከር እና በጥናት ላይ ተመስርቶ የማቋቋም እና ተያያዥ ስራዎችን የመለየትና የማከናወን ተግባራት የዕቅድ ዘመኑ ቁልፍ ተግባራት ተደርገዉ ተለይተዋል፡፡

**ግብ ስድስት፡ የአገልግሎት ቅልጥፍና እና ጥራት በማሻሻል የተገልጋይ እርካታን በዘላቂነት ማሳደግ፣**

ይህ ግብ በዘርፉ ተቋማት የሚስተዋለዉን የአገልግሎት ቅልጥፍና፣ጥራት እና ውጤታማነት ችግር በመሰረታዊነት የመፍታት እና የተገልጋይ እርካታን የማሳደግ ዓላማ የያዘ ሲሆን በጥናት ላይ በመመስረት የዳኝነትና ፍትህ ስርዓት ዉጤታማነትን አዳጊ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት፣ ዝርዝር የአገልግሎት መለኪያዎችን በመቅረፅና ተግባራዊ በማድረግ፣ የአገልግሎት ቅልጥፍና መለኪያ ስርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ፣ የአገልግሎት ጥራት መመዘኛ ስርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ፣ የተገልጋዮች እርካታ መለኪያ ስርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳዳር ስርዓት በመዘርጋት እና ውጤታማነቱን በማረጋገጥ እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን በማከናወን ግቡን ለማሳካት ይሰራል፡፡

## ግብ ሰባት፡ ውጤታማ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

ውጤታማ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ጉዳይ የዘርፉን ተቋማት የተናጠልና የጋራ እንቅስቃሴዎች ለማዘመንና የፍትህ አቅርቦትን ለማሳደግ ቁልፍ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህን ግብ ዳር ለማድረስ የቴክኖሎጅ መሰረተ-ልማት ዝርጋታን የማሟላት፣ ጠንካራ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ አደረጃጀት እና አሰራር ስርዓት የመፍጠር፣ የቴክኖሎጅ አተገባበር የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ የማዘጋጀት እና የመተግበር፣ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሳለጥ አስፈላጊ የሆኑና ዘመኑ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች የመለየት፣ የማበልፀግ፣ የማስፋት እና የመጠቀም እንዲሁም ኤሌክትሮኒክ ሕግ እና ፍትህ (e-Legislation and e-Justice) ተግባራዊ የማድረግ ተግባራትን ጥናትን መሰረት ያደረጉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

## ግብ ስምንት፡ ተቋማዊ አቅም ግንባታ እና የሰው ሐብት ልማት ማጠናከር፣

በዘርፉ ለሚስተዋለዉ የፍትህ ክፍተት እና የአገልግሎት አሰጣጥ አንዱና ዋንኛዉ ምክንያት ከተቋማዊ አቅም ግንባታ እና ሰው ሐብት ልማት ጋር የተያያዙ ዉስንነቶች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ የተቋማትን አደረጃጀት እና አሰራር በጥናት ላይ ተመስርቶ የማሻሻል፣ ከተቋማዊ መዋቅርና ስራ ስፋት ጋር የተመጣጠነ የሰው ሀብት አቅርቦት የማሟላት፣ በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮች አቅማቸውን ለማሳደግ የአጫጭርና ረጂም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና የመስጠት፣ለባለሙያዎችና ሰራተኞች (ፈጻሚ አካላት) የመፈጸም አቅማቸውን የማጎልበት፣ የተቋማት አመራሮች እና ሰራተኞችን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ እና የስራ ተነሳሽነትን የሚያሳድጉ አሰራሮችን በጥናት ለይቶ ተግባራዊ የማድረግ፣ ለተቋማት ተልዕኮ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማት እና የሎጅስቲክ አቅሞችን የማሳደግ፣ እንደየተቋማቱ ልዩ ባህሪ በተፈቀዱ ዘርፎች ገቢ ማመንጨት የሚስችል ስርዓት በመዘርጋት የመተግበር፣ በዘርፉ የሴት አመራር እና ባለሙያዎችን ብቃት እና ተሳትፎ የማሳደግ፣ ብቃት ያላቸው ተተኪ አመራሮችን ለማፍራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የመተግበር እና ተያያዥ ተግባራት በልዩ ትኩረት ይሰራሉ፡፡ ለዚህ ግብ መሳካት በዘርፉ የሚገነዉን አቅም አሟጦ ለመጠቀም የህግና ፍትህ ኢንስቲትዩት፣ ፖሊስ ኮሌጅ እና ሌሎች ጥራት ያላቸው እና ተወዳዳሪ የሆኑ የትምህርት፣ ስልጠና እና ምርምር ልህቀት ማዕከላትን የማጠናከርና የማደራጀት ተግባራት ጥናትን መሰረት በማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

## ግብ ዘጠኝ፡ ቅንጅታዊ አሰራር ማሳደግ፣

የዳኝነትና ፍትሕ አገልግሎት በአንድ ተቋም ተጀምሮ በዚያዉ የሚያልቅ ሳይሆን ሁሉን ተቋማት የሚያሳትፍ እና የአንዱ የሥራ ዉጤት ለሌላዉ ግብዓት የሚሆን በመሆኑ የዘርፉ ተቋማት ትብብር እና ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር አማራጭ የማይሰጥ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ በዘርፉ የተጀመረዉን የዳኝነትና የፍትህ አካላት የትብብር መድረክ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ የሚያደርጉ (የአደረጃት፣ አሰራር፣ የሕግ እና ስትራቴጅ) ማሻሻያዎችን በጋራ በመቅረጽ ተግባራዊ የማድረግ፣ (የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ) ዕቅዶችን ጥናትን መሰረት ባደረገ መልኩ በጋራ በመቅረጽና ተግባራዊ የማድረግ፣ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ የጋራ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የማከናወን፣ የጋራ ፕሮጀክቶች መቅረጽና ተግባራዊ በማድረግ፣ ተናባቢ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት የመዘርጋት፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች (priority prosecution) የጋራ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባዊ የማድረግ፣ የተከሳሽና ምስክር አቀራረብ ሥርዓት የመዘርጋት፣ ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት

አሰጣጥን በተመለከተ ተናባቢ የሆኑ የጋራ ማሻሻዎችን በመቅረጽ ተግባዊ የማድረግ፣ የዳኝነት እና ፍትሕ አካላት የትብብር መድረክ ጽ/ቤትን የማጠናከር፣ ከፌደራል እና ከአጎራባች ክልሎች የፍትህ አካላት ጋር የአጋርነት ግንኙነት የሚያጠናክር ስርዓት ዘርግቶ የመተግበር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር እና አጋርነትን የማጠናከር፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ የጋራ የመረጃ ማዕከል የማደራጀት፣ በክልሉ አጠቃላይ የፍትህ መለኪያ ስርዓት መዘርጋት እና ተናባቢ የዘርፉ ተቋማት የስራ አፈፃፀም መለኪያ አመላካቾችን የመቅረፅ እና የመተግበር እና የዳኝነት እና ፍትሕ ተቋማቱ የተቀናጀ ቴክኖሎጅ ተጠቃሚነት እና የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓትን የመዘርጋትና የመተግበር ስራዎችን በማከናወን ቅንጅታዊ አሰራር የማሳደግ እና ቀልጣፋና ጥራት ያለው የፍትህ አገልግሎትን በክልሉ የማረጋገጥ ስራ ቁልፍ ተግባራት ተደርገዉ ተለይተዋል፡፡

## ግብ አስር፡ ለተጎጂዎች፣ ጠቋሚዎች እና ምስክሮች የሚደረግ ጥበቃን ማጠናከር፣

ለምስክሮች፣ ጠቋሚዎች እና ተጎጂዎች የሚደረግ ድጋፍ እና ጥበቃ የህግ የበላይነትን ለማስፈን እና የወንጀል ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያለዉ ሚና ከፍተኛ ሲሆን የዘመናዊ የወንጀል ፍትህ አስተዳዳር መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ ለምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃና ድጋፉ የሚያሳልጥ የሕግ ማዕቀፍ እና አሰራር በመቅረፅ እና ተግባራዊ በማድረግ፣ ተጎጅዎችን ማዕከል ያደረገ የፍትሕ ስርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ አሰራሮችን ቀርጾ ተግባራዊ በማድረግ፣የተጎጂ ፈንድ ማቋቋም እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ እና የተጎጅዎች የካሳ አሰራር ስርዓት በመቅረፅና በመተግበር የዳኝነት ስርዓቱን የማጠናከርና ሰዉ ተኮር የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

## ግብ አስራ አንድ፡ ፍርደኞችን የማረም፣ ማነፅ እና መልሶ መቀላቀል ስራዎችን ማጠናከር፣

ማረሚያ ቤቶችን እንደስማቸው ትክክለኛ የማስተማሪያ እና የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ የመጨረሻ ፍሬ የሚታይባቸዉ ተቋማት መሆናቸዉን ለማረጋገጥ በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን መቅረፍ እና አሰራሮችን ከሕገ መንግሥቱ፣ ሌሎች ህጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንፃር መቃኘት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ የማረም፣ ማነጽ እና መልሶ ማቋቋም ተግባራት የሚመሩበትን የሕግ ማዕቀፍ፣ ስትራቴጅ እና አሰራር ስርዓት የመቅረፅ እና ተግባራዊ የማድረግ፤ በማረም፣ ማነፅ እና መልሶ ማቋቋም ሂደት የማህበረሰብ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ስርዓት የመዘርጋት፤ ደጋጋሚ ወንጀለኝነትን መቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የማዘጋጀት እና የመተግበር፤ ወጣት፣ ሴት እና ህጻናት የያዙ ወላጅ ታራሚዎችን በተመለከተ ልዩ አሰራር የመዘርጋት እና የመተግበር፤ የምህረት፣ ይቅርታ እና አመክሮ አሰራር ስርዓትን የመቅረፅ እና የማሻሻል፤ የአማራጭ ቅጣት ማስፈጸሚያ አደረጃጀት እና የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት እና የመተግበር እና ተያያዥ ተግባራት የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡

## ግብ አስራ ሁለት፡ ስነ-ምግባርን መገንባት፣ሙስናን መከላከል እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

በዕቅድ ዘመኑ የዳኝነትና ፍትህ ዘርፉ አሰራር የሚጠይቀዉን ስነ-ምግባር እሴቶችን በዘላቂነት የሚያሳድጉ የሕግ እና አሰራር ስርዓቶችን ለማጠናከር ብሎም ጥሰት ሲከሰት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት ጥናትን መሰረት በማድረግ ይፈጠራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከዘርፉ ተጋላጭነት አንፃር ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ብሎም ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የሕግ፣ ስትራቴጅ እና አሰራር ስርዓቶችን የመቅረፅ እና የመተግበር ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪም ዳኞች፣ አቃብያን ህግ እና ሌሎች በህግ የተፈቀደላቸዉ የዘርፉ ባለሙያዎች የሚሰባሰቡበት እና የሙያ ደረጃዎችን የሚያስጠብቁባቸዉ ማህበራትን የማጠናከር ስራ ከግቡ ዓላማ አንፃር በትኩረት ይሰራል፡፡

## ግብ አሥራ ሶስት፡ የሕግ አገልግሎት ውጤታማነት ማረጋገጥ፣

የሕግ አገልግሎት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎች በክልሉ የህግ የበላይነትን ለማስፈንና ፍትህ ተደራሽ ለማድረግ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም በክልሉ የሕግ አገልግሎት የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት የመቅረጽ እና የመተግበር፣ለጠበቆች እና ሌሎች በህግ አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች ተከታታይነት እና አስገዳጅነት ያለዉ የሙያ ስልጠና እና ምዘና ስርዓት የመዘርጋትና የመተግበር፣ የክልሉን መንግስት እና ተቋማት የህግ አገልግሎት ዉጤታማ በሚያደርግ መልኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ የማሻሻል እና የማጠናከር፣ ጥራት ያለው የተከላካይ ጠበቆች አገልግሎት በመስጠት ለአገልግሎት ፈላጊዎች ነጻ

የህግ ድጋፍ ሽፋን በተሟላ አግባብ የመስጠት፣ የነጻ የህግ አገልግሎት ሽፋን፣ ጥራት እና ውጤታማነት በዘላቂነት የማረጋገጥ፣ የጠበቆች ስነ-ምግባር እና የአገልግሎት ጥራት እና ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያሥችል ጥብቅ እና ዘላቂ የቁጥጥር ስርዓት የመዘርጋት እና የመተግበር፣ በክልሉ የጠበቆች ማህበርን እና የጥብቅና ድርጅቶችን የማጠናከር፣ የጥብቅና አገልግሎት የጋራ አስተዳዳር ስርዓትን የመዘርጋት እና የመተግበር፣ በሂደት የጠበቆች ማህበር ራሱን የሚችልበትን ስርዓት ተግባራዊ የማድረግ፣ የተቋማት የሕግ ባለሙያዎች የሕግ አገልሎትን በውጤታማነት መተግበራቸውን በተመለከተ የጥራት መለኪያ መስፈርት በማውጣት የመለካት፣ በጥናት ላይ በመመስረት የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት እና አሰራር የመወሰን እና ተያያዥ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

**ግብ አሥራ አራት፡ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና የሕግ ግንዛቤ ማረጋገጥ፣**

የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማረጋገጥ እና የህዝቡን የሕግ ግንዛቤ ማሳደግ ለዳኝነትና ፍትህ ስርዓቱ ዉጤታማነት ለማሻሻል እና የሕዝብ አመኔታ እና ቅቡልነት ለማሳደግ ቁልፍ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህን ግብ ዳር የሚያደርሱ የወንጀል መከላከልና የንቃተ ህግ ትምህርቶችን ጥራትና ሽፋን የማሳደግ፣ የምክክር መድረኮችንና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ የህብረተሰቡን ተሳትፎ የማሳደግ፣ ተገልጋይ፣ ባለድርሻ እና አጋር አካላት በፍትህ ስርዓቱ ላይ ያላቸውን ትብብር እና ተሳትፎ የማጠናከር፣ የዳኝነትና የፍትህ አካላት የተግባቦት ስትራቴጂ በመቅረፅ ተግባራዊ የማድረግ እና ተያያዥ ተግባራት በልዩ ትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

**ግብ አስራ አምስት፡ ብዝሃ-ሕግ እና አማራጭ ፍትሕ ስርዓቶችን ማጠናከር፣**

በሁኔታ ትንተናዉ በግልፅ እንደተመላከተዉ በዘርፉ ተቋማት የሚስተዋለዉን የፍትህ ክፍተት በመሰረታዊነት ለመፍታት የክልሉን ህዝን የረጅም ጊዜ የልምምድ እና የፍህት መስጫ አማራጮች አሟጦ መጠቀም ይገባል፡፡ በመሆኑም ብዝሃ-ሕግ እና አማራጭ ፍትሕ መስጫ ስርዓት የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት በመቅረጽና በመተግበር፣ መሰረተ-ማህበረሰብ ፍትሕ ሰጭ ማዕከላትን በጥናት በመለየት፣ በመደገፍና በማጠናከር፣ የክልሉ የባህል ፍርድ ቤቶችን በዘላቂነት ለማጠናከር የሚስችል የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር፣ በክልሉ የሐይማኖት ፍርድ ቤቶችን በመደገፍ፣ ዘመናዊ አማራጭ አለመግባባት መፍቻ ማዕከላትን በጥናት በመለየት፣ በመደገፍ እና በማጠናከር፣ ጠንካራ የግልግል ዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በመገንባት ክልሉን የግልግል ዳኝነት ማዕከል (arbitration hub) በማድረግ፣ አማራጭ የቅጣት እና ጠባይ ማረሚያ ማዕከላትን በማቋቋም እና በመደገፍ፣ በክልሉ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ስርዓትን በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተያዘው አቅጣጫ መሰረት በመተግበር እና ተያያዥ ተግባራትን በማከናወን በክልሉ ብዝሃ-ሕግ እና አማራጭ ፍትሕ መስጫ ስርዓቶችን የማጠናከር በልዩ ትኩረት ይሰራል፡፡

**ግብ አስራ ስድስት፡ ሰብአዊ መብትን ማሳዎቅ፣ ማክበር፣ማስከበር እና ማሟላት፣**

ሰብአዊ መብቶች ሰዎች ሁሉ ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ ያገኟቸው የመረ የመንግስት-ዜጎች ግንኙነት እና የዜጎችን የኑሮ ጥራት መሻሻል ሁነኛ መገለጫዎች ናቸዉ፡፡ ከዚህ አንፃር በዕቅድ ዘመኑ በክልሉ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ የእያንዳንዱ ተቋማት ተግባር እንዲሆኑ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመቅረጽ፣ የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርሃ-ግብር አፈጻጸም እና የማስተባበር አቅምን በማሳደግ፣ በወንጀል መከላከል፣ ምርመራ፣ ክርክር፣ ማረም እና ማነፅ ሂደት ሰብአዊ መብቶች መለኪያዎች መከበራቸውን በመከታተል እና እርምት በማድረግ፣ በፖሊስ የሚፈፀምን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ጥቆማ የሚቀበልና የሚመረምር ራሱን የቻለ የስራ ክፍል ማደራጀትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር፣ የሃይል አጠቃቀም መርሆዎች መለኪያ ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር፣ የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ መስጫ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና በመተግበር እና ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር እና ለማሟላት አስፈላጊ መለኪያዎችን መሰረት አድርጎ በመተግበር በክልሉ የሚስተዋለዉን የአስተዳዳርና የልማት ተግባራት ሰዉ ተኮር እና ሰብዓዊነትን ያከበሩ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

**ግብ አስራ ሰባት፡ የሴቶች፣ሕፃናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣**

የዳኝነትና የፍትህ ዘርፉ ተቋማት ተጋላጭ እና ልዩ ትኩረት ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊዉን ጥበቃና ድጋፍ በማድረግ ለሌሎች ተቋማት ምሳሌ መሆን እና አሰራሮቻቸዉን ሰዉና ሰብዓዊነት ተኮር ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ በክልሉ የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጅ፣ የሕግ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት በመቅረጽ የመተግበር፣ ለሕጻናት ምቹ የፍትሕ ስርዓት የመዘርጋት እና ተግባራዊ የማድረግ እና በባሕል፣ በቋንቋ፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ላይ የተመሰረተ መድሎ የማይደረግበት የፍትሕ ስርዓት ተግባራዊ የማድረግ ተግባራት በልዩ ትኩረት የሚሰሩ ይሆናል፡፡

### 29.7. የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ የክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ስርዓት፣

### የማስፈፀሚያ ስልቶች

- ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ማስተዋወቅ፣ ማስገንዘብና የጋራ መግባባት መፍጠር፣
- ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግና ተጨማሪ ሀብት የማፈላለግ አቅጣጫ መከተል፣
- የፍትህ ተቋማትን መዋቅርና የሰው ሀይል ስምሪት የማሻሻል አቅጣጫን መከተል፣
- ስራን በውጤት በመለካት ጠንካራ ሙያተኞችን ማበረታታት እና ውስንነት ያለባቸውን በመደገፍ የማብቃት አቅጣጫ መከተል፣
- ምርጥ ተሞክሮን የመቀመርና የማስፋት አቅጣጫ መከተል፣
- ተግባራትን በህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን የታገዙ በማድረግ የፍትህ ተቋማትን ገፅታ መገንባት፣
- የተቀናጀ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት መከተል፣

### 29.8. ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና ምዘና ስርዓት፣

የ25 ዓመት የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ በየደረጃው የሚገኙ የዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎችን፣ ተገልጋዮች፣ አጋሮችና ባለድርሻ አካላት የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡

የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ ተቋማት የክልሉን 25 እና የ5 ዓመት ጥቅል ስትራቴጅክ የዕድገት ዕቅድ መነሻ በማድረግ የተናጠል የ5 ዓመትና ዓመታዊ ዕቅድ አዘጋጅተው በየደረጃው ባሉ ፈፃሚ፣ባለድርሻና አጋር አካላት ዘንድ የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጎ ወደ ስራ ይገባል፡፡

ዕቅዱ የዳኝነትና የፍትሕ ዘርፉ የጋራ እንደመሆኑ መጠን የዚህ አይነት የጋራ ጉዳዮችን ለመከታተልና ለማስተባር ኃላፊነት የተሰጠው የዘርፉ ተቋማት የበላይ አመራሮች የተሰየሙበት የዳኝት እና ፍትሕ ተቋማት የትብብር መድረክ አብይ ኮሚቴ እና የትብብር መድረኩ ጽ/ቤት የስትራቴጅክ ዕቅዱን አተገባበር በበላይነት የመምራትና የማስተባበር ሚና የሚኖራቸው ሲሆን ይህ የጋራ መዋቅር አስቀድሞ መደራጀቱ እና በሕግ ጭምር እው ቅና መሰጠቱ የስትራቴጅክ ዕቅዱ ው ጤታማነት ላይ የራሱ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል የጋራ ስትራቴጅክ ዕቅዱ እንዳለ ሆኖ ሁሉም ተቋማት ከስትራቴጅክ ዕቅዱ የተቀዳ የተናጠል የተቋም አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በየደረጃው ካሉት አመራሮች ጋር ይፈፅማሉ፡፡

ስለሆነም የጋራ ስትራቴጅክ ዕቅድ አፈጻጸም የክትትል ግምገማ ስርዓቱ በዋነኝነት በሚከተሉት ላይ በመመስረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

1. የዘርፉን የጋራ ስትራቴጅክ ዕቅድ አፈፃፀም በበላይነት የሚመራው የዳኝነትና የፍትህ አካላት የትብብር መድረክ አብይ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

2. የዘርፉ ተቋማት በየስድስት ወሩ በአመት ሁለት ጊዜ ዝርዝር የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለዳኝነትና ፍትህ አካላት የትብብር መድረክ ጽ/ቤት ይልካሉ፡፡

3. የዳኝትና የፍትሕ አካላት ትብብር መድረክ ጽ/ቤት ከዘርፉ ተቋማት የተቀበለው ን ሪፖርት በአግባቡ በማደራጀት እና በትብብር መድረኩ ቴክኒክ ኮሚቴ በማስገምገም ለዳኝነትና ፍትህ አካላት አብይ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

4. አብይ ኮሜቴው የቀረበለትን ሪፖርት በአግባቡ በመገምገምና በማጽደቅ ለክልሉ ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ እና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተልኮ በክልል ደረጃ ይገመገማል፡፡

5. ክልል ደረጃ ወይም በራሱ በአስተባባሪ ኮሚቴው በሚደረጉ ግምገማዎችና ክትትሎች ለዘርፉ የተሰጡ ግብረ መልሶችና የማስተካከያ አቅጣጫቻዎችን በዳኝነትና የፍትህ አካላት የትብብር መድረክ ጽ/ቤቱ በማደረጀት ለዘርፉ ተቋማት ያስተላልፋል፤መፈጸማቸው ንም ይከታተላል፡፡

6. የትብብር ጽ/ቤቱ እንደ አግባብነቱ የስትራቴጅክ ዕቅዱ አፈጻጸም በሕዝብ የሚገመገምበት መድረክና የአካል ምልከታን ጨምሮ ሌሎች የክትትል፣ የግምገማና ድጋፍ ስልቶች እንዲሁም የላቀ ው ጤት ላስመዘገቡ አካላት እው ቅና እና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ስርዓት በማዘጋጀት እና በአብይ ኮሚቴው በማፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

7. የዘርፉ ስትራቴጂክ ዕቅድ በትብብር መድረኩ እየተገመገመ ከሀገራዊ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ሊከለስ የሚችልበትን አቅጣጫ በመከተል ይሰራል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ የስትራቴጅክ ዕቅዱ ትግበራ ወቅትና ሂደት የእቅድ ትውውቅ እና የአፈጻጸም ግምገማ በማካሄድ፣ የሪፖርት እና ግብረ-መልስ ስርዓት በመዘርጋት፣ የመስክ ድጋፍና ክትትል በማካሄድ፣ የአጋር አካላትን ያሳተፈ የፍትህ ተቋማት የጋራ የግምገማ መድረክ በማካሄድ እንዲሁም የፍትህ ዘርፍ ተቋማት አመራሮችና አባላት በስትራቴጅክ ዕቅዱ አፈፃፀም ያመጡት ለውጥና ስኬት በትኩረት ክትትልና ግምገማ እየተደረገ በተገኘው የአፈፃፀም ስኬት ውስጥ እያንዳንዱ አመራር እና ፈፃሚው የተጫወተው ሚና እየተመዘገበና አስፈለጊው የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሠላሳ

# ባሕል፣ እሴቶች እና ወጎች ለልማት

## የዘርፉ ሚና

1. የአማራ ክልል ዓይነተ ብዙ የታሪክ፣ የባህልና እሴት ሀብት ያለው ሲሆን ዘርፉ የክልሉን ባህልና እሴቶች የማጠናት፣ መልካም የባህል ገፅታውን የማዳበር፣ በክልሉ ውስጥ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና መጤ ባህሎች እንዲወገዱና ጠቃሚ የባህል እሴቶች እንዲስፋፉ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የመስራት፣ በክልሉ ውስጥ የባህልና እሴት ቡድኖችና የኪነ-ጥበብም ሆነ የእደ-ጥበብ ክበባት እንዲደራጁና በባህል ኢንዱስትሪ ልማት ገብተው በንቃት እንዲሳተፉ ማነሳሳትና የማበረታታት፣ በክልሉ ውስጥ የባህልና እሴት ተቋማት እንዲስፋፉ የማድረግ፣ በዘርፉ ለሚሰማሩ ወገኖች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የመስጠት፣ በክልሉ ውስጥ የሚኖሩት ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ታሪክ፣ ባህል እና እሴት በሚገባ ተመዝግቦ እንዲያዝና እንዲጠና፣ ቋንቋዎቻቸውም እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ የማድረግ ሚና አለው፡፡

2. እነዚህ ባህሎች፣ እሴቶችና ልምዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱ በማድረግ በክልሉ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው አስተዋፅኦ በማድረግ በኩል የዘርፉ ሚና የጎላ አስተዋፅኦ አለው፡፡ እንዲሁም ግበረ-ገባዊ ዕሴቶችንና ባህልን በመፍጠር ወይም በመቅረፅና በማሳደግ፣ በማክበርና በማስከበር፣ በማወቅና በማሳወቅ፣ በመቀበልና በማስፈን፣ በመረከብና በማስተላለፍ ለሠላምና የህግ የበላይነት አስተዋጽኦ በማድረግ ረገድ ዘርፉ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዘርፉ ባህልና ዕሴትን ጠብቆና ተንከባክቦ መያዝ የታሪክ አሻራና የማንነት መገለጫ በመሆን ለጥናትና ምርምር መነሻነት እንዲያገለግል የማድረግ፣ ያለፈውን ባህልና ዕሴት እንደ መነሻ በመውሰድ ጠቃሚነቱን አጉልቶ ለማሳየትና ለቀጣይ ትውልድ ማንነት በማስተላለፍ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብት ባለቤት የማድረግ፣ የእርስ በርስ መረዳዳት፣ የዜግነት ድርሻን የመወጣት፣ አንዱ የሌላውን መብት የማክበር፣ የብዝሃ አሴቶችና ባህል መኖር ትልቅ ማህበራዊ ካፒታል በመሆኑ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለመልካም ገጽታ ግንባታ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ፣ ብዝሃ እሴትና ባህል የማንነት መገለጫ እንደመሆኑ ይህን በእኩል በማክበርና በመጠቀም ለአገር አንድነት፣ ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳር ግንባታ እና ፍትህና ሠላምን ለማስፈን እንዲውል ማድረግ እንዲሁም ባህልንና ዕሴትን ለክልላዊ፣ አገራዊና ቀጠናዊ ትስስር ማዋል የሚሉት ሚናዎች አሉት፡፡ በአጠቃላይ ለልማት ወሳኝ ሚና ያላቸው በመሆኑ እሴቶችንና ባህልን በማጥናት በመጠበቅና በማልማት ለዕድገት የሚኖራቸውን ድርሻ ማጎልበት ከዘርፉ ይጠበቃል፡፡

## የሁኔታ ትንተና

3. ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ፡- ባህል የአንድን ማህበረሰብ ወግና ልማድ የሚገልጽና የማንነት ጉዳይ ስለሆነ ጥበቃና ከለላ እንደሚያስፈልገው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብት ድንጋጌ አንቀጽ 1(2) እና በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህል መብት ድንጋጌ አንቀጽ 6(2) እንደተመላከተው ሁሉም ህዝቦች የራሳቸውን መብት በራስ የመወሰን በነጻነት በፖለቲካ የመሳተፍ እንዲሁም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታቸውንና ባህላቸውን እሴቶቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡ ይህን እውን ከማድረግ አንጻርም መንግስታት የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን የመቅረጽና ፖሊሲዎችን የማውጣት ኃላፊነት እንዳለባቸውም ተደንግጓል፡፡

4. በዘላቂ የልማት ግቦች አጀንዳ (2030) ላይ እንደተጠቀሰው ዘላቂ ልማት ያለ ሰላምና ደህንነት እውን እንደማይሆንና ሠላምና ደህንነትም ያለ ዘላቂ ልማት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ከዚህ አንጻር ዘላቂ ልማት፣ ሠላምና ደህንነት

የሚመጋገቡና የማይነጣጠሉ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የዘላቂ ልማት አጀንዳ ሰብዓዊ ሙብትን መሠረት ያደረገ ሠላም፣ ፍትህ እና አካታች ማህበረሰብ የመገንባትን አስፈላጊነት አጉልቶ ያሳያል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በማህበረሰቦች መካከል ያለውን ባህል እና እሴት ማለትም መረዳዳት፣ መቻቻል፣ እርስ በርስ መከባበር፣ ሁሉም የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አካል መሆኑን መረዳት የሚያስችል ስነምግባር ማዳበር እንዲሁም የጋራ ኃላፊነት መውሰድ መበረታታት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ብዝሀነትን መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነና ሁሉም ባህሎች፣ እሴቶችና ስልጣኔዎች ለዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱና አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥሩ እንደሆነ እውቅና የተሰጠው ጉዳይ ሆኗል፡፡ በዘላቂ ልማት ግብ 4 ኢላማ 7 ላይ እንደተገለጸው የባህል ብዝሀነትን መጠበቅና ባህል ለዘላቂ ልማት የሚኖረውን ሚና ማጎልበት እንደሚገባ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

5. ይሁንና ሉላዊነት በዓለም ዙሪያ ተመሳይ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይሄዳል (Rittzer,2011)፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ቀጣይነት ባለው የባህል ልውውጥ ሂደት ትልቁ ባህል ይበልጥ ጥልቅ እየሆነና ይበልጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ እየሆነ ከካባቢያዊ የሆኑ ሌሎች ባልሎችን እና እሴቶችን እያቀጨጨ የባህልና እሴት መሸርሸርና መጥፋት ሊያስከትል እንደሚችል ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ ቀጣይነት ባለው ግንኙነትና የባህል ልውውጥ ሂደት ዓለም ወደ ሉላዊ ካፒታሊዝም ወይም ምዕራባዊነት ልትለወጥ እንደምትችል ጥናቶች ያመላክታሉ /Boli & Lechner, 2005/፡፡ ስለሆነም ባህል እና እሴት ተጠብቆ እንዲኖር ዋስትና ከሚሰጡ ጉዳዮች መካከል የሚዲያና የቋንቋ ብዝሀነት እንዲኖር ማድረግ፣ ሁሉም ባህሎች እና እሴቶች በስነጥበብ ስራዎች፣ በምርምርና ጥናት፣ በሚዲያ ሥርጭት ተደራሽ ማድረግ፣ ፖሊሲዎችን ማውጣትና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን ማውጣት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

6. አህጉራዊ ሁኔታ፡- የአፍሪካ አህጉር 54 አገሮችን ያቀፈና 2ኛው ትልቁ የዓለማችን የመሬት ክፋይ ሲሆን በህዝብ ብዛትም 2ኛው ትልቁ አህጉር ነው፡፡ አህጉሩ በሚገርም ሁኔታ በመሬት አቀማመጥ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በታሪክ፣ በፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ በተፈጥሮ ሀብት እና በመሳሰሎት ሠፊና ብዝሀነት ያለው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲል አገሮች ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ፣ የፓን አፍሪካኒዝም አስተሳሰብን ለማስረጽና የአፍሪካን አንድነት ለመፍጠር ባደረጉት ጥረት ሂደት ያዳበሯቸው የጋራ እሴቶች አሏቸው፡፡ የአፍሪካ አጀንዳ 2063 ርዕይም " በህዝቦቿ ጥረት የተዋሀደች፣ የበለጸገች እና ሠላማዊ አፍሪካ መፍጠር" የሚል ሲሆን ይህን እውን ከማድረግ አንጻር ትኩረት ከተሰጣቸው አቅጣጫዎች መካከል አህጉሩን የጠንካራ ባህልና ማንነት፣ እሴቶችና ግብረገብ ባለቤት ማድረግ ነው፡፡

7. በአፍሪካ የሰብዓዊ ሙብት ቻርተር እንደተጠቀሰው የማህበረሰቡን ሞራልና እሴት ማጎልበትና ጥበቃ ማድረግ የመንግስታት ድርሻ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል መንግስታት ከፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ባህል አንጻር የሚደረግ ተጽዕኖን ለመከላከል የሚያደርጉትን ጥረት ህዝቡ መደገፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

8. በተጨማሪም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ2015 የሚሊንየም ልማት ግቦችን (MDGs) በመተካት እንደ አዲስ "አጀንዳ 2030" በሚል እስከ 2030 (እ.ኤ.አ) ተግባራዊ የሚሆን የዘላቂ ልማት አንዱ ነው፡፡ ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚ የሚሆን ዕቅድ በዋናነት በ2030 ይደረስበተል ተብሎ የተቀመጠው ጉዳይ አፍሪካውያን ጠንካራ የሆነ የባህል ማንነት፤ የጋራ የሆነ ቅርሶች፣ እሴቶች፣ ሞራላዊና ግብረገባዊ የባህል ገጽታዎችን በማጎልበት የህዝቦችን ማንነትና የስልጣኔ መገለጫዎች በማጠናከር የአፍሪካን የጉዞ ተሀድሶ በማፋጠን ከሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ጋር ተወዳዳሪ ለማድረግ በአፍሪካ ሀገሮች የጋራ ትልም ተደርጎ በስምምነት ሰነዱ ተደንግጓል፡፡

9. ነገር ግን ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍሪካ አብዛኞቹ አገሮች ለአብነት በሩዋንዳ፣ ሱዳን፣ ላይቬሪያ፣ ሴራሊዮን፣ አይቬሪኮስት፣ ናይጀሪያና የመሳሰሉት አገሮች ላይ የተከሰቱት ግጭቶች መነሻዎች የአፍሪካዊያን ባህልና እሴቶች እየተሸረሸሩና እየጠፉ በመጤ ባህሎች መተካታቸው አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ቀለል ተደርጎ

ሊታይ የሚገባው ጉዳይ እንዳልሆነ እና በአህጉሩ ያለውን የባህልና የዕሴት ሀብት ጠብቆ ማቆየትና ለዘላቂ ልማትና ሠላም ግንባታ ግብዓት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

10. አገራዊ ሁኔታ፡- አገራችን በህብረ ባህል ፀጋ የታደለች አገር ናት፡፡ ከእነዚህ መካከልም እንደ ሀገር በዓለም አቀፍ የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት/UNESCO/ የተመዘገቡ 9 የሚዳሰሱ እና 12 የማይዳሰሱ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡ ህዝቦቿም እነዚህን ባህላዊ ፀጋዎች ለዘመናት ተንከባክበው ከትውልድ ወደ ትውልድ እያሸጋገሩ አሁን ላለንበት ዘመን አድርሰዋል፡፡ ባህል በተለይ በጥበባት ዘርፍ (ዕደ-ጥበባት፣ ትውን-ጥበባት፣ ዕይታዊ-ጥበባት እና የስነ-ጽሁፍ ጥበባት) ወይም በፈጠራ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመደቡ የባህል ምጣኔ ሃብታዊ ዘውጎችን እና ልዩ ልዩ ባህላዊ ዕሴቶች፣ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች፣ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች፣ የሰው ልጆች ታሪክና የመሳሰሉትን ሃብቶች አካቶ የያዘ ሰፊ ዘርፍ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የሀገራችን ህገመንገስት በመግቢያው ላይ "ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባህል ያለን፣ የየራሳችን መልከዓ ምድር አሠፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና አብረን የምንኖርባት ሀገር በመሆኗ ያፈራነው ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን" ሲል ይገልጻል፡፡ ይህም አገሪቱ በዘመናት የተገነቡና ለወደፊት አብሮነት፣ እድገትና ብልጽግና ፋይዳ ያላቸው የብዙ ባህሎች፣ እሴቶችና ወጎች ባለቤት እንደሆነች ያመላክታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 39(2) ላይ እንደተጠቀሰው ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብና ህዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ እና በማንነቱ የመኩራት መብት አለው፡፡ ይህን እውን ከማድረግ አንጻርም ከባህል ጋር የተያያዙ ስምምነቶችንና ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠርና በቂ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግም ተብራርቷል፡፡

11. ከላይ የተጠቀሱትን መነሻ በማድረግ እንዲሁም የአገሪቱ የባህል ብዝሀነት ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሰብዓዊ ሀብት ልማት መሠረትና መነሻ መሆኑን በማመን ይህን ሀብት ለተለያየ ልማትና ኢንቨስትመንት ጥቅም ላይ ማዋል በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የባህል ፖሊሲ በ2008 ዓ.ም ወጥቷል፡፡ የፖሊሲው ዓላማ የባህል መስህቦችን በመለየት፣ በማልማት፣ በመጠበቅ፣ እና ጥቅም ላይ በማዋል ለኢኮኖሚዊ፣ ማህበራዊ እና ሰብዓዊ ልማት አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግና ባህሎችና እሴቶች እንዲጠኑ፣ በመረጃ እንዲያዙ፣ ለእይታ አመችነት እንዲኖራቸው እንዲሁም ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ ይህን እውን ከማድረግ አንጻርም አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን የማዋቀር፣ የአሠራር ሥርዓቶችን የመዘርጋትና የተለያዩ የአቅም ግንባት ሥራዎችን ማከናወን አስፈላጊ እንደሆነ ተብራርቷል፡፡ ትምህርት ባህልን እሴትን ወደ ሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፊያ ዋና መሳሪያ እንደመሆኑ በአገሪቱ ያለውን ሠፊ የባህል እሴት ሀብት ጠብቆ ለማቆየት እና ለወደፊት ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በባህልና በትምህርት ሥርዓቱ ያለውን ቁርኝት/ትስስር ማሳደግ ተገቢ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በተጨማሪ የህብረተሰቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ አሠራሮችን መከተል፣ በዲፕሎማሲው የባህል ጉዳይን ማስፋፋትና ማስተዋወቅ፣ የባህል መረጃ ሥርዓት መገንባት እንዲሁም ባህልና እሴትን ከጥፋት መጠበቅ የሚሉት የፖሊሲው ዋና ዋና ትኩረቶች ናቸው፡፡ ፖሊሲውም ዛሬ በምንገኝበት ዘመን በዓለማችን የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ መስፋፋት እና የሕዝብ ፍልሰት እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት በሀገሪቱ ባህል እሴት ላይ የሚፈጠረውን የዘመነ ሉላዊነት ተፅዕኖ ለመቋቋም፣ መንግሥት ለባህል ዘርፍ ልማት የሰጠውን ትኩረት የበለጠ ለማጠናከር፣ የሰላምና የልማት መሠረት የሆኑትን የመቻቻል፣ የመከባባርና የመወያየት እሴቶችን ለማበልጸግ በሚያስችል ሁኔታና ሀገሪቱ የደረሰችባቸውን የልማት ትልሞች ሊያካትትና ሊያፋጥን በሚችል መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

12. በተጨማሪም ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የባህልና የታሪክ ሀብት አንጻር የባህል ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና በትክክለኛው መስመር ለመምራት፣ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ፣ የሚፈጠረውን የስራ እድል እና የገጽታ ግንባታ ስራ ለማሳደግ፣

አዲሲቷን ኢትዮጵያን ያጤነ የፊልም ኢንደስትሪ ለመገንባት ዘርፉን በፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጦ ማንቀሳቀስና መምራት ተገቢ በመሆኑ የፊልም ፖሊሲም በ2010 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ዜጎች ቋንቋዎቻቸውን በማልማት በሁለንተናዊ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማድረግ በ2012 የኢትዮጵያ የቋንቋ ልማት ፖሊሲም ወጥቷል፡፡

13. ይሁን እንጅ የባህል ዘርፉን በትክክለኛው አቅጣጫ አስቀምጦ ለመምራት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ከላይ በተገለጸው መልኩ ቢዘጋጁም ፖሊሲዎቹንና ስታራቴጂዎቹን ሙሉ በሙሉ ከመተግበር አንጻር ውስንነቶች ይስተዋላሉ፡፡ ስለሆነም በባህል ዘርፉ የሚታዩ ውስንነቶችን በማስወገድ የዘርፉን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ የወጡ የህግ ማእቀፎች የሚተገበሩበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በየደረጃው ባለ የአስተዳደር እርከን ወርዶ ተፈጻሚ እንዲሆን አስተሳስሮ መስራትን ይጠይቃል፡፡

14. በሌላ በኩል ባለፉት ዓመታት እንደ ሀገር በዘርፉ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን በፓሊዮንቶሎጂ በፓሊዮአንትሮፖሎጂ እና በአርኪዎሎጂ መስክ በርካታ አዳዲስ የቅሪተ አካል ግኝቶች እንዲሁም የመስኩን የሳይንስ እውቀት ወደፊት ያራመዱ ጥናትና ምርምሮች በማድረግ፣ ቅርሶችን በማስመለስና ሕገ ወጥ የቅርሶች ዝውውርን በመከላከል ረገድ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ለአብነት ያህልም በእንግሊዝ አገር በመቅደላ ጦርነትና በተለያዩ ጊዜያት የተወሰዱ ቅርሶች ማስመለስን አስመልክቶ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን በዚህም ከ150 ዓመት በላይ የቆየ የአፄ ቴዎድሮስ የራስ ፀጉርን ሹሩባ ከእንግሊዝ አገር፣ የአክሱም ሀውልትን ከጣሊያን እንዲሁም የአፍሮ አይገባም መስቀል መመለሳቸው ማሳያ ለመሆን የሚችሉ ናቸው፡፡ ይህም በቀጣይ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ለምናደርገው ጥረት ከፍተኛ መነቃቃትን የፈጠረ ሆኗል፡፡

15. ከዚህ በተጨማሪም የባህል እሴት ልማትና አጠቃቀምን ለማጎልበትም የብሄር ብሄረሰቦችን ባህላዊ እሴቶችን በጥናት ለይቶ ለመሰነድ በተደረገው ጥረት ባህላዊ እሴቶች ተጠንተው በመጽሀፍ መልክ ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡ የብሔር ብሄረሰቦች ቀንና የበዓላትን ቀን በማክበርና ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት አኩሪ ባህሎችና እሴቶችን ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግና ኅብረብሔራዊነትን ለማጠናከርና ትስስርን ለማጎልበት፣ አንድነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ አገር በቀል እውቀቶችን በማልማትና በመጠበቅ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ ጠቃሚ የባህል እሴቶቻችንን በመለየት ለማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ እንዲውሉ ለማድረግ፣ አሉታዊ መጤ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከላከል ጤናማና ለሀገርና ለወገኑ መከታና ኩራት ሊሆን የሚችል ትውልድን ለማፍራት፣ የክብረ-በዓላትንና የፌስቲቫሎችን ሁነት በማዘጋጀት የህዝብ ለህዝብ ትስስርን እና አንድነትን ለማጠናከር በሚያስችል መልኩ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ይሁንና እነዚህ ነባር እሴቶችና ባህሎች እየተሸረሸሩ በመምጣታቸው ምክንያት የመቻቻልና የእርስበርስ መከባበር እየቀነሰ መምጣት፣ ግለኝነት፣ ጥላቻ/የጥላቻ ንግግር/ እንዲሁም የሥርቆት መጎለበት እየታዩ ያሉ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ይህም የጋራ እሴቶቻችንን ለሰላምና ለአንድነት በመጠቀም ረገድ ገና ብዙ ርቀት መሄድ የሚያስፈልግ እንደሆነ የሚያሳይ በመሆኑ በቀጣይ እነዚህን የታዩ ችግሮች በማረም ሀገራችን በምትጠቀምበት መልኩ እንደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ ይዞ መስራትን ይጠይቃል፡፡

## ክልላዊ ሁኔታ

16. አማራ ክልል ሠፊና የተለያዩ ባህሎችና ቅርሶች እንዲሁም እሴቶች ባለቤት ሲሆን በክልሉ እንደ ጎንደር አብያተ መንግስታት እና የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ያሉ በዩኔስኮ የተመዘገቡ የሚዳሰሱ ቅርሶችም ይገኛሉ፡፡ ባለፉት ዓመታት የክልሉ ሕዝብ የማንነት መገለጫ የሆኑትን ቋንቋዎችና ባህላዊ ሀብቶች እንዲጠበቁ፣ እንዲጠኑና

እንዲሰነዱ፣ እንዲከበሩና እንዲለሙ፣ ለሰላምና ለእድገት እንዲውሉ እንዲሁም ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ተደርጓል፡፡

17. በሌላ በኩል በክልላችን ለረዥም ዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገሩ የመጡ በየአከባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ዕሴቶች አሉ፡፡ ከባህላዊ እሴቶቻችን መካከል ለአብነት ያህል ዕድር፣ ደቦ (ጅጊ)፣ ጽጌ፣ ሰንበቴ፣ ማኅበር፣ አበልጅ፣ ጉዲፈቻ፣ የጡት ልጅ፣ አቆልቋይ (አዝማች)፣ ማህበራዊ ደህንነቱን እና ሰላሙን የሚያስጠብቅባቸው ተቋማት ደግሞ በወሎ ዘወልድ፣ አበጋር፣ ሽህ ለጋ፣ አማሬ፣ በሸዋ ቁራኛ፣ በጎጃም ሽንጎ፣ በዋግኽምራ መርካባ (ሸመርነይ)፣ በአዊ አሬቅስጊ፣ መኸይ፣ ወዘተ የሽምግልና እና የዳኝነት ስርዓቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በየአከባቢው ያሉት እነዚህ ማህበራዊ ዕሴቶች እንደየአካባቢው ማህበረሰብ ልማድ፣ እምነት እና የአኗኗር ሁኔታ መጠሪያቸውና የአከዋወን መንገዳቸው ቢለያይም ጥቅማቸውና እሳቤያቸው ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

18. የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የተፈጥሮ ሃብት፣ የመሬት፣ የጋብቻና ሌሎች ማህበራዊ ግጭቶች ዘላቂ በሆነ መንገድ የሚፈቱበት ተጨማሪ ጉዳት ሳያደርሱ በጋራ ባህላዊ የህግ ስርዓት ሲፈቱ የቆዩ ከመሆኑም በላይ ማህበረሰቡ በፈጠረው የመተጋገዥና የመረዳጃ አደረጃጀቶች አማካኝነት በጋራ ተባብረውና ተጋግዘው በመስራት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በጋራ ሲያቃላሉ ኖረዋል፡፡ እነዚህ አደረጃጀቶች በማኅበረሰቡ እምነትና ስነ ልቦና ላይ የተመሰረቱና በበላይነት የሚያስተባብሩትና የሚከውኑት በማኅበረሰቡ ከፍተኛ እምነትና ተቀባይነት በተሰጣቸው የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት መሪዎች በመሆናቸው ውጤታማነታቸው አስተማማኝ ነው፡፡

19. ከባህል አኳያም የብዝሃ ባህል ባለቤትነታችንን አክብረን ማስከበር የምንችለው ሁሉንም በቅርበት በማወቅ እና አንዱ የሌላውን ወግ፣ ባህል፣ እምነትና ማህበራዊ እሴቶችን እንደራሳችን ማየትና መንከባከብ እንዲሁም መጠበቅም ስንችል ነው፡፡ ህብረተሰቡ ለባህላዊና ሀይማኖታዊ መገለጫዎች እኩል ዋጋና እውቅና በመስጠት መቀራረቡን፣ ፍቅሩንና አንድነቱን የበለጠ በተግባር ሊያሳይ ይገባል፡፡ የወንድማማችነት እሴት ብዝሀነትን አክብራ በምትኖር ሀገራችን በእጅጉ ጠቃሚ ከመሆኑም ባሻገር በሁሉም አካባቢዎች የሚከበሩ ባህላዊ ክዋኔዎች እውቅና በመስጠትና በማጎልበት ለሁለንተናዊ እድገት ፋይዳ እንዲኖራቸው ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

20. ስለሆነም እነዚህን የክልል ሀብቶች ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ሳይበረዝ ለትውልድ ማስተላለፍ አበርክቶው ከፍ ያለ ነው፡ ፡ እንደ መስቀል፣ ኢድ አል አድሃ/አረፋ፣ ጥምቀት፣ ገና፣ ቡሄ፣ እንግጫ ነቀላ፣ ሻደይ፣ አሸንድየ፣ ሶለል እና ሌሎች መሰል ሀይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት እንደ ክልል መከበራቸው በህዝቡ መካከል መቀራረብን ያጠናክራል፣ ማህበራዊ ትስስርና አንድነትን ይፈጥራል፡፡ ኢኮኖሚያዊ እሴቶቻችንም ሰፊ፣ ጥልቅና ፈርጀ ብዙ ሲሆኑ በስፋት ከሚታወቁት መካከል የቁጠባ ባህል (እቁብ)፣ ግብርና ነክ አውቀቶች (የአስተራረስ ዘዴ፣ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ብልሀት፣ የማዳበሪያ አመራረትና አጠቃቀም፣ የሰብል ማላመድ፣ አመራረት እውቀትና ክህሎት፣ የእንስሳት እርባታ እውቀቶች /ማድለብ፣ ንብ ማነብ፣ አሳ ማስገር፣ ...)፣ የአካባቢ ጥበቃ እውቀቶች (ደኖችንና እጽዋትን የመንከባከብ፣ የውሀ አካላትን ከብክለት የመጠበቅ፣ ለስነ ምህዳርና ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ አካባቢያዊ እውቀቶች...)፣ ባህላዊ መድሀኒቶችና ህክምና (የሰው እና የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ክህሎት)፣ ባህላዊ የእደ ጥበብ ስራ እውቀትና ክህሎቶች (የቀርቀሃ፣ የቀንድ፣ የእንጨት፣ የቆዳ፣ የሸክላ፣ የስፌት፣ የሽመና፣ የድንጋይ፣ የብረት፣ የከበሩ ማዕድናት ወዘተ.)፣ ባህላዊ የምግብ እና የመጠጥ አዘገጃጀት፣ ትውፊታዊ የኪነ ጥበብ ወይም ኪነ ህንጻ /እንደ ላሊበላና ፋሲለደስ ያሉ/፣ የስነ ጥበብ፣ የቅርጻ ቅርጽ እውቀቶች ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው እሴቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የመጡና የኢኮኖሚ ልማትን በራስ አቅም በዘላቂነት ለመፍጠር የሚያስችሉ ናቸው፡፡

21. ሀይማኖታዊ ከሆኑ መሰረታዊ የጋራ ዕሴቶች መካከልም ሀይማኖተኝነት፣ ሰላማዊነት፣ አብሮነት፣ መከባበር፣ ሀቀኝነት፣ ፍትሃዊነት፣ ይቅርታ፣ ሰብዓዊ ርህራሄ (ሩህሩህነት)፣ መልካም ምሳሌነትና በጎነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም የሀይማኖት ዕሴቶችን ማክበር ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብና ለሀገር የሚሰጡት ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

22. ይሁን እንጅ ከክልሉ እምቅ ባህልና ቋንቋ፣ የቅርስ ከምችት፣ የማንነት መገለጫዎች የሆኑትን ባህላዊ ትውፊቶችንና ቅርሶችን ለገቢ ማመንጫ ከመዋል እና ከማስተዋወቅ አንጻር የክልሉን መልካም ገፅታ ለመገንባት የተደረገው ጥረት በቂ አይደለም፡፡ በተለይም በክልሉ የሚገኙ ሁሉንም ቅርሶች በበቂ ሁኔታ መንከባከብና መጠገን ባለመቻሉ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡ በክልሉ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቅርሶች በመሠረተ ልማት እጥረት፣ በሰፊው አለመተዋወቅ እና በየጊዜው በሚከሰቱ የሰላምና ጸጥታ ችግሮች እንዲሁም በማህበራዊ ቀውሶች ምክንያት ክልሉ ባለው የባህልና የቅርስ ፀጋ ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ መጠቀም አልተቻለም፡፡

23. ከዚህ በተጨማሪም አሁን ያለው ትውልድ በባህል ወረራ ተጽዕኖ ሥር በመውደቁ ለነባር ባህሎችና እሴቶች መሸርሸር ምክንያት እየሆነ ሲሆን የክልሉ ባህሎችና እሴቶች እየደበዘዙ ይገኛሉ፡፡ መልካም ባህልና እሴቶችን በአግባቡ ጠብቆ በመጠቀም በኩል ትልቅ ክፍተት እየታየ ሲሆን የባህላዊ ሽምግልና እና የዳኝነት ሥርዓቶች ተቀባይነት ማጣት፣ የመተባበር የመከባበርና የመተጋገዝ እሴቶች መሸርሸርና የግለኝነትና የኔ ብቻ ባይነት መንገስ፣ አለመደማመጥ፣ በጋራ ችግር ላይ በጋራ መክሮና ተነጋግሮ መፍትሄ የመሻት እሴት እየቀጨጨ መምጣቱ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡

24. በመሆኑም እንደ ክልል በቀጣዮቹ የዕቅድ ዓመታት በትኩረት ተይዘው ሊሰራባቸው የሚገባ ወጥ የሆኑ እሴቶች እንዲኖሩ ከማስቻል አንጻር የተመረጡ እሴቶችና መገለጫቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

25. **ሙያዊ ብቃት፡-** ሙያዊ ብቃት ማለት አንድ ሰው በሰለጠነበትና በሚሰማራበት ሙያ የሚገኙ ማናቸውንም ሳይንሳዊ ንድፈ-ሀሳቦችና ትግበራዎች እንዲሁም ባህላዊ የሆኑ አገር በቀል ዕውቀቶች በሚገባ ያወቀና የጨበጠ፣ የሙያውን ስነ-ምግባር ጠንቅቆ የተረዳና የሚተገብር እንዲሁም ሙያዊ ብቃቱን ለማሻሻልና ለማሳደግ ምንጊዜም የሚጥርና ለመመማር ዝግጁነት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

26. **አገልጋይነት፡-** ሙያዊ መርሆችን አክብሮ በታማኝነት፣ በቅንነት እና በታታሪነት ጊዜውን፣ ዕውቀቱን እና ጉልበቱን ለተመደበበት ስራ ማዋል ነው፡፡ ለማንኛውም ህብረተሰብ ያለ አድሎ በጾታ፣ በዝምድና፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ ወዘተ...ልዩነት ሳይፈጥሩ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

27. **ባህልን መጠበቅ፡-** ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት የሚያንጸባርቅ፣ ማህበረሰቡ የሚጋራው የእምነት፣ የእሴት፣ የአስተሳሰብና የባህርያዊ ሂደት ተዋጽኦ በመሆኑ ጠንቅቆ ማወቅ፣ በመጤ ባህል እንዳይበረዝ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዲሁም ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የሚንቀሳቀስ በተጨማሪም የመልካም ባህል እሴቶች ተጠብቀው ለተተኪው ትውልድ እንዲሻገሩ የበኩሉን ጥረትና አስተዋጽኦ ማበርከት ማለት ነው፡፡

28. **ሕግን ማክበር፡-** ስራውን ለማሳለጥ የወጡትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በመተግበርና የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነት በመተግበር የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ማህበረሰቡ ለመንግስት ያለውን አመኔታ ከፍ ማድረግ ነው፡፡

29. **ሕዝባዊ ወገንተኝነት፡-** ሀገሩንና ህዝቡን አጥብቆ የሚወድ፣ ምንጊዜም ከራሱ ጥቅም ይልቅ ለህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ቅድሚያ የሚሰጥ፣ በማንኛውም ጊዜ በህዝብ ጥቅም ፍላጎት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን አምርሮ የሚታገልና ጥብቅና የሚቆም ማለት ነው፡፡

30. **አርበኝነት፡-** የአገር ሉአላዊነት ሲደፈር በጦር ሜዳ ተዋግቶ የላቀ የጀግንነት ጀብድ መፈጸም፣ ለአገሩ፣ ለባንዲራው፣ ለህዝቡ ፍቅር ያለውና ታማኝ የሆነ ብቻ ሳይሆን በተሰማራበት መስክ ሁሉ ልዕልናው የላቀ ተግባርን ፈጽሞ መገኘት፣ ለህዝብ አለኝታ የሆነ ተግባርን ማከናወን ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በተሰማራበት መስክ ለቀጣይ ትውልድ ቤዛ የሆነ ድርጊትን መፈጸም ከአርበኝነት ጎራ ያስመድባል፡፡

31. **ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም፡-** ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብትን፣ የሚመደብን በጀት፣ ቴክኖሎጅና ጊዜን በአግባቡ እና በቁጠባ መጠቀም፣ እንዲሁም እምቅ የተፈጥሮ ሀብትን (መሬት፣ ውኃ፣ ማዕድናት፣ የቱሪስት መስህቦችን፣ ወዘተ... በአግባቡ እና በፍትሃዊነት ለክልሉ ህብረተሰብ ጠቀሜታ ማዋል ነው፡፡

32. **ለልዕለ ሐሳብ ተገዢነት፡-** ዜጎች የሚያነሷቸውን ሀሳቦች ሰከን ባለ መንፈስ ያለምንም ተጽዕኖ በመመርመር የምክክር መድረክ በማዘጋጀትና በመምከር ምክንያታዊ የሆኑ ሀሳቦችን የመፍትሄ አካል ማድረግ ማለት ነው፡፡

33. **ግብ ተኮር፡-** ሁሉም የአንድ ተቋም ሰራተኞች ተቋሙ አሳካቸዋለሁ ብሎ የቀረጻቸውን ግቦች በጥራትና በቅልጥፍና እንዲሁም በውጤታማነት መፈጸም ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ማንኛውም የተቋሙ ሀብት መዋል የሚገባው ተቋሙ በስትራቴጂክ እቅድ ዘመኑ ፍጻሜ ላይ ሊያስመዘግብ በቀረጻቸው ግቦች ላይ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

34. **ብዝሐነትን መቀበል፡-** በብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ መካከል የባህል፣ የቋንቋ፣ የእምነት ወዘተ... ልዩነት እንዳለ ማወቅ፣ መቀበልና ማክበር፣ የመቻቻል፣ የመከባበር፣ የመወያየት እና የሥራ ባህልን የማሳደግ፣ የጋራ እሴቶቻችንን በማላቅ፣ በልዩነት ውስጥ ያለ ህበረትን የማጠናከር እሴት ነው፡፡

35. **ምርምርና ፈጠራ፡-** በእለት ከእለት ስራችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ችግሮች በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለማፍለቅ እና አዳዲስ አሰራሮችን ለመዘርጋት፣ ህይወትን የሚያሻሽሉ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎትን በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ ከፍ የሚያደርግ እሴት ነው፡፡

36. **ቅንጅታዊ አሠራር፡-** የክልሉ መንግስት ከሌሎች ክልሎች ጋር፣ ተቋማት ከተቋማት ጋር እንዲሁም በአንድ ተቋም ውስጥ በመንግስት መዋቅር ስር ያሉ የስራ ክፍሎች ተግባራቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ጎናዊና ተዋረዳዊ በሆነ አግባብ ተባብረው እና ተናበው ለተሻለ ውጤት በጋራ መስራት ነው፡፡

37. **ግልፅነትና ተጠያቂነት፡-** ዜጎች በየደረጃው በህዝብና በመንግስት የተሰጣቸውን ሀላፊነት በህግ፣ በደንብና በመመሪያ በመታገዝ ያለ ዘር፣ ሀይማኖት፣ ፆታና እጅ መንሻ ማገልገል ሲሆን ከዚህ አግባብ ውጭ ሲፈጸም አስቀድሞ በተቀመጠ የህግ አግባብ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት በመዘርጋት የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው፡፡

38. በአጠቃላይ ነባር እሴቶቻችንና ባህሎቻችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተሸረሸሩ በመምጣታቸው ትውልዱ ለመጤ የባህል ወረራ እየተጋለጠ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የብዙ ችግሮቻችን መፍቻ የነበረው የሽምግልና እና የመመካከር ባህላችን በትውልዱ ዘንድ ተሰሚነቱ እና ሚናው እጅግ እየቀነሰ በመምጣቱ በሽምግልናና በምክር ይፈቱ የነበሩ ችግሮቻችን አሁን ላይ እየተፈቱ ባለመሆናቸው ለበርካታ ችግሮች ተጋላጭ ሆነናል፡፡ በሌላ በኩል ቀደም ባሉት ዘመናት የነበረው የመከባበርና የመደማመጥ ባህላችን አሁን ላይ በእጅጉ የተሸረሸረበትና የተቀዛቀዘበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡

39. ከዚህ በተጨማሪም የስራ ባህላችን፣ የአገር ወዳድነታችን፣ ውሸትን፣ ሌብነትንትን፣ አስመሳይነትን፣ አድርባይነትን፣ አለመቻቻል፣ ከጋራ ጥቅም ይልቅ የራስን ጥቅም ማስቀደም፣  ሠርቶ ከመለወጥ ይልቅ አቋራጭ መንገድ መፈለግ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የመጠየፍ ስብዕናችን እጅግ እየቀጨጨ በመምጣቱ ለስራ አጥነት፣ ለድህነት፣ ለብጥብጥ፣ ለሙስና እንዲሁም አንዱ ለሌላው ከመቆምና ከመቆርቆር ይልቅ ለምናገባኝነት ዳርጎናል፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ የመጡ ቢሆንም ለችግሮቹ ምላሽ ሸጭ የሆነ ተቋም የመገንባትና እየተሸረሸሩ የመጡትን ባህሎቻችንና እሴቶቻችንን ትኩረት ሰጠቶ በማጥናትና በማልማት በኩል የተደረገው ስራ እጅግ ዝቅተኛ ነበር፡፡

40. ባህል፣ እሴትና ልማት የማይነጣጠሉ እንደሆኑና ባህልም ሆነ እሴት ለልማት መሠረት እንደሆኑ በልማት ጥረትም ባህልም ሆነ እሴት እንሚዳብር ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ሰላምን ለማምጣት፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት እንዲሁም ድህነትና ሥራ አጥነትን ለመቀነስ በሚደረግ ጥረት የባህል እና እሴት ጉዳይ እኩል ትኩረት የሚሰጠው ካልሆነ አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ይታመናል፡፡

41. በመሆኑም በቀጣይ አምስት ዓመታት ባህልን እና ዕሴትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንዲሁም ለማልማት ከአሠራርና አደረጃጀት አንጻር ተግባሩ የሚመራበት በህግ ማዕቀፍ የተደገፈ አደረጃጀት እና ተቋማዊ የአሠራር ማሻሻያ ሥርዓትን የተከተለ ሥራ መዘርጋት ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በየደረጃው በሚቀረጸው ስርዓተ-ትምህርት፣ በሁሉም የሚዲያ ዓይነቶች እንዲሁም በትምህርት ቤት ክበባት ስለባህልና እሴት በሰፊው መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ከህብረተሰቡ፣ ከሀይማኖታዊ ተቋማት፣ ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር በትብብር በመስራት ባህልንና እሴትን ለክልሉ ዘላቂ እድገት በማዋል የቱሪዝም ኢደስትሪውን፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቱን ማፋጠን ተገቢ ይሆናል፡፡

## ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

42. የባህልና እሴት መሸርሸር፡- በሁኔታ ትንተናው ላይ በሰፊው እንደተመላከተው ባህሎቻችንና እሴቶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸሩ በመምጣታቸው ምክንያት ክልላችን ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦበታል፡፡ በመሆኑም የባህልና አሴት መሸርሸር በዕቅድ ዘመኑ ሊስተካከል የሚገባው ስትራቴጅክ ጉዳይ ሆኖ ተለይቷል፡፡
43. ባህልንና እሴትን የማልማት ውስንነት፡- ምንም እንኳን ባህሎቻችንና እሴቶቻችን አደጋ የተጋረጠባቸው ቢሆንም ይህንን ለማስተካከል ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥናትና ምርምር በማድረግና በማልማት በኩል ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በሚጠበቀው ደረጃ ስራ እየተሰራ አይደለም፡፡ በዚህ እና በሁኔታ ትንተናው ላይ በተመላከቱት መሰል ምክንያቶች የባህልና ልማት እንቅስቃሴው እየተዳከመ መጥቷል፡፡ በመሆኑም ይህ ሥትራቴጅያዊ ጉዳይ በ5 ዓመቱ የዕቅድ ዘመን እንዲፈታ ተለይቷል፡፡
44. የተቋማዊ አቅም ግንባታ ውስንነት፡- ዘርፉን በተገቢው በማደራጀት፣ አቅሙን በመገንባትና በመምራት ባህልና እሴቶች ለሠላም ግንባታ፣ ለኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚጠበቅ ቢሆንም ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ዘርፉ የሚጠበቅበትን እንዳይወጣ አድርጎት ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አንጻር በቀጣዩ 5 ዓመታት ዘርፉን የሚመጥን የአደረጃጀትና የአሠራር ማዕቀፍ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተቋማዊ አቅም ግንባታ ውስንነት ስትራቴጅያዊ ጉዳይ ሆኖ ተለይቷል፡፡

## የትኩረት መስኮች

- የባህልና እሴት ጥናት፣ ምርምርና ልማት
- የአሠራር ስርዓትና የተቋማዊ አደረጃጀት ግንባታ
- ዘላቂ የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ
- ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

45. የተቋም ግንባታና አደረጃጀት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣ ክልሉ ያለውን ተፈጥሮአዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሀብትን እንዲሁም እሴቶችን በሚገባ መለየትና ማልማት፣ የባህል እና እሴት ሀብቶችን በማጥናት፣ በመንከባከብ እና በመጠበቅ ለክልል ልማት ያላቸውን አስተዋጽዖ በማጉላት በአግባቡ መጠቀም፣ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ህብረተሰብን ለመፍጠር የንባብ ባህልን የሚያዳብሩ ዲጅታል ቤተ-መጽሀፍትን ማስፋፋትና ተደራሽ ማድረግ፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስራ መስራት፣ በዘርፉ የተሰማራዉን የሰው ኃይል በእውቀትና በክህሎት

ማብቃት፣ በክልሉ በተከሰተው ግጭት ጉዳት የደረሰባቸውን ቅርሶች መልሶ ማልማት፣ ጠንካራ የገበያና የፕሮሞሽን ስትራቴጅዎችን መተግበር እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሳደግ የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዓላማ**:- በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ባህሎችን፣ እሴቶችን እና ቅርሶችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በመንከባከብና በማልማት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በዘላቂነት ማረጋገጥና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ፤

## ዋና ዋና ግቦች

46. የክልሉን የባህል፣ እሴት እና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ፣ አዳዲስ አደረጃጀትና አሠራርን በመፍጠር ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣ የክልሉን የሥነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ሥራዎችን ማጎልበት፣ የዕደ-ጥበብ ምርትን ማስፋፋት እና ገበያን ማጎልበት፣ የቋሚ እና የተንቀሳቃሽ ቅርስ ምዝገባ፣ አያያዝና ጥገናን ማሳደግ፣ የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚገነቡ ሙዚየሞችን ከ11 ወደ 55 ማሳደግ፣ በክልሉ የሚለሙ ባህላዊ እሴቶችን ከ14 ወደ 124 ማሳደግ፣ በክልሉ የሚዘጋጁ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ትኩረት ሰጥቶ ማሳደግ፣ በባህል ኢንዱስትሪ የገበያ ትስስር በመፍጠር ባህሉ ለክልሉ ልማት የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ፣ በክልሉ የሚገኙ የባህል ተቋማትን ቁጥር ከ96 ወደ 150 ማድረስ፣ 44 የህዝብ ቤተመጻሕፍትን በቴክኖሎጂ፣ በቁሳቁስ እና በአደረጃጀት ማጠናከር፣ መጤ ባህሎችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እና አመለካከቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት የክልሉን ባህልና እሴት ከመሸርሸር ማዳን፣ በባህል ዕሴቶች ልማት እና በማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ፋይዳቸው ጉልህ የሆኑ 20 አገር በቀል ዕውቀቶችን እና ባህላዊ ዕሴቶችን ማልማት እና መጠበቅ እንዲሁም በባህልና እሴት ዙሪያ የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማጎልበት የሚሉትን ግቦች ለማሳካት በከፍተኛ ትኩረት ይሰራል፡፡

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

47. አደረጃጀቶችን መፍጠርና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ የፖሊሲ ማስፈፀሚያ የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ፤፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብዝኃ ባህላዊ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በማልማት፣ ለመልካም ገጽታ ግንባታና ለዘላቂ ፍትሐዊና ተደራሽ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ማዋል፣ ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር መግባባት መፍጠርና ቅንጅዊ አሠራርን ማዳበር፣ በባህል ዘርፉ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የባህልና ቋንቋ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወን፣ የቅርስ ጥበቃ ልማት፣ የባህል ልማት፣ ስትራቴጅ ማውጣት፣ ቴክኖሎጅንና የባህልና ዕሴቶችን የመረጃ ስርጭትን ማዘመን የሚሉት ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

## የመንግሥት ተቋማት እና የአመራር ሚና

### ክልላዊ ተግዳሮቶች

1. ያለፉት ሰላሳ (30) ዓመታት የክልላችን የዕድገት ጉዞ ስንመለከት ትምህርት የወሰድንባቸው ተግዳሮቶች መኖራቸውን ነው፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች በዋነኛነት በሁለት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡፡ አንደኛው የግጭት አዙሪት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የድህነት አዙሪት ነው፡፡ በክልላችን የድህነት አዙሪት አንዱ ችግር ተደርጎ ሲወሰድ ግልጽ መገለጫዎች አሉት እነሱም፡- የህዝብ ቁጣ መስፋት፣ የአመጽ መበራከት፣ ማህበረሰብን አስተሳስረው የሚይዙ እሴቶች መሸርሸር፣ የኢኮኖሚ እድገት መቀዛቀዝ፣ ፈጣን እድገት አለማስመዝገብ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የስነ-ልቦና ጫና መፈጠር፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጦር መሳሪያ ዝውውር መበራከት፣ መፈናቀልና የስደተኞች ሙብዛት መገለጫዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መገለጫዎች ላለፉት ዓመታት እየተደጋገሙና በክልላችን እየተከሰቱ ያየናቸው እንዲሁም አሁንም እየፈተኑን ያሉ ችግሮች በመሆናቸው አሁንም ክልሉ ከግጭት አዙሪት አለመውጣቱን ድምዳሜ ላይ ደርሰናል፡፡
2. በሌላ በኩል የድህነት አዙሪት ሌላኛው የክልሉ ፈተና ነው ስንል ለዚህም ግልጽ መገለጫዎችን ማንሳት ለመግባባት ዕድል ይሰጣል፡፡ በክልላችን ለድህነት አዙሪት መገለጫዎች ተደርገው ከሚወሰዱት መካከል ዝቅተኛ ገቢ፣ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ችግር፣ የጤና አገልግሎትና ጥራት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት፣ ከፍተኛ የስራ ፈላጊ ቁጥር መኖር፣ በቂ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት አለመኖር፣ ዝቅተኛ የመሰረተ ልማት መኖር፣ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነት ደካማ መሆን፣ የአካታችነት ችግር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ስለሆነም ላለፉት አመታት ከድህነት አዙሪት አለመውጣታችን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ፈተናችን መሆኑ ግንዛቤ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡
3. ስለሆነም በክልላችን የተከሰተውን የግጭትና የድህነት አዙሪት ለመፍታት ቁልፍ መሳሪያው ፖለቲካ ነው፡፡ ፖለቲካ የግጭትና የድህነት አዙሪትን ለመፍታት አይነተኛ ሚና አለው ካልን የፖለቲካ ሶስት ወሳኝ አምዶች ላይ ርብርብ በማድረግ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡
    1. የመንግስት ተቋማትና አስተዳደርን ማሻሻል /Governance and institutions/
        - የመንግስት አገልግሎት አሳጣጥ የተሻሻለ መሆን፣ የመንግስት ተቋማት የማስፈጸም አቅም ከፍተኛ መሆን፣ የህግ የበላይነት መረጋገጥ የተረጋጋ ፖለቲካ ለመኖር ዕድል ይከፍታል፡፡
    2. ችግር ፈቺ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ /Policy response/
        - መንግስት የህብረተሰቡን ዕድገት ለማረጋገጥ በየደረጃ ለሚገጥሙ ፈተናዎች ተገቢውን የፖሊሲ ስርዓት ለመዘርጋት በቁርጠኝነት ለመተግበር መቻል አለበት፡፡
    3. አመራር ሰጭነት /Political will and leadership/
        - አመራሩ በቁርጠኝነት ውሳኔ መስጠት ሲችል ለሚገጥሙ ቀውሶች መፍትሔ ማበጀት ሲችል እንዲሁም የረጅም ጊዜ ዕድገት ለማምጣት በተግባር የተገለጸ ቁርጠኝነት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
4. ፖለቲካን የግጭትና የድህነት አዙሪት ቁልፍ መፍቻ ነው ስንል በሚያመጣው መሰረታዊ ለውጥ ነው፡፡ ፖለቲካ የግጭት አዙሪትን ከመፍታት አንፃር ያለውን ሚና ብንመለከት ጠንካራ የመንግስት ተቋማትን በክልላችን መፍጠር ከቻልን ይህ የተቋማት ጥንካሬ የመንግስት አስተዳደርን በማሻሻል ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህ ደግሞ በወቅቱ

ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስችል አግባብነት ያለው ፖሊሲ አውጥቶ ለመተግበር ዕድል ይሰጣል፡፡ በዚህም የተነሳ ፖለቲካ የግጭት አዙሪትን በመፍታት ረገድ አይተኬ ሚና ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሙስናን የመዋጋት አቅም እየደከመ ሲመጣ በማህበረሰብ ውስጥ የሚሰጠው መንግስታዊ አገልግሎት ኢ-ፍትሐዊነት ስለሚስተዋልበት ይህም ተገቢውን የህዝብ ጥያቄ ለመፍታት መንግስት አቅም ስለሚያንሰው የግጭት መነሻ መንስኤ ለመሆን ያገለግላል፡፡ የፖለቲካ ሚናን ከድህነት አዙሪት ከማውጣት አንፃር ያለውን ስንመለከት ደግሞ ጤናማ ፖለቲካ በክልሉ ውስጥ ማራመድ ከተቻለ የሚደረጉ የመንግስት ውሳኔዎችን በትምህርት፣ በጤና፣ በኢኮኖሚ እዲሁም በማህበራዊ ዋስትና ስራዎች የተሻለ ስለሚሆን ይህ ደግሞ በቀጥታ ድህነትን ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ሚና ይጫዎታል ማለት ነው፡፡

## የመንግስት ተቋማትና አስተዳደርን ማሻሻል

5. ከተቋማት ግንባታ ጋር ተያይዞ በበለጸጉትና ባልበለጸጉት ሀገሮች መካከል የታዩ ልዩነቶች በዋናነት የሚንጸባረቁት በሀገረ መንግስት ጥንካሬ፣ በህግ የበላይነት መረጋገጥ እና በተጠያቂነት መስፈን ጉዳዮች ዙሪያ ነው፡፡ የበለጸጉ ሀገሮች ከሞላ ጎደል በሶስቱም ጉዳዮች ጠንካራ የማስተዳደርና የማስፈጸም ብቃት ያላቸው ተቋማትን የገነቡ ሲሆን በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ግን በእነዚህ መመዘኛዎች ሲመዘኑ በብዙ መልኩ ወደ ኋላ የቀሩ ናቸው፡፡
6. ሀገራችን ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ተምሳሌት ተደርገው እንደሚወሰዱት የአውሮጳና የእስያ ሀገራት ሁሉ በረጅም የመንግስትነት ታሪኳ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት የመሰረተች ቢሆንም በታሪኳ የተሟላ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ያለበት ፖለቲካዊ ስርዓት ለማስፈን አልቻለችም፡፡ በዚህም ምክንያት ፖለቲካዊ መረጋጋቷን በዘላቂነት ለማስጠበቅ አቅቷት በታሪክ አቻዋ ከሆኑ ሀገራት ተለይታ በሁለንተናዊ ኋላ ቀርነትና ድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ ሆናለች፡፡
7. በዓለማችን ላይ ዘግይተው መልማት ከቻሉ ሀገራት መካከል ጃፓን አንዷ ነች፡፡ የልማታዊ መንግስት የእድገት ፈለግ አብነት ተደርጋ የምትጠቀሰው ጃፓን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከደረሰባት አሰቃቂ ሽንፈት አገግማ ዓለምን ያስደመመ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማስመዝገብ የቻለችው በእውቀትና በችሎታ ላይ የተመሰረቱ ጠንካራ ተቋማትን በመገንባቷ ነው፡፡ ይህ ጃፓን ከምዕራቡ ዓለም የቀሰመችውና ከሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥማ ተግባራዊ ያደረገችው የጠንካራ ተቋማት ግንባታ ተሞክሮ ለብዙ የሩቅ ምስራቅ እስያ ሀገሮች በምሳሌነት አገልግሏል፡፡
8. በአጭር ጊዜ ውስጥ "ተአምራዊ" የተባለና ዓለምን ያስደመመ እድገት ያስመዘገቡት ሲንጋፖር፣ ታይዋን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ማሌዥያና ሌሎች የደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገሮች ከጃፓን ባገኙት ተሞክሮ ተነስተው ጠንካራ ተቋማትና ቢሮክራሲ በመገንባት ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡
9. በሀገራችን ምንም እንኳን ላለፉት ዓመታት የልማታዊ መንግስት ፈለግን እንከተላለን ብንልም የልማታዊ መንግስት ዋነኛ መለያና የጥንካሬ ምንጭ የሆነውን ብቁ ተቋማትን የመገንባት ውስንነታችን ከፍተኛ ነው፡፡ ሀገረ መንግስቱ የተዋቀረባቸው ተቋማት በፓርቲና በመንግስት መደበላለቅ፣ መንግስታት ሲቀያየሩ አፍርሶ በመገንባት አባዜ እንዲሁም ነፃና ገለልተኛ ባልሆኑ ተቋማት የተደራጀ ነው፡፡
10. በፓርቲና በመንግስት መካከል ያለው መደበላለቅ፣ መንግስታት ሲቀያየሩ አፍርሶ የመገንባት አባዜያቸው አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ተቋማት ሀገረ መንግስቱን ሳይሆን መንግስታቱን ብቻ እንዲያገለግሉ ተደርገው ከተቀረጹ መንግስት ሲቀየር ከአዲስ መንግስት ጋር ለመቀጠል የሚያስችላቸውን ገለልተኛነት አያዳብሩም፡፡ ይህም ተቋማቱን አፍርሰን እንደ አዲስ እንድንጀምር ስለሚያደርገንና ክምችትን ስለሚያጠፋ ስራዎቻችን ካለበቂ ወረት እንድንጀምር እንገደዳለን፡፡ ስለዚህም ሁሌም ለማጅ የሆኑ ተቋማትን ይዘን እናዘግማለን፡፡
11. በሌላ በኩል ተቋማት ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር አብረው አለመታደላቸው ከተገነቡበት የጊዜ ታካኪነት አስተሳሰብ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ከለውጥ ጋር አብሮ ለመለወጥና ለውጥን እያነበቡ አመራርን ለመቀየር ከወግ

አጥባቂነት አስተሳሰብ መላቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀርና ተቋማት በወግ አጥባቂ ሰዎች ሲሞሉ፤ ከአካባቢያቸው ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ስለሚቋረጥ በብቸኝነት ጉድለት ውስጥ እየበሰበሱ ይመጣሉ፡፡

12. ህብረተሰቡ ነባራዊ ሁኔታው ሲለወጥ የተቋማቱም ሁኔታ ተጣጥሞና ተዛምዶ እንዲለወጥ ለማድረግ ከተሳነው ደካማ ሀገረ መንግስት ይፈጠራል፡፡ ነባሮቹን ተቋማት ጠብቆ የማቆየት ጠንካራ የወግ አጥባቂነት ፍላጎት ለወቅቱ ሁኔታ የማይመጥኑ አሮጌ ተቋማትን ተሸክመን እንድንንገታገት ከማድረጉም በላይ ውድቀት ውስጥ እየተዘፈቅን መሆናችንንም እንድናይ ያደርገናል፡፡ የተቋማዊ ችኮነት ችግርን ለመቅረፍ አስቀድሞ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ተንትኖና ተንብዮ የሚሰራ ቀድሞ የነቃ አመራር፣ ቢሮክራሲ እና ባለሙያ መፍጠርን ይጠይቃል፡፡

13. ጠንካራና መልካም የመንግስት አስተዳደር ለመፍጠር የተቋማት ግንባታ የሪፎርም ስራዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሪፎርሙ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያልነበሩ አዎንታዊ ውጤቶችን ለማግኘት የመንግስት ስራዎች የሚሰሩባቸው የቆዩ አመለካከቶች፣ አሰራሮች፣ አደረጃጀቶችና ሂደቶች በታቀደና በተቀናጀ ሁኔታ በአዳዲስ የሚለወጡበት መሳሪያና ትግል ነው፡፡ ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ያለው ተቋምና መንግስት ሲፈጠር፣ ብቁና ሥነ-ምግባር ያለው እንዲሁም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ባለሙያ ይኖራል፡፡ በመንግስታዊ ጉዳዮች በንቃት የሚሳተፍ ህብረተሰብ ይፈጠራል፡፡ ሁሉም አካላት በህግ የበላይነት አምነው የሚንቀሳቀሱበትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት ይገነባል፡፡

14. ሀገራዊ ቅርጽ ከያዘ የሪፎርም አዲስ ፓኬጅ ይልቅ ያልተማከለና ለዘርፍ ልዩ ባህርይ ትኩረት የሚሰጥ፣ በእውቀት የሚመራና የሴክተሩን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ሪፎርም የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡ እንዲህ አይነት ዘርፍና ተልዕኮ ተኮር የተቋማት ግንባታ ሪፎርም ታክቲክ ስኬታማነት በዋናነት የሚወሰነው በየተቋማቱ የበቁ የለውጥ ሐዋርያት ካሉ ነው፡፡ ይህን ለመፍጠር ደግሞ የአመራር ብቃት እጅግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

## የፖለቲካ ቁርጠኝነትና አመራር ሰጭነት

15. የአመራር የፖለቲካ ቁርጠኝነት መረጋገጥ ክልሉ በቀጣይ 25 ዓመት እደርስበታለሁ ያለውን ርዕይ ለማሳካት ከፍተኛ ዕድል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የአመራሩ የፖለቲካ ቁርጠኝነት መገለጫው ደግሞ የክልሉን ልማት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችንና ደንቦችን እንዲሁም ሊያሰሩ የሚችሉ መመሪያዎችን ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በመፈተሽ አዘጋጅቶ መተግበር ሲችል ነው፡፡ ለዚህም ዓለም በፈጣን ለውጥ ውስጥ ስለሆነ ከተቸካይነት ተላቆ በዓለም ውድድር ውስጥ ክልላዊ ሚናው ጎልቶ የሚያወጣው የፖሊሲ ማዕቀፎችን ቀርፆ የመተግበር ስራዎችን ማከናወን የግድ ይሆናል፡፡

16. በተጨማሪም አመራሩ የክልሉን ህዝብ ከድህነት ለማላቀቅና ወደ ተሟላ ሰላም ለመመለስ የክልሉን መሰረታዊ ችግሮች በየግዜው እየለየና መፍትሄ እያስቀመጠ መሄድ ይኖርበታል፡፡ የዓለም ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው የችግር አለያየት እና የመፍትሔ አሰጣጥ ሂደታቸው የሀገራትን የዕድገት ጉዞ ለይቶ እናየዋለን፡፡ ለአብነት የሁለት ሀገራትን ተሞክሮ ማለትም የላቲን አሜሪካ በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ከችግር ለመውጣት የጠየቁት ጥያቄ "ይህን ያደረገብን ማን ነው ? /who did this to us? /" የሚለው ነው ይህ ጥያቄ በባህሪው መልስ እንድንሰጥ የሚያስገድደን በሴራ ትንተና ላይ ተመስርተን ነው፡፡ ምክንያቱም የህልውና ጥያቄ ስለሆነ መልሱም እንቅፋት ያላቸውን ለማስወገድ ጥረት የሚያደርግ ነው፡፡ በሌላ በኩል ጃፓኖች ከገጠማቸው ብዙ ቀውስ በኋላ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሀገራቸውን ከችግር ለማውጣት ያነሱት ጥያቄ ከላቲን አሜሪካኖች በተቃራኒው ነው ይኸውም "ምን ላይ ነው የተሳሳትነው ? /what did we do wrong?/ " የሚለውን ነበር በመሆኑም ጃፓኖች ይህንን ጥያቄ በማንሳታቸው ወደ አዲስ እሳቤ የሚገፋ መልስ ወደ መስጠት ነው የሄዱት ማለትም እንዴት ከችግራችን ፈጥነን መውጣት እንችላለን ? /how do we put it right? / በማለት ወደ ስራ ገቡ በመሆኑም ጃፓን ዛሬ ለደረሰችበት ዕድገት ከውድቀታቸው የተነሱት

የውስጣቸውን ችግር በማየታቸው ነው ላቲን አሜሪካኖች ግን በወቅቱ ለችግራቸው ውጫዊ ምክንያት ማስቀመጥ ስለፈለጉ የዕድገታቸው ልዩነት ከጃፓን ጎልቶ ያነሰ ሆኗል፡፡ ስለሆነም ይህ ዕቅድ የክልላችንን ችግር ክልሉ ከተመሠረተበት ግዜ ጀምሮ ያለውን በመፈተሽና ውስጡን ያየ በመሆኑ በቀጣይ ይህን ዕቅድ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚያስተባብረው አመራር ሁልጊዜ እንደ ጃፓኖች ውስጥን በማረም እና ለገጠሙ ችግሮች የውስጥን አቅም አሟጦ በመረባረብ መፍትሔ እያስቀመጠ የሚሄድ ይሆናል፡፡

17. የክልላችን አመራር ህዝቡን በማስተባበር ዕቅዱን በማሳካት ሂደት ምን አይነት የአመራር ዘይቤ (ስልት) መከተል አለበት ለሚለው ወሳኙ ጉዳይ የክልሉ ፍላጎት ነው፡፡ ይህም ሲባል የክልላችን ህዝብ በአሁኑ ሰዓት ቀርቦ የሚያገለግለው አመራር ይፈልጋል፡፡ ይህን ለማሳካት ደግሞ ቀልጣፋና ብቁ ተቋማት በሙሉ አቅማችን ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ አገልግሎት እንዲሰጡ ጠንካራ ሪፎርም ይፈልጋሉ እንዲሁም የህግ የበላይነት ተከብሮ ጠንካሮች የሚሸለሙበት ጥፋተኞች የሚጠየቁበት መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም አንድ አይነት የአመራር ዘይቤ መከተል ብቻውን ስለማያዋጣ ሶስት የአመራር ዘይቤዎችን አዋህዶ መጠቀም ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ይህም ሲባል የክልሉ አመራር በዋናነት አገልጋይ አመራር እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም ትራንስፎርሜሽናል እና የትራንዛክሽናል አመራር ባህሪን በማላበስ ተግባራዊ እንዲያደርገው የሚደረግ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስምንት

# የማስፈጸሚያ ሥልቶች


| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት | **የቀጠና ልማት** |
| ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት | **ልዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች** |
| ምዕራፍ ሠላሳ አራት | **የዘርፍ ስትራቴጂዎች እና ፖሊሲዎች** |
| ምዕራፍ ሠላሳ አምሥት | **የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት** |
| ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት | **የተቋማት አደረጃጀት እና ሚና** |

## ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

# የቀጠና ልማት

### የዘርፉ ሚና

1. ዘርፉ ቀጣይነት ያለው በክልሉ ለተቋቋሙ ከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን (የኢንዱስትሪ መንደሮችን፣ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስተሪ ፓርኮች እና የክላስተር ማዕከላትን) የማደራጀትና መገኛ ቦታዎችን የማመላከት እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮችን (የመንገድ እና የድልድይ) ግንባታዎች የሚደረጉባቸውን ቦታዎች የማሳየት ሚና አለው፡፡
2. የክልሉን የውኃ ሀብት ስርጭት፣ የከርሰ ምድርና ገጸ-ምድር እና የንፁህ መጠጥ ውኃ ሀብት መገኛ ቦታ የመለየት፣ በከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን የማመላከት፣ ለንፁህ መጠጥ ውሀ የሚያገለግሉ የውኃ ተቋማት በስታንዳርዳቸው መሰረት እንዲገነቡ እና እየተገነቡ መሆናቸውን እንዲሁም ፍትሀዊነታቸውን የማረጋገጥ ሚና አለው፡፡ በተመሳሳይ የኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨትና የማሰራጨት፣ ስራዎችን ለማከናወንና እንዲለሙ ለማድረግ እንዲሁም መገኛ ቦታዎችን የማመላከት ሚና ይኖረዋል፡፡
3. በክልሉ መንግሥት አማካኝነት ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የመስኖ ግድቦችና የመስኖ አውታሮችን የሚገነቡበትን ቦታ የማሳየት፣ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማቶች መገኛ ቦታ የማመላከት፣ በፌደራልና በክልል መንግስታት በቀጣይ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ባላቸው በመስኖ የሚታረስ መሬት እና በከፍተኛ ሁኔታ ማልማት በሚችሉት መሬት መሰረት እና ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ የማድረግ፣ መለስተኛና ከፍተኛ ጥገና የሚደረግባቸውን የመስኖ ተቋማት የመለየትና መገኛ ቦታዎችን በጅኦ-ስታሻል የመስራት ሚና አለው፡፡
4. የክልሉን ዕምቅ የማዕድን ሀብቶች ዓይነት፣ ክምችት፣ ጥራት እና ስርጭት መገኛ ቦታዎችን ማሳየት፣ የማዕድን ኢንቨስትመንትን ለማሳለጥ መሰረታዊ ጂኦሎጅካል ካርታና ጥናቶች እንዲሁም ማዕድን አመልካች ካርታዎችን የማዘጋጀት፣ በቀጣይ የሚገነቡ የማዕድን ፋብሪካዎችን በጅኦ-ስፓሻል የማደራጀት ሚና ይኖረዋል፡፡
5. በክልሉ የሚገኙ መንገዶችን ዓይነትና አውታሮቻቸውን መገኛ ቦታ ማመላከት፣ የቀበሌ ማዕከላት ከዋና መንገድ ጋር በማገናኘት ተደራሽነት ማሳየት፣ በፌደራል፣ በክልል እና በህብረተሰብ ተሳትፎ በቀጣይ የሚገነቡትን የፍጥነት መንገድ፣ የአስፓልት፣ የጠጠር፣ የኮብል እና የጥርጊያ መንገዶችን እንዲሁም ከፍተኛ እና የእግረኛ ተንጠልጣይ ድልድዮችን በስፓሻል ማመላከትና በስታንዳርዳቸው መሰረት ፍትሀዊነታቸውን የማሳየት ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ግንባታ ላይ ያሉ የመንገድ ፕሮጀክቶች እና የጥገና ፕሮጀክቶች የሚከናወንባቸው ቦታዎች የማመላከት ሚና አለው፡፡
6. በፌደራልና በክልል መንግስታት የሚገነቡ ነባርና አዳዲስ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን (የህዝብ ማመላለሻ መናኀሪያ፣ ትራፊክ ኮምፕሌክስ፣ ፓርኪነግ፣ የአነስተኛ አዉቶቢስ መጫኛ ተርሚናል፣ የከተማ አዉቶቢስ ዴፖ እና የዉሃ ወደብ)፣ የአየር ትራንስፖርት መዳረሻዎች እና የባቡር መንገዶች በጅኦ-ስፓሻል የማሳየት ሚና አለው፡፡
7. ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት መሰረተ ልማቶችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ተደራሽ ለማድረግ ስርጭታቸውን ማሳየት፣ በቀጣይ ትምህርት ቤቶች በሚገነቡበት ወቅት ሀገራዊ እና ክልላዊ የትምህርት ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ፣ የአካባቢውን የቦታ አቀማመጥ፤ የትምህርት ቤቶች ፍትሃዊ ስርጭት እና መሰረተ ልማቶችን ታሳቢ በማድረግ የትምህርት አቅርቦቱን ሚዛናዊና ፍትሐዊ ለማድረግ እና መገኛ ቦታዎችን የማመላከት ሚና አለው፡፡

በተጨማሪም በክልሉ የመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆችንና ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን በስፓሻል የማሳየት ሚና አለው፡፡

8. የክልሉን የጤና ተቋማት ዓይነትና ስርጭት መገኛ ቦታዎችን ማሳየት፣ አዲስ የህክምና ተቋማት ግንባታዎችን በሀገሪቱ የጤና ስታንዳርድ መሠረት የሚገነቡበትን ቦታ እና ፍትሀዊነታቸውንም የማሳየት ሚና አለው፡፡ የጤና ተቋማት (ጤና ኬላ፣ ጤና ጣቢያዎች እና ሆስፒታሎችን) የጤና መሠረተ-ልማት ግንባታዎች የኤልክትሪክ እና የውሀ አገልግሎት ያላቸው እና የሌላቸው ተቋማት የመለየት እና በስፓሻል የማመላከት ሚና አለው፡፡

## ክልላዊ ሁኔታ

9. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀገሪቱ ካሉ 12 ክልሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ክልሉ በ8° 41'4" እስከ 14° 26'10" ሰሜን የኬክሮስ እና በ35° 26' 50" እስከ 40° 25'20" ምሥራቅ የኬንትሮስ መስመር ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የቆዳ ስፋቱ 181,190.16 ስኩየር ኪ.ሜ. ወይም 18.12 ሚሊዮን ሄክታር ነው፡፡ የሚያዋስኑትም በምስራቅ አፋር ክልል፣ በምዕራብ ሱዳንና ቤንሻንጉል ክልል፣ በሰሜን ትግራይ እና ኤርትራ እንዲሁም በደቡብ የኦሮሚያ ክልል ናቸው፡፡

10. ክልሉ በ14 ዞኖች፣ 8 ሪጅ-ፖሊታን ከተሞች (36 ክፍለ ከተሞች)፣ 77 ከተማ አስተዳደሮች፣ በ153 የገጠር ወረዳ አስተዳደሮች፣ 4176 (3544 የገጠር እና 632 የከተማ) ቀበሌ አስተዳደሮች የተከፋፈለ ነዉ፡፡

11. በ2017 ዓ.ም በተደረገው የትንበያ መረጃ መሠረት የአማራ ብሐራዊ ክልላዊ መንግስት የህዝብ ብዛት 23,878,999 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 11,884,006 ወንዶችና 11,994,993 ሴቶች ናቸው፡፡ ከክልሉ ጠቅላላ ህዝብ እድሜያቸዉ 14 ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑት 9,427,256 (39.48%)፣ ከ15-64 ዓመት 13,449,286 (56.32%)፣ 65 እና ከዚያ በላይ የሆኑት ደግሞ 1,002,458 (4.2%) ይሸፍናሉ፡፡ የህብረተሰቡን መኖሪያ አካባቢ መሰረት በማድረግ በከተማ 5,438,997 በገጠር ደግሞ 18,440,002 ያህል ሕዝብ ይኖራል፡፡ የሕዝብ ጥግግቱ ሲሰላ 131.8 ህዝብ በካሬ ኪ.ሜ እንደሚኖር ተገምቷል፡፡




ካርታ፤ ክልሉን በዞኖች የሚያሳይ ካርታ

## የልማት ቀጠናዎች አስፈላጊነት

12. የልማት ቀጠና የማህበራዊ ዘርፉን ስርጭትና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚ እድገትና ልማትን ለማፋጠን፣ ለኢንቨስትመንት ቅድሚያ የሚሰጠው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ለመለየት፣ የተሻሉ እና ምቹ መሠረተ ልማቶችን በመስራት አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ፣ የግብርና ምርትን ለማሳደግ እና ወደ አለም ገበያ የሚላኩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ያግዛል፡፡
13. የክልሉን ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ያለውን እምቅ ሀብት ማለትም የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃ፣ ለክረምትና ለበልግ እንዲሁም በመስኖ ሊለማ የሚችል ተስማሚ የሆነ ሰፊ ለእርሻ የሚውል መሬት፣ ምቹ የእንስሳት እርባታ፣ የሰብል ልማት፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የዓሳ ሀብት፣ በብዝሃ ሕይወት የበለፀጉ ደኖች፣ እፅዋትና አእዋፋት፣ ምቹ የአየር ንብረትና የመሬት አቀማመጥ፣ የዳበረ ባህላዊና ማህበራዊ መስተጋብር፣ የከበሩ ማዕድናት፣ ታዳሽ የሃይል ምንጭ፣ የቱሪዝም አማራጮች፣ የሰዉ ሀይል እና ሌሎች ሃብቶችን በመለየት በተቀናጀ መንገድ መጠቀም የሚቻልበትን ስልት በመቀየስ ዘላቂ ዕድገት ለማረጋገጥ እንዲቻል በልማት ቀጠና ከፋፍሎ ወደ ስራ መግባት አስፈላጊ ነው፡፡
14. ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የዝናብ ሁኔታ ከፍና ዝቅ ማለቱን ተከትሎ ኢኮኖሚው ከፍና ዝቅ በማለቱ የኢትዮጵያ የግብርና እድገትና በአጠቃላይም የኢኮኖሚውን ሁኔታ በአብዛኛው የተመሠረተው በዝናብ ውሃ ላይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከዝናብ ጥገኝነት የተላቀቀና የግብርና ልማቱ በመስኖ ልማት ጭምር የታገዘ እንዲሆን ውሃን ማዕከል ያደረገ የመስኖ ስራን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ይህንንም እውን ለማድረግ በርካታ አርሶ አደሮች የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር ውሃን፣ የውሃ ፓምፖችን እና የተለያዩ የዝናብ ውሃ ማሰባሰቢያ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ለውጦች እየታዩ መጥተዋል፡፡

15. በተፋሰስ ልማት ላይ ያተኮረ የግብርና ምርት እድገት ከክልል አልፎ በሀገር አቀፍ ደረጃ ዋነኛ አላማው ድህነትን በመቀነስ በተለይም ድርቅን በመቋቋምና በምግብ እህል እራሰን ከመቻል ያለፈ በኢንዱስትሪና በኤክስፖርት እድገታችን አስተማማኝና የማያቋርጥ እድገት ለማምጣት ዋነኛውና አማራጭ የማይገኝለት መንገድ ነው።

16. የከርሰ ምድርን፣ የገፀምድርና የዝናብ ውኃን በመጠቀም የተሻለና አስተማማኝ እድገት ለማምጣት ተፋሰስን እንዲሁም አካባቢያዊ የአየር ንብረት ቀጠናዎች መሠረት በማድረግ ክልሉ በስድስት የልማት ቀጠናዎች ተከፍሏል፡፡

## የልማት ቀጠናዎች አመሰራረት

17. የልማት ቀጠናዎች መሰረታዊ መነሻ ተፋሰስን፣ የአካቢቢያዊ የአየር ንብረት እና የወረዳ አስተዳደር እርከንን መሰረት ያደረገ በመሆኑም የተወሰኑ ወረዳዎች በሁለትና ሶስት የልማት ቀጠናዎች የተካተቱ በመሆናቸው በልማት ትግበራ ወቅት ሊገጥም የሚችለውን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት የተከፈለው ወረዳ አብዛኛው ቀበሌዎች በሚገኙበት የልማት ቀጠና እንዲጠቃለል ተደርጓል፡፡ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ እጅግ በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኘውን የክልሉን ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና ድህነትን ለመቀነስ መሰረት በማድረግ ክልሉ ስድስት የልማት ቀጠናዎች አዋቅሯል፡፡ በዚህም መሰረት መካከለኛው አማራ፣ ሰሜን ምዕራብ አማራ፣ ተከዜ፣ ምስራቅ አማራ፣ ደቡብ ምዕራብ አማራ፣ እና ጣና የልማት ቀጠናዎች ናቸው፡፡

18. የመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 27,019.37 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን የክልሉን 14.91% ይሸፍናል፡፡ የልማት ቀጠናው 32 ወረዳዎች፣12 ከተማ አስተዳደሮች፣ 1ሪጆ-ፖሊታን ከተማ(ደብረ ብርሀን)እና 703 የገጠር ቀበሌዎች፣ 92 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 795 ቀበሌዎችን ይይዛል፡፡ በ2017 ዓ.ም የትንበያ መረጃ መሰረት 4,217,246 ህዝብ የሚኖር ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 55.38% የሚሆነው በምርታማ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የልማት ቀጠናው የህዝብ ጥግግት 156 ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ የሚኖሩ ቢሆንም ከወረዳ ወረዳ የህዝብ ጥግግቱ የተለያየ ነው፡፡

19. የሰሜን ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 50,912.29 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን የክልሉን 28.1% ይሸፍናል፡፡ የልማት ቀጠናው 18 ወረዳዎች፣12 ከተማ አስተዳደሮችንና 381 የገጠር ቀበሌዎች፣ 69 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 450 ቀበሌዎችን ይይዛል፡፡ በ2017 ዓ.ም የትንበያ መረጃ መሰረት 1,948,436 ህዝብ (ከወልቃት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ወጭ) የሚኖር ሲሆን በUN Habitat Regional Spatial 2023 እ.አ.አ ጥናት መሰረት በወልቃት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ውስጥ 555,267 ህዝብ በድምሩ 2,503,703 ይኖራል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከዚህም ውስጥ 55.08% (ወልቃይት ዞንን ሳይጨምር) የሚሆነው ህዝብ በምርታማ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን የልማት ቀጠናው የህዝብ ጥግግት 49 ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ (ወልቃይት ዞንን ጨምሮ) የሚኖሩ ቢሆንም ከወረዳ ወረዳ የህዝብ ጥግግቱ የተለያየ ነው፡፡

20. የተከዜ የልማት ቀጠና ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 33,652.72 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን የክልሉን 18.6% ይሸፍናል፡፡ የልማት ቀጠናው 38 ወረዳዎች፣10 ከተማ አስተዳደሮችንና 586 የገጠር ቀበሌዎች፣ 69 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 655 ቀበሌዎችን ይይዛል፡፡ በ2017 ዓ.ም የትንበያ መረጃ መሰረት 3,317,077 ህዝብ የሚኖር ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 53.89% የሚሆነው በምርታማ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን የልማት ቀጠናው የህዝብ ጥግግት 99 ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ የሚኖሩ ቢሆንም ከወረዳ ወረዳ የህዝብ ጥግግቱ የተለያየ ነው፡፡

21. የምስራቅ አማራ የልማት ቀጠና ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 20,562.23 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን የክልሉን 11.35% ይሸፍናል፡፡ የልማት ቀጠናው 24 ወረዳዎች፣15 ከተማ አስተዳደሮች፣ 3ሪጆ-ፖሊታን ከተሞች (ወልድያ፣ኮምቦልቻ እና ደሴ)እና

526 የገጠር ቀበሌዎች፣ 121 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 647 ቀበሌዎችን ያካትታል፡፡ በ2017 ዓ.ም የትንበያ መረጃ መሰረት 3,661,930 ህዝብ የሚኖር ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 57.64% የሚሆነው በምርታማ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን የልማት ቀጠናው የህዝብ ጥግግት 178 ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ የሚኖሩ ቢሆንም ከወረዳ ወረዳ የህዝብ ጥግግቱ የተለያየ ነው፡፡

22. የደቡብ ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 32,550.95 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን የክልሉን 17.97% ይሸፍናል፡፡ የልማት ቀጠናው 38 ወረዳዎች፣22 ከተማ አስተዳደሮች፣ 1 ሪጅ ፖሊታን ከተማ (ደብረ ማርቆስ) እና 938 የገጠር ቀበሌዎች፣176 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 1,114 ቀበሌዎችን ያካትታል፡፡ በ2017 ዓ.ም የትንበያ መረጃ መሰረት 6,598,940 ህዝብ የሚኖር ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 56.95% የሚሆነው በምርታማ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን የልማት ቀጠናው የህዝብ ጥግግት 202 ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ የሚኖሩ ቢሆንም ከወረዳ ወረዳ የህዝብ ጥግግቱ የተለያየ ነው፡፡
23. የጣና የልማት ቀጠና ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 16,487.86 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን የክልሉን 9.1% ይሸፍናል፡፡ የልማት ቀጠናው 13 ወረዳዎች፣ 6 ከተማ አስተዳደሮች፣ 3 ሪጅ ፖሊ.ታን ከተሞች (ጎንደር፣ደብረ ታቦርና ባህርዳር) እና 410 የገጠር ቀበሌዎች፣105 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 515 ቀበሌዎችን ያካትታል፡፡ በ2017 ዓ.ም የትንበያ መረጃ መሰረት 4,135,372 ህዝብ የሚኖር ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 57.66% የሚሆነው በምርታማ የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን የልማት ቀጠናው የህዝብ ጥግግት 250 ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ የሚኖሩ ቢሆንም ከወረዳ ወረዳ የህዝብ ጥግግቱ የተለያየ ነው፡፡



## የልማት ቀጠናዎች እምቅ ሀብቶቻቸው

24. አማራ ክልል እምቅ በከርሰ ምድርና በገጸ ምድር የበለፀጉ ውሀማ አካላት፣ በክረምት፣ በበልግና በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት፣ ምቹ የአየር ንብረት ሁኔታዎች እና የመሬት አቀማመጥ፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የቱሪዝም አማራጮች፣ የእንሰሳትና ዓሳ ሀብት፣ የሰብል ልማት፣ አምራች የሰዉ ሀይል እና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች (ታሪካዊ፣ የተፈጥሮ፣ አርኪኦሎጂካዊ እና ሃይማኖታዊ) መዳረሻዎች በብዛት በመገኘታቸው ለውጭ እና ለአገር ውስጥ ጎብኚዎች ምቹ የሆነ ክልል ነው፡፡
25. ውሃ ለመጠጥ፣ ለመስኖ ልማት፣ ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት፣ ለብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ለመጓጓዣ፣ ለቱሪስት መስህብነትና ለመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያገለግላል፡፡ ስለሆነም ወደፊት የሚታሰበውን ዘላቂ ልማት ከማረጋገጥ አንጻር ያለንን የውሀ ሀብት እምቅ አቅም መለየትና በዘላቂነት መጠቀም የሚቻልበትን ስልት መቀየስ አስፈላጊ ነው። ከአገሪቱ የገጽ ምድር የውሃ ሀብት የአማራ ክልል ከፍተኛውን/60 በመቶ/ ሚሆነውን የውሃ መጠን ያመነጫል፡፡ ክልሉ በአባይ፣ ተከዜና አዋሽ ተፋሰሶች ውስጥ የሚገኙ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ነው፡፡ በዓለም በርዝመቱ የሚታወቀውን አባይን ጨምሮ ተከዜ፣ በለስ፣ አንገርብ፣ አትባራ፣ ጓንግ፣ አይማ፣ ሚሌ፣ በሽሎ፣ ከሰም እና ጀማ የመሳሰሉ ትልልቅ ወንዞች በክልሉ ይገኛሉ፡፡ ክልሉ በአጠቃላይ 44.8 ቢሊዮን ሜትር ኩዩቢክ የገጸምድር ውኃና ሰፊ የከርሰ ምድር ውኃ ባለቤት ሲሆን ከተፋሰሶች ዉስጥም የአባይ ተፋሰስ 60.46%፣ የተከዜ ተፋሰስ 27.56%፣ የአዋሽ ተፋሰስ 10.22%፣ እና የጎሉና /ደረቅ ተፋሰስ/ 1.76% የክልሉን ስፋት ይሸፍናሉ፡፡ እንደ ውሀና ኢነርጂ ቢሮ መረጃ መሰረት 1677 የሚደርሱ ዓመቱን በሙሉ የሚፈሱ እና 297 በክረምት ብቻ የሚፈሱ ወንዞች በክልሉ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም በዓመት ወደ 35 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ይገኛል፡፡
26. ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት በተገኘው መረጃ መሰረት በስድስቱ የልማት ቀጠናዎች ዉስጥ 17 የአፈር አይነቶች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ የአፈር አይነቶች በእያንዳንዱ የልማት ቀጠና የቁጥር እና የአፈር አይነት ልዩነት ያላቸዉ ሲሆን መካከለኛዉ አማራ የልማት ቀጠና 11 አፈር አይነቶች፣ ምስራቅ አማራ የልማት ቀጠና 13 የአፈር አይነቶች፣ ሰሜን ምዕራብ አማራ 8 የአፈር አይነቶች፣ ደቡብ ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና 11 የአፈር አይነቶች ይገኙበታል፡፡
27. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ ትንበያ መሠረት በ2017 ዓ/ም በክልሉ 11,884,006 (49.78 በመቶ) ወንድ እና 11,994,993 (50.23 በመቶ) ሴት በድምሩ 23,878,999 ህዝብ ይኖራል ተብሎ ይገመታል፡፡ በክልሉ ያለ የህዝብ ቁጥር ሲታይ እጅግ በጣም ግዙፍና ትልቅ የልማት አቅም ሊሆን የሚችል አምራች የሰው ሀይል ነው፡፡ ክልሉ ወጣት የሚበዛበት የእድሜ ስብጥር ያለው ሲሆን በ2017 ዓ.ም ከአጠቃላይ ህዝቡ አምራች ሰብዓዊ የሰው ሀብት 15 እስከ 64 የእድሜ ክፍል 56.32 በመቶ (13,449,286) የሚሆነውን ይይዛል፡፡ይህ ሀይል ትኩስ ሀይልና የልማት አለኝታ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ክልሉ የቀጣይ የስነ ህዝብ ትሩፋት ተጋሪ በመሆኑ ይህም እንደ አንድ የእድገት አቅም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
28. ማዕድን ለአንድ ሀገር የገቢ ምንጭነት፣ ለኢንዱስትሪ ግብአትነት፣ ለመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለዉጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን ሃገራችንም ከግብርና መርህ ወደ ኢንዱስትሪ መርህ ኢኮኖሚ በምታደርገው ጉዞ ቀላል የማይባል ድርሻ አለዉ፡፡ በክልላችን በርካታ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ የኢንዱስትሪ፣ የከበሩ፣የብረትና ብረት ነክ፣የኮንስትራክሽንና የኢነርጂ ማዕድናት እንዳሉ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የአብክመ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ የክልሉን የማዕድን ሃብት ክምችት በጥናት በመለየት ልማት ላይ እንዲዉል እያደረገ ይገኛል፡፡

29. በመሆኑም በጥናቱ መሰረት አሲዳማ አፈርን ለማከም ጥቅም ላይ የሚውለወን ኖራ ድንጋይ ጨምሮ እንደ ጀሶ ድንጋይ (ጂፕሰም)፣ ሲልካ ሳንድ፣ ፑሚስ፣ ካኦሊን፣ ሸክላ አፈርና የመሣሠሉት ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ማዕድናት በሰ/ሸዋ፣ በደቡብ ወሎና ምስ/ጎጃም አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል እንደ ኦፓል፣ አምበር እና ጃስፐር ያሉ የከበሩ ማዕድናት በሰሜን ሸዋ፣ በደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ወሎና ምዕራብ ጎጃም በሚገኙ በርካታ ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ ብረት ነክ ማዕድናትን በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች በዋግኽምራ፣ ምስራቅ ጐጃም፣ደቡብ ወሎ እና ምዕራብ ጎንደር ዞን አካባቢዎች እንዳለ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪ በዋግ ህምራ ዞን አበርገሌ፣ በአዊ ዞን ቅላጅ አካባቢ እና በወልቃይት ሰቲት ሁመራ ዞን ወልቃይት እና ቃፍታ ሁመራ ወረዳዎች የወርቅ ክምችት መኖሩ ታዉቋል፡፡ በክልሉ ከሚገኙ ከኢነርጂ ማዕድናት ዉስጥ የድንጋይ ከሠል በጭልጋ፣ በውጫሌ እና በሙሽ ሸለቆ የክምችት መጠን እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም አይል ሼል /ነዳጅ አዘል አለት/ በመርሳ አካባቢ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ አንኮበር እንዳለ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪ ለግንባታ የሚያገለግሉ እንደ እምነበረድ፣ ግራናይት፣ ሳንድስቶን፣ ነጭ ድንጋይ፣ ጥቁር ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ቀይ አሸዋ እና ለዘመናዊ ህንፃ ማስዋቢያ በጣም ተፈላጊ የሆነው የጥርብ ድንጋይ በክልሉ አዊ፣ምዕራብ ጎጃም፣ምስራቅ ጎጃም እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች በስፋት ይገኛሉ፡፡

30. የቱሪዝም ልማት የኢኮኖሚ እድገትን ለማሳደግ፣ ድህነትን ለመቅረፍ፣ የስራ እድል ለመፍጠር እና የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል እንደ አንድ ጠቃሚ ስትራቴጂ ጥቅም ላይ ይውላል።የአማራ ክልል በሁሉም የቱሪዝም ዓይነቶች የተፈጥሮ፣ ቅርስ ወይም የባህል ቱሪዝም በበቂ ሁኔታ የበለፀገ ነው፡፡ በክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በመንከባከብ፣ በማስተዋወቅ እና በማስፋፋት ለቱሪዝም ዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠትና ከቱሪዝም ዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ማግኘት እና ማህበራዊ ልማትን ማረጋገጥ ይቻላል።

31. የአማራ ክልል ሠፊ የቆዳ ስፋት ያለውና በዚህም የተለያዩ የአየር ንብረቶች፣ የመልከዓ ምድር አቀማመጥና ብርቅዬና ድንቅዬ የዱር እንስሳት፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች፣ ገዳማትና አድባራት፣ሀይቆች፣ፍል ዉሀዎች፣ፓርኮች፣የትግል ቦታዎች፣ ባህላዊ እሴቶች እና ሌሎች የቱሪስት መስህብ ሃብቶች ያሉት አካባቢ ነው። ከማይንቀሳቀሱ ቅርሶች መካከል አገሪቱ በዩኔስኮ ለዓለም ቅርስነት ካስመዘገበቻቸው ቅርሶች መካከል የላል-ይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣የጭስ አባይ ፏፏቴ፣የጎንደር ቤተመንግስታት፣ጮቄ ምርጥ የቱሪዝም መንደር፣የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ እንዲሁም በዙሪያውና በውስጡ በርካታ የቱሪስት መዳረሻ ቅርሶችን/አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት/ እና ብዝሃህይወቶችን ያቀፈው የጣና ሃይቅና አካባቢው በክልሉ ይገኛሉ፡፡ ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል የጥምቀት በዓል በሁሉም የክልሉ አካባቢዎችና በተለይም በጎንደር በስፋት የሚከበር፣ የመስቀል በዓል በደቡብ ወሎ በግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ቤተክርስቲያን እንዲሁም የልደት በዓል በተለይም በላል-ይበላ የሚከበሩ የክልሉም መስህቦች ናቸው፡፡ በክልሉ ከሚገኙ የዱር እንስሳት መካከል ዋልያ፣ ቀይቀበሮ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ የምኒሊክ ድኩላ፣ ሚዳቋ፣ነብር፣ አቦሸማኔ፣ ቆቅ የተለያዩ ዝርያ ያላቸው አዕዋፋት እና ሌሎችም ይገኙበታል።

## ስትራቴጅክ ጉዳዮች

1. የፕሮጀክቶች ፍትሃዊነትና የተደራሽነት ችግር

2. የፕሮጀክት አስተዳደር (የቅልጥፍናና ውጤታማነት) ችግር

3. የመፈጸምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት

## የትኩረት መስኮች

1. ፍትሃዊነት እና ተደራሽነት

2. ጥራት፣ ምርታማነትና ቅልጥፍና

3. ፀጋን መሰረት ያደረገ የመሰረተ ልማት አቅርቦት

4. የመፈጸምና ማስፈጸም አቅም ግንባታ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

32. በክልሉ የሚገነቡ መሰረተ ልማቶችን አቅርቦት ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፣ የክልሉን እምቅ ሀብቶች ወይም ፀጋዎች መሰረት በማድረግ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ስታንዳርዳቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ በማድረግ የመሰረተ ልማት ሃብቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ምቹ እና እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የመሰረተ ልማቶች ዝርጋታ ፀጋንና በሚያበረክቱት ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸው መሰረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ማድረግ፣ ፍትሃዊ የተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀምን ማረጋገጥ እና በመሰረተ ልማቶች ስርጭት የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ማስወገድ የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዓላማ**

የክልሉ መሠረተ ልማት ስርጭት፣ ፍትሀዊ እና ተደራሽ እንዲሆን በስነ-ምድር መረጃ እና እቅድ ምድር ነክ በማድረግ ፕሮጀክቶች ውጤታማ፣ አስተማማኝና ጥራት ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ፣

## ዝርዝር ዓለማዎች

- ኢኮኖሚያዊ ቅልጥፍናን ለማሳደግ እና ሀገር አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማጠናከር
- ለክልላዊ ውህደት እና ትስስር ሚዛናዊ የስድስቱ ቀጠናዎችን ልማት ማሳደግ
- ለዘላቂ ልማት የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ለማመቻቸት
- በከተማ እና በገጠር ለኑሮ ምቹ እና ተግባራዊ የሰው አሰፋፈር መፍጠር

## ዋና ዋና ግቦች

33. የክልሉን አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 34,077.72 ኪ.ሜ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 53,242.81 ኪ.ሜ ለማሳደግ በፌዴራል መንግስት የአስፋልት መንገድ 4,880 ኪ.ሜ እና ኤክስፕረስ ዌይ (የፍጥነት መንገድ) 873 ኪ.ሜ፣ በክልሉ የካፒታል በጀት የጠጠር መንገድ 4,232.09 ኪ.ሜ፣ በወረዳ አስ/ር ምክር ቤት በጀት ድጋፍና በህብ/ሰቡ ተሳትፎ 3,130 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ፣ በከተሞች የሚገነባ አስፋልት መንገድ ግንባታ 102 ኪ.ሜ፣ በከተሞች የሚገነባ ጠጠር መንገድ ግንባታ 4,360 ኪ.ሜ ይገነባል፡፡ በመንገድ ተደራሽ ያልሆኑ ቀበሌዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ቀበሌን ከቀበሌ፣ ወረዳን ከዋና መንገድ ማገናኘት በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 3,004 ቀበሌዎች በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3,383 ቀበሌዎች ለማድረስ ይሰራል፡፡ በተጨማሪ በመደበኛና በወቅታዊ ጥገና ዘዴዎች 75,189.01 ኪ.ሜ የመንገድ ጥገና ይካሄዳል፡፡

34. በዕቅድ ዘመኑ የተለያዩ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 249 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 344 ለማሳደግ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ መዳረሻዎችን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 5 በ2022 በጀት

ዓመት ወደ 9 ለማሳደግ፣ 3 አውሮፕላን ማረፊያዎች ወደ ዓለም አቀፍ በረራዎች እንዲያድጉና አቅማቸዉ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡በተጨማሪም የክልሉን የባቡር መንገድ ግንባታ በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 335 ኪ.ሜ በ2022 በጀት ዓመት 620 ኪ.ሜ ለማድረስ የአዋሽ-ኮምቦልቻ-ሃራ ገበያ 370 ኪ.ሜ የባቡር መንገድ ግንባታ የማጠናቀቅና ከወልዲያ-ወረታ-መተማ የባቡር መንገድ 500 ኪ.ሜ ውስጥ 250 ኪ.ሜ የመገንባት ስራ ይሰራል፡፡

35. የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማቶችን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 2 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 74 ማሳደግ እና የኮምቦልቻና የወረታ ደረቅ ወደቦች በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የማስፋፊያ ግንባታ ይደረግላቸዋል፡፡
36. በዕቅድ ዘመኑ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 6,148 ወደ 6,481 በማሳደግ የሚለማውን መሬት ከ260,269 ሄ/ር ወደ 464,177 ሄ/ር ለማድረስ በክልሉ 333 አዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች ይገነባሉ፡፡ በተመሳሳይ በፌዴራል መንግስት የተጀመሩ ከ32,000 ሄ/ር መሬት በላይ የሚያለሙ 7 ሜጋ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ እንዲጠናቀቁ ይደረጋል፡፡
37. በሌላ በኩል ክልላዊ የመጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 77.96% በ2022 በጀት ዓመት ወደ 90% ለማድረስ የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 77.85% በ2022 በጀት ዓመት ወደ 90% ለማድረስ 12,748 የገጠር አነስተኛ የውሃ ተቋማት ግንባታ፣ 818 ባለመስመር የቀበሌ አገናኝ የዉሃ ተቋማት ግንባታ፣ 4,826 የመለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ እና 573 የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ እንዲሁም የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በ2017 በጀት አመት ከተደረሰበት 78.07% በ2022 በጀት ዓመት ወደ 90% ለማድረስ 112 የከተማ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ እና 199 የከተማ መጠጥ ዉሃ ግንባታ የማከናወን ስራ ይሰራል፡፡
38. በክልሉ 1 የሳይንስና ቴክኖሎጅ ፓርክ እንዲገነባ ይደረጋል፡፡ በባህር ዳር እና ደሴ ከተሞች የእስማርት ሲቲ ፕሮጀክት ግንባታን የማጠናቀቅና በ6 ሪጅኦፖሊታንት ከተሞች አዲስ የእስማርት ሲቲ የቴክኖሎጅ መሰረተ ልማቶች እንዲሁም በ8 ሪጅኦፖሊታንት እና 6 የዞን ከተሞች የጥገና ማዕከላት ይገነባሉ፡፡ በ9 የዞን ከተሞች የቴክ-እስታርታፕ ማዕከላት፣ 38 የወረዳኔት ማዕከላት እና 68 የማህበረሰብ ቴክኖሎጅ መረጃ ማዕከላት፣ 17 ደረጃ-1 የስልጠና ማዕከላት፣ 18 የዞን እና ሪጅኦፖሊታንት ከተሞች የወጣቶች ሳይንስ ካፌ ይገነባሉ፡፡ የፍትህ ስርዓቱን አገልግሎት ለማሻሻል 165 ነባር የወረዳኔት ማዕከላትን እና 87 የማህበረሰብ የቴክኖሎጅ መረጃ ማዕከላትን በዘመናዊ የቴክኖሎጅ ግብዓት ይገነባሉ፡፡
39. ወደፊት ከገጠር ወደ ከተማ የሚኖረውን ፍልሰት ታሳቢ ያደረገና የሚመጣውን ፈጣን ከተሜነት ለማስቀጠል ሳይንሳዊና ዕምቅ ሃብት ላይ የተመሰረቱ 9 ዘመናዊ የከተማ ማዕከሎች (የእኔ ዘመን ትውልድ ከተሞች) በመፍጠር ቀጣይነትና የማይበገር የኢኮኖሚ ዕድገት ለመፍጠር ይሰራል፡፡
40. በክልሉ የትምህርት ቤቶችን ቁጥር በ2015 በጀት ዓመት ከደረሰበት 10,853 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 17,566 ለማሳደግ 5,650 ቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ 285 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ፣ 772 ሁለተኛ ደረጃ እና 6 ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ 6,713 ትምህርት ቤቶች የመገንባት ስራ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም 10,129 የመማሪያ ክፍሎች ማስፋፊያ፣ 150 ልዩ ፍላጎት ለሚሹ ተማሪዎች የአካቶ ትምህርት ማዕከል እንዲሁም 22 ልዩ ትምህርት ቤቶች ይገነባሉ፡፡ በሌላ በኩል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን አሁን ካሉበት 126 ተጨማሪ 28 በመገንባት ወደ 154 የማሳደግ፣ መሰረተ ልማት የማሟላት እና በነባር የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች 341 ወርክ ሾፖችን የመገንባት ስራ ይሰራል፡፡ የግብርና ምርምር ማዕከላት አሁን ካሉበት 7 ተጨማሪ 2 በመገንባት ወደ 9 ማሳደግ እንዲሁም ለ3 ነባር የግብርና ኮሌጆች መሰረተ ልማት የማሟላት ስራ ይሰራል፡፡
41. በክልሉ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 48.7% በ2022 ወደ 74% ለማድረስ 8 ነባር ሆስፒታሎች እና 2 የአዕምሮ ማገገሚያ ሆስፒታሎች ማጠናቀቅ፣ 5 አዲስ ኢመርጀንሲ ሆስፒታል፣ 3 አዲስ የአእምሮ ማገገሚያ ሆስፒታል፣ 5 አዲስ የእናቶችና ህፃናት ማስፋፊያ፣ 60 አዲስ የመጀመሪያ ደረጃ

ሆስፒታሎች፣ 2,196 አዲስ የቤዚክ ጤና ኬላዎች፣ 518 አዲስ የኮምፕርሄሲቭ ጤና ኬላዎች፣ 66 የጤና ጣቢያ፣ 6 መድሃኒት የተላመደ ቲቪ ህክምና ማዕከል እና 4 የደም ባንኮች የሚገነቡ ሲሆን ለ5 የጤና ሳይንስ ኮሌጆች የማስፋፊያ ስራ ይሰራል፡፡

42. ለ22 የኢንዱስትሪ መንደሮች 142 ኪ.ሜትር መንገድ፣ 5 ድልድይ፣ 19 ነባርና 13 አዲስ የመብራት መስመር ዝርጋታና ትራንስፎርመር ተከላ ስራዎች እንዲጠናቀቁ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም 8 የኢኮኖሚ ዞኖች (የኮንስትራክሽን ግብዓት፣ የኬሚካል ውጤቶች፣ የተቀናጀ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስተሪ፣ ለደን ውጤቶች፣ ለእንስሳትና የቆዳ ውጤቶች፣ ለጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ፣ ለማዕድናት ውጤቶች እና ለቅመማቅመም ኢንዱስትሪ) የቦታ ልየታና የጥናት ዲዛይን፣ ግንባታ እና መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡
43. በዕቅድ ዘመኑ የማዕድን ፋብሪካዎችን ቁጥር በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 18 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 50 ለማሳደግ 2 የመለስተኛ ሲሚንቶ፣ 10 የግራናይት፣ 6 የጅፕሰም፣ 2 የእምነ በረድ፣ 1 የሴራሚክ፣ 1 የብረት ማቅለጫ፣ 1 የድንጋይ ከሰል ማዕድን ማጣሪያ፣ 1 የኖራ፣ 1 የጡብ፣ 1 የቀለም፣ 1 የብርጭቆ፣ 1 የወርቅ ማውጣት ፕሮሰሲንግ፣ 1 የኮንክሪት ፖል፣ 1 የባዛሌት ፋይበር ፋብሪካ እና 2 ለከበሩ ማዕድናት እሴት መጨመሪያ ማዕከል የሚቋቋም ሲሆን የራስጌና የግርጌ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የመሠረተ ልማት አቅርቦት ክፍተት እንዲሟላ ይደረጋል፡፡
44. ከተማ ላይ የባለ መስመር የፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃና ማጣሪያ ግንባታ፣ በ8 የሪጅዮፖሊታን ከተማዎች የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃና ማጣሪያ እንዲሁም በ83 ሌሎች የክልሉ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃና ማጣሪያ ግንባታ፣ የቆሻሻ መለያ ሲስተም መዘርጋት፣ ዘመናዊ የቆሻሻ መጣሪያ ቦታ ማመቻቸት እና ቆሻሻዎች እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ ሲሰተም ይገነባል፡፡

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

1. ፍትሃዊነት፤ በመሰረተ ልማቶች ስርጭት የክልሉን ህዝብ ፍትሃዊና እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መንገድ እንዲዘረጉ ማድረግ፤ ጸጋንና የመልማት አቅምን እንዲሁም ለክልሉ ማክሮ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ዘርፎችን በስድስቱ የልማት ቀጠናዎች መሰረት ያደረገ ፍትሃዊ የመሰረተ ልማት ዝርጋታን ማረጋገጥ፣
2. ስፓሻል መረጃዎችን ጥቅም ላይ ማዋል፤ ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋገጥ የክልሉን ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና ድህነትን ለመቀነስ ክልሉ በስድስት የልማት ቀጠናዎች ተዋቅሯል፡፡ በመሆኑም በክልሉ የሚተገበሩ መሰረተ ልማቶች መሬት ለማስነካትና ለመተግበር በቦታ በማመላከትና አስተሳስሮ በመስራት የመሰረተ ልማት ስርጭትን፣ ፍትሃዊነትንና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣
3. ተደራሽነት፤ የክልሉን የመሰረተ ልማት አውታሮች ስርጭት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣
4. ተጠያቂነት፤ የመሰረተ ልማት አስተዳደርን የሚያሳልጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የህግ ማዕቀፎች እና ሌሎች የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በተለይ በዘርፉ የተንሰራፋውን ሌብነት፣ የመሰረት ልማቶች ዝርፊያና ስርቆት ማስቀረት እንዲሁም ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ፣ በጀትና ጥራት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ተጠያቂነትን ማስፈን፣
5. የመፈፀምና ማስፈፀም አቅም፤ የመሰረተ ልማት ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የመፈጸምና ማስፈጸም ክፍተት ያለበት ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም በፕሮጀክት ባለቤት ተቋማት፣ በተቋራጮች፣ በአማካሪዎች፣ በአጋር አካላትና በህብረተሰቡ ያለውን የአቅም ክፍተት የጥናትና የምርመር ተቋማትን ማጠናከርና ሌሎች የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም አቅማቸውን ማሳደግ የሚሉት ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ሥልቶች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

# ልዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች

### የዘርፉ ሚና

1. በሰሜኑ ጦርነት እና በተለያዩ የውስጥ ግጭቶች በክልላችን ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት የደረሰ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በወረራውና በግጭቱ ምክንያት በበርካታ የክልሉ አካባቢዎች ላይ ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና አካባቢያዊ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ብዛት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ለአስከፊ ድህነት እና ኢ-ሰብአዊ ሁኔታ በመዳረጋቸው የተነሳ ክልሉ ከደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት የሚያገግምበትንና መልሶ የሚገነባበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

2. ስለሆነም የዘርፉ ሚና በጦርነቱና በውስጥ ግጭት የደረሱ ጉዳቶችን በጥናት በመለየት፤ በመሰነድ እና በማሳተም በክልሉ በህዝብ ላይ የደረሰዉ ሰብአዊ፣ ቁሳዊ እና አካባቢያዊ ውድመት በትክክል እንዲታወቅ ማድረግ፤ በሙዚየም ተሰንዶ ለታሪክ ፍርድ እና ለተተኪው ትውልድ መማሪያ እንዲቀመጥ ማድረግ፣ ዓለም አቀፉ ማኅበረ-ሰብና ተቋማት በክልሉ ህዝብ ላይ የደረሰውን ሰብዓዊ፣ ቁሳዊ እና አካባቢው ሀብት ጉዳት በአግባቡ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤ የደረሰውን ዘረፋና ውድመት በመለየት በመልሶ ማቋቋሙ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎት ሥራዎች በፍጥነት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ማድረግ፤ ክልሉን መልሶ ለማቋቋም፣ ለመገንባት፣ በዘላቂነት ለማልማት እና ለማበልጸግ የሚያስፈልጉትን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂዎች መንደፍ፤ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አሳትፎ የተቀናጀና የተናበበ የመልሶ ማቋቋም ሥራ እንዲሠራ እንዲከናወን በማድረግ ጉዳት የደረሰባቸውን የክልሉን አካባቢዎች በዘላቂነት መገንባት፤ ባጋጠመው ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት ምክንያት የደረሰውን የሥነ-ልቦና ስብራት ለመጠገን የሚያስችል ጠንካራ የሥነ-ልቦና ግንባታ ሥራ ማካሄድ፤ ከሌሎች ተቋማትና ተባባሪ አካላት ጋር በመሆን የተፈናቀሉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ቀያቸው መመለስና ማቋቋም እንዲሁም ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ለማቋቋምና ለመገንባት የሚያስችል ሀብት ከተለያዩ አካላት በማፈላለግና በማሰባሰብ ክልላዊ አቅምን ማጠናከር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

### ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

3. በዓለማችን የእርስ በእርስ ግጭቶች እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ ከነበረው በ2000ዎቹ መጀመሪያ ላይ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም እ.ኤ.አ ከ2012 ወዲህ ግን እየጨመረ የመጣ መሆኑን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግጭቶች የተጀመሩት እ.ኤ.አ በ2011 በአረብ አገራት አመፅ ሲሆኑ ግጭቱ የጀመረባቸው አገራት ሊቢያ፣ ሶሪያ እና የመን ነበሩ። ከዚያም እ.ኤ.አ በ2020 በአዘርባጃን-አርሜኒያ፣ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ የትግራይ ክልል፣ እ.ኤ.አ በ2021 ደግሞ በማያንማር፣ እ.ኤ.አ በ2022 በሩሲያና በዩክሬን እና በ2023 በሱዳን እና በጋዛ ግጭቱ ተስፋፍቷል። በመሆኑም በዓለም ዙሪያ በጦርነት የሚሞቱ፣ ከቤታቸው የሚፈናቀሉ እና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር ባለፉት አሥርተ ዓመታት ከነበረው ቁጥር እንዲጨምር አድርጎታል (International Crisis Group, 2024)።

4. በዓለማችን በጣም ድሃ የሆኑ አገሮች ለእርስ በእርስ ግጭት በጣም የሚዳረጉ ሀገሮች መሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የማክሮ ኢኮኖሚያዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በትጥቅ ግጭት ውስጥ ያሉ ሀገሮች ለኢኮኖሚ ውድቀት የተጋለጡ መሆናቸውን ያስረዳል። በአገራት ደረጃ ግጭቶች በአማካይ በነፍስ ወከፍ የሀገር ውስጥ ምርት በ10 በመቶ እንደሚቀንስ ጥናቶች ያመላክታል። ይህ ኢኮሚያዊ ዕድገት መቀነስ ግጭቱ ካበቃ በኋላም እንደሚቀጥልና የበለጠ

የኢኮኖሚ ውድቀት ሊያስከትል እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለአብነት ያህል የዓለም ባንክ ባካሄደው ዝርዝር ጥናት መሰረት እ.ኤ.አ በ2017 በተካሄደው የሶሪያ አረብ ሪፐብሊክ ግጭት ላይ እ.ኤ.አ ከ2011 እስከ 2016 መጨረሻ ድረስ በግጭቱ ሳቢያ በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ላይ 226 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ መድረሱን ያመላክታል፡፡ ይህም ኪሳራ እ.ኤ.አ በ2010 የሶሪያ GDPን አራት እጥፍ ገደማ ነው(World Bank 2020)።

5. የእርስ በእርስ ጦርነቶች በኢኮኖሚው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት በሁለት ደረጃዎች ሲሆን እነሱም በጦርነቱ ወቅት እና ከጦርነቱ በኋላ ነው። በግጭት ወቅት በቀጥታ ለማምረት ስራ ሊውል የሚችለውን ሀብት እንዲወድም በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ከዚህም በተጨማሪ በእርስ በእርስ ግጭት የተጎዱ አገሮች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በምርት ወጪዎች መጨመርና በትራንስፖርት አለመረጋጋት በተዘዋዋሪ ጉዳት ይደርስባቸዋል። የሚከሰቱ ጉዳቶች በአካባቢ አገራት ላይም ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ስለሆነም በኢኮኖሚ ልማት ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ድህነትን እንዲባበስ፣ ሰብአዊ ድጋፍ እንዳይኖር እና ኢንቨስትመንቶች እንዲቀንስ ያደርጋል። በተጨማሪም የእርስ በእርስ ግጭቶች በትምህርት እጦት፣ በሞት፣ በአካል ጉዳት እና በአእምሮ ህመም ምክንያት የሰራተኞችን ምርታማነት ይጎዳሉ (የዓለም ባንክ፣ 2020)። በተመሳሳይ ግጭቶች ከተማዎችን እና መሰረተ ልማቶችን በማውደም፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በማቋረጥ፣ ኢንቨስትመንትን በመቀነስ እና ለልማት የሚውለውን የመንግስት ወጪን ለጦርነት እንዲውል በማድረግ በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል(Thai-Ha Le, etal, 2022)።
6. በሌላ በኩል በአለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ በ2006 278 ግጭቶች የተከሰቱ ሲሆን ከአስር ዓመት በኋላ ደግሞ ወደ 402 ከፍ ብሏል። እ.ኤ.አ በ2006 ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ግጭቶች የተከሰተበት አህጉር እስያ ስትሆን አፍሪካም በሁለተኛ ደረጃ ላይ ነበረች። እ.ኤ.አ በ2016 በዓለም አቀፍ ደረጃ 22.5 ሚሊዮን ሰዎች በግጭት ምክንያት ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ በሶሪያ ጦርነት 6.3 ሚሊዮን ሰዎች የተፈናቀሉ ሲሆን 5.5 ሚሊዮን ደግሞ ስደተኞች ሆነዋል። በተጨማሪም በእርስ በእርስ ግጭት በአፍጋኒስታን፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሶማሊያ፣ በሱዳን፣ በፓኪስታን፣ በሊባኖስ፣ በኢራን እና በኡጋንዳ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለስደት ዳርጓል (International Journal of Research in Business Studies and Management, 2019)::
7. እንደ UNHCR ሪፖርት እ.ኤ.አ በ2023 መጨረሻ 117.3 ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎች  በግጭት፣ በዓመፅ፣ በሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና በሌሎች ስርዓት መጓደል ክስተቶች ምክንያት በግዳጅ ተፈናቅለዋል። ይህም እ.ኤ.አ በ2022 ከነበረው ጋር ሲነፃፀር የተፈናቃዮች ቁጥር 8 በመቶ (8.8 ሚሊዮን) መጨመሩን የሚያመለክት ሲሆን ባለፉት 12 ዓመታት በተከታታይ በየዓመቱ መፈናቀል እየጨመረ መምጣቱን መረጃው ያሳያል። በዓለም ዙሪያ ከ69 ሰዎች አንዱ ወይም ከጠቅላላው የዓለም ህዝብ 1.5% በግዳጅ ይፈናቀላል ተብሎ ይገመታል፡፡ ይህም ከአስር ዓመት በፊት ከነበረው ከ125 ሰዎች አንዱን የመፈናቀል መጠን ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ ማደጉን ያሳያል። በተመሳሳይ በሪፖርቱ እ.ኤ.አ በ2024 መጨረሻ ላይ የተፈናቀሉ ሰዎች ብዛት ከ120 ሚሊዮን በላይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።
8. በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ የመጣ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2023 መጨረሻ 75.9 ሚሊዮን ሰዎች በሀገር ውስጥ ተፈናቅለዋል፡፡ ይህም በ2022 ከነበረው 71.1 ሚሊዮን ከፍ ያለ ነው፡፡ በዋናነት በአደጋ፣ በግጭት ወይም በሙብት ጥሰት ምክንያት ቀያቸውን ጥለው ለመሰደድ የተገደዱ ሰዎች ለዓመታት ተፈናቅለው ከሚኖሩ ስደተኞች ጋር በመቀላቀል በመጠለያ ካምፕ የሚኖሩ ተፈናቃዮችን ቁጥር እየጨመረ እንዲሄድ በማድረጉ ለአዲሶቹም ሆነ ለነባሮቹ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ተግዳሮት ሆኗል፡፡ ሱዳን፣ ሶሪያ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ኮሎምቢያ እና የመን በዓለም ላይ ከሚገኙት ተፈናቃዮች ግማሽ ያህሉን ያስተናግዳሉ። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ፣ በኮንጎ፣ በሱዳን እና በዩክሬን ግጭቱ እየተባባሰ በመምጣቱና ረዘም ላለ ጊዜ በመቆየቱ ምክንያት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር እንደሚጨመር ይገመታል (IDMC, 2023)፡፡

9. በአብዛኛው ግጭት የመንግሥት አቅም ደካማነት ምልክትም ሆነ መንስኤ ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡ ይህም ደካማ የሆነ ኢኮኖሚ እንዲኖር በማድረግ ድህነትን ለመቀነስ በሚረዱ እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል (የዓለም ባንክ፣ 2020)። ስለሆነም በዓለም ላይ የሚደርሱ ግጭቶችን ለመቀነስና ለመከላከል ቁርጠኛ የሆነ መንግስታትና አስተዳደር እንዲኖር በማድረግ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣትና የህዝቦችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ድህነትን መቀነስ፣ ሙስናን መከላከል፣ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መልኩ መፍታት፣ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና መገንባት፣ ስደተኞችን ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በማድረግ ወደ መደበኛ ኑሯቸው እንዲመለሱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## አህጉራዊ ሁኔታ

10. ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ በአፍሪካ ውስጥ ትልቅ ፈተና ሆኖ የቆየው ግጭት ነው። ምንም እንኳን በአፍሪካ እ.ኤ.አ ከ1990 ዎቹ በኋላ ያነሰ ግጭት የነበረ ቢሆንም እ.ኤ.አ ከ2000 አጋማሽ ጀምሮ በአህጉሪቱ ግጭቶች እንደገና ተቀስቅሰዋል። ስለሆነም እ.ኤ.አ በ2019 ከ30 በመቶ በላይ የሚሆኑ የአፍሪካ አገራት በግጭት ውስጥ እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በግጭት ምክንያት የሚደርስ ከፍተኛ ሰብዓዊ ጉዳት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ኪሳራም ያስከትላል። ይህም ገቢን በመቀነስ፣ የመከላከያ ወጪን በመጨመር እና ለማህበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ልማት የሚውለውን ሀብት በማዞር በአገሮች ላይ ከባድ ኪሳራ ያስከትላል። ከዚህ በተጨማሪ ግጭቶች በዋነኛነት ያለመረጋጋት መንስኤዎች ከመሆናቸው ባሻገር የኢኮኖሚያዊ መዘዞችን የሚያስከትሉ እንደሆኑ በሰፊው ይታመናል። በሌላ በኩል ግጭቶች የሰው ሕይወት መጥፋት፣ የንብረትና የመሰረተ ልማት ውድመት እንዲሁም የማህበራዊ መስተጋብር መናጋትን ያስከትላሉ፡፡ እንዲሁም ሴቶችና ህፃናትን ጨምሮ ድሃ እና ተጋላጭ የሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎችን ከሌሎች በተለየ ሁኔታ በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል። በአጠቃላይ ግጭቶች ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፣ ከፍተኛ ማህበራዊ ጉዳት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የአካባቢ ጉዳት ያስከትላሉ። እነዚህ ችግሮች በግጭቱ ወቅት ብቻ ሳይሆን ከግጭት በኋላ የሚቀጥሉ በመሆናቸው አገራት በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ከችግሩ ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት ፈታኝ ያደርገዋል (UNECA, 2024)።

11. በተመሳሳይ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች ባለፉት ጥቂት አሥርተ ዓመታት በግጭቶች ውስጥ ነበሩ። በጦርነት ምክንያት የሚደርሰው ሰበዓው ጉዳት ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር ግጭት ባጋጠማቸው አገሮች አማካይ ዓመታዊ እድገት በ2.5 በመቶ ዝቅተኛ እንዲል በማድረግ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች በሚከሰቱ ግጭቶች ምክንያት የሰው ህይወት መጥፋት፤ የመሠረተ ልማት፣ ሰብዓዊ ሀብትና ተቋማት መውድደም፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዲሁም ከግጭት ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳቶች ከማድረስ ባለፈ ኢንቨስትመንትንና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያደናቅፋል (IMF, 2020)፡፡

12. በተጨማሪም የIMF ጥናት እንደሚያመለክተው እ.ኤ.አ በ1990 ዎቹ በግጭት ምክንያት ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት የደረሰው ሞት ቢያንስ 825,000 ሲሆን ይህም ከዓለም አቀፍ የግጭት ሞት ከሁለት ሦስተኛ በላይ ድርሻ ነበረው። በሩዋንዳ በቱትሲዎች ላይ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተካሄደው ጦርነት እንዲሁም በአንጎላ፣ በኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ፣ በሊቤሪያና በሴራሊዮን ለረጅም ጊዜ የዘለቀው ግጭት በከፍተኛ ሁኔታ የሟቾችን ቁጥር እንዲጨምር አድርጎታል። በተመሳሳይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተደጋጋሚ እየተከሰቱ ባሉት ግጭት ምክንያት የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ የመጣ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ2014 ወዲህ በየዓመቱ የሚሞቱ ሰዎች መጠን በአማካይ 14,000 ገደማ ደርሷል።

13. በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶች መንስኤዎች በአብዛኛው በቅኝ ገዢዎች በዘፈቀደ የተፈጠሩ ድንበሮች፣ የተለያዩ ብሄረሰቦች ስብጥር መኖር፣ ብቃት የሌለው አመራር፣ ሙስና፣ የውጭ ዕዳ ጫና እና ድህነት ዋና ዋናዎች ተደርገው

ተለይተዋል። በተለይም በሃያኛው ክፍለ ዘመን በአፍሪካ የዘር ፖለቲካ ግጭቶች እየጨመሩ እንዲሄዱ ከማድረጉ ባሻገር በህዝቦቿ መካከል የጥርጣሬ፣ የጥላቻና ያለመተማመን ስሜት እንዲፈጠር እንዲሁም በአፍሪካ የፖለቲካ ውህደት እንዳይፈጠር አድርጓል። ለአብነት በዘር ልዩነት ምክንያት እ.ኤ.አ ከ1967-1970 እና ከ1993-1999 በናይጀሪያ የውስጥ ግጭት ተከስቶ እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ። በተመሳሳይ በሊቤሪያ፣ በኡጋንዳ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣ በሶማሊያ፣ በሱዳን፣ በኮንጎ እን በሌሎች በርካታ የአፍሪካ አገሮች ግጭቶች ተከስተው ነበር። በተጨማሪም በአፍሪካ አህጉር ውስጥ በተስፋፋው ፍጹም ድህነት ምክንያት ግጭቶች ለረጅም ጊዜ የአፍሪካ ችግር ሆኖ እንዲቀጥል አድርጓል። ስለሆነም በአፍሪካ የሚፈጠሩ ጦርነቶችና ግጭቶች ለመፍታት ያለባትን የአመራር ችግር መፍታት እና ከድህነት ለመውጣት ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ጥናቶች ያሳያሉ (Africa Research Review, 2010)፡፡ በተጨማሪም በአፍሪካ የእርስ በእርስ ግጭቶችን ለመቀነስ እና ለመከላከል ዜጎች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በብቃት የሚፈቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እናዴሞክራሲያዊ ተቋማት መገንባትና ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ይታመናል(Journal of African Economies, 2000)፡፡

## አገራዊ ሁኔታ

14. በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ከፍተኛው ግጭት ከሚከሰትባቸው አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ግጭቶ እ.ኤ.አ ከ1974 አብዮት በፊት በነበረው የንጉሡ ነገሥቱ ዘመን፣ በደርግ መንግስት ዘመን እ.ኤ.አ ከ1974-1991 መካከል የእርስ በእርስ ጦርነት የተካሄደበት እንዲሁም እ.ኤ.አ ከ1998-2000 የኢትዮጵያ-ኤርትራ ጦርነት ተከስቶ ነበር። በተጨማሪም በቅርብ ጊዜ እ.ኤ.አ በ2021 መጨረሻ ላይ በሰሜናዊው የአገሪቱ ክፍል በህወሃትና በፌደራል መንግስቱ መካከል ከፍተኛ ግጭት ተከስቷል፡፡ ለዚህ ግጭት መከሰት ዋናው ምክንያት በትግራይ ውስጥ በህወሓት በኢትዮጵያ ወታደራዊ ሰፈሮች ላይ የተፈፀመ ጥቃት ነበር። ይህ ግጭት ጉዞውን ወደ አገሪቱ ማዕከል አዲስ አበባ በማድረግ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በመስፋፋት መጠነ ሰፊ ጉዳት አድርሷል፡፡ በሌላ በኩል በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ በዋናነት በአብዛኛዎቹ አማራ ክልል፣ የኦሮሚያ ክልል፣ በቢኒሻንጉል ጉምዝ እና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በርካታ ግጭት ያሉ መሆኑን ጥናቶች ያመላክታሉ (Alemayehu, 2018 and Gebeyaw etal, 2023)።

15. በ GLOBAL PEACE INDEX (2023) ጥናት መሠረት ኢትዮጵያ የሰላም ችግር ከዓመት ዓመት እየተባባሰ መሆኑን እና እ.አ.አ በ 2023 ከ 163 አገራት መካከል 144ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኛ ያሳያል። በመሆኑም የኢትዮጵያ የሰላም ሁኔታ በአለም አቀፍ የሰላም መረጃ ጠቋሚ መሰረት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በተመሳሳይ በአፍሪካ ኢትዮጲያ ያላት የሰላም ደረጃ በጥናቱ ከተካተቱ 44 አገሮች ውስጥ 37ኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ 7 አገሮችን ብቻ እንደምትበልጥ መረጃዉ ያሳያል። ስለሆነም ኢትዮጵያ የሰላም እጦት ያለባት ሀገር ሁና ተፈርጃለች። እንደ ዓለማየሁ ገዳ (እ.ኤ.አ 2004) ገለፃ ግጭት ለኢትዮጵያ ድህነት እና ኋላቀርነት ዋነኛው እና ቁልፍ ምክንያት እንደሆነ ተመላክቷል። በተጨማሪም ግጭቶች የህይወት መጥፋትን፣ የመሠረተ ልማት ውድመትን እንዲሁም በእድገትና በልማት ላይ አሉታዊ ተፅእኖን በማድረስ አስከፊ ውጤት ያስከትላሉ፡፡

16. በሌላ በኩል ግጭት የሚያስከትለው ጉዳት ውስብስብና ብዙ ገጽታ ያለው ሲሆን ከሰው ልጅ ሞት እስከ ቁሳዊ ውድመት ያስከትላል። በዚህም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲስተጓጎሉ በማድረግ ሁለንተናዊ እድገትንና ለውጥ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በግጭቱ ዓመታት ውስጥ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት እንደሚቀንስ ይገመታል። ለአብነት እ.ኤ.አ ከ1969-74 በአማካይ 3.8 በመቶ የነበረዉ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት ከ1975-80 (የርስ በርስ ጦርነት እና ከሶማሊያ ጋር በተደረገዉ ግጭት) ምክንያት ወደ 2.6 በመቶ ቀንሷል (Alemayehu, 2018)፡፡

17. በኢትዮጵያ የተከሰቱ ግጭቶች በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት አጥፍቷል በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትንም ደግሞ አፈናቅሏል፡፡ በትግራይ ግጭት፣ በአንበጣ ወረራ እና በድርቅ ምክንያት በአትዮጵያ ሰብዓዊ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር 20 ሚሊዮን በላይ ደርሶ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በችግሮቹ ከ500,000 በላይ ሰዎች ሞተዋል፣ ከ3 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በሀገር ውስጥም ሆነ በአቅራቢያው ወደሚገኙ ሀገሮች ተፈናቅለዋል፡፡ በአውሮፓ ፓርላማ ሪፖርት (2022) መሰረት ሆስፒታሎች እና ትምህርት ቤቶች ከሌሎች ተቋማት በበለጠ በግጭቱ እንደወደሙ ያሳያል። ከዚህም በላይ ግጭቱ ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በግዳጅ መፈናቀል እንዲሁም በጾታ ላይ የተመሠረተ እና ወሲባዊ ጥቃት እንዳስከተለ መረጃዎች ያሳያሉ (Olileanya and Moses ,2023)።
18. በአለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (እ.ኤ.አ 2023) ሪፖርት እንደሚያመለክተው እኤ.አ በ2022 መጨረሻ ላይ ከ3 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈናቅለዋል። አብዛኛዎቹ 69 በመቶ የሚሆኑት ተፈናቃዮች በቀጥታ በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን በድርቅ 17 በመቶ እና በሌሎች እንደ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተት እና የእሳት አደጋዎች ያሉ ምክንያት ደግሞ 9 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በሰሜን የአገሪቱ ክፍል በዋናነት በግጭት ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የውስጥ ተፈናቃዮች ያሉ ሲሆን በምስራቅ የአገሪቱ ክልል ደግሞ በድርቅ ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የውስጥ ተፈናቃዮች እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡
19. በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት (GBV) የሚጨምረው በድንገተኛ ሁኔታዎች ወቅት ሲሆን ይህም በግጭት፣ የኢኮኖሚ ቀውስ ወይም የበሽታ ወረርሽኝ በሚከሰትበት ወቅት እንደሆነ ጥናቶች ያመላክታሉ። ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶች እድገት፣ ጤና፣ ኑሮ፣ አካላዊና አእምሯዊ ደህንነት ላይ እንቅፋት ይፈጥራል። የትግራይ ጦርነት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከ 1,300 በላይ የአስገድዶ መድፈር ክስተቶች ሪፖርት የተደረገ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች በሪፖርቱ ያልተካተቱ ጉዳቶች እንደሚኑ ይገመታል። ከዚህ በተጨማሪ በጤና ተቋማት ላይ በደረሰው ጉዳት እና ዝርፊያ ምክንያት ጥቃት ለደረሰባቸው እንዲሁም በሕይወት ለተረፉ ሰዎች የጤና እንክብካቤ መስጠት ባለመቻሉ ጉዳቱን ይበልጥ ውብስብና አሳሳቢ ያደርገዋል። በተመሳሳይ በሰሜናዊ ኢትዮጵያ በ84 የወሲብ ጥቃት ድርጊቶች ላይ በተደረገው ጥናት መሰረት 471 ሴቶች እና ልጃገረዶች ተጠቂ እንደነበሩ ያሳያል። ጾታን መሰረት ያደረገ የጉዳት መጠን ጥናት ካርታ እንደሚያመለክተው ጥቃቱ በከፍተኛ ደረጃ የደረሰባቸው አካባቢዎች በአብዛኛው ከፍተኛ የትጥቅ ግጭት በተከሰተባቸው የሦስቱ ክልሎች ድንበር እንደሆነ ያሳያል። እነዚህም በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ፣ በደቡብ ወሎ እና በዋግሂምራ ዞኖች፣ በአፋር ክልል በአውሲ እና በኪልብርቲ ዞኖች እንዲሁም በትግራይ ክልል በሁሉም ዞኖች ነበር (IMMAP, 2022)፡፡
20. በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በተደረገው የጉዳትና የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት (ቅጽ 1፣ እ.ኤ.አ 2022) መሰረት ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገሪቱ የተከሰተው ግጭት ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ጉዳት ማድረሱን ያሳያል። ግጭቱ በመጀመሪያ በህዳር ወር 2013 ዓ.ም በትግራይ ውስጥ የተከሰተ ሲሆን እስከ ሰኔ 2013 ድረስ ወደ አጎራባች የአማራ እና የአፋር ክልሎች ተስፋፍቶ ነበር። በጥናቱ መሰረት ጦርነቱ የሰሜኑ የሃገሪቱ ክፍልን ማዕከል አድርጎ የተካሄደ ቢሆንም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በተለይም በኮንሶ አካባቢም ግጭቶች እንደነበሩ ያስቀምጣል። በዚህም ምክንያት በአገሪቱ ወደ 2.2 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉ ሲሆን ከ20 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በሰብዓዊ ድጋፍ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ተገድደው ነበር።
21. በተካሄደው የጉዳትና የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በተቋማት/በዘርፎች እና በክልሎች ላይ የደረሰው አጠቃላይ ውድመት 22.69 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እደሚደርስ የተገመተ ሲሆን ለመልሶ ማቋቋምና ግንባታ የሚየስፈልግ የገንዘብ መጠን 19.73 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚሆን ይገመታል። በሌላ በኩል በግጭቱ ምክንያት የደረሰው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ኪሳራ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት(GDP) 5.5 በመቶ ያህል እንደሚሆን

እና በንብረቶችና በመሰረተ ልማት ላይ የደረሰው ውድመት ደግሞ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 20.4 በመቶ እንደሆነ ተገምቷል። ስለሆነም በግጭት ምክንያት ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት የሚደርስ በመሆኑ እንዲሁም በአገር ልማትና ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚያስከትል የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ስራዎችን መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

## ክልላዊ ሁኔታ

22. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና ህዝቦች ላይ በትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር/ትህነግ/ እና በትግራይ ሰራዊት በተለያየ ጊዜ ወራራ ተፈጽሞበታል፡፡ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዙር ወረራ በአማራ ክልል በሚገኙ 8 ዞኖች 89 ወረዳዎችን የሸፈነ በ973 የቀበሌ አስተዳደሮች ላይ ወራሪው ኃይል ጥቃት ያደረሰ ሲሆን 292 ቢሊየን ብር ቁሳዊ ውድመት እነዳከተለ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህም በላይ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰላማዊ ሰዎችን በግፍ ገድሏል፤ በእድሜ የገፉ አዛውንት እናቶችን፣ እድሜያቸው ለጋ የሆኑ ህጻናትን፣ ባለትዳር ሴቶችን ጨምሮ በርካቶችን በጉልበት ደፍሯል፤ ከፍተኛ ሰብአዊና የስነልቦና ጠባሳ አድርሷል እንዲሁም ከ14.1 ሚሊዮን በላይ ሰላማዊ ነዋሪዎችን ከቀያቸው አፈናቅሎ እርዳታ ጠባቂ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የአማራ ህዝብ በሌሎች እንዲጠላ አድርጓል፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሟል፤ ከኢትዮጵያዊ ባህል ያፈነገጠ ነውር ፈጽሟል፤ የአምልኮ ተቋማትን ጭምር ክብራቸውን አርክሷል፤ ዘርፏል፤ አውድሟል (ARRFO፣ 2015 ዓ.ም)፡፡
23. በዚህ የውድመት ጥናት እንደተመላከተው ወራሪ ሃይል የተወሰነ ጊዜ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ ለሦስተኛ ጊዜ (ከነሃሴ 2014 እስከ መስከረም 2015 ድረስ) በክልሉ ላይ ወረራ በማካሄድ በዋግ ኽምራ፣ በሰሜን ወሎ እንዲሁም በሰሜን ጎንደር በሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከፍተኛ የሆነ ተመሳሳይ አይነት ውድመትና ዝርፊያ መፈጸሚል፡፡ በወረራ የቆየባቸው ጊዜያት አጭር ቢሆንም የግልና የመንግስት ተቋማትን፤ የግል ሃብትና ንብረት፤ የሃይማኖት ተቋማትን ወዘተ በፊት ካደረገው በበለጠ በደልና ውድመት ፈጽሟል፡፡ ተመሳሳይ ሰብአዊ ግፍ ፈጽሟል፡፡ የወረራው ወቅት በክረምት ወቅት በመሆኑ አርሶ አደሩ የሚዘራበት፣ የዘራውን ሰብል የሚያርምበት ወሳኝ ወቅት በወረራ ያለፈበት በመሆኑ ማምረት ባላመቻሉ እርዳታ ጠባቂ እንዲሆን እና ህይወቱ እንዲጨልምበት ሆኗል፡፡
24. ከዚህ በተጨማሪ በግጭቱ በርካቶች ውድ ህይወታቸውን ሲያጡ በርካቶች ደግሞ አካላቸው ጎድሏል፤ ለዘመናት ጥረው ግረው ያፈሩት ሀብት ንብረት ወድሟል፤ በርካታ ሕጻናት ያለ አሳዳጊ፣ አረጋውን ያለ ያለጧሪና ቀባሪ ቀርተዋል፤ ቤቶች እና አዝመራዎች ተዘርፈዋል፣ እንስሳት ተዘርፈዋል ታርደው ተበልተዋል፣ ህጻናት እና ሴቶች ተደፍረዋል፣ ብዙ ሺህ ሴቶች እና ህጻናት በደረሰባቸው ጾታዊ ጥቃት ምክንያት ቅስማቸው ተሰብሯል፤ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወገኖች ዛሬም ድረስ በመጠለያ እና በየአካባቢው ተጠልለው ለእለት ጉርስ እንኳ የሰው እጅ ጠባቂ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ጦርነቱ ቁሳዊና ሰብአዊ ውድመት እንዲሁም ስነልቦና ጉዳት በክልሉ ነዋሪዎች ላይ በከፋ ሁኔታ አድርሷል፡፡
25. በአማራ ክልል በተደረገው የውድመትና የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት (ቅጽ 2፣ እ.ኤ.አ 2024) መሰረት በሦስተኛው ዙር በክልሉ በነበሩባቸው ዞንና ወረዳዎች ግጭቶቹ በሁሉም ተቋማት ውድመት እና ኪሳራ ያስከተሉ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ ጥናቱ እንደሚያሳየው በግጭቱ 24,418 ቤቶችን ውድመት በማድረሱ 122,090 ሰዎች ያለመጠለያ እንዲቀሩ አድርጓል፡፡ በጤናው ሴክተር በ318 ጤና ኬላዎች፣ በ111 ጤና ጣቢያዎች እና በ15 ሆስፒታሎች ላይ ግጭቱ ውድመት አድርሷል፡፡ በተመሳሳይ በ492 ትምህርት ቤቶች ላይ ሙሉ በሙሉ እና በ111 ትምህርት ቤቶች በከፊል ውድመትና የተዘረፉ ያደረሰ ሲሆን ከ35,877 በላይ መምህራንን እና የትምህርት ሰራተኞችን ከስራ እንዲፈናቀሉ በማድረግ ከ 210,600 በላይ ልጆች ከትምህርት ገበታቸው እንዲቀሩ አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል በቱሪዝም ሴክተር በ964 የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና 2,572 የቅርስ ጥበቃ ተቋማትና ቅርሶች ላይ ውድመት

አድርጓል። በውሃና ኢነርጂ ዘርፍ በግጭቱ ከ360 በላይ የውሃና የኃይል ማመንጫ ተቋማት ላይ ወድመት አስከትሏል፡፡

26. በአጠቃላይ የውድመትና የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እንደሚያመለክተው በግጭቱ ምክንያት በክልሉ 41.53 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ እና 7.48 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በንብረቶች እና በመሠረተ ልማት ላይ ውድመት በድምሩ 49.01 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ውድመትና ኪሳራ መድረሱን ያመላክታል፡፡ ለመልሶ ማቋቋምና ግንባታ የሚየስፈልግ የገንዘብ መጠን 46.11 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚሆን ይገመታል።

## ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች

1. ክልሉ ለተደጋጋሚ ጦርነትና ግጭት የተዳረገና የተጋለጠ መሆን፣
2. አስከፊ ሰብዓዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ቁሳዊና አካባቢያዊ ውድመትና ጉዳት መድረስ፣
3. የመልሶ ማቋቋም፣ መገንባትና ማልማት ውስንነት፣

## የትኩረት መስኮች

1. አካባቢዎችንና ተጎጅዎችን መልሶ ማቋቋም
2. ተቋማትንና መሰረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት
3. ጉዳት የደረሰባቸዉን አካባቢዎች መልሶ ማልማት እና
4. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

27. የሀብት ማሰባሰብ እና ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፣ የተጎዱና የወደሙ አካባቢዎችን መልሶ መገንባት፣ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች መደገፍና መልሶ ማቋቋም፣ የስነ ልቦና ድጋፍና አገልግሎቶችን ማጎልበት፣ የአደጋ ጊዜ ምላሽን ማጠናከር፣ ለተጎዱ ማህበረሰቦች በተለይም ለወጣቶች የኢኮኖሚ ድጋፍ በማድረግ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ እና የስራ ዕድል መፍጠር፣ ዘላቂ ሰላምንና ልማትን ማምጣት፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የጉዳት መጠን መረጃ ማደራጀትና ጥቅም ላይ ማዋል እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን ለመልሶ ማቋቋምና ግንባታ በስፋት መጠቀም የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዓላማ፡- በጦርነት ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ማህበረሰቦችን እና ተቋማትን መልሶ በማቋቋምና በመገንባት ከዚህ ቀደም ከነበሩበት በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣**

## ዋና ዋና ግቦች

28. የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽን በማጠናከርና የተለያዩ የድጋፍ አማራጮችን ስራ ላይ በማዋል ተጎጂዎች ጥሪት እንዲያፈሩ ማስቻል፣ የተጎዱ ተቋማትን በመጠገን፣ መልሶ በመገንባት እና በማቋቋም ከነበሩበት በተሸለ ደረጃ ላይ ማድረስ፣ የስነልቦና ማህበራዊ ድጋፍ ማጠናከር፣ የገንዘብ ማሰባሰብን፣ የሀብት አጠቃቀምን እና ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት፣ በጦርነቱ የተጎዱ ተቋማትንና መሰረተ ልማቶችን መልሶ በመገንባት ወደ ቀድሞ ይዞታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣ አስፈላጊ አገልግሎቶች ተደራሽነት፣ አካታችነት፣ ፍትሃዊነት እና ጥራት ማረጋገጥ፣ ወሲባዊ እና በፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት የደረሰባቸውን የህብረሰብ ክፍሎች በመደገፍ ከጉዳታቸው እንዲያገግሙ ማድረግ፣ በጦርነቱ የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎችን እና የመንግስት ሰራተኞችን የኑሮ ደህንነትን ማረጋገጥ፣ በክልሉ የሚከሰቱ ችግሮችን መቋቋም የሚያስችል አቅም መገንባት እንዲሁም የማህበረሰቡን ተሳትፎ፣ አቅምና ባለቤትነት ማሳደግ የሚሉትን ግቦች ለማሳካት በከፍተኛ ትኩረት ይሰራል፡፡

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

29. ሥራውን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ እንዲመራ ማድረግ፣ ጉዳቱ በደረሰበት አካባቢ የተፈናቀሉና ቀያቸውን ለቀው የተሰደዱ የህብረትብ ክፍሎች ወደ ነበሩበት አካባቢ እንዲመለሱ በማድግ መደበኛ ኑሮአቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ፣ በተጎዱ አካባቢዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የደረሰውን ውድመት ሊያካካስ በሚችልና ከዚያም በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ የሚያስችል የልማት፣ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ስራዎችን መስራት፤ የተለያዩ አካላትን ማለትም የክልሉ መንግስትን፣ በክልሉ የሚሰሩ የልማት ድርጅቶችን፣ ረጂ ድርጅቶችን፣ የፌደራል ሚኒስተር መ/ቤቶችን፣ የግል ባለሀብቶችን እንዲሁም ህብረተሰቡን በማስተባበር በተጠናከረ መልኩ ሀብት የማፈላለግና የማሰባሰብ ስራ መስራት፣ የተገኘውን ሀብትም በአግባቡ ለታለመለት አላማ እንዲውል ማድረግ፣ የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ስራውን በተቀናጀ አግባብ ለመፈጸሚ የሚያግዙ አደረጃጀቶችን በማቋቋም ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ፣ ተቋማዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን መገንባት፣ ከዋናው እቅድ የተቀዳ የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ተግባራትን ሚመለከታቸው ፈጻሚ ተቋማት በእቅዳቸው አካተው እንዲያቅዱና እንዲተገብሩ ማድረግ፣ በየጊዜው በሚከሰቱ ግጭቶች የሚደርሰውን ሁለንተናዊ ውድመትና ከሳራ ከዩኒቨርስቲዎችና ከክልል ተቋማት ጋር በመሆነ መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት የዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ማድረግ፤ ተያያዥ የሆኑ የፖሊሲ ሃሳቦችን ማመንጨት፣ ስትራቴጂዎችን መንደፍ እና የአሰራር መመሪያዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በጋራ ማዘጋጀትና ተፈጻሚ የሚሆኑበትን አሰራር መፍጠር፤ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት የተደራጀ የመረጃ ቋት እንዲኖር በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድግ፣ የደረሰውን ውድመትና በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎችን በሚመለከታቸው አካት እንዲታወቅ ከሚዲያ አካላት ጋር በጋራ መስራት እንዲሁም ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ የሚሉት ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

# የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት

30. የዕቅድ ዘመኑ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በጥብቅ ዲስፐሊን የሚመራ ወደፊት ራሱን የቻለ በክልሉ ፕሬዝዳንት ስር ሆኖ በሚደራጅ እና የእለት ከለት ተግባሩ የእቅዱን የተግባር አፈጻጸም እየገመገመ ሳይንሳዊ ትንታኔዎችን እያካተተ ለፕሬዝዳንቱ እያቀረበ እያስወሰነ እቅዱን በስኬት ላከናዉኑ አካላት የማበረታቻ ስርአት እንዲኖር በማድረግ የሚበረታቱበት፡ እቅዱን በአግባቡ በማይፈጽሙ አካላት ላይ ደግሞ ተገቢዉ ድጋፍ እንዲደረግላቸዉ ተገቢዉ ድጋፍም ተደርጎላቸዉ ማስፈጸም የማይችሉ አካላት ደግሞ በአቅማቸዉ ወደሚያከናዉኑበት ቦታ ስምሪት እንዲሰጥ ለፕሬዝዳንቱ ምክረ ሀሳብ እያቀረበ እያስወሰነ የሚሄድ ተቋም የድጋፍ የክትትል እና የግምገማ ስርአቱን እንዲመራ የሚደረግ ሲሆን የተለያዩ አካላትን የሚያካትትና በትኩረት በየደረጃው የሚተገበር የድጋፍ የክትትል እና ግምገማ ስርአት የሚያከናዉኑ አካላት በተጨማሪነት የሚሳተፉበት ይሆናል። በመሆኑም በየደረጃው ተሣታፊ የሚሆኑ አካላት እና የሚኖራቸው ሚና እንደሚከተለው በዝርዝር ተመላክቷል።

31. **በየደረጃዉ የሚገኙ የሕዝብ ምክር ቤቶች፡-** ምክር ቤቶች በቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት፣ አሠራር፣ በመስክ ክትትልና ቁጥጥር፣ በየደረጃው በሚካሄዱ የምክር ቤት ጉባዔዎች፣ በሚፈጥሯቸው የሕዝብ ውይይቶች ውስጥ ዋና ዋና የእቅዱ የግብ ማዕከሎችን በቼክሊስት በመያዝ የመገምገሚያና የመወያያ አጀንዳ አድርገው በመንቀሳቀስ አስፈጻሚ አካላት ችግር ፈች ዕቅድ ስለማቀዳቸው፣ ዓመታዊ ዕቅዶች ከረጅም ጊዜ ዕቅዶች የተቀዱ እና የተንሰላሰሉ ስለመሆናቸው፣ አሳታፊና አካታች ስለመሆናቸው ግምገማ፡ ትንተና ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣ በተለዩ ችግሮች ላይ አስፈላጊ ድጋፍ ፤ውሣኔዎችና መፍትሄዎች እንዲሰጡ ማድረግ፣ የተለዩ ጉዳዮችን በመቀመር ለቀጣይ የተሻለ አፈጻጸም ግብዓት እንዲሆኑ እያስቻላሉ እንዲሄዱ ማድረግ የሚገባ ይሆናል፡፡

32. **በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት፡-** ከክልል ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ዕቅዶች ከዋናዉ እቅድ ጋር ተናባቢ እና የተንሰላሰሉ መሆናቸዉን ፡ በወቅቱ፣ በጥራት የታቀዱ መሆናቸዉን እና ተግባራዊ ሲደረጉ በተጠያቂነትና በተሻለ አመራርና በሕዝብ ተሣትፎ እየተፈፀሙ መገኘተቸውን መከታተል፣ መገምገም፣ መደገፍና ቀጣይ አቅጣጫና አመራር መስጠት ይጠበቅባቸዋል። በየደረጃው የሚዘጋጁ ግምገማዎችና ሪፖርቶችም የዕቅዱን ዋና ዋና ግቦች ማዕከል በማድረግ በወቅቱ እንዲፈጸሙ ማድረግና ከቀበሌ እስከ ክልል ባለው መንግሥታዊ የመዋቅር ትስስር ውስጥ በቅብብሎሽ በጥብቅ ዲስፒሊን እንዲመሩ ማድረግ የሚገባ ይሆናል፡፡

33. **የክልሉ ህዝብ** ፡- የልማት ባለቤትና ተጠቃሚ የሆነው የክልሉ ሕዝብ እስካሁን ድረስ የዕቅዱን አፈጻጸም ለመከታተል፣ ለመገምገምና ድጋፍ ለመሥጠት በሚያመችው መልኩ ሊመራና ሊሳተፍ ይገባል። በአፈጻጸሙ ላይ የመላ ሕብረተሰቡ አስተያየት የሚካተትበትን ሥርዓት መዘርጋትና በበጀት ዓመቱ የታዩ ለውጦች በሕዝቡ ተተችተዉ ወደ ላይ እንዲመጡ ማድረግ ይገባል።

34. **ፕላንና ልማት ቢሮ፡-** በየጊዜው ያልታዩ ጉዳዮችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከሚተላለፉ ውሣኔዎችና ከሚሠጡ አቅጣጫዎች በመነሣት በየዘርፉና በየደረጃው የዕቅድ ክለሳና ማሻሻያ እንዲደረግ ማድረግ ይጠበቅበታል። አመታዊ እቅዶች ከዋናዉ እቅድ የተቀዱ እና የዘመኑን እና ባለፈዉ የበጀት አመት ታቅደዉ ሙሉ በሙሉ ያልተፈጸሙትን አካቶ የታቀደ መሆኑን እንዲሁም በፖሊሲ ማትሪክስ የተቀመጡትን ምርት አይነት እና መጠን በእቅዱ የተካከተተ ስለመሆኑ ዋና ዋና የልማትና የመልካም አስተዳደር ግቦች በሚጠበቀው ደረጃ እየተፈጸሙ ያሉ ስለመሆናቸው ማለትም መሰረታዊ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችሉ የማክሮ ኢኮኖሚ እና ዋና ዋና ዘርፎች ውጤት አመልካቾች መለየት የተዘጋጀ ስለመሆኑ የዘርፎች ዕቅድ የተመረጡ አመልካቾችን የያዙና ከሚደርስባቸው ዒላማዎች ጋር ተናባቢ መሆናቸውን በማረጋገጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ የተሳለጠ እንዲሆን ማድረግ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መረጃዎች ማመንጨትና ለግምገማ መነሻ እንዲሆኑ ማስቻል፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት፣ ከወቅቱ ጋር የሚሄድና ደረጃውን የጠበቀ የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማቶች ማዘጋጀት፣ የየሩብ ዓመታትና የዓመቱን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፣ በመስክ ስራ የተደገፈ የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የካፒታል ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ተከታትሎ ሪፖርት ማቅረብ፣ በክልሉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መደገፍ መከታተል እና ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሰነዶችን ማዘጋጀትና የውሳኔ ሃሳብ ለወሳኝ አካላት ማቅረብ ይጠበቅበታል። ከዚህ በተጨማሪ በሀብት አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን ስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ ይሰራል። ለዚህም ራሱን የቻለ የፕሮጀክት አስተዳደር ስርዓት እንዲሰፍንና ከመደበኛው ልማት ጋር የተቀናጀ ስራ መስራት የሚቻልበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

35. **የሴቶችን፣ የወጣቶችን እና ሌሎች ልዩ ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጉዳይ የሚከታተሉ አካላት፡-** ሴቶች፣ ወጣቶችና ሌሎች ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በልማቱ ውስጥ በየደረጃው ተሣታፊ መሆናቸውን እንዲሁም በልማቱ ሂደት ውስጥ ጥቅሞቻቸዉ የሚረጋገጥበትን፡ ችግሮቻቸው የሚፈቱበትን አሠራር መኖሩን በእቅዱ አፈጻጸም ሂደት ዉስጥ ማረጋገጥ ይገባል፡፡

36. **በአካባቢ ተፅዕኖ ላይ የሚሠሩ የመንግሥት አካላት፣ ድርጅቶችና ተቋማት፡-** በገጠርና በከተማ የሚካሄዱ የልማት ኘሮግራሞችና ተግባሮች እንዲሁም የግልና የመንግሥት የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶች ከአካባቢ ጥበቃና ደህንነት አኳያ ቅድመ ግምገማ እንዲሁም የሂደትና የአፈጻጸም ግምገማ በማድረግ የአካባቢን ተፈጥሮ በማይጎዳ አግባባብ እንዲፈፀሙ ማደረግ እና በሚደረግ ክትትል የሚገኙ አካባቢን ለጉዳት የሚዳርጉ ተግባራት ሲገኙ የማስተካከያ ዕርምጃዎች እንዲወሰዱ እያደረጉ በእቅድ ትግበራዉ ወቀት ሃላፊነት ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ የፀጥታና የፍትህ አካላት፡- ትክክለኛ የልማት ሂደትና የአተገባበር ሥርዓት ሰላምንና የሕግ የበላይነት መረጋገጥን የቅድሚያ

ቅድሚያ የሚጠይቅ ከመሆናቸው ባሻገር አጠቃላይ የእቅድ አፈጻጸሙ እና ልማቱ ያለምንም ሥጋትና ችግር የሚፈጸምበት የሰላም እና ደህንነት ሁኔታ መኖሩን እያረጋገጡ አመራር ማረጋገጥ የሚገባ ይሆናል፡፡

37. **የክልሉ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት፡-** በየትኛውም መሥፈርት ከሕብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎች ከልማት ተሣታፊነት፣ ተጠቃሚነት፣ በልማት አመራር ሥርዓት መጓደልና መዛባት ጋር ተያይዘው የሚታዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህንን ከሚከታተሉ አካላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በየጊዜዉ በመቀመር ለቀጣይ አፈጻጸም ግብዓት አድርጎ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ የክልሉ ቅሬታ ሰሚ፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና እንባ ጠባቂ ተቋማት ለአስፈጻሚ አካላት በእቅዱ ትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ የህዝብ ቅሬታ ግኝቶችን እያቀረቡ እያስወሰኑ መሄድ የሚገባ ይሆናል፡፡

38. **የጥናትና ምርምር ተቋማት፡-** የዕቅዱ አፈጻጸም በዳሰሳዊ ጥናቶች፣ አሠራርና ክህሎት ታግዞ መተግበር ያለበት በመሆኑ የዩንቨርስቲዎች፤ በየደረጃዉ የሚገኙ ኮሌጆች እና የጥናትና ምርምር ተቋማት የዋናዉን እቅድ እና የየተቋማትን አመታዊ እቅድ ግብዓት አድርጐ በመጠቀምና እነዚህ ተቋማት በክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውስጥ በጥናት ላይ የተደገፈ ሙያዊና ተቋማዊ ሃላፊነታቸዉን እንዲወጡ እና ለእቅድ አፈጻጸሙ ዉጤታማነት በሳይንሳዊ እዉቀት የተደገፈ ያልተቋረጠ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

39. **የኦዲት ተቋም፡-** አጠቃላይ የሃብት አጠቃቀም ሥርዓቱ ላይ የፊዚካል /የአካል/ እና የፋይናንስ ኦዲት በማድረግ የሃብት አጠቃቀም ሥርዓቱ ከአሠራርና ሕግ አኳያ ትክክል ስለመሆኑ ከማረጋገጥ ባሻገር ከእቅዱ ግቦች መሳካት ጋር ያለውን መመጣጠን እያረጋገጡ መሄድ ይገባል፡፡

40. **የሚዲያና የኮሚኒኬሽን ተቋማት፡-** ተቋማቱ የሚሠሯቸው የዘገባ፣ የሕዝብ ግንኙነት ስራዎች፤ የሚፈጥሯቸው የሕዝብ ውይይቶችና መድረኮች ለክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ማዕከል ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረግና የተቋማቱ እንቅስቃሴዎች ዋና ዋና የእቅዱ ግቦች ላይ ያተኮረ እንዲሆንና ለእቅዱ ግቦች መሣካት አስተዋፅኦ በሚያደርግ መልኩ መፈጸምና ማሥፈጸም ያስፈልጋል፡፡

41. **የብዙሀን፣ የሙያና የሲቪል ማህበራት፡-** ማህበራቱ የሚወከሉበትን ማህበረሰብ እና አካል ድምጽና ፍላጐት የሚወከሉ በመሆናቸዉ ምክንያት፣ በእቅዱ አፈጻጸም ሂደት ንቁ ተሳታፊ በመሆን የወከሉት የህብረተሰብ ክፍል ከእቅዶቹ ተጠቃሚ እየሆኑ መሆን አለመሆናቸዉን እያረጋገጡ መሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ ሌሎች የልማት አጋር አካላት፡ - በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዕቅድ አፈጻጸሙን በማጠናከር አስተዋጽኦ ያላቸው አካላት፣ ረጅ ድርጅቶች፣ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የፌድራል መንግስት ፣ የዲያስፖራ አካላት፣ የንግድ ማህበራት፣ ወዘተ... በሚዘጋጁ የክትትልና የግምገማ ማጠናከሪያ አሠራሮች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

42. በአጠቃላይ እቅዱ በታሰበለት አግባብ በጥብቅ ዲስፕሊን ተመርቶ የአሰብነዉን የልማት እና የመልካም አስተዳደር እቅድ የተሳካ ለማድረግ የዕቅዱን አፈጻጸም በመከታተልና በመገምገም ዙሪያ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሣታፊ የሚሆኑና ሀላፊነት ያለባቸው አካለት እንዲሳተፉ ይጠበቃል፡፡

## ምዕራፍ ሠላሳ አራት

# ስትራቴጂዎች እና ፖሊሲዎች

# ምዕራፍ ሠላሳ አምሥት

# የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት

## 35 1. መነሻ

1. የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ጨምሮ የአለፉ ዘመናት ዕቅዶች አፈጻጸም ከግብ በታች መሆን ዋና ምክንያቶች ዝቅተኛ ምርታማነት ዝቅተኛ ቅልጥፍና (inefficiency) ናቸው። የዝቅተኛ ምርታማነት እና ዝቅተኛ ቅልጥፍና መገለጫዎችም፤
   - በካፒታል በጀት የሚከናወኑ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ከልክ በላይ መዘግየት፣ ከፍተኛ የዋጋ ክለሳ እና የተጋነነ ተጨማሪ ወጪ፣
   - የግል ዘርፍ መዋዕለ-ንዋይ ከፈቃድ አሰጣጥ እስከ መሠረተ- ልማት ዝርጋታ የተንዛዛ ቢሮክራሲ፣
   - የልማት ድርጅቶችም ሆኑ የግል የኢንዱስትሪ ተቋማት በመሠረተ- ልማት እና ተያያዥ አቅርቦቶች ውስንነት ምክንያት ከአቅም በታች ማምረት፣
   - በግል ዘርፍ ተዋኒያን አቅም ማነስ ወይም ኪራይ ሰብሳቢ ባሕርይ ምክንያት ለልማት መዋል የነበረባቸውን ውስን መሬቶች አጥሮ ለረጅም ጊዜ ያለ ልማት ማቆየት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

2. በእነዚህ መገለጫዎች ለሚንጸባረቁት ዝቅተኛ ምርታማነት እና ዝቅተኛ ቅልጥፍና አንዱ እና ዋናው ምክንያት ጥብቅ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት አለመኖር ነው። የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ውጤታማ እንዳይሆን የሚደርጉ ጉዳዮችም፤
   - የመንግሥት ተቋማት ግምገማን መፍራት፣
   - ግምገማዎች በወቅቱ ተካሂደው ችግርን ከመፍታት ይልቅ ውድቀት ላይ ማተኮራቸው፣
   - ተቋመት ለግሉ ዘርፍ ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ ከመስጠት እና ድጋፍ ከማድረግ ይልቅ ተቆጣጣሪ ሆኖ መቅረብ፣
   - የወጡ አስገዳጅ የማስፈጸሚያ ሕጎች ተግባራዊ አለመደረግ፣
   - ለፕሮጀክቶች መጓተት ወይም ጥራት መጓደል ወይም መቋረጥ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሕጎች እና አሠራሮች መኖር፣
   - ተቋማት በእቅድ፣ በትግበራ፣ እና በመረጃ ልውውጥ ተቀናጅቶ አለመሥራት፣
   - አስተዳደራዊ መረጃዎች የተጋነኑ መሆን፣
   - በገለልተኛ አካል በሳይንሳዊ መንገድ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ውስን መሆን፣
   - እንደ Big Data እና GIS የመሳሰሉ ዘመናዊ መረጃዎች ገና በስፋት ጥቅም ላይ አለመዋል፣
   - የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ አፈጻጸሞች በሳይንሳዊ መንገድ ተተንትነው ለግምገማ አለመቅረብ፣ እና
   - የተማከለ እና የዳበረ የመረጃ ሥርዓት፣ እንዲሁም ይህን መተንተን የሚችል ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

3. የዚህ የልማት ዕቅድ ዋና የትኩረት አቅጣጫም በየዘርፉ ቅልጥፍና እና ከፍተኛ ምርታማነትን በማስፈን በዘርፎች ትስስር በተለይ በዘመናዊ ግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች እመርታ መፍጠር፣ በውጤቱም ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ጨምሮ የመዋቅራዊ ሽግግር ዓላማዎችን ማሳካት ነው። የዚህ ዓላማ ዋና ማስፈጸሚያ ሥልት ከክልል ርዕሰ-መስተዳድር ጽሕፈት ቤት እስከ ቀበሌ ማሕበረሰብ በሚዘልቅ አስተዳደራዊ እና ሕዝባዊ አደረጃጀት መዋቅር ችግርን በወቅቱ መፍታትን ዓላማ ያደረገ ጥብቅ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ማስፈን ነው።

## 35.2. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የትኩረት አቅጣጫዎች

4. የልማት ዕቅዱ የትግበራ ወቅት የክትትል እና ግምገማ የትኩረት አቅጣጫዎች
    - በተቋማት ትብብር እና ቅንጅት ችግርን በወቅቱ ቀድሞ መፍታትን ግብ ያደረገ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ማስፈን፣
    - የመንግሥት ወጪን መቆጠብ እና በመንግሥት ተቋማት የጊዜ አጠቃቀም ዲስፕሊን ማስፈን፣
    - ብክነትን በመከላከል የቁሳዊ እና ሰብዓዊ አቅሞችን አጠቃቀም ምርታማነት ማሳደግ፣
    - ጥራትን ማስጠበቅ፣
    - የተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራር ማዳበር እና ማዘመን፣
    - የሰፊ አውድ ሙስናን መከላከል (ጉቦ፣ ሌብነት፣ ጊዜን ላልተገባ ዓላማ መጠቀም፣ የመንግሥት ሀብትን ማባከን፣ ወዘተ)
    - ተጠያቂነትን ማስፈን ናቸው።

## 35.3. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የትኩረት መስኮች

5. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት በሦስት ዋና የትኩረት መስኮች ላይ ያተኩራል፤
    1. የመንግሥት ልማት ኢንቨስትመንት አስተዳደር
        - የልማት ፕሮጀክቶች
        - በመንግሥት ዋስትና ወይም መዋጮ የተመሠረቱ የልማት ድርጅቶች
    2. የተቀላጠፈ የግል ኢንቨስትመንት ሥርዓት፣ እና
    3. የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ልማት አፈጻጸሞች።

### የመንግሥት ልማት ኢንቨስትመንት አስተዳደር

6. መንግሥት በፐብሊክ ፖሊሲ የኢኮኖሚ ቅልጥፍናን (efficiency)፣ ማሕበራዊ ፍትህ (equity)፣ እና የጥቅል ኢኮኖሚ መረጋጋት (stabilization) ግቦችን ለማሳካት ይጥራል። የመንግሥት የልማት ኢንቨስትመንቶች (public investment) ዋና ዓላማም በኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ መሠረተ- ልማት፣ በቤቶች ግንባታ፣ በሥራ ፈጠራ ፕሮግራሞች፣ እና በልማት ኢንተርፕራይዞች በሚፈጠሩ አቅሞች እና ዕድሎች የፈጣን እድገት፣ የፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ ግቦችን ማሳካት ነው።

7. የመንግሥት ልማት ኢንቨስትመንት የአጠቃላይ አገራዊ ወይም ክልላዊ ቋሚ ካፒታል ኢንቨስትመነት (gross fixed capital formation) አካል ሲሆን የመንግሥት የካፒታል ወጪን፣ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች (state-owned enterprises - SOEs) የሚደረግ የካፒታል ሽግግር፣ ድጎማ እና የፋይናንስ ዋስትና (guarantees for SOEs investment finance) ያጠቃልላል። የመንግሥት ልማት ኢንቨስትመንት በክልል ወይም በፌደራል ወይም በክልል እና በፌደራል ማዕቀፍ ውስጥ ያሉትን ያካትታል።

8. **የአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግሥት የልማት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በበርካታ አገራት የሚስተዋሉ ዝቅተኛ ቅልጥፍናን ይጋራሉ።** በዓለም አቀፍ ደረጃ በተደረጉ ጥናቶች እንደተረጋገጠው የመንሥት ልማት ኢንቨስትመንት የጋራ ባሕርያት ብክነት የበዛበት እና ዝቅተኛ ቅልጥፍና (inefficiency) የሚስተዋልበት መሆኑ ነው። የችግሮቹ ምንጮችም ያለ በቂ ጥናት በፖለቲካ ውሳኔ የሚደረጉ የፕሮጀክት መረጣዎች፣ ከፕላን እስከ አፈጻጸም የሚዘልቅ ደካማ የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር፣ የዲዛይን መዘግየት፣ የተደጋገመ የዲዛይን ለውጥ፣ ለሙስና የተጋለጡ የግዥ ሂደቶች፣ የማጠናቀቂያ ጊዜ መዘግየት፣ የተጋነነ የዋጋ ክለሳ እና የተጋነነ ተጨማሪ ወጪ፣ የተገነቡ መሠረተ - ልማት ዝቅተኛ ጥራት፣ እና ድህረ-ፕሮጀክት የጥገና፣ ማሻሻያ፣ እና በውጤት ላይ ክትትል እና ግመገማ አለመኖር ናቸው። ሁሉም ምክንያቶች በጥቅሉ እንደ አገር እና ክልል የፕሮጀክቶችን አዋጭነት በመሸርሸር የኢኮኖሚ ዕድገትን እና የማሕበረሰብ ተጠቃሚነትን በእጅጉ ይጎዳሉ።

9. በአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ የትግበራ ወቅት በመንግሥት የልማት ኢንቨስትመንት አስተዳደር (public investment management) የሚዘረጋው የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የሚከተሉት 8 በዓለም አቀፍ ተቋማት የተመሰከረላቸው ርከኖች ይተገበራሉ፤
    1. ከክልላዊ እና አገራዊ ግቦች ጋር መጣጣማቸውን የሚረጋግጥ ቅድመ ጥናት አቅጣጫ (guidance)
    2. የፕሮጀክት አዋጭነት እና ተጽዕኖ ጥናት (appraisal)
    3. ገለልተኛ የመንግሥት ተቋማት የፕሮጀክቶች ግምገማ (Independent review)
    4. በጥብቅ የበጀት እና የአዋጭነት ግምገማ ላይ የተመሠረተ መረጣ (Selection)
    5. አሳማኝ ድርጂታዊ መዋቅር፣ የጨረታ ሥርዓት፣ የጊዜ ሠሌዳን እና የክትትል ሥርዓት የተከተለ አፈጻጸም (Implementation)
    6. ተፈጻሚነታቸው እና አዋጭነታቸው አጣራጣሪ የሆኑ ፕሮጀክቶችን እስከ ማቋረጥ የሚደርስ ክለሳ (Adjustments)
    7. የፕሮጀክቱን ቀጣይነት እና ለታለመለት ዓላማ እንደሚውል ለማረጋገጥ የአሴት እና ሥርዓት ርክክብ (Operational sustainability)
    8. ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜ እና በጀት መጠናቀቁን እና የታለመለትን ዓለማ እና ግብ ማሳካቱን መገምገም (Evaluation)።

10. ቅድመ ጥናት አቅጣጫዎች እና የአዋጭነት ጥናት ከአሰማኝ የወጪ አሸፋፈን እና አቅም ጋር ትኩረት የሚሰጥባቸው ርከኖች ናቸው። እነዚህን መርሆዎች ግምት ውስት ያስገባ ግልጽ የመንግሥት ልማት ኢንቨስትመንት አስተዳደር መመሪያዎች ይዘጋጃሉ፣ በሥራ ላይ ያሉትም ይሻሻላሉ።

11. የክትትል እና ግምገማ ሥርዓቱ ለሚከተሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ያደረጋል፤
    - የፕሮጀክት ወጪዎች በአግባቡ መታቀዳቸውን እና መፈጸማቸውን
    - ወቅታዊ እና መደበኛ የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት መቅረቡን፣
    - በሚመለከታቸው ተቋማት እና ተጠቃሚዎች ጭምር መደበኛ ክትትል መደረጉን፣
    - ስጋትን ለመንግሥት እና ለተቋራጭ የሚያለድል የጨረታ ሥርዓት መስፈኑን፣
    - ጥብቅ እና ዘመናዊ የንብረት ምዝገባ እና አያያዝ፣ አጠቃላይ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱን፣
    - የፋይናንስ እና የፊዚካል ምርመራ በማድረግ ጥራት መጠበቁን፣ ፋይናንስ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን፣ እና
    - ድህረ-ፕሮጀክት የመልካም ተጽዕኖ ጥናት መከናወኑን።

## የግል ኢንቨስትመንት ሂደት ክትትል እና ግምገማ

12. የተማከለ እና የተቀናጀ ክትትል የሚከተሉትን ጉዳዮች ያረጋግጣል፤
    - የኢንቨስትመንት መረጣ እና ስምሪት ለዘርፎች ልማት በተሰጠው የትኩረት ልክ መከናወኑን
    - የኢንቨስትመንት ስምሪት እንደ ሀብት መሠረታቸው በተመረጡ የልማት ቀጠናዎች፣ እና የኢኮኖሚ ዞኖች መደልደላቸውን
    - የመሬት፣ የመሠረተ-ልማት፣ የማበረታቻ እና ተያያዥ ድጋፎች ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች ለተሰማሩ አልሚዎች በአግባቡ መከናወኑን
    - የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ መጀመራቸውን እና መጠናቀቃቸውን

## የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ልማት አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ

13. የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ልማት አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት
    - ለዘርፎች የሚሰጡ ድጋፎችን አግባብነት ከትኩረት አቅጣጫ እና የትኩረት መስክ አንጻር ይገመግማል፣

- የዘርፎችን አፈጻጸም በዕቅድ ከተቀመጠው ቁልፍ የውጤት አመልካቾች (key performance indicators - KPIs) አንጻር በመደበኛ ጊዜ ማለትም በሩብ ዓመት፣ በመንፈቅ እና በዓመት ይገመግማል፣
- በጥናት እና ምርምር የተደገፈ የውጤት እና ተጽዕኖ ግምገማ ያካሂዳል።

## 36.4. የመረጃ ሥርዓት

14. ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የክትትል እና ግምገማ ዋና ማስፈጸሚያ መሣሪያ ነው።
    1. የመንግሥት የተቀናጀ የመረጃ ሥርዓት
        - ዲጂታል የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሂደት መረጃ (የክልል እና የፌደራል)
        - የዘርፎች የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ልማት አፈጻጸም መረጃ
    2. የዳሰሳ እና የሙሉ ቆጠራ የስታትስቲክስ መረጃ ሥርዓትን ማዘመን
        - የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃዎችን መሰነድ
        - የፕላን እና ልማት ቢሮ ከዘርፍ ቢሮዎች እና ሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመተበበር የዳሰሳ መረጃዎች፣ ሙሉ ቆጠራዎች፣ እና የወሳኝ ኩነት መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማዘመን፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካይነት ተደራሽ ማድረግ
        - በወሳኝ ኩነቶች እና የነዋሪነት መረጃዎች የቀበሌ - ወረዳ - ዞን - ክልል የተቀናጀ መረጃ ሥርዓት ማስፈን በተለይም ቀበሌዎች ድጋፍ ተደርጎላቸው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ታግዘው ነዋሪዎቻቸውን ከመሠረታዊ መረጃዎች ጋር መሠነድ፣
        - የዜጎችን መረጃ ከብሔራዊ (የዲጂታል) መታወቂያ (ፋይዳ) ጋር ማቀናጀት።

    3. ዘመናዊ የመረጃ ምንጮችን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤
        - Big Data
        - GIS መረጃዎችን

## 37.4. ተቋማዊ አደረጃጀት

15. በክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ውስጥ የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፤
    - የፌደራል - ክልል - ዞን/ሪጂዮ ፖሊታን - ወረዳ/ከተማ አስተዳደር -ቀበሌ ቀንጅት
    - የአስፈጻሚ ተቋማት ቀንጅት
16. ችግርን በጊዜ የመፍታት ሚና ያለው አሳላጭ የክትትል ኮሚቴ
    - የርዕሰ - መስተዳድር ጽሕፈት ቤት
    - የፕላን እና ልማት ቢሮ
    - የሚመለከታቸው የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች
    - የፌደራል እና የክልል የመሠረተ-ልማት ተቋማት
    - ፕሮጀክቶቹ የሚገነቡባቸው አካባቢዎች የመንግሥት አስፈጻሚዎች እና የማሕበረሰብ ተወካዮች
17. የግምገማ እና ኦዲት ኮሚቴ
    - **ገንዘብ ቢሮ እና የኦዲት መሥሪያ ቤት - ለፋይናንስ ኦዲት**
    - **የፕላን እና ልማት ቢሮ - ለፊዚካል ኦዲት እና የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ልማት አፈጻጸም ግምገማ**
    - የርዕሰ - መስተዳድር ጽሕፈት ቤት - ለቅንጅት
18. በመጨረሻም፣ የክልሉን ልማት በፖሊሲ ጥናት እና በሥልጠና የሚደግፍ፣ የክትትል እና ግምገማ ተግባራትን በዕውቀት የሚያግዝ  የአማራ መካነ ልማት ማቋቋም።

# ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

# የተቋማት አደረጃጀት እና ሚና

## የተቋማት አደረጃጀት መሰረታዊ መነሻዎች

1. **ለተቋማት አደረጃትና ግንባታ ትኩረት ሳይሰጥ ውጤት መጠበቅ ረብ የለሽ በመሆኑ፡-** ክልላችን በሁሉም የስራ መስኮች ተሰማርቶ ምርታማ መሆን የሚችል ከ13.4 ሚሊዮን በላይ አምራች የሰው ኃይል፣ ወደ 1,677 የሚጠጉ በጋ ከክረምት የሚፈሱ ወንዞች፣ ለእርሻ ስራ ተስማሚ የሆነ ከ5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቶችን የሚያሳልጡ የመንገድ፣ የውኃ፣ የኃይል አቅርቦት መሰረተ ልማቶች፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ መነሻ የሚሆኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ያልተሟጠጡ የዕድገት አማራጮች ባለቤት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከቁመጣችን ብዙ ሳይርቁ ተሰቅለው የሚገኙትን እምቅ ሰብአዊና ቁሳዊ የልማት አቅሞች በውል ተገንዝቦ በጥራት በማቀድ የግጭትና የድህነት አዙሪትን መስበር የሚችል ለውጥ ለማስመዝገብ ዕቅድን መሬት ማስነካትና ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ ተቋማትን ማደራጀት በጣም ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይሁን እንጅ የእስካሁኑ  የተቋማት አደረጃጀት በዘፈቀደ የሚከናወንና ከዕቅድ የማይነሳ ከመሆኑም በላይ ተደጋጋሚ መፍረስና መሰራቶች የተፈራረቁበት በመሆኑ የተቋማት አደረጃጀትና የግንባታ ስራው የሚፈለገውን ያህል ለውጥ አለመጣም፡፡ ይህ ሁኔታ ክልሉ የብዙ ፀጋዎች ባለቤት ሆኖ ሳለ ከድህነትና የግጭት አዙሪት እንዳይላቀቅና የኋላ ቀርነት ችግሮች የሰፈሩበት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ህግ ባለበት አገር ህገ ወጥነት የበላይ ሆኖ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚጣሱትና መንግስት ዋና ስራው የሆነውን የህዝብን ሰላምና ደኅንነት የመጠበቅ ተልዕኮ በሚፈለገው ደረጃ መወጣት ያልተቻለው የተቋማት አደረጃጀት ከትናት ጥንካሬዎችን ወስደው የሚያስቀጥሉና ከችግሮች የሚማሩ፣ ለዛሬው ሁኔታ የሚመጥኑና መጭውን ዘመን የሚዋጁ ሆነው እንዲደራጁና በተግባር ውስጥ እያለፉ በሂደት ራሳቸውን እያበቁ እንዲሄዱ ባለመደረጉ ነው፡፡
2. በአሁኑ ጊዜ ብዙዎቹ የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት ዓላማቸውና ራዕያቸው ባሸበረቁ ሰሌዳዎች ደጃፋቸው ላይ በግልጽ ቢሰፍርም ውስጣቸው ሲገባ ከተራ ጉዳይ ማስፈፀሚያ ጉቦ ጀምሮ በብልሹ አሰራሮቻቸው ተገልጋዮችን የሚያማርሩ ተቋማት ብዙ መሆናቸውን የሚያውቁት አገልግሎት ፍለጋ ሄደው ፍዳቸውን የሚያዩ ዜጎች ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ አሁን ላለንበት ዘመን የሚመጥን ባለመሆኑ ሳይውል ሳያደር በፍጥነት ተቀይሮ ከርዕሰ መስተዳድሩ የዞንና የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የከተማ ከንቲባዎችና በተለያዩ ኃላፊነቶች የተሰየሙ ሹማምንት ስራቸውን በውጤታማነት፣ በግልጽነት፣ በተጠያቂነትና በኃላፊነት መርህ መወጣት እንዲችሉ ጠንካራ ተቋማትን ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡
3. ከዚህ ቀደም ካለው ተሞክሮ መረዳት የሚቻለው የክልሉን የዕድገት ትልሞች በሚያሳካ አግባብ በጥናት ላይ ተመስርቶ የተቋማት አደረጃጀትና ግንባታ የሚከናወን ባለመሆኑ የልማት ውጥኖችን ዳር የማድረስም ሆነ ህዝብ የማገልገል ጥንካሬ አልነበራቸውም፡፡ ዜጎች በነፃነት እየተንቀሳቀሱ መኖር የሚችሉት ህግ ሲከበርና ህግ አስከባሪ ተቋማትም ሲጠናከሩ፣መንግስታዊ አገልግሎቶችን በስርዓት ማግኘት የሚችሉት ተቋማቱ ህግ አክብረው የሚሰሩበት ተቋማዊ አደረጃጀትና ጥንካሬ ሲኖራቸው ነው፡፡ ተሿሚዎች በህግ የተሰጣቸውን ስልጣን በአግባቡ ሊሰሩበት የሚችሉት ተቋማቱ ከህግ ውጪ ዝንፍ እንዳይሉ የሚያደርጋቸው አደረጃጀትና አቅሙ ሲኖራቸው ነው፡፡ በሥልጣን መባለግ፣ ዝርፊያ፣ ማናለብኝነትና ሥርዓት አልበኝነት፣ ሰፈርተኝነት የመሳሰሉት ችግሮች የሚሰፍኑት ተቋማቱ ከአደረጃጀት ጀምሮ ሲበላሹና ሲሽመደመዱ ነው፡፡ ስለሆነም በክልሉ የ5 ዓመት የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ በተለይም የህግ የበላይነት ተከብሮና ሰላም ሰፍኖ የክልሉ መንግስት ሙሉ ትኩረቱን ልማት ማፋጠን

ላይ እንዲያደርግ እንዲሁም የመንግሥት አሰራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ኃላፊነት የተሞላበት እንዲሆን የሚያስችል ውጤታማ የተቋማት አደረጃትና ግንባታ ስራ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

4. **የ5 ዓመቱን የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ መሸከምና መሬት ማስነካት የሚችል የተቋማት አደረጃት መፍጠር በማስፈለጉ፡-** የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀገሪቱ የልማት ስትራቴጂዎች ላይ የተመሰረተና በክልሉ መንግስት የሚፈፀም የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን አዘጋጅቷል፡፡ የክልሉን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ፣ ጠቃሚ የሆኑ ክልላዊ ወጎችን፣ እሴቶችንና ባህሎችን በማዳበር በስነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት፣ ሃብትና ፈጠራን ለማሳደግ የሚያስችል እውቀት ለማዳበርና ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በማሳደግ ጥራት ያለው ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮችን በአምስት ዓመቱ የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ላይ ተቀምጧል፡፡

5. ከዚህ በተጨማሪ በ2022 ሰላምና ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ በግብርና ምርት እምርታ ከመፍጠር ባለፈ መካከለኛ ገቢ ያለው፣ በ2027 በመሰረታዊ የኢንዱስትሪ ምርቶች የራሱን ፍላጎት የሚሸፍንና የተሳካ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በማድረግ በትክክለኛ የብልፅግና ፍኖት ላይ የሚገኝ፣ በ2042 ደግሞ በዓለም በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ የሆነ የዘመናዊ ኢኮኖሚ ባለቤት ክልል የማድረግ ርዕይ ተቀምጧል፡፡

6. ስለሆነም እነዚህን በአምስት ዓመቱ የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ የተቀመጡትን ስትራቴጂክ ጉዳዮችና ርዕዮች በትክክል መሬት ማስነካት የሚችሉና የትናንት ችግሮችን በመሻገር፣ ላለንበት ዘመን የሚመጥኑና መጭውን ዘመን የዋጁ ተቋማትን ለማዋለድ ውጤታማ መዋቅራዊ አደረጃጀት መፍጠር መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ የክልልና የቀበሌ ተቋማትን መዋቅራዊ አደረጃጀት በጥናት ፈትሾ የማስተካከል ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

7. **የተቋማትን ቀጣይነት በማረጋገጥ ኃላፊነታቸውን በብቃት የሚወጡና ሲያጓድሉ ተጠያቂ የሚሆኑ ተቋማትን በማደራጀት በማስፈለጉ፡-** የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከተመሰረተበት ጀምሮ ላለፉት 30 ዓመታ የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በየጊዜው የወጡ አዋጆች ከአስር ጊዜ በላይ ተሻሽለዋል፡፡ በየጊዜው የተደረጉ የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጆች ማሻሻያዎች ብዙውን ጊዜ በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ በመሆናቸው በአማካይ አንድ የምርጫ ዘመን የሞላ ጊዜ እንኳን ሳይቆዩ በፍጥነት ይለዋወጡ እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አዋጅ 280/2014 ከታወጀበት ቀን ጀምሮ በቢሮዎች መካከል የስልጣን መገፋፋት በመፍጠር በትልቁ ሲተች የቆየና እርካታ ያልፈጠረ መሆኑም የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተቋማት ቀጣይነትና የስያሜ ዘላቂነት ላይ የራሱን አሉታዊ አሻራ እያሳረፈ በመሆኑ በቀጣይ ወጥ የሆነ የተቋማት አደረጃጀትና ስያሜ እንዲኖር ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተቋማት ሲደራጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስችል፣ ከሌሎች ተቋማት ስልጣንና ተግባር ጋር የማይጋጭ ተግባርና ኃላፊነት ያላቸው ማድረግና ተናጠላዊና የጋራ ኃላፊነቶችን በትብብርና ፉክክር መካከል ሚዛን ጠብቀው እንዲያከናውኑ ማድረግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የመንግስት ተቋማትን ቀጣይነት የሚያረጋግጥ፣ ኃላፊነታቸውን ሲያጓድሉ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ተናጠላዊና የጋራ ኃላፊነቶችን በትብብርና ፉክክር መካከል ሚዛን ጠብቆ ለማከናወን የተመቸ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

8. **በፍጥነት እየተለዋወጡ ካሉ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ የሚጓዝና የህዝብን ችግሮች የሚፈታ ተቋማዊ አደረጃጀት ለመፍጠር፡-** ዓለም ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ፈተናዎችንና እድሎችን ለመሪዎች አምጥቷል። በየጊዜው ፈጣን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ለውጦች በሚስተናገድበት ዓለም ውስጥ መሰናክሎችን በብቃት ለማለፍና እድሎቹን ሳያባክኑ በአግባቡ ለመጠቀም ዘመኑን የዋጁ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን መፍጠር በጣም ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል። የዓለም ተለዋዋጭነት ፍጥነት ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅና በቴክኖሎጂ ፈጣን እድገት፣ ጉልህ የኢኮኖሚ ለውጦችና እያደጉ በመጡት የማህበራዊ ለውጦች የሚደገፍ ነው።

የመንግስት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ለውጦችን በማፋጠን ድህነትን የማስወገድ ፍላጎት ማደግ፣ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን መስፋፋት፣ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ገቢራዊነት፣ ሉላዊነት፣ ብዝሃነት፣ ፍትሃዊነትና አካታችነት፣ ዘላቂነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ ወዘተ የመሳሰሉት አጀንዳዎችና ለውጦች የተቋማዊ አደረጃጀት ለውጥ የሚፈልጉ መሆናቸው ጉልቶ እየታየ ነው። በሌላ በኩል ያልተቋረጠ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ዓለም የሚያመጣቸውን ዕድሎችና ፈተናዎች አስቀድሞ በመረዳት በሚጠቅም መንገድ ለመግራት የተመቹ ተቋማዊ አደረጃጀቶች ያስፈልጋል።

9. የክልሉን ተቋማዊ አደረጃጀቶች በማሻሻል ለአሁኑና ለመጭው ዘመን የሚመጥኑ እናድርጋቸው ሲባል የተለዋዋጭ ዓለምና ሉላዊነት ዕድሎችና ጫናዎችን በአግባቡ ለማስተዳደርና ክልሉ የመልማት ፀጋዎቹን ተጠቅሞ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ዝቅተኛ ምርታማነት፣ አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ፣ ከፍተኛ ስራ አጥነት፣ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት፣ ድህነትና የግጭት አዙሪት፣ የህግ የበላይነት አለመከበር፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና የመሳሰሉትን አንገብጋቢ ችግሮች በመቅረፍ የህዝቡን ፍላጎቶች ለማሟላትና ሁለንተናዊ ብልፅግናን እውን ለማድረግ የተመቹ እንዲሁም ያለፈውን የብክነት ዘመን የሚያካክሱና የሚያሻግሩ ተቋማትን እንፍጠር ማለታችን ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዚህ ቀደም የነበረው መዋቅራዊ መንዛዛትና የኃላፊነት መገፋፋት አገልግሎቶችን በመፈለግ ወደ መንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሄደውን ህዝብ የሚያንገላታና መንግስት እንደሌለ የሚያስቆጥር ከመሆኑም ባሻገር ህዝቡ የመንግስት አገልግሎቶችን አላገኘሁም ብሎ ባመነ ጊዜ መንግስትን እስከ መገልበጥ የደረሱ ሙከራዎችን (የምርጫ 1997 ዓ/ም ፖለቲካዊ ቀውስ፣ ኢህአዴግን በብልጽግና እንዲተካ ያደረገው ህዝባዊ አመጽ፣ አሁንም ብልጽግናን ለመገዳደር የሚንቀሳቀሰው ጽንፈኛ ኃይል ወዘተ) እንዳደረገ የሚዘነጋ አይደለም።

10. ስለሆነም አዲሱ የተቋማ አደረጃጀት መገፋፋትን የሚያስቀር፣ የ5 ዓመቱን የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ግቦች መሬት በማስነካት ዘመኑን የዋጀ ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ማህበረሰቡን ያማረሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ጊዜ ወጭና ጉልበት ቀናሽ በሆነ እንዲሁም ህግና አሰራሮች በሚፈቅዱት አግባብ ብቻ ለመፍታት የሚያስችልና በአጠቃላይ የመንግስት የልማት ጥረቶችን መሬት በማስነካት የህዝቡን ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ የተመቸ የማድረግ ክልላዊ ቁርጠኝነት እንደ አንድ መነሻ ተወስዷል።

11. ***ወደ ነገ የሚያሻግሩ ዘመኑን የዋጁ ተቋማትን ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ፡-*** የአሁኑም ሆነ የመጭው ዘመን ትልቅ ዕድልም ፈተናም ሆነው ከመጡት ነገሮች መካከል የዓለም ሁኔታ ተለዋዋጭነት፣ የለውጥ ኢ-ተገማችነትና ፍጥነት፣ ለውጥ የሚፈጥራቸው ዕድሎችና ፈተናዎች ውስብስብነት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ዘመኑን የዋጁ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን የሚፈልጉ ናቸው። የክልል ተቋማዊ አደረጃት ባለፉት 10 ዓመታ ከስምንት ጊዜ በላይ እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን የአደረጃጀት ማሻሻያ ፍጥነቱ በየትኛውም መመዘኛ አዋጭ ሊባል የሚችል አይደለም።

12. ባለፉት ዓመታት የቢሮዎች አስተዳደራዊ መዋቅር መንግስት የህዝቡን ድህነትና ኋላቀርነት ለማስወገድ ይበጃሉ ብሎ የነደፋቸውን የግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጅዎች በማስተግበር ረገድ የማይናቁ ስኬቶችን ለማስመዝገብ ያገለገለ ቢሆንም የግብርናው ዘርፍ አሁንም የሚጠበቅበትን መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ ለማድረግ አላስቻለም።

13. በጤናው ዘርፍም መከላከልን መሰረት ያደረገው የጤና ፖሊሲ ጤናማና አምራች ዜጋ እንዲፈጠር፣ የማህበረሰቡ የጤና ግንዛቤ እንዲሻሻል፣ የእናቶችና የህፃናት ጤና በመሻሻሉ ምክንያት የሞት ምጣኔ ትርጉም ባለው ደረጃ እንዲቀንስ፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻና ተመጋጋቢ ችግሮቹ እንዲቀንሱ፣ የአካባቢና የግል ንፅህና አጠባበቅ እንዲሻሻል ተድርጓል። እነዚህና መሰል የዘርፉ ለውጦች ቢኖሩም እንደ አገርም ሆነ እንደ ክልል ስንሞገስበት የነበረው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚፈለገውን ኢላማ አልመታም። ለምሳሌ ብናነሳ የ18ቱ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ዘላቂ መሆን ሳይችሉ ተቀልብሰዋል።

14. በትምህርት ዘርፍ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በስፋት በመገንባት ትምህርትን ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች ቀላል የማይባሉ ለውጦችን አምጥተዋል፣ የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ ረገድም ለውጦች አሉ። ይሁን እንጅ የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ ጥራትና አግባብነት የማረጋገጥ ስራዎች በሚፈለገው ደረጃ ስላልተሳኩ እንደ አገርም ሆነ እንደ ክልል ብቁና በቂ የሰው ኃይል ማፍራት አልተቻለም። የትምህርት ተቋማት ግንባታ ካለበት የተደራሽነትና የጥራት ጉድለት ባለፈ በክልሉ አሁንም ድረስ ከስታንዳርድ በታች የሆኑ ት/ቤቶች ቁጥራቸው ቀላል ዓይደለም። በተጨማሪም ማንበብና መፃፍ የሚችልና ግንዛቤው ያደገ አ/አደር ለማፍራት ታልሞ ሲተገበር የነበረው ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ስኬታማ አልሆነም። ከእነዚህ በሚፈለገው ደረጃ ካልተሳኩ ዕቅዶችና መሬት ላይ ካሉት ተጨባጭ እውነታዎች መረዳት የሚቻለው ቁም ነገር ተቋማዊ አደረጃጀቱ ተሻሽሎ ከዘመኑ ጋር እንዲዘምን ካልተደረገ በስተቀር ወደ ነገ የማያሻግር እና የክልሉን ርዕይ እንዳይሳካ የሚያደርግ መሆኑን ነው። ስለሆነም የክልል ተቋማዊ አደረጃጀት የክልሉ መንግስት ነገን አርቆ ለመመልከትና ዛሬ አልቆ ለመስራት ላለው ፍላጎት የተመቹ እንዲሆኑ የማድረግ አስፈላጊነት እንደ መነሻ ተወስዷል።

15. **በክልሉ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ብቁ ተቋማትን ለመገንባት፡-** የበለጸጉ ሃገራት በሀገረ መንግስት ጥንካሬ፣ በህግ የበላይነት መረጋገጥና ተጠያቂነትን በማስፈን ረገድ ስኬታማ መሆናቸው የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ ክልላችን የስልጣኔ ተምሳሌት ተደርገው የሚወሰዱ የበርካታ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት ቢሆንም ላለፉት በርካታ ዓመታት የተሟላ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጡ፣ ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ፣ የመፈፀም ብቃታቸው ያደጉና ህዝብ የሚተማመንባቸው ተቋማትን በመገንባት ረገድ ብዙም ተሳክቶለታል ሊባል አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት ፖለቲካዊ መረጋጋትን በዘላቂነት ለማስጠበቅና ድህነትን ለማሸነፍ ተስኖን በሁለንተናዊ ኋላ ቀርነትና ድህነት ውስጥ እየማቀቅን እንገኛለን፡፡

16. በአንፃሩ የልማታዊ መንግስት የእድገት ፈለግ አብነት ተደርጋ የምትጠቀሰው ጃፓን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከደረሰባት አሰቃቂ ሽንፈት አገግማ ዓለምን ያስደመመ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማስመዝገብ የቻለችው በእውቀትና በችሎታ ላይ የተመሰረቱ ጠንካራ ተቋማትን መገንባት በመቻሏ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ "ተአምራዊ" የተባለና ዓለምን ያስደመመ እድገት ያስመዘገቡት ሲንጋፖር፣ ታይዋን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ማሌዥያና ሌሎች የደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገሮች ከጃፓን ባገኙት ተሞክሮ ተነስተው ጠንካራ ተቋማትና ቢሮክራሲ በመገንባት ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡

17. በሌላ በኩል ተቋማት ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር አብረው አለመታደሳቸው ከተገነቡበት የጊዜ ታካኪነት አስተሳሰብ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ከለውጥ ጋር አብሮ ለመለወጥና ለውጥን እያነበቡ ተቋማትን ለመቀየር ከወግ አጥባቂነት አስተሳሰብ መላቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀርና ተቋማት በወግ አጥባቂ ሰዎች ሲሞሉ፣ ከአካባቢያቸው ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ስለሚቋረጥ በብቸኝነት ጉድለት ውስጥ እየበሰበሱ ይመጣሉ፡፡ ህብረተሰቡ ነባራዊ ሁኔታው ሲለወጥ የተቋማቱም ሁኔታ ተጣጥሞና ተዛምዶ እንዲለወጥ ለማድረግ ከተሳነው ደካማ ሀገረ መንግስት ይፈጠራል፡፡ ነባሮቹን ተቋማት ጠብቆ የማቆየት ጠንካራ የወግ አጥባቂነት ፍላጎት ለወቅቱ ሁኔታ የማይመጥኑ አሮጌ ተቋማትን ተሸክመን እንድንንገታገት ከማድረጉም በላይ ውድቀት ውስጥ እየተዘፈቅን መሆናችንንም እንድናይ ያደርገናል፡፡ የተቋማዊ ችኮነት ችግርን ለመቅረፍ አስቀድሞ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር አብረው እራሳቸውን እያሻሻሉ የሚሄዱ ተቋማትን መፍጠር ይጠይቃል፡፡

18. ጠንካራና መልካም የመንግስት አስተዳደር ለመፍጠር የተቋማት ግንባታ የሪፎርም ስራዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሪፎርሙ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያልነበሩ አዎንታዊ ውጤቶችን ለማግኘት የመንግስት ስራዎች የሚሰሩባቸው የቆዩ አመለካከቶች፣ አሰራሮች፣ አደረጃጀቶችና ሂደቶች በታቀደና በተቀናጀ ሁኔታ በአዳዲስ የሚለወጡበት መሳሪያ

ነው፡፡ ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው ተቋምና መንግስት ሲፈጠር ብቁና ስነ-ምግባር ያለው እንዲሁም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ሊሆን የሚችል አመራርና ባለሙያ ይኖራል፡፡ በመንግስታዊ ጉዳዮች በንቃት የሚሳተፍ ህብረተሰብ ይፈጠራል፡፡ ሁሉም አካላት በህግ የበላይነት አምነው የሚንቀሳቀሱበትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት ይገነባል፡፡

19. ስለሆነም ሀገራዊ ቅርጽ ከያዘ የሪፎርም አዲስ ፓኬጅ ይልቅ ያልተማከለና ለዘርፍና ለከባቢያዊ ሁኔታዎች ወይም ልዩ ባህሪያት ትኩረት የሚሰጥ፣ በእውቀት የሚመራና የሴክተሩን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የተቋማት አደረጃጀት የበለጠ ውጤታማ በመሆኑ ሁሉንም የክልል ተቋማት ያሉባቸውን የመዋቅራዊ አደረጃጀት ችግሮች በጥናት በመፈተሽ ተናባቢ የሆኑ እንዲሁም ዘርፍና ተልዕኮ ተኮር ተቋማዊ አደረጃጀቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራበት ይሆናል፡፡

## የተቋማት ሚና

20. **የ5 ዓመቱን እቅድ መሬት በማስነካት የኢኮኖሚ እድገትና ብልጽግና እንዲረጋገጥ ማድረግ፡-** ስለ ተቋም አደረጃጀት ከማንሳታችን በፊት የተቋማትን ምንነት በትክክል መረዳት በአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያላቸውን አወንታዊ ፋይዳ ለመገንዘብ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ዶግላስ ኖርዝ የተባለ የምጣኔ ሃብት ባለሙያ ተቋማዊ ለውጥና የምጣኔ ሃብት አፈፃፀም በሚል ርዕስ  እ.ኤ.አ 1990 ባካሄደው ጥናት ተቋማት በህብረተሰብ መካከል የሚካሄዱ መስተጋብሮችን የሚዳኙ፣ የሰዎችን ግንኙነቶች መልክ የሚያስይዙ፣ በምጣኔ ሃብት ውጤቶች (የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ ፍትሃዊነት፣ ድህነት ቅነሳ ወዘተ) ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በራሳቸው በሰው ልጆች የተፈጠሩ ህጎች ናቸው በማለት ገልፆታል፡፡

21. የአንድ አገርና ህዝብ ህልውና የሚለካው በዋናነት ባለው የኢኮኖሚ ጥንካሬ መሆኑ ማንንንም አያከራክርም፡፡ ኢኮኖሚ ሲጠነከር ድህነት ይጠፋል፣ የስራ አጥነት ችግር ይቀረፋል፣ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ችግር ይስተካከላል፣ ብልፅግናም ይሰፍናል፡፡ በአንፃሩ ኢኮኖሚው ሲዳከም ደግሞ ድህነት ይንሰራፋል፣ የሰራ አጥ ቁጥር ይጨምራል፣ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ይባባሳል፣ ሰላም ይደፈርሳል፣ ነፃነት ይጠፋል በአጠቃላይ የህዝብ ህልውና እና የአገር ሉአላዊነት በሌሎች እጅ ላይ ይወድቃል፡፡

22. በኢኮኖሚ የበለፀጉ አገራት ለከፍታቸው አበይት የሚሏቸውን ምክንያቶች እንደሚጠቅሱት ሁሉ ድህነት መገለጫቸው የሆኑ አገራትም የሚደረድሯቸው በርካታ ሰበቦች አሏቸው፡፡ የመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ለኢኮኖሚ እድገት ምቹ አለመሆንና አገራቱ በተፈጥሮ ሃብት የታደሉ አለመሆናቸው ከሚደረዱት ሰበቦቹ መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ አገራት በእድገት ወደ ኋላ ለመቅረታቸውና ለድህነታቸው እነዚህ ሰበቦች በመንስኤነት መቅረባቸው ሚዛን የሚደፋ አይደለም የሚል የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ምልከታ አለ፡፡ እርግጥ ነው ለግብርና ልማት ምቹ በሆኑና በቂ የተፈጥሮ ሃብት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖር ህዝብ ከሌላው ህዝብ የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት የማረጋገጥ እድል ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ብቻውን የኢኮኖሚ እድገት ምንጭ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ በተፈጥሮ ሃብት መበልፀግ ብቻውን የዕድገት ምንጭ መሆን ቢችል ኖሮ የተሻለ የተፈጥሮ ሃብት ያላቸው እንደ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንኮ ያሉ አገራት ድሃ ሆነው ከዚህ ግባ የሚባል የተፈጥሮ ሃብት የሌላቸው እንደ እስራኤል ያሉ አገሮች በኢኮኖሚ የበለፀጉ አይሆኑም ነበር የሚል መከራከሪያ ሃሳብ በተደጋጋሚ ይነሳል፡፡

23. ከዚህ እውነታ በመነሳት በርካታ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ለአንድ አገር በኢኮኖሚ ማደግና መበልፀግ ወይም በድህነት ውስጥ መኖር ተቋማት ወሳኝ መሆናቸውን ያሰምሩበታል፡፡ ታዋቂዎቹ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ዳሮን አሴሞግሉ እና ጀምስ ሮቢንሰን እ.ኤ.አ በ2012 Why Nations Fail: The Origions of Power, Prosperity and

Poverty በሚል ርዕስ ያስነበቡት መጽሃፍ አገራት ድሃ ከሚሆኑባቸው አበይት ምክንያቶች ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተቋማት ሁኔታ መሆኑን ያስረዳል፡፡ መጽሃፉ በኢኮኖሚ ማደግ ያልቻሉ አገራት መበልፀግ የተሳናቸው ለኢኮኖሚ ተስማሚ የሆኑና የሚመጥኑ ተቋማትን ማደራጀትና በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባት ባለመቻላቸው መሆኑን ያብራራል፡፡ ይህም የተቋማት አቅምና የኢኮኖሚ ብልፅግና ጥብቅ ቁርኝት እንዳላቸው ያሳያል፡፡

24. **በክልሉ ተንሰራፍቶ የቆየውን የድህነትና የግጭት አዙሪት መስበር፡-** ክልሉ አሁንም ከፖለቲካ ውጥረት መገላገል አልቻለም፡፡ የፖለቲካ ውጥረቱ ኢኮኖሚውን እያሽመደመደው መሆኑም በግልጽ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ሲዳከም የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመጠለያ፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ እንዲሁም የሌሎች ሸቀጦችና አገልግሎቶች አቅርቦት እጥረት በከፋ ደረጃ ይባባሳል፡፡ ክልሉን ካደቀቀው የሰሜኑ አውዳሚ ጦርነት በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መሰረት አንፃራዊ ዕፎይታ ቢገኝም አሁንም ከግጭት አዙሪት ውስጥ መውጣት ባለመቻሉ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ውድመት እየደረሰ ነው፡፡ ይህ ውድመት የማይተካውን የሰው ልጅ ህይወት ከማሳጣቱም በላይ ኢኮኖሚውን ለማሳደግና ድህነትን ለመቅረፍ ይውል የነበረውን ሃብት በእጅጉ እየተሻማ ክልሉን ከድህነትና ከግጭት አዙሪት እንዳይላቀቅ እያደረገው መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በቅጡ በማጤን የፖለቲካ ውጥረቱን ለማርገብና ክልላዊ ሰላሙን በመመለስ ረገድ ልማት የሚጫዎተው ሚና የጎላ ሲሆን ይህንን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ደግሞ የተደራጁ፣ ጠንካራና ህዝብ ማገልገል የሚችሉ ተቋማት ያስፈልጋሉ፡፡

25. ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል በሚታወቀው የኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ባህል ውስጥ አንደኛው አስቸጋሪ ነገር የጉልበተኝነትና የሴረኝነት ባህሪ የወረረው የፖለቲካ ምኅዳር መፈጠሩ ሲሆን ይህም በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ምድር የበርካታ ንፁኃን ደም በከንቱ እንዲፈስ ምክንያት ሆኗል፡፡ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ዙፋናዊ መንግሥት ካስወገደው ከ1966 ዓ/ም አብዮት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የንፁኃን ደም በሰበብ አስባቡ እየፈሰሰ ነው፡፡ በዘመነ ነጭና ቀይ ሽብር አንድ ትውልድ እርስ በርሱ ጎራ ለይቶ ተጨፋጨፏል፡፡ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት አንድ መቶ ሺህ ያህል ወገኖች እንደ ወጡ ቀርተዋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ግጭቶችና ማንነትን መነሻ አድርገው በተፈፀሙ ጥቃቶች ብዙዎች ላይመለሱ አሸለበዋል፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ የሁለት ዓመታት አውዳሚ ጦርነት በመቶ ሺዎች በላይ የሚቆጠሩ ወገኖች አልቀዋል፡፡

26. የፖለቲካ ውጥረቱ እየተባባሰ ሲሄድ በኢኮኖሚው ላይ የሚከተለው ችግር ከባድ እንደሚሆን ማንም አይስተውም፡፡ አምራቾች በአግባቡ አምርተው ምርቶቻቸውን ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ካልቻሉ የዋጋ ንረቱ የበለጠ እየተባባሰ በክልሉ ላይ ከባድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ያስከትላል፡፡ በተጨማሪም ዜጎች አሁን ከሚስተዋለው የባሰ ከቦታ ወደ ቦታ ተንቀሳቅሰው መስራትም ሆነ ጥሪት ማፍራት ካለመቻላቸውም በላይ የስራ አጦች ቁጥር በእጥፍ እየጨመረ ክለልን የማይወጣው አዘቅት ውስጥ ይከተዋል፡፡ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም፣ በአገልግሎት፣ በንግድና በሌሎች ዘርፎች የሚጠበቀው ውጤት ከአቅም በታች እየሆነ ችግሩ ይጠናል፡፡ በክልሉ በተከሰተው ግጭት ምክንያት የምግብ እጥረት ሲፈጠርና የመሰረተ ልማቶች አገልግሎት አሰጣጥ ሲዳከም ኢንቨስትመንት ለመሳብም ያዳግታል፡፡ የክልሉን ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ሃይማኖታዊና መሰል የቱሪዝም መስህቦች ለመጎብኘት የሚፈልጉ የውጭና የአገር ውስጥ ዜጎችም ይሸሻሉ፡፡

27. ስለሆነም ህግና ሥርዓት ተከብሮ ከጉልበት ይልቅ ሰላማዊ መንገድ ብቸኛ አማራጭ እንዲሆን፣ ክልሉ በ5 ዓመቱ የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ያስቀመጣቸው ግቦች እንዲሳኩ፣ ህዝቡ በመንግስት ተቋማት እንዲገለገልና እርካታው እንዲጨምር በማድረግ ሁሉም ዜጋ እንደየ ችሎታውና እንደየ አቅሙ ሰርቶ እንዲበለጽግ በማድረግ ረገድ ተቋማት የሚኖራቸው ሚና ትልቅ ነው፡፡

28. ቀበሌዎች ላይ እግር በመትከል ዘላቂ ሰላምና ልማት ማረጋገጥ፡- ቀበሌዎች ሰፊ ማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች የሚከናወንባቸውና መንግስት ህዝብን ከድህነት ለማውጣት ያለውን ፍላጎት በተግባር የሚተረጉምባቸው ሁነኛ የአስተዳደር እርከኖች መሆናቸው ይታወቃል። ቀበሌዎች ሰፊ ህዝብ ሚኖርባቸው ከመሆናቸውም በላይ በተለያዩ ጊዜት የሚቀረፁ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት አጋር ድርጅቶች የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ውጤታማነትና ተገቢነት በተግባር የሚፈተንባቸውም ናቸው። በተጨማሪም ቀበሌዎች ቁጥሩ ቀላል የማይባል በግብርናና ከግብርና ውጭ በሆኑ የስራ ዘርፎች የተሰማራ ህዝብ የሚኖርባቸው፣ መንግስት ህዝቡን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ በምርጫ ቃል ሲገባና ሲያቅድ ቃሉን በተግባር እንደሚፈፀም የሚተማመንባቸውና አይኑን የሚጥልባቸው ዘርፈ ብዙ ፀጋዎችን የተጎናፀፉ ናቸው። በሌላ በኩል የመንግስትነት ስልጣን የሚገኝባቸውም ሆነ የሚታጣባቸው የስልጣን ማህፀኖች ቀበሌዎች ናቸው ቢባል ትክክል ነው። በምርጫ ተወዳድረውም ሆነ ነፍጥ አንግበው በሃይል ወደ ስልጣን የሚመጡ መንግታት የሚጠነሰሱት፣ የሚወለዱትና አድገው አገር እስከማስተዳደር የሚደርሱት በአብዛሃኛው በእነዚሁ ሰፊ ህዝብ በሚኖርባቸው ቀበሌዎች ውስጥ ነው። ለዚህ ሃሳብ በአስረጅነት የሚጠቀሱ ብዙ የተሳኩም ያልተሳኩም የመንግስትነት ሙከራዎች ቢኖሩም የቅርቡን ወያኔን እንኳ ብናነሳ  የትጥቅ ትግል ጀምሮ የገዘፈና አስፈሪ ሰራዊት የነበረውን ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከስልጣን በሃይል በማስወገድ አራት ኪሎ ቤተ መንግስትን መቆጣጠር የቻለው ፅንሰቱን፣ ውልደቱንና እድገቱን ሰፊ ህዝብ በሚኖርባቸው በእነዚህ ቀበሌዎች ላይ በማድረግ ነበር። በአሁኑ ሰዓትም በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች እየተካሄዱ ያሉ መንግስትን በሃይል የማስወገድ እንቅስቃሴዎች መሰረታቸው ቀበሌ ነው። ጠቅለል ባለ አገላለፅ ቀበሌዎች መልካም አስበው ለሚሰሩ አካላት በብዙ የሚያተርፍ ፀጋን የሚያጎናፅፉ፣ ክፉተኛ ሃሳብ ላላቸው ደግሞ አውዳሚና ጎታች የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስብራቶችን የሚወልዱ ናቸው።

29. ከእነዚህ መሰረተ ሃሳቦች ልንረዳው የሚገባ ጭብጥ ለቀበሌዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚገባውን ስራ የማይሰራ መንግስት እግሩ የተቆረጠና ከሰፊው ማህበራዊ መሰረቱ የተነጠለ የመሆን ዕድሉ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ነው። እንደዚህ ዓይነት መንግስት የተረጋጋ ሀገረ መንግስት ለመገንባትም ሆነ የህዝብ የዘመናት ጥያቄ የሆኑትን ሰላምንና ብልፅግናን የማረጋገጥ አጀንዳዎች መመለስ አይቻለውም። በሌላ በኩል መንግስት የትኛውንም ያህል የሚያማልሉ የልማት ዕቅዶችን ቢያቅድም መሬት የሚያስነካ የተስተካከለ የቀበሌ ተቋማዊ አደረጃጀት ከሌለው በስተቀር የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ከቶውንም አይችልም። በአሁኑ ሰዓትም የገጠመንን ክልላዊ የፀጥታ አለመረጋጋት ችግር በቀላሉ መቀልበስ ያልተቻለው በብዙ አካባቢዎች ጠንካራ ተቋማት ቀበሌ ላይ ባለመኖራቸው እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ስለሆነም ክልሉ ያቀደውን የአምስት አመት የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ግቦች ለማሳካት፣ የህግ የበላይነት የተረጋገጠበትና አስተማማኝ ሰላም የሰፈነበት ክልል ለመገንባት እንዲሁም መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለህዝቡ ለማቅረብና ቀበሌዎች ላይ በአስተማማኝ ደረጃ እግር ለመትከል ተቋማት በጣም አስፈላጊ ናቸው።